አንሰ እመውት ወእግዚአብሔር ይሔ ውጽክሙ ፣

እኔ እሞታለሁ እግዚአብሔር እናንተን በረድኤት ይጎበኛችኋል ፤

ወያወፅአክሙ እምዛቲ ምድር ወያበውአክሙ ውስተ ምድር ዘመሐለ ለአበዊነ አብርሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ፣

ከዚህች አገር አውጥቶ ለአባቶቻችን ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ ወደማለላቸው አገር ያገባችኋል አላቸው ፤

፳፭፤ ወአምሐሎሙ ዮሴፍ ለደቂቀ እስራኤል ፣ ወይቤሎሙ አመ ይሔ ውጽክሙ እግዚአብሔር አውዕኡ አዕፅምትየ እምዝየ ምስሌክሙ ፣

ዮሴፍም የእስራኤልን ልጆች እግዚአብሔር በረድኤት በጎበኛችሁ ጊዜ አጥንቴን ይዛችሁ ውጡ እንጂ ከዚህ አትተዉ ብሎ አማላቸው ፤ አንድም ለጊዜው ፀአት እንዳላቸው ለማጠየቅ ነው ፤ ፍጻሜው ግን ግብጽ የመቃብር ፣ ከነዓን የትንሣኤ ፣ ግብጽ የገሃነም፣ ከነዓን የመንግሥተ ሰማይ አምሳል ናትና፤ (ሐተታ) ያዕቆብም እንዲህ አለ ዮሴፍም እንዲህ አለ፣ ስለምነው ቢሉ፣ አባቶቻችን እንዲህ ማለታቸው መውጣታችንን ቢያውቁ ነው ብለው እንዲነቁ ፣ እንዲተጉ ፤ አንድም ለማስጸየፍ ፣ አባቶቻችን አጥንታችን ስንኳ ከዚህ አይቅር ብለዋል ብለው እንውጣ እንዲሉ ፤

፳፮፤ ወሞተ ዮሴፍ በ፻ት ወ፲ቱ ዓመት ፣

ዮሴፍም በመቶ ዐሥር ዘመኑ ሞተ ፤

ወአምዓዝዎ ወሤምዎ በነፍቅ ውስተ ብሔረ ግብጽ ፣

ሽቱ ቀብተው በሣጥን አድረገው በግብጽ አኖሩት ፤

ተፈጸመ ኦሪት ዘልደት በሰላመ እግዚአብሔር ፈጣሬ ኵሉ ፍጥረታት ፣

ሃያ ሁለቱን ሥነ ፍጥረት በፈጠረ በእግዚአብሔር አጋዥነት ፣ የሥነ ፍጥረትን ነገር የሚናገር ኦሪት ዘልደት ደረሰ ተፈጸመ፤ ወስብሐት ለእግዚአብሔር ፤

አነሣሥቶ ለአስጀመረን፣ አተጋግቶ ለአስፈጸመን፣ ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው፤

አሜን



## መ ቅ ድ ም

ኦሪት ዘፀአት ዜና ዘፀአት ሲል ነው፣ እስራኤል ከግብፅ መውጣታቸውን የሚናገር መጽሐፍ ይህ ነው፣ መውረዳቸውን ተናግሮ ነበርና መውጣታቸውን ተናገረ፣ ምነው ይህንማ ተናግሮት አልነበረም ስለምን ደገመው ቢሉ፣ ከቆመበት አያይዞ ተናገረ፤ አንድም በመካከል ነገር እንዳልቀረው ሲያጠይቅ፣ አንድም ለአብርሃም የነገረው ተስፋ እንዳልቀረ ሲያጠይቅ፣ ዘፍ፣፲፭፣፲፫-፲፬፤ አንድም ከመ ወጽኡ ሲል ነው፣ ሰባ ሆነው ወርደው ይህን ያህል ሁነው ወጡ ለማለት፣ ይህ አርእስት ነው፣ ፫ቱ ፶ት ለመጻሕፍት ሁሉ አርእስት ሲሰጡ አርእስት ሰጥተውታል፣ እርሱ ግን ነገሩን ዝውእቱ አስማቲሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ብሎ ያመጣዋል።

### ምዕራፍ ፩

የኦሪት ዘፀአት አንደኛው ምዕራፍ ይህ ነው፤ አንድም ምዕራፊ አሐዱ ይላል፤ ከስምንቱ ብሔረ ኦሪት የአንደኛው የኦሪት ዘፀአት ምዕራፍ ይህ ነው፣ ለሁሉም ምዕራፍ ምዕራፍ አላቸውና አንድም ምዕራፊ አሐዱ አሐዱ ይላል፣ ከስምንቱ ብሔረ ኦሪት የአንዱ የኦሪት ዘፀአት አንደኛው ምዕራፍ ይህ ነው፤ አንድም ምዕራፊ ክልኤቱ አሐዱ ይላል፣ ለኦሪት ዘልደት ሁለተኛ የሚሆን የኦሪት ዘፀአት አንደኛ ምዕራፍ ይህ ነው፤

፩፣ ዝውእቱ አስማቲሆሙ ለደቂቀ እስራኤል እለ ቦኡ ብሔረ ግብጽ ምስለ ያዕቆብ አቡሆሙ ብእሲ ብእሲ ወቤቱ፤

አንዱም አንዱ ወገኑና፣ አንዱም አንዱ ሰው ከአባታቸው ከያዕቆብ ጋራ ወደ ግብጽ አገር የገቡ የእስራኤል ልጆች ስማቸው ይህ ነው፤ ብእሲ ብእሲ ብሎ አንድ አርእስት፣ ወቤቱ ብሎ ሁለት አርእስት ተናገረ፣ ወቤቱ ያለው ደቂቀ እስራኤል ላለው ነው፤ ብእሲ ብእሲ ያለውን ወደፊት ያመጣል፡

፪፣ ቦአ ሮቤል ወስምዖን ሌዊ ወይሁዳ፣

ሮቤል ስምዖን ሌዊና ይሁዳ፤

፫፣ ይሳኮር ወዛብሎን ዳን፣

ይሳኮር፣ ዛብሎንና ዳን፤

፬፣ ወንፍታሌም ጋድ ወአሴር ወብንያም፣

ንፍታሌም፣ ጋድ፣ አሴርና ብንያም ናቸው፤

www.ethiopianorthodox.org

እለ ቦኡና ቦኡ አንድ ወገን፤ አንድም ገዘውእቱ አስማቲሆሙ ብሎ አሥሮ በዋዌ ወቦኡ ይላል፣ እኒህ ሁሉ ከአባታቸው ከያዕቆብ ጋር ወደ ግብጽ አገር ገቡ አለ፣ ብእሲ ብእሲ ያለውን አመጣ፤

፭፣ ወዮሴፍሰ ሀሎ በብሔረ ግብጽ፣

ዮሴፍ ግን ያን ጊዜ ከወንድሞቹ ተለይቶ ተሸጠ አስቀድሞ በግብጽ አገር ይኖር ነበር፤ አንድም ዮሴፍ ግን ተሸጠ ከወንድሞቹ ተለይቶ ያንጊዜ በግብጽ አገር ይኖር ነበር፤

ወኮነት ኵሉ ነፍስ እንተ እም ያዕቆብ ፸፭፣

ከአባታቸው ከያዕቆብ ጋር ወደ ግብጽ የወረዱ የሕዝቡ ሰውነት በቊጥር ሰባ ናት፣ ሰባአምስትም ይላል፤

፮፣ ወሞተ ዮሴፍ ወኵሉ አኃዊሁ ወኵሉ ውእቱ ትውልድ፣

ከዚህ በኋላ ወንድሞቹና ዮሴፍ የልጅ ልጆቹም በግብጽ አገር ሳሉ ሞቱ፤

፯፣ ወበዝኁ ደቂቀ እስራኤል ወመልዑ፣

ከዚያ በኋላ ግን ከሞት የተረፉ፣ ከጥላ ያረፉ የእስራኤል ልጆች በእግዚአብሔር ቸርነት ፈጽመው በዙ፤

ወኮኑ ሕቁራነ፣

ጽሉዓነ ሲል ነው፣ በግብጻውያን ዘንድ ግን የተጠሉ ሆኑ፤

ወጸንዑ ጥቀ እዙዘ፣

እስራኤል ግን ፈጽመው የጸኑ ሆኑ፤

ወመልአት ምድር እምኔሆሙ፣

ከእነሱ የተነሣ፤ አንድም እምእንሞሙ ይላል፣ ከድንኳናቸው ብዛት የተነሣ፤ አንድም እምድኅሬሆሙ ይላል፣ ከእነሱ ብዛት በኋላ ምድር ሰውን ተመላች፤

፰፣ ወተንሥአ ካልእ ንጉሥ ዲበ ግብጽ ዘኢየአምሮ ለዮሴፍ፣

ዮሴፍን የማያውቀው፤ አንድም ደግነቱን ጥበቡን የማያውቅለት፤ አንድም ዮሴፍን የማይወደው አእመርኩክ ሙሴ ወልደ እንበረም እንዲል፣ በግብጽ አገር ሌላ ንጉሥ ነገሠ፣ በዕገሌ አገር እገሌ ተነሣ እንዲሉ፤

፱፣ ወይቤሎሙ ለሕዝቡ ናሁ ሕዝበ ደቂቀ እስራኤል ዐቢይ ወብዙኀ ወይጸንዑነ፤

እነሆ የእስራኤል ልጆች ብዙ ጽኑ ሆኑ ይበረታቱብናል፤

፲፣ ንዑ ንጠበቦሙ እስመ እምከመ በዝኁ ወእምከመ በጽሐነ ፀብዕ ይትዌሰኩ እሉሂ ዲበ ጸርነ ወይጸብኡነ እምድኅሬነ ወየወፅኡ እምድርነ፤

ይቤሎሙ ንዑ ንጠበብ ቦሙ ብለህ ግጠም፣ የግብጹ ንጉሥ



ፈርዖን ወገኖቹን፣ የእስራኤል ልጆች ወገኖች እነሆ ፈጽመው በዝተዋል፣ ወይጸንዑነ፣ ከኛም እነሱ ይጸናሉ፣ ከኛ እነሱ ከበዙ በኛም ጠላት ከተነሣብን፣ ይትዌሰኩ እነሱ ከጠላቶቻችን ጋር ሁነው እምድኅሬነ ኪያነ ሲል ነው፣ እኛን ይወጉናል፤ አንድም እንዳለ ይሆናል፣ እየ ተከተሉ ይወጉናል፣ ከአገራችንም ያስወጡናልና፣ ኑ ብልሃት እንሥራባቸው፣ ጡብ እናስጥ ላቸው፣ ኖራ እናስወቅጣቸው፣ ጭቃ እናስረግጣቸው አላቸው፣ ጡብ ሲጥሉ፣ ኖራ ሲረግጡ /ሲወቅጡ/ ጭቃ ሲረግጡ ከዋሉ ልሙዳን ፀብዕ አይሆኑም ብሎ ነው፤ አንድም ጡብ ሲጥሉ፣ ኖራ ሲወቅጡ፣ ጭቃ ሲረግጡ ከዋሉ ይደክማሉ፣ ከደከሙም ከሚስቶቻቸው አይደርሱም፣ ካልደረሱም አይባዙም፣ ካልተ ባዙም እኛን አያጠፉንም ብሎ ነው፤

፲፩፣ ወሢመ ዲበሆሙ ሊቃነ ግባር፤ ከመ ይሣቅይዎሙ በግብር፣

ይህንም ብሎ አልቀረ፣ በግብር በሥራው ሁሉ፤ አንድም በግድ መከራ እንዲያጸኑባቸው የሥራ ተኛ አለቆች ሾመባቸው፤

፲፪፣ ወነደቁ አህጉረ ጽኑዓተ ለፈርዖን ፊቶም ወራምሴ ወዖን እንተ ይእቲ ሀገረ ዐሐይ፣

ሀገረ ዐሐይ አላት፣ ዖን ጊዜ ዐሐይ የሚባል ሰው ነበረባትና፤ አንድም ጥንቱንም ዐሐይ የሚባል ሰው አቅንቷታልና፤ አንድም በግብጽ ዝናም ዘንሞ አይወቅምና ሀገረ ዐሐይ አላት፣ እነሱም ለፈርዖን ዖን፣ ራምሴ ፊቶም የሚባሉ ሦስት የጸኑ ቅጽሮች ሠሩ፤

ወበአምጣነ ይሣቅይዎሙ ከማሁ ይበዝኁ ወይጸንዑ፣

መከራ የሚያጸኑባቸውን ያህል እንደ መከራው ብዛት እየበዙ ይጸኑ ነበር፤

ወያስቈርርዎሙ ግብጽ ለደቂቀ እስራኤል፣

ግብጻውያን ግን የእስራኤልን ልጆች ያስመርሯቸው ነበር፤

፲፫፣ ወይቀንይዎሙ በሥቃይ፣

እየገፉ እያዳፉ በማስጨነቅ ይገዙዋቸው ነበር፤

፲፬፣ ወያሔሥሩ ሕይወተ ነፍሶሙ በግብር ዕፁብ፣

በሕይወት መኖርን በሚያሰቅቅ ሥራ ሰውነታቸውን ያስጨንቋት ነበር፤

ወበግንፋል፣

ጡብ በማስጣል፤

www.ethiopianorthodox.org

ወበዕቡር፣

ጭቃ በማስረገጥ፥

ወበኵሉ ግብረ ሐቅል፣

ገለባ በማስለቀም ያስጨን ቋቸው ነበር፤

ወበኵሉ ግብር ዘይቀንይዎሙ በሥቃይ፣

የሚገዙዋቸው በሥራው ሁሉ በማስጨነቅ ነበር፤

ከዚህ በኋላ ሁለተኛ ዓቀብተ መወልዳትን ሾሞባቸዋል፤

፲፭፣ ወይቤሎን ንጉሠ ግብጽ ለመወ ልዳተ ዕብራውያት ስማ ለአሐቲ ሲፓራ ወስመ ካልእታ ፎሃ፣

የግብጽ ንጉሥም የዕብራውያንን ሴቶች አዋላጆች እንዲህ ሲል አዘዛቸው፣ ስማቸውም ያንዲቱ ፎሃ፣ የሁለተኛዪቱም ሲፓራ ይባላል፤

፲፮፣ ሶበ ታወልዳሆን ለዕብራውያት እምከመ በጽሐት ለወሊድ፣

አንዲቱም አንዲቱ የምትወል ድበት ቀን ደርሶ በምታዋል ዱበት ጊዜ፤

እመ ተባዕት ውእቱ ቅትላሁ፣

የሚወለደው ልጅ ወንድ ቢሆን ግደሉት፣

ወእመሰ ወለት ይእቲ አሕይዋሃ፣

የምትወለደው ልጅ ሴት ብትሆን ግን አትግደሉዋት፣ ወይፈኑ አሐደ አሐደ እመላእ ክቲሁ ለተባለው ምሳሌ ነው፤

፲፯፣ ወፈርሃ ለእግዚአብሔር እልኩ መወልዳት፣

እሊያ የታዘዙት አዋላጆች ግን እግዚአብሔርን ፈርተው፤

ወኢገብራ በከመ አዘዞን ንጉሠ ግብጽ፣

የግብጹ ንጉሥ እንዳዘዛቸው አላደረጉም፤

ወአሕየዋ ተባዕተ፣

ግደሉ ያላቸውን ወንድ ወን ዱን በሕይወት ተዉ፣

፲፰፣ ወፀውዖን ንጉሠ ግብጽ ለመወ ልዳት ወይቤሎን እፎኑ ትገብራ ከመዝ ወተሐይዋ ተባዕተ፣

የግብጹ ንጉሥም አዋላጆችን ጠርቶ ለምን እንዲህ ታደርጋ ላችሁ? ወንድ ወንዱን ከሞት ለምን ታድናላችሁ? አላቸው፤ ሐተታ በምን አውቆ ቢሉ ጠርጥሮ፤ አንድም ከነገረ ሠሪ ሰምቶ፤ ከሦስት ወር በኋላ ወንድ ልጅ ሲያለቅስ ሲያን ጥስ በድምፁ ይታወቃልና፤

፲፱፣ ወይቤላሁ መወልዳት ለፈርዖን አኮ ከመ አንስተ ግብጽ ዕብራውያት አላ እንበለ ትምጻእ መወልዲት ይወልዳ፣

አዋላጆቹም የዕብራውያን ሴቶች እንደ ግብፃውያን ሴቶች አይደሉም፣ አዋላጇቱ ሳትመጣ ወልደው ይቆያሉ እንጂ ብለው ለፈርዖን መለሱለት፣ ሴቶች ምክንያት አያጡምና፤



፳፣ ወአሠነየ እግዚአብሔር ለመወ ልዳት፣

እነሱ ለወገኖቹ ለእስራኤል በጎ ነገር ቢያደርጉ ዋጋ የማይ ስቀረው እግዚአብሔር ለነሱም በጎ ነገር አደረገላቸው ማለት ንጉሡ እንዳይገድላቸው አደረገ፤

፳፩፣ ወመልአ ሕዝብ ወጸንዑ ጥቀ፣

በአዋላጆች በጎነት በእግዚአብ ሔርም ቸርነት ወገኖቹ እስራ ኤል እጅግ በዙተው በረቱ፤

እስመ ፈርሃ መወልዳት ለእግዚ አብሔር ወገብረ ሎን አብያተ፣

አዋላጆቹም እግዚአብሔርን ስለ ፈሩ ቤት ንብረት ሰጣቸው፤ አንድም ዐቢያተ ይላል፣ ድንቅ ድንቅ ሥራ ሠራላቸው፤

፳፪፣ ወአዘዞሙ ፈርዖን ለኵሉ ሕዝቡ ወይቤሎሙ ኵሎ ተባዕተ ዘይትወለድ ለዕብራውያን ገርዎ ውስተ ተከዚ ወኵሎ አንስተ አሕይዉ፣

ያንጊዜም ፈርዖን ተቈጥቶ ከዕብራውያን የሚወለደውን ወንድ ወንዱን ልጅ ሁሉ ከፈሳሽ ውሃ ጣሉት፣ ሴት ሴቱን ግን በሕይወት ተዉት ብሎ ለሕዝቡ ሁሉ አዋጅ ነገረ፤ /ሐተታ/ ይትፈኑዋ ነፍሳት ውስተ ገሃነም እስከ ይመልአ አብያተ ሞት ለተባለው ምሳሌ ነው።

## ምዕራፍ ፪

፩፣ ወሀሎ ፩ዱ ብእሲ እምነገደ ሌዊ ዘስሙ እንበረም ዘነሥአ ሎቱ እምአዋልደ ሌዊ ብእሲተ፣

ከሌዊ ልጆች ወገን የሆነች አንዲት ሴት ያገባ ስሙ እንበረም የሚባል ከነገደ ሌዊ የተወለደ አንድ ሰው ነበረ፤ አንድም ወነሥአ ይላል ብሎ ከነገደ ሌዊ የተወለደ አንድ ሰው ነበረ፣ ከሌዊ ልጆች ወገን የሆነችም ሴት አግብቶ ነበረ፤

፪፣ ወፀንሰት ወወለደት ተባዕተ፣

እርስዋም ፀንሳ ወንድ ልጅን ወለደች፤

ወሶበ ርእይዎ ከመ ሠናይ ውእቱ አንበርዎ ሠለስተ አውራኀ፣

ያማረ የተወደደ እንደሆነ ባዩት ጊዜ እናት አባቱ፤ አንድም ሹማምቱ ሦስት ወር ሠውረው አኖሩት፤ /ሐተታ/ ሙሴ ሲወ ለድ ብርሃን ተሥሎበት ነበርና አዋላጆቹ ራርተው ይህንስ የፈጠረው ይግደለው ብለው ትተውታል፤

፫፣ እምድኅረ ሠለስቱ አውራኅ ሶበ ስዕኑ እንከ ኃቢዮቶ ነሥአት እሙ ነፍቀ ወቀበዓታ አስፈሊጣ ወጊሳ፣

ከሦስት ወር በኋላ ግን ሠውሮ ማኖር ባይቻላቸው እናቱ ሣጥን ወስዳ፣ ሰም፣ አደሮማር፣ ሙጫ፣ የባሕር አረፋ ቀብታ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወወደየቶ ለውእቱ ሕፃን ውስቴታ፣

ሕፃኑንም በሣጥኑ ውስጥ አኑራ፣

ወሤመቶ ውስተ ማዕዶት ኀበ ገበዘ ተከዚ፣

ወስዳ ከወንዙ ማዶ በፈሳሹ ዳር ጣለችው፣

፬፣ ወትሔውፅ እኅቱ እምርኁቅ ከመ ታእምር ምንት ይበጽሖ፣

እኅቱ ምን የገኘው እንደሆነ ለማወቅ ከሩቅ ሁና ትጐበኘው ነበር፣ /ሐተታ/ ቀን ቀን እኅቱ እየጠበቀች፣ ሌሊት ሌሊት እናቱ እየሔደች ታጠባው ነበር፤

፭፣ ወወረደት ወለተ ፈርዖን ከመ ትትሐፀብ በውስተ ተከዚ፣

ተርሙት የምትባል የፈርዖን ልጅ ልትታጠብ ወደ ፈሳሹ ወረደች፣ ስለምን ቢሉ በፈሳሹ ዳር እንደ መዋት ያለ ነበረ፣ ኩብሽ የሚባል ደዌ ነበረባትና ለመጠመቅ፤ አንድም ነጋዴ ወዳጅ ነበራትና ያንን ለመቀበል፤ አንድም አዞ ጉማሬ ታመልክ ነበረችና ስለዚህ፤ አንድም መንግሥት በጐርጐራ ሳለ ያጤ መለክ ሰገድ ልጆች ውሀ ዋና ይማሩ እንደ ነበረ ውሀ ዋና ልትማር ነው፤

ወአንሶሰዋ አዋልዲሃ ኀበ ተከዚ፤

ደንገጡሮቿም በወንዙ ዳር ለዳር ይመላለሱ ነበር፤

ወሰበ ርእየታ ለይእቲ ነፍቅ ውስተ ማዕዶት ፈነወት ወለታ ወአምጽአታ፡

እነሱ ሳያዩ እሷ አሻግራ ባየችው ጊዜ ከእሷ ጋር ያለችውን ደንገጡሯን ከነጋዴ ተረስቶ ወድቆ የቀረ ዕቃ ይሆናል ሒጂ አምጭልኝ ብላ ላከቻት፣ ሒዳ አመጣችላት፤ አንድም ሣጥኒቱን አመጣቻት፤

፮፣ ወከሠተታ ወርእየት ሕፃነ ይበኪ ውስተ ይእቲ ነፍቅ፣

ሣጥኑንም ከፍታ ባየች ጊዜ ሕፃን እያለቀሰ አገኘች፣

ወምሕከቶ ወለተ ፈርዖን ወትቤ እምደቂቀ ዕብራውያት ውእቱ ዝ ሕፃን፣

የፈርዖንም ልጅ ይህስ ልጅ ከዕብራውያን ልጆች ወገን ይሆናል ብላ፣ ምነው የኔ ልጅ በሆነ ስትል ተመኘችው፤ ሐተታ ገረዲቱም ምኞትዋን ሰምታ እመቤቴ አሁንስ ወለድኩ ቢሉ ይሆን የለምን ብትላት፣ ማርገዜ ሳይታወቅ ወለድኩ ብል ማን ያምነኛል አለቻት፣ እሷም የነገሥታት ልጆች በእልፍኝ ትኖራላችሁ መውለዳችሁ ነው እንጂ ማርገዛችሁ ይታወቃልን ብላ መለሰችላት፤



፯፣ ወትቤላ እኅቱ ለውእቱ ሕፃን ለወለተ ፈርዖን ትፈቅዲኑ እፀውዕ ለኪ ብእሲተ ሐፃኒተ እምዕብራውያት ወትሕፅና ለዝ ሕፃን፣

ያንጊዜም የሕፃኑ እኅት ማርያም የፈርዖንን ልጅ ሕፃኑን ታሳድግልሽ ዘንድ ከዕብራውያን ወገን ሞግዚት የምትሆን ሴት ጠርቼ ላመጣልሽ? ትወጃለሽን አለቻት፤

፰፣ ወትቤላ ወለተ ፈርዖን ሑሪ ጸውዒ ሊተ፣

የፈርዖንም ልጅ እንኪያስ ሒደሽ ጠርተሽ አምጭልኝ አለቻት፣

ወሖረት እንታክቲ ወለት ወጸውዓታ ለእሙ ለውእቱ ሕፃን፣

ያችም ብላቴና ሔዳ የሕፃኑን እናት ጠርታ አመጣቻት፤

ወትቤ ነየ ሐፃኒት ፣

እነሆ ሞግዚት አመጣሁልሽ አለቻት፤

፱፣ ወትቤላ ወለተ ፈርዖን ዕቀቢ ሊተ ዘ ሕፃነ ወሕፅኒዮ ወአነ እሁበኪ ዐስበኪ፣

የፈርዖንም ልጅ የሕፃኑን እናት ይህን ልጅ ተንከባክበሽ ጠብቀሽ አሳድጊልኝ፣ እኔም የአሳዳጊነትሽን ዋጋ እሰጥሻለሁ አለቻት፣

ወነሥአቶ ይእቲ ብእሲት ለውእቱ ሕፃን ወሐፀነቶ፣

ያችም ሴት ሕፃኑን ተቀብላ አሳደገችው፣ ሐተታ ስታሳድገውም እንዲያው ያሳደገችው አይደለም፣ ተስፋ ያልተነገረላቸው የእሊህ የቈላፋን የግብፃውያን ልጅ አይደለህም፣ ተስፋ የተነገረላቸው የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ ልጅ ነህ እንጂ እያለች ተስፋውን እየነገረች አባቱም ዜና አበውን እየነገረ አሳድገውታል፤

፲፣ ወሶበ ጸንዐ ውእቱ ሕፃን ወሰደቶ ኀበ ወለተ ፈርዖን፤

ሕፃኑም ባደገ ጊዜ ሞግዚቲቱ ወስዳ ለፈርዖን ልጅ ሰጠችው፤

ወኮና ወልዳ ፣

ከዚህም በኋላ ልጅዋ ሆነ፤

ወሰመየቶ ስሞ ሙሴ ወትቤ እስመ እማይ ዘአውፃእክዎ፤

ስሙንም ከውሀ ያገኘሁት ስትል ሙሴ አለችው፣

፲፩፣ ወኮነ እምድኅረ ብዙኅ መዋዕል ልሕቀ ሙሴ ወወፅአ ኀበ አኃዊሁ ወርእየ ሕማሞሙ፤

ሙሴም የአርባ ዘመን ጐልማሳ ከሆነ በኋላ ወንድሞቹ እስራኤል ወደ አሉበት ወደ ራምሴ በሔደ ጊዜ ግብጻውያን የሚሠሩባቸውን ግፍ አይቶ ፈጽሞ

www.ethiopianorthodox.org

አዘነ፤ ሐተታ ሔዶ መጐብኘቱ እናት አባቱ ተስፋ የተነገረ ላቸው የእስራኤል ወገን መሆኑን እየነገሩ አሳድገው ታልና ስለዚህ ነው፤

ወረከበ ብእሴ ግብፃዌ እንዘ ይዘብጦ ለ፩ዱ ዕብራዊ እምአኀዊሁ ደቂቀ እስራኤል፣

አንድ የግብጽ ሰው ከእስራኤል ልጆች ከወንድሞቹ አንዱን ዕብራዊ ሲመታው አገኘ፤ ሐተታ ጠባቸውስ በምን ምክንያት ነው? ቢሉ በመስኖ ውሀ፤ አንድም ዕብራዊ ያወጣውን ዓሣ ግብጻዊው ልውሰድብህ ብሎት፤ አንድም በዘረጋው ጀንዲ በበጠበጠው እንዶድ ልጠብ ብሎት፣ ስንኳንስ በጀንዲው በገላህ፣ ስንኳን በእንዶዱ በደምህ ባጥብበት ማን አለ ብኝ በገዛ ባሪያዬ ብሎ፤

፲፪፣ ወነጸረ ለፌ ወለፌ ወአልቦ ዘርእየ፤

ሙሴም ለካ መምለኬ ጣዖቱ መምለኬ እግዚአብሔሩን እንዲህ አድርጎ ይበድለዋልን ብሎ ግራ ቀኝ አይቶ ያየው ሰው ሳይኖር፤

ወቀተሎ ለዝኩ ግብጻዊ ወደፈኖ ውስተ ፃ፤

ያን ግብፃዊ፣ ሙሴ ክቡደ መዝራዕት ነውና ወዲያው ገድሎ በአሸዋ ውስጥ ቀበረው፣ ይኸውም ምሳሌ ነው፣ ለጊዜው ግብፃውያንን አጥፍቶ ፳ኤልን ለማውጣቱ፣ ፍጻሜው ግን ግብጻዊ የዲያብሎስ፣ ዕብራዊ የአዳም፣ ሙሴ የወልደ እግዚአብሔር መትቶ መግደሉ፣ ጌታም በመስቀል ተሰቅሎ ዲያብሎስን ድል የመንሳቱ፤

፲፫፣ ወወፅአ በሳኒታ ዕለት ወረከበ ክልኤተ ዕደወ ዕብራውያነ እንዘ ይትበዓሱ፤

በበነጋው በራምሴ በጋምሴ ያሉትን ዘመዶቹን ጠይቆ ሲመለስ ከዕብራውያን ሁለት ሰዎች ሲጣሉ አገኘ፤

ወይቤሎ ሙሴ ለዘይገፍዕ ለምንት ትዘብጦ ለካልእከ፣

ሙሴም በደለኛውን አይቶ አንተሳ ወንድምህን ለምን ትመታዋለህ? አለው፤

፲፬፣ ወይቤሎ ዝኩ ዘይዔምፆ ለካልኡ መኑ ሤመከ መልአከ ወመኰንነ ላዕሌነ አው ትፈቅድኑ ትቅትለኒ በከመ ቀተልኮ ትማልም ለግብጻዊ፣

ያም ወንድሙን የሚበድለው ሰው በእኛ ፈራጅ ዳኛ አድርጎ የሾመህ ማነው? ወይስ ትናንት ያንን ግብጻዊ እንደ ገደልከው ዛሬም እኔን ልትገድለኝ ትወዳለህን አለው፤ /ሐተታ/ ምነዋ



ወነጸረ ለፌ ወለፌ ወኢርእየ ምንተኒ አላለምን ቢሉ፣ እሱ አላየም አለ እንጂ ሌላው እሱን አላየውም አልን? በዱር በገደል ያለ ሰው አይቶ ነግሮ በታል፤ አንድም አመስጋኝ አማሳኝ እንዲሉ ትናንት ወንድሜ ሙሴ ባይኖር ያ ግብፃዊ ገድሎኝ ነበር ሲል የሰማ ሰው ነግሮበታል፤ አንድም አምባ ጓሮ ወዳጅ፣ በትረ ፈሪ እንዲሉ የው ያዳነው ሰው ነው፤

ወፈርሀ ሙሴ ወይቤ ከመዝኑ ክሡተ ኮነ ዝ ነገር፣

ሙሴም ይህ ነገር እንዲህ በሁሉ ዘንድ የተገለጸ ሁኖአል? ብሎ ፈራ፤

፲፭፣ ወሰምዐ ፈርዖን ዘንተ ነገረ ወፈቀደ ይቅትሎ ለሙሴ፣

ፈርዖንም ይህንን ነገር ሰምቶ ሙሴን ሊገድለው ወደደ፤

ወተግኅሠ ሙሴ እምገጸ ፈርዖን ወኃደረ ውስተ ምድረ ምድያም፣

ሙሴም ከፈርዖን ሸሽቶ ሔዶ ምድያም ከሚባል አገር ኖረ፤

ወሶበ በጽሐ አሐተ ምድረ ምድያም ነበረ ዲበ አዘቅት፣

ሸሽቶ ሲሔድ በምድያም አውራጃ ከአንዲቱ አገር በደረሰ ጊዜ በውሀ ዳር ተቀመጠ፣ ስለምን ቢሉ በመንገደኛ ልማድ መንገደኛ ከውሀ ዳር አርፎ ጥሬ ቈርጥሞ ውሀ ጠጥቶ እንዲሄድ፤

፲፮፣ ወቦ ለማርያ ምድያም ሰብዑ አዋልድ፣

ለምድያሙ ካህን ለዮቶር ሰባት ሴቶች ልጆች ነበሩት፤

ወይርእያ አባግዓ አቡሆን፣

እነሱም የአባታቸውን በጎች ይጠብቁ ነበር፣

ወመጽአ ወሔበ ሎን እስከ መልዐ ገብላተ ከመ ያስትያ አባግዓ አቡሆን፣

የአባታቸውን በጎች ውሀ ለማጠጣት በመጡ ጊዜ ውሀውን እየቀዱ በገንዳ መላላቸው፤ (ሐተታ) የአገራቸው ውሀ እንደ ደንቢያ እንደ ፎገራ እንደ አኵስም የጕድጓድ ውሀ ነው፣ ጠላት መርዝ እንዳይጥልበት ብለው ደንጊያ ይገጥሙታልና፣ የሚከፍትላቸው አጥተው ዳር ዳሩን ሲያበሉ አይቶ ምነው እናንተ አታጠጡም? አላቸው፣ እረኞች ተሰብስበው ካልመጡ የሚከፍትልን የለም እንጂ አሉት፣ ሙሴ ክቡደ መዝራዕት ነውና ከፍቶላቸው አጠጥተዋል፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፯፤ ወሶበ መጽኡ ኖሎት አሰስ ልዎን፤

ኖሎትም /እረኞችም/ ተሰብስ በው በመጡ ጊዜ ከመ፝ቼ ወዲህ ነው ከእኛ ቀድማችሁ የምታጠጡ ብለው ወግደው አሉዋቸው፤

ወተንሥአ ሙሴ ወአድኃኖን ወአስ ተየ አባግዓ አቡሆን፤

ሙሴም ተነሥቶ ግዳይ ለፈ ለመ፤ ውሀ ለቀደመ አይደለ ምን፤ እናንተም እንደ መጣችሁ አጠጡ፤ እነሱም እንደ መጡ ያጠጡ እንጂ ብሎ ተከራክሮ አስጣላቸው፤ ፍትሐ ሙሴ የሚያሰኘው ቅሉ ይህ ነው፤ እነሱም የአባታቸውን በጎች አጠጥተው፤

፲፰፤ ወሐራ ኀበ ራጉኤል አቡሆን፤

ወደ አባታቸው ወደራጉኤል ፈጥነው ሔዱ፤

ወይቤሎን እሮኑመ አፍጠንክን መጺአ ዮምሰ፤

አባታቸው ራጉኤልም ልጆቼ ዛሬስ እንደምን ፈጥናችሁ መጣችሁ በጎችም ከወትሮው ይልቅ ጠግበዋል አላቸው፤ /ሐተታ/ አፍጠንክን አለ፤ ወትሮ በኋላ አጠጥተው ከመሸ ይሔዱ ነበርና ጠግበዋል አለ፤ በኋላ አጠጥተው ውሀው አልቆ ባቸው፤ አንድም ውሀው ተበላ ሽቶባቸው ሳይጠግቡ ይሔዱ ነበርና፤

፲፱፤ ወይቤላሁ ብእሲ ግብጻዊ አድኃነነ እምኖሎት ወሔበ ለነ ወአስተየ አባግዒነ፤

አንድ ግብፃዊ ሰው ከእረኞች ተከራክሮ አስጥሎ ውሀውንም እየቀዳ በጎቻችንን አጠጥቶልን ነው አሉት፤ /ሐተታ/ በምን አውቀው ግብጻዊ አሉት ቢሉ ባነጋገሩ ባጠማጠሙ፤

፳፤ ወይቤሎን ለአዋልዲሁ አይቴ ውእቱ ብእሲሁ፤

ልጆቼ ያ ሰው አሁን የት ነው?

ወለምንት ኃደጋሁ ለውእቱ ብእሲ፤

እንዲህ ያለውን ሰው ለምን ትታችሁ መጣችሁ፤

ፀውዕሁ ከመ ይብላዕ እክለ፤

አሁንም ጥሩትና እህል ይቅመስ፤ ሐተታ ያንጊዜም ሚስቱ ሲፓራ አሁንም አሳጣውም ልሒድ ብላ ሒዳ ይዛው መጥታለች፤ ባሏ የሚሆን ነውና ፈቃደ እግዚአብሔር አነሣስቷት፤ አንድም መልአክ እየመራ ከዚያው አድርሷታል፤

፳፩፤ ወኃደረ ሙሴ ኀበ ውእቱ ብእሲ ወወሀቦ ወለቶ ሲፓራሃ ትኩኖ ብእሲተ፤

ሙሴም ሲፓራ የምትባለውን ልጁን ሚስት ልትሆነው ሰጥ



ቶት ከዚያ ሰው ጋራ አደረ፤ ሐተታ አንድ ቀን አድሮ በበነጋው ልሒድ አሰናብተኝ ቢለው፤ እሱም የት ትሔዳለህ? አለው፤ እግሬ ካደረሰኝ አለው፤ ውሀ ቢቀዱት ቢቀዱት መንገድ ቢሔዱት ቢሔዱት ያልቃልን ለኔ ወንድ ልጅ የለኝምና ከእነዚህ ከልጆቼ አንዲቱን አግብተህ በጎቼን እየጠበቅህ ተቀመጥ ብሎት በዚህ ተዋው ለው ሚስት ልትሆነው ሲፓራ ልጁን ሰጥቶታል፤

፳፪፤ ወፀንሰት ይእቲ ብእሲት ወወለደት ወልደ፤

ያችም ሴት ወዲያው ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለደች፤

ወሰመዮ ስሞ ሙሴ ጌርሳም ወይቤ እስመ ነግድ አነ በምድረ ነኪር፤

ሙሴም በባዕድ አገር የምኖር ስደተኛ መጻተኛ ነኝ ሲል ስሙን ጌርሳም አለው፤

፳፫፤ ወፀንሰት ዳግመ ወወለደት ወልደ ወሰመዮ ኤልዛር ወይቤ ፈጣሪ ዘአቡየ ረዳእየ፤

ዳግመኛም ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለደችለት፤ ረዳቴ የአባቴ ፈጣሪ ከፈርዖን እጅ አዳነኝ ሲል ስሙን ኤልዛር አለው፤ አንድም ረድአኒ ወአድኃነኒ ይላል፤ የአባቴ ፈጣሪ ረዳኝ ከፈርዖንም እጅ አዳነኝ ሲል ነው፤

፳፬፤ ወእምድኅረ ብዙኅ መዋዕል ሞተ ንጉሠ ግብጽ፤

ከብዙ ቀንም በኋላ የግብጹ ንጉሥ ፈርዖን ሞተ፤ ሐተታ የእስራኤል ነገሥታት የሆኑ እንደሆኑ ተስፋው ይነገርላቸዋል፤ ዘመን ይቈጠርላቸዋልና በዚህ ቀን ሞተ፤ በዚህ ቀን ተወለደ ይባላል፤ የአሕዛብ ነገሥታት ግን ተስፋው አይነገ ርላቸውም፤ ዘመን አይቈጠ ርላቸውምና ቀኑን ሳይለይ ብዙኅ መዋዕል አለ፤

ወግዕሩ ደቂቀ እስራኤል እምግብ ሮሙ ወአውየዉ፤

የእስራኤልም ልጆች ከሥራቸው ጽናት የተነሣ ተጨንቀው ወደ እግዚአብሔር ጮሁ፤

ወዐርገ አውያቶሙ ኀበ እግዚአ ብሔር እምግብሮሙ፤

ከሥራቸው የተነሣ ወደ እግዚ አብሔር ተጨንቀው ጮሁ ለመኑ፤ ዐርገ ማገኘ፤ አንድም ከጽኑ ሥራቸው የተነሣ ጩኸ ታቸው፤ አንድም እምገዓሮሙ ይላል፤ ከጩኸታቸው የተነሣ ልመናቸው ወደ እግዚአብሔር ደረሰ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፩፣ ወሰምዐ እግዚአብሔር ገዓሮሙ ወተዘከረ መሐላሁ ዘመሐለ ለአብርሃም ወለይስሐቅ ወለያዕቆብ፣

እግዚአብሔርም ጩኸው የለመኑትን ልመናቸውን ሰምቶ ለአባቶቻቸው ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ የማለውን መሐላ አሰበ፤

ወሐወፆሙ ለደቂቀ እስራኤል፣

መሐላውንም አስቦ የእስራኤልን ልጆች በረድኤት ጐበኛቸው፤ አንድም በረድኤት መጐብኘቱም ታወቀላቸው::

## ምዕራፍ ፫

### ገባኤ

፩፣ ወሀሎ ሙሴ ይርኢ አባግዓ ዮቶር ሐሙሁ ማርያ ምድያም፣

ሙሴም የምድያም ካህን የአማቱ የዮቶርን በጎች ይጠብቅ ነበር፤

ወወሰደ አባግዒሁ ሐቅለ ወበጽሐ ውስተ ኮሬብ ደብረ እግዚአብሔር፣

በጎቹንም እየነዳ እግዚአብሔር ወደሚገለጥባት የኮሬብ ምድረ በዳ ደረሰ፤

፪፣ ወአስተርአዮ ለሙሴ መልአከ እግዚአብሔር በነደ እሳት እምዕፀት፣

ከእግዚአብሔር የተላከ መልአክ በዕንጨቱ ላይ በሚነድ እሳት ላይ ሁኖ ለሙሴ ታየው፤ አንድም ከዕንጨቱ ላይ በሚነደው እሳት አጠገብ ቁሞ ታየው፤

ወርእየ ሙሴ ከመ እምዕፀታ ይነድድ እሳት ወዕፀታ ኢትውኢ፣

ሙሴም ከዕንጨቲቱ ላይ እሳት ሲነድ እንጨቲቱ ሳትቃጠል አየ፤ (ሐተታ) ነበልባል ከሐመልማል፣ ሐመልማል ከነበልባል ተዋሕዶ ነበልባሉ ሐመልማሉን ሳያቃጥለው፣ ሐመልማሉ ነበልባሉን ሳያጠፋው አይቷል፤ ይኸውም ምሳሌ ነው፣ ሐመልማል የእስራኤል፣ ነበልባል የመከራቸው፣ ሐመልማሉ ነበልባሉን እንዳላጠፋው እስራኤልም መከራ ግብጽን አዝነን ተክዘን ግብር ገብተን እናርቀው ያለማለታቸው ምሳሌ፣ ነበልባሉ ሐመልማሉን እንዳላቃጠለው መከራ ግብጽም እስራኤልን ጨርሶ አላጠፋቸውምና፣ ለጊዜው ይህ ነው፣ ፍጻሜው ግን ነበልባል የመለኮት፣ ሐመልማል የትስብእት፣ ነበልባሉ ሐመልማሉን እንዳላቃጠለው ሐመልማሉ ነበልባሉን እንዳላጠፋው መለኮት ምልዓቱን ስፋቱን ርቀቱን ሳይተው፣ ሥጋም ግዙፍነቱን ዕበቱን ውሱንነቱን ሳይተው በተዓቅቦ የመዋሐዳቸው ምሳሌ፣ አንድም ነበልባል የጌታችን፣ ሐመል



ማል የእመቤታችን ምሳሌ፣ ነበልባሉ ሐመልማሉን እንዳላቃጠለው፣ ጌታም ሰው ሲሆን እመቤታችንን ባሕርየ መለኮቱ አላለወጣትምና፤

፫፣ ወይቤ ሙሴ እብጻሕ ወእርአይ ዘ ራእየ ዓቢየ እፎ ኢትውዒ ዛ ዕፀት፣

ሙሴም ይህንንስ ደገኛ ራእይ ቀርቤ ልረዳው ይህች ዕንጨት ከእሳቱ ጋር ተዋሕዳ እንደምን አትቃጠል? አለ፣ ይህንንም ብሎ፣ ወቀርበ ይጠይቆ ይላል፣ በጎቹን አንድ ወገኑ ከፈረስ ግንብ አግብቶ ዘግቶባቸው ሒዷል፤ አንድም ከፈረፈር ዘለሳ መትቶባቸው ሒዷል፣ ስለምን ቢሉ ለጊዜው የሰው ገንዘቦች ናቸውና እንዳይጠፉበት ነው፣ ፍጻሜው ግን ሙሴ የመናንያን አምሳል ነው፣ እንመንናለን እንማራለን፣ ምሥጢር እንረዳለን ባላችሁ ጊዜ ልብ እንዳይቀራችሁ ገን ዘባችሁን መጽውታችሁ፣ አንድ ወገን ሁናችሁ ሒዱ ሲል ነው፣ ኢትፈር ኀቤሃ ለጥበብ በክልኤ ልብ አላ ኩን ከመ ዘይዘርእ ወየዓርር ወየዓዕድ እንዲል ሲራክ፤

ከላይ መልአክ ብሎ ነበር ከዚህ እግዚአብሔር አለ፣ እንደም ነው ቢሉ እግዚአብሔር ካለ መልአክ፣ መልአክ ካለ እግዚአብሔር አይለይምና፤

፬፣ ወሶበ ርእየ እግዚአብሔር ከመ መጽአ ይርአይ ጸውዖ እምዕፀት ወይቤሎ ሙሴ ሙሴ ወይቤ ምንትውእቱ እግዚእ፣

እግዚአብሔርም ሙሴ ይኸንን ራእይ ሊያውቅ ሊረዳ እንደ መጣ ባየው ጊዜ፣ መልአኩ ነው ያሉ እንደሆነ ከዕንጨቲቱ አጠገብ ሁኖ፣ እግዚአብሔር ነው ያሉ እንደ ሆነ በመልአኩ አድሮ፣ ሙሴ ሙሴ ብሎ ጠራው ሙሴም ጌታዬ ምንነው? አለው፤

፭፣ ወይቤሎ ኢትቅረብ ዝየ ፍታሕ አሣዕኒከ እምእገሪከ እስመ መካን እንተ አንተ ትቀውም ባቲ ምድር ቅድስት ይእቲ፣

ጌታም በሩቅ ባየው ጊዜ ይህች የምትረግጣት ምድር የተቀደሰች ናትና፣ ጫማህን ከእግርህ ሳታወልቅ ወደዚህ አትቅረብ አለው፣ ስለምን ቢሉ ሥርዓት ሲያስተምረው ነው፣ ስንኳንስ ከሰማያዊ ንጉሥ ከምድራዊ ንጉሥ ጋር ሲገናኙ ጫማ አውልቆ፣ ታጥቆ መሔድ ይገባልና፤ አንድም ለጊዜው በዘፈቀደ ታይቶባታል፣ ያም የሥጋዊ አምሳል ነው፣ የሥጋዊ ነገር ከሚነገርበት ቦታ ጫማ አውልቆ ታጥቆ መሔድ ይገባልና፤

www.ethiopianorthodox.org

አንድም የቤተ ክርስቲያን አምሳል ናት፤ ዛሬም ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ ጫማ አውልቆ ታጥቆ መግባት ይገባልና፡ አንድም አሁን ነዓ እፌኑከ ኀበ ፈርዖን ንጉሠ ግብጽ የሚለው ነውና፤ አሳዕነ ፍርሃትን ከልቡናህ አርቅ ሲለው ነው፡ አንድም ከግብጽ ከወጣህ በኋላ የምሠራልህ ሕግ ክብርት ናትና፡ ክህደት ጥርጥርን ተው ሲለው ነው፤ አንድም ፋል የሚባል ጥንቈላ ተምሮ ነበርና ያንን ተው ሲለው ነው፤ ልማደ ዮቶርንም ተው ሲለው ነው፡

፮፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር አነ ውእቱ አምላከ አበዊከ አምላከ አብርሃም ወአምላከ ይስሐቅ ወአምላከ ያዕቆብ፤

እግዚአብሔርም ሙሴን የአባቶችህ የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ ፈጣሪ እኔ ነኝ አለው፤ ከዚህም ሦስት ጊዜ አምላክ አምላክ አምላክ ብሎ የሦስትነቱን፤ አነ ውእቱ ብሎ የአንድነቱን ተናገረ፡

ወሜጠ ገጾ ሙሴ እስመ ፈርሀ ነጽሮ ቅድመ እግዚአብሔር፤

ሙሴም የእግዚአብሔርን ፊት ማየት ስለፈራ ፊቱን መለሰ፡

፯፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ርእየ ርኢኩ ሥቃዮሙ ለሕዝብየ እለ ውስተ ግብጽ ወአውያቶሙ ሰማዕኩ እምንዳዕተ ገባር ወአእመርኩ ገዓሮሙ፤

እግዚአብሔርም ሙሴን በግብጽ ያሉ የወገኖቼን መከራ አይቼ በሠራተኞች የተሾሙ ሹማምቱ ካመጡባቸውም መከራ የተነሣ ጩኸታቸውን ሰምቼ መጨነቃቸውንም አይቼአለሁ አለው፡

፰፤ ወወረድኩ ከመ አድኅኖሙ እምእደ ግብጽ ወእሰዶሙ ውስተ ምድር ሠናይት ወርኅብት፤

ከግብጻውያን እጅ አድናቸው ዘንድ ወደ አማሬች ወደ ተወደዶች ሰፊ ወደምትሆን ወደ ከነዓንም እወስዳቸው ዘንድ ወረድኩ፤ (ሐተታ) መውጣት መውረድ ኖሮበት አይደለም መራዳቱን መናገር ነው፡

ወአወፅአሙ እምይእቲ ምድር ወእወስዶሙ ውስተ ምድር እንተ ታውኅዝ ሐሊበ ወመዓረ፤

ከግብጽም አውጥቼ ማርና ወተት የሚጐርፍባት ማለት ተድላ ደስታ ወደማይታጣባት ወደ ከነዓን እወስዳቸዋለሁ፡

ውስተ ምድሮሙ ለከናኔዎን፤ ወለኬጤዎን፤ ወለአሞሬዎን፤ ወለፌርዜዎን፤ ወለጌርጌሴዎን፤ ወለኤዌዎን፤ ወለኢያቡሴዎን፤

ይህቺውም እነሱን የምወስድባት አገር የከናኔዎን፤ የኬጤ



ዎን፤ የአሞሬዎን፤ የፌርዜዎን፤ የጌርጌሴዎን፤ የኤዌዎን፤ የኢያቡሴዎን አገር ናት፡

፱፤ ወይእዜኒ ናሁ ገዓሮሙ ለደቂቀ እስራኤል በጽሐ ኀቤየ፤

አሁንም የእስራኤል ልጆች ጩኸታቸው እነሆ ከእኔ ደረሰ፡

ወርኢኩ አነ ሥቃዮሙ ዘይሣቅይዎሙ ግብጽ፤

ግብጻውያን የሚያጸኑባቸው ጽኑ መከራቸውንና ጭንቀታቸውንም አየሁ፡

፲፤ ወይእዜኒ ነዓ እፌኑከ ኀበ ፈርዖን ንጉሠ ግብጽ ወታወፅኦሙ ለሕዝብየ ደቂቀ እስራኤል እምድረ ግብጽ፤

አሁንም ወደ ግብጹ ንጉሥ ወደ ፈርዖን ና ልላክህ ወገኖቼ የእስራኤልን ልጆች ከግብጽ አገር ታወጣቸዋለህና አለው፤ ነዓ እፌኑከ ባለው አኢ ይሳል ጥሬ፡

፲፩፤ ወይቤሎ ሙሴ ለእግዚአብሔር መኑ አነ ከመ እሑር ኀበ ፈርዖን ንጉሠ ግብጽ ወከመ አውፅኦሙ ለደቂቀ እስራኤል እምድረ ግብጽ፤

ሙሴም እግዚአብሔርን ወደ ግብጹ ንጉሥ ወደ ፈርዖን ተልኬ እሔድ ዘንድ፤ የእስራኤልንስ ልጆች ከግብጽ አገር አወጣቸው ዘንድ እኔ ማንኝ? አለ፤ እኔ ምን ቁም ነገር ነኝ? ማለቱ ነው፡

፲፪፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ እስመ አነ ሀለውኩ ምስሌከ፤

እግዚአብሔርም ሙሴን እኔ ካንተ ጋራ በረድኤት አለሁና፤

ወዝንቱ ተአምር ለከ ከመ አነ እፌንወከ፤

እኔም እንደ ላክሁህ የሚያስረዳልህ ምልክቱ ይህ ነው፡

ሶበ አውጻእካሆሙ ለሕዝብየ እምብሔረ ግብጽ ወትጸመድዎ ለእግዚአብሔር በዝ ደብር፤

ወገኖቼ እስራኤልን ከግብጽ ካወጣሃቸው በኋላ በዚህ በደብረ ሲና ታገለግሉኛላችሁ አለ፤ ሕጌን ትጠብቃላችሁ መሥዋዕት ትሠዋላችሁ ማለቱ ነው፡

፲፫፤ ወይቤሎ ሙሴ ለእግዚአብሔር ናሁ አነ አሐውር ኀበ ደቂቀ እስራኤል ወእብሎሙ አምላከ አበዊክሙ ፈነወኒ ኀቤክሙ፤

ሙሴም እግዚአብሔርን እንዲህ አለው ተልከህ ትሔዳለህ እንዳልከኝ ወደ እስራኤል ልጆች አሁን ተልኬ ሒጄ፤ የአባቶቻችሁ ፈጣሪ ወደ እናንተ ልኮ ሰድዶኛል እላቸዋለሁ፡

ወሶበ ይሴአሉኒ ስመከ ምንተ እብሎሙ፤

ማን ላከህ? ብለው ስምህን በጠየቁኝ ጊዜ ማን ላከኝ ልበላቸው? አለው፡

www.ethiopianorthodox.org

፲፬፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር አነ ውእቱ ዘሀሎ ወይሄሉ፤

እግዚአብሔርም ዘሀሎ ቅድመ ዓለም የነበርኩ፤ ወይሄሉ ይህን ዓለም አሳልፌ /የምቀር/ የምኖር እኔ ነኝ፤

ወከመዝ ትብሎሙ ለደቂቀ እስራኤል ዘሀሎ ፈነወኒ ኀቤክሙ፤

የእስራኤልም ልጆች ማን ላከህ ብለው ቢጠይቁህ፤ ቅድመ ዓለም የነበረ እግዚአብሔር ወደ እናንተ ልኮኛል በላቸው አለው፤

፲፭፤ ወዓዲ ይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ከመዝ ትብሎሙ ለደቂቀ እስራኤል እግዚአብሔር አምላከ አበዊክሙ ፈነወኒ ኀቤክሙ፤

ዳግመኛ እግዚአብሔር ሙሴን የእስራኤልን ልጆች የአባቶቻችሁ የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ ፈጣሪ ወደ እናንተ ላከኝ በላቸው፤

ዝንቱ ስምየ ዘለዓለም ወዝክርየኒ ለትውልደ ትውልድ፤

ይህም ስሜ የዘለዓለም ነው፤ የስሜ አጠራርም ለልጅ ልጅ ዘመን ነው፤ ዘሀሎ ወይሄሉ ያለውን ተረጐመ፤ አንድም አኽያ ሸራኽያ አልሻዳይ ይላል፤ አኽያ ዘሀሎ፤ ሸራኽያ ወይሄሉ፤ አልሻዳይ አምላከ ተስፋ አምላከ ዕብራውያን ማለት ነው፤

፲፮፤ ሑር አስተጋብእሙ ለአዕሩገ እስራኤል ወበሎሙ እግዚአብሔር አምላከ አበዊክሙ አምላከ አብርሃም ወአምላከ ይስሐቅ ወአምላከ ያዕቆብ አስተርአየኒ፤ ወፈነወኒ እንዘ ይብል ሐውፆ ሐወፅኩክሙ በእንተ ኵሉ እንተ በጽሐተክሙ በብሔረ ግብጽ፤

ሒደህ የእስራኤልን ሽማግሎች ሰብስበህ የአባቶቻችሁ የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ ፈጣሪ እግዚአብሔርም ተገልጾልኝ በግብጽ አገር ስላገኛችሁ መከራ ሁሉ በረድኤት ጐበኘኋችሁ በላቸው ብሎ ላከኝ ብለህ ንገራቸው አለው፤

፲፯፤ ወእቤ አነ እንሥአክሙ እምሥቃየ ግብጽ ወአዐርገክሙ ውስተ ምድረ ከናኔዎን ወኬጤዎን ወኤዌዎን ወአሞሬዎን ወፌርዜዎን ወጌርጌሴዎን ወኢያቡሴዎን ውስተ ምድር እንተ ታውኅዝ ሐሊበ ወመዓረ፤

እኔም ከግብጽ መከራ አውጥቼ ወተትና ማር የምታፈስ ማለት፤ ተድላ ደስታ በሚበዛባት በከነዓን ከናኔዎን ኬጤዎን ኤዌዎን አሞሬዎን ፌርዜዎን ጌርጌሴዎን ኢያቡሴዎን የሚባሉ ሰዎች ወርሰዋት ወደ ነበረች ምድር እወስዳችኋለሁ አለ በላቸው፤



፲፰፤ ወይሰምዑ ቃለከ፤

ይህንንም በነገርኻቸው ጊዜ ነገርህን ይቀበሉሃል፤

ወትበውእ አንተ ወአዕሩገ እስራኤል ኀበ ንጉሠ ግብጽ ወትብሎ እግዚአብሔር አምላከ ዕብራውያን ጸውዐነ ንሑር ምሕዋረ ሠሉስ ዕለት ውስተ ሐቅል ከመ ንሡዕ ለእግዚአብሔር አምላክነ፤

አንተም ከእስራኤል ሽማግሎች ጋራ ወደ ግብጽ ንጉሥ ወደ ፈርዖን ገብተህ ለፈጣሪያችን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ለመሠዋት የሦስት ቀን መንገድ ወደ ምድረ በዳ እንሔድ ዘንድ የዕብራውያን ፈጣሪ እግዚአብሔር ጠርቶናል በለው፤

፲፱፤ ወአነ አአምር ከመ ኢያበውሐክሙ ፈርዖን ንጉሠ ግብጽ ትሃእ ዘእንበለ በእድ ጽንዕት፤

የግብጽ ንጉሥ ፈርዖን ግን በጸናች እጅ ማለት፤ በዐሥር መቅሠፍት፤ በዐሥራ አንደኛ ሥጥመት ነው እንጂ፤ በፍቅር ተሰናብታችሁ ትሔዱ ዘንድ እንዳያሰናብታችሁ እኔ አውቃለሁ፤

፳፤ ወእሰፍሕ እዴየ ወእቀትሎሙ ለግብጽ በኵሉ መድምምየ ዘእገብር ቦሙ፤

እኔም እደ መዓቴን ዘርግቼ በማደርግባቸው ተአምራት ሁሉ ግብፃውያንን አጠፋቸዋለሁ፤

ወእምድኅረዝ ይፌንወክሙ፤

ከዚያ በኋላ ግን አሰናብቶ ይሰድዳችኋል፤

፳፩፤ ወእሁቦሙ ሞገሰ ለሕዝብየ በቅድሜሆሙ ለግብጽ፤

በግብፃውያን ፊት ለወገኖቼ ለእስራኤል ባለሟልነትን እሰጣቸዋለሁ አለ፤

፳፪፤ ወአመ ተሐውሩ ኢትወፅኡ ዕራቃኒክሙ፤

መሣሪያ እንዲያውሷችሁ አደርጋለሁ ማለቱ ነው፤ ከግብጽም ወጥታችሁ በምትሔዱበት ጊዜ ባዶዋችሁን ወጥታችሁ አትሔዱም፤

አላ ታስተዋሕስ ብእሲት እምነራ ወእምኃደርታ እምእግዝእታ ንዋየ ወርቅ ወብሩር ወልብስ፤

ታስተዋሕስ ሴት ጎረቤት ከጎረቤቷ፤ ባሪያ ከእመቤቷ፤ የወርቅና የብሩን መሣሪያ ወልብስ ልብሱንም ትዋስ እንጂ፤

ወትወድይዎ በዲበ ደቂቅክሙ ወአዋልዲክሙ ወተሀበልይዎሙ፤

ይህንንም ለሴቶችና ለወንዶች ልጆቻችሁ ጌጥ ታደርጉላቸዋላችሁ፤ እንዲህ አድርጋችሁ ግብጻውያንን በዝብዛችኋቸው ትወጣላችሁ፤ ምክንያት አድርጋችሁ፤ ምንዋ የሰው ገንዘብ

www.ethiopianorthodox.org

አትውሰዱ ይል የለም ቢሉ፣ ህየንተ ተቀንዮ ተቀንዩ፣ ወህየንተ ገብሩ ግንፋለ ይላል ሊቁ፣ የሦስት ከተማ ቅጽር አስቀጽረዋቸው ነበርና የዚያ ዋጋ ነው።

## ምዕራፍ ፬

### ገባኤ

፩፣ ወአውሥአ ሙሴ ወይቤ ለእመኬ ኢአምኑኒ ወኢሰምዑኒ ቃልየ ወይቤሉኒ ኢያስተርአየከ እግዚአብሔር ምንተ እብሎሙ፣

ሙሴም መለሰ፣ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር አልታየህም አልተነጋገረህም ብለው ቃሌን ባይሰሙኝ እኔንም ባያምኑኝ ምን ልበላቸው? ብሎ ጠየቀ፣

፪፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ምንት ዝ ዘውስተ እዴከ፣

እግዚአብሔርም ሙሴን ይህ በእጅህ የያዝከው ምንድነው? አለው፣ አሁን ሙሴ የያዘው ጠፍቶት አይደለም፣ ሊያናግረው ሊተረጕምለት ነው፤

ወይቤ በትር፣

ሙሴም በትር ነው አለው፤

፫፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ግድፎ ውስተ ምድር፣

እግዚአብሔርም ሙሴን በትሩን ወደ መሬት ጣለው አለው፤

ወገደፎ ውስተ ምድር ወኮነ አርዌ ምድር፣

ሙሴም በትሩን ቢጥለው እባብ ሆነ፤

ወጐየ ሙሴ እምኔሁ፣

ሙሴም እምኔሁ ከእባቡ ሸሽቶ ሔደ፤

፬፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ስፋሕ እዴከ ወንሥአ በዘነቡ፣

እግዚአብሔርም ሙሴን ተመልሰህ እጅህን ዘርግተህ ጅራቱን ይዘህ አንሣው አለው፤

ወሰፍሐ እዴሁ ሙሴ ወነሥአ በዘነቡ ወኮነ በትረ ውስተ እዴሁ ከመ ቀዳሚ፣

ሙሴም ተመልሶ ጅራቱን ይዞ ቢያነሣው እንደ ቀደመው በትር ሆነ፤ (ሐተታ) ይኸም ምሳሌ ነው፣ በትር የእስራኤል፣ እባብ መሆኑ በመከራ የመለወጣቸው፣ ሙሴ ፈርቶ መሸሹ ፈርቶ ምድያም የመሔዱ፣ ተመልሶ ቢያነሣው በትር መሆኑ፣ ሙሴም ግብጽ ተመልሶ ወርዶ ፈርዖንን ከነሠራዊቱ አጥፍቶ እስራኤልን የማውጣቱ ምሳሌ፤ አንድም በትር የሰውነታችን፣ እባብ መሆኑ የመሞታችን፣ ተመልሶ በትር መሆኑ የትንሣኤያችን፤ አንድም በትር የእኛ፣ መውደቁ የመሞታችን፣ እባብ መሆኑ የትንሣኤያችን፣ ያቺ ደመ ነፍስ የሌላት በትር ደመ ነፍስ ያላት እባብ እንደሆነች፣ እኛም ከፈረስን ከበሰበስን በኋላ እንደ ገና አእምሮ ንባብ፣ ሕይወት፣ አግኝተን የመነሣታችን ምሳሌ ነው፤

፭፣ ወይቤሎ ከመ ይእመኑከ ከመ አስተርአየከ እግዚአብሔር አምላከ አበዊሆሙ አምላከ አብርሃም ወአምላከ ይስሐቅ ወአምላከ ያዕቆብ፣

የአባቶቻቸው የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ ፈጣሪ እኔ እንደ ታየሁህ እንደ ተነጋገርሁህ እንዲያምኑህ ምልክቱ ይህ ነው አለው፣ በትሩ እባብ መሆኑ ነው፤ አንድም ወደፊት ደይ እዴከ ብሎ የሚያመጣውን ነው፤

፮፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ካዕበ ለሙሴ ደይ እዴከ ውስተ ሕፅንከ ወወደየ እዴሁ ውስተ ሕፅኑ ወይቤሎ አውፅአ እዴከ እምውስተ ሕፅንከ ወአውፅአ እዴሁ እምሕፅኑ ወኮነት ፀዓዳ ኰለንታሃ ለምፀ፣

ዳግመኛስ ቢሉኝ አለው፣ እግዚአብሔርም ዳግመኛ እጅህን ወደ ብብትህ አግባው አለው፤ ሙሴም እጁን ወደ ብብቱ አገባው፣ እግዚአብሔርም እጅህን ከብብትህ መልሰህ አውጣው አለው፣ መልሶ ቢያወጣው ለምፅ ሆነ፤

፯፣ ወይቤሎ ካዕበ ደይ እዴከ ውስተ ሕፅንከ ወወደየ እዴሁ ውስተ ሕፅኑ ወዓዲ ይቤሎ አውፅአ እዴከ እምሕፅንከ ወአውፅአ እዴሁ እምሕፅኑ ወገብአት ከመ ኅብረ ሥጋሁ፣

ጌታም ዳግመኛ እጅህን ከብብትህ አግብተህ አውጣው አለው፣ አግብቶ ቢያወጣው እንደ ቀደመው ደኅና ሆነ፣ ምሳሌው እንዳለፈው ነው፤

፰፣ ወይቤሎ ለእመ ኢአምኑከ ወኢሰምዑ ቃለከ በተአምር ዘቀዳሚ የአምኑከ በቃለ ተአምሩ ለካልእ፣

ከዚህ ቀድሞ ሙሴ ለእመኬ ኢአምኑኒ ወኢሰምዑኒ ቃልየ ብሎት ነበርና ጌታም በትርህን እባብ አድርገህ አሳይተሃቸው ቃልህን ባይሰሙህ ባያምኑህ፣ እጅህን ለምፅ አድርገህ አሳይተሃቸው በዚህ ምልክት ያምኑሃል አለው፤

፱፣ ወእምከመ ኢአምኑከ በእሉ ፪ቱ ተአምራት ወኢሰምዑ ቃለከ ትነሥእ እማየ ተከዚ ወትክዑ ውስተ የብስ ወይከውን ደመ ውስተ የብስ ዝኩ ማይ ዘነሣእከ እምተከዚ፣

በትርህን እባብ፣ እጅህን ለምፅ አድርገህ አሳይተሃቸው በእኒህ በሁለቱ ምልክቶች ባያምኑህ፣ ቃልህንም ባይሰሙህ፣



www.ethiopianorthodox.org

ከፈሳሹ ውሀውን ዘግነህ ወደ የብሱ እርጨው፣ ከፈሳሹ ዘግነህ የረጨኸው ውሃ ደም ይሆናል አለው፤ የእስራኤልን ልጆች እያነቁ ከፈሳሹ ጥለዋቸው ነበርና የዚያ ፍዳ ነው፤

፲፣ ወይቤሎ ሙሴ ለእግዚአብሔር አስተበቍዐከ እግዚኦ ቀዳሚየ ቃል አልብየ ወትካትየ ወኢእምአመ አእኀዝ እንብብ ቍልዔከ ጸየፍ ወላዕላዓ ልሳን አነ፣

ሙሴም እግዚአብሔርን ጌታዬ እለምንሃለሁ እኔ መጀመሪያ ነገር አላውቅም፣ ይኸውም ዛሬ አይደለም፣ ከጥንት ጀምሮ ነው፤ እኔም ባሪያህ መናገር ከጀመርሁ ይዞ አንደበቴ ያልቀና ድዳ ነኝ፣ ይህ ነገር እንደምን ይሆንልኛል አለው፤

፲፩፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ መኑ ወሀበ አፈ ለዕጓለ እመሕያው ወመኑ ገብሮ በሐመ ወጽሙመ ወፍቱሐ ወዘይሬኢ ወዕውረ፣ አኮኑ አነ ውእቱ እግዚእ እግዚአብሔር፣

እግዚአብሔርም ሙሴን ለሰው ሁሉ አንደበትን የፈጠረ ማነው? የሚናገረውን የሚሰማውን እንዳይናገር እንዳይሰማ፣ የማ ይናገረውን እንዲናገር፣ የሚያ የውን እንዳያይ፣ የማያየውን እንዲያይ የሚያደርገው ማነው?

የሁሉ ገዥ የምሆን እኔ እግዚ አብሔር አይደለሁምን አለው፤

፲፪፣ ወይእዜኒ ሑር ወአነ እፈትሕ አፉከ ወአሌብወከ ዘሀለወከ ትንብብ፣

አሁንም ወደ ላክሁህ ቦታ ሒድ፣ እኔም አንደበትህን አቀናል ሃለሁ፣ የምትናገረውንም ነገር ልብ አስደርግሃለሁ አለው፤

፲፫፣ ወይቤ ሙሴ አስተበቍዐከ እግዚኦ ኅሥሥ ለከ ባዕደ ዘይክል ዘትልእክ፣

ሙሴም አቤቱ እለምንሃለሁ ወደ ንጉሥ ቤት የሚላክ፣ ነገር አከናውኖ የሚናገር ሰው ነው፣ እኔ ነገር አከናውኖ መናገር አይቻለኝምና ሌላ ሰው ፈልገህ ላክ አለው፤

፲፬፣ ወተምዐ እግዚአብሔር መዓተ ላዕለ ሙሴ ወይቤሎ ነዋ አሮን እኁከ ሌዋዊ ወአእምር ከመ ነቢብየ ይነብብ ለከ፣ ወናሁ ውእቱ ይወፅእ ይትቀበልከ ወይሬእየከ ወይትፌሣሕ፣

ሙሴም የጌታን ቃሉን ቢያጥ ፍበት እግዚአብሔር በተግሣጽ ቃል ተናገረው፣ ከሌዊ ወገን የተወለደ ወንድምህ አሮን አለ፣ እኔ ለአንተ የነገርኩህን ለእሱ ነግረኸው እሱ እንዲና ገርልህ አውቃለሁ፣ እሱም አንተን ሊቀበልህ ከከተማው ይወጣል፣ አንተንም አይቶ ደስ ይለዋል አለው፤



፲፭፣ ወትነግሮ ወትወዲ ቃልየ ውስተ አፉሁ ወአነ እፈትሕ አፉከ ወአፉሁ ወአሌብወክሙ ዘትገብሩ፣

የነገርኩኽን ነገር እንድትነግ ረው አንደበትህን አቀናልሃ ለሁ፣ እሱም ደፍሮ እንዲናገር አደርገዋለሁ፣ የምትሠሩትንም ሥራ ሁሉ አውቃችሁ እንድ ትሠሩት አደርጋለሁ፣ ሳያውቁ በልማድ የሚሠራ ሥራ አለና፤

፲፮፣ ወውእቱ ይትናገር ለከ ኀበ ሕዝብ ውእቱ ይኩንከ አፈ ወአንተ ትከውኖ ለኀበ እግዚአብሔር፣

አንተ ከእኔ ያገኘኸውን ለእሱ ንገረው፣ እሱ ከአንተ ያገኘውን ለሕዝቡ ይንገርልህ አለው፤

፲፯፣ ወለዛቲ በትር እንተ ትገብር ባቲ ተአምረ ንሥኣ ውስተ እዴከ፣

ምልክት የምታደርግባት ያቺ ንም በትር ይዘሃት ሒድ አለው፣ ሐተታ ሙሴስ የተላ ከበት ምክንያት ምንድነው? ቢሉ፣ ራኄል የምትባል ሴት ነበረች፣ ባሏ ምናሴ ይባላል፣ መንገድ ሒዶ፤ አንድም ሙቶ ባት ነዪ ጡብ እርገጭ ብለው ወሰዱዋት፣ ሒዳ ስተረግጥ ፀንሳ ነበረችና ምጥ ተሰማት ሹሙን ምጥ ተሰምቶኛልና ወጥቼ ልውለድ አለቺው፣ አንቺማ ስትወጪ የንጉሥ ሥራ ይፈታ የለምን ብሎ በዘንግ

ወገቧን መታት፣ ያን ጊዜ መንታ አስወረዳት፣ ባይሆንም አውጥቼ ልቅበራቸው አለችው፣ የሰው ደም ማሸጋ ግንብ ያጸናል እንጂ ምን ይከፋ ብለሽው በይ አብረሽ እርገጫቸው ብሎ አስ ረግጧታል፣ እስዋም ኢሀሎኑ በገ ሰማይ አምላከ እስራኤል ብላ አልቅሳ እንባዋን ወደ ሰማይ ብትረጨው እስራኤል ሁለት መቶ አሥራ አምስት ዘመን ሳለቀሱት እንባ ሠረገላ ሁኖ አውጥቷቸዋል፤ አንድም አብርሃም በአካለ ነፍስ በአራት መቶ ሠላሳ ዘመን ከዚህ እስከ ዚህ ለልጆችህ ከነዓንን አወርስሃ ለሁ ያልከኝ ተስፋው ይህን ነውን? በየሔዱበት ወድቀው ወድቀው ከቀሩ በምን ይፈጸ ማል? እያለ ይካሰስላቸው ነበርና ስለዚህ ነው፤

፲፰፣ ወሖረ ሙሴ ወገብአ ኀበ ዮቶር ሐሙሁ ወይቤሎ አሐውር ወእገብእ ኀበ አኃውየ እለ ሀለው ውስተ ብሔረ ግብጽ ወእሬኢ ለእመ ዓዲሆሙ ሕያዋን፣

ሙሴም ከደብረ ሲና ወደ አማቱ ወደ ዮቶር ለመሰናበት ተመልሶ ሒዶ በግብጽ ያሉ ወንድሞቼ ደኅና እንደ ሆኑ ለማየት ወደ ግብጽ ተመልሼ እሔዳለሁና አሰናብተኝ አለው፤

www.ethiopianorthodox.org

ለእመ ኢመጽአ እኁክሙ ዘይንዕስ ምስሌክሙ ፤

ይሁዳም እንዲህ አለው አገረ ገገርው ታናሽ ወንድማችሁ ከናንተ ጋራ ካልመጣ ፤ ከእን ግዴህ ወዲህ ፊቴን አታዩትም ብሎ አዳኝቶብናል ፤

፬፡ ወእመሰ ትፌንዎ ለእኁነ ምስሌነ ነሐውር ወንሣየጥ ለከ እክለ ፤

አሁንም ወንድማችንን ከኛ ጋራ ትሰድደው እንደሆነ ሒደን እኽል እንሸምትልሃለን ፤

፭፡ ወለእመሰ ኢትፌንዎ ለእኁነ ምስሌነ ኢንሐውር ፤

ወንድማችንን ከኛ ጋራ የማት ልከው ከሆነ ግን አንሔድም ፤

እስመ ይቤለነ ውእቱ ብእሲ ኢት ሬእዩ እንከ ገጽየ ለእመ ኢየምጻእ ክምዎ ምስሌክሙ ለእኁክሙ ዘይን ዕስ ፤

አገረ ገገርው ታናሽ ወንድ ማችሁን ይዛችሁ ካልመጣችሁ እንግዲህ ወዲህ ፊቴን አታዩ ትም ብሎናልና ፤

፮፡ ወይቤሎሙ እስራኤል ምንትኑ ዛቲ እኪት ዘገበርክሙ ላዕሌየ ፤

ያዕቆብም እንዲህ አላቸው ፤ በኔ ላይ የመከራችሁት ይህ ክፉ ምክር ምንድር ነው ?

ዘነገርክምዎ ለውእቱ ብእሲ ከመ ብክሙ እኁ ፤

እኪት ያለውን ገለጠው ፤ ለዚያ ሰው ወንድም አለን ብላችሁ የነገራችሁት ለምንድር ነው ?

፯፡ ወይቤልዎ እስመ ተሰአለነ ብእሲ ፍጥረተነ ፤

እነሱም እንዲህ አሉት ፤ ልደ ተነ ሲል ነው ፤ ያ ሰው ትው ልዳችንን ስለ ጠየቀን ፤

ወይቤለነ ሀለወኑ አቡክሙ አረጋዊ ሕያውኑ ፤

ሽማግሌ አባት አላችሁን አለን፤ አዎን ብንለው ከጉልበት ነውን ፤

ወቦኑ ዘብክሙ እኁ ፤

ወንድምሳ አላችሁን ብሎ ስለ ጠየቀን ፤

ወነገርናሁ ዘከመ ተስእለነ ፤

እንደጠየቀን ነገርነው ፤

ቦኑ አእመርነ ከመ ይብለነ አምጽ እዎ ለእኁክሙ ፤

በውኑ ወንድማችሁን አምጡት እንዲለን አውቀን ኑረናልን ፤

፰፡ ወይቤሎ ይሁዳ ለአቡሁ ፈንዎ ለገዘ ሕፃን ምስሌየ ፤

ይሁዳም ይህነን ልጅ ከኔ ጋራ ስደደው፤ ማለት በኔ እምነት ስደደው ፤



ንትነሣእ ወንሑር ከመ ንሕየው ወኢ ንሙት ንሕነሂ ወደቂቅነሂ ፤

እኛም ልጆቻችንም በረኃብ ከመሞት እንድን ዘንድ እሱን ይዘን እንሂድ ፤

፱፡ ወአነ እትሐበዮ ፤

እኔ ዋስ፤ መያገ እሆነዋለሁ፤

ወኪየየ ኅሥሥ ለእመ ኢየግባእክዎ ኀቤከ ፤

ወደ አንተ መልሼ ያላመጣሁት እንደሆነ መርገምህ ይመራመ ረኝ ፤

ወለእመ ኢያቀምክምዎ ቅድሜከ ጊጉየ ኮንኩ ላዕሌከ በኵሉ መዋዕልየ፤

መልሼ አምጥቼ በፊትኽ ያላ ቆምኹት እንደሆነም ባለ በዘ መኔ ሁሉ ርጉም ልሁን ፤

፲፡ ወሶበ አኮ ዘጐንደይነ እምደገምነ ካዕበ ገቢዓ ፤

እስካሁን ባልዘገየን ዳግመኛ ሒደን ሸምተን በተመለስን ነበር፤

፲፩፡ ወይቤሎሙ እስራኤል አቡሆሙ ለእመሰ ከመዝ ውእቱ ነገር ፤

አባታቸው ያዕቆብም እንዲህ አላቸው፤ ነገሩ እንዲህስ ከሆነ፤

ንሥኡ እምፍሬ ምድር ወደዩ ውስተ አንሳሊክሙ ፤

በከነዓን የሚገኘውን ፤ በግብፅ የማይገኘውን የተክል ፍሬ በአ ቁማዳችሁ ይዛችሁ ፤

ወሰዱ ለብእሲ አምኃ ርጢነ ፤

ለዚያ ሰው እጅ መንሻ መድኃ ኒት የሚሆነውን ሽቱ ፤

ወመዓረ ወዕጣነ ፤

ማሩንም፤ ዕጣኑንም፤ ውሰዱ፤ መዓረ ባለው ሰንደቀ ወመን ደቀ ፤ ርጢነ ባለው ፤ ደቢሰ ወደባቢሰ ይላል ፤ ወዕጣነ ዕጣ ኑን ፤

ወማየ ልብን ፤

ልባንጃ የሚባለውንም የውሀ ሽቱ ውሰዱ ፤

ወጠርቤንቶሰ ወከርካዐ ፤

ጠርቤንቶስ የሚባል ሽቱ፤ ለው ዙን፤ ገውዙን፤ እጅ መንሻ ይዛ ችሁለት ሒዱ ፤

፲፪፡ ወርቀክሙሰ ንሥኡ ካዕበቶ ምስ ሌክሙ ወዘንተኒ ዘረከብክሙ በው ስተ አንሳሊክሙ ፤ ወዘነሥእክምዎ ፤

የምትሸምቱበትንም ወርቅ፤ ከፊ ተኛው እጥፍ አድርጋችሁ ፤ ያነንም ባቁማዳችሁ አግኝታችሁ ያመጣችሁትን ይዛችሁ ሒዱ ፤

በኢያእምሮ ኮነ ዮጊ ፤

ወይም እንጂ ባለማወቅ ተሳስቶ መጥቶ ይሆናል ፤ አንድም ወይም አገረ ገገርው ባለማወቅ አድርገውት ይሆናል ይላቸ ኋል ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፫፤ ወንሥእዎ ለእኁክሙ ምስሌክሙ ወተንሥኡ ወረዱ ኀበ ብእሲ ፤

ወንድማችሁን ከናንተ ጋራ ይዛችሁ ተነሥታችሁ ወደዚያ ሰው ሒዱ ፤ ከዚህስ ቢቀር ችጋር ይገድለው የለምን ብሎ ነው ፤

፲፬፤ ወአምላኪየ የሀብክሙ ሞገሰ በኀበ ውእቱ ብእሲ ፤

ፈጣሪዬም ባገረ ገዥው ዘንድ ባለሟልነትን ይስጣችሁ ፤

ወያግብእ ለክሙ ውእቱ ለእኁክሙ፤

ወንድማችሁ ስምዖንንም እንዲመልስላችሁ ያድርግላችሁ ፤

ወለብንያሚ ፤

ብንያምንም አይቶ ሳስቀረው ሳይል እንዲመልስላችሁ ያድርግላችሁ ፤

ወአንሰ ዳዕሙ በከመ ኃጣዕኩ ውሉደ ኃጣዕኩ ፤

እኔ ግን ዮሴፍንና ስምዖንን እንዳጣሁ፤ ብንያምንም አጣሁ፤ አንድም ምን ጊዜም ልጆቼን አላገኘሁም ምን አደርጋለሁ ? አላቸው ፤

፲፭፤ ወነሥኡ እሙንቱ ዕደው ውእተ አምኃ ፤

እነሱም ያዙ ያላቸውን እጅ መንሻውን ፤

ወርቆሙኒ ካዕበተ ነሥኡ ምስሌሆሙ ፤

ወርቁንም ዕጽፍ አድርገው ይዘው ፤

ወለብንያምኒ ነሥእዎ፤ ወተንሥኡ ወወረዱ ብሔረ ግብጽ ፤

ብንያምንም አስከትለው ፤ ተነሥተው ወደ ግብጽ ወረዱ ፤

ወበጽሑ ቅድሜሁ ለዮሴፍ ወሰገዱ ሎቱ ፤

ከዮሴፍም ፊት በደረሱ ጊዜ ሰገዱለት ፤

፲፮፤ ወርእዮ ዮሴፍ ለብንያም ምስሌሆሙ ፤ ይቤሎ ለመጋቢ ቤቱ ፤

ዮሴፍም ብንያምን ከወንድሞቹ ጋራ ባየው ጊዜ ፤ ሹሙን እንዲህ አለው ፤

አብአሙ ለእሉ ሰብእ ውስተ ቤት፤

እነዚህን ሰዎች ወደ ቤት አግብተህ ፤

ወጥባሕ ወአስተዳሉ ፤

በጉን ፍሪዳውን አርደህ መብሉን መጠጡን አዘጋጅ ፤

እስመ ምስሌየ ይመስሑ እሉ ዕደው፤

ለእሊህ ሰዎች በአዳራሽ እገኛላቸዋለሁና ፤

ወምስሌየ ይበልዑ መዓልተ ፤

ቀትር ሲሆን ከኔ ጋራ ይበላሉና ፤

፲፯፤ ወገብረ ውእቱ ብእሲ በከመ ይቤሎ ዮሴፍ ፤

ሹሙም ዮሴፍ እንዳዘዘው ፤



ወአብኦሙ ለእሙንቱ ዕደው ውስተ ቤተ ዮሴፍ ፤

እነዚያን ሰዎች ወደ ዮሴፍ እልፍኝ አስገባቸው ፤

፲፰፤ ወሶበ ርእዩ እሙንቱ ዕደው ከመ አብአሙ ውስተ ቤተ ዮሴፍ ፤

እነሱም ወደ ዮሴፍ እልፍኝ እንዳገባቸው ባዩ ጊዜ ፤

ይቤሉ በእንተ ዝንቱ ወርቅ ዘገብአ ውስተ አሕሳሊነ ዘቀዲሙ ፤ ይወስዱነ ከመ ይኩንኑነ ወይቅንዩነ ፤

ቀድሞ በአቁማዳችን ተመልሶ ስለ መጣው ወርቅ፤ አሥረው ገርፈው ሊገዙን ይሆናል ፤

ወይንሥኡነ እንስሳነ ፤

ከብቶቻችንንም ሊወስዱብን ይሆናል አሉ ፤

፲፱፤ ወቀርቡ ኀበ ውእቱ ብእሲ፤ ዘላዕለ ቤተ ዮሴፍ፤ ወተናገርዎ በኆኅተ ቤቱ ፤

በዮሴፍ ቤት አዛዥነት ወደ ተሾመው ሰው ቀርበው በደጃፉ ቆመው ተነጋገሩት ፤

፳፤ ወይቤልዎ ናስተበቍዓከ እግዚኦ፤

አቤቱ እንማልድሃለን ስማን አሉት ፤

ቀዲሙ ወረድነ ንሣየጥ እክለ ፤

ከዚህ ቀድሞ እህል ልንሸምት መጥተን ነበር ፤

፳፩፤ ወኮነ ሶበ በጻሕነ ለኃዲር ወፈታሕነ አኅሳሊነ ፤

ሸምተን ተመልሰን ከምናድርበት ቦታ በደረስን ጊዜ፤ አቁማዳችንን ብንፈታ ፤

ወረከብነ ወርቀ ውስተ አሕሳሊነ ዘዘዚአነ ፤

የሸመትንበትን ወርቅ በየራሳችን አቁማዳ ተቋጥሮ አገኘነ ፤

ወይእዜኒ ወርቀሰ አግባእነ ምስሌነ በመድሎቱ ፤

አሁንም ያንኑ ያገኘነውን ወርቅ በሚዛን መዝነን መለስን ፤

፳፪፤ ወካልዓኒ ወርቀ አምጻእነ በዘ ንሣየጥ እክለ ፤

ከዚህም ሌላ እህል የምንሸምትበትን ወርቅ ይዘን መጥተናል ፤

ወኢያእመርነ መኑ ወደዮ ለውእቱ ወርቅ ውስተ አኅሳሊነ ፤

ያንን ወርቅ ግን በአቁማዳችን ውስጥ አግብቶ ማን እንደቋጠረው አላወቅንም አሉት ፤

፳፫፤ ወይቤሎሙ ውእቱ ብእሲ ሐሰ ለክሙ ኢትፍርሁ ፤

ሹሙም ወርቅ ሰርቀው ወስደዋል ብለው ይጣሉናል ብላችሁ አትፍሩ ፤

www.ethiopianorthodox.org

አምላክክሙ ወአምላከ አበዊክሙ ወሀበክሙ መድፍነ በውስተ አኀሳ ሊክሙ ፤

የናንተም የአባቶቻችሁም ፈጣሪ፤ የተቀበረ ወርቅ በአቁማዳችሁ ሰጥቷችሁ ይሆናል ፤ አንድም ፈጣሪያችሁ የተቀበረውን ወርቅ ቢገልጽላችሁ እኔን ምን ትሉኛላችሁ ?

ወርቀክሙሰ ሠሚርየ ነሣእኩ ፤

ያመጣችሁትንስ ወርቅ ወድጄ (መዝኜ) ተቀብያለሁ ብሎ ፤

ወአውፅአ ለስምዖንሂ ኀቤሆሙ ፤

ስምዖንንም ደስ ይበላቸው ብሎ እነሱ ወዳሉበት አውጥቶ አገናኘው ፤

፳፬፡ ወአምጽአ ማየ ለእገሪሆሙ ፤

ለእግራቸውም ውሃ አመጣ ፤

ወወሀበ እክለ ለአዕዱጊሆሙ ፤

ለአህዮቻቸውም ገፈራውን ሰጠ፤

፳፭፡ ወአስተዳለዉ አምኃሆሙ እስከ ይበውእ ዮሴፍ መዓልተ ፤

ዮሴፍ በቀትር እስኪመለስ ድረስ የሚያቀርቡትን እጅ መንሻ አዘጋጁ ፤

እስመ ሰምዑ ከመ በህየ ይመስሕ፤

ለምሳ በአዳራሽ እንዲገኝ ሰም ተዋልና ፤

፳፮፡ ወሶበ መጽአ ዮሴፍ ውስተ ቤቱ ፤

ዮሴፍ ከፈርዖን ቤት ተመልሶ ወደ ቤቱ በመጣ ጊዜ ፤

አምጽኡ ሎቱ አምኃሁ ዘውስተ እደዊሆሙ ውስተ ቤት ፤

በእጃቸው ያለውን እጅ መንሻ ከእልፍኝ ሳለ አምጥተው አበረከቱት ፤

ወሰገዱ ሎቱ በገጾሙ ውስተ ምድር፤

በግምባራቸው ወድቀው ሰገዱለት ፤

፳፯፡ ወተስእሎሙ ዜናሆሙ፤

ታሪካቸውን ጠየቃቸው ፤ አንድም ወሬ ጠየቃቸው ፤

ወይቤሎሙ ዳኅንኑ ገሩ አቡክሙ አረጋዊ ዘትቤሉኒ ፤

ሽማግሌ አባት አለን ያላችሁት ያ ሽማግሌ ደኅና ነውን ?

ዓዲሁ ሕያውኑ ውእቱ ፤

ገና ከጉልበት ነውን? አላቸው ፤

፳፰፡ ወይቤልዎ ዳኅን ገብርከ አቡነ አረጋዊ ፤

ባሪያህ ሽማግሌው አባታችን አዎን ደኅና ነው ፤

ወዓዲሁ ሕያው ውእቱ ፤

ገና ከጉልበት ነው አሉት ፤

ወይቤ ዮሴፍ ቡሩክ ውእቱ ብእሲሁ ለእግዚአብሔር ፤

ዮሴፍም እግዚአብሔር ያከበረው ደግ ፍጥረት ነው አለ ፤



ወአትሐቱ ርእሶሙ ወሰገዱ ሎቱ ፤

አባታቸውን ቢያመሰግንላቸው ደስ ብሏቸው ራሳቸውን ዝቅ ዝቅ አድርገው ሰገዱለት ፤

፳፱፡ ወሶበ ነጸረ ዮሴፍ ወርእዮ ለብንያም እኁሁ ወልደ እሙ ፤

ዮሴፍም የናቱን ልጅ ወንድሙ ብንያምን በአየው ጊዜ ፤

ወይቤሎሙ ዝኑ ውእቱ እኁክሙ ዘይንዕስ ዘትቤሉኒ ናመጽአ ኀቤከ፤

ወደ አንተ እናመጣዋለን ያላችሁኝ ታናሽ ወንድማችሁ ይህ ነውን ? አላቸው ፤

ወይቤልዎ እወ ፤

አዎን እሱ ነው አሉት ፤

ወይቤሎ ዮሴፍ እግዚአብሔር ይሣሃልከ ወልድየ ፤

ዮሴፍም ልጄ እግዚአብሔር ይቅር ይበልህ አለው ፤ ከወንድሞችህ ምቀኝነት ይጠብቅህ ሲለው ነው ፤

፴፡ ወተሀውከ ዮሴፍ አማዑቲሁ ፤ ወፈቀደ ይብኪ፤ ወቦአ ውስተ ቤቱ ወበከየ ፤

ዮሴፍም እንባ ፈልቶበት ልቡናው ቢታወክ፤ ለብቻው ሊያለቅስ ወደ እልፍኝ ገብቶ አለቀሰ፤

፴፩፡ ወተሐጽበ ገጾ ፤ ወወፅአ ተዓገሠ ፤

አልቅሶ ፊቱን በዕንባው ታጠበ፤ አንድም ልቅሶውን ትቶ እንባውን በውሃ ታጥቦ ወጣ ፤

ወይቤ አቅርቡ ለነ ኅብስተ ፤

ወደ አዳራሽም ገብቶ ግብር አግቡልን አለ ፤

፴፪፡ ወአቅረቡ ሎሙ እንተ ባሕቲቶሙ ፤

ለወንድሞቹ ለብቻቸው አቀረቡላቸው ፤

ወሎቱኒ እንተ ባሕቲቱ ፤

ለሱም ለብቻው አቀረቡለት ፤

ወለሰብአ ግብጽ እለ ይመስሑ ምስሌሁ እንተ ባሕቲቶሙ ፤

ከሱ ግብርም ለሚበሉ ለግብጽ ሰዎችም ለብቻቸው አቀረቡላቸው ፤

እስመ ኢይክሉ ሰብአ ግብጽ በሊዓ እክል ምስለ ዕብራውያን ፤

የግብጽ ሰዎች ከዕብራውያን ጋራ እኽል መብላት አይችሉምና፤

እስመ ያስቌርርዎሙ ሰብአ ግብጽ ለኵሎሙ ኖሎት ፤

የግብጽ ሰዎች ዘላኖችን ሁሉ የሚጸየፏቸው ስለሆነ ፤

፴፫፡ ወነበረ ቅድሜሆሙ በኵሮሙ ዘይልሕቅ ፤

ከሁሉ የሚበልጠው በኵራቸው ሮቤል መጀመሪያ ተቀመጠ ፤

ወዘይንዕስኒ በበናዕሱ ፤

በበመዓርጉ ሲል ነው ፤ ሐተታ ትንሹም እንደ ትንሽነቱ ተቀ

www.ethiopianorthodox.org

መጠ ፤ ታላቁም እንደ ታላቅ ነቱ፡ ቢቀመጡ ፤ እንደ ትውል ዳችሁ ተቀመጡ ብሏቸዋል ፤ በፊት ሮቤል ፤ ቀጥሎ ስምዖን፤ ቀጥሎ ሌዊ ፤ ቀጥሎ ይሁዳ ፤ እንዲህ እያሉ ቢቀመጡ ፤ ብንያም ዙሮ በዮሴፍ አጠገብ ተቀምጧል ፤

ወነበሩ ፩ዱ ፩ዱ ምስለ ካልኡ ፤

አንዱም አንዱም ከአንዱ ጋራ በየትውልዳቸው ተቀመጡ፤

፴፬፡ ወነሥኡ ክፍሎሙ በኀቤሁ ዘዘዚአሆሙ፤

በእሱ ፊት እየራሳቸው ፈንታ ፈንታቸውን ተቀበሉ ፤

ወዓብየ ክፍሉ ለብንያም እምክፍ ሎሙ ኃምስተ እደ ፤

ከነዚያ ፈንታ የብንያም ፈንታ አምስት እጅ በለጠ ፤ ሐተታ ደራርቦ አስጥሎለታል ፤ ስለ ምን ቢሉ ፤ እንግዳ ነውና ፤ አንድም በእሱ ይቀኑበት እንደ ሆነ ልይ ብሎ ፤

ወበልዑ ወሰትዩ ወሰክሩ ምስሌሁ ፤

ከእሱም ጋራ አብዝተው በሉ ጠጡ ፡፡

## ምዕራፍ ፵ወ፬

፩፡ ወአዘዞ ዮሴፍ ለመጋቢሁ ወይ ቤሎ ፤

ዮሴፍም ሹሙን እንዲህ ብሎ አዘዘው ፤

ምላዕ ሎሙ አኅሳሊሆሙ ለእሉ ዕደው መጠነ ይክሉ ጸዊረ ፤

ለእነዚህ ሰዎች የሚችሉትን ያህል እህል በአቁማዳቸው ምላ ላቸው ፤ (ሐተታ) ወርቁ ከተ መለሰ ያንሳቸዋል ብሎ የቻሉ ትን ያህል አለ ፤

ወደይ ለለ፩ዱ ወርቆሙ ውስተ አኅ ሣሊሆሙ ፤

ወርቃቸውንም ያንዱንም ያን ዱን በየአቁማዳቸው አድርግላ ቸው ፤

፪፡ ወኩሬየ ዘብሩር ደይ ውስተ ኃስሉ ለዘይንዕስ ፤ ወሤጠ እክሉሂ ደይ ፤

እኔ የምጠጣበትን የብር ጽዋና የእህሉን መሸመቻ ወርቅ በታ ናሹ ወንድማቸው አቁማዳ ቋጥ ረህ ስጠው ፤ ኩሬየ ባለው ገይበ ዘብሩር ይላል ፤

ወገብረ በከመ አዘዞ ዮሴፍ ፤

ሹሙም ዮሴፍ እንዳዘዘው አደ ረገ ፤



፫፡ ወሶበ ጎሐ ጽባሕ ፈነዎሙ ለእ ሙንቱ ዕደው ምስለ እንስሳሆሙ ፤

በነጋም ጊዜ እነዚህን ሰዎች ከነንዛቸው ሸኝቶ ሰደዳቸው ፤

፬፡ ወሶበ ወፅኡ እሙንቱ ዕደው ዘእ ንበለ ይርኃቁ እምሀገር ነዋኃ ፤ ይቤሎ ዮሴፍ ለመጋቢ ቤቱ ፤

እነሱም ወጥተው ከሔዱ በኋላ፤ ከከተማው እጅግ ሳይርቁ ዮሴፍ ሹሙን እንዲህ አለው ፤

ተንሥእ ዴግኖሙ ወትልዎሙ ለእሉ ዕደው ወአኀዞሙ ፤

ሒድ ተከትለህ እኒህን ሰዎች ያዛቸው ፤

ወበሎሙ እሮ ትፈድዩኒ እኪተ ህየ ንተ ሠናይ ፤

ስለ በጎ ነገር ፈንታ እንዴት ክፉ ነገር ትመልሱልኛላችሁ ?

፭፡ ለምንት ትሰርቁኒ ገይበ ብሩር ዘቦቱ ይሰቲ እግዚእየ ፤

ጌታዬ የሚጠጣበትን የብር ጽዋ ለምን ሰረቃችሁኝ ? ይሰቲ ባለው ያቃሪ ይላል ፤ (ሐተታ) እኩየ ገበርክሙ በሎሙ ፤ ክፉ ነገር አደረጋችሁ በላቸው አለው፤

፮፡ ወሐረ ወረከቦሙ ወይቤሎሙ ለም ንት ትገብሩ ከመዝ ፤

ተከትሎ ሒዶ ባገኛቸው ጊዜ፤ ለምን እንዲህ ያለ ሥራ ሠራ ችሁ ? አላቸው ፤

ወትፈድዩኒ እኪተ ህየንተ ሠናይት ዘገበርኩ ለክሙ ፤

በጎ ስላደረግሁላችሁ ፈንታ ክፉ ነገር ለምን ትመልሱልኛላችሁ?

ወትሰርቁኒ ገይበ ብሩር ዘእግዚእየ፤

የጌታዬን የብር ጽዋ ለምን ሰረቃችሁኝ ፤

፯፡ ወይቤልዎ ለምንት ትብል ከመዝ እግዚእነ ፤

ጌታችን እንዲህ ያለ ነገር ለምን ትናገራለህ ?

ሐሰ ሎሙ ለአግብርቲከ ኢይገብርዎ ለዝ ነገር ፤

ይህ የተናገርኸው ነገር ለኛ ለባሮችህ አግባባችን አይደለም፤ እንዲህ ያለውን ነገር አናደር ገውም ፤

፰፡ ወርቀ ዘረከብነ በውስተ አኅሳ ሊነ አግባዕነ ኀቤከ እምድረ ከነዓን፤

ስንኳን ከዚህ ጽዋ ሰርቀን ልን ወስድ ፤ ከአቅማዳችን ያገኘነ ውን ወርቅ ከከነዓን መልሰን አላመጣንም ?

ወእፎኬ ንሰርቅ እምቤትከ ወርቀ፤ አው ብሩረ ፤

ከአንተ ቤት ወርቅስ ብርስ እንዴት እንሰርቃለን ?

፱፡ ይእዜኒ በኀበ ዘረከብከ ኩሬከ እምአግብርቲከ ለይሙት ፤

አሁንም ከእኛ ከባሮችህ የወርቅ ጽዋ የተገኘበት ሰው ይሙት ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወንሕነኒ ንኩን አግብርተ ለእግዚእከ ።

እኛም ለጌታህ ባሮች ሁነን እን ገዛ አሉት ፤

፲፤ ወይቤሎሙ ይእዜኒ ለይኩን በከመ ትቤሉኒ ዘነቤሁ ተረክበ ውእቱ ገይብ ይኩነኒ ገብረ ።

መሞትማ ለምና አሁን እናንተ እንደ ተናገራችሁት ይህ ጽዋ የተገኘበት ሰው ባሪያ ሆኖ ይገ ዛል እንጂ ፤

ወአንትሙሰ አንጻሕክሙ ርእሰክሙ።

እናንተ ግን ራሳችሁን አነጻ ችሁ ማለት ፤ ያልተገኘበት ሰው ነፃ ነው አላቸው ፤

፲፩፤ ወአውረዱ አኅሳሊሆሙ ውስተ ምድር ፍጡነ ወአኀዙ ይፍትሑ ።

አቅማዳቸውን ፈጥነው ወደ መሬት አውርደው ይፈቱ ጀመር ፤

፲፪፡ ወኃሠሠ እምነ ዘይልሕቅ እስከ ዘይንዕስ ።

ከወዳጅ ይነሡ ከጠላት ይደ ርሱ እንዲሉ ። እንዳይታወቅ በት ከሮቤል ጀምሮ እስከ ብንያም ድረስ በረበረ ፤

ወረከበ ውእቱ ገይበ ውስተ ኀሰለ ብንያም ።

የነንም የብር ጽዋ ከብንያም አቅማዳ ውስጥ አገኘው ፤

፲፫፡ ወሠጠጡ አልባሲሆሙ ።

እነሱም ደንግጠው ተናደው ልብ ሳቸውን ቀደዱ ። አሰለቡ ፤

ወጸዓኑ አኅሳሊሆሙ ዲበ አዕዱጊሆሙ ወገብኡ ውስተ ሀገር ።

አቋማዳቸውን በአህዮቻቸው ላይ ጭነው ወደ ከተማው ተመ ለሱ ፤

፲፬፤ ወቦኡ ኀበ ቤተ ዮሴፍ እንዘ ሀሎ ውእቱ ሀየ።

እሱ ከዚያ ሳለ ገና ሳይወጣ ከዮሴፍ ቤት ገብተው ፤

ወወድቁ ውስተ ምድር በገጾሙ ።

በግምባራቸው ፍግም ብለው ወደቁ ፤

፲፭፡ ወይቤሎሙ ዮሴፍ ምንትኑ ዝንቱ ዘገበርክሙ ።

ዮሴፍም ይህ ያደረጋችሁት ነገር ምንድር ነው ? አላቸው ፤

፲፮፡ ወይቤ ይሁዳ ምንተ ናወሥእ ለእግዚእነ ።

ይሁዳም ለጌታችን ምን እን መልስለታለን ?

ወምንተ ንብል ወበምንት ንነጽሕ ዘእግዚአብሔር አግብአ ለዓመፃነ ላዕሌነ ።

ምንስ እንላለን? እግዚአብሔር ፍዳችንን በእኛ ላይ ካመጣው በምን እንድናለን ?



ወባሕቱ ናሁ ኮነ አግብርቲሁ ለእግ ዚእነ ንሕነኒ ወዘክቱኒ ዘተረክበ በኀ ቤሁ ገይብ ።

የብር ጽዋ የተገኘበት እሱም እኛም የጌታችን ባሮች ሁነን እንገዛለን እንጂ አለው ፤

፲፯፡ ወይቤ ዮሴፍ ሐሰ ሊተ እስከ እገብሮ ለዝንቱ ነገር ።

ዮሴፍም እንዲህ አለ ። ይህን ነገር እስከ አደርገው ድረስ ማለት ባንድ በእሱ ምክንያት እናንተን ሁሉ ባሮቼ አድርጌ እስከ መግዛት ደርሼ እንዲህ ያለ ግፍ አልሠራም ፤

አላ ውእቱ ብእሲ ዘበላዕሌሁ ተረ ክበ ኩራይ ውእቱ ይኩነኒ ገብረ ።

የምጠጣበት ጽዋ የተገኘበት እሱ ብቻ ባሪያ ሁኖ ይገዛልኝ እንጂ፤

ወአንትሙሰ ሑሩ ወግብኡ ኀበ አቡክሙ በዳኅን ።

እናንተስ ሒዱ ወደ አባታችሁ በደኅና ያግባችሁ አላቸው ፤

፲፰፡ ወቀርበ ይሁዳ ኀቤሁ ወይቤ ብቍዓኒ እግዚእ ።

ይሁዳም ወደ እሱ ቀርቦ ጌታዬ በጄ በለኝ አለው ፤

አብሐኒ እንብብ ቅድሜከ እግዚእየ።

ጌታዬ በፊትህ እናገር ዘንድ ፍቀድልኝ ፤

ኢትትመዐዐ ለገብርከ እስመ አንተ እምድኅረ ፈርዖን እግዚእ ።

እምታሕተ ፈርዖን ሲል ነው ፤ ከፈርዖን በታች ጌታ አንተ ነህና እኔን ባሪያህን ደፈረኝ ብለህ አትቆጣኝ ፤

፲፱፡ አንተ ተስእልከሙ ለአግብር ቲከ ፣ ወትቤሎሙ ቦኑ ዘብክሙ አብ አው እኁ ።

አንተው ራስህ ባሮችህን በአ ገራችሁ አባት ወይስ ወንድም አላችሁን ብለህ ጠየቅኸን ፤

፳፡ ወንቤለከ እግዚእ ብነ አብ አረ ጋዊ ወቦ ወልድ ንኡስ ዘበርስዓኑ ወለዶ ።

እኛም ጌታችን ሆይ አዎን ሽማግሌ አባት አለን ፤ ከአረጀ በኋላ የወለደውም ታናሽ ወን ድም አለን አልንህ ፤

ወእኁሁሰ ሎቱ ሞተ ወውእቱ ባሕ ቲቱ ተርፈ ለእሙ ።

አንድ ወንድም ነበረው ሙቶ ለእናቱ እሱ ብቻ ቀርቷል ፤

ወያፈቅሮ አቡሁ ።

አባቱም ይወደዋል ብለን ነገ ርንህ ፤

፳፩፡ ወትቤሎሙ ለአግብርቲከ አም ጽእዎ ኀቤየ ወአዓቅቦ ።

አንተም እኛን ባሮችህን ። ወደ እኔ አምጡት ተንከባክቤ አሳ ድገዋለሁ አልኸን ፤

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

፳፪፤ ወንቤለከ ኢይክል ነዲገ አቡሁ ውእቱ ሕፃን ፣

እኛም ያ ልጅ ከአባቱ መለየት አይችልም ፡

ወእመሰ ኃደገ ይመውት ፣

የተለየው እንደሆነ ግን አባቱ በኀዘን ይሞታል ብለን ነግረ ንህ ነበር ፡

፳፫፤ ወአንተሰ ባሕቱ ትቤሎሙ ለአግብርቲከ ለእመ ኢየምጻእክምዎ ለእኁክሙ ዘይንዕስ ኢትሬእዩ ገጽየ ዳግመ ፣

አንተ ግን እኛ ባሮችህን ታናሽ ወንድማችሁን ካላመጣችሁት ዳግመኛ ፊቴን አታዩትም አልኸን ፡

፳፬፤ ወኮነ ሶበ ዓረግነ ኀበ አቡነ ገብርከ ዜነውናሁ ዘንተ ዘትቤለነ እግዚኦ ፣

ኮነ ያለውን ዜነውናሁ ብሎ አመጣው ፤ እኛም ወደ አባታችን ተመልሰን በሔድን ጊዜ ይኸን የነገርኸንን ሁሉ ነገር ነው ፡

፳፭፤ ወይቤለነ አቡነ ሑሩ ካዕበ ተሣየጡ ለነ ኅዳጠ እክለ ፣

አባታችንም ዳግመኛ ሒዳችሁ ጥቂት እህል ሸምታችሁ አምጡ አለን ፡

፳፮፤ ወንቤሎ ንሕነሰ ኢንክል ሐዊረ እመ እኁነ ዘይንዕስ ኢመጽአ ምስሌነ ፣

እኛም ታናሽ ወንድማችን ከኛ ጋራ ካልሔደ መሔድ አይቻለንም ፡

እስመ ኢንክል ርእየ ገጹ ለውእቱ ብእሲ፣ እመ ኢሀሎ እኁነ ዘይንዕስ ምስሌነ ፣

ታናሽ ወንድማችንን ይዘን ካልሔድን የዚያን ሰው ፊት ማየት አይቻለንምና አልነው ፡

፳፯፤ ወይቤለነ ገብርከ አቡነ ተአምሩ ለሊክሙ ከመ ፪ተ ወለደት ሊተ ይእቲ ብእሲት ፣

ባሪያኸ አባታችንም እንዲህ አለ ፣ ራኄል ሁለት ልጆች እንደ ወለደችልኝ እናንተ ታውቃላችሁ ፡

፳፰፤ ወፅዱሰ ወፅአ እምኀቤየ ወትቤሉኒ አርዌ በልዖ ፣

አንዱም ከኔ ተልኮ ወደ እናንተ በመጣ ጊዜ አውሬ በላው አላችሁኝ ፡

ወኢርኢክዎ እንከ ዳግመ እስከ ይእዜ ፣

ሁለተኛ ፊቱን ሳላይ ቀረሁ ፡

፳፱፤ ወለእመ ነሣእክምዎ ለዝኒ እምቅድመ ገጽየ ፣

ይህንንም ከኔ ለይታችሁ ብት ወስዱት ፡



ወእምከመ ደወየ በፍኖት ፣

በጎዳና ታሞ ቢሞት ፡

ወታወርድዎ ለርስዓንየ በኀዘን ውስተ መቃብር ፣

በኀዘን ያረጀ ሰውነቴን በሞት ወደ መቃብር ታወርዱኛላችሁ ብሎን ነበር ፡

፴፤ ወይእዜኒ ለእመ ሖርነ ኀበ ገብርከ አቡነ ወኢሀሎ ምስሌነ ዝንቱ ሕፃን ይመውት ፣

አሁንም ወደ ባሪያህ ወደ አባታችን ይህን ልጅ ሳንይዝ ብን ሔድ ፣ አባታችን በኀዘን ተቀጥቅጦ ይሞታል ፡

፴፩፤ ወናወርዶ ውስተ መቃብር በፃዕር በርስዓኒሁ ለገብርከ አቡነ ፣

የባሪያህ የአባታችን ያረጀ ሰውነቱን ፣ በፃዕር ወደ መቃብር እናወርደዋለን ፡

፴፪፤ እስመ ገብርከ ተሐበዮ ለዝንቱ ሕፃን እምአቡሁ ፣

እኔ ባሪያህ ይህን ልጅ ዋስ ሆኜ ከአባቱ አምጥቸዋለሁና ፡

ወእቤሎ ለእመ ኢየግባእክዎ ኀቤከ ወኢያቀምክዎ ቅድሜከ ፣

ወደ አንተ መልሼ አምጥቼ በፊትህ ያላቆምኹት እንደሆነ፤

ጊጉየ ለእኩን ላዕሌከ አባ በኵሉ መዋዕለ ሕይወትየ ፣

አባቴ ባለ ዘመኔ ሁሉ በአ ንተ ዘንድ ርጉም ልሁን ብዬ አምጥቼዋለሁ ፡

፴፫፤ ወይእዜኒ እከውነከ ገብረ ህየንተ ዝ ሕፃን ፣

አሁንም ስለዚህ ልጅ ፈንታ እኔ ባሪያህ ሆኜ ልገዛ ፣ ከሱም እኔ እሻላለሁ ፣ የቆመውን እቆ ርጣለሁ ፣ የወደቀውን እፈል ጣለሁ ፡

ወእኑበር ኀቤከ እግዚኦ ፣

አቤቱ ለአንተ ተገዢ ሆኜ እኖ ራለሁ ፡

ወሕፃንሰ ይሑር ምስለ አኀዊሁ ፣

ልጁ ግን ከወንድሞቹ ጋራ ይሂድ ፡

፴፬፤ እስመ ኢይክል አነ ሐዊረ ኀበ አቡነ እመ ኢሀሎ ዝንቱ ሕፃን ኀቤነ፣

ይህ ልጅ ከኛ ጋራ ካልሄደ እኔ ወደ አባታችን መሄድ አልችል ምና ፡

ከመ ኢይርአይ እኪተ እንተ ትረክቦ ለአቡነ ፣

አባታችንን የምታገኘውን መከራ እንዳላይ በኀዘን ተቀጥቅጦ ሲሞት አላይም ማለቱ ነው ።

## ምዕራፍ ፵ወ፭

፩፤ ወሶበ ስእነ ዮሴፍ ተዓግሦ እንዘ ኵሉ ይቀውሙ ቅድሜሁ ፣

ሰዎቹ ሁሉ በፊቱ ቆመው ሳለ፣ ዮሴፍ ዕንባውን መታገሥ በተ ሳነው ጊዜ ፡

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ይቤ ዮሴፍ ያስስሉ ኵሎ ሰብአ እምቅድሜሁ ፤

ዮሴፍ ሰው ሁሉ ከፊቴ ይመለስ አለ ፤

ወአውፅኡ ኵሎ ሰብአ እምቅድሜሁ ፤

ሰውን ሁሉ ከፊቱ አስወጡ፤

ወአልቦ ዘተርፈ ህየ ኀበ ዮሴፍ ፤ ሶበ ይትአመር ምስለ አኃዊሁ ፤

ዮሴፍ ከወንድሞቹ ጋር ሲተዋወቅ ከዚያ የቀረ ሰው የለም ፤ (ሐተታ) በምን አውቀውታል ቢሉ ፤ ወአፍለጠሙ በነፍስቱ ይላል ፤ በግዙርነቱም አሳወቃቸው፤ ግብጻውያን ቈላፋን ናቸውና ፤ አንድም ደብድበውት ነበርና በእትራቱ ፤ አንድም ቀድሞ የሚጨዋወቱባት ቋንቋ ነበረችና እሷን ነግሯቸዋል ፤ አንድም እንደ ማርያም ሳመችኝ ያለ ነበረበትና ያን አሳይቷቸው በዚህ አውቀውታል ፤ ይኸውም ጌታ በተነሣ በ፰ኛው ቀን ለሐዋርያት ተገልጦ በእደ ቶማስ ለመዳሰሱ ምሳሌ ነው፤

፪፡ ወጸርሐ በዐቢይ ቃል ወበከየ ፤

ቃሉን አሰምቶ ጮሆ አለቀሰ ፤

ወሰምዑ ኵሉ ሰብአ ግብጽ ፤

የግብጽ ሰዎችም ሁሉ ጩኸቱን ሰሙ ፤

ወተሰምዐ በቤተ ፈርዖንሂ ፤

በፈርዖንም ቤት ጩኸቱ ተሰማ፤

፫፡ ወይቤሎሙ አነ ውእቱ ዮሴፍ እኁክሙ ፤

ዮሴፍም እኔ ወንድማችሁ ነኝ አላቸው ፤

ሕያውኑ ዓዲሁ ውእቱ አቡየ ፤

አባቴ ገና ከገልበት ነውን ?

ወኢክህሉ አውሥኦቶ እስመ ደንገፁ ፤

ደንግጠዋልና መመለስ አልተቻላቸውም ፤

፬፡ ወይቤሎሙ ዮሴፍ ለአኃዊሁ ቅረቡ ኀቤየ ፤ ወቀርቡ ኀቤሁ ፤

ዮሴፍ ወንድሞቹን ወደ እኔ ቅረቡ አላቸው፤ ወደ እርሱም ቀረቡ ፤

ወይቤሎሙ አነ ውእቱ እኁክሙ ዮሴፍ ዘሤጥክሙኒ ኀበ ብሔረ ግብጽ ፤

እኔ ወደ ግብጽ የሸጣችሁኝ ወንድማችሁ ዮሴፍ ነኝ አላቸው ፤ ግብረ ሐዋ. ምዕ. ፯ ቁ. ፲፫ ፤

፭፡ ወይእዜኒ ኢትፍርሑ እስመ ሤጥክሙኒ ዝየ ፤

አሁንም ወደ ግብጽ ስለ ሸጣችሁኝ አትፍሩ ፤

እስመ ለሕይወት ፈነወኒ እግዚአብሔር በቅድሜክሙ ፤

እግዚአብሔር ከእናንተ አስቀድሞ ለሕይወት ሰዶኛልና ፤



አለ ፤ እናንተ ለክፋት አድርጋችሁ በግፍ ብትሸጡኝ ፤ እግዚአብሔር ለበጎ አድርጎኛልና፤

፮፡ እስመ ናሁ ፪ቱ ዓመት ዘረኃብ ዘኃለፈ ላዕለ ምድር ፤

በምድር ላይ ከታዘዘው ዘመነ ረኃብ እነሆ አሁን ሁለት ዓመት አልፎ ፤

ዓዲ ሀሎ ፭ቱ ዓመት ፤

አምስቱ ዓመት ገና ቀርቷልና፤

ወአልቦ ዘየሐርስ ወዘይዘርዕ ፤

የሚያርስም ፤ የሚዘራም የለምና ፤

፯፡ ወፈነወኒ እግዚአብሔር ቅድሜክሙ ትሕየዉ ወትትርፉ ዲበ ምድር ከመ እሴሲክሙ ፤

በረኃብ ከመሞት ድናችሁ በዚህ ዓለም ትኖሩ ዘንድ ልመግባችሁ እግዚአብሔር አስቀድሞ ሰዶኛልና አይዟችሁ አትፍሩ ፤

፰፡ ወይእዜኒ አኮ አንትሙ ዘፈኖክሙኒ ፤ ዳእሙ እግዚአብሔር ፈነወኒ ፤

አሁንም እግዚአብሔር ነው እንጂ እናንተ የሰደዳችሁኝ አይደለም ፤

ወረሰየኒ ወልዶ ለፈርዖን ፤

ይኸውም ሊታወቅ የፈርዖን ባለሟል አድርጎኛል ፤

ወእግዚአ ለኵሉ ቤቱ ፤

ለቤቱ ሁሉ ጌታ አድርጎኛል ፤

ወመልአከ ለኵሉ ግብጽ ፤

ለግብጽ ሁሉ ገገር ቢትወደድ አድርጎኛል ፤

፱፡ ወይእዜኒ ሑሩ ንግርዎ ፍጡነ ለአቡየ ፤

አሁንም ፈጥናችሁ ሔዳችሁ ለአባቴ ንገሩት ፤

ወበልዎ ከመዝ ይቤ ወልድከ ዮሴፍ፤

ልጅህ ዮሴፍ እንዲህ ብሏል ፤

እግዚአብሔር ረሰየኒ እግዚአ ለኵሉ ብሔረ ግብጽ ፤

እግዚአብሔር ለግብጽ ሁሉ ገዥ ጌታ አድርጎኛልና ፤

፲፡ ወረድአ ፤ ፍጡነአ ፤ ወኢትንበርአ ፤ ህየአ ፤

ወደ ግብጽ ና እንጂ በከነዓን አትቀመጥ ፤

ወተኃድርአ ውስተ ምድረ ጌሴምአ፤ ዘዓረብአ ፤

በምዕራብ በኩል ባለ በጌሴም አውራጃ ትኖራለህ ፤

ወትሄሉአ ፤ ቅሩብየአ ፤ አንተአ ፤ ወደቂቅከአ ፤ ወአባግዒከአ ፤ ወአልሕምቲከአ ፤ ወኵሉ ዘብከአ ፤

አንተም ልጆችህም ፤ በጎችህም ፤ ላሞችህም ፤ የአንተ ገንዘብ ሁሉ በኔ አቅራቢያ ትኖራላችሁ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፩፡ ወእሴስየከአ ፣ በሀየአ ፣

በጌሴም ተቀምጠህ እመግብሃ ለሀ፡ ፤

እስመ ዓዲአ ፣ ሀሎአ ፣ ፭፡ቱአ ዓመ ትአ ፣ ዘረኃብአ ፣

አምስቱ ዓመት ዘመነ ረኃብ ገና አላለፈምና ፤

ከመ ኢትሙ፡ትአ፣ አንተአ፣ ወኵሉ ጥሪትከአ ፣

አንተም ልጆችህም በረኃብ እን ዳታልቁ ፤

፲፪፡ ወናሁ ትሬእዩ በአዕይንቲክሙ፣

እነሆ በዓይናችሁ ታያላችሁ ፤

ወብንያምኒ እኁየ ርእየ በአዕይንቲሁ ከመ ለልየ ተናገርኩክሙ በአፉየ ፣

ወንድሜ ብንያምም እኔ በቃሌ እንደ ተነጋገርኋችሁ በዓይኑ አይቷል ፤

፲፫፡ ወዜንውዎ ለአቡየ ኵሎ ክብ ርየ ዘበብሔረ ግብጽ ፤ ወኵሎ ዘር ኢክሙ በአዕይንቲክሙ ፣

በግብጽ ያለ ክብሬን ጌትነቴን በዓይናችሁ ያያችሁትንም ሁሉ ለአባቴ ንገሩት ፤

ወአፍጥኑ አምጽኡቶ ለአቡየ ዝየ ፣

አባቴንም ፈጥናችሁ ወደዚህ አምጡልኝ ብሏል ብላችሁ ንገ ሩት ፤

፲፬፡ ወሐቀፎ ክሣዶ ለብንያም እኁሁ ወበከየ ላዕሌሁ ፣

የወንድሙ የብንያምን አንገት አቅፎ ይዞ አለቀሰ ፤

ወብንያምኒ በከየ ላዕለ ክሣዱ ፣

ብንያምም የዮሴፍን አንገት አቅፎ ይዞ አለቀሰ ፤

፲፭፡ ወሰዓሞሙ ለኵሎሙ ወበከየ ላዕሌሆሙ ፣

ሁሉንም እያለቀሰ ሳማቸው ፤

ወእምድኅረዝ ተናገርዎ አኃዊሁ ለዮ ሴፍ ፣

ከዚህ በኋላ ወንድሞቹ ዮሴፍን ተናገሩት ፤ ሐተታ አፍረው ፈርተው ነበርና ኃፍረታቸውን ቢገልጥላቸው ተጨዋወቱት ፤

፲፮፡ ወተሰምዐ ነገሩ በቤተ ፈርዖን፣

ነገሩም ከፈርዖን ቤት ድርሶ ተሰማ ፤

ወይቤልዎ አኃዊሁ ለዮሴፍ መጽኡ፣

ፈርዖን ምንድር ነው ? ብሎ ቢጠይቅ፣ የዮሴፍ ወንድሞቹ መጥተው ነው ብለው ነገሩት ፤

ወተፈሥሐ ፈርዖን ወኵሉ ሰብኡ ፣

ፈርዖንም ቤተሰቦቹም ሁሉ ደስ አላቸው ፤ (ሐተታ) ስለ ምን ቢሉ ? ኩብላይ ባሪያ አስ ልጥኖብን ይሉት ነበርና የባለ ተስፋ የአብርሃም ልጅ መሆኑ ቢገለጥ ፤ አንድም ከአንድ



ከዮሴፍ ይህን ያህል ጥበብ ያገ ኘሁ ከነዚህማ ሁሉ ምን ያህል ጥበብ አገኝ ይሆን ? ብሎ ፤

፲፯፡ ወይቤሎ ፈርዖን ለዮሴፍ ፣

ፈርዖንም ዮሴፍን እንዲህ አለው፤

በሎሙ ለአኃዊከ ምልኡ ንዋያቲክሙ ወሑሩ ብሔረ ከነዓን ፣

ወንድሞችህን ገንዘባችሁን ይዛ ችሁ ወደ ከነዓን ሒዱችሁ ፤

፲፰፡ ወንሥእዎ ለአቡክሙ ወለኵሉ ንዋይክሙ ወንዑ ኀቤየ ፣

አባታችሁን ገንዘባችሁን ሁሉ ይዛችሁ ወደኔ ኑ ፤

ወእሁበክሙ እምኵሉ በረከተ ግብፅ፣

በግብፅ ከተገኘው እህል ሁሉ እሰጣችኋለሁ ፤

ወትበልዑ አንጕዓ ለምድር ፣

ፍሬሃ ለምድር ሲል ነው ፤ የምድርን ፍሬዋን ትመገባላችሁ በላቸው አለው ፤

፲፱፡ ወአንተሰ አዝዞሙ ከመዝ ለአ ኃዊከ ፣

አንተም ወንድሞችህን እንዲህ ብለህ እዘዛቸው ፤

ይንሥኡ ሎሙ ሠረገላተ ዘብሔረ ግብጽ፣ ለደቂቆሙ ወለአዋልዲሆሙ፣ ወለአንስቲያሆሙ ፣

ለወንዶች ልጆቻቸው፣ ለሴቶች ልጆቻቸው ፣ ለሚስቶቻቸውም

የግብጽን ሠረገላ ይዘው ይሒዱ ዘንድ ፤

ወይንሥእዎ ለአቡሆሙ ወያምጽእዎ፣

አባታቸውን በሠረገላ አስቀም ጠው ያመጡት ዘንድ እዘዛቸው፤

፳፡ ወኢይምሐኩ ቈሳቍሶሙ ወዘ ርእዮት ዓይኖሙ ፣

ዓይናቸው ያየውን ጥቃቅኑን ዕቃ ሁሉ ፣ ቀረብን ብለው አይዘኑ ፤

እስመ ኵሉ በረከተ ግብጽ ሎሙ ውእቱ ፣

የግብጽ ድልብ ሁሉ ገንዘባቸው ነውና ፤ አንድም ዓይናቸው ያየው ጥቃቅኑ ዕቃ ሁሉ ይቀ ርብናል ብለው አይዘኑ ፤ የግ ብጽ ሠረገላ ሁሉ ገንዘባቸው ነውና ፣ ማለት ጭነው ያመ ጡታል አለው ፤

፳፩፡ ወገብሩ ከማሁ ደቂቀ እስራ ኤል በከመ ይቤሎሙ ፣

የእስራኤል ልጆች እንደ አዘ ዛቸው አደረጉ ፤

ወወሀቦሙ ሠረገላተ ዮሴፍ በከመ ይቤሎ ፈርዖን ንጉሠ ግብፅ ፣

ዮሴፍም የግብጽ ንጉሥ ፈር ዖን እንዳዘዘው ሠረገላውን ሰጣ ቸው ፤

ወወሀቦሙ ስንቆሙ ለፍኖት ፣

ለጐዳና የሚሆን ስንቃቸውንም ሰጣቸው ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፪፡ ወወሀቦሙ አራዘ በበ፪ኤቱ ፤

ለሰሥሩ ወንድሞቹ እያፈራረቁ የሚለብሱት ሁለት ሁለት ልብስ ሰጣቸው ፤

ወለብንያምስ ወሀቦ ፫፻ተ ምእተ ዲናረ ፤

ለብንያም ግን ሦስት መቶ ብርና ፤

ወ፭ተ አራዘ በዘያስተባርዩ ፤

አፈራርቆ የሚለብሰው አምስት ልብስ ሰጠው ፤

፳፫፡ ወለአቡሁኒ ከማሁ ፤

ለአባቱም እንደዚሁ ፤ ሦስት መቶ ብርና አፈራርቆ የሚለብሰው አምስት ልብስ ሰጠው ፤

ወፈነወ ዐሠርተ አዕዱገ ዘይፀውሩ እምኵሉ በረከተ ግብጽ፤

ከግብጽ እህሉን ሁሉ ተጭነው የሚሔዱ ዐሥር ወደልጋዝ ሰደደ ፤ አንድም አዕዱገ ባለው ዐሠርተ አግማለ ይላል፤

ወ፲ተ አብቅለ እለ ይፀውሩ ስንቀ ለአቡሁ በፍኖት ፤

በጎዳና ለአባቱ ስንቅ የሚጭን ባቸው ዐሥር በቅሎዎች ሰደደ፤

፳፬፡ ወፈነዎሙ ለአኃዊሁ፤ ወይቤሎሙ አልቦ ዘትትገዓዙ በፍኖት ፤

አንተ እንጂ እንሸጥ ብለኸኝ፤ አንተ እንጂ እንሸጥ ብለኸን እየተባባላችሁ በጎዳና አትጣሉ ብሎ ወንድሞቹን መክሮ ሸኝቶ ሰደዳቸው ፤

፳፭፡ ወወፅኡ እምብሔረ ግብጽ ወሖሩ ፤

እነሱም ከግብጽ መሬት ወጥተው ሔዱ ፤

ወበጽሑ ምድረ ከነዓን ኀበ አቡሆሙ ፤

አባታቸው ወዳለበት ወደ ከነ ዓን በደረሱ ጊዜ ፤

፳፮፡ ወዜነውዎ ወይቤልዎ ሕያው ዮሴፍ ወልድከ ፤

ልጅህ ዮሴፍ ደህና ነው ብለው ነገሩት ፤

ወውእቱ መልአከ ለብሔረ ግብጽ ወለኵሉ ደወላ ፤

ለግብጽ አገር ለአውራጃዋ ሁሉ፤ ገዥ ቢትወደድ እሱ ነው አሉት፤

ወደንገፆ ልቡ ወኢአምኖሙ ፤

ልቡናው ደንግጠበት ነገራቸ ውን አላመናቸውም ፤

፳፯፡ ወነገርዎ ኵሎ ዘይቤሎሙ ዮሴፍ ወኵሎ ዘተናገሮሙ ፤

እነሱም አላምንም ቢላቸው ፤ ዮሴፍ ያላቸውን የተነጋገራቸ ውን ሁሉ ነገሩት ፤

ወሶበ ርእየ ሠረገላተ ዘፈነወ ዮሴፍ ሐይወ ልቡ ፤ ወተፈሥሐ ነፍሱ ለያዕቆብ አቡሆሙ ፤

ዮሴፍ የሰደደለትን ሠረገላውን ባየ ጊዜ ፤ የአባታቸው የያዕቆብን ልቡናውን ፈጽሞ ደስ አለው፤ አንድም በኀዘን ቈስሎ የነበረ ልቡናው ዳነ፤ (ሐተታ) የግብጽ ሠረገላ የሚገዛ በስድ ስት መቶ ወቄት ነው ልጄ ቢሆን ነው እንጂ ባዕድማ ቢሆን ይሰድልኝ ነበር ? ብሎ በዚህ ተረድቷል ፤

፳፰፡ ወይቤ ያዕቆብ ዐቢይ ውእቱ ሊተ ዝንቱ ፤

ያዕቆብ ይህ ነገር ለኔ ደግ ነው አለ ፤

እመ ዓዲሁ ሕያው ውእቱ ዮሴፍ ወልድየ አሐውር እርእዮ እንበለ እሙት ፤

ልጄ ዮሴፍስ እስካሁን ሕያው ከሆነ ሳልሞት ሔጄ አየዋለሁ አለ ።

## ምዕራፍ ፵፮

### ገባኤ

፩፡ ወተንሥአ እስራኤል ምስለ ኵሉ ንዋዩ ፤

እስራኤል ገንዘቡን ሁሉ ይዞ ተነሣ ፤

ወበጽሐ ኀበ አዘቅተ መሐላ ፤

ቤርሳቤህም በደረሰ ጊዜ ፤

ወሦዓ መሥዋዕተ ለአምላከ ይስሐቅ አቡሁ ፤

ከዚህ ቀድሞ መልአኩ ከግብጽ ወርደህ ትሞታለህ ብሎት ነበርና ፈርቶ አባቱ ይስሐቅ ለሚ ያመልከው ፈጣሪ መሥዋዕት ሠውቶ ልሒድን ? ልቅርን ? ብሎ ቃለ እግዚአብሔር ጠየቀ፤

፪፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር በሕልም ለእስራኤል ያዕቆብ ፤ ያዕቆብ ፤

መሥዋዕቱን ሠውቶ ስቡን አጢሶ ተኝቷል፤ እግዚአብሔር እስራኤልን በሕልም ያዕቆብ ያዕቆብ ብሎ ጠራው ፤

ወይቤ ምንት ውእቱ ፤

አቤቱ ምንድን ነው ? አለ ፤

፫፡ ወይቤሎ አነ ውእቱ አምላከ አበዊከ ፤ ኢትፍራህ ወሪደ ኀበ ብሔረ ግብጽ ፤

የምጠብቅህ የአባቶችህ ፈጣሪ እኔ ነኝና ወደ ግብጽ መውረ ድን አትፍራ አለው ፤ እንደ ፈራ በዚህ ይታወቃል ፤

እስመ ሕዝበ ዐቢየ እሬስየከ በህየ ፤

በግብጽ ብዙ ወገን አደርግሃ ለሁ ፤

፬፡ ወአነ እወርድ ምስሌከ ውስተ ብሔረ ግብጽ ፤

እኔም ከአንተ ጋራ በረድኤት ወደ ግብጽ እወርዳለሁ ፤

ወእሄሉ ምስሌከ ዘልፈ ፤

ዘወትር እኔ በረድኤት ከአ ንተ ጋራ እኖራለሁ ፤



www.ethiopianorthodox.org

ወዮሴፍ ወልድከ ይከድነከ አዕይን ቲከ ፤

ልጅህ ዮሴፍም አማውቶ ይቀብርሃል፤ (ሐተታ) የልጁን ደግነት ፤ የእሱንም ሞት አንድ ጊዜ ነገረው ፡

፭፡ ወተንሥአ ያዕቆብ እምነበ አዘቅተ መሐላ ፤

ያዕቆብም ከቤርሳቤህ ተነሥቶ ተጓዘ ፡

ወነሥእዎ ደቂቁ ለያዕቆብ እስራኤል አቡሆሙ ፤

ልጆቹም እስራኤል የተባለ አባታቸው ያዕቆብን ፡

ወንዋዮሙኒ ምስሌሆሙ ፤

ከሳቸው ጋራ ያለ ገንዘባቸውንም ይዘው ፡

ወአንስቲያሆሙኒ በዓኑ ላዕለ ሠረገላት ዘፈነወ ዮሴፍ በዘያመጽእዎሙ፤

ሚስቶቻቸውንም ዮሴፍ በዚህ አምጧቸው ብሎ በሰደደላቸው ሠረገላ ላይ አስቀምጠው ሔዱ፡

፮፡ ወነሥኡ ንዋዮሙ ወኵሎ ጥሪቶሙ ዘአጥረዩ በምድረ ከነዓን ፤

በከነዓን ያጠራቀሙትን ገንዘባቸውንም ፤ ከብታቸውንም ሁሉ ይዘው ሔዱ ፡

ወቦአ ያዕቆብ ብሔረ ግብጽ ፤

ያዕቆብ ወደ ግብጽ ገባ ፡

ወኵሉ ዘርኡ ምስሌሁ ፤

ልጆቹም ሁሉ ከእሱ ጋራ ወደ ግብጽ ገቡ ፡

ደቂቁ ፤

ወንዶች ልጆቹ ፡

፯፡ ወደቂቀ ደቂቁ ፤

የልጅ ልጆቹ ከእሱ ጋራ ወደ ግብጽ ገቡ ፡ ደቂቁ ብሎ አንድ አርእስት ፤ ወደቂቀ ደቂቁ ብሎ ሁለት አርእስት ተናግሯል ፤ ለሁለቱም ያመጣል ፡

ወአዋልዲሁ ፤

ሴቶች ልጆቹ ፡

ወአዋልደ አዋልዲሁ ምስሌሁ፤

የሴቶች ልጆቹ ልጆችም ከእሱ ጋራ ወደ ግብጽ ገቡ ፡

፰፡ ወከመዝ ውእቱ አስማቲሆሙ ለደቂቀ እስራኤል እለ ቦኡ ብሔረ ግብጽ ፤

ወደ ግብጽ የገቡ የእስራኤል ልጆች ስማቸው እንዲህ ነው፡

፱፡ በኵሩ ለያዕቆብ ሮቤል ፤

ደቂቁ ሳለው አመጣ ፤ የያዕቆብ የበኵር ልጁ ሮቤል ነው ፡

ወደቂቀ ሮቤል ፬ቱ ፤

ወደቂቀ ደቂቁ ሳለው አመጣ፡ የሮቤል ልጆች አራት ከሱ ጋራ አምስት ይሆናሉ ፡



፲፡ ወደቂቀ ስምዖን ፮ቱ ፤

የስምዖን ልጆች ስድስት ከሱ ጋራ ሰባት ይሆናሉ ፡ አምስትና ሰባት አሥራ ሁለት ይሆናል ፡

፲፩፡ ወደቂቀ ሌዊ ፫ቱ ፤

የሌዊ ልጆች ሦስቱ ፤ ከሱ ጋራ አራት ፡

፲፪፡ ወደቂቀ ይሁዳ ፭ቱ ፤

የይሁዳ ልጆች አምስት ከሱ ጋራ ስድስት ይሆናሉ ፡ አራትና ስድስት ዐሥር ይሆናል ፡ ከአሥራ ሁለት ላይ ቢጥሉት ሀያ ሁለት ይሆናል ፡

ወሞቱ ከልኤቱ በምድረ ከነዓን ፤

ሁለቱ ኤርና አውናን በከነዓን ሞቱ ፡ እሊህን ያወጡ እንደሆነ ሃያ ብቻ ይሆናሉ ፡

ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ፋሬስ ክልኤቱ ፤

የፋሬስም ልጆች ሁለት ናቸው፡ ሃያ ሁለት ይሆናሉ ፤ ፋሬስ አባታቸው ወደቂቀ ይሁዳ ኃምስቱ ካለው ውስጥ ተቈጥሯል ፡

፲፫፡ ወደቂቀ ይሳኮር ፬ቱ ፤

የይሳኮር ልጆችም አራት ናቸው፤ ከእሱ ጋራ አምስት፡

፲፬፡ ወደቂቀ ዛብሎን ፫ቱ ፤

የዛብሎን ልጆች ሦስት ናቸው ከሱ ጋራ አራት ፡

፲፭፡ ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ልያ ዘወለደት ለያዕቆብ በመስጴጦምያ ዘሶርያ ፤

የሶርያ ክፍል በምትሆን በመስጴጦምያ ለያዕቆብ የወለደ ችለት የልያ ልጆች እሊህ ናቸው ፡

ወዲና ወለቶሙ ወኵሉ ነፍሰ ደቂቅ፤ ወአዋልድ ዘልያ ፴ወ፫ቱ ፤

ልጃቸው ዲናም ተጨምራ ተቈጥራ ከልያ የተወለዱ ሴቶችም ወንዶችም ልጆች ሠላሳ አራት ናቸው፤ ዲናን፤ ኤርን፡ አውናንን ጨምሮ ነው ፡ እሊህን ሦስቱን ያወጡ እንደሆነ ሠላሳ አንድ ይሆናሉ ፡

፲፮፡ ወደቂቀ ጋድ ፯ቱ ፤

የጋድ ልጆች ሰባት ናቸው ፤ ከሱ ጋራ ስምንት ፡

፲፯፡ ወደቂቀ አሴር ፭ቱ ፤

የአሴር ልጆች አምስት ናቸው፡ ከሱ ጋራ ስድስት ፡ ስድስትና ስምንት ዐሥራ አራት ይሆናሉ ፡

ወደቂቀ ባርያ ፪ቱ ፤

የባርያ ልጆች ሁለት ናቸው ፤ በዐሥራ አራቱ ላይ ሁለት

www.ethiopianorthodox.org

ሲጨመር ዐሥራ ስድስት ይሆናል ፤

፲፰፤ ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ዘለፋ እንተ ወሀባ ላባ ለልያ ፣

ላባ ለልያ የሰጣት የዘለፋ ልጆች እሊህ ናቸው ፤

ወይእቲ ዘወለደት ለያዕቆብ ፲ቱ ወ፮ቱ ነፍስ ፣

ዘለፋ ለያዕቆብ የወለደችለት ዐሥራ ስድስት ናቸው፤ ሠላሳ አንድና ዐሥራ ስድስት አርባ ሰባት ይሆናል፤ ዲናን ያወጡ እንደሆነ አርባ ስድስት ይሆናል ፤

፲፱፤ ወደቂቀ ራኄል ብእሲተ ያዕቆብ ፤ ዮሴፍ ወብንያም ፣

የያዕቆብም ሚስት የራኄል ልጆች ዮሴፍና ብንያም ናቸው፤

፳፤ ወተወልዱ ደቂቅ ሎቱ ለዮሴፍ በብሔረ ግብጽ፣ ምናሴ ወኤፍሬም፣

ለዮሴፍ በግብጽ ልጆች ተወለዱለት ፣ እነዚህም ምናሴና ኤፍሬም ናቸው ፤

፳፩፤ ወደቂቀ ብንያም ፲ቱ ፣

የብንያም ልጆች ዐሥር ናቸው፣ ከሱ ጋራ ዐሥራ አንድ ፣ ዮሴፍ ከነልጆቹ ሦስት ፤

፳፪፤ ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ራኄል፤ ዘወለደት ለያዕቆብ ፲ቱ ወ፬ቱ ነፍስ፣

ራኄል ለያዕቆብ የወለደችለት የራኄል ልጆች ዐሥራ አራት ናቸው ፣ በአርባ ስድስት ላይ ዐሥራ አራት ቢጨምሩ ስሳ ይሆናል ፤

፳፫፤ ወደቂቀ ዳን ኡሳ ፣

የዳን ልጅ ኡሳ ነው ፤ ከሱ ጋራ ሁለት ፤

፳፬፤ ወደቂቀ ንፍታሌም ፬ቱ ፣

የንፍታሌም ልጆች አራት ናቸው ፤ ከሱ ጋራ አምስት ፤ ሁለትንና አምስትን ቢያገናኙት ሰባት ይሆናል ፤ ሰባትን ከስሳው ቢገጥሙት ስሳ ሰባት ይሆናል ፤

፳፭፤ እሉ እሙንቱ ደቂቀ ባላ እንተ ወሀባ ላባ ለራኄል ወለቱ ፣

ላባ ለልጁ ለራኄል የሰጣት የባላ ልጆች እኒህ ናቸው ፤

ወወለደቶሙ ለእሉ ለያዕቆብ ፣

እሊህን ለያዕቆብ ወለደችለት፤

ወኵሉ ነፍስ ዘወለደት ባላ ፯ቱ ፣

ባላ የወለደቻቸው ሰባት ናቸው፤

፳፮፤ ወኵሉ ነፍስ ዘቦአ ብሔረ ግብጽ ምስለ ያዕቆብ ዘእንበለ አንስትያ ደቂቁ ፷ወ፮ቱ ፣

ከልጆቹ ሚስቶች በቀር ከያዕቆብ ጋራ ወደ ግብጽ የወረዱት ስሳ ሰባት ናቸው ፤



፳፯፤ ወደቂቀ ዮሴፍ እለ ተወልዱ በብሔረ ግብጽ ፪ቱ ፣

በግብጽ የተወለዱ የዮሴፍ ልጆች ሁለት ናቸው ፤

ወኮነ ኵሉ ነፍስ እንተ ቦአ ብሔረ ግብጽ ምስለ ያዕቆብ ፸ ፣

ወደ ግብጽ የወረዱት ከያዕቆብ ጋራ ሰባ ናቸው ፤ በእውነት የወረዱት ግን ስሳ አራት ናቸው ፤

ስሳ ሰባት ማለቱ ዮሴፍን ከነ ልጆቹ ጨምሮ ነው ፤ በስሳ ሰባቱ ላይ ኤርን ፤ አውናንን ቢጨምሩ ስሳ ዘጠኝ ይሆናል፤ ያዕቆብን ቢጨምሩ ሰባ ይሆናል ፤ ኤርና አውናንስ የሞቱ በኢየሩሳሌም ነው ብሎ፣ ማራ ወለተ አሴርን ዲናን አግብቶ ስሳ ዘጠኝ ይሆናል ፤ ያዕቆብን ጨምሮ ሰባ ይሆናሉ ፤ ሴትንስ ከወንድ ጋር አግብተው አይቆጥሩም ብሎ ፣ ዮሴፍ አስቀድሞ ነው የወረደ፣ ልጆቹም የተወለዱ በግብጽ ነው ብሎ ፣ ወደቂቀ ዳን ኡሳ ባለው ፣ የዳን ልጆች አምስት ነበሩ ፣ አራቱ ሙተው አንድ ቀርቷል፤ ደቂቀ ንፍታሌም ፬ቱ ካላቸው ኃምስቱ ይላል፣ የንፍታሌም ልጆች አምስት ነበሩ አንዱ ሙቶ አራት ቀርተዋል ፤ እኒህን አምስቱን በስሳ አራት ላይ ቢጨምሩ ስሳ ዘጠኝ ይሆናሉ፤ ያዕቆብን ጨምሮ ሰባ ይሆናሉ ፣ ሰባ ሁለት ቢል ፣ ኤርንና አውናንን ጨምሮ ዮሴፍን ከነልጆቹ አውጥቶ፣ ሰባ ሦስት ቢል ዮሴፍን ከነልጆቹ አግብቶ ኤርንና አውናንን አውጥቶ ፣ ሰባ አምስት ቢል ዮሴፍን ከነ ልጆቹ ፣ ኤርን ፣ አውናንን ጨምሮ ነው ፤

፳፰፤ ወለይሁዳ ፈነዎ ቅድሜሁ ኀበ ዮሴፍ ከመ ይትቀበሎ እስከ ምድረ ራምሴ እንተ ስማ ቃቴሮአስ ፣

ስሟ ቃቴሮአስ እስከምትባል እስከ ራምሴ አውራጃ ድረስ ወጥቶ ይቀበለው ዘንድ ይሁዳን አስቀድሞ ወደ ዮሴፍ ላከው ፤

፳፱፤ ወአንሥአ ዮሴፍ ሠረገላቲሁ ወሖረ ይትቀበሎ ለያዕቆብ አቡሁ ውስተ ምድረ ቃቴሮአስ ፣

ዮሴፍም ሠረገላውን ጭኖ አባቱን ይቀበለው ዘንድ ወደ ቃቴሮአስ ሔደ ፤

ወሶበ ረከቦ ሐቀፎ ክሣዶ ወበከየ ዐቢየ ብካየ ፣

ባገኘውም ጊዜ አንገቱን አቅፎ ይ፲ ጽኑ ልቅሶ አለቀሰ ፤

፴፤ ወይቤሎ እስራኤል ለዮሴፍ እምይእዜሰ ለእሙት እንከ ፣

እስራኤልም ዮሴፍን እንግዲህ ወዲህስ ልሙት ፤

www.ethiopianorthodox.org

እስመ ርኢኩ ገጸከ እንዘ ሕያው አንተ ፤

አንተ በሕይወተ ሥጋ ሳለህ ፊትህን አይቼዋለሁና ፤ ካየ ሁት ልሙት አለው ፤

፴፩፡ ወይቤሎሙ ዮሴፍ ለአኃዊሁ ፤

ዮሴፍም ወንድሞቹን እንዲህ አላቸው ፤

ወአሐውር እንግሮ ለፈርዖን ወእቤሎ፤

ሔጄ ለፈርዖን እንዲህ ብዬ እነግረዋለሁ ፤

አኃውየ ወቤተ አቡየ እለ ሀለዉ በምድረ ከነዓን መጽኡ ኀቤየ ፤

በከነዓን ይኖሩ የነበሩ ወንድሞቼ የአባቴ ወገኖች ወደኔ መጥተዋል ፤

፴፪፡ ወኖሎተ እንስሳ፣ ወሰብአ መራዕይ እሙንቱ ሰብእ ፤

እኒሁም መንጋ ያላቸው ከብት ጠባቆች ዘላኖች ናቸው ፤

አባግዒሆሙ ፤ ወአልሕምቲሆሙ ወኵሎ ንዋዮሙ አምጽኡ ፤

በጎቻቸውንም፣ ላሞቻቸውንም፣ ገንዘባቸውንም ሁሉ ይዘው መጥ ተዋል ብዬ እነግረዋለሁ አላ ቸው ፤ (ሐተታ) አባግዒሆሙ ወአልህምቲሆሙ ማለቱ ለመ ታመን ነው ፤

፴፫፡ ወእመ ጸውዓክሙ ፈርዖን ወይ ቤለክሙ ምንት ተግባርክሙ ፤

ፈርዖንም ጠርቶ ምን ሥራ ታውቃላችሁ ብሎ ቢጠይቃ ችሁ ፤

፴፬፡ በልዎ ኖሎተ እንስሳ ንሕነ አግ ብርቲከ እምንዕስነ እስከ ይእዜ ፤

እኛ ባሮችህ ፤ ከሕፃንነታችን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ከብት ጠባቆች ዘላኖች ነን በሉት ፤

ወአበዊነኒ ከማሁ ከመ ፤

አባቶቻችንም መቼም መች ከብት ጠባቆች ነበሩ በሉት ፤

ከመ ትኅድሩ ምድረ ጌሤም፣ እንተ ዓረብ ፤

በምዕራብ በኩል ባለ በጌሤም አውራጃ ትኖሩ ዘንድ፣ (ሐተታ) ሴቶችንም ይመክሩቸዋል፤ መፍ ተል ፤ መስፋት እናውቃለን አትበሉ፤ መፍጨት፣ መጋገር እናውቃለን በሉ ብሏቸዋል ፤ ስለምን ቢሉ ፤ በክፉ ቀን ከእ ህል ፤ ከከብት የተጠጋ ይድና ልና ብሎ ነው ፤

እስመ ያስቈርርዎሙ ሰብአ ግብጽ ለኵሎሙ ኖሎተ አባግዕ ፤

የግብፅ ሰዎች ዘላኖችን ሁሉ ይጠየፏቸዋልና ፤ ከመ ትኅድሩ ምድረ ጌሤም ላለው ።



## ምዕራፍ ፵፯

፩፡ ወቦአ ዮሴፍ ወነገሮ ለፈርዖን ፤ ወይቤሎ ፤ አቡየ ወአኃውየ ምስለ እንስሳሆሙ ወንዋዮሙ መጽኡ እም ድረ ከነዓን ፤

ዮሴፍም ወደ ፈርዖን ገብቶ ፤ አባቴና ወንድሞቼ ፤ ከብታቸ ውን ፤ ገንዘባቸውን ይዘው ከከ ነዓን መጥተዋል ፤

ወናሁ በጽሑ ውስተ ምድረ ጌሤም ፤

አሁንም ጌሤም ከምትባል ቦታ ደርሰዋል ብሎ ለፈርዖን ነገ ረው ፤

፪፡ ወነሥአ ዮሴፍ ፭ተ ዕደወ እም አኃዊሁ ፤ ወአብጽሐሙ ምስሌሁ ኀበ ፈርዖን ፤

ዮሴፍም ከወንድሞቹ አምስቱን ለይቶ ከእሱ ጋራ ፈርዖን ወዳ ለበት ይዟቸው ገባ ፤

፫፡ ወይቤሎሙ ፈርዖን ለአኃዊሁ ለዮሴፍ፣ ምንት ተግባርክሙ ፤

ፈርዖን የዮሴፍን ወንድሞች፣ ምን ሥራ ታውቃላችሁ ? አላ ቸው ፤

ወይቤልዎ ኖሎተ እንስሳ ንሕነ አግ ብርቲከ ወአበዊነኒ ፤

እኛ ባሮችህ ከብት ጠባቆች ፤ ዘላኖች ነን ፤ አባቶቻችንም እንደ እኛ ዘላኖች ነበሩ ፤

፬፡ ወይቤልዎ ለፈርዖን አኅድረነ ውስተ ምድር እንተ ኀበ መጻእነ ፤

ፈርዖንን በመጣንበት ኅዳና ባለው አገር ቦታ ሰጥተህ አኑ ረን አሉት ፤

እስመ አልቦ ምርአይ ለእንስሳ አግ ብርቲከ ፤

በዚህ በከተማው እንዳንቀመጥ ለኛ ለባሮችህ ከብት መሰማሪያ የለምና ፤

ወጸንዐ ረኃብ ውስተ ምድረ ከነዓን ፤

ከአገራችንም የወጣንበት ምክ ንያት ፤ በከነዓን ረኃብ ቢጸና ብን ነው ፤
ወይእዜኒ አኅድረነ ለአግብርቲከ ውስተ ምድረ ጌሤም ፤

አሁንም እኛን ባሮችህን በጌ ሤም አውራጃ እንድንኖር አድ ርገን አሉት ፤

፭፡ ወይቤሎ ፈርዖን ለዮሴፍ ፤ እም ከመ መጽኡ አቡከ ወአኃዊከ ኀቤከ ፤

ፈርዖን ዮሴፍን እንዲህ አለው፣ አባትህ ፤ ወንድሞችህ አንተን ሲሉ ወደ አንተ ከመጡ፤

፮፡ ናሁ ኵላ ምድረ ግብጽ ቅድሜከ ይእቲ ውስተ እንተ ትኄይስ ምድር ይኅድሩ ፤

ግብጽ ሁሉ በአንተ እጅ ናትና አገር መርጠህ ስጥተሃቸው ይቀ መጡ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወእመኒ ተአምር ከመቦ ጽኑዓን ዕደው በውስቴቶሙ ሢሞሙ መላ እክተ ኖሎት ለእንስሳየ ፤

ከወንድሞችህም ብርቱ ብርቱ ዎች እንዳሉ የምታውቅ እንደ ሆነ፣ ለመንጋዬ የዘላን አለቆች አድርገህ ሹማቸው አለው ፤

፯፡ ወአብአ ዮሴፍ ለአቡሁ ወአቀሞ ቅድመ ፈርዖን ፤

ዮሴፍ አባቱን ይዞ ገብቶ በፈ ርዖን ፊት አቆመው ፤

ወተአምኆ ያዕቆብ ለፈርዖን ፤

ያዕቆብ ፈርዖንን እጅ ነሣው ፤

፰፡ ወይቤሎ ፈርዖን ለያዕቆብ ሚመ ጠን መዋዕል ዘሐየውከ ፤

ሽማግሌ ከሽማግሌ ሲገናኝ ዘመን መጠያየቅ ልማድ ነውና ፤ ፈር ዖን ያዕቆብን የኖርኸው ዘመን ምን ያህል ነው ? አለው ፤

፱፡ ወይቤሎ ያዕቆብ ለፈርዖን መዋ ዕለ ሕይወትየሰ ዘሐየኩ ፻ት ወ፴ ዓመት እማንቱ ፤

ያዕቆብም ፈርዖንን በሕይወት የኖርኹት ዘመንስ መቶ ሠላሳ ነው አለው ፤

ወእማንቱ ኅዳጣት ዓመታት ፤

ጥቂቶች ዘመኖች ናቸው ፤

ወእኩያተ ኮናኒ ፤

እነዚህም ክፉዎች ሆኑብኝ ማለት በመከራ ተፈጸሙ ማለት ነው ፤ አንድም በተድላ በደ ስታ ከኖርኹት በመከራ የኖ ርኹት ዘመን ይበዛል ሲል ነው ፤

መዋዕለ ሕይወትየሰ ወዓመታትየኒ ወኢከመ ምንት ኮናኒ በነበ መዋ ዕለ ሕይወተ አበውየ ዘሐይዉ ፤

መዋዕልና ዓመታት አንድ ወገን ፤ በሕይወት የኖርኋቸው ዘመኖች አባቶቼ በኖሩት ዘመን መጠን እንደ ኢምንት ናቸው (ሐተታ) የአባቶቼ ዘመን ሰባት መቶ ስምንት መቶ ነውና፤

፲፡ ወባረኮ ያዕቆብ ለፈርዖን ወወዕአ እምኅቤሁ ፤

ያዕቆብ ፈርዖንን ሺህ ዓመት ያንግሥህ ብሎ መርቆት ከሱ ተለይቶ ወጣ ፤

፲፩፡ ወአኅደሮሙ ዮሴፍ ለአቡሁ ወለአኀዊሁ ወወሀቦሙ ምኵናነ በም ድረ ግብጽ ውስተ እንተ ትኄይስ ምድር ውስተ ምድረ ራምሴ ዘአዘዘ ሎሙ ፈርዖን ፤

ውስተ እንተ ትኄይስና ውስተ ምድረ ራምሴ አንድ ወገን ፤ ዮሴፍም አባቱንና ወንድሞቹን ፈርዖን በአዘዘላቸው በግብጽ ውስጥ ባለች ከሀገሩ ሁሉ በም ትበልጥ በራምሴ ጉልት ሰጥቶ አኖራቸው ፤



፲፪፡ ወዮሴፍ ይሰፍር ሥርናየ፡ ሲሳየ አቡሁ ወአኃዊሁ ፤

ዮሴፍም የወንድሞቹንና የአ ባቱን ምግብ ስንዴውን እየሰ ፈረ ይሰጥ ጀመር ፤

ወለኵሉ ቤተ አቡሁ ለለ፩ዱ ነፍስ ይሰፍር ሥርናየ ሲሳየ ፤

ለአንዱም ለአንዱም ለአባቱ ወገን ስንዴውን እየሰፈረ ይሰጥ ነበር ፤ (ሐተታ) የሚሰጣቸው ስንዴ ብቻ ሆኖ አይደለም ፤ በስንዴ መላውን መናገር ነው፤

፲፫፡ ወአልቦ ሥርናይ ውስተ ኵሉ ምድረ ግብጽ እስመ ጸንዓ ረኃብ ጥቀ ፤ ወኃልቀ ብሔረ ግብጽ ወከነ ዓን በረኃብ ፤

በግብጽ አውራጃ ሁሉ እህል ጠፍቶ ረኃብ ስለ ጸና በግብጽና በከነዓን ያለ ሰው ሁሉ በረኃብ ምክንያት አለቀ ፤

፲፬፡ ወአስተጋብዓ ዮሴፍ ኵሎ ወርቀ ዘአምጽኡ ሰብአ ግብጽ ፤ ወሰብአ ከነዓን ሤጠ እክል ዘሤጠ ሎሙ ፤

ያቀናላቸው የእህሉን ዋጋ ፤ የግብጽና የከነዓን ሰዎች ያመ ጡት ወርቁን ዮሴፍ ሰበሰበ፤

ወአብዓ ዮሴፍ ኵሎ ወርቀ ውስተ ቤተ ፈርዖን ፤

ዮሴፍ ወርቁን ሁሉ ወደ ፈር ዖን ቤት አገባ ፤

፲፭፡ ወኃልቀ ኵሉ ወርቅ ዘብሔረ ግብጽ ወዘኵሉ ብሔረ ከነዓን ፤

በግብጽ አውራጃና በከነዓን አው ራጃ ያለው ወርቅ ሁሉ፣ ከፈ ርዖን ቤት ገብቶ አለቀ ፤

ወመጽኡ ኵሉ ሰብአ ግብጽ ኀበ ዮሴፍ ወይቤልዎ ሀበነ እክለ ከመ ኢንሙት በቅድሜከ እስመ ኃልቀ ወርቅነ ፤

የግብጽ ሰዎችም ከዮሴፍ ቤት ገብተው፣ የምንሸምትበት ወር ቃችን ሁሉ አልቋልና ካንተ ዘንድ እህል ሳለ፣ እያየኸን እን ዳንሞት ያለ ዋጋ እህል ስጠን አሉት ፤ (ሐተታ) ሁለቱን ዓመት የሰበሰቡትን እህላቸውን በልተዋል ፤ አንዱን ዓመት በወርቃቸው ሸምተው በልተ ዋል፤ በአራተኛው ዓመት ከብ ታቸውን ይዘው ከእሱ ዘንድ ሒደዋል፤ በአምስተኛው ዓመት ምድራችንንም ውሰድ፣ እኛን ባሪያ አድርገህ ግዛን ብለው ታል ፤

፲፮፡ ወይቤሎሙ ዮሴፍ አምጽኡ እንስሳክሙ ፤ ወእሁበክሙ እክለ ህየ ንተ እንስሳክሙ አመ ኃልቀ ወርቅ ክሙ ፤

ዮሴፍም ወርቃችሁ ካለቀ ፤ ስለ ከብታችሁ ፈንታ እህል እሰጣችኋለሁና ከብቶቻችሁን አምጡ አላቸው ፤

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

፲፯፤ ወአምጽኡ እንስሳሆሙ ኀበ ዮሴፍ ፣

ከብቶቻቸውን አምጥተው ለዮሴፍ ሰጡት ፤

ወወሀቦሙ እክለ ህየንተ አባግዒሆሙ ወአልሕምቲሆሙ ወህየንተ አዕዱጊሆሙ ፣

በጎቻቸውን ላሞቻቸውን ፣ አህዮቻቸውን ተቀብሎ እህል ሰጣቸው ፣ በአራተኛዪቱ ዓመት በከብታቸው ዋጋ እህል መገባቸው ፤

፲፰፤ ወኃልቀት ይእቲ ዓመት ፣

አራተኛዪቱ ዓመት ተፈጸመች፤

ወመጽኡ ኀቤሁ በካልዕት ዓመት፣

በሁለተኛው ዘመን ከሱ ዘንድ መጥተው ፤

ወይቤልዎ ሀበነ እክለ ከመ ኢንሙት ወኢንኅልቅ ለእግዚእነ ፣

የሕዝብ ጥፋት ለንጉሥ ጉዳት ነውና ፣ ጌታችን በረኃብ እንዳናልቅብህ እህል ስጠን አሉት፤

እስመ ተወድዓ ወርቅነሂ ወንዋይነሂ፣ ወእንስሳነሂ ፣

ወርቃችንም ፣ መሳሪያችንም ከብታችንም ተጨርሷልና ፤

ወአኀለቅናሁ ለኵሉ እግዚእ ፣

አቤቱ ሁሉን ሸጠን ጨርሰን በላነው ፤

ወአልቦ ዘተርፈ ለነ በቅድሜከ እግዚእ ፤ ዘእንበለ ሥጋነ ዘዚአነ ወምድርነ ፣

አቤቱ ከምድራችን፣ ከሰውነታችን በቀር ፣ አንተ እንደምታውቀው የቀረን የለም ፤

፲፱፤ ከመ ኢንሙት እንከ በቅድሜከ ወምድርነኒ ከመ ኢትማስን ፣

እያየኸን እንዳንሞት ፣ ሀገራችንም ምድረ በዳ እንዳትሆን ፤

ንሥአነ ወአጥርየነ ኪያነሂ ወምድረነሂ ህየንተ እክል ፣

ስለ እህል ፈንታ፣ ማለት እህል እያበላህ ግዛን ፤ ምድራችንንም ውሰድ ፤

ወንኩን አግብርተ ለፈርዖን ህየንተ እክል ፣

እኛ ለፈርዖን ተገዦች እንሁን፤

ወምድርነሂ ትኩን ሎቱ ፣

ምድራችንም ለእሱ ሁዳድ ትሁን ፤

ወወሀበነ ዘርዓ ከመ ንዝራእ ከመ ንሕየው ወኢንሙት ፣

በረኃብ ከመሞት እንድን ዘንድ ዘር ስጠን እንዝራ ፤

ወምድርነሂ ከመ ኢትማስን ፣

ምድራችንም የሚያርሳት አጥታ ምድረ በዳ እንዳትሆን አሉት ፤

፳፤ ወአጥረየ ዮሴፍ ኵሎ ምድሮሙ ለግብጽ ፣

ዮሴፍ የግብጻውያንን ሁሉ ምድር እጅ አደረገ ገዛ ፤



ወአግብአ ለፈርዖን ኵሎ ምድሮሙ እስመ ኃየሎሙ ረኃብ ፣

ረኃብ ስለ ጸናባቸው እህል እየሰጠ ምድራቸውን ሁሉ ለፈርዖን ገዛ ፤

ወኮነ ኵሉ ምድር ለፈርዖን ፣

ምድር ሁሉ ለፈርዖን ሁዳድ ሆነ ፤

፳፩፤ ወኵሉ ሕዝብ ኮንዎ አግብርተሁ ፣

ሕዝቡም ሁሉ የእሱ ተገዥዎች ሆኑ ፤

ወቀነዮሙ እምአጽናፈ ምድር ፣

ከጽንፍ እስከ ጽንፍ አንድ አድርጎ ገዛቸው ፤

ወአድባሪሆሙኒ ወኵሎ ደወሎሙ ለግብጽ እምአጽናፈ ደወሎሙ ለከነዓን ፣

ከከነዓን ወሰን ዳርቻ ጀምሮ የግብጽን አውራጃ ሁሉ ፣ ቆላውንም ደጋውንም ገዛ ፤

፳፪፤ ዘእንበለ ምድሮሙ ለማርያን ባሕቲታ ዘኢያጥረየ ዮሴፍ ፣

ዮሴፍ ካልገዛው ከካህናተ ጣዖቱ ምድር ብቻ በቀር ሁሉንም ሁዳድ አደረገው ፤

እስመ ወሀቦሙ ፈርዖን፤ ወፈተቶሙ ለማርያን ወጸገዎሙ ፣

ለካህናተ ጣዖቱ ፣ ፈርዖን ድርጎ ዳርጓቸው ፣ ቀለብ ፣ ደመወዝ ሰጥቷቸው ፤

ወበእንተዝ ኢሤጡ ምድሮሙ ፣

ስለዚህ ምድራቸውን አልሸጡም ነበርና ፤ ዘእንበለ ምድሮሙ ለማርያን አለ ፤

፳፫፤ ወይቤሎሙ ዮሴፍ ለኵሎሙ ሰብአ ግብጽ ፣

ዮሴፍም የግብጽን ሰዎች ሁሉ እንዲህ አላቸው ፤

ናሁ ተሣየጥኩክሙ ኪያክሙሂ ወምድረክሙ ለፈርዖን ፣

ለፈርዖን ልትገዙ ምድራችሁንም፣ እናንተንም ገዝቻችኋለሁና ፤

ንሥኡ ለክሙ ዘርአ ወዝርእዋ ለምድርክሙ ፣

ዘር ወስዳችሁ ምድራችሁን ዝሩት ፤

፳፬፤ ወታገብኡ ለፈርዖን እክለ ኃምስተ እደ ፣

አምስቱን እጅ ለፈርዖን ትሰጣላችሁ ፤

ወ፬ቱ እድ ለክሙ ፣

አራቱ እጅ ለናንተ ይሆናል፣ (ሐተታ) ዘጠኝ ተከፍሎ ነው ፤ ይህስ ይጎዳሉ ብሎ አምስተኛውን ለፈርዖን ትሰጣላችሁ ፤ አራቱ እጅ ለእናንተ ይሆናል ፤

ዘይከውነክሙ ዘርዐ ለምድርክሙ፣

ለምድራችሁ ዘር የሚሆን ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወለሲሳይክሙ ወለሲሳየ ኵሉ ሰብ እክሙ ፤

ለእናንተም ለቤተሰቦቻችሁም፤ ምግብ የሚሆን አራቱ እጅ ለእናንተ ይሆናል አላቸው፤

፳፭፡ ወይቤልዎ አሕየውከነ ፤

እንዲህ ካደረግህልንስ በረኃብ ከመሞት አዳንኸን ፤

ወረከብነ ሞገሰ በቅድሜሁ ለእግዚእነ ፤ ወኮነ አግብርተ ለፈርዖን ፤

እኛም ባንተ በጌታችን ፊት ባለሟልነትን አግኝተን ለፈርዖን ተገዥዎች እንሆናለን አሉት፤

፳፮፡ ወኮነት ዛቲ ሥርዓት እንተ ሠርዓ ዮሴፍ ውስተ ምድረ ግብጽ ፡ ወቆመት እስከ ዛቲ ዕለት ፤

ይህችም ዮሴፍ የሠራት ሥርዓት ፤ በግብጽ አገር እስከዚህች ቀን ድረስ ጸንታ ኖረች ፤

ከመ ያግብኡ ኃምሰ እደ ለፈርዖን እስከ ዮም ፤ ዘእንበለ ምድረ ማርያን ባሕቲታ እንተ ኢኮነት ለፈርዖን ፤

ለፈርዖን ካልሆነች ከካህናተ ጣዖት ምድር ብቻ በቀር አምስተኛውን እጅ ለፈርዖን የገበዘንድ የሠራት ሥርዓት እስከ ዛሬ ድረስ ጸንታ ትኖራለች ፤

፳፯፡ ወነበረ እስራኤል ውስተ ጌሤም፤

እስራኤልም በጌሤም ሰፍሮ ኖረ ፤

ወኮነት ይእቲ ክፍሎሙ ፤

ይህች ጌሤም እድላቸው ርስታቸው ሆና ኖረች ፤

ወበዝኁ ወመልኡ ጥቀ ፤

እስራኤልም ፤ ፈጽመው በዝተው በጌሤም መሉ ፤

፳፰፡ ወሐይወ ያዕቆብ በምድረ ግብጽ ፲ወ፯ ዓመተ ፤

ያዕቆብም በግብጽ ዐሥራ ሰባት ዓመት ኖረ ፤

ወኮነ ኵሉ ዓመተ ሕይወቱ ለያዕቆብ ፻ተወ፵ወ፯ተ ዓመተ ፤

ያዕቆብም በሕይወተ ሥጋ የኖረው መላ ዘመኑ መቶ አርባ ሰባት ዓመት ነው ፤

፳፱፡ ወቀርበ መዋዕሊሁ ለእስራኤል ለመዊት ፡ ጸውዖ ለዮሴፍ ወልዱ ወይቤሎ ፤

እስራኤልም የሚሞትበት ቀን በደረሰ ጊዜ ፤ ልጁን ዮሴፍን አስጠርቶ እንዲህ አለው ፡

እመ ረከብኩ ሞገሰ በቅድሜከ ደይ እዴከ ላዕለ እዴዬ ፤

በፊትህ ባለሟልነትን አግኝቼ እንደ ሆነ ፤ እጅህን በእጄ ላይ አድርግ ፤ አንድም ደይ እዴከ ላዕለ አብራክየ ይላል ፤ እጅህን በጕልበቴ ላይ አድርግ አለው ፤



ወግበር ምስሌየ ምሕረተ ወጽድቀ ከመ ኢትቅብረኒ ውስተ ምድረ ግብጽ ፤

በግብጽ እንዳትቀብረኝ ለኔ ርኅራኄን ፤ ቸርነትን አድርግልኝ ፤

፴፡ ዳዕሙ ከመ እኑም ምስለ አበውየ ወአውዕአኒ እምብሔረ ግብጽ ወቅብረኒ ውስተ መቃብሮሙ ለአበውየ ፤

አባቶቼ ከተቀበሩበት እቀበር ዘንድ ፤ ከግብጽ አውጥተህ በአባቶቼ መቃብር ቅበረኝ እንጂ ፤ በግብጽ እንዳትቀብረኝ ፤ ርኅራኄን ቸርነትን አድርግልኝ አለው ፤

ወይቤሎ ዮሴፍ አሆ እገብር ለከ ዘትቤለኒ ፤

ዮሴፍም እሺ ያዘዝኸኝን አደርግልሃለሁ አለው ፤

፴፩፡ ወይቤሎ መሐልከ ሊተ ወመሐለ ሎቱ ፤

ደይ እዴከ በእዴየ ያለውን አመጣ ፤ እጄን በእጅህ መትተህ ማልልኝ አለው ማለለት ፤

ወሰገደ እስራኤል ላዕለ ርእሰ ዓራቱ፤

እስራኤልም ዮሴፍ ያልኸኝን አደርግልሃለሁ ቢለው ደስ ብሎት ፤ በአልጋው ሸንኮር ሰገደ ፤ (ሐተታ) ከአንተ ለተወለደ ለኢየሱ ሰው ሁሉ ይሰግድለታል ሲል ፤ አንድም ላዕለ ርእሰ አዕባዕቱ ይላል ፤ ጣቱን አመሳቅሎ ሰገደ፤ አንድም በከተማ በትሩ ይላል ፤ በመቋሚያ ሰይፉ ሰገደ ፤ ሰው ሁሉ ለመስቀል ይሰግዳል ሲል ።

## ምዕራፍ ፵ወ፰

፩፡ ወኮነ እምድኅረ ዝንቱ ነገር ፤

ዝንቱ ሲናገረው ለመጣው ነው፤ ከዚህ ነገር በኋላ እንዲህ ሆነ፤

ወይቤልዎ አኃዊሁ ለዮሴፍ ደክመ አቡነ ፤

ኮነ ያለውን ይቤልዎ ብሎ አመጣው ፤ ወንድሞቹ ዮሴፍን አባታችን ደከመ ብለው ነገሩት ፤

ወነሥአ ዮሴፍ ፪ተ ደቂቆ ምናሴሃ ወኤፍሬምሃ ፤

ዮሴፍም ሁለቱን ልጆቹን ምናሴንና ኤፍሬምን ይዞ ወደ አባቱ ሔደ ፤

፪፡ ወይቤልዎ ለእስራኤል ናሁ ወልድከ ዮሴፍ መጽአ ኀቤከ ፤

እስራኤልንም እነሆ ልጅህ ዮሴፍ ወደ አንተ መጣ ብለው በነገሩት ጊዜ ፤

ወተኃየለ እስራኤል ወተንሥአ ነበረ ዲበ ምስካቢሁ ፤

እስራኤልም ተጸናንቶ ተነሥቶ በአልጋው ላይ ተቀመጠ፤

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

፫፡ ወይቤሎ ያዕቆብ ለዮሴፍ ፤

ያዕቆብም ዮሴፍን እንዲህ አለው ፤

አምላኪየ ዘአስተርአየኒ በሎዛ በምድረ ከነዓን ወባረከኒ ፤

በከነዓን አውራጃ በሎዛ የታየኝ ፈጣሪዬ ፤

፬፡ ወይቤለኒ ናሁ አነ አበዝኀከ ወአስተባዝኀከ ፤

እኔ ብዙ የብዙ ብዙ አደርግሃለሁ ፤

ወእገብረከ ማኅበረ አሕዛብ ፤

የአሕዛብ መገናኛ አደርግሃለሁ፤

ወእሁበከሃ ለዛቲ ምድር ፤

ይህችን አገር አወርስሃለሁ ፤

ወለዘርእከሂ እምድኅሬከ ፤ ከመ ይምልክዋ ለዓለም ፤

ለዘለዓለም ወርሰዋት ይኖሩ ዘንድ ፤ ከአንተም በኋላ ለልጆችህ እሰጣታለሁ ያለኝ ፈጣሪዬ ፤ አንድም ዓለም ከነዓንን ይገዟት ዘንድ አወርሳቸዋለሁ ያለኝ ፈጣሪዬ ለይባርካችሁ ለእሉ ሕፃናት ያለበት ነው፤ ኋላ በሚያመጣው ይታወቃል፤ እኒህን ሕፃናት ያክብራቸው ፤

፭፡ ወይእዜኒ እሉ ደቂቅከ ፪ቱ ኤፍሬም ወምናሴ እለ ተወልዱ ለከ በብሔረ ግብፅ ዘእንበለ እምጻእ አነ ኀቤከ ፤

አሁንም እኔ ከአንተ ዘንድ ወደዚህ ሳልመጣ፤ በግብጽ የተወለዱ እኒህ ሁለቱ ልጆችኽ ኤፍሬምና ምናሴ ፤

ከመ ሮቤል ወስምዖን ሊተ እሙንቱ፤

እንደ ሮቤልና እንደ ስምዖን ይሁኑ ማለት ከእነሱ ጋር ይቈጠሩ ፤

፮፡ ወእመቦ ዘወለድከ እምይእዜ በአስማተ አኀዊሆሙ ይሰመዩ ፤

እንግዲህ ወዲህ የምትወልዳቸው ልጆች ቢኖሩ ፤ በወንድሞቻቸው ስም ይጠሩ ፤ ማለት ያንተ ልጆች የኔ የልጅ ልጅ ይባሉ ፤

ወይኩኑ ውስተ ክፍለ አኀዊሆሙ ፤

የወንድሞቻቸውን ዕጣ ይውረሱ፤

፯፡ ወአመ መጻእኩ አነ እመስጴጦምያ ዘሶርያ ሞተት ራኄል እምከ በምድረ ከነዓን በፍኖት ሶበ ቀረብኩ ኀበ ምርዋጸ አፍራስ ዘኤፌፍራታ ለበጺሐ ኤፍራታ ፤

እኔም የሶርያ ዕፃ ከምትሆን ከመስጴጦምያ ተነስቼ ኤፍራታ ለመድረስ የኤፍራታ ዕጣ በምትሆን ፈረስ በሚገሩበት ሜዳ በደረስኹ ጊዜ በጉዳና ሳለሁ እናትህ ራኄል ሞተች ፤



ወቀበርክዋ ውስተ ፍኖት ዘምርዋጸ አፍራስ ዘስሙ ቤተልሔም ፤

ቤተልሔም በሚባል ፈረስ በሚገሩበት ጎዳና አጠገብ ቀበርኳት ፤ (ሐተታ) ስለምን አነሣት ቢሉ ፤ ጣዖት ታመልክ ነበርና ፤ የሷን ግብር አትያዝ የኔን ግብር ያዝ ሲል ፤ አንድም ካልሆነ ስፍራ ተቀብራ ነበርና (አምጥተህ) አፍልሰህ ከእኔ ዘንድ ደርባት ሲል ፤ አንድም ይወዳት ነበርና የናፍቆት አነጋገር፤ ሰው ሲሞት የሚወደውንም የሚጠላውንም ማንሳት ልማዱ ነውና ፤

፰፡ ወሶበ ርእየ እስራኤል ደቂቆ ለዮሴፍ ወይቤሎ ምንትከ እሉ ፤

እስራኤል የዮሴፍን ልጆች በአየ ጊዜ ፤ እኒህ ምኖችህ ናቸው አለው ፤

፱፡ ወይቤሎ ዮሴፍ ለአቡሁ ደቂቅየ፤ ዘወሀበኒ እግዚአብሔር በዝየ ፤

ዮሴፍ አባቱን በግብጽ እግዚአብሔር የሰጠኝ ልጆቼ ናቸው አለው ፤

ወይቤሎ ያዕቆብ አምጽኦሙ ኀቤየ ከመ እባርኮሙ ፤

ያዕቆብ እመርቃቸው ዘንድ ወደ እኔ አቅርብልኝ አለው ፤

፲፡ ወአዕይንቲሁሰ ለእስራኤል ከበዳ ወተከድና እምርስዕ ፤

ያዕቆብ እንዲህ ማለቱ ዓይኖቹ ከዕርግና የተነሣ ከማየት ተገተው ነበርና ስለዚህ ነው ፤

ወኢይክል ከሚዶተ ወነጽሮ ፤

ዓይኑን ገልጦ ማየት አይቻለውም ነበር ፤

ወአቅረቦሙ ኀቤሁ ወሰዓሞሙ ወሐቀፎሙ ፤

ዮሴፍም ወደሱ ቢያቀርብለት ያዕቆብ አቅፎ ሳማቸው ፤

፲፩፡ ወይቤሎ እስራኤል ለዮሴፍ ፤ ናሁ ኢተፈለጥኩ እምገጽከ ፤

እስራኤል ዮሴፍን ሞተ ካሉኝ ጀምሮ አንተን ከማሰብ አልተለየሁም ፤ አንድም አለ ካሉኝ ጀምሮ አንተን አያለሁ ከማለት አልተለየሁም ነበር አለው፤

ወናሁ ዘርአከኒ አርአየኒ እግዚአብሔር ፤

ስንኳን አንተን እነሆ እግዚአብሔር ልጆችህን አሳየኝ አለው ፤

፲፪፡ ወአውፅኦሙ ዮሴፍ እማዕከለ ብረኪሁ ፤

ዮሴፍም ልጆቹን ከያዕቆብ ከጉልበቱ መካከል አውጥቶ ፤

ወሰገደ ሎቱ በገጹ ውስተ ምድር፤

በግምባሩ ከምድር ወድቆ ሰገደለት ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፫፤ ወነሥኦሙ ዮሴፍ ለ፪ቱ ደቂቁ፣
ዮሴፍም ሁለቱን ልጆቹን አም ጥቶ ፤

ወአቀሞ ለኤፍሬም በየማኑ ኀበ ፀጋመ እስራኤል ፣
ኤፍሬምን በእሱ ቀኝ፣ በእስ ራኤል ግራ ፤

ወለምናሴ አቀሞ በጸጋሙ ኀበ የማነ እስራኤል፤ ወአቅረቦሙ ኀበ አቡሁ፣
ምናሴን በእሱ ግራ ፣ በእስራ ኤል ቀኝ አቁሞ ወደ አባቱ አቀረባቸው ፤

፲፬፤ ወሰፍሐ እስራኤል እዴሁ እንተ የማን፣ ወአንበረ ላዕለ ርእሰ ኤፍሬም፣
እስራኤል ቀኝ እጁን በኤፍ ሬም ራስ ላይ ጫነበት ፤

ወውእቱ ይንእስ እምእኁሁ ፣
ይኸውም የወንድሙ የምናሴ ታናሽ ነው ፤

ወእዴሁ እንተ ጸጋም አንበረ ላዕለ ርእሰ ምናሴ ፣
ግራ እጁን በምናሴ ራስ ላይ ጫነበት ፤

ወአስተኃለፈ እደዊሁ ፣
እንዲህ አድርጎ እጁን አስተ ላልፎ ጫነባቸው ፤

፲፭፤ ወባረኮሙ ወይቤ ውእቱ እግ ዚአብሔር ዘአሥመርዎ አበውየ ቅድ ሜሁ አብርሃም ወይስሐቅ ፣
አባቶቼ አብርሃም ይስሐቅ በሕግ ጸንተው ያገለገሉት እግዚአብ ሔር ፤

ወእግዚአብሔር ውእቱ ዘሐፀነኒ ወሴ ሰየኒ እምንዕስየ እስከ ዛቲ ዕለት ፣
ከሕፃንነቴ ጀምሮ እስከዚች ቀን ድረስ ያሳደገኝ የመገበኝ እግ ዚአብሔር ፤

፲፮፤ ወመልአከ እግዚአብሔር ዘአድ ኃነኒ እምኵሉ እኩይ ፣
መልአኩን ሰዶ ከመከራውም ሁሉ ያዳነኝ ፤

ውእቱ ለይባርኮሙ ለእሉ ሕፃናት ፣
እሱ እኒህን ሕፃናት ያክብራ ቸው ፤

ወይሰመይ ስምየ ቦሙ ፣
ስሜ በእነሱ ይጠራ ፤

ወስመ አበውየ አብርሃም ወይስ ሐቅ ፣
የአባቶቼም የአብርሃምና የይ ስሐቅ ስም በእነሱ ይጠራ ፤

ይብዝኁ ወይትባዝኁ ወይምልኡ ዲበ ምድር ፣
ብዙ ፣ የብዙ ብዙ ሆነው በም ድር ይምሉ፣ ብሎ መረቃቸው፤

፲፯፤ ወሶበ ርእየ ዮሴፍ ፣ ከመ አን በረ እዴሁ እንተ የማን ላዕለ ርእሰ ኤፍሬም ፤ ወእንተ ጸጋም ላዕለ ርእሰ ምናሴ ፣
ዮሴፍም አባቱ ቀኝ እጁን በኤፍሬም ራስ ላይ፣ ግራ እጁን በምናሴ ራስ ላይ እንደጫነ ባየ ጊዜ ፤



፲፰፤ ወይቤሎ ዮሴፍ ለአቡሁ አኮ ከመዝ አባ ፣
አባቱን አባቴ ነገሩ እንዲህ አይደለም አለው ፤

እስመ ዝንቱ በኵርየ አንብር እዴከ እንተ የማን ላዕሌሁ ፣
ያላወቀው መስሎት የበኵር ልጄ ይህ ነውና ቀኝ እጅህን በእሱ ላይ ጫንበት እንጂ አለው ፤

፲፱፤ ወይቤሎ እስራኤል አአምር ወልድየ አአምር ፣
እስራኤልም ልጄ አላወቅሁም መስሎህ ነው ? አውቃለሁ አለው ፤

ዝኒ ይከውን ሕዝበ ዐቢየ ፣
ይህም ደግ ወገን ይሆናል ፤ (ሐተታ) ይከውን ሕዝበ ዐቢየ አለ ፣ እለ ጌዴዎን ከእሱ ይወ ለዳሉና ፤

አላ እኁሁ ዘይንዕስ የዐብዮ ፣
ነገር ግን ታናሽ ወንድሙ ይበ ልጠዋል ፤ (ሐተታ) መስፍኑ ኢያሱ ፤ ኢዮርብአም ንጉሡ ፣ ከእሱ ይወለዳሉና ፤

ወዘርዑ ብዙኃ አሕዛበ ይከውን ፣
ልጁ የልጅ ልጁ ብዙ ወገን ይሆናል ፤

፳፤ ወባረኮሙ በይእቲ ዕለት ፣
በዚህች ቀን እንዲህ ብሎ መረ ቃቸው ፤

ወይቤ ብክሙ ይትባረክ እስራኤል፣
እስራኤል በእናንተ ምክንያት ይክበር ይታወቅ አለ ፤ አን

ድም አምላከ እስራኤል ይላል፣ የእስራኤል ፈጣሪ በእናንተ ምክ ንያት ይክበር ይገለጽ ፤

ወይበሉ ይባርከ እግዚአብሔር ከመ ኤፍሬም ወምናሴ ፣
ኤፍሬምንና ምናሴን እንደ አከበረ እግዚአብሔር ያክብርህ እያሉ ይመራረቁባችሁ አላ ቸው ፤

፳፩፤ ወይቤሎ እስራኤል ለዮሴፍ ፣
እስራኤልም ዮሴፍን እንዲህ አለው ፤

ናሁ አነ እመውት ወየሃሉ እግዚአ ብሔር ምስሌክሙ ፣
እነሆ እኔ እሞታለሁ፣ እግዚአ ብሔር በረድኤት ከእናንተ ጋራ ይኑር ፤

ወየግብዕክሙ ውስተ ምድረ አበዊ ክሙ ፣
ወደ አባቶቻችሁ አገር ተመልሶ ለመግባት ያብቃችሁ ፤

፳፪፤ ወአነ እሁበከ ምህርካ ሠናየ ዘይኄይስ እምአኃዊከ ዘነሣእኩ እም እዴሆሙ ለአሞሬዎን በቀስትየ ወበ ኲናትየ ፣
እኔም ከአሞሬዎን እጅ በጦሬ በፍላፃዬ ያመጣሁትን ከወንድ

www.ethiopianorthodox.org

ሞችህ የሚበልጥ ያማረ የተወደደ ምርኮ ሰቂማን እሰጥሃለሁ ፤ (ሐተታ) የወገማ ስም ያንና ሌዊ አይደሉም ? ምነው ዘነማእክዋ በቀስትየ አለ ቢሉ ፣ የልጆቹን ለስ ሰጥቶ ተናገረ ፣ መጽሐፍ የአንዱን ለአንዱ ሰጥቶ መናገር ልማዱ ነው ፤ እስመ ሕዝበ እግዚአብሔር ገብሩ ለዛቲ ኃጢአት እንዲል ፤ አንድም ያዕቆብ ሁሉን ያበላል ያጠጣልና ሁሉ ይወደው ነበር፤ ሰብአ ሰቂማ አንተን ሊወጉህ ነው ብለው ነገሩት ፣ ድንገት አደጋ ጥሎ አጥፍቷቸዋልና ዘነማእክዋ በቀስትየ አለ ፣ ይኸውም ምሳሌ ነው ፤ ያዕቆብ የአዳም ፣ ዮሴፍ የወልደ እግዚአብሔር፣ ያዕቆብ ዮሴፍ እስኪመጣ ድረስ መድከሙ ፣ ጌታ እስኪወለድ ድረስ አዳምን ድካመ ነፍስ የማግኘቱ ምሳሌ፣ ኋላ ያዕቆብ ዮሴፍ መጣ ባለት ጊዜ ተጽናንቶ መነሣቱ፣ ጌታ በተወለደ ጊዜ አዳም ጽንዓ ነፍስ አግኝቶ የመዳኑ ምሳሌ ነው ።

## ምዕራፍ ፵ወ፱

### ግባኤ

፩፡ ወጸውዖሙ ያዕቆብ ለደቂቁ ወይቤሎሙ ተጋብኡ ነቢየ ፣ ወአየድዓክሙ እንተ ትረክበክሙ በደኃሪ መዋዕል ፣

ያዕቆብም ልጆቹን ጠርቶ፤ በኋላ ዘመን የምታገኛችሁን መከራ እነግራችኋለሁና ወደ እኔ ተሰብሰቡ አላቸው ፤

፪፡ ወተጋብኡ ወመጽኡ ደቂቁ ለያዕቆብ ፣

የያዕቆብም ልጆች ተሰብስበው መጡ፤ (ሐተታ) አበ ማኅበርም ቢሆን ፤ ኤጲስቆጶስም ቢሆን ፣ በጊዜ ሞቱ ያወገዘውን ፈትቶ፣ የተጣላውን ታርቆ ፣ የሚረግመውን ረግሞ ፤ የሚመርቀውን መርቆ ፤ የሚያወርሰውን አውርሶ ፣ የበቃ ቢሆን መጻእያትን ተናግሮ እንዲሞት ፤ ያዕቆብም የሚረግመውን ረግሞ፣ የሚመርቀውን መርቆ ፤ የሚታረቀውን ታርቆ ፣ የሚያወርሰውን አውርሶ ፣ መጻእያትን ተናግሮ ሙቷል ፤

ወይቤሎሙ ስምዕዎ ስምዕዎ ለአቡክሙ ፣

እኔ አባታችሁ የምነግራችሁን እስተውላችሁ ስሙኝ ስሙኝ አላቸው ፤

፫፡ ሮቤል ወልድየ ኃያል ውእቱ ፣

የበኵር ልጄ ሮቤል ባለአእምሮ ነበረ ፣ ዮሴፍን አትግደሉት ብሎ ነበርና ፤



ዘቀዳሚ በኵርየ ፣

የመጀመሪያው የበኵር ልጄ ሮቤል፣ ዘቀዳሚ አለ፣ ኋላ ብኵርናው ለይሁዳ ሁኗልና ፤

እኩየ ኮነ ፣

ክፉ ኾነ ፤

ወእግዚፈ ክሣዱ፣

ክሣደ ልቡናውን አጸና ፤

ወዕፁበ ገብረ ፣

ጭንቅ ነገርን አደረገ፤ ዕፁበ ገብረ አለ ፣ ከእሱ በቀር ከአባቱ ዕቅብት የደረሰ የለምና ፤

፬፡ ቄረ ከመ ማይ ፣

ይቀሩርር ከመ ማይ ሲል ነው፤ ሙቀተ ጸጋ አያግኝ ፤

እስመ ዐርገ ዲበ ምስካበ አቡሁ ፣

ከእኔ ከአባቱ ዕቅብት ከባላ ደርሷልና ፤

ወአርኰሰ ለውእቱ ምስካበ ይእተ አሚረ ዘዲቤሁ ዐርገ ፣

እኔ ከተኛሁበት ምንጣፍ በተኛ ጊዜ አሳድፎታልና፣ ማለት እኔ ከደረስኹባት ሴት በደረሰ ጊዜ፣ ሕግን አፍርሷልና ፤ አንድም ሮቤል ወልድየ ርእሰ ጥብዓንየ ጸነ ከመ ማይ ጊዜ ስቅየተ ምድር ወባሕቱ ይኀድር ጸጋ እግዚአብሔር ላዕሌሁ፣ እስመ ገብረ ምሕረተ ላዕለ ዮሴፍ ወልድየ የሚል አብነት ይገኛል ፤ በሕፃንነቴ የወለድኹት ልጄ ሮቤል ፣ አንድም ፤ ጨክኜ የረገምኹት ልጄ ሮቤል፣ ምድር ውሀ በምትጠማበት ጊዜ፣ ውሀው እንዲያዘነብል ወደ ኃጢአት አዘነበለ ፤ ነገር ግን ጸጋ እግዚአብሔር ይደርበት ፤ ለልጄ ለዮሴፍ በጎ ነገርን አድርጓልና፣ የአባት ርግማን እንዲጎዳ ሲያጠይቅ እንዲህ ብሎ በረገመው ጊዜ አጥንቱ ጠቁሯል፤ የአባት ምርቃንም እንዲጠቅም ኋላ ሙሴ ይሕየወኒ ሮቤል ወኢይሙተኒ ብሎ በጸለየ ጊዜ በሁለት መቶ ሦስት ዘመን አጥንቱ ነጥቷል ፤ አንድም ሮቤል በኵርየ ብለህ መልስ ፣ በዓለ አእምሮ የነበረ እስራኤል ኦሪትን ተቀብሏልና ወልድየ ዘበኵርየ ያልሁት እስራኤል መጀመሪያ የበኵር ልጅ እንዲወደድ፣ የወደድኹት እስራኤል ዘቀዳሚ አለ ፣ ኋላ ብኵርናው ለአሕዛብ ሁኗልና ክፉ ሆነ ፤ ፈጣሪውን ገደለ ፤ ጭንቅ ነገር አደረገ ፤ ፈጣሪውን የገደለ ከእሱ በቀር ሌላ የለምና፣ አብየሥራት ሕገ ኦሪትን አፍርሷልና ፣ ጸንቶባት ይኖር የነበረ ሕገ ኦሪትን አፍርሷልና፤ ምነው ኦሪትንማ ይፈጽሟታል እንጂ ያፈርሷታል ? ቢሉ ፤ ኦሪት

www.ethiopianorthodox.org

**ሎቱ ስምዕዎ ትላለች ያነን አያምኑላትምና ፤**

፭፡ ስምዖን ወሌዊ አኃው እሙንቱ ፈጸምዋ ለዓመፃ ፤

**ወንድማማቾች የሚሆኑ ስምዖንና ሌዊ ሰብአ ሰቂማ የጀመሯትን ዓመፅ ጨረሷት ፤**

በቃህምሙ ወበኵናቶሙ ፤

**በክፉ ፍከራቸው በጦራቸው ፈጸሟት ፤**

፮፡ ነፍስየ ኢትትራከቦሙ ፤

**ሰውነቴ በበረከት አትገናኛቸውም ፤ ትትራከቦሙ ቢል በመርገም ትገናኛቸው ፤**

ወኢይረድ ውስተ ሁከቶሙ ፤

**ሁከተኞች በመሆናቸው ምክንያት በረከት አይደርባቸው ፤**

እስመ በመዓቶሙ ቀተሉ ሰብአ ፤

**ተቈጥተው ሰብአ ሰቂማን ገድለዋልና ፤**

ወበፍትወቶሙ መተሩ ሥርወ አህጉር ፤

**በክፉ ፈቃዳቸው የሀገር ቀንድ የሚሆኑ ሴኬምንና ኤሞርን ገድለዋልና ፤**

፯፡ ርጉመ ለይኩን መዓቶሙ ፤

**ቍጣቸው መርገምን ያምጣባቸው ፤**

እስመ ኢገገጹ እምቍጥአሆሙ ወኢተመይጡ እመዓቶሙ ፤

**ከመዓታቸው አልተመለሱም ከቍጣቸውም ተግ ተግ አላሉምና ፤**

እከፍሎሙ ውስተ ያዕቆብ ወእዘርዎ ውስተ እስራኤል ፤

**ርስታቸውን በሁለቱ ነገድ እከፍለዋለሁ ፤ በዐሥሩ ነገድ እበትነዋለሁ ፤ ይኸውም አልቀረ ለስምዖን ዕጣ አንሶታል፤ ለሌዊ ቀርቶበታል ፤ ወበእንተዝ ተኃርየ ዘርዓ ሌዊ ለክህነት እንዲል ፤ በዚህስ ዕዳ አላደረገባቸውም ብሎ በበጎ ያወርዱታል፤ አንድም ወንድማማቾች የሚሆኑ ስምዖንና ሌዊ ሰብአ ሰቂማ የጀመሯትን ዓመፅ ፈጸሟት ፤ በበጎ ፍከራቸው በጦራቸው ፈጸሟት ፤ ልቡናዬ በመርገም አትገናኛቸውም ፤ በሁከታቸው ምክንያት መርገም አይምጣባቸው ፤ ተቈጥተው ሰብአ ሰቂማንን ገድለዋልና ፤ ምንም ቢገድሉ በበጎ ፈቃዳቸው የሀገር ቀንድ ሴኬምንና ኤሞርን ገድለዋልና ፤ ምንም ቢገድሉ ቁጣቸው መርገምን አያምጣባቸው ከቁጣቸው አልተመለሱምና ፤ ምንም ባይመለሱ ዕዳም ቢልባቸው**



**በዐሥሩ ነገድ እንነሳነሳታለን፤ በሁለቱ ነገድ እንተናተናታለን፤**

**እስመ ሕዝበ እግዚአብሔር ገብራ ለዛቲ ኃጢአት እንዲል፤ አንድም ወንድማማቾች የሚሆኑ ጸሐፍት ፈሪሳውያን አባቶቻቸው የጀመሩትን ዓመፅ ፈጸሟት ፤ ነቢያትን መግደል መጀመር ነው ፤ የባሕርይ አምላክ ክርስቶስን መግደል መፈጸም ነውና ፤ በክፉ ፉከራቸው በጦራቸው ፈጸሟት ፤ ምነው የወጋው አንድ ሐራዊ አይደለም ? ቢሉ ፤ መጽሐፍ ምሥጢር ይጠነቅቃል እንጂ አንድና ብዙ አይጠነቅቅምና ፤ አንድም ፈቃድ የሁሉ ከሆነ ብሎ ፤ አንድም መውጋት በጦር ብቻ ነው ? በቀኖትም ወግተውታልና ፤ ልቡናየ በበረከት አትገናኛቸውም ፤ በሁከታቸው ምክንያት በረከት አይደርባቸው ፤ ተቈጥተው ክርስቶስን ገድለዋልና ፤ በክፉ ፈቃዳቸው በኵረ ምእመናን ጌታን ገድለዋልና፤ ቍጣቸው ርጉም ይኹን ማለት ፤ መርገም ያምጣባቸው፤ ከቍጣቸውም አልተመለሱምና ፤ ይኸን ርስታቸውን በዐሥሩ ነገድ ፤ በሁለቱ ነገድ ፤ እከፍለዋለሁ እበትነዋለሁ ፤**

፰፡ ይሁዳ ይሴብሑከ አኃዊከ ፤

**ይሁዳ ወንድሞችህ ያመሰግኑሃል ፤**

እደዊከ ላዕለ ዘባኖሙ ለጸላእትከ ፤

**ሥልጣንህ በጠላቶችህ ላይ ነው፤**

ይሰግዱ ለከ ደቂቀ አቡከ ፤

**የአባትህ ልጆች ይገዙልሃል ፤**

፱፡ ይሁዳ ዕጓለ አንበሳ እምኀዘአትከ ዕርግ ወልድየ ፤

**የአንበሳ ግልገል ደስ እንዲያሰኝ ፤ ደስ የምታሰኝ ይሁዳ ፤ ከከተማህ ውጣ ፤**

ሰከብከ ወኖምከ ከመ አንበሳ ወከመ ዕጓለ አንበሳ ፤ አልቦ ዘያነቅሐከ ፤

**አባት አንበሳ፤ የአንበሳ ግልገል ሥጋውን በልቶ ደሙን ጠጥቶ በመደቡ በተኛ ጊዜ ፤ የሚቀሰቅሰው እንደሌለ ፤ አንተም አሕዛብን ወግተህ፤ ዘርፈህ ከከተማህ ገብተህ ተቀመጥህ፤ አልቦ ዘያነቅሐከ ማንሻ ፤ አንድም አባት አንበሳ ፤ የአንበሳ ግልገል ፤ ሥጋውን በልቶ ደሙን ጠጥቶ በተኛ ጊዜ የሚቀሰቅስ ሰው እንደሌለ ፤ አንተም አሕዛብን ወግተህ፤ ዘርፈህ ከከተማህ ገብተህ በተቀመጥህ ጊዜ፤ የሚቀሰቅስህ የለም ፤ አንድም ሰከብከ ወኖምከ ከመ አንበሳ ወከመ ዕጓለ አንበሳ አልቦ ዘያነቅሐከ**

www.ethiopianorthodox.org

ብሎ ማካፈል ነው ፤ ትርጓሜው አንድ ነው ፤

፲፤ ኢይጠፍእ ምልክና እምይሁዳ ፣

ከይሁዳ አገዛዝ አይጠፋም ፤

ወምስፍና እምአባሉ ፣

ምስፍናም ከወገኑ አይጠፋም፤

እስከ አመ ይረክብ ዘጽኑሕ ሎቱ ፣

ደጅ የሚጸናውን መንግሥቱን እስኪያገኝ ድረስ ፤

ወውእቱ ተስፋሆሙ ለአሕዛብ ፣

የአሕዛብም አለኝታቸው እሱ ነው ፤

፲፩፤ የአሥር በዓጸደ ወይን ዕዋሎ ፣

በወይን ሐረግ ውርንጫውን ያሥራል ፤

ወበዕፀ ዘይት አድጎ ፣

አህያውን በዘይት ዕንጨት ያሥራል ፤

ወየሐጽብ በወይን አልባሲሁ ፣

ልብሶቹንም በወይን ያጥባል ፤ አንድም በወይን ልጠብ ቢል አያጣም ፤

ወበደመ አስካል ሰንዱኖ ፣

ቀሚሱንም በዘለላው ደም ያጥባል ፣ ልጠብ ቢል አያጣም ፣ ባለጸግነቱን መናገር ነው ፤

፲፪፤ ፍሡሐት አዕይንቲሁ እምወይን ፣

ዓይኖቹ ከወይን ይልቅ ደስ ያሰኛሉ ማለት ዓይነ መልካም ነው ፤

ወፀዓዳ ከመ ሀሊብ ስነኒሁ ፣

ጥርሶቹም እንደ ወተት ነጭ ናቸው ማለት ጥርሰ መልካም ነው ፤ አንድም ይሁዳ ይሴብሑከ አኃዊከ ብለህ መልስ ፤ ክርስቶስ ወንድሞችህ ምእመናን ያመሰግኑሃል፣ ሥልጣንህ በጠላቶችህ በአጋንንት ላይ ነው ፤ የአባትህ ልጆች ምእመናን ይሰግዱልሃል ፤ ዕጓለ አንበሳ ክርስቶስ ከመቃብር ተነሥ፣ ሰከብከ ወኖምከ ከመ አንበሳ፣ አባት አንበሳ በመደቡ እንዲተኛ፣ ሦስት መዓልት፣ ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አደርክ ፤ ወከመ ዕጓለ አንበሳ ተንሥእከ ያለበት ነው ፤ አንበሳ በተወለደ ጊዜ ሦስት ቀን እንሳሕስሖ ጠፍቶበት ይሰነብታል፣ (ያድራል) በሦስተኛው ቀን አባቱ ጣሕሩን ያሰማዋል ይነሣል፤ ጌታንም አበሁ አንሥኦ እንዲል፣ በሦስተኛው ቀን ተነሥቷል ፤ ከጌታ የባሕርይ አገዛዝ ከወገኖቹ ከምእመናን የጸጋ አገዛዝ አይጠፋም፣ ደጅ የሚጠናው (የሚጠብቀው) ድኅ



ነተ ምእመናንን እስኪያገኝ ድረስ ፤ በእንተ ፍሥሐሁ ዘጽኑሕ ሎቱ እንዲል ፤ የአሕዛብ መምህራቸው እርሱ ነው ፤ በኦሪት ያልተገዘሩ አሕዛብን በደሙ ያድናል ፤ በኦሪት የተገዘሩ እስራኤልን በመስቀል ያድናል ፣ ምእመናንን በጥምቀት ያነጻል፤ በሥጋው በደሙም ያከብራል ፣ ዓይኖቹ ነቢያት ደስ ያሰኛሉ ፤ ሐዋርያትም ደስ ያሰኛሉ ፤

፲፫፤ ዛብሎን ሰዑኖ የኃድር ከመ መርሶ አሕማር ፣

ዛብሎን ከወደብ የተጠጋ መርከብ ለጠላት እንዳይመች ፣ ጠላቶቹን አድክሞ በጸጥታ ይኖራል ፤ ሳዕኖ ቢል ጫማውን አገዞ ይኖራል ፤

ወይሰፍሕ እስከ ሲዶና ፣

ግዛቱም እስከ ሲዶና ድረስ ይደርሳል ፤ አንድም ዛብሎን ክርስቶስ ፣ መርከብ በውሃ እንዲከበብ ፣ በአጋንንት በመናፍቃን ተከብቦ ሳለ ጠላቶቹን አድክሞ ይኖራል ፤ ሳዕኖ ቢል ሕገ ወንጌልን ያስተምራል ፣ ተስዒነክሙ ኃይለ ወንጌል ዘበሰላም እንዲል ፣ እስከ ሲዶና ድረስ ያስተምራል ፤

፲፬፤ ይሳኮር ፈተዋ ለሠናይት ፣

ይሳኮር እርሻ ቁፋሮን ወደዳት፣ ሠናይት አላት ከሁሉ እርሻ ቁፋሮ ትበልጣለችና ፤

ወየአርፍ ማዕከለ መዋርስት ፣

በወረሾች በሰብአ ከነዓን መካከል ይኖራል ፤

፲፭፤ ወሶበ ርእየ ከመ ሠናይት ይእቲ ዕረፍት ፣

እርሻ ቁፋሮ ደግ እንደሆነች ባየ ጊዜ ፤

አትሐተ መትከፍቶ ከመ ይትቀነይ ለምድር ፣

ምድርን ያርሳት ይቈፍራት ዘንድ ትከሻውን ዝቅ ዝቅ አደረገ ፤

ወኀመወ ወኮነ ሐረሳዌ ብእሴ ፣

በማረስ በመቈፈር ደከመ ፣ ገባርም ሆነ ፤ አንድም ይሳኮር ፈተዋ ለሠናይት ብለህ መልስ፤ ይሳኮር ክርስቶስ ድኅነተ ዓለምን ወደዳት ፣ በምእመናን አድሮ ባቸው ይኖራል ፤ ድኅነተ ዓለም ደግ እንደሆነች በአየ ጊዜ መስቀልን ይሸከም ዘንድ ትከሻውን ዝቅ ዝቅ አደረገ ፣ ደካማ ሰው ሆነ ፤ አንድም ምሳሌ ዘርን አስተማረ ፤ አንድም ሐራሲ በዕርፈ መስቀል ተባለ ፤

www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

፲፮፡ ዳን ይኴንን ሕዝበ ከመ አሐቲ እምነገደ እስራኤል ፤

ከነገደ ዳን የተወለደ ሶምሶን ፤ ከአሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ከሆነ ከነገደ ይሁዳ ተወልደው፤ ዳዊት ሰሎሞን እንዲገዙ ይገዛል ፤ አንድም ከአሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል የተወለደች ዲቦራ እንድትገዛ ይገዛል ፤

፲፯፡ ኮኖ ለዳን አርዌ ምድር ዘይጸንሕ ውስተ ፍኖት ፤

ሶምሶን በየኼደበት የሚያስተው ምክረ ደሊላ ተሰጠው ፤

ዘይነስኮ ሰኰናሁ ለፈረስ ፤

ሰኰና ልቡናውን የሚያስተው ምክረ ደሊላ ተሰጠው ፤

ወይወድቅ ዘይፄዓኖ ድኅሬሁ ፤

ያደረበት ረድኤተ እግዚአብሔር ይለየዋል ፤

፲፰፡ ወይጸንሕ ከመ ያድኅኖ እግዚአብሔር ፤

እግዚአብሔር ያድነው ዘንድ ይጠብቀዋል ፤ በኋላ ጠገሩ አድጐለት ኢሎፍላውያንን አጥፍቷልና ፤ አንድም ዳን ይኴንን ሕዝበ ብለህ መልስ ፤ ከነገደ ዳን የተወለደ ሐሳዊ መሢሕ ሕዝቡን ሁሉ ይገዛል ፤ ከዐሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ከነገደ ይሁዳ የተወለደ ጌታ እንዲገዛ ይገዛል ፤ ለሐሳዊ መሢሕ በየሔደበት ሰኰና ልቡን የሚያስተው ምክረ ሰይጣን ተሰጠው ፤ ያደረበት እግዚአብሔር ይለየዋል ፤ አድሮበት ይለየዋል ማለት አይደለም፤ ጥንቱን ሰው መፈጠሩ ማኅደረ እግዚአብሔር ሊሆን ነውና ፤ ኋላ ያድነው ዘንድ ይጠብቀዋል ፤ ዕልፍ ወእስራ ምዕት እለ እምውስተ ሕዝበ ዳን የሚላቸው አሉና ፤

፲፱፡ ጋድ ፈያት ፈየትዎ ፤

ለጋድ ሲል ነው፤ ጋድን ወንበዴዎች ቀሙት ፤

ወውእቱሂ ፈየቶሙ ተሊዎ ዐሠሮሙ ፤

እሱም ፍለጋቸውን ተከትሎ ቀማቸው ፤ ሲቀሙት ሲቀማ ይኖራል ፤ አንድም ጋድ ፈያት ፈየትዎ ብለህ መልስ፤ ጌታን በመባሕተ መኑ ትገብር ዘንተ ብለው ጠየቁት ፤ እሱም ነገራቸውን ተከትሎ ምላሽ አሳጣቸው ፤ ጥምቀቱ ለዮሐንስ እም አይቴ ይእቲ ብሎ ቢጠይቃቸው አናውቅም ብለዋል ፤ አንድም አጋንንት አዳምን ቀሙት ጌታ ፤ ግብራቸውን ተከትሎ ድል ነሣቸው ፤ ዲያብሎስ አዳምን በሥጋ ከይሲ ተሠውሮ ቢያስተው ጌታ በሥጋ ብእሲ ተሠውሮ ድል ነሥቶታልና ፤



በተሠውሮተ ቃለ እግዚአብሔር በዘመድነ እንዲል ፤

፳፡ አሴር ጽጉብ እክል ፤

አሴር እህል የጠገበ ነው ፤

ወውእቱ ይሁብ ሲሳየ ለመላእክት ፤

እሱ ለአለቆች በአዳራሽ ይገኛል ፤ አንድም አሴር ጽጉብ እክል ብለህ መልስ ፤ ክርስቶስ እክለ ትምህርትን የሚያጠግብ ነው ፤ ወውእቱ ይሁብ ፤ ሐዋርያ ያስተምራል፤ ሲሲተ ልብ ቃላቲሁ ለእግዚአብሔር እንዲል፤ ጌታ ሥጋውን ደሙን ይሰጣል ፤

፳፩፡ ንፍታሌም በቀልት ዕፍረት እንተ ትሤኒ አውዕአት እክለ ፤

ለንፍታሌም ሲል ነው ፤ እንደ ዘንባባ ልዑል የሆነ ፤ እንደ ሽቱ የምትወደድ የንፍታሌም ሀገሩ እኽልን አስገኘች ፤ አንድም ምጡቀ ባሕርይ የሚሆን ሐዋርያ ክርስቶስ ሽቱ እንድ ትወደድ የምትወደድ ሰውነቱ እክለ ትምህርትን አስገኘች ፤

፳፪፡ ወልድ ዘይልሕቅ ውእቱ ዮሴፍ፤

ዮሴፍ ከወንድሞቹ በሹመት ፤ በማዕርግ የሚበልጥ ነው ፤

ወልድየ ዘይልህቀኒ ፤

ልጄ ዮሴፍ በሹመት የሚበልጠኝ ነው ፤

ወዘይቀንዕ ሊተ ፤

ለእኔ የሚቀናልኝ ፤ ዘይቀንዕ ሊተ አለ ፤ ሠረገላ ሰድዶለታልና ፤

ወልድየ ወሬዛ ዘይገብእ ኀቤየ ፤

ሞተ ካልሁ በኋላ ያገኘሁት ልጄ ጽኑዓ አእምሮ ነው ፤

፳፫፡ እለ ጸአልዎ በምክሮሙ ፤

ለእለ ጸአልዎ ሲል ነው ፤ ኩብ ላይ ባሪያ ብለው የሰደቡት ፤

ወኮንዎ አጋዕዝተ ፤

ጌቶች የሆኑት ማለት ፤ ባሪያ ብለው የሸጡት ፤

ወነደፍዎ ፤

በቀስተ ምክራቸው የወጉትም ፤

፳፬፡ ወተቀጥቀጡ አቅስስቲሆሙ በኃይል ፤

ይትቀጥቀጥ ሲል ነው ፤ በሐፀ ምክራቸው የወጉት ቀስተ ምክራቸው ይጥፋ ፤

ወደክመ ሥርወ መዝራዕተ እደዊሆሙ ፤

ይድከም ሲል ነው ፤ ሥልጣናቸው ይጥፋ ፤

በእደ ኃይሉ ለያዕቆብ ፤

በቃለ ጸሎቱ ለያዕቆብ ሲል ነው ፤ በኔ በያዕቆብ ጸሎት ፤ አንድም ወልድ ዘይልሕቅ ውእቱ ብለህ መልስ እንደ አምላክነቱ

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

በክብር በዘመን ከሁሉ የሚበልጥ ክርስቶስ ፣ እኩብር አይል ክቡር ፣ እጸድቅ አይል ጻድቅ የባሕርይ አምላክ በሰውነቱ ሕማምን ሞትን ተቀብሎ የሚያድነኝ ነው ፤ በትንሣኤ በካሣ ወደኔ የሚመለስ ክርስቶስ ኃያል አምላክ ነው ፤ ዕሩቅ ብእሲ ብለው የሰደቡት፣ ዝንቱ ድልው ለሞት ብለው የፈረዱበት ፣ አይሁድ የወጉት አለ ፣ ሐተታው እንዳለፈው ነው ፤ ምክራቸው ሥልጣናቸው ይጥፉ ፤ በእደ ኃይሉ ለያዕቆብ ያለው አይመችም ፤

በህየ አጽንአ ለእስራኤል በኀበ አምላኩ ለአቡከ ፣

አምላከ አቡከ ሲል ነው ፤ የአባትህ ፈጣሪ እስራኤልን በሎዛ፣ በሴኬም አጸናው፤ አንድም እኔ ባለሁበት በከነዓን ፣ አንተም ባለህበት በግብጽ አጸናህ ፤ በኀበ ሀሎከ በኀበ ሀሎኩ ሲል ነው ፤

፳፭፡ ወረድአከ አምላከ ዚአየ ፣

የኔ ፈጣሪ ረዳኸ ፤

ወባረከከ በበረከተ ሰማይ እምላዕሉ ፣

ከምድር በላይ ባለ ከሰማይ በሚገኝ በረከት አከበረኸ ፤

ወበበረከተ ምድር እንተ ባቲ ኵሉ ፣

ሁሉ በሚገኝባት ከምድር በተገኘ በረከት ያክብርህ ፤

በበረከተ አጥባት ወማኅፀን ፣

ከጡት ፣ በማኅፀን በሚገኝ በረከት ያክብርህ ፤

፳፮፡ በበረከተ አቡከ ወእምከ ጽኑዓን ፣

ጽኑዓን ከሚሆኑ ከእናት ከአባትህ በተገኘ በረከት ያክብርህ ፤

እምበረከቶሙ ለአድባር እለ ውዱዳን ፣

ጽኑዓን ሲል ነው ፣ ጽኑዓን ከሚሆኑ ከአብርሃም ከይስሐቅ በሚገኝ በረከት ያክብርህ ፤

ወበረከተ መላእክቲሁ ለእግዚአብሔር የሀሉ ዲበ ርእሱ ለዮሴፍ ፣

እሱን ከሚያገለግሉት ከመላእክት የሚገኝ በረከት በዮሴፍ ላይ ይደር ፤

ወዲበ ርእሶሙ ለእለ ኮነዎ አኃዊሁ ፣

ወንድሞቹ በሚሆኑ ላይ ሁሉ ይደር ፤

፳፯፡ ብንያም ተኵላ መሳጢ ይበልዕ በነግህ ፣

ተኵላ መሳጢ የሚሆን ብንያም በነግህ የሰውን ሁሉ ገንዘብ ይበላል ፤

ወፍና ሠርክ ይሁብ ሲሳየ ፣

በሠርክ በአዳራሽ ይገኛል ፤ አንድም ተኵላ መሳጢ የሚሆን ብንያማዊ ሳኦል በፊት



የሰውን ሁሉ ገንዘብ ይበላል ፤ በሠርክ ለሰው ሁሉ ምግብ ይሰጣል ፣ ሳኦል በፊት እስራኤልን በድሏቸው ነበር፣ ኋላ ግን በጎ ነገር አድርጎላቸዋልና ፤ አዋልደ እስራኤል ብክያ ላዕለ ሳኦል ዘአልበሰክን ለየ ምስለ ሠርጐክን እንዲል ፤ አንድም ብንያማዊ ጳውሎስ በፊት የሰውን ሁሉ ገንዘብ ይበላል ፣ ኋላ ግን ምእመናንን ያስተምራቸዋል ፤ ይሞቅሕ ዕደ ወአንስተ ወይደቢ አብያተ ሰብእ እንዲል ፣ በፊት ምእመናንን ከዋሉበት አላሳድር ፣ ከአደሩበት አላውል እያለ ያውካቸው ነበር ፤ ኋላ ግን አስተዋፅኦ እየተቀበለ የሚረዳቸው ሁኗል፤

፳፰፡ እሉ እሙንቱ ደቂቀ ያዕቆብ ፲ቱ ወ፪ቱ ፣

ዐሥራ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆች እሊህ ናቸው ፤

ወዘንተ ነገረ ነገሮሙ አቡሆሙ ፣

አባታቸው ይህን ነገር ነገራቸው ፤

፳፱፡ ወባረኮሙ ለለ፩ዱ ፩ዱ በከመ በረከቱ ፣

አንዱንም አንዱንም እንደ በረከቱ ማለት እንደሚገባ እንደሚገባ መረቃቸው ፤

ባረኮሙ ወይቤሎሙ ናሁ አሐውር አንሰ ኀበ ሕዝብየ ፣

እነሆ እኔ በሞት ወደ ወገኖቼ እሔዳለሁ ፤

ወቅብሩኒ ምስለ አበውየ ውስተ በዓት እንተ ሀለወት ውስተ ገራህተ ለኤፍሮን ኬጢያዊ ፣

በኤፍሮን እርሻ ውስጥ ባለች ዋሻ ከአባቶቼ ጋራ ቅበሩኝ ፤

፴፡ ውስተ በአተ ካዕበት እንተ አንፃረ ምንባሬ ፣

በዓተ ካዕበት ለማለት ደግሞ ታል ፣ አብርሃም ይቀመጥበት በነበረ አንፃር እጥፍነት ባላት ዋሻ ፤

ውስተ ምድረ ከነዓን እንተ ተሣየጣ አብርሃም እምኀበ ኤፍሮን ኬጢያዊ ለመቃብር ፣

ለመቃብር ሊሆን አብርሃም ከኤፍሮን በገዛት በከነዓን ውስጥ ባለች ዋሻ ውስጥ ቅበሩኝ ፤

፴፩፡ ህየ ቀበርዎ ለአብርሃም ወለሣራ ብእሲቱ ፣

አብርሃምን ከዚያ ቀበሩት ፣ ሚስቱ ሣራንም ከዚያ ቀበሩዋት ፤

ወበህየ ቀበርዎ ለይስሐቅ ወለርብቃ ብእሲቱ ፣

ይስሐቅንም ከዚያ ቀበሩት ፣ ሚስቱ ርብቃንም ከዚያ ቀበሩዋት ፤

www.ethiopianorthodox.org

፴፪፤ ወበህየ ቀበርክዋ ለልያሂ ውስተ በዓተ ገራህት እንተ ተሣየጡ እም ኀበ ደቂቀ ኬጢ ፤

ልያንም ከኬጢ ልጆች በገዟት እርሻ ባለች ዋሻ ውስጥ ቀበር ኋት ፤

፴፫፤ ወአኅለቀ ያዕቆብ አገዘዞቶሙ ለደቂቁ ሰፍሐ እደዊሁ ወእገሪሁ ዲበ ምስካቢሁ ፤

ያዕቆብ ልጆቹን አገዘ ከፈ ጸመ በኋላ እጁን ፤ እግሩን በመኝታው ላይ ዘረጋ ፤ ማለት እራሱን አማዋተ ፤

ወሞተ ወተወሰከ ኀበ ሕዝቡ ፤

ሞተ ከወገኖቹ ተጨመረ ።

## ምዕራፍ ፶

## ገባኤ

፩፤ ወወድቀ ዮሴፍ ቅድመ ገጸ አቡሁ ወበከየ ላዕሌሁ ፤

ዮሴፍ በአባቱ ፊት ወድቆ በላዩ ላይ አለቀሰ ፤

፪፤ ወአዘዞሙ ዮሴፍ ለአግብርቲሁ እለ ይቀርቡ ኀቤሁ ያምዕዝዎ ለአ ቡሁ ፤

ዮሴፍ ወደሱ የሚቀርቡ ባሮ ቹን አባቱን ሽቱ ይቀቡት ዘንድ አዘዛቸው ፤

ወአምዓዝዎ ለእስራኤል እለ ያም ዕዙ ፤

ሽቱ የሚቀቡ ሰዎች እስራኤ ልን ሽቱ ቀቡት ፤ ሐነጥዎ እለ የሐንጡ ይላል አብነት ፤

፫፤ ወፈጸሙ ሎቱ ፵ዓ ጽባሐ ፤

አርባ ቀን እስኪፈጸም ድረስ ሽቱ እየቀቡ አለቀሱለት ፤ (ሐተታ) የአርባ ቀን ፍትሐት አምሳል ነው ፤

እስመ ከማሁ ይኄልቁ መዋዕለ በዘ ያምዕዙ ፤

ሽቱ የሚቀቡበት አርባው ቀን እስኪፈጸም አርባ ቀን እየቈ ጠሩ ይቀቡ ነበርና ፤

ወለሀውዎ ሰብአ ግብፅ ፸ መዋዕለ፤

የግብፅ ሰዎችም ሰባ ቀን አለ ቀሱለት ፤

፬፤ ወእምድኅረ ተፈጸመ መዋዕለ ላሁ ይቤሎሙ ዮሴፍ ለኃያላነ ፈር ዖን ፤

ለመኳንንተ ፈርዖን ሲል ነው ፤ የኃዘኑ ወራት ከተፈጸመ በኋላ ዮሴፍ የፈርዖንን መኳንንት እንዲህ አላቸው ፤

እንዘ ይብል እመ ረከብኩ ሞገሰ በቅድሜክሙ ንግርዎ ለፈርዖን በእ ንቲአየ ፤

በፊታችሁ ባለሟልነትን አግ ኝቼ እንደ ሆነ የእኔን ነገር ለፈርዖን ንገሩት ብሎ ነገሩ



ቸው ፤ (ሐተታ) ምን ባለሟል ቢኾን የራሱን ነገር መናገር አይቻልምና ፤

፭፤ ወበልዎ አቡየ አምሐለኒ ዘእ ንበለ ይሙት ፤ ወይቤለኒ ውስተ መቃብር ዘከረይኩ ሊተ በምድረ ከነዓን ህየ ቅብረኒ ፤

አባቴ ሳይሞት አስቀድሞ በከ ነዓን ለኔ ብዬ ባስቆፈርኩት መቃብር ቅበረኝ እንጂ በሌላ አትቅበረኝ ብሎ አምሎኛል ፤

ወይእዜኒ እዕርግ ወእቅብሮ ለአቡየ ወእግባዕ ፤

አሁንም ሒጄ አባቴን ቀብሬ ልመለስ አለ ብላችሁ ንገሩት አላቸው ፤

፮፤ ወይቤሎ ፈርዖን ዕርግ ወቅብሮ ለአቡከ በከመ አምሐለከ ፤

መኳንንቱም ለፈርዖን ቢነግሩ ለት ፤ ፈርዖን አባትህ እንዳ ማለህ ሒደህ ቀብረህ ተመለስ አለው ፤

፯፤ ወዐርገ ዮሴፍ ይቅብሮ ለአቡሁ፤

ዮሴፍም አባቱን ይቀብር ዘንድ ወደ ከነዓን ወጣ ፤

ወዓርጉ ምስሌሁ ኵሎሙ ደቀ ፈር ዖን ወኵሎሙ ዓበይተ ግብጽ ፤

የግብጽ መኳንንቱም ፤ የፈር ዖን ብላቴኖቹ ሁሉ ከእሱ ጋራ ወጡ ፤

፰፤ ወኵሉ ሰብአ ቤቱ ለዮሴፍ ወኵሉ አኃዊሁ ፤

የዮሴፍ ቤተሰቦቹም ፤ ወንድ ሞቹም ሁሉ ፤

ወኵሉ ሰብአ ቤቱ ለአቡሁ ፤

የአባቱ ቤተሰቦችም ሁሉ ከእሱ ጋራ ወጡ ፤

ወሕፃናቲሆሙሰ ፤ ወአባግዒሆሙ ፤ ወአልሕምቲሆሙ ኀደጉ ውስተ ምድረ ጌሤም ፤

ላሞቻቸውን፤ በጎቻቸውን፤ ልጆ ቻቸውን ግን በጌሤም አው ራጃ ትተው ወጡ ፤

፱፤ ወአዕረገ ምስሌሁ ሠረገላተ ወአ ፍራሰ ፤

ሠረገላዎቹን ፤ ፈረሰኞቹን አስ ከትሎ ወጣ ፤

ወኮነ ትዕይንቶሙ ዐቢየ ጥቀ ፤

ሰፈራቸው እጅግ ብዙ ሆነ ፤

፲፤ ወበጽሑ ኀበ ዓውደ እክል ዘአ ጣታ ዘሀሎ ማዕዶተ ዮርዳኖስ ፤

በዮርዳኖስ ማዶ ካለ ከአጣታ እህል አውድማ ደረሱ ፤

ወበከይዎ ዐቢየ ብካየ ፤

ጽኑዕ ብዙ ልቅሶ አለቀሱለት ፤

ወጽኑዓ ጥቀ ላሀ ገብሩ ለአቡሆሙ ሰቡዓ መዋዕለ ፤

ሰባት ቀን ለአባታቸው እጅግ ጽኑዕ ልቅሶ አደረጉ ፤ የሰባት ቀን ፍታት አምሳል ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወይቤሎ ዮቶር ለሙሴ ሑር በዳኅን፤

ዮቶርም ሙሴን ሒድ በደኅና ይመልስህ አለው፤

፲፱፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ በምድረ ምድያም ነዓ ሑር ብሔረ ግብጽ እስመ ሞቱ ኵሎሙ እለ የኃሥሥዋ ለነፍስከ፤

እግዚአብሔርም ሙሴን በምድያም አገር ሳለ ና ወደ ግብጽ አገር ሒድ አለው፤ ሰውነትህን ለጥፋት የሚፈልጓት ሰዎች ሁሉ ሙተዋልና፤ ሐተታ ይህን ንግ ቀድሞ ነግሮት አልነበረም? ስለምን ደግሞ ተናገረው ቢሉ ነግ ሰልሥት እያለ ቢውልበት ቢያድርበት፤ አንድም ፈርዖንን ወፈቀደ ይቅትሎ ለሙሴ ብሎ ነበርና፤ ሙሴንም ፈርህ ብሎት ነበርና የጠላቶቹን ሞት ከሰማ ደስ እያለው ፈጥኖ ይሔዳል ሲል ደግሞ ተናገረው፤

፳፤ ወነሥአ ሙሴ ብእሲቶ ወደቂቆ ወዐዓኖሙ ዲበ አዕዱግ ወገብዓ ብሔረ ግብጽ ወነሥአ ሙሴ ለእንታክቲ በትር እንተ እምኀበ እግዚአብሔር ውስተ እዴሁ፤

ሙሴም ልጆቹንና ሚስቱን በአህዮች ጭኖ ወደ ግብጽ አገር ተመልሶ ሔደ፤ ከእግዚአብሔር ዘንድ ምልክት ያገኘባትን ያችንም በትር ይዟት ሔደ፤

፳፩፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ እንዘ ተሐውር፤ ወትገብእ ውስተ ብሔረ ግብጽ አእምር ኵሎ መድምምየ ዘወሀብኩከ፤ ውስተ እዴከ ከመ ትግበሮ ቅድሜሁ ለፈርዖን ወአነ አጸንዕ ልቦ ወኢይፌንዎሙ ለሕዝብ፤

እግዚአብሔርም ሙሴን ወደ ግብጽ አገር ተመልሰህ ሒደህ በእጅህ ልታደርገው የአዘዝኩህ ተአምራቴን ሁሉ በፈርዖን ፊት እንድታደርገው ዕወቅ፤ እኔም ወገኖቼን አሰናብቶ እንዳይሰዳቸው ልቡናውን አጸናዋለሁ አለው፤

፳፪፤ ወአንተሰ ትብሎ ለፈርዖን ከመዝ ይቤ እግዚእ እግዚአብሔር ወልድየ ዘበኵርየ ውእቱ እስራኤል ወእብለከ ፈኑአ ሕዝብየ ከመ ይፀመዱኒ፤

ፈርዖንንም ፈጥሮ የሚገዛ እግዚአብሔር እስራኤል የበኵር ልጄ ነውና ሕግ በመጠበቅ፤ መሥዋዕት በመሠዋት ያገለግለኝ ዘንድ ስደድልኝ አለህ በለው፤ ሐተታ የበኵር ልጅ አለ በፍቅር በሃይማኖት የበኵር ልጅ እንዲወደድ፤

፳፫፤ ወአንተሰ እመ ኢፈቀድከ ትፈንዎ አእምርኬ እንከ ከመ እቀትሎ አነ ለወልድከ ዘበኵርከ፤

አንተ ግን የበኵር ልጄ እስራኤልን አሰናብተህ ካልሰደድ ከው እኔም የበኵር ልጅህን



ሁሉ እንድገድለው ዕወቅ አለ በለው አለው፤

፳፬፤ ወኮነ በፍኖት በውስተ ማኅደር ተራከቦ መልአከ እግዚአብሔር ወፈቀደ ይቅትሎ፤

ሙሴም ተነሥቶ ወደ ግብጽ ሲሄድ ባደረበት ኀዳና ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክ አግኝቶ /ተገልጾ/ ሊገድለው ወደደ፤ ሐተታ ሙሴ አንዱን ልጁን የእኔ ፈንታ ነው ብሎ ገዝሮት ነበር፤ አንዱን ልጁን ግን የእሷ ፈንታ ነው ብሎ አልገዘረውም ነበርና በዚያ ነው መስሎት፤

፳፭፤ ወነሥአት ሲፓራ መላጼ ወገዘረት ከተማ ነፍስቱ ለወልዳ ወወድቀት ኀበ እገሪሁ ወትቤ ለይኩን ህየንቴሁ ዝ ደመ ግዝሮሁ ለወልድየ፤

ሲፓራም ምላጩን አንሥታ የልጄ የግዝራቱ ደም ለባሌ ቤዛ ይሁነው ብላ ሒዳ የልጁን የብልቱን ጫፍ ቆርጣ ጥላ ከመልአኩ እግር ወደቀች፤ ምነው ምን አደረግሁ? አለው፤ ከግብጽ ያሉትን አውጣቸው ብዬ ብልህ ከዚህ ያሉትን ይዘህ ትሔዳለህ አለው፤ እኔማ ማን ይመግባቸዋል ብዬ ነዋ አለው፤ ከአጠገባቸው ባሕር አለ፤ እስኪ ከዚህ እጅህን ስደድ አለው፤ እጁን ቢሰድ ደንጊያ ይዞ ወጣ፤

ስበረው አለው ሰበረው ያን ጊዜ ዕውር ትል መንታ ቅጠል ያላት ዕንጨት በቅሎላት አንዷቱን እስክትበላ አንዷቱ እያደገችላት አየ፤ ይህን የሚመግብ ማነው? አለው እግዚአብሔር አለው፤ አሁንም ይህቺን የመገበ ይመግባቸዋል፤ ትተሃቸው ሒድ አለው፤ ትቷቸው ሒዷል፤

፳፮፡ ወሖረ እንከ እምኔሁ እስመ ትቤ ለይኩን ህየንቴሁ ዝ ደመ ግዝሮሁ ለወልድየ፤

ይህ የልጄ የግዝራት ደም ለባሌ ቤዛ ይሁን ብላ ስለ ገዘረች መልአኩ ሳይገድል ትቶት ሔደ፤

፳፯፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአሮን ሑር ተቀበሎ ለሙሴ ውስተ ሐቅል፤

እግዚአብሔርም አሮንን ከከተማው ወጥተህ ወንድምህ ሙሴን በምድረ በዳው ተቀበለው አለው፤

ወሖረ ወተራከቦ በደብረ እግዚአብሔር ወተአምኆ፤

አሮንም ከከተማው ወጥቶ እግዚአብሔር ተገናኘው ባለው ቦታ ተገናኝቶ እጅ ነሣው፤ ሑር ወአስተጋብዖሙ ለአዕሩገ እስራኤል ብሎት ነበርና፤ ሐተታ፤ ሙሴ አሮንን እጅ ነሣው፤ ታላቅ ወንድሙ ነውና፤ አንድም አሮን ሙሴን እጅ

www.ethiopianorthodox.org

ነግ እግዚአብሔር ያከበረው ነውና ዘይንዕሶ የዓብዮ እንዲል ደብረ እግዚአብሔር አለው፤ ነገረ እግዚአብሔር ስለተጨዋወቱበት ነው፡

፳፰፤ ወአይድዐ ሙሴ ለአሮን ኵሎ ቃለ እግዚአብሔር ዘለአኮ ወኵሎ ተአምረ ዘአዘዞ፤

ሙሴም እግዚአብሔር የላከውን ቃል አድርግ ብሎ የአዘዘውንም ተአምራት ሁሉ ለአሮን ነገረው፡

፳፱፤ ወሖሩ ሙሴ ወአሮን ወአስተጋብኡ ኵሎ አዕሩጊሆሙ ለደቂቀ እስራኤል፤

ሔር ወአስተጋብኦሙ ለአዕሩገ እስራኤል ብሎት ነበርና፤ ሙሴና አሮንም ሒደው የእስራኤልን ልጆች ሽማግሌዎች ሰበሰቡ፤ ምክር ከሽማግሌ ነውና ከሽማግሌ ምክር፤ ከጎበዝ ውረር እንዲሉ፡

፴፤ ወነገሮሙ አሮን ኵሎ ቃለ ዘተናገሮ እግዚአብሔር ለሙሴ፤

አሮንም እግዚአብሔር ለሙሴ የተናገረውን ቃል ሁሉ፤ እንድም ሙሴ እምእግዚአብሔር ይላል፤ ሙሴ ከእግዚአብሔር አግኝቶ የነገረውን ቃል ሁሉ ለሕዝቡ ነገራቸው፤

ወገብረ ተአምረ በቅድሜሆሙ፤

በፊታቸውም ተአምራትን አደረገ አለ፤ በትሩን እባብ፤ እጁን ለምፅ አድርጎ አሳያቸው፡

፴፩፤ ወአምኑ ሕዝብ ወተፈሥሑ እስመ ሐወፆሙ እግዚአብሔር ወእስመ ርእየ ሥቃዮሙ ወአትሐቱ ርእሶሙ ወሰገዱ፤

እግዚአብሔር በረድኤት ጐብኝቷቸዋልና፤ መከራቸውንም አይቶላቸዋልና፤ ተአምራቱን አይተው በዚህስ ታወጡናላችሁ ብለው ደስ ብሏቸው አመኑ፤ እግዚአብሔር በረድኤት ስለ ጐበኛቸው መከራቸውንም ስላየላቸው በግንባራቸው ወድቀው ለእግዚአብሔር ሰገዱ፤ ሐተታ ተአምራቱን አይተው፡ አንድም ወነገሮሙ አሮን ቃሎ ብሎ ነበርና ቃሉን ሰምተው ሰገዱ፤ ንግሬ የንጉሥ ቃል የተላከለት ሰው ቃሉን ቆሞ ሰምቶ እጅ ነሥቶ እንዲቀመጥ፤ ለእነሱም የሰማያዊ ንጉሥ ቃል ተልኮላቸዋልና።

## ምዕራፍ ፭

### ገባኤ

፩፤ ወእምድኅረዝ ቦኡ ሙሴ ወአሮን ኀበ ፈርዖን ወይቤልዎ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር አምላከ



እስራኤል ፈንዎ ሕዝብየ ከመ ይግበሩ በዓልየ በሐቅል፤

ከዚህ በኋላ ሙሴና አሮን ወደ ፈርዖን ገብተው የእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔር ወገኖቼ እስራኤልን በምድረ በዳው በዓል ያደርጉልኝ ዘንድ አሰናብተህ ስደድ ብሎሃል አሉት፡

፪፤ ወይቤ ፈርዖን መኑ ውእቱ እግዚአብሔር ዘእሰምዖ ቃሎ ከመ እፈንዎሙ ለደቂቀ እስራኤል ለእግዚአብሔርኒ ኢየአምሮ ወለእስራኤልኒ ገብርየ ኢይፈንዎ፤

ፈርዖንም ባሮቼ እስራኤልን አሰናብቼ እሰዳቸው ዘንድ ቃሉን የምሰማው እግዚአብሔር የሚባል ማነው? እኔስ እግዚአብሔርንም አላውቅ ባሪያዬ እስራኤልንም አልለቅ አለ፡

፫፤ ወይቤልዎ አምላከ ዕብራውያን ፀውዐነ ንሑር እንከ ምሕዋረ ሠለስ ዕለት ውስተ ሐቅል ከመ ንሡዕ ለእግዚአብሔር አምላክነ ከመ ኢይርከበነ ሞት ወቀትል፤

የዕብራውያን ፈጣሪ እግዚአብሔር ወደ ምድረ በዳው ሦስት ቀን ልንሔድ ጠርቶናል አባር ቸነፈሩ እንዳያገኘን፡ አንድም በእናንተ ቃል የታዘዘ ሞት እንዳያገኘን ለፈጣሪያችን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት እንሠዋ ዘንድ አሉት፡

፬፤ ወይቤሎሙ ንጉሠ ግብጽ ለምንት ለክሙ ሙሴ ወአሮን ትገፈትዕዎ ለዝ ሕዝብ እምግብሩ ወእም ብሔሩ ሑሩኬ ውስተ ግብርክሙ፤

የግብጹ ንጉሥ ፈርዖንም ሙሴ አሮን፤ ለምን ይህን ሕዝብ ሥራ ታስፈቱታላችሁ፤ ሥራ የላችሁ ምን ይልቁንስ ወደ ሥራችሁ ሒዱ አላቸው፡ አንድም ሙሴ አሮን ባሪያዬ እስራኤልን ለምን ሥራ ታስፈቱታላችሁ ካለ በኋላ ባሮቹ እስራኤልን ሒዱ ወደ ሥራችሁ አለ፡

፭፤ ወይቤሎሙ ፈርዖን ለሕዝቡ ናሁ ይእዜ በዝኁ ወመልኡ ሕዝብ ውስተ ምድር ወአዕረፍክምዎሙ እምግብሮሙ፤

የግብጹ ንጉሥ ፈርዖንም ወገኖቹን ግብጻውያንን እሊህ እስራኤል በግብጽ በሀገራችን እነሆ ፈጽመው በዝተዋል፤ አዕረፍክምዎሙኑ ሥራ ማሠራቱን ትታችኋቸዋልን፡ አንድም እኒህ እስራኤል በሀገራችን ፈጽመው በዝተዋል፤ እናንተም ሥራ አናሠራ ብላችሁ አሳርፋችኋቸዋል፤ እንውጣ እንውጣ የሚሉኝ ስለዚህ ነውን አላቸው፤

፮፤ ወአዘዞሙ ፈርዖን ለነዳዕተ ገባር ዘሕዝብ ወለጸሐፍት፤

የግብጹ ንጉሥ ፈርዖንም በሕዝቡ ዘንድ ያሉ የሠራተኞችን አለቆች፤

www.ethiopianorthodox.org

ወለጸሐፍት የአለቆችን አለቆች፤ አንድም ነዳዕተ ጸሐፍት ወገባር ይላል፣ በሕዝቡ ላይ የተሾሙ ሹማምቱን እንዲህ ብሎ አዘዛቸው፤

፯፣ ወይቤሎሙ እምይእዜ ኢተሀብዎሙ ኃሠረ ዳግመ ለሕዝብ ለገቢረ ግንፋል በከመ መዋዕለ ትካት አላ ለሊሆሙ ይሑሩ ወያስተጋብኡ ሎሙ ኃሠረ፣

እነሱ እየሔዱ ገለባውን ይሰብስቡ እንጂ ጡብ የሚሠራበትን ገለባ እንግዲህ እንደ ቀድሞ እናንተ አትስጡአቸው፣ ቀድሞ ገለባውን እየለቀሙ የሚሰጡአቸው ግብጻውያን ነበሩና፤

፰፣ ወበአምጣነ ጥቦቶሙ ዘይገብሩ ግንፋለ ከማሁ ይግበሩ ኵሎ ዕለተ ወአልቦ ዘታሐፅፅዎሙ ወኢምንተኒ ዓዲ እመ ኢወሰክምዎሙ እስመ ጽሩዓን ጸርሑ ወይቤሉ ንሑር ወንሡዕ ለእግዚአብሔር አምላክነ፤

ቀድሞ ጡብ እየጣሉ ግንብ በሚሠሩት መጠን ሁሉ ጊዜም እንደዚያው ይሥሩ፤ አንድም ጥብዓቶሙ ይላል፣ ቀድሞ ጸንተው የሚሠሩትን ሥራቸውን ሁሉ እንግዲህም ወዲያ ብትጨምሩላቸው እንጂ ጊት ማታ እንደዚያው ይሥሩ ከቀድሞው ሥራ ምንም ምን የምትከፍሉላቸው የምትቀንሱላቸው አይኑር፣ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት እንሠዋ ዘንድ እስከ ሦስት ቀን እንሒድ ማለታቸው ሥራ ስለ ፈቱ ነውና፤

፱፣ ወአክብዱ ግብሮሙ ላዕለ ሕዝብ ወዘንተ ይሔልዩ ወኢይሔልዩ ነገረ ዘኢይበቍዕ፣

ሰው ሥራ ከፈታ መኮብለልን እንጂ ሌላ አያስብምና በእነዚህ ወገኖች ሥራ አጽኑባቸው፣ ይህንም ያደረጋችሁባቸው እንደሁ ሥራ ሥራቸውን ያስባሉ እንጂ የማይረባ የማይ ጠቅም እንውጣ ማለትን አያስቡም አለ፣ ዘይበቍዕ ለእስራ ኤል፤ አንድም ዘኢይበቍዕ ለግብጻውያን ነው፤

፲-፲፩፣ ወወፅኡ ነዳዕተ ሕዝብ ወጸሐፍት ወይቤልዎሙ ለሕዝብ ከመዝ ይቤ ፈርዖን ኢየሀብክሙ እንከ ኃሠረ ለሊክሙ ሑሩ ወአስተጋብኡ ለክሙ ኃሠረ በኀበ ረከብክሙ ወአልቦ ዘየሐጽጽ እምግብሮትክሙ ወኢምንተኒ ፣

ነዳዕተ ሕዝብ በሕዝቡ ላይ የተሾሙ ጸሐፍት ከሹማምቱ በላይ የተሾሙ፤ አንድም ነዳዕተ ሕዝብ ጸሐፍት ይላል፣ በሕዝቡ ላይ የተሾሙ ሹማምት ወጥተው ገለባውን እንደ ወትሮው ሰብስበው እንዳይሰጧችሁ፤ አንድም ኢነሀብክሙ ይላል፣ እኛ ሰብስበን እንዳንሰ



ጣችሁ ፈርዖን አትስጡአቸው ብሏል አሏቸው፣ እናንተ ሒዳችሁ በአገኛችሁበት ቦታ ገለባውን ሰብስባችሁ አምጡ እንጂ የጡቡንም ሥራ ቀድሞ ከምትሠሩት ሥራ ምንም ምን የሚያጐድልላችሁ የለም አሏቸው፤

፲፪፣ ወተዘርወ ሕዝብ ውስተ ኵሉ ምድረ ግብጽ ከመ የአልዱ ሎሙ ብርዐ ወኃሠረ፣

ብርዐ የቆመውን ወኃሠረ የወደቀውን፤ አንድም ብርዐ የቆመውን የወደቀውን፣ ወኃሠረ የአውድማውን ለራሳቸው ለመሰብሰብ በየቦታው ተበተኑ፤

፲፫፣ ወውእቶሙሰ ነዳዕቶሙ ያጔጕእዎሙ ወይብልዎሙ ፈጽሙ ግብረክሙ ዘለለዕለትክሙ በከመ አመ ንሁብክሙ ኃሠረ፣

ሹማምቱም ገለባውን በምንሰጣችሁ ጊዜ እንደምትሠሩት ሥራ ዛሬም ዕየዕለቱ ሥራችሁን ጨርሱ፤ አንድም ዘለለ ዕለትክሙ አመ ከመ ንሁብ ክሙ ይላል፣ ገለባውን ለቅመን እየሰጠናችሁ ትሠሩት እንደ ነበረ ጊዜ ዛሬም ዕለት ዕለት ሥራችሁን ጨርሱ እያሉ ያጣድፏቸው ነበር፤

፲፬፣ ወይቀሥፉ ጸሐፍት ነዳዕቶሙ ለደቂቀ እስራኤል እለ ተሠይሙ ዲቤሆሙ በኀበ ፈርዖን ወይቤልዎሙ ለምንት ኢትፌጽሙ ጥቦተክሙ ግንፋለ በከመ ትካት ዮምኒ፣

ከፈርዖን ዘንድ በእስራኤል ላይ የተሾሙ ሹማምቱ እስራ ኤልን ይገርፏቸው ነበር፤ አንድም ጸሐፍት ነዳዕትን፣ ነዳዕት እስራኤልን ይገርፋሉ፣ ቀድሞ የምትሠሩትን የጡቡን ሥራ ዛሬስ እንደ ቀድሞው ለምን እየቸኰላችሁ አትጨ ርሱም አሏቸው፤ አንድም ቀድሞ የምትሠሩትን የጡቡን ሥራ ዛሬስ ለምን ፈጥናችሁ አትጨርሱም? እያሉ ይቀሥፉ ይገርፏቸው ነበር፤

፲፭፣ ወቦኡ ጸሐፍቶሙ ለደቂቀ እስራኤል ወአውየዉ ኀበ ፈርዖን ወይቤሉ ለምንት ከመዝ ትሬስዮሙ ለአግብርቲከ ኃሠረ ኢይሁብዎሙ፣

በእስራኤል የተሾሙ የፈርዖን ሹማምት፤ አንድም ከእስራኤል ወገን የተሾሙ የእስራኤል ሹማምት ወደፈርዖን ገብተው አገልጋዮችህ እስራኤልን ለምን እንዲህ ታደርጋቸዋለህ ብለው ጮኹ፣ ገለባውን እንደ ወትሮው ሰብስበው አይሰጡአቸውምና፤

፲፮-፲፯፣ ወይቤልዎሙ ግበሩ ግን ፋለ ወናሁ አግብርቲከ ይትቀሠፉ ወይትገፍኡ ወይቤሎሙ ፈርዖን ዕሩፋን አንትሙ ወጽሩዓን በእንተ

www.ethiopianorthodox.org

ዝንቱ ትቤሉ ንሑር ወንሡዕ ለእግዚአብሔር አምላክነ፤

የጡቡንም ሥራ እንደ ወትሮው ጸንታችሁ ሥሩ ይሏቸዋል፤ አገልጋዮችህ እስራኤል በዚህ ምክንያት እነሆ እየተገረፉ ብዙ ግፍ ይቀበላሉ አሉት፤ ፈርዖንም እናንተ ቦዝናችሁ አርፋችኋል፤ ስለዚህ ነገር ለፈጣሪያችን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት እንሠዋ ዘንድ እንሒድ ትላላችሁ አላቸው፤

፲፰፤ ወይእዜኒ ሑሩ ወግበሩ ኃሠረስ ኢይሁቡክሙ ወጥቦተሰ ግንፋለክሙ ታመጽኡ፤

አሁንም ጡቡን ለመሥራት ጭዱን ገለባውን አይሰጧችሁም፤ እናንተ ሒዳችሁ እየመጣችሁ ሥሩ እንጂ፤ ጡቡንም እየተከፉሳችሁ አምጡ፤

፲፱፤ ወርእዩ ጸሐፍቶሙ ለደቂቀ እስራኤል ከመ በእኪት ሀለዉ ወይቤሉ እምጥቦትነሂ ዘለለ ዕለትነ ኢየሐፅፅ ግንፋል፤

በእስራኤል የተሾሙ ሹማምቱ እስራኤል በጽኑ መከራ እንዳሉ አይተው፤ አንድም አዕረፍክም ምሙ እምግብሮሙ ብሎ ተቈጥሮቻቸው ነበርና ራሳቸው በጽኑ መከራ እንዳሉ አይተው ዕለት ዕለት ጨክነን ከምንሠራው

ሥራ አያንስልንም? አይጐድልልንም? አሉ፤ ድኃ ጽኑ ትእዛዝ ሲታዘዝ ሹማምቱም ይፈራሉና፤

፳፤ ወተራከብዎሙ ለሙሴ ወለአሮን እንዘ ይመጽኡ በፀአቶሙ እምኀበ ፈርዖን፤

የፈርዖን ሹማምት እስራኤልን ከፈርዖን ቤት አውጥተው እየገፉ እያዳፉ ሲያመጧቸው ሙሴ አሮንን አገኟቸው፤ አንድም ተራከብዎሙ ሙሴ ወአሮን ይላል፤ ሙሴ አሮን ከቤታቸው ተነሥተው ወደ ፈርዖን ከተማ ሲሔዱ አገኟቸው፤ ወየመጽኡ ክብራ ለወለተ ጽዮን እንዲል፤

፳፩፤ ወይቤልዎሙ ይርአይ እግዚአብሔር ለነ ወይፍታሕ ከመ ገበርክምዎ ለዒናነ ሰቌራረ በቅድመ ፈርዖን ወበቅድመ ዓበይቱ ከመ ትመጥውዎ ሰይፈ ውስተ እዴሁ ለዘይቀትለነ፤

ለሚገድለን ለፈርዖን በእጁ የተሳለ ሰይፍ እንድትሰጡት ሁናችሁ በሹማምቱና በፈርዖን ዘንድ እንደ በጎ ሽቱ እንወደድ የነበርን እኛን እንዲጸየፉን ያደረጋችሁን እናንተንና እኛን እግዚአብሔር ያፈራርደን አሏቸው፤



፳፪፤ ወገብአ ሙሴ ኀበ እግዚአብሔር ወይቤ እግዚኦ ለምንት አኅሠምከ በዝ ሕዝብ ወለምንት ፈነውከኒ፤

ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ተመልሶ አቤቱ በዚህ ወገን ለምን ክፉ ሥራ ሠራህበት? እኔንስ ላላወጣቸው ለምን አውጣቸው ብለህ ላክኸኝ? አለው፤

፳፫፤ እምአመ መጻእኩ ኀበ ፈርዖን እንግሮ በቃልከ አኅሠመ ዲበ ሕዝብከ ወኢያድኃንካሁ ለዝ ሕዝብ፤

እግዚአብሔር ላከኝ ብዬ የአንተን ቃል ልነግረው ወደ ፈርዖን ከመጣሁ ጀምሮ በወገኖችህ በእስራኤል ላይ ፈርዖን መከራ አጸናባቸው፤ በእኔም ቃል አላዳንኻቸው አለው።

## ምዕራፍ ፮

፩፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ናሁ ትሬኢ ዘእገብር በፈርዖን እስመ በእድ ጽንዕት ይፌንዎሙ ወበመዝራዕት ልዕልት ያወፅኦሙ እምድሩ፤

እግዚአብሔርም ሙሴን አሁን በፈርዖን የማደርገውን ታያለህ፤ የጸናች ገናና በሆነች ሥልጣኔ ዐሥር መቅሠፍት ባመጣሁበት ጊዜ እስራኤልን ከአገሬ ውጡልኝ ብሎ ይሰድዳቸዋልና ታያለህ አለው፤

፪-፫፤ ወተናገሮ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ አነ ውእቱ እግዚአብሔር ዘአስተርአይኩ ለአብርሃም ወለይስሐቅ ወለያዕቆብ እስመ አምላኮሙ አነ ወስምየ ውእቱ አይዴዕክዎሙ፤

ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ የታየኋቸው አምላካቸው ስሜንም አቸናፊ እንደ ሆነ የነገርኳቸው እኔ እግዚአብሔር ነኝ ብሎ ነገረው፤

፬፤ ወአቀምኩ መሐላየ ኀቤሆሙ ከመ አሀቦሙ ምድረ ከነዓን ምድር ዘኃደሩ ውስቴታ፤

ኀቤሆሙ ለሙ ሲል ነው፤ ይኸውም ሊታወቅ ፀንተው የሚኖሩባት የከነዓንን አገር እንዳወርሳቸው መሐላዬን አጸናሁላቸው አለው፤

፭፤ ወአነ ሰማዕኩ ገዓሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ዘይሳቅይዎሙ ግብጽ ወተዘከርኩ መሐላየ፤

እኔም ግብጻውያን መከራ ያጸኑባቸው የእስራኤልን ልጆች ጩኸት ሰምቼ መሐላዬን አሰብኩ፤

፮፤ ወአፍጥን በሎሙ ለደቂቀ እስራኤል አነ ውእቱ እግዚእ እግዚአብሔር ወአወፅአክሙ እምኃይሎሙ ለግብጽ ወእምቅንየቶሙ ወአድኅነክሙ ወእቤዝወክሙ በመዝራዕትየ ልዑል ወበኰነኔየ ዐቢይ፤

እኔ እግዚአብሔር ከግብጻውያን ሠራዊት ለይቼ ከአገዛዛቸው

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

አወጣችኋለሁ፣ በጽኑ ሥልጣኔ፣ በታላቅ ፍርዴም ተቤዥቼ አድናችኋለሁ አለ ብለህ ለእስራኤል ልጆች ፈጥነህ ንገራቸው አለው፤

፯፣ ወእነሥአክሙ ሊተ ወእከውነክሙ አምላከ ወተአምሩ እንከ ከመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክክሙ ዘአውፃእኩክሙ እምድረ ግብጽ ወእምኃይሎሙ ለግብጽ፣

ወገን ልትሆኑኝ መርጬ የፍቅር የሃይማኖት አባት እሆናችኋለሁ እንግዲህም ከሠራዊታቸው ለይቼ ከግብጽ አገር ያወጣኋችሁ አምላካችሁ እግዚአብሔር እኔ እንደ ሆንኩ ታውቃላችሁ፤

፰፣ ወእወስደክሙ ውስተ ምድር ዘሰፋሕኩ እዴየ ከመ አህቦሙ ለአብርሃም ወለይስሐቅ ወለያዕቆብ ወእሁብክሙ ለክሙ ለርስት አነ እግዚእ እግዚአብሔር፣

ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ አወርሳቸው ዘንድ እጄን ወደ ዘረጋሁባት ማለት ቃል ኪዳን ወደ ሰጠሁባት ገነር የምሆን እኔ እግዚአብሔር እርሷን ርስት አድርጌ አወርሳችኋለሁ አለ በላቸው አለው፤

፱፣ ወነገሮሙ ሙሴ ከመዝ ለደቂቀ እስራኤል ወኢሰምዕዎ ለሙሴ እምእንብዝና ነፍሶሙ ወእምዕፀበ ግብሮሙ፣

አእምሮአቸውን ከማጣታቸው ከሥራውም ጭንቀት የተነሣ አልሰሙትም እንጂ፣ ሙሴም ሒዶ የጌታን ቃል ነገራቸው፤ አንድም ሙሴ ሒዶ ጌታ እንዳዘዘው አድርጎ ነገራቸው፣ ነገር ግን አእምሮአቸውን ከማጣታቸው የተነሣ ከሥራውም ጭንቀት የተነሣ አልሰሙትም፤

፲፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ባእ ወንግሮ ለፈርዖን ንጉሠ ግብጽ ከመ ይፈንዎሙ ለደቂቀ እስራኤል እምድሩ፣

እግዚአብሔርም ሙሴን ከሀገሩ ከግብጽ የእስራኤልን ልጆች አሰናብቶ እንዲሰድዳቸው ለግብጹ ንጉሥ ለፈርዖን ገብተህ ንገረው አለው፤

፲፩፣ ወተናገረ ሙሴ ወይቤ በቅድመ እግዚአብሔር ናሁ ደቂቀ እስራኤል ዘኢሰምዑኒ እፎ ፈርዖን ይሰምዐኒ ወአነ በሐም፣

ሙሴም የተወለዱኝ የሚወዱኝ የእስራኤል ልጆች ነገሬን ያልሰሙኝ፣ ያልተወለደኝ የማይወደኝ ፈርዖንማ እንደምን ይሰማኛል፣ ወዲያውም እኔ ድዳ ነኝ፣ ነገር አከናውኖ መናገር አይቻለኝም አለው፣ ሐተታ



ከመከራቸው ጽናት የተነሣ ተበሳጭተው አንሰማህም ቢሉት በድዳነቱ አንሰማህም ያሉት መስሎት እንዲህ አለ፤

፲፪፣ ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን ወአዘዞሙ ይበልዎ ለፈርዖን ንጉሠ ግብጽ ያወፅኦሙ ለደቂቀ እስራኤል እምድረ ግብጽ፣

እግዚአብሔርም የእስራኤልን ልጆች ከግብጽ መሬት አሰናብቶ እንዲሰድዳቸው ለግብጹ ንጉሥ ለፈርዖን ንገሩት ብሎ ሙሴንና አሮንን አዘዛቸው፤

ገባኤ

፲፫፣ ወእሉ እሙንቱ መላእክት በበቤተ አበዊሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ደቂቀ ሮቤል በኵሩ ለእስራኤል ሄኖኅ ወፍሉስ ወአስሮን ወከርሚ ዝውእቱ ትውልዱ ለሮቤል፣

በያዕቆብ ልጆች በአባታቸው ወገን የተሾሙ አለቆች እሊህ ናቸው የያዕቆብ የበኵር ልጁ የሮቤል ልጆች ሄኖኅ ፍሉስ አስሮን ከርሚ ናቸው፣ የሮቤልም የትውልዱ ቍጥር ይህ ነው፤

፲፬፣ ወደቂቀ ስምዖን ዩምኤል ወያሚን፣ ወአዑድ፣ ወያኩን፣ ወሱሃር፣ ወሱኡል፣ ዘእምነ ፋኒኢስ ዝውእቱ ትውልዱ ለስምዖን፣

የስምዖንም የልጆቹ ስም ዩምኤል፣ ያሚን አዑድ ያኩ ሱሐር ሱኡል፣ ዘእምነ ፋኒኢስ ስመ ሀገር፣ ስመ ሰብእ ነው፣ የስምዖንም የትውልዱ ቍጥር ይህ ነው፤

፲፭፣ ወዝውእቱ አስማቲሆሙ ለደቂቀ ሌዊ በበዘመዶሙ ጌድሶን ወቀዓት፣ ወሜራሪ ወዓመተ ሕይወቱ ለሌዊ ፻ ወ፴ወ፯ቱ፣

የሌዊም ልጆች ስማቸው ይህ ነው፤ እሊዚህም በየወገናቸው ጌድሶን፣ ቀዓት ሜራሪ ናቸው፤ ሌዊም በሕይወት የኖረበት ዘመን መቶ ሠላሳ ሰባት ነው፣ እነዚህንማ አበውን ከታች በኦሪት ዘልደት ተናግሯቸው አልነበረምን ስለ ምን በኦሪት ዘፀአት መልሶ ተናገራቸው ቢሉ፣ ሌዊን ሲሻ እሱንሳ ለምን ይሻዋል ቢሉ ከነገደ ሌዊ የተወለደ ሙሴ በእግዚአብሔር ቸርነት፣ በቅዱስ ሚካኤል አማላጅነት ግብጽ ተመልሶ ወርዶ የፈርዖንን ሥር መሠረቱን አጥፍቶ እስራኤልን ከግብጽ አወጣቸው ለማለት፣ ያውስ ቢሆን ሌዊን ብቻ ተናግሮ ባልተወውም ነበር? ስለምን ሮቤል ብሎ ቈጠረ ቢሉ፣ ነገር ከሥሩ ውሃ ከጥሩ እንዲሉ ከሥር ተርኮ ለመናገር፤ አንድም እነዚህን ሦስቱን አበው ብቻ ተናገረ፣ እንደ ሦስት ምስክር ልማ በሥሉስ፣ ጥፉ በሥሉስ እንዲሉ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፭፤ ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ጌድሶን ሎቤኒ ወሰሜዕ በበቤተ አበዊሆሙ፤

እለዚህም በአባታቸው ወገን የሚቈጠሩ የጌድሶን ልጆች ሰሚዕና ሎቤኒ ናቸው፤

፲፮-፲፰፤ ወደቂቀ ቀዓት እንበረም ወይስዓር ወኬብሮን ወእዝየል ወዓመተ ሕይወቱ ለቀዓት ፻ት ወ፴ወ፫ቱ ዓመት፤

የቀዓትም ልጆች አዝየልና ኬብሮን ይሥአርና እንበረም ናቸው፤ ቀዓትም በሕይወት የኖረበት ዘመን መቶ ሠላሳ ሦስት ነው፤

፲፱፤ ወደቂቀ ሜራሪ ሙሐሊ ወሐሙሲ እሉ እሙንቱ ትውልደ ቤተ ሌዊ በበዘመዶሙ፤

የሜራሪም ልጆች ሙሃሊ ሐሙሲ ናቸው፤ በየወገናቸው በየዘመዳቸው የሚቈጠሩ የሌዊ ልጆችም ሁሉ እሊህ ናቸው፤

፳-፳፩፤ ወነሥአ ሎቱ እንበረም ብእሲተ እንተ ስማ ዮካብድ ወለተ እኁሁ ለአቡሁ ወወለደቶሙ ሎቱ ለአሮን ወለሙሴ ወለማርያም እኅቶሙ ወዓመተ ሕይወቱ ለእንበረም ፻ትወ፴ወ፯ቱ ዓመት፤

እንበረምም በዚዩ ወራት የአባቱን የወንድም ልጅ ስሟ ዮካብድ የምትባል ሚስት አገባ፤ እሷም ሙሴንና አሮንን እኅታቸው ማርያምንም ወለደ

ችለት፤ እንበረምም በሕይወት የኖረው ዘመን መቶ ሠላሳ ሰባት ነው፤

፳፪፤ ወደቂቀ ይሥአር ቆሬ ወናፌግ ወዝክር፤

የይሥአርም ልጆች ቆሬ ናፌግ ዝክር ናቸው፤

፳፫፤ ወደቂቀ ዖዝየን ሚሳኤል ወኤልሳፌን ወስትሪ፤

የኦዝየንም ልጆች ሚሳኤል ኤልሳፌን ስትሪ ናቸው፤

፳፬፤ ወነሥአ ሎቱ አሮን ብእሲተ እንተ ስማ ኤልሳቤጥ ወለተ አሚናዳብ እኅቱ ለነአሶን ወወለደቶሙ ሎቱ ለናዳብ ወለአብዩድ ወለአልዓዛር ወለይታምር ፤

አሮንም የነአሶንን እኅት የአሚናዳብን ልጅ ስሟ ኤልሳቤጥ የምትባል ሚስት አገባ፤ እሷም አብዩድንና ናዳብን ይታምርንና አልአዛርን ወለደችለት፤

፳፭፤ ወደቂቀ ቆሬ አሴር ወሕልቃና ወአብያሴፍ ዝውእቱ ትውልዱ ለቆሬ፤

የቆሬም ልጆች አሴር ሕልቃና አብያሴፍ ናቸው፤ የቆሬም የትውልዱ ቍጥር ይህ ነው፤

፳፮፤ ወአልአዓዛር ወልደ አሮን ወነሥአ ሎቱ ብእሲተ እምአዋልደ ፋጢይን፤

የአሮን ልጅ አልዓዛርም ከፋጢይን ልጆች ወገን ሚስት አገባ፤



ወወለደቶ ሎቱ ለፊንሐስ ወእሉ እሙንቱ ቀዳምያተ ትውልዶሙ ለሌዋውያን በበነገዶሙ፤

እሷም ፊንሐስን ወለደችለት በየወገናቸው የሚቈጠሩ ከሌዋውያን ልጆች የሚቀድሙ እሊህ ናቸው፤ በትውልድማ የሚቀድሙ እለሮቤል አይደሉምን ቢሉ፤ ገና ወደ ፊት ከሚያመጣቸው ቀዳምያት አሳቸው፤ አንድም በክብር ከሁሉ የሚበልጡ አሳቸው፤ ቀዳሚሆሙ ለአሕዛብ አማሌቅ እንዲል፤ ይህን ባለው ዝውእቱ ቀዳሚ ትውልዶሙ ለሌዋውያን ይላል፤

፳፯፤ ወእሉ እሙንቱ አሮን ወሙሴ እለ ይቤሎሙ እግዚአብሔር ያውፅእዎሙ ለደቂቀ እስራኤል እምድረ ግብጽ ምስለ ኃይሎሙ፤

የእስራኤልን ልጆች ከሠራዊቶቻቸው ጋራ ከግብጽ አገር ያወጡዋቸው ዘንድ፤ አውጡአቸው ብሎ እግዚአብሔር የነገራቸው ሙሴ አሮን እሊህ ናቸው፤

፳፰፤ ወእሉ እሙንቱ እለ ተበሀልዎ ለፈርዖን ንጉሠ ግብጽ ከመ ይፈንዎሙ ለደቂቀ እስራኤል እምብሔረ ግብጽ ሙሴ ወአሮን እሙንቱ፤

እሉ እሙንቱና እሙንቱ አንድ ወገን፤ የእስራኤልን ልጆች ከግብጽ አገር አሰናብቶ ይሰ

ድዳቸው ዘንድ የግብጹን ንጉሥ ፈርዖንን ያነጋገሩት ሙሴ አሮን እሊህ ናቸው፤

በዕለት ዘተናገሮ እግዚአብሔር ለሙሴ በምድረ ግብጽ፤

ይህም የተደረገ እግዚአብሔር ሙሴን በግብጽ አገር በተነጋገረበት ቀን ነው፤

፳፱፤ ወተናገሮ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ አነ ውእቱ እግዚአብሔር ንግሮ ለፈርዖን ንጉሠ ግብጽ ኵሎ ዘአነ እቤለከ፤

እግዚአብሔርም ሙሴን የላክሁህ እግዚአብሔር እኔ ነኝ፤ ይህንንም እኔ የላክሁህን ነገር ሁሉ ለግብጹ ንጉሥ ለፈርዖን ንገረው ብሎ ተናገረው፤

፴፤ ወይቤሎ ሙሴ ለእግዚአብሔር ናሁ ጸዮፍ አነ እፎ ይሰምዐኒ ፈርዖን፤

ሙሴም እግዚአብሔርን እኔ ነገር አከናውኖ መናገር የማይቻለኝ ድዳ ነኝ ፈርዖን ነገሬን እንደምን ይሰማኛል አለው።

## ምዕራፍ ፯

### ግባኤ

፩፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ናሁ ረሰይኩከ አምላከ ለፈርዖን፤

እፎ ይሰምዓኒ ፈርዖን ቢለው እግዚአብሔርም እነሆ ለፈርዖን

www.ethiopianorthodox.org

አምላኩ አድርጌሃለሁ አለው፣ አሠለጥንሃለሁ ሲለው ነው። አንድም አምላክ የወደደውን እንዲያደርግ የወደድከውን አድርገው አለው፣ አምላኮ ባለው ታኦኒ ይላል፣ በዓረቢ ምላሽ እንደዚሁ ያስተረጉ ማልና።

ወአሮን እኁከ ይኩንከ ነቢየ፣

ወንድምህ አሮንም ስለ አንተ ሁኖ ይናገርልህ።

፪፣ ወአንተሰ ንግሮ ኵሎ ዘአዘዝ ኩከ ወአሮን ይንግሮ ለፈርዖን ከመ ይፈንዎሙ ለደቂቀ እስራኤል እም ድሩ፣

አንተም የአዘዝኩህን ሁሉ ለአሮን ንገረው፣ አሮንም የእስ ራኤልን ልጆች አሰናብቶ ከአገሩ እንዲሰድዳቸው ለፈርዖን ይንገረው።

፫፣ ወአነ አጸንዕ ልቦ ለፈርዖን ወአ በዝኀ ተአምርየ ወመድምምየ በም ድረ ግብጽ ወኢይሰምዓክሙ ፈርዖን፣

እኔም የፈርዖንን ልቡናውን አጸ ናለሁ አለ፣ በረድኤት እለየዋ ለሁ ሲል ነው፣ በግብጽ አገርም ፍጹም ተአምራቴን አብዝቼ አደርጋለሁ፣ ፈርዖንም አይሰማ ችሁምና።

፬፣ ወእወዲ እዴየ ዲበ ብሔረ ግብጽ ወአወፅኦሙ በኃይልየ ለሕዝ ብየ ለደቂቀ እስራኤል እምድረ ግብጽ በበቀል ዐቢይ፣

እኔም በግብጽ ሥልጣኔን እገል ጻለሁ ወገኖቼ እስራኤልንም በኃይል በታላቅ በቀል ከግብጽ አወጣቸዋለሁ አለ፣ በኃይል ዐሥሩን መቅሠፍት፣ በበቀል ዐቢይ ስጥመትን አድርጌ አወ ጣቸዋለሁ ሲል ነው።

፭፣ ወየአምሩ እንከ ኵሉ ግብጽ ከመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር ወእሰፍሕ እዴየ ዲበ ብሔረ ግብጽ ወአወፅ አሙ ለደቂቀ እስራኤል እማዕከ ሎሙ፣

የግብጽ ሰዎችም ሁሉ እግዚአ ብሔር እኔ እንደ ሆንኩ ያው ቃሉ፣ ሥልጣኔንም በግብጽ አገር እገልጻለሁ፣ የእስራኤ ልንም ልጆች ከመካከላቸው ለይቼ አወጣቸዋለሁ አላቸው።

፮፣ ወገብሩ ሙሴ ወአሮን በከመ አዘዞሙ እግዚአብሔር፣

ሙሴ አሮንም እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው አደረጉ፤ አንድም እግዚአብሔር ያዘዛቸውን አደረጉ አለ በባለቤት የገባ ከመ ነው።

፯፣ ወኮኖ ለሙሴ ፹ዓም፣ ወለአሮን ፹ወ፫ቱ ዓም አመ ተናገርዎ ለፈር ዖን፣

ፈርዖንንም በተናገሩት ጊዜ ለሙሴ ፹ ዓመት ሆኖት ነበር፣ ለአሮንም ሰማንያ ሦስት ዘመን ሆኖት ነበር።



፰፣ ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን፣

እግዚአብሔርም ሙሴ አሮንን እንዲህ አላቸው።

እመ ይቤለክሙ ፈርዖን ሀቡኒ ተአ ምረ ወመድምመ በሎ ለአሮን እኁከ ንሥአ ለዛቲ በትር ወግድፋ ቅድሜሁ ለፈርዖን ወቅድመ ዓበ ይቱ ወትከውን አርዌ ምድር፣

ፈርዖን ተአምራትን አድርጋችሁ አሳዩኝ ቢላችሁ፣ ወንድምህ አሮንን ይህቺን በትር አንሥ ተህ በሹማምቱና በፈርዖን ፊት ጣላት፣ እባብ ትሆናለች በለው።

፱-፲፣ ወቦኡ ሙሴ ወአሮን ቅድመ ፈርዖን ወገብሩ ከማሁ በከመ አዘ ዞሙ እግዚአብሔር ወገደፈ አሮን በትሮ ቅድመ ፈርዖን ወቅድመ ዓበይቱ ወኮነት አርዌ ምድር፣

ነበ ፈርዖን ሲል ነው፣ ሙሴ አሮን ወደ ፈርዖን ገብተው እግ ዚአብሔር እንዳዘዛቸው አደ ረጉ፤ አዘዞሙ ያለውን አመጣ፣ አሮንም በሹማምቱና በፈርዖን ፊት በትሩን ጣላት እባብ ሆነች።

፲፩፣ ወጸውዖሙ ፈርዖን ለጠቢባን ወለመሠርያን ወገብሩ ሐራስያን ግብጽ በሥራያቲሆሙ ከማሆሙ፤

ፈርዖንም ይኸንን አይቶ ይህን ንስ የኔም ፈላስፎች ያደርጉታል ብሎ አዋቂዎችን ሥራየኞችን አስጠርቶ አምጥቶ እንደ ሙሴ አሮን አድርጉ አላቸው፣ የግብጽ ሟርተኞችም በሥራያቸው እንደ ሙሴና እንደ አሮን አደረጉ።

፲፪፣ ወወገሩ አብትሪሆሙ ወኮኑ አራዊተ ምድር ወውኅጠቶሙ በትረ አሮን ለአብትረ እልኩቱ፣

ወገብሩ ያለውን አመጣ፣ ኢያኔስ ኢያንበሬስም በትሮቻቸውን ወደ መሬት ጣሉ፣ በትሮቻቸ ውም እባብ ሆኑ፣ ሙሴ አሮን እባብ የሆነውን መልሰው በትር አደረጉ፣ ኢያኔስ ኢያን በሬስ ግን እባብ የሆነውን መልሶ በትር ማድረግ ተሳና ቸው፣ ሙሴ አሮን መልሰው በትራቸውን ቢጥሏት እባብ ሁና የኢያኔስ፣ የኢያንበሬስን በትር ለቃቅማ ውጣ ወደ እነሱ ብትሔድ፣ ወሖሩ በስላቅ ይላል፣ ዛሬስ የሙሴ የአሮን በትር የእኛን በትር ለቃቅማ ውጣ ወደ እኛ መጣች? ብለው በውስጠ ፍርሃት ሸሽተው ሒደዋል፣ ከዚህም ምንም እባብ የነበረችውን መልሶ በትር ማድረግ ቢሳናቸው በትራቸውን እባብ አድርገዋልና ይህንን አይቶ ፈርዖን እምቢ እያለ ሙሴ አሮን እየጸለዩ በዐሥሩ መቅሠፍት ይፈጸማል።

www.ethiopianorthodox.org

፲፫፣ ወጸንዐ ልቡ ለፈርዖን ወዐበየ ሰሚዐ በከመ ይቤ እግዚአብሔር፣

እግዚአብሔር አጸንዕ ልቦ ለፈርዖን ብሎ እንደተናገረው የፈርዖን ልቡናው በክፋት ጸና፣ አ.ይሰምዐክሙ ብሎ እንደ ተናገረ ትእዛዙን መስማት እምቢ አለ፤

፲፬፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ከብደ ልቡ ለፈርዖን ከመ ኢይፌንዎሙ ለሕዝብ፣

እግዚአብሔርም ሙሴን ወገኖቼ እስራኤልን አሰናብቶ እንዳይ ሰዳቸው የፈርዖን ልቡና በክፋት ጸና አለው፤

፲፭፣ ወሑር ኀበ ፈርዖን በጽባሕ ወናሁ ኀበ ማየ ተከዚ ይወጽእ ውእቱ ወይቀውም ወተቀበሎ ኀበ ገበዘ ተከዚ ወለእንታክቲ በትር እንተ ኮነት አርዌ ምድር ንሥአ ውስተ እዴከ፣

አሁንም ነገ ጧት ወደ ፈርዖን ሒድ እሱም ከቤቱ ወደ ወንዙ ዳር ወጥቶ ይቆማል፣ አንተም ወደ ወንዙ ዳር ወጥተህ ተቀበለው፣ እባብ የሆነች በትሪቱንም በእጅህ ይዘሃት ሒድ አለው፤

፲፮፣ ወበሎ እግዚአብሔር አምላከ ዕብራውያን ፈነወኒ ኀቤከ እንዘ ይብል ፈኑአ ሕዝብየ ከመ ይፀመዱኒ በሐቅል ወናሁ ኢሰማዕከ እስከ ዛ ዕለት፣

የዕብራውያን ፈጣሪ እግዚአብሔር በምድረ በዳው መሥዋዕት ሠውተው ያገለግሉኝ ዘንድ ወገኖቼ እስራኤልን አሰናብተህ ስደዳቸው ቃሌንም እስከ ዛሬ ድረስ እነሆ አልሰማኸም ብሎ ወደ አንተ ልኮኛል በለው፤

፲፯፣ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር በዝንቱ ተአምር ከመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር ናሁ አነ እዘብጥ በዛ በትር እንተ ውስተ እዴየ ማየ ተከዚ ወይከውን ደመ፣

እግዚአብሔር እንዲህ አለ ይህን ያደረግሁ እኔ ፈጣሪህ እግዚአብሔር እንደ ሆንኩ በዚህ ታውቀዋለህ፣ በእጄ በተያዘ ችው በዚህች በትር ውሀውን እመታዋለሁ ደም ይሆናል በለው አለ፤

፲፰፣ ወይመውቱ ዓሣት ዘውስተ ተከዚ ወይፀይዕ ተከዚ ወኢይክሉ ግብጽ ሰትየ ማየ ተከዚ፣

ምግብ ቢለወጥባቸው በወንዙ ያሉ ዓሣዎች ይሞታሉ፣ ወንዙም ይሸታል የግብጽ ሰዎችም የወንዙን ውሀ መጠጣት አይችሉም፤ አንድም ሰትየ እማየ ተከዚ፣ አንድም ሰትየ ማይ እምተከዚ ይላል፣ ከፈሳሹ መጠጣት አይቻላቸውም፤

፲፱፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ በሎ ለአሮን ንሥአ ለበትርከ ወስ ፋሕ እዴከ ዲበ ማያተ ግብጽ ወዲበ አፍላጊሆሙ ወዲበ አሥራ ጊሆሙ ወዲበ አዕያጊሆሙ ወዲበ



ኵሉ ምቅዋመ ማዮሙ ወይከውን ደም ውስተ ኵሉ ምድረ ግብጽ ውስተ ዕፀው ወውስተ አዕባን፣

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፣ ወንምድህ አሮንን እባብ የሆነች በትርህን አንሥተህ እጅህን ዘርግተህ የግብጽን ውሃ ዎች ምታቸው በለው አለው፣ ማያት ያለውን ይተረትራል፣ ዲበ አፍላጊሆሙ ፈሳሹን፣ ወዲበ አሥራጊሆሙ ምንጩን፣ ወዲበ አዕያጊሆሙ ኩሬውን፣ ወዲበ ኵሉ ምቅዋመ ማዮሙ፣ አልፎ አልፎ የሚቆመውን ውሀ ሁሉ ምታው ደም ይሆናል፣ እየታፈንክም ርጨው፣ ጣሩም ዕንጨቱም ደንጊያውም ደም ይሆናል አለው፣ የእስራኤልን ልጆች እያነቁ ባሕር ጥለው ነበርና በዚያ ፍዳ ነው፤

፳፣ ወገብሩ ከመዝ ሙሴ ወአሮን በከመ አዘዞሙ እግዚአብሔር ወአልዓለ በትሮ አሮን ወዘበጠ ማየ ዘው ስተ ተከዚ በቅድመ ፈርዖን ወበቅ ድመ ዓበይቱ ወኮነ ደመ ማይ ዘው ስተ ተከዚ፣

ሙሴ አሮንም እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው አደረጉ፣ ገብሩ ያለውን አመጣ፣ አሮንም በትሩን ከፍ ከፍ አድርጎ በሹማምንቱና በፈርዖን ፊት ውሀውን መታው፣ የፈሳሹም ውሀ ደም ሆነ፤

፳፩፣ ወሞቱ ዓሣት ዘውስተ ተከዚ ወፄዐ ተከዚ ወስዕኑ ግብጽ ሰትየ ማይ እምተከዚ ወኮነ ደም ውስተ ኵሉ ምድረ ግብጽ፣

በፈሳሹ ውስጥ ያሉ ዓሣዎችም ምግብ ቢለወጥባቸው ሞቱ፣ ፈሳሹም ሸተተ፣ ግብጻውያንም ከፈሳሹ ውሀ መጠጣት ተሳናቸው፣ በግብጽ አገር ሁሉ ደም ሆነ፤

፳፪፣ ወገብሩ ከማሁ ሐራሲያን ግብጽ በሥራያቲሆሙ ወጸንዐ ልቡ ለፈር ዖን ወዐበየ ሰሚዖቶሙ በከመ ይቤ እግዚአብሔር፣

የግብጽ ሟርተኞች ኢያኔስ ኢያንበሬስም በሟርታቸው እንደ እሱ አደረጉ አለ እንደ አሮን፡ አንድም አሁን እንደ ተናገርኩት አደረጉ፣ እግዚአ ብሔር አጸንዕ ልቦ ለፈርዖን እንዳለ የፈርዖን ልቡ በክፋት ፀና፣ ኢ.ይሰምዓክሙ ብሎ እንደ ተናገረ አልሰማችሁም አለ፤

፳፫፣ ወገብአ ፈርዖን ወቦአ ቤቶ ወኢተመይጠ ልቡ በዝንቱ ኵሉ፣

ፈርዖን ተመልሶ ወደ ቤቱ ገባ፣ ነገር ግን በዚህ ሁሉ ነገር ልቡ ናው ወደ ኃዘን አልተመለሰም፤

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

፳፬፤ ወከረዩ ኵሉ ግብጽ ዓውደ ለተከዚ ከመ ይስተዩ ማየ ወስዕኑ ሰትየ ማይ እምተከዚ፤

ግብጻውያን ሁሉ ከፈሳሹ ውሀ መጠጣት ተስኗቸዋልና ውሀ ሊጠጡ ከወንዙ ዳር ጉድጓድ ቈፈሩ፤

፳፭፤ ወተፈጸመ ሰብዑ መዋዕል እምድኅረ ዘበጦ እግዚአብሔር ለተከዚ፤

እግዚአብሔር ፈሳሹን ደም ካደረገው በኋላ ሰባቱ ቀን ተፈጸመ።

## ምዕራፍ ፰

፩፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ባእ ኀበ ፈርዖን ወበሎ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ፈኑ ሕዝብየ ከመ ይጸመዱኒ በሐቅል፤

እግዚአብሔር ሙሴን ወደ ፈርዖን ገብተህ በምድረ በዳ መሥዋዕት ሠውተው ያገለግሉኝ ዘንድ ወገኖቼ እስራኤልን አሰናብተህ ስደድ ብለሎሃል በለው አለው፤

፪፤ ወለእመ ዐበይከ አንተ ፈንዎ ቶሙ ናሁ አነ እዘብጥ ኵሎ አድባሪከ በቈርነነዓት፤

አንተ አልሰድዳቸውም ብትል ግን እኔም ተራራህን ሁሉ፤ ተሳቦ ቀንዳማ ትል፤ ጓጉን ቸር፤ ዛጐል ልብሱን እንዲያ ስገኝ አደርገዋለሁ፤

፫፤ ወይቀድሐ ተከዚ ቈርነነዓተ ወየዐርግ ወይበውእ ውስተ አብያቲከ ወውስተ ውሣጥያተ ቤትከ ወጽርሕከ ወዲበ ዓራትከ ወውስተ አብያተ ዓበይትከ ወዲበ ሕዝብከ ወውስተ ሐሪጽከ ወውስተ ዕቶናቲከ፤

ፈሳሹም ቀንዳማ ትሉን ያስገኛል፤ ቀንዳማ ትሉም ከፈሳሹ ወጥቶ ወደ ቤትህ ይገባል፤ አብያቲከ ያለውን ይተረትራል፤ ውሳጥያተ ቤትከ፤ ወደ እልፍኝህ፤ ወጽርሕከ ወደ አዳራሽህ፤ ወዲበ ዓራትከ ወደ ዙፋንህ፤ ወደሹማምትህም ቤት፤ ወደ ወገኞችህም ቤት፤ ዲበ ሐሪጽከ ወደ ዶቄትህም፤ ወውስተ ዕቶናቲከ ወደ ምድጃህም ይገባል፤

፬፤ ወዲቤከ ወዲበ ዓበይትከ ወዲበ ሕዝብከ የዓርግ ቈርነነዓት፤

በአንተ፤ በሹማምትህ፤ በወገኖችህም ላይ ቀንዳማ ትል ይወጣል፤

፭፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ በሎ ለአሮን እኅከ ስፋሕ እዴከ ወበትረከ ዲበ አፍላግ ወዲበ አሥራግ ወዲበ አዕያግ ወይዓእ ቈርነነዓት፤

እግዚአብሔር ሙሴን ወንድምህ አሮንን እጅህን ዘርግተህ በበትርህ ፈሳሹን፤ ምንጩን፤ የኩሬውን ውሀ ምታው፤ ከዚያ ተሳቦ፤ ቀንዳማ ትል፤ ጓጉንቸር፤ ዛጐል ልብሱ ይውጣ ብሏል በለው አለው፤ ሙሴም ሒዶ ለአሮን ነገረው፤



፮፤ ወሰፍሐ አሮን እዴሁ ዲበ ማያተ ግብጽ ወወፅአ ወዓርገ ቈርነነዓት ወከደኖ ለምድረ ግብጽ፤

አሮንም እጁን ዘርግቶ የግብጽን ውሀ በበትሩ መታው ተሳቦ፤ ቀንዳማ ትል፤ ጓጉንቸር፤ ዛጐል ልብሱ ከዚያ ወጥቶ የግብጽን አገር በብዛት ሸፈነው፤

፯፤ ወገብሩ ከማሁ ሐራስያነ ግብጽ በሥራያቲሆሙ ወአውፅኡ ቈርነነዓተ ዲበ ምድረ ግብጽ፤

የግብጽ ሟርተኞች ኢያኔስ ኢያንበሬስም በሟርታቸው እንደሱ አደረጉ፤ እንድም አሁን እንደ ተናገርኩት አደረጉ፤ በግብጽ አገርም ቀንዳማ ትል ጓጉንቸር ዛጐል ልብሱን አስ ገኙ ገብሩ ያለውን አመጣ፤

፰፤ ወጸውዖሙ ፈርዖን ለሙሴ ወለ አሮን ወይቤሎሙ ጸልዩ ሊተ ኀበ እግዚአብሔር ከመ ይሰስል ቈርነነዓተ እምኔየ ወእምሕዝብየ ወእፌ ንዎ ለሕዝብ ይሠዕ ለእግዚአብ ሔር፤

ፈርዖንም ሙሴ አሮንን ጠርቶ ይህ ተሳቦ ቀንዳማ ትሉ፤ ከእኔ እንዲርቅልኝ እናንት ወደ ፈጣ ሪያችሁ ወደ እግዚአብሔር ለምኑልኝ፤ እኔም ወገናችሁ እስራኤልን ለፈጣሪው ለእግዚ አብሔር ሊሠዋ አሰናብቼ እስ ድደዋለሁ አላቸው፤

፱፤ ወይቤሎ ሙሴ ለፈርዖን አድ መኒ ማእዜ እጼሊ ለከ ወለዓበይትከ ወለሕዝብከ ከመ ይማስን ቈርነ ነዓት እምኔከ ወእምሕዝብከ ወእምዓ በይትከ እንበለ ውስተ ተከዚ ይትርፍ፤

ሙሴም ፈርዖንን በፈሳሹ ውስጥ ከሚቀረው በቀር ከሹማምትህ ከወገኖችህ ከአንተ ተሳቦ ቀንዳማ ትል፤ ጓጉንቸር፤ ዛጐል ልብሱ እንዲርቅልህ ለወገኖችህ ለሹማምትህ ለአንተ እጸልይልህ ዘንድ መቼ ልለምንልህ ቀን ቅጠረኝ አለው፤

፲፤ ወይቤሎ ፈርዖን ለጌሠም ወይ ቤሎ አሆ በከመ ትቤለኒ ከመ ታእምር ከመ አልቦ ባዕድ አምላክ ዘእንበለ እግዚአብሔር፤

ማእዜ እጼሊ ለከ ቢለው ፈርዖ ንም የዛሬን እንደምንም ታግ ሼው አድራለሁ ነገ ይሁንልኝ አለው፤ ሙሴም ከእግዚአብ ሔር በቀር ሌላ ባዕድ አምላክ እንደሌለ ታውቅ ዘንድ አንተ እንዳልኸኝ እሺ ነገ እጸልይል ሃለሁ አለው፤

፲፩፤ ወይሴስል ቈርነነዓት እምኔከ ወእምአብያቲከ ወእምዓበይትከ ወእ ምሕዝብከ እንበለ ውስተ ተከዚ ይተርፍ፤

ይህን ያደረግሁልህ እንደሆነ ተሳቦ ቀንዳማ ትሉ በፈሳሹ ከሚቀረው በቀር ከወገንህ ከሹ ማምትህ ከቤትህ ከአንተም ይርቅልሃል አለው፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፪፣ ወወፅአ ሙሴ ወአሮን እምነበ ፈርዖን ወአውየወ ኀበ እግዚአብሔር በእንተ ሙስና ቈርነነዓት በከመ አዘዘ ፈርዖን፣

ፈርዖን ለነገ ጸልዩልኝ ብሎ እንደለመነ ሙሴ አሮንም ከፈ ርዖን ዘንድ ወጥተው ተሳቦ ውን ቀንዳማ ትሉን አጥፋልን ብለው ወደ እግዚአብሔር ጮኸው ለመኑ፤

፲፫፣ ወገብረ እግዚአብሔር በከመ ይቤ ሙሴ ወሞተ ቈርነነዓት እምአብያት ወእምአህጉር ወእም ሐቅል፣

እግዚአብሔርም ሙሴ ተሳቦ ውን አጥፋልኝ ብሎ እንደ ለመነው አደረገለት፣ በምድረ በዳው በከተማው በቤትም ያለው ተሳቦ፣ ቀንዳማ ትል ሞተ፤

፲፬፣ ወአስተጋብኡ ክምረ ክምር ወጊዓተ ምድር፣

ግብጻውያንም ሰብስበው በየቦ ታው አልፈው አልፈው ከመ ሩት፣ ምድርም ሸተተች፤

፲፭፣ ወሶበ ርእየ ፈርዖን ከመ ኮነ ዕረፍት ክብደ ልቡ ወአበየ ሰሚዖ ቶሙ በከመ ነበበ እግዚአብሔር፣

ፈርዖንም ዕረፍት እንደ ተደረገ ባየ ጊዜ ልቡናው ጸና፣ እግዚአ ብሔርም ኢይሰምዓክሙ ፈርዖን ብሎ እንደ ተናገረ አልሰማም አለ፤

፲፮፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ በሎ ለአሮን ስፋሕ በእዴከ በትረከ ወዝብጥ መሬተ ምድር ወይወፅአ ፃውት ዲበ ሰብእ ወዲበ እንስሳ ወውስተ ኵሉ ምድረ ግብጽ፣

መሬት ያልጸናው፣ ምድር የጸ ናው ነው፣ እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው፣ ወንድ ምህ አሮንን በእጅህ በትርህን አንሥተህ መሬቱን ምታው፣ በሰውም በከብቱም በግብጽ አገርም ሁሉ ጭጭን፣ ዘመ ሚት፣ ትንኝ፣ ሳንጃ ይወጣል በለው፤ አንድም እግዚአብሔር ይወጣል ብሏል ብለህ ንገረው አለው፤ ሐ.ዶ ነገረው፤

፲፯፣ ወሰፍሐ አሮን በእዴሁ በትሮ ወዘበጠ መሬተ ምድር ወወፅአ ፃውት ዲበ ሰብእ ወዲበ እንስሳ ወውስተ ኵሉ ምድረ ግብጽ፣

አሮንም በእጁ በትሩን አንሥቶ መሬቱን መታው፣ በሰውም በከብቱም በግብጽም አገር ሁሉ ጭጭን፣ ዘመሚት፣ ትንኝ፣ ሳንጃ ወጣበት፤

፲፰፣ ወገብሩ ከማሁ ሐራስያን በሥራያቲሆሙ ከመ ያውፅኡ ፃውተ ወስዕኑ ወወፅአ ፃውት ዲበ ሰብእ ወዲበ እንስሳ፣

የግብጽ ሟርተኞች ኢያኔስ ኢያ ንበሬስም እንደአሮን (አሮን እንዳደረገው) በሟርታቸው ጭጭን ዘመሚት ትንኙን፣



ሳንጃውን እናወጣለን አሉ፣ ማውጣት ተሳናቸው፣ እስካ ሁን ለእኪያትስ ኢከላዕናሆሙ ይላል፣ ለመቅሠፍቱ መጨመ ሪያ ይሁን ብሎ ፈቅዶላቸው ነበር፣ አሁን ግን ኃይል ተአ ምራት የባሕርያችን ነው እን ዳይሉ ከልክሏቸዋል፣ እነሱን ተሳናቸው አልን እንጂ ሳንጃው ትንኙ ግን በሰው በከብቱ ወጣ፤

፲፱፣ ወይቤልዎ ሐራስያን ለፈርዖን አጽባዕተ እግዚአብሔር ውእቱ ዝንቱ ወጸንዐ ልቡ ለፈርዖን ወአበየ ሰሚዖቶሙ በከመ ነበበ እግዚአ ብሔር፣

ኢያኔስ ኢያንበሬስም ፈርዖንን በአፋቸው በአፍንጫቸው በዓይ ናቸው በጆሮዋቸው ጥልቅ ጥልቅ እያለ ቢወጋቸው ይህስ የእግዚ አብሔር ጣት ነው፤ አንድም የእግዚአብሔር ሰልፍ ነው፤ አንድም ጸባዒተ እግዚአብሔር ይላል፣ የእግዚአብሔር አርበኛ ነው አሉት፣ የፈርዖንም ልቡ ናው በክፋት ጸና፣ እግዚአብ ሔርም ኢይሰምዓክሙ ፈር ዖን ብሎ እንደ ተናገረ መስ ማቱን እምቢ አለ፤

፳፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ጊሥ በጽባሕ ወቁም ቅድሜሁ ለፈ ርዖን ናሁ ኀበ ማይ ይወፅእ ውእቱ ወበሎ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ፈኑ ሕዝብየ ከመ ይፀመዱኒ፣

እግዚአብሔርም ሙሴን ነገ ጧት ገስግሠህ ሒደህ በፈርዖን ፊት ቁም፣ እሱም ወደ ፈሳሹ ይወጣል እግዚአብሔር እንዲህ አለ፣ ወገኖቼ እስራኤል መሥ ዋዕት ሠውተው ያገለግሉኝ ዘንድ አሰናብተህ ስደድ አለ ብሎሃል በለው አለው፤

፳፩፣ ወለእመ አበይከ ፈንዎተ ሕዝ ብየ ናሁ አነ እፌኑ ዲቤከ ወዲበ አበይትከ ወዲበ ሕዝብከ ወዲበ አብያቲከ ጽንጽንያ ከልብ ወይመ ልዕ ውስተ አብያተ ግብጽ ወው ስተ ምድርሂ እንተ ሀለውከ ውስቴታ፣

አንተ ወገኖቼ እስራኤልን አል ሰድም ያልክ እንደሆነ እኔም በአንተ በሹማምቶችህ በወገኖ ችህ በቤትህም ሁሉ ተርብ፤ አንድም የውሻ ዝንብ አመጣ ለሁ፣ ይኸውም በግብጽ ሰዎች ቤት አንተም በምትኖርባት አገር ሁሉ ይመላል አለ በለው፤

፳፪፣ ወእሴብሕ በይእቲ ዕለት በምድረ ጌሤም እንተ ውስቴታ ሀለው ሕዝብየ ወኢይሄሉ ህየ ጽንጽንያ ከልብ ከመ ታእምር ከመ አነ ውእቱ እግዚእ ለኵሉ ምድር፣

ወገኖቼ እስራኤል ባሉበት በጌሤም አገር ግን ለወገኖቼ ለእስራኤል ተአምራት አድር

www.ethiopianorthodox.org

ጌላቸው በዚህች ቀን እመሰገ ናለሁ፣ ለዓለሙ ሁሉ ገዥ እኔ እንደ ሆንኩም እንድታ ውቅ ይህ ተርቡ፣ የውሻ ዝንቡ ወገኖቼ እስራኤል በአሉባት በጌሤም አገር አይኖርም፤

፳፫፣ ወእፈልጥ ማዕከለ ሕዝብየ ወማዕከለ ሕዝብከ ወይከውን ጌሠመ ዝ ነገር፣

ይህንም ተአምራቱን በወገኖች ህና በወገኖቼ መካከል ለይቼ አደርገዋለሁ፣ ይኸውም አይው ልም አያድርም ነገ ይደረጋል አለ በለው አለው፣ ሒዶ ነገ ረው፤

፳፬፣ ወገብረ እግዚአብሔር ከማሁ ወመጽአ ጽንጽንያ ከልብ ብዙኀ ውስተ አብያተ ፈርዖን ወውስተ አብያተ ዓበይቱ ወውስተ ኵሉ ምድረ ግብጽ ወማሰነት ምድር እምጽንጽንያ ከልብ ብዙኀ፣

ይከውን ጌሠመ ዘነገር ብሎ ነበርና እግዚአብሔርም በበነጋው እንዳለው አደረገ፣ ወገብረ ያለውን አመጣ፣ ብዙም ተቈናጣጭ ዝንብ ወደ ፈርዖን ቤት ወደ ሹማምቱም ቤት ወደ ግብጽ አገርም ሁሉ መጣ፣ ከተቈና ጣጭ ዝንቡም የተነሣ ግብጽ ጠፋች፤

፳፭፣ ወጸውዖሙ ፈርዖን ለሙሴ ወለአሮን ወይቤሎሙ ሑሩ ወሡዑ ለአምላክክሙ በዛ ምድር፣

ፈርዖንም ሙሴ አሮንን ጠርቶ ሳትርቁ በዚህች አገር ለፈጣሪ ያችሁ ሒዳችሁ ሠዉ አላቸው፤

፳፮፣ ወይቤሎ ሙሴ ኢይትከሃል ከመዝ ይኩን እስመ ዘየሐርሙ ግብጽ ንሠውዕ ለአምላክነ ወለእመ ሦዕነ ዘየሐርሙ በቅድሜሆሙ ይዌ ግሩነ፣

ሙሴም ፈርዖንን ግብጻውያን የሚያመልኩት ላሙን ለፈጣ ሪያችን ለእግዚአብሔር እንሠ ዋለንና የሚያመልኩት ላሙንም በፊታቸው ከሠዋነው በደንጊያ ወግረው በእሳት አቃጥለው ይገድሉናልና እንዲህ ያለው ነገር ይደረግ ዘንድ አይቻልም አለው፣ ይዌግሩነ ብሎ በዕብ ራውያን ሥርዓት ተናገረ፤

፳፯፣ ምሕዋረ ሠሉስ ዕለት ንሑር ውስተ ሐቅል ወንሠዕ ለእግዚአ ብሔር አምላክነ በከመ ይቤለነ፣

እኛስ ወደ ምድረ በዳው ሦስት ቀን ገሥግሰን ሒደን በምድረ በዳው ሠዉልኝ ብሎ እንደ ነገረን ለፈጣሪያችን ለእግዚአ ብሔር እንሠዋለን አለው፣ ትእዛዝ ካልአይ ሁኖ ይተረጐ ማል የሚሉት በብሉይ ቤት ይህ ነው፤ አንድም እንዳለም ይሆናል፣ አላ ያለበት ነው፣



ሦስት ቀን ገሥግሠን ሒደን እሱ ሠዉልኝ ብሎ እንደ ነገረን በምድረ በዳው ለፈጣሪ ያችን ለእግዚአብሔር እንሠዋ እንጂ እነሱ የሚከለከሉትን በፊታቸው ልንሠዋ አይቻልም አለው፤ አንድም እንዳለ ይሆ ናል፣ ሑሩ ወሡዑ ለአምላ ክክሙ ብለህስ ካልከን እንኪ ያስ ሦስት ቀን ገሥግሠን ሒደን ለፈጣሪያችን ለእግዚአ ብሔር መሥዋዕት እንሠዋ፣ ፍቀድልን አሉት፤

፳፰፣ ወይቤሎ ፈርዖን አነ እፌንወ ክሙ ትሡዑ ለእግዚአብሔር አምላ ክክሙ በሐቅል ወባሕቱ ኢትት አተቱ ወርሑቀ ኢትሑሩ ወጸልዩ እንከ ሊተ ኀበ እግዚአብሔር፣

ፈርዖንም ሙሴን በምድረ በዳው ለፈጣሪያችሁ ለእግዚአብሔር ልትሠዉ እኔ አሰናብቼ እሰድ ዳችኋለሁ፣ ነገር ግን ርቃችሁ አትሒዱ፣ ለእኔም ወደ ፈጣ ሪያችሁ ወደ እግዚአብሔር ለምኑልኝ አለው፤

፳፱፣ ወይቤሎ ሙሴ ናሁ አነ እወ ፅእ እምኀቤከ ወእጼሊ ኀበ እግዚ አብሔር ወይሴስል ጽንጽንያ ከልብ እምኔከ ወእምዓበይትከ ወእምሕዝ ብከ ፍጡነ ወኢትድግም እንከ አስተአብዶ ከመ ኢትፈኑ ሕዝቦ ይሡዑ ሎቱ፣

ሙሴም ፈርዖንን አሁን ከአንተ ዘንድ ወጥቼ ጸልዩ ሊተ ብለህ እንዳልክ ወደ እግዚአብሔር እለምንልሃለሁ፣ ይህም ተርቡ፣ የውሻ ዝንቡ ከወገኖችህ ከሹማ ምትህ ከአንተ ፈጥኖ ይርቃል፣ ነገር ግን በምድረ በዳው መሥ ዋዕት ሊሠዉለት ወገኖቹ እስራ ኤልን አሰናብተህ እንዳትሰድ ሁነህ ዳግመኛ እግዚአብሔርን አላዋቂ አታድርገው አለው፤

፴፣ ወወፅአ ሙሴ እምኀበ ፈርዖን ወጸለየ ኀበ እግዚአብሔር፣

ሙሴም ከፈርዖን ዘንድ ወጥቶ እጼሊ ለከ እንዳለው ወደ ፈጣሪው ወደ እግዚአብሔር ለመነለት፣

፴፩፣ ወገብረ እግዚአብሔር በከመ ይቤ ሙሴ ወአሰሰለ ጽንጽንያ ከልብ እምፈርዖን ወእምዓበይቱ ወእም ሕዝቡ ወኢተርፈ ወኢአሐዱሂ፣

ሙሴም ይራቅለት ብሎ እንደ ለመነ እግዚአብሔር አደረገ ለት፣ ገብረ ያለውን አመጣ፣ ተርቡን የውሻ ዝንቡን ከወገኖቹ ከሹማምቱ ከፈርዖን አራቀ ለት፣ አንድ ስንኳን አልቀረ በትም፤

፴፪፣ ወአክበደ ልቦ ፈርዖን ወበዝ ንቱሂ ጊዜ ዐበየ ፈንዎተ ሕዝቡ፣

ፈርዖንም ልቡናውን በክፋት አጸና በዚህም ጊዜ ወገኖቹ እስራኤልን አሰናብቶ መስደ ዱን እንቢ አለ።

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፱

፩፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ባእ ኀበ ፈርዖን ወበሎ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር አምላከ ዕብራውያን ፈኑ ሕዝብየ ከመ ይጸመዱኒ፤

እግዚአብሔር ሙሴን ወደ ፈርዖን ገብተህ የዕብራውያን ፈጣሪ እግዚአብሔር እንዲህ አለ፤ በምድረ በዳው መሥዋ ዕት ሠውተው እንዲያገለግ ሉኝ ወገኖቼ እስራኤልን አሰ ናብተህ ስደድ ብሎሃል ብለህ ንገረው አለው፤

፪፤ ወእመ ዓበይከ ፈንዎተ ሕዝብየ ወዓዲ አጽናዕከሙ፤

ወገኖቼ እስራኤልን አንተ አሰና ብተህ ባትሰድዳቸው ዳግመ ኛም ልቡናህን ብታጸናባቸው፤ አንድም አጽናሕከሙ ይላል፤ ዳግመኛ ብታቆያቸው፤

፫፤ ናሁ ትከውን እዴየ ዲበ እንስ ሳከ በሐቅል ዲበ አፍራስ ወዲበ አዕ ዱግ ወዲበ አግማል ወዲበ አልሕ ምት ወዲበ አባግዕ ሞት ዐቢይ ጥቀ፤

እነሆ እደ መዓቴ በምድረ በዳው ባለ ከብትህ በፈረሶችህም፤ በአህዮችህ፤ በግመሎችህም፤ በላሞችህ፤ በበጎችህም የላም ጌታ ፈጽሞ ይታዘዝባቸዋል፤

፬፤ ወእሴባሕ አነ ማዕከለ እንስሳ ግብጽ ወማዕከለ እንስሳ ደቂቀ እስራኤል ወኢይመውት እንከ እም ኵሉ ዘደቂቀ እስራኤል ወኢም ንትኒ፤

በእስራኤል ከብቶችና በግብጻ ውያን ከብቶች መካከል ተአም ራት አድርጌ እመሰገናለሁ ይኸ ውም ተአምራት በተደረገ ጊዜ ከእስራኤል ልጆች ከብቶች ወገን ሁሉ ምንም ምን አይሞ ትም አለ ብለህ ንገረው አለው፤ የግብጻውያንና የእስራኤል ከብቶች አብረው ተሰማርተው ሳሉ የግብጻውያንን ከብቶች እየለየ እየለየ ያጠፉ ነበርና፤ አንድም አብረው ተሰማርተው ውለው ማታ ሲያርዱአቸው የግብፃውያን ከብቶች ተለ ይተው አርረው ከስለው ይገኙ ነበርና፤

፭፤ ወወሀበ እግዚአብሔር ዕድሜ ወይቤ ጌሠመ እገብር ዘ ነገረ ዲበ ምድር፤

እግዚአብሔር ለፈርዖን ቀጠሮ ሰጠው፤ ይህንንም ነገር ነገ ይኸን ጊዜ አደርገዋለሁ አለ፤ ዕድሜ ያለው ይህን ነው፤

፮፤ ወገብረ እግዚአብሔር ዘ ነገረ በሳኒታሁ ወሞተ ኵሉ እንስሳ ግብጽ ወእምእንስሳ ደቂቀ እስራኤልሰ ኢሞተ ወኢአሐዱ፤

እግዚአብሔርም ዘ ነገረ እገብር እንዳለ በበነጋው ይኸን ነገር አደረገው፤ ገብረ ያለውን አመጣ፤



የግብጻውያን ከብት ሁሉ ሞተ ከእስራኤል ልጆች ከብት ወገን ግን አንድ ስንኳ አልሞተም፤

፯፤ ወሶበ ርእየ ፈርዖን ከመ ኢሞተ እምእንስሳ ደቂቀ እስራኤል ወኢአ ሐዱ ከበደ ልቡ ወኢፈነዎ ለሕዝብ፤

ፈርዖንም ከእስራኤል ልጆች ከብቶች ወገን አንድ ስንኳን እንዳልሞተ ባየ ጊዜ ልቡናው በክፋት ጸናበት፤ እስራኤል ንም አሰናብቶ አልሰደደውም፤ ይህንም ማድረጉ የእኔ ከብት ቢያልቅ የባሮቼ የእስራኤል ከብት የእኔ አይደለምን ብሎ ነው፤

፰፤ ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን ንሥኡ ለክሙ ምልዓ እደ ዊክሙ ሐመደ እምዕቶን ወይዝ ርዎ ሙሴ ውስተ ሰማይ በቅድመ ፈርዖን ወበቅድመ ዓበይቱ፤

እግዚአብሔርም ሙሴ አሮንን ከምድጃው በእጃችሁ ምሉ አመዱን አንሡታችሁ፤ አንድም የምድጃውን አመድ በእጃችሁ ምሉ አንሡታችሁ ዘግናችሁ በሹማምቶቹና በፈርዖን ፊት ሙሴ ወደ ሰማይ ይበትነው አላቸው፤

፱፤ ወይኩን ቆባር ውስተ ኵሉ ምድረ ግብጽ ወይኩን ፀልዕ ዘይ ፈልህ ዲበ ሰብእ ወዲበ እንስሳ ወዲበ ዘአርባዕቱ እግሩ በኵሉ ምድረ ግብጽ፤

ይኸውም በግብጽ አገር ሁሉ ጽጋግ ይሆናል፤ ይኸውም ጽጋጉ በሰውም በከብቱም በግብጽ አገርም አራት እግር ባለው ሁሉ ችፌ ቁጥኝ ዋጣ ጉርምጥ ይሆናል አላቸው፤

፲፤ ወነሥአ ሙሴ ሐመደ ዕቶን በቅድመ ፈርዖን ወዘረዎ ውስተ ሰማይ ወኮነ ፀልዕ ዘይፈልሕ ዲበ ሰብእ ወዲበ እንስሳ፤

ሙሴም የምድጃውን አመድ፤ አንድም ከምድጃው አመዱን በእጁ አንሥቶ በፈርዖን ፊት ወደ ሰማይ በተነው፤ በሰውም በከብቱም የሚወጣ ችፌ፤ ቁጥኝ፤ ዋጣ፤ ጉርምጥ ሆነ፤

፲፩፤ ወስዕኑ ሰብአ ሥራይ ቀዊመ ቅድመ ሙሴ በእንተ ፀልዕ እስመ አሐዞሙ ፀልዕ ለመሠርያን ወለ ኵሉ ሰብአ ግብጽ፤

የግብጽ ሰዎችን ሁሉና ሟርተ ኞች ኢያኔስ ኢያንበሬስን ችፌው ቁጥኙ ይዟቸዋልና ስለዚህ ነገር ሟርተኞች ኢያኔስ ኢያንበሬስ በሙሴ ፊት መቆም ተሳናቸው፤

፲፪፡ ወአጽንዐ እግዚአብሔር ልበ ለፈርዖን ወኢሰምዖሙ በከመ ነገሮሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን

እግዚአብሔርም የፈርዖንን ልቡና በክፋት አጸና፤ ለሙሴና ለአሮንም እግዚአብሔር ኢይሰምዓክሙ

www.ethiopianorthodox.org

ፈርዖን ብሎ እንደ ነገራቸው ቃላቸውን አልሰማውም፤

፲፫፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ጊሥ በጽባሕ ወቁም ቅድሜሁ ለፈርዖን ወበሎ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር አምላከ ዕብራውያን ፈኑ ሕዝብየ ከመ ይጸመዱኒ፣

እግዚአብሔርም ሙሴን ነገ ጧት ገሥግሠህ ሒደህ በፈርዖን ፊት ቁም፣ የዕብራውያን ፈጣሪ እግዚአብሔር በምድረ በዳው መሥዋዕት ሠውተው እንዲያገለግሉኝ ወገኖቼ እስራኤልን አሰናብተህ ስደድ ብሎሃል፣ ብለህ ንገረው አለው፣ እግዚአብሔርም እንዲህ ማድረጉ ከዛሬ ነገ ልብ አድርጎ በንስሐ ይመለሳል ብሎ ነው፤

፲፬፣ እስመ ይእዜ በዛ ጊዜ አነ እፌኑ ኵሎ መዓትየ ውስቴትከ ወበዓበይትከ ወበሕዝብከ ከመ ታእምር ከመ አልቦ ከማየ ውስተ ኵሉ ምድር፣

አንተ ይኸን ያላደረግህ እንደ ሆነ እኔም በዓለሙ ሁሉ እንደ እኔ ያለ ሌላ ገናና ፈጣሪ እንደ ሌለ ዕንድታውቅ በወገኖችህና በሹማምቶችህ በአንተም ቍጣዬን ሁሉ በዚህች ቀን አመጣብሃለሁ፣ እኮን አለ ብለህ ንገረው አለው፤

፲፭፣ ወይእዜኒ እፌኑ እዴየ ወእዘብጠከ ወለሕዝብከኒ ወእቀትለክሙ ወትትቀጠቀጥ ምድርክሙ፣

አሁንም እደ መዓቴን አምጥቼ አንተን ወገኖችህንም አጠፋችኋለሁ አገራችሁም ከዚህ የተነሣ ትጠፋለች አለ በለው አለው፤

ገባኤ

፲፮፣ ወበእንተዝ አነ ዐቀብኩከ ከመ አርኢ ብከ ጽንዕየ ወከመ ይትየዳዕ ስምየ ውስተ ኵሉ ምድር፤

እኔስ ስለዚህ ነገር እስከ ዛሬ ድረስ ዐቀብኩከ አስተደኃርኩከ፣ ከመከራው ወደ ኋላ አድርጌ ጠበቅሁህ፣ ኃይሌን ከሃሊነቴን በአንተ እገልጠው ዘንድ፣ ስሜም በቸርነት በዓለሙ ሁሉ ይነገር ዘንድ፣ እሱስ ታግሦት ነበር ፈርዖን ንስሐ አልገባ ብሎ ጠፋ እንጂ ተብሎ፤ አንድም አንሣእኩከ አንቃሕኩከ ይላል፣ ኃይሌን ከሃሊነቴን በአንተ እገልጠው ዘንድ ከግብጽ አነቃቅቼ አነሣስቼ አወጣሁህ፣ ወከመ ይትየዳዕ ስምየ፣ ፈርዖንን ከግብጽ አውጥቶ በኤርትራ አሰጠመው ተብሎ ስሜ ይነገር ዘንድ አንሣእኩከ አንቃሕኩከ አለ፣



፲፯፣ ወአንተሰ ዓዲ ታጸንዕ ሕዝብየ ወኢትፌንዎሙ፣

አንተ ግን በወገኖቼ በእስራኤል ዳግመኛ ልቡናህን በክፋት ታጸናባቸዋለህ፤ አንድም ታጸንሕ ይላል፣ ዳግመኛ ወገኖቼ እስራኤልን ታቆያቸዋለህ፣ አሰናብተህም አትሰድዳቸውም፤

፲፰፣ ናሁ አነ አዘንም ጌሠመ ዘጊዜ በረደ ብዙኃ ጥቀ ዘኢኮነ ከማሁ እምአመ ተፈጥረ ብሔረ ግብጽ እስከ ዛቲ ዕለት፣

እኔም የግብጽ አገር ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ተደርጎ የማይታወቅ ብዙ በረድን ነገ ይህን ጊዜ አዘንማለሁ፤

፲፱፣ ወይእዜኒ አፍጥን አስተጋብእ እንስሳከ ወኵሎ ዘብከ ውስተ ሐቅል እስመ ኵሉ ሰብእ ወእንስሳ ዘተረክበ ውስተ ሐቅል ወዘኢቦአ ቤተ ይወድቅ ዲቤሁ በረድ ወይመውት፣

አፍጥን ታስተጋብእ አፍጥን ወአስተጋብእ ይላል፣ በምድረ በዳ የተገኘ ከብትና ሰው ሁሉ ወደ ቤት ያልገባውም ሁሉ በእሱ ላይ በረዱ ይወድቅበታልና፣ እሱም ይሞታልና በምድረ በዳ ያለህን ገንዘብ ሁሉና ከብትህን ፈጥነህ ሰብስብ አለው፤

፳፣ ወዘፈርሀ ቃለ እግዚአብሔር እምዓበይተ ፈርዖን ያስተጋብእ እንስሳሁ ውስተ አብያት፣

ከፈርዖን ሹማምቶች የእኔን የፈጣሪውን የእግዚአብሔርን ቃል የፈራ ከብቱን ወደ ቤቱ ይሰበስባል፤

፳፩፣ ወዘኢሐለየሰ በልቡ ቃለ እግዚአብሔር የኃድግ እንስሳሁ ውስተ ገዳም፣

የእኔን የፈጣሪውን የእግዚአብሔርን ቃል በልቡናው ያላሰበ ሰው ግን ከብቱን በምድረ በዳው ይተዋል፤ አንድም መተርጒም እንዲህ አለ፣ ከፈርዖን ሹማምት የፈጣሪው የእግዚአብሔርን ቃል የፈራ ከብቱን ወደ ቤት ሰበሰበ፣ የፈጣሪው የእግዚአብሔርን ቃል በልቡናው ያላሰበ ሰው ግን ከብቱን በምድረ በዳ ተወ አለ፣ ቀዳማይ በካልአይ፣ ካልአይ በቀዳማይ ይተረጐማል ያለው ይህ ነው፤

፳፪፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ስፋሕ እዴከ ውስተ ሰማይ ወይኩን በረድ ዲበ ኵሉ ምድረ ግብጽ ዲበ ሰብእ ወዲበ እንስሳ ወዲበ ኵሉ ሣዕር ዘውስተ ኵሉ ምድር፣

እግዚአብሔርም ሙሴን እጅህን ወደ ሰማይ ዘርጋ፣ በግብጽ አገር ሁሉ በሰውም በከብቱም በግብጽ

www.ethiopianorthodox.org

አገር ሁሉ ባለው በሣሩ፤ አን ድም በእህሉ በረድ ይዝነም በት አለው፤

፳፫፣ ወሰፍሐ እዴሁ ሙሴ ውስተ ሰማይ ወወሀበ እግዚአብሔር ቃለ ወበረደ ወሮጸ እሳት ዲበ ምድር ወአዝነመ እግዚአብሔር በረደ ዲበ ኵሉ ምድረ ግብጽ፣

ሙሴ እጁን ወደ ሰማይ ዘረጋ፣ እግዚአብሔርም ቃለ መብረቅ ነጐድጓድ ወበረደ፣ በረዱን አመጣ እሳቱም በበረዱ መካከል ብልጭ ሲል /እያለ/ ይታይ ነበር፣ እግዚአብሔርም በግብጽ አገር ሁሉ በረዱን አዘነመ፤

፳፬፣ ወእሳቱ ይነድድ ውስተ በረድ ወበረድሰ ብዙኅ ጥቀ ወእዙዝ ዘኢኮነ ከማሁ እምአመ ተፈጥሩ አሕዛብ ውስተ ገጸ ምድር በግብጽ እስከ ይእቲ ዕለት፤

እሳቱም በበረዱ መካከል ብልጭ ይል ነበር፣ በረዱ ግን አሕዛብ በግብጽ ከተፈጠሩ ጀምሮ እስከዚያች ቀን ድረስ ተደርጎ የማያውቅ ብዙ ጽኑ ነበር፤

፳፭፣ ወቀተላ በረድ ለኵላ ምድረ ግብጽ እምሰብእ እስከ እንስሳ ወኵሎ ሣዕረ ዘውስተ ገዳም አማ ሰነ ወኵሎ ዕፀወ ዘውስተ ሐቅል ቀጥቀጠ፣

ከሰው ጀምሮ እስከ ከብት ድረስ የግብጽን አገር ሁሉ በረድ አጠ ፋት፣ በምድረ በዳም ያለውን ሣር ሁሉ፤ አንድም እኽሉን ሁሉ አጠፋ፣ በምድረ በዳም ያለውን ዕንጨት ሁሉ አጠፋ፤

፳፮፣ ዘእንበለ ምድረ ጌሤም ኀበ ሀለዉ ደቂቀ እስራኤል ኢወረደ በረድ፣

እስራኤል ባሉበት በጌሤም አገር በረዱው አልወረደም እንጂ ኵሎ ዕፀወ ቀጥቀጠ፣ ዕፀዋቱን ሁሉ አጠፋ፤

፳፯፣ ወለአከ ፈርዖን ወጸውዖሙ ለሙሴ ወለአሮን ወይቤሎሙ አበ ስኩ ይእዜሂ እግዚአብሔር ጻድቅ አንሰ ወሕዝብየ ረሲዓን፤

ፈርዖንም ሙሴ አሮንን ልኮ አስጠራቸው፣ እኔ ዛሬ በደልኩ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር እው ነተኛ ነው፣ ወገኖቼና እኔ ግን በደለኞች ሐሰተኞች ነን አላቸው፤ አንድም ፈጣሪያ ችሁ እግዚአብሔር ቸር ርኅ ሩኅ ነው፣ እኔና ወገኖቼ ግን በደለኞች ነን፤ አንድም አበ ስኩ ይእዜሂ እግዚአብሔርሂ ጻድቀ አንሰ ወሕዝብየ ረሲ ዓን ይላል፣ እኔ ዛሬ እውነተኛ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔርን በደልኩ፣ በደለኞች ወገኖቼም በደሉ አለ፤



፳፰፣ ጸልዩ እንከሰ ኀበ እግዚአ ብሔር ወይኅዳዕ እንከ ወኢይኩን ቃለ እግዚአብሔር በረድኒ ወእሳ ትኒ እፌንወክሙ ወኢያነብረክሙ ዳግመ፤

እንግዲህስ ወዲያ ወደ ፈጣሪ ያችሁ ወደ እግዚአብሔር ጸልዩልኝ፣ መቅሠፍቱም ጸጥ ዝግ ይበልልኝ፣ ቃለ እግዚአ ብሔር መብረቅ ነጐድጓድ ነው፣ በረዱም እሳቱም አይው ረድብኝ እንደ ቀድሞ ዳግመኛ በአገሬ አላኖራችሁም እሰናብቼ እሰድዳችኋለሁ አለው፤

፳፱፣ ወይቤሎ ሙሴ ለፈርዖን ሶበ ወፃእኩ እምሀገር አሌዕል እዴየ ኀበ እግዚአብሔር ወየኀድዕ ቃል፣ ወበረድኒ ወእሳትኒ ወዝናምኒ አልቦ እንከ ከመ ታእምር ከመ ለእግዚአብሔር ይእቲ ምድር፣

ሙሴም ፈርዖንን ከከተማ ከወ ጣሁ በኋላ እጄን ቃሌን ከፍ ከፍ አድርጌ ወደ እግዚአ ብሔር እለምናለሁ፣ ቃል መብረቅ ነጐድጓዱ እሳቱና በረዱም ጸጥ ይላል፣ ምድርም የእግዚአብሔር ገንዘብ እንደ ሆነች ታውቅ ዘንድ ዝናሙ አይዘንምም፤

፴፣ ወአንተሰ ወዓበይትከ አአምር ከመ እምአመ ኮንክሙ ኢፈራህክ ሙዎ ለእግዚአብሔር፣

ሹማምቶችህና አንተ ግን ከተ ፈጠራችሁ ጀምሮ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔርን እንዳልፈራ ችሁት እንዳላመለካችሁት እኔ አውቃለሁ፤

፴፩፣ ተላቤ ወሰገም ማሰነ ወሰገምሰ ዘእንበለ ይስብል ተዘብጠ ወተላቤ በዘአውዕአ ዘርአ፣

ተላቤ ተልባው ገብሱ ጠፋ፣ ዘእንበለ ይስብል፣ ሳይዘረዝር፤ አንድም ዘእንበለ ይብስል ይላል፣ ሳይሸት ገብሱ ጠፋ ተልባው ግን ሲዘረዝር ጠፋ፤

፴፪፣ ወሥርናይ ወአተር ኢተዘ ብጠ እስመ ብሱል ውእቱ፣

እሸቱ ደርቆ ነበርና አተርና ስንዴው አልተመታም፣ ይህማ የሸተ የደረቀ አይመታምን ብሎ እሸቱ ደርቆ ተወቅቶ ገብቶ ተከትቶ ነበርና፤

፴፫፣ ወወፅአ ሙሴ እምኀበ ፈርዖን አፍአ እምሀገር ወአልዐለ እዴሁ ኀበ እግዚአብሔር ውኅድዐ ቃል ወበረድ ወዝናምኒ ኢነፍነፈ እንከ ዲበ ምድር፣

ሙሴም ከፈርዖን ዘንድ ከከተማ በአፍአ ሁኖ እጁን ቃሉን ከፍ ከፍ አድርጎ ወደ እግዚአ ብሔር ለመነ፣ መብረቅ ነጐ ድጓድ በረድ ጸጥ አለ፣ በግብጽ አገር ዝናሙ ስንኳን አላካ ፋም፤

www.ethiopianorthodox.org

፴፬፣ ወሶበ ርእየ ፈርዖን ከመ ኀድዓ ዝናም ወበረድ ወቃል ወሰከ አብሶ ወአክበደ ልቦ ውእቱ ወዓበይቱሂ፣

ፈርዖንም መብረቅ ነጐድጓዱ በረዱና ዝናሙ ጸጥ እንዳለ ባየ ጊዜ በበደል ላይ በደል ጨመረ፣ ልቡናውን በክፋት አጸና የሹማምቱንም ልቡና በክፋት አጸና፤ አንድም አክበደ ልቦ ወዓበይቱሂ ይላል፣ ፈርዖን ልቡናውን በክፋት አጸና፣ ሹማምቶቹም እንደ እሱ ልቡናቸውን በክፋት አጸኑ፣ ንጉሡ ቢያጐብጥ ሠራዊቱም አጎንብሶ ሔደ እንዲሉ፤

፴፭፣ ወጸንዐ ልቡ ለፈርዖን ወኢፈነዎሙ ለደቂቀ እስራኤል በከመ ነገሮ እግዚአብሔር ለሙሴ፣

የፈርዖን ልቡናው በክፋት ጸና እግዚአብሔርም ኢይፌኑ ወክሙ ብሎ ለሙሴ እንደ ነገረው የእስራኤልን ልጆች አሰናብቶ አልሰደዳቸውም::

## ምዕራፍ ፲

፩፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ባእ ኀበ ፈርዖን እስመ አነ አክበድኩ ልቦ ለፈርዖን ወለዓበይቱሂ ከመ ዕሩየ ይምጽእ ተአምርየ ላዕሌሆሙ፣

እግዚአብሔርም ሙሴን መቅሠፍቱ በሹማምቶቹና በፈርዖን ተካክሎ እንዲመጣባቸው እኔ የሹማምቱና የፈርዖንን ልቡና በክፋት አጽንቼባቸዋለሁና ወደ ፈርዖን ግባ አለው፤

፪፣ ወከመ ትንግሩ ለደቂቅክሙ ወለደቂቀ ደቂቅክሙ ኵሎ ዘተሣለቁ በግብጽ ወተአምርየ ዘገበርኩ ቦሙ ወታእምሩ ከመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር፣

መቅሠፍቱም በሹማምቱና በፈርዖን ተካክሎ ይመጣባቸው ዘንድ እናንተም በግብጽ ሰዎች የዘበትኩባቸውን ሁሉ ያደረግሁባቸውንም ተአምራት ሁሉ ለልጆቻችሁ ለልጅ ልጆቻችሁም ትነግሩ ዘንድ፤ ይህንም ሁሉ ነገር ያደረግሁ እኔ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር እንደ ሆንኩ ታውቁ ዘንድ፤ እኔ የሹማምንቱንና የፈርዖንን ልቡና በክፋት አጽንቼዋለሁና፣ እግዚአብሔር ሙሴን ወደ ፈርዖን ግባ አለው፤ አንድም ወተአምሩ ይላል፣ አንተ የላክሁህን ወደ ፈርዖን ገብተህ ንገር፣ ይኸንም ሁሉ ነገር ያደረግሁ እኔ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር እንደሆንኩ ኋላ ታውቃላችሁ አለው፤

፫፣ ወቦኡ ሙሴ ወአሮን ቅድመ ፈርዖን ወይቤልዎ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር አምላከ ዕብራውያን እስከ



ምንትኑ ተዓቢ ኃፊሮትየ ወኢትፌኑ ሕዝብየ ከመ ይፀመዱኒ፣

ኀበ ፈርዖን ሲል ነው፣ ሙሴ አሮን ወደ ፈርዖን ገቡ፤ አንድም እንዳለ ይሆናል፣ መግባትም ፊት ለፊት ነውና ገብተውም የዕብራውያን ፈጣሪ እግዚአብሔር እንዲህ አለ፣ እኔን የማታፍረኝ ምን እስክትሆን ድረስ ነው? አንድም እስከ ማእዜኑ፣ እኔን የማታፍረኝ እስከ መቼ ድረስ ነው? በምድረ በዳውስ መሥዋዕት ሠውተው እንዲያገለግሉኝ ወገኖቼ እስራኤልን አሰናብተህ የማትሰድዳቸው እስከ መቼ ድረስ ነው? አለ እግዚአብሔር አሉት፤

፬-፭፣ ወእመሰ ዐበይከ ፈንዎተ ሕዝብየ ናሁ አነ አመጽእ ጌሠመ ዘ ጊዜ አንበጣ ብዙኀ ዲበ ኵሉ አድባሪከ ወይከድን ገጸ ለምድር ወኢትክል ርእዮታ ለምድር ወይበልዕ ኵሎ ተረፈ ዘተርፈ ውስተ ምድር ዘአትረፈ በረድ ወይበልዕ ኵሎ ዕፀ ዘአብቈልክሙ ውስተ ምድር፣

አንተ ወገኖቼ እስራኤልን አሰናብቶ መስደዱን እምቢ ካልክ እኔም ነገ ይህን ጊዜ በተራራህ ሁሉ ብዙ አንበጣን አመጣለሁ፣ እሱም ምድርን በብዛት ይሸፍናታል፣ አንተም ምድርን ማየት አይቻልህም፤ አንድም ወኢትክል ፈርዮታ ይላል፣ ምድርም ማፍራት አይቻላትም፣ አንበጣውም በረድ ያስቀረውን በግብጽ የቀረውን ሁሉ ፈጽሞ ይበላዋል አለህ አሉት፣ አሁን በረዱ ለአንበጣው ይሆናል ብሎ አይደለም፣ ከበረድ የቀረውን አንበጣ ይበላዋል ሲል ነው፣ በግብጽ የተከላችሁትን ሁሉ ሰንደሉንም ሁሉ ይበላዋል፤

፮፣ ወይመልዕ አብያቲከ ወዘዓበይትከ ወኵሎ አብያተ ዘውስተ ምድረ ግብጽ ዘእምአመ ኮኑ ኢርአዩ አበዊክሙ ወኢእምቅድሜሆሙ ወኢአማሑቶሙ እምአመ ተፈጥሩ አሕዛብ ውስተ ምድር እስከ ዛቲ ዕለት ወተግኅሠ ወወፅአ እምኀበ ፈርዖን፣

አሕዛብ በዚህ ዓለም ከተፈጠሩ ጀምሮ እስከዚህች ቀን ድረስ አባቶቻችሁ፣ አያቶቻችሁ፣ ወኢአማሑቲክሙ፣ ቅድም አያቶቻችሁ፤ አንድም አባቶቻችሁ ወኢእምቅድሜሆሙ አባቶቻቸው፣ ወኢአማሑቶሙ አያቶቻቸው፤ አንድም ለአሕዛብ ነው፣ አበዊሆሙ አባቶቻቸው፣ ወኢእምቅድሜሆሙ አያቶቻቸው፣ ወኢአማሑቶሙ፣ ቅድም አያቶቻቸው፤ አንድም አይለወጥም፤ አበዊሆሙ ለአሕዛብ፣ የአሕዛብ አባቶቻቸው፣ ወኢእም

www.ethiopianorthodox.org

ቅድሚሆሙ፣ የአባቶች አባቶ ቻቸው፣ ወኢአማሐቶሙ የአባ ቶች አያቶቻቸው ከተፈጠሩ ጀምሮ አይተውት ሰምተውት የማያውቁ አንበጣ በቤትህ በሹማምቶችህ ቤት በግብጽ አገር ባለው ሰው ሁሉ ቤትም ይመላል አለ እግዚአብሔር አሉት፣ ይህንም ነገር ተናግረው ሙሴ አሮን ከፈርዖን ዘንድ ወጥተው ሔዱ፤

፯፣ ወይቤልዎ ዓበይቲ ለፈርዖን እስከ ማዕዜኑ ትከውን ላዕሌነ ዛቲ እኪት ዕፅብት ፈኑ ሰብአ ከመ ይጸመድዎ ለእግዚአብሔር አምላ ኮሙ አው እንዘ ተአምርኑ ትፈ ቅድ ከመ ትትኀጐል ምድረ ግብጽ፣

የፈርዖን ሹማምቱ ይህች ጭንቅ መከራ በእኛ የምትደረግብን እስከመች ድረስ ነው? አሁንም እኒህ እስራኤልን መሥዋዕት ሠውተው ለፈጣሪያቸው ለእግዚ አብሔር እንዲያገለግሉ አሰና ብተህ ስደድ፣ ወይስ እያወቅህ የግብጽ አገር ልትጠፋ ትወዳ ለህን አሉት፤

፰፣ ወጸውዕዎሙ ለሙሴ ወለአሮን ኀበ ፈርዖን ወይቤሎሙ ፈርዖን ሑሩ ወተፀመድዎ ለእግዚአብሔር አምላ ክክሙ ወባሕቱ መኑ ወመኑ አን ትሙ እለ ተሐውሩ፣

ይህንም ብለው አልቀሩ ቢሠ ለጥኑ ሙሴ አሮንን ጠርተው ወደ ፈርዖን አመጧቸው፣ ፈርዖ ንም ሲያልበው ሲጨንቀው ሒዱ አላቸው፤ እንድም ወጸው ዖሙ ይላል፣ ፈርዖን የሹማምቱን ምክር ሰምቶ ሙሴ አሮንን አስጠርቶ ወደ እሱ አመጣቸው፣ ለፈጣሪያችሁ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ሠውታችሁ ልታገ ለግሉት መሔዱንስ ሒዱ፣ ነገር ግን መሥዋዕት ልትሠዉ የምትሔዱት ማንና ማናችሁ? አላቸው፤

፱፣ ወይቤሎ ሙሴ ምስለ ወራዙ ቲነ ወአዕሩጊነ ነሐውር ወምስለ ደቂቅነ ወአዋልዲነ ወአባግዒነ ወአልሕምቲነ ንወስድ እስመ በዓለ እግዚአብሔር አምላክነ ወእቱ፣

ሙሴም የፈጣሪያችን የእግዚ አብሔር በዓል ነውና ከሽማግ ሎችና ከጐልማሶች ጋራ ከሴቶች ልጆቻችንና ከወንዶች ልጆቻችንም ጋራ እንሔዳለን፣ ላሞቻችንንምና በጎቻችንንም ይዘን እንሔዳለን አለው፤

፲፣ ወይቤሎ ፈርዖን ይኩን ከመዝ እግዚአብሔር ምስሌክሙ ናሁ ኪያ ክሙሰ እፌንወክሙ ወንዋየክሙሂ አእምሩኬ ከመ እኪተ ትሔልዩ፣

ፈርዖንም አሁን እንደ ተናገር ከው ይሁን ሒዱ አለው፣ ክዳት ተንኰል ልማዱ ነውና እግዚ አብሔር በረድኤት አድሮባ ችሁ ይኑር አለው፤ አንድም



ግብጻውያን ሰው መመረቅ ልማዳቸው ነውና እኔ እናንተን ግን እነሆ አሰናብቼ እሰድዳ ችኋለሁ፣ ልጆቻችሁን ገንዘባ ችሁን እንውሰድ ማለታችሁ ግን ክዳት ተንኰል እንዳ ሰባችሁ ዕወቁ አለ፣ እንደ ራሱ መስሎት ነው፤

፲፩፣ ከመገዞ የሐውር ሰብእ ዘይ ፀመዶ ለእግዚአብሔር ምንተ እንከ ተኃሥሡ ወአውፅእዎሙ እፍአ እምገጸ ፈርዖን፣

እግዚአብሔርን የሚያገለግል ሰው እንዲህ ሁኖ ይሔዳልን፤ አንድም ይፀመዶ ይላል፣ ሰው ፈጣሪው እግዚአብሔርን ሊያገ ለግል እንዲህ ሁኖ ይሔዳልን እንግዲህ ወዲያ ምን ትፈል ጋላችሁ? ብሎ ተቈጣ፣ ያንጊዜ የሰለጠኑ አሽከሮች ባለሟሎች የልቡናውን አውቀው እየገፉ እየዳፉ ከፈርዖን ፊት አወጧ ቸው፤ አንድም አውፅእሙ እፍአ ይላል፣ እሱ ተቈጥቶ ወግዱልኝ ከፊቴ ብሎ ሙሴ አሮንን አስወጣቸው፤

፲፪፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ስፋሕ እዴከ ዲበ ምድረ ግብጽ ወይዕርግ አንበጣ ዲበ ምድር ወይብላዕ ኵሎ ሣዕረ ምድር ወኵሎ ፍሬ ዕፀ ዘአትረፈ በረድ፣

እግዚአብሔርም ሙሴን በግብጽ አገር እጅህን ዘርጋ፣ ወደ ግብጽ አገርም አንበጣው ይውጣ፤ የግ ብጽን ሣር ሁሉ፤ አንድም የግ ብጽን እህል ሁሉ በረድ ያስቀ ረውን የዕንጨቱንም ፍሬ ሁሉ አንበጣ ይብላው አለው፣ አሁን በረዱ ለአንበጣ ይሆናል ብሎ አስቀርቶት አይደለም፣ ከበረድ የቀረውን አንበጣ ይብላው ሲል ነው፤

፲፫፣ ወአልዓለ ሙሴ በእዴሁ በትሮ ውስተ ሰማይ ወአምጽአ እግዚአብሔር ነፋሰ አዜብ ውስተ ምድር ኵላ ይእተ ዕለተ ወኵላ ይእተ ሌሊተ እስከ ጸብሐ ወገዘኡ ነፋሰ አዜብ ነሥአ ለአንበጣ፣

ሙሴም በእጁ በትሩን ወደ ሰማይ ከፍ ከፍ አድርጎ ጸለየ፣ እግዚአብሔርም በግብጽ አገር እስኪነጋ ድረስ አንድ መዓልት አንድ ሌሊት የአዜብን ነፋስ አመጣ፣ ያም የአዜብ ነፋስ አንበጣውን ወደ ግብጽ አገር ወሰደው፤

፲፬፣ ወአምጽአ ኀበ ምድረ ግብጽ ወነበረ ዲበ ኵሉ በዙኃ ጥቀ ወእዙዝ ዘእምቅድሜሁ ኢኮነ ከማሁ አንበጣ ወእምድኅሬሁ ኢይከውን ከማሁ፣

ነፋሱም አንበጣውን ወደ ግብጽ አገር አመጣው፣ አንበጣውም በግብጽ አገር ሁሉ ሰፍሮ ኖረ፣ አንበጣውም ከዚህ ቀድሞ እን ደዚህ ያለ ተደርጎ የማያውቅ

www.ethiopianorthodox.org

እንግዲህም ወዲያ እንደዚህ ያለ ይደረጋል የማይባል እጅግ ብዙ ጽኑ ነው፤ /ነበር/

፲፭፣ ወከደኖ ገጸ ምድር ወማሰነት ምድር ወበልዐ ኵሎ ሣዕረ ምድር ወኵሎ ፍሬ ዕፅ ዘተርፈ እምበረድ ወኢተርፈ ሐመልማል ውስተ ዕፀው ወኢአሐቲ ወኢውስተ ኵሉ ሣዕረ ሐቅል በኵሉ ምድረ ግብጽ፣

አንበጣውም በብዛት የግብጽን አገር ሸፈነው፣ ምድርም እልም ድርግም ብላ ጠፋች፣ ጣፋን፤ አንድም እህሉን ሁሉ ከበረድ የቀረውን የዕንጨቱንም ፍሬ ሁሉ በላው፣ በዕንጨቱም ሁሉ ልምላሜ አልቀረም፣ ከዕን ጨቱ ሁሉ አንዲት ዕንጨት ስንኳን በልምላሜ አልተገ ኘችም፤ አንድም በአንዲቱ ዕንጨት አንዲት ቅጠል አልተገኘችም፣ ወኢአሐዱም ይላል፣ በግብጽ አገር ባለው ሣዕር ሁሉ፤ አንድም በእህሉ ሁሉ ልምላሜ አልተገኘበትም፤

፲፮፣ ወአፍጠነ ፈርዖን ጸውዖቶሙ ለሙሴ ወለአሮን ወይቤሎሙ አበስኩ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክክሙ ወዲቢክሙ፣

ያንጊዜም ፈርዖን ሙሴ አሮንን ፈጥኖ አስጠርቶ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔርን ኪያክሙ ሲል ነው፣ እናንተንም በደልኹ፤

፲፯፣ ሥረዩ እንከ እንተ ይእዜኒ ዓዲ አበሳየ ወጸልዩ ኀበ እግዚአብሔር አምላክክሙ ይሰስል እምኔየ ዝ ሞት፣

እናንተም አሁን ዛሬ የበደል ኹትን በደል ይቅር በሉኝ፣ ይህም ሞት ከእኔ ይርቅልኝ ዘንድ ወደ ፈጣሪያችሁ ወደ እግዚአብሔር ለምኑልኝ፤ አን ድም ወይሰስል እምኔየ ይላል፣ እናንት ወደ ፈጣሪያችሁ ወደ እግዚአብሔር ለምኑልኝ፣ ይህም ሞት ከእኔ ይራቅልኝ አላቸው፤

፲፰፣ ወወፅአ ሙሴ እምኀበ ፈርዖን ወጸለየ ኀበ እግዚአብሔር፣

ሙሴም ከፈርዖን ዘንድ ወጥቶ ሒዶ ወደ እግዚአብሔር ለመነለት፤

፲፱፣ ወሜጠ እግዚአብሔር ነፋሰ እምባሕር ዐቢይ ወነሥኦ ለአንበጣ ወወሰዶ ውስተ ባሕረ ኤርትራ ወኢተርፈ ወኢአሐዱ አንበጣ ውስተ ኵሉ ምድረ ግብጽ፣

ነፋስ ዐቢየ እምባሕር ዐቢይ ይላል ዘር፣ እግዚአብሔርም ያንጊዜ ከታላቁ ባሕር ጽኑውን ነፋስ ወደ ግብጽ መለሰው ነፋሱም አንበጣውን ከግብጽ አገር አንሥቶ ወደ ኤርትራ ባሕር ወሰደው፣ በግብጽ አገርም ሁሉ አንድ አንበጣ ስንኳን አልቀረም፤



፳፣ ወአጽንዐ እግዚአብሔር ልቦ ለፈርዖን ወኢፈነዎሙ ለደቂቀ እስራኤል፣

እግዚአብሔርም የፈርዖንን ልቡና በክፋት አጸና፣ ፈርዖንም የእስራኤልን ልጆች አሰናብቶ አልሰደዳቸውም፤

፳፩፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ስፋሕ እዴከ ውስተ ሰማይ ወይኩን ጽልመት ውስተ ኵሉ ምድረ ግብጽ ጽልመት ዘይመረስስ፣

እግዚአብሔርም ሙሴን እጅህን ወደ ሰማይ ዘርጋ፣ በግብጽ አገርም ሁሉ ጨለማ ይሁን፣ ይኸውም ጨለማው ደኅነኛ ሰው በመዓልት ኀዳናው ጠፍቶበት የሚዳሰስበት፣ ኀዳናውን የሚፈልግበት ግዙፍ ጨለማ ነው፤ አንድም ዘይትገሠሥ ይላል፣ ይኸውም ጨለማ በእጅ የሚያዝ የሚዳሰስ የሚመስል ግዙፍ ጨለማ ነው አለው፤

፳፪፣ ወሰፍሐ ሙሴ እዴሁ ውስተ ሰማይ ወኮነ ጽልመት ወቆባር ዲበ ኵሉ ምድረ ግብጽ ሠሉሰ ዕለተ፣

ሙሴም እጁን ወደ ሰማይ ዘረጋ፣ በግብጽም አገር ሁሉ ሦስት ቀን ጭጋግና ጨለማ ሆነ፤

፳፫፣ ወኢርእየ አሐዱ ካልአ ወአ ልቦ ዘተንሥአ እምስካቡ ሠሉሰ ዕለተ ወለኵሉ ደቂቀ እስራኤልሰ በርሃ በኵሉ ኀበ ህለዉ፣

ያንጊዜም ከጨለማው ጽናት የተነሣ አንዱ አንዱን አያየ ውም ነበር፣ ሦስቱንም ቀን ሁሉ ከመኝታው የተነሣ ሰው አልነበረም፣ ለእስራኤል ልጆች ሁሉ ግን በአሉበት ቦታ ሁሉ ብርሃን ነበር፤

፳፬፣ ወፀውዖሙ ፈርዖን ለሙሴ ወለአሮን ወይቤሎሙ ሑሩ ወተፀመድዎ ለእግዚአብሔር አምላክ ክሙ እንበለ አባግዒክሙ ወአልሕም ቲክሙ ዘተኀድጉ ወደቂቀክሙሰ ንሥኡ ምስሌክሙ፣

ፈርዖንም ሙሴ አሮንን ጠርቶ ትታችሁት የምትሔዱት ላሞ ቻችሁንና በጎቻችሁን ነው እንጂ፣ ፈጣሪያችሁ እግዚአብ ሔርን ሒዳችሁ መሥዋዕት ሠውታችሁ አገልግሉት፣ ልጆ ቻችሁን ግን በዓል ነውና ከእናንተ ጋር ውሰዷቸው አላቸው፤

፳፭፣ ወይቤሎ ሙሴ ለፈርዖን አልቦ አንተኑ ዓዲ ትሁበነ ለመሥ ዋዕት ዘንገብር ለእግዚአብሔር አምላክነ እብነኑ ንገብር፣

እንበለ አባግዒክሙ ወአልሕም ቲክሙ ዘተኃድጉ ቢለው ሙሴም ፈርዖንን አይደለም አለው፣ ለፈጣሪያችን ለእግዚአ

www.ethiopianorthodox.org

ብሔር ለምናቀርበው መሥዋ ዕት ገና አንተ ትሰጠናለህን፣ በምድረ በዳውስ መሥዋዕት ሠዉልኝ ባለን ጊዜ ደንጊያውን መሥዋዕት አድርገን እናቀር በዋለን? አለው፣ ደንጊያ ከከተማ ይልቅ በምድረ በዳ በዝቶ ይገኛልና፤

፳፮፣ ወእንስሳነሂ የሐውር ምስሌነ ወኢንነድግ ወኢምንተኒ እስመ እምኔሁ ንነሥእ ለመሥዋዕተ እግዚአብሔር አምላክነ ወንሕነሰ ኢነአምር ምንት ውእቱ ተፀምዶ ለእግዚአብሔር አምላክነ እስከ ንበጽሕ ህየ፤

ለፈጣሪያችን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ሊሆን ከላሙ ከበጉ እናቀርባለንና እኛም ከዚያው እስክንደርስ ድረስ በጎዳና ሰዉልኝ፤ አንድም ከዚያው ደርሰን ላም ሠዉልኝ፣ በግ ሠዉልኝ፣ ይለን እንደ ሆነ አናውቅምና ላሞችን በጎችን አብሮን ከእኛ ጋር ይሔዳል፣ እኛም ከላሞችን ከበጎችን ምንም ምን አንተውም አለው፤

፳፯፣ ወአጽንዐ እግዚአብሔር ልቦ ለፈርዖን ወአበየ ፈንዎቶሙ ለደቂቀ እስራኤል፣

እግዚአብሔርም የፈርዖንን ልቡና በክፋት አጸና፣ ፈርዖንም የእስራኤልን ልጆች አሰናብቶ መስደዱን እንቢ አለ፤

፳፰፣ ወይቤሎ ፈርዖን ለሙሴ ሑር እምኔየ ወዑቅ ርእሰከ ዳግመ እንከ እመ ርኢከ ገጽየ ወእም ከመ ርኢኩከ ዳግመ ትመውት፣

ፈርዖንም ሙሴን ወግድ ከፊቴ፣ አንተ የእኔን ፊት ያየኸው እንደሆነ፣ እኔም ዳግመኛ አንተን ያየሁ እንደሆነ እንግዲህ ወዲያ ለራስህ ዕወቅ፤ አንድም ዳግመኛ አንተ ፊቴን ያየህ እንደሆነ፣ እኔም አንተን ዳግመኛ ያየሁህ እንደሆነ ለራስህ ዕወቅ፣ ትመውት ማንኛ ነው፤ አንድም ዳግመኛ አንተ የእኔን ፊት ያየኸው እንደሆነ እኔም ዳግመኛ አንተን ያየሁ እንደሁ ትሞታለህ አለው፤

፳፱፣ ወይቤሎ ሙሴ አሆ ኢይሬኢ እንከ ገጸከ፣

ሙሴም እሺ በጎ እንግዲህ ወዲያ ፊትህን አላይም አለው፣ ፍና ተሣልቆ ነው፤ አንድም በእውነቱ ነው፣ ኋላ በሥጥመት የሚሆነውን ትንቢት ተናገረ።

## ምዕራፍ ፲ወ፩

፩፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ዓዲ አሐተ መቅሠፍተ አመጽእ ዲበ ፈርዖን ወዲበ ግብጽ ወእምድኅረዝ ይፌንወክሙ እምዝየ ወአመ



ይፌንወክሙ ምስለ ኵሉ ንዋየ ፀአት ያወፅአክሙ፣

እግዚአብሔርም ሙሴን በግብጽ ሰዎችና በፈርዖን ገና አንዲት መቅሠፍት አመጣለሁ አለ፣ ሞተ በኵር ነው፣ ከዚያ በኋላ ግን ከግብጽ አሰናብቶ ይሰድ ዳችኋል ሲሰድዳችሁም እንዲያው አይሰድዳችሁም መነሻ ካሣ ሰጥቶ ከግብጽ ያወጣች ኋል አለው፤

፪፣ ወንግሮሙ ጽሚተ በዕዝኖሙ ለሕዝብ ወይትወሐስ ፩ዱ እምካልኡ ውብእሲትኒ እምካልእታ ንዋየ ብሩር ወወርቅ ወልብስ፣

ይህንንም ነገር ለወገኖችህ ለእስ ራኤል ቀስ ብለህ በጆሮአቸው ንገራቸው አለ፣ አሐተ መቅሠ ፍተ ያለውን፤ አንድም ወይት ወሐስ ፩ዱ እምካልኡ ያለውን ነው፣ አንዱ ከአንዱ፣ ጎረቤት ከጎረቤቷ፣ ገረድም ከእመቤቷ የብሩንና የወርቁን የልብሱን ዕቃ፤ አንድም ወልብሰ ይላል፣ ልብሱንም ትዋስ እስከ ሦስት ቀን ድረስ በዓል እናደርጋለን ብላችሁ በዝብዛችኋቸው ውጡ አለው፣ ምነው ምክንያት ሆና ችሁ የሰው ገንዘብ አታጥፉ ይል የለምን ስለ ምን እንዲህ አለ? ቢሉ ሊቁ ህየንተ ተቀንየ ተቀንዩ፣ ወህየንተ ገብሩ ግንፋለ

ብሎ ወስዶታል፣ አን፣ ፊቶም ራምሴ የሚባሉ ሦስት ቅጽር አስቀጽረዋቸው ነበርና የዚያ ካሣ ነው፣ የዚያ ዋጋ ነው አለ እግዚአብሔር፣ ሊቁ ባወቀው ዋጋ ሆናቸው ማለቱ ነው፤

፫፣ ወወሀቦሙ እግዚአብሔር ለሕ ዝብ ሞገሰ ቅድመ ግብጽ ወአው ሐስዎሙ ወዝ ብእሲ ሙሴ ዓቢየ ኮነ ጥቀ ቅድመ ግብጽ ወቅድመ ፈርዖን ወቅድመ ዓብይቱ፣

እግዚአብሔርም ለወገኖቹ ለእስ ራኤል በግብጻውያን ፊት ባለሟ ልነትን ሰጣቸው አለ፣ መሟሪያ እንዲያውሷቸው አደረገ ሲል ነው፣ አውሱን ያሏቸውን ዕቃ ሁሉ አዋሷቸው፣ ይህንም የተ ናገረ ሙሴ በግብጽ ሰዎች በሹ ማምቱና በፈርዖን ፊት ፈጽሞ ከበረ፣ ገነነ፤

፬፣ ወይቤ ሙሴ ከመዝ ይቤ እግዚ አብሔር መንፈቀ ሌሊት እበውእ አነ ማዕከለ ግብጽ፣

ሙሴም እግዚአብሔር እንዲህ አለ፣ በመንፈቀ ሌሊት ወደ ግብጽ ሰዎች መካከል እገባለሁ ብሎ ተናገረ አለ፤

፭፣ ወይመውት ኵሉ በኵር በምድረ ግብጽ እምበኵረ ፈርዖን ዘይነብር ዲበ መንበረ መንግሥት እስከ በኵረ አመት እንተ ትነብር

www.ethiopianorthodox.org

ዲበ ማኅረዕ ወእስከ ኵሉ በኵረ እንስሳ፣

በመንግሥቱ ዙፋን /ከሚቀመጥ/ ከሚጋደም ከፈርዖን በኵር ጀምሮ በወፍጮ እግር ሥር እስከምትተኛ ምርኮኛ ባሪያ በኵር ድረስ፤ እስከ ከብቱ በኵር ሁሉ በግብጽ አገር በኵር በኵሩ ይሞታል አለ እግዚአ ብሔር፤

፮፣ ወይከውን ጽራሕ ዐቢይ በኵሉ ምድረ ግብጽ ዘከማሁ ኢኮነ ወኢይ ከውንሂ እንከ ዘከማሁ፣

ከዚህ ቀድሞ እንደዚህ ያለ ተደርጎ የማያውቅ፣ እንግዲ ህም ወዲያ እንደዚህ ያለ የማ ይደረግ ብዙ ጩኸት በግብጽ አገር ሁሉ ይደረጋል፤ /ይሆናል/ አለ እግዚአብሔር፤ አንድም ነቢዩ ሙሴ በግብጽ በኵር በኵሩ ይሞታል፣ ከዚህም ቀድሞ ተደርጎ የማያውቅ ጩኸት ይደረጋል አለ፤

፯፣ ወለኵሉ ደቂቀ እስራኤል ከልብ ጥቀ ኢይልሕሶሙ በልሳኑ እምሰብእ እስከ እንስሳ ከመ ታእምር መጠነ ይሴባሕ እግዚአ ብሔር ማዕከለ ግብጽ ወማዕከለ እስራኤል፣

በእስራኤልና በግብጻውያን መካከል እግዚአብሔር ተአምራት አድርጎ የሚመሰገነውን ምስጋና እንድታውቅ፤ አንድም እግዚአ ብሔር በእስራኤልና በግብጻ ውያን መካከል ተአምራት አድርጎ እንዲመሰገን ልታውቅ ከሰው ጀምሮ እስከ ከብቱ ድረስ የእስራኤልን ልጆች ሁሉ ግን ውሻ በምላሱ ስንኳ አይል ሳቸውም አለ፣ የውሻ ምላሱ ልዝብ ነው፣ ጥቂት ስንኳን መከራ አይመጣባቸውም ሲል ነው፤

፰፣ ወይወርዱ እሉ ኵሎሙ ደቂቅ ኀቤየ ወይሰግዱ ሊተ ወይብሉኒ ጻእ አንተ ወሕዝብከ ይእዜ እምዛ ምድር ወእምድኅረዝ አወፅአ ወወፅአ ሙሴ እምኀበ ፈርዖን በመዓት፣

ይመጽኡ ሲል ነው፣ በዚያ ወራት የእስራኤል ልጆች ሁሉ ወደ እኔ መጥተው ለኔ ይሰግ ዱልኛል፣ ዛሬ ከዚህች ሀገር ከግብጽ ወገኖችህና አንተ ውጣ ይሉኛል፣ ከዚያ በኋላ ከግብጽ እስራኤልን ይገርው እወጣለሁ አለ እግዚአብሔር፤ አንድም ነቢዩ ሙሴ በተገለ ጠለት ትንቢቱ የእስራኤል ልጆች ሁሉ ወደኔ ይመጣሉ፣ በኔ ትንቢት በእኔ መልእክት አምነው ለእግዚአብሔር ይሰግ ዳሉ፣ ወገኖችህና አንተም ዛሬ ከዚህች አገር ከግብጽ ውጣ ይሉኛል፣ ከዚያ በኋላ ወገኖቼ እስራኤልን ከግብጽ አወጣቸዋለሁ አለ ሙሴ፣ አወፅአሙ ብሎ ነው፣ ወወፅአ



ሙሴ የተሳለፈ ነው፣ እመ ርኢከ ገጽየ ወእምከመ ርኢኩከ ዳግመ ትመውት ቢለው /ብሎት ነበርና/ ሙሴ ከፈርዖን ፊት ተቈጥቶ ወጣ፤ አንድም እምከመ ርኢኩከ ዳግመ ትመ ውት ብሎ ፈርዖን ቢቆጣው ሙሴ ከፈርዖን ፊት ወጥቶ ሔደ፤

፱፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ኢይሰምዐክሙ ፈርዖን ከመ አብዝኃ ተአምርየ ወመድምምየ በምድረ ግብጽ፣

እግዚአብሔርም ሙሴን በግብጽ አገር ፍጹም ተአምራቴን አብዝቼ አደርገው ዘንድ ፈርዖን የነገራ ችሁትን ቃል አይሰማችሁም አለው፤

፲፣ ወሙሴ ወአሮን ገብሩ ኵሎ መድምመ በቅድመ ፈርዖን ወአጽንዐ እግዚአብሔር ልቦ ለፈርዖን ወአበየ ፈንዎቶሙ ለደቂቀ እስራኤል እምድረ ግብጽ፣

ሙሴና አሮንም አበዝኀ ያለውን ተአምራቱን በፈርዖን ፊት አብዝተው አደረጉ፣ እግዚአብ ሔርም የፈርዖንን ልቡና በክፋት አጸናው፣ ፈርዖንም የእስራኤልን ልጆች ከግብጽ አገር አሰናብቼ አልሰድም አለ።

# ምዕራፍ ፲ወ፪

## ገባኤ

፩-፪፣ ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን በምድረ ግብጽ ዝ ወርኅ ቀዳማየ አውራኅ ይኩንክሙ ወአቅድምዎ እምአውርኃ ዓመት፣

እግዚአብሔር ሙሴና አሮንን በግብጽ አገር እንዲህ አላቸው፣ ይህን ወር ከወራቱ ሁሉ አስቀ ድማችሁ የምታከብሩት ወር ይሁን፤ አንድም ይህ ወር በዓመት ከሚውለው ወር ሁሉ የሚበልጥ የሚከበር ይሁን፣ እናንተም ከወራቱ ሁሉ አብል ጣችሁ አክብሩት፣ ዝ ወርኅ ያለው ሚያዝያን ነው፣ ይህን ንም ሚያዝያን በዓመት ከሚ ውለው ወር ሁሉ አስቀድሙት አላቸው፣ ዛሬ እኛ በዓመት ከሚውለው ወር ሁሉ መስከረ ምን እንድናስቀድም እንደ ዚያ ነው፤

፫፣ ወንግር ለኵሉ ማኅበረ ደቂቀ እስራኤል ወበሎሙ በአሡሩ ለዝ ወርኅ ይንሣእ ሎቱ ብእሲ ብእሲ በበቤቱ ወበበዘመዱ ወለለ ማኅደሩ በግዐ፣

ሙሴን ከአሮን ለይቶ ሚያገዝ በገባ በዓሥረኛው ቀን አንዱም አንዱም በየቤቱ በየዘመዱ፤ አንድም በበቤተ ዘመዱ ይላል፣ በየዘመዱ ወገን በየአንድነቱ

www.ethiopianorthodox.org

በጉን ይያዝ ብለህ ለእስራኤል ልጆች ወገኖች ሁሉ ንገር አለው፤

፬፣ ወለእመ ውሑዳን እሙንቱ እለ ውስተ ቤት ወኢይቄድኡ አሐደ በግዐ ይንሣእ ምስሌሁ ካልአ ዘጎሩ በኍልቍ ዘነፍስ ለለ ፩ዱ ፩ዱ ዘየአክሎ ከመ ይወድዕ በግዐ አሐደ፣

በአንድ ቤት ያሉት ሰዎችም ቢያንሱ አንዱን በግ የማይ ጨርሱት ቢሆን አንዱን በግ እንዲጨርስ የሚበቃውን ያህል አንዱንም አንዱን በሰው ቍጥር የጎረቤቱን ሌላውን ሰው ከእሱ ጋር ሊበላ ጠርቶ ያምጣው፤

፭፣ ወበግዕ ፍጹመ ተባዕተ ዘዓመት ይኩንክሙ እመራዕይ ትነሥኡ መሐስዓ፣

በጉም ቀንዱ ያልከረከረ፣ ጥፍሩ ያልዘረዘረ፣ ጠጉሩ ያላረረ ዓመት የሆነው ጠቦት ይሁን፣ ይህንንም ጠቦቱን ከመንጋችሁ አምጡት አላቸው፤

፮፣ ወዕቁበ ይኩንክሙ እስከ ዓሡሩ ወረቡዑ ለዝ ወርኅ ወይኅርድዎ ኵሉ ማኅበሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ፍና ሠርክ፣

ይኸውም በጉ እስከ ሚያዝያ አሥራ አራት ቀን ድረስ ይጠበቅ አለ፣ ከዐሥር እስከ አሥራ አራት ቀን ይጠበቅ ሲል ነው፣ ይኸንንም በጉን የእስራኤል ልጆች ወገኖች ሁሉ በሠርክ ጊዜያት ሲመሽ ይረዱት፤

፯፣ ወይንሥኡ እምደሙ ወይደዩ ውስተ ራግዛት ክልኤቱ ወውስተ መርፈቁ ለውእቱ ቤት ኀበ ይበልዕዎ፣

ከደሙም ወስደው በሁለቱ መቃኖች በጉን በሚበሉበትም ቤት መድረክ ይቀቡት፤

፰፣ ወይብልዑ ሥጋሁ በዛ ሌሊት ጥብሶ በእሳት ወናዕተ ምስለ ሐምለ ብሒዕ፣

ትበልዑ ሲል ነው፣ ይኸን ንም ሥጋውን በእሳት የተጠበ ሰውን ጥብሱን ከአዛኩል ጋራም ቂጣውን በዚህች ሌሊት ይብሉት፤

፱፣ ወኢትብልዑ እምኔሁ ጥሬየ ወኢብሱለ በማይ ዘእንበለ ጥብሰ በእሳት ርእሶ ምስለ እገሪሁ ትዌድዕዎ፣

ከዚያም ከበጉ ሥጋ በእሳት የተጠበሰውን ነው እንጂ ብርን ዶውን፣ ቅቅሉን፣ ዝግኑን አት ብሉ፣ ራሱንም ከእግሩ ጋራ ጨርሳችሁ ጋጡት፤

፲፣ ወኢታትርፉ እምኔሁ ለነግህ ወዓፅሞ ኢትስብሩ እምኔሁ፣ ወለእመቦ ዘተርፈ እምኔሁ ለነግህ አውዕይዎ በእሳት፣

አንድ ቀን ጨርሱት እንጂ ለነገ ብላችሁ አታሳድሩ፣ ከበጉም አጥንቱን አትስበሩ በሌሊታችሁም ከበጉ ሥጋ የተረፈ ቢኖር በእሳት አቃጥሉት፤



፲፩፣ ወከመዝ ብልዕዎ እንዘ ቅኑት ሐቌክሙ ወአሳዕኒክሙ ውስተ እገሪክሙ ወቀስታማቲክሙ ውስተ እደዊክሙ ወትበልዕዎ እንዘ ትጔጕኡ እስመ ፋሲካሁ ለእግዚአብ ሔር ውእቱ፣

ስትበሉትም እንዲህ አድርጋ ችሁ ብሉት፣ ወገባችሁን በዝናር ታጥቃችሁ፣ በእግራ ችሁ ጫማ አገባችሁ /ተጫምታ ችሁ/ በእጃችሁም መንደርቆ ጠርሙዝ በሎታ ይዛችሁ፣ የእግዚአብሔር በዓል ፋሲካ ነውና እየቸኰላችሁ ብሉት አላቸው፤

፲፪፣ ወእመጽእ ውስተ ምድረ ግብጽ በዛ ሌሊት ወእቀትል ኵሎ በኵረ በምድረ ግብጽ እምሰብእ እስከ እንስሳ ወእገብር በቀለ እምኵሉ አማልክተ ግብጽ አነ እግዚአብሔር፣

በዚህች ሌሊት ወደ ግብጽ አገር እመጣለሁ፣ መጥቼም ከሰው ጀምሮ እስከ ከብት ድረስ በግብጽ አገር ያለውን በኵር በኵሩን ሁሉ እገድላለሁ፣ እኔ እግዚአብሔር በካህናተ ጣዖቱ፤ አንድም በግብጽ ባሉ ጣዖታት በቀልን አደርጋለሁ፤ አንድም የግብጽ ካህናተ ጣዖት ከበደሉኝ በደል የተነሣ በግብጽ ሰዎች ሁሉ በቀልን አደር ጋለሁ፤

፲፫፣ ወይከውን ዝ ደም ተአምረ ለክሙ ውስተ አብያት ኀበ ሀሎ ለክሙ ህየ ወእሬእዮ ለውእቱ ደም ወእከድነክሙ ወኢይከውን ዲቤ ክሙ መቅሠፍት ዘቅጥቃጤ ሶበ አምጻእክዎ በምድረ ግብጽ፣

ይህም የበጉ ደም ባላችሁበት ቤት የድኅነታችሁ ምልክት ይሆንላችኋል፣ እኔም በመጣሁ ጊዜ በመቃን በመድረኩ ያለውን ደም አይቼ ከጥፋት እሠውራ ችኋለሁ፣ መቅሠፍቱንም በግ ብጽ አገር ባመጣሁት ጊዜ ጥፋት የታዘዘበት መቅሠፍቱ በእናንተ አይደረግባችሁም፤ አንድም መቅሠፍት ለቅጥቃጤ ይላል፣ መቅሠፍቱ ለጥፋት አይሆንባችሁም፤

፲፬፣ ወትኩንክሙ ዛቲ ዕለት ተዝካረ ወትገብሩ በዓለ ለእግዚአ ብሔር ባቲ በመዋዕሊክሙ ሕገ ዘለዓለም በዓልክሙ ይእቲ፣

ይህችም ቀን መታሰቢያ ትሁና ችሁ /ትሁንላችሁ/፣ እናንተም ባለ ዘመናችሁ የእግዚአብሔ ርን በዓል አድርጉባት፣ አን ድም በዓለ እግዚእ ይላል፣ ለእ ግዚአብሔር በዓል አድርጉ ባት፣ ይህችውም የዘለዓለም ሕጉን የምትጠብቁባት በዓላ ችሁ ናት፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፭፤ ሰቡዐ ዕለተ ናዕተ ትበልዑ ወአመ ቀዳሚት ዕለት ታማስኑ ብሑዐ እምአብያቲክሙ ወኵሉ ዘበልዐ ብሑዐ ለትሠሮ ይእቲ ነፍስ እምእስራኤል እምዕለት ቀዳሚት እስከ ዕለት ሳብዕት፤

ሰባት ቀን ቂጣውን ብሉ፤ በመጀመሪያዪቱ ቀን ከቤታችሁ መፃፃውን አጥፉ፤ ወኵሉ ዘበልዐ ብሑዐ እምዕለት ቀዳሚት እስከ ዕለት ሳብዕት ለትሠሮ ነፍሱ እምእስራኤል ሲል ነው፤ ከመጀመሪያዪቱ ቀን ጀምሮ እስከ ሰባተኛዪቱ ቀን ድረስ መፃፃ የበላ ሰው ሁሉ ሰውነቱ ከእስራኤል ተለይታ በድንጋይ ተወግራ በእሳት ተቃጥላ ትሙት አለ፤

፲፮፤ ወዕለት ቀዳሚት ትሰመይ ቅድስተ ወዕለት ሳብዕት ትኩን ክሙ ዕረፍተ ወኵሎ ግብረ ማኅረስ ኢትግበሩ ባቲ ዘእንበለ ኵሉ ዘይትገበር ለነፍስ ባሕቲቱ ይትገበር ለክሙ፤

መጀመሪያዪቱ ቀን ትከበር፤ ሰባተኛዪቱም ቀን ትከበር አለ፤ እንደ ትንሣኤና እንደ አግብኦተ ግብር ነው፤ ልትበሉባት ልትጠጡባት ከተሠራላችሁ ሥራ ብቻ በቀር አትረሱባት፤ አትቆፍሩባት፤ አንድም ባሕቲቱ ይትገበር ለክሙ ይላል፤ ልትበሉት፤ ልትጠጡት የተሠራላችሁ ሥራ ነው እንጂ ከዚህ በቀር አትረሱባት አትቆፍሩባት፤

፲፯፤ ወዕቀብዋ ለዛቲ ትእዛዝ እስመ በዛቲ ዕለት አወፅአ ለኃይልክሙ እምድረ ግብጽ ወትገብርዋ ለዛቲ ዕለት በዓለ ሕግ ዘለዓለም፤

በዚህች ቀን ከግብጽ አገር ሠራዊታችሁን አወጣዋለሁና ይህችን ትእዛዝ ጠብቋት፤ ምንዋ ሌባን ወንበዴን አለ፤ ጠብቋት ያለ ስለምን ነው? ቢሉ አጽንዕዋ ሲል ነው፤ ይህችን ትእዛዝ አጽኗት፤ አንድም እንዳለም ይሆናል፤ እነሱ ሕጊቱን ቢጠብቋት፤ እሷም እነሱን ትጠብቃቸዋለችና፤ ይህችንም ቀን የዘለዓለም ሕጉ የሚጠበቅበትን በዓል የምታከብሩባት ቀን አድርጓት፤ አንድም በዓለ ወሕገ ዘለዓለም ይላል፤ በዓለ፤ በዓሉን የምታከብሩባት፤ ወሕገ፤ የዘለዓለም ሕጉንም የምትጠብቁባት ቀን አድርጓት፤

፲፰፤ ወትቀድሙ ትእኅዙ እምዐሡሩ ወረቡዑ ለዝ ወርኅ እምሠርኩ ትበልዑ ናዕተ እስከ ዕሥራ ወአሐዱ በዝ ወርኅ እስከ ሠርኩ፤

ከሚያዝያ ወር ከዐሥራ አራተኛው ቀን ከሠርኩ ጀምራችሁ እስከ ሃያ አንደኛው ቀን እስከ ሠርኩ ድረስ ቂጣውን ብሉ፤



፲፱፤ ሰቡዐ ዕለተ ብሑዕ ኢይትረከብ ውስተ አብያቲክሙ ወኵሉ ዘበልዐ ብሑዐ ለይሠሮ ውእቱ ብእሲ እማኅበረ እስራኤል እምግዩር እስከ ዘፍጥረቱ ውስተ ምድርክሙ፤

ሰባቱን ቀን ከቤታችሁ መፃፃ አይገኝበት፤ ወኵሉ ዘበልዐ ብሑዐ ውእቱ ብእሲ ለይሠሮ እማኅበረ እስራኤል ሲል ነው፤ በእሊህ በሰባቱ ቀኖች መፃፃውን የበላ ሰው ሁሉ ከእስራኤል ወገን ከመጻተኛውም በአገራችሁም ከተወለደው ሰው ሁሉ ተለይቶ በድንጋይ ተወግሮ በእሳት ተቃጥሎ ይሙት፤

፳፤ ወኵሎ ብሑዐ ኢትብልዑ በኵሉ ማኅደርክሙ ናዕተ ብልዑ፤

ኢትብልዑ ብሑዐ በበማኅደርክሙ ናዕተ ብልዑ በበማኅደርክሙ ብለው ይገጥሙታል፤ አላ ያለበት ነው፤ በየቤታችሁ ቂጣውን ብሉ እንጂ፤ በየቤታችሁ መፃፃውን አትብሉ አለው፤ እስከዚህ ድረስ ጌታ ለሙሴ የነገረው ቃል ነው፤ ከዚህ ቀጥሎ ሙሴ ለእስራኤል የነገረውን ቃል ያመጣል፤

፳፩፤ ወጸውዖሙ ሙሴ ለኵሉ አዕሩገ እስራኤል ወይቤሎሙ ሑሩ ንሥኡ ለክሙ በግዐ በበዘመድክሙ ወኅርጹ ለፋሲካ፤

ሙሴም የእስራኤልን ሽማግሌዎች ሁሉ ጠርቶ በየወገናችሁ ሂዳችሁ በጉን ያዙ፤ ይዛችሁም ለፋሲካው ረዱት አላቸው፤ ይህንን ሦስት ጊዜ መላልሶ ይጽፈዋል፤ ጌታ ለሙሴ ሲነግረው ሙሴ ለእስራኤል ሲነግራቸው እስራኤል ሲሠሩት፤

፳፪፤ ወንሥኡ ዕሥረተ አዛብ ወጥምዕዎ እምዘኩ ደም ዘኀበ ኆኅት ወሚጥዎ ዲበ ምርፋቅ ወዲበ ክልኤሆሙ ራግዛት እምውእቱ ደም ወአንትሙሰ ኢትፃኡ እምውእቱ ቤት እስከ ይጸብሕ፤

ዕሡረ አዛብ ሲል ነው፤ አውባን፤ ስሚዛ፤ እንዶድ ነው፤ ይህንን በሐር ገመድ አሥራችሁ፤ በዕቃው ካለው ደም ንከሩት፤ በዕቃው ካለው ደም ወስዳችሁም በሁለቱ መቃኖችና በመድረኩ ቅቡት፤ እናንተ ግን ከዚያ ካላችሁበት ቤት እስኪነጋ ድረስ አትውጡ፤

፳፫፤ ወይመጽእ እግዚአብሔር ከመ ይቅትሎሙ ለግብጽ ወይሬኢ ለውእቱ ደም ዲበ መርፈቅ ወዲበ ክልኤሆሙ ራግዛት ወይትአደዋ እግዚአብሔር ለይእቲ ኆኅት ወኢየኃድጎ ለቀታሊ ይባእ ውስተ አብያቲክሙ ከመ ይቅትል፤

የንጊዜ እግዚአብሔር ግብጻውያንን ሊያጠፋቸው ይመጣል፤ መጥቶም በሁለቱ መቃኖችና በመድረኩ ላይ ያለውን ደሙን ያየዋል፤ እግዚአብሔርም ደጃፊቱን አይገባባትም፤ አልፏት ይሔዳል አለ፤ ቸነፈሩ ወደ

www.ethiopianorthodox.org

እርስዋ እንዳይገባባት ያደር ጋል፣ ይትአደዋ ያለውን አመጣ፣ ቸነፈሩም እናንተን ሊገድል ወደ ቤታችሁ እንዲ ገባ አያሰናብተውም፤

፳፬፣ ወዕቀቡ ዘንተ ሕገ ይኩንክሙ ወለውሉድክሙ ዘለዓለም /እስከ ለዓለም/

ዛ ሕገ ዘንተ ሕገ ይላል አብነት፣ ለእናንተም ለልጆቻ ችሁም ለዘላለሙ ይረባችሁ ይጠቅማችሁ ዘንድ ይህነን ሥርዓት ጠብቁ፤ አንድም ዕቀቡ ዘንተ ብሎ ሕገ ይኩን ክሙ ይላል፣ ለእናንተም ለልጆቻችሁም ለዘለዓለሙ ሥርዓት ይሆናችሁ ዘንድ ይህነን የምንግራችሁን ሁሉ ጠብቁ፤

፳፭፣ ወእመ ቦእክሙ ውስተ ምድር ዘይሁበክሙ እግዚአብሔር ለክሙ ዘከመ ነበበ ዕቀብዋ ለዛቲ ሥርዓት፣

እግዚአብሔር ለእናንተ አወርሳች ኋለሁ ብሎ እንደ ተናገረ፤ አንድም ዘነበበ ይላል፣ ለእናንተ አወርሳችኋለሁ ብሎ የተናገረ እግዚአብሔር ወደሚያወርሳ ችሁ ወደ ከነዓንም ብትገቡ ይህችን ሥርዓት ጠብቋት፣

፳፮፣ ወእመ ይቤሉክሙ ውሉድ ክሙ ምንትኑ ዛቲ ሥርዓት፣

ይህች ሥርዓት ምንድር ናት? ብለው ኋላ ልጆቻችሁ ቢጠ ይቋችሁ፤

፳፯፣ ትብልዎሙ መሥዋዕተ ፋሲ ካሁ ዝንቱ ለእግዚአብሔር ዘከደነ አብያቲሆሙ ለደቂቀ እስራኤል በምድረ ግብጽ አመ ቀተሎሙ ለግብጽ ወአድኃነ አብያቲነ ወደነኑ ሕዝብ ወሰገዱ፣

የግብጻውያንን በኵር በኵሩን ባጠፋ ጊዜ በግብጽ አገር የእስ ራኤልን ልጆች ቤት ከጥፋት የሠወረ፣ እኛንም ቤታችን ንም፤ አንድም ወገናችንን ያዳነ የእግዚአብሔር የበዓለ ፋሲ ካው መሥዋዕት ነው በሏቸው አሏቸው፣ ሕዝቡም ይህነን ሰም ተው ሰገዱ፣ አድኅኖ የአንገት የደረት፣ ስግደት የወገብ፣ አስተብርኮ የጕልበት ነው፣ እስካሁን ሙሴ ከጌታ ታዝዞ የነገራቸውን ቃል ሲናገር መጥቶ ነበር እንግዲህ ወዲያ ግን እስራኤል ከሙሴ ቃል ሰምተው የሚሠሩትን ሥራ ይናገራል፤

፳፰፣ ወሖሩ ወገብሩ ከማሁ ደቂቀ እስራኤል በከመ አዘዞሙ እግዚ አብሔር ለሙሴ ወለአሮን፣

ከማሁና በከመ አዘዞሙ አንድ ወገን፣ የእስራኤልም ልጆች



ሒደው እግዚአብሔር ሙሴና አሮንን እንዳዘዛቸው አደረጉ፤ አንድም እየራሱን ለማውጣት ይህ ከመ በባለቤት የገባ ከመ ነው፣ የእስራኤልም ልጆች ሒደው እግዚአብሔር ለሙሴ ለአሮን ያዘዛቸውን ቃል አደረጉ፣ እስካሁን ጌታ ለሙሴ የነገረውን፣ ሙሴም ከእግዚአ ብሔር አግኝቶ ለእስራኤል የነገራቸውን ከዚህ ሲደርስ እንደ ወርቅ እንክብል፣ እንደ ሸማ ጥቅል አድርጎ፣ ገብሩ በከመ አዘዞሙ ብሎ ተናገረው፤ አንድም ይህነን ሁሉ ወደፊት ገና ያመጣዋል፤

፳፱፣ ወሶበ ኮነ መንፈቀ ሌሊት ቀተለ ኵሎ በኵረ እግዚአብሔር በምድረ ግብዕ እምበኵረ ፈርዖን ዘይነብር ዲበ መንበረ መንግሥት እስከ በኵረ ፂውውት ቀዳሒት ወኵሎ በኵረ እንስሳ፣

ፂውውት ቀዳሒት ለማለት ደግሞታል፤ ሐተታ እንዳለፈው፣ የሌሊት እኩሌታም በሆነ ጊዜ በዙፋን ከሚቀመጥ ከፈርዖን የበኸር ልጅ ጀምሮ ውሀ እስከ እምትቀዳ አገልጋይ ልጅ ድረስ በግብጽ አገር የበኸር ልጁን ሁሉ፣ ከከብትም መጀመ ሪያ የተወለደውን ሁሉ ገደለ፤

፴፣ ወተንሥአ ፈርዖን በሌሊት ወኵሉ ዓበይቱ ወኵሉ ግብጽ ወኮነ አውያት ዐቢይ በኵሉ ምድረ ግብጽ እስመ አልቦ ቤት ዘአልቦ ውስቴቱ ምውት፣

የሞተ ሰው የሌለበት ቤት የለም ነበርና ፈርዖን ሹማምቱ የግብጽ ሰዎች ሁሉ ተነሥተው በመንፈቀ ሌሊት ብዙ ጩኸት ሆነ ወጸውዖሙ ይላል፤ አንድም ጸውዖሙ ማግኘሻ ነው፣ ሶበ ኮነ ይላል፣ የሞተ ሰው የሌለበት ቤት የለም ነበርና ፈርዖን ሹማምቱ የግብጽም ሰዎች ሁሉ በሌሊት ተነሥተው ብዙ ጩኸት በተደረገ ጊዜ ፈርዖን ይኸን አይቶ፤

፴፩፣ ወጸውዖሙ ፈርዖን ለሙሴ ወለአሮን በሌሊት ወይቤሎሙ ተንሥኡ ወፃኡ እምሕዝብየ አንትሙሂ ወደቂቀ እስራኤልሂ ወሑሩ ወተጸመድዎ ለእግዚአብሔር አምላ ክክሙ በከመ ትቤሉ፣

ሙሴና አሮንን በሌሊት አስ ጠርቶ እናንተም የእስራኤልም ልጆች ተነሥታችሁ ከወገኖቼ ተለይታችሁ ወጥታችሁ ሒዱ፣ ሒዳችሁም ንሑር ወንጽመዶ ለእግዚአብሔር አምላክነ እንዳ ላችሁ ለፈጣሪያችሁ ለእግዚአ ብሔር መሥዋዕት ሠውታችሁ አገልግሉት አላቸው፤

www.ethiopianorthodox.org

፴፪፣ ወአባግዒክሙሂ ወአልህምቲክሙሂ ንሥኡ ወሑሩ ወባርኩኒ ኪያየ፣

አባግዒክሙሂ፣ አባግዒነሂ ንነሥእ ብላችሁ እንደ ተናገራችሁ ላሞቻችሁንና በጎቻችሁን ይዛችሁ ሒዱ፣ ምንንም ቢኾን ይኾን ያደረግሁላችሁ እኔን ባለወረታችሁ ነኝና አክብሩኝ መርቁኝ አላቸው፤

፴፫፣ ወአዕሐብዎሙ ግብጽ ለሕዝበ እስራኤል ከመ ፍጡነ ያውፅእዎሙ እምድረ ግብጽ እስመ ይቤሉ ኵልነ ንመውት፣

ግብጻውያን እስራኤልን ዘበዘቧቸው፣ አጉጉዕዎሙም ይላል /ዘር/፣ ሁላችን እንሞታለን ብለዋልና የግብጽ ሰዎች የእስራኤልን ወገኖች ከግብጽ አገር ፈጥነው ያስወጧቸው ዘንድ አስቸኰሏቸው አለ፣ ውጡልን ውጡልን አሏቸው፤

፴፬፣ ወነሥኡ ሕዝብ ሐሪዖሙ ዘእንበለ ይትበሐእ ዕፉረ በአልባሲሆሙ ዲበ መትከፍቶሙ፣

እስራኤልም ሳይቦካ /ሳይለወስ/ ዱቄቱን በልብሳቸው ቋጥረው በትከሻቸው ተሸከሙ፣

፴፭፣ ወገብሩ ደቂቀ እስራኤል በከመ አዘዞሙ ሙሴ ወተወሐሱ እምግብጽ ንዋየ ብሩር ወወርቅ ወልብስ፣

የእስራኤልም ልጆች ሙሴ ለትትወሐስ ጎር እምኅራ ብሎ እንዳዘዛቸው፣ ከግብጽ ሰዎች የብሩንና የወርቁን የልብሱን እቃ /ገንዘብ/፤ አንድም የወርቁንና የብሩን ዕቃ ወልብሰ ይላል፣ ልብሱንም ተዋሱ፤

፴፮፣ ወወሀቦሙ እግዚአብሔር ሞገሰ ለሕዝበ እስራኤል በቅድሚሆሙ ለግብጽ ወአውሐስዎሙ ወሐብለ ይዎሙ ለግብጽ፣

እግዚአብሔርም በግብጻውያን ፊት ለእስራኤል ባለሟልነትን ሰጣቸው አለ፣ መሣሪያ እንዲያውሷቸው አደረገ፣ ግብጻውያንም ለእስራኤል እቃቸውን አዋሷቸው፣ እስራኤልም በዚህ ምክንያት ግብጻውያንን በዝብዘዋቸው ወጡ፣ ሐተታ እንዳለፈው፤

## ጉባኤ

፴፯፣ ወግዕዙ ደቂቀ እስራኤል እምራምሴ ውስተ ሰኩት ፷፻፻ አጋር ዕደው ዘእንበለ ዘምስለ ንዋይ፣

የእስራኤልም ልጆች ከራምሴ ተነሥተው ወደ ሰኮት ተጓዙ እለዚህም ከጓዝ ጋራ ካሉት፣ በቀር ስሳ እልፍ አርበኞች /አጋር/ ናቸው፤ አንድም ከልጅ ከሴት ከጓዝ ካሉት በቀር ለጦር ለጋሻ የበቁት ስሳ እልፍ /አጋር/ አርበኞች ናቸው፤



፴፰፣ ወዘተደመረ ዘዐርገ ምስሌሆሙ ብዙኅ ወአባግዕ ወአልህምት ወእንስሳ ብዙኅ ጥቀ፣

ዘተደመረና ዘዐርገ አንድ ወገን ነው፣ ጎዳና አጋጥሞት አብሮ የወጣው ብዙ ነው፤ አንድም አምኖ ተጋብቶ፣ አብሮ የወጣው ብዙ ነው፤ አንድም ዘተደመረ ወዘዐርገ ይላል፣ ዘተደመረ አምኖ ተጋብቶ፣ ወዘዐርገ ለጌታ አዳር ከእነሱ ጋር የወጣው ብዙ ነው፣ ላሙና በጉ ከብቱም ሁሉ ብዙ ነበር፤

፴፱፣ ወሐበዙ ሐሪዖሙ ዘአውፅኡ እምግብጽ ወገብርዎ ዳፍንተ ናዕተ እስመ ዘእንበለ ያብሕው አውፅእዎሙ ግብጽ ወኢክህሉ ነቢረ ወኢገብሩ ሎሙ ስንቀ ለፍኖት፣

እስራኤል ዱቄቱን ሳያቦኩ ሳይጋግሩ የግብጽ ሰዎች ከሀገራቸው ከቤታቸው አስወጥተዋቸዋልና፣ እስራኤልም በግብጽ መኖር አልተቻላቸውምና፣ ከዚያም አስቀድሞ ለጎዳናቸው ስንቅ አላዘጋጁም ነበርና፣ ከግብጽ ያወጡትን ዱቄት ድፎ አምባሻ ዳቦ አድርገው /እያደረጉ/ ጋገሩት፤

፵፣ ወኅድረቶሙ ለደቂቀ እስራኤል ዘነበሩ በምድረ ግብጽ ወበምድረ ከነዓን እሙንቱ ወአበዊሆሙሂ ፬፻፴ ዓመት፣

እነሱም አባቶቻቸውም በከነዓንና በግብጽ አገር የኖሩት የእስራኤል አኗኗራቸው አራት መቶ ሠላሳ ዘመን ነው፣ ይኸውም ሁለት መቶ አሥራ አምስት በከነዓን፣ ሁለት መቶ አሥራ አምስት በግብጽ ነው፤

፵፩፣ ወኮነ እምድኅረ ፬፻፴ ዓመት ወፅአ ኵሉ ኃይለ እግዚአብሔር እምድረ ግብጽ ሌሊተ፣

ከአራት መቶ ሠላሳ ዘመን በኋላ እንዲህ ሆነ አለ፣ ኮነ ያለውን ወፅአ ብሎ አመጣው፤ የእግዚአብሔር ሠራዊት የሚሆን እስራኤል ሁሉ ከግብጽ አገር በሌሊት ወጣ፤

፵፪፣ እምቅድመ ዕቅበቱ ውእቱ ለእግዚአብሔር ከመ ያውፅእዎሙ እምድረ ግብጽ ዛቲ ሌሊት ይእቲ እምቅድመ ዕቅበቱ ለእግዚአብሔር ከመ የሀልዉ ኵሉ ደቂቀ እስራኤል በትውልዶሙ፣

ሌሊተ እምቅድመ ዕቅበቱም ይላል፣ ከሦስተኛው /ክፍል/ አካች አስቀድሞ በሁለተኛው አካች /አካፋይ/ እስራኤልን ከግብጽ አገር ያወጣቸው ዘንድ፤ አንድም ኋላ ከሚጠብቃቸው መጠበቅ አስቀድሞ፤ አንድም እምቅድመ ዕቅበቱ ይላል፣ ይኸውም መጠበቁ ዛሬ ብቻ አይደለም፣ ከጥንት ጀምሮ ነው፣ እስራኤል በየወገናቸው ጸንተው ይኖሩ ዘንድ የወጡባት ይህችም ሌሊት ከሦስተኛው አካች አስቀድሞ የምት

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ሆን ሁለተኛዪቱ /ክፍል/ አካች ናት፤ አንድም እምቅድመ ዕቅበቱ ከጥንት ጀምሮ ታውቃ ነበር፣ ወዐቀቦ ዳዊት ለዝንቱ ነገር በልቡ እንዲል፤ አንድም ከጥንት ጀምሮ ተጠብቃ ነበር፤

፵፫፣ ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን ዝውእቱ ሕጉ ለፋሲካ ኵሉ ዘእምባዕድ ዘመድ ኢይብላዕ እምኔሁ፣

እግዚአብሔርም ሙሴና አሮንን የበዓለ ፋሲካው ሥርዓት ይህ ነው፣ ዝውእቱ፣ ያለውን አመጣ ከራቀ ነገድ፤ አንድም ከአሕዛብ የተወለደ ከበጉ ሥጋ አይብላ አላቸው፤

፵፬፣ ወኵሉ ገብር ዘኮነ ወዘበሤጥ ትገዝርዎ ወይእተ ጊዜ ይብላዕ እምኔሁ፣

ውላጅ፣ ወዘበሤጥ በወርቅ ተገዝቶ የመጣ፣ ባሪያውንም ግዘሩት፣ ያንጊዜ ግን ይብላ፤

፵፭፣ ኃዳሪ ወገባኢ ኢይብላዕ እምኔሁ፣

ኃዳሪ ሎሌ፣ ወገባኢ የዕለት ምንደኛም ሳይገዝር ከበጉ ሥጋ አይብላ፣

፵፮፣ ወበአሐዱ ቤት ይትበላዕ ወኢታውዕኡ አፍአ እምቤት እም ውእቱ ሥጋ ወአጽሞሂ ኢትስብሩ፣

ይኸውም የበጉ ሥጋ በአንድ ቤት ይበላ፣ ይኸንንም የበጉን ሥጋ ከአላችሁበት ቤት አውጥ ታችሁ ወደ ሌላ ቤት አትው ሰዱት፣ አጥንቱንም አትስበሩ፤

፵፯፣ ወኵሉ ማኅበረ እስራኤል ለይግበሮ፣

ይህንንም በዓል የእስራኤል ወገን ሁሉ ተሰብስቦ ያድርገው፤

፵፰፣ ወእመቦ ዘመጽአ ኀቤክሙ ግዩር ይግበር ፋሲካሁ ለእግዚ አብሔር ትገዝሩ ኵሎ ተባዕቶ ወይእተ ጊዜ ይበውእ ይግበር ወይከውንክሙ ከመ ትውልደ ብሔር ወኵሉ ቈላፍ ኢይብላዕ እምኔሁ፤

የእግዚአብሔርን በዓል ሊያደ ርግ መጻተኛ ወደ እናንተ የመጣ ቢሆን፣ ወንድ ወንዱን ግዘሩት ያን ጊዜ በዓሉን ሊያደርግ ወደ እናንተ ይግባ፣ በአገራችሁ እንደ ተወለደ እንደ እስራኤልም ይሁን፣ ያልተገዘረው ግን ከበጉ ሥጋ አይብላ፤

፵፱፣ አሐዱ ሕግ ይኩን ለትውል ድክሙ ወለግዩር ዘይመጽእ ኀቤክሙ፣

በዓል ሊያደርግ ወደ እናንተ ለመጣው ለመጻተኛውና ለእናንተ አንድ ሕግ ይሁን፤ አንድም ወለዘይመጽእ ኀቤክሙ ይላል፣ ይኸውም አንዱ ሕግ ለእናንት፣ ወለግዩር ለመጻተ



ኛው፣ ወለዘይመጽእ ኀቤክሙ ወደ እናንተ መጥቶ ለአመነ ውም ለተጋባውም ሁሉ ይሁን፤

፶፣ ወገብሩ ከማሁ ደቂቀ እስራ ኤል በከመ አዘዞሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን፣

እግዚአብሔር ሙሴና አሮንን አዝዟቸው እንዳደረጉ፣ ከማሁ የእስራኤል ልጆችም ሙሴ እንዳዘዛቸው አደረጉ፤

፶፩፣ ወኮነ በይእቲ ዕለት አውፅኦሙ እግዚአብሔር ለደቂቀ እስራኤል እምድረ ግብጽ ምስለ ኃይሎሙ፣

ኮነ ያለውን አውፅኦሙ ብሎ አመጣው፣ እግዚአብሔርም በዚህች ቀን ከግብጽ አገር የእ ስራኤልን ልጆች ከሠራዊቶቻ ቸው ጋራ አወጣቸው፣ ታሪክ፣ ጌታ ሙሴን በግብጻውያን ሞተ በኵር አምጥቼ በኵር በኵሩን አጥፍቼ ከግብጽ አገር አወጣችኋለሁ አለው፣ እንዲህማ ከሆነ የእስራኤልስ በኵር በኵሩ መች ይድን ልኛል ሊሞትብኝ አይደለምን አለው፣ ጌታም እንዲህ እንዳ ይሆን የሚያዝያ ጨረቃ ሡርቅ ባደረገች (በወጣች) በዐሥር ቀን ቀንዱ ያልከረከረ፣ ጥፍሩ ያልዘረዘረ፣ ጠጉሩ ያላረረ፣

ዓመት የሆነው ጠቦት፤ ያለው ከመንጋው፣ የሌለው ገዝታችሁ፣ እስከ ዐሥራ አራት ቀን ድረስ አሥራችሁት ሰንብቱ፣ በዓሥራ አራተኛው ቀን አንዱን ሰዓት ከሦስት ከፍላችሁ፣ አንዱን እጅ ትታችሁ በሁለት እጅ ብርሃን፣ ከሌሊቱም አንዱን ሰዓት ከሦስት ከፍላችሁ ሁለቱን እጅ ትታችሁ በአንዱ እጅ ጨለማ ሠዉት፣ ስትሠ ዉትም ሰባት፣ አሥር፣ አሥራ ሁለት ሁናችሁ ሠዉት፣ ያለው ቤተሰቡን ይዞ፣ የሌለው ጐረቤ ቱን ጠርቶ አምጥቶ አንድ በግ እንድትጨርሱ ሁናችሁ ሠዉት፣ ደሙን መቃን መድረኩን ቀቡት /እርጩት/ ያንን እያየ ሞተ በኵር ይከለክልላችኋል፣ ዝግኑን፣ ቅቅሉን፣ ብርንዶ ውን አትብሉ፣ ጥብሱን ብሉ፣ ወኢታትርፉ ለነግህ፣ አትር ፉችሁ ለበነጋው አታሳድሩ፣ ወኢታትርፉ እስከ ደግደግ እንዲል፣ መሥዋዕቱንም ሠው ታችሁ ከአንዱ ወደ አንዱ አትውሰዱት፣ የበላችሁትን በልታችሁ፣ የተረፈውን በእሳት አቃጥሉት፣ ምስለ ሐምለ ብሒዕ ትበልዕ ይላል፣ በአገ ራቸው አራት ነገር ያመጣሉ፣ የወይን ቅጥራን፣ የበለስ ቅጥ ራን፣ የስንዴ ቅጥራን፣ አዞ

www.ethiopianorthodox.org

ከል ነው፣ በዚያ ወራት የሚበ
ሉት ቂጣ ነውና፣ እንደ አረቄ
እንዲበትንላቸው ነው፣ ስትበ
ሉትም ጫማችሁን አዝባችሁ፣
ዝናራችሁን ታጥቃችሁ፣ ኩፌ
ታችሁን ደፍታችሁ፣ በሎታ
ችሁን ይዛችሁ፣ እየቸኰላችሁ
ብሉት፣ አጥንቱን ግን አትስ
በሩት ብሏቸዋል፣ ይህ ሁሉ
ምሳሌ ነው፣ በጉ የጌታ ምሳሌ
ነው፣ ዓመት የሆነው ጠቦት
ወርድ እንጂ ቁመት አያክልም
/አይጨምርም/ጌታም የተሰቀለ
ፍጹም የሠላሳ ዓመት ጉልማሳ
ሁኖ ነውና፣ ዓመት የሆነው
ጠቦት ቀንዱ ያልከረከረ፣ ጥፍሩ
ያልዘረዘረ፣ ላቱ /ጠጕሩ/
ያላረረ ማለቱ ለጌታም ምክን
ያተ ኃጢአት የለበትም፣ ንጹሐ
ባሕርይ ነውና፣ የሚያዝያ ጨረቃ
ሠርቅ ባደረገች በዓሥር ቀን
ይዛችሁ እስከ ዓሥራ አራት
አስራችሁ በዓሥራ ዓራተኛው
ቀን ሠዉት ማለቱ፣ የጌታም
ምክረ ሞቱ በዓሥር ተጀምሮ
በዓሥራ አራተኛው ቀን ተፈጽ
ሟል፣ በሁለት እጅ ብርሃን
በአንድ እጅ ጨለማ ሠዉት
ማለቱ፣ ከነግህ እስከ ቀትር
ብርሃን ሁኗል፣ ከቀትር እስከ
ዘጠኝ ሰዓት ጨለማ ሁኗል፣
ወጸልመ ኵሉ ዓለም እንዲል፣
በሠርክ ብርሃን ሁኗል፣ ወፍና
ሠርክ ይበርህ ብርሃን ፀሐይ
እንዲል፣ ስትሠዉትም ሰባት
ዐሥር፣ ዓሥራ ሁለት ሁናችሁ
ሠዉት ማለቱ ሰባት በእርሳ
ቸው ፍጹም ነው፣ ዐሥርም
በእኛ ፍጹም ነው፣ ፍጹማን
ሁናችሁ ተቀበሉ ሲል ነው፣
ዓሥራ ሁለት ሁናችሁ ማለቱ
ለጊዜው የሚበሉት ዓሥራ
ሁለቱ ነገደ እስራኤል ናቸው፣
ፍጻሜው ግን ሥጋውን ደሙን
የሚቀበሉ ዓሥራ ሁለቱ ሐዋር
ያት ናቸውና፤ አንድም ወለ
እመ፤ ውሑዳን ሥጋውን
ደሙን ብቻውን ለመቀበል
የማይቻለው ሰው ቢኖር፣
ወንዱ ሚስት ፈልጎ፣ ሴቲቱም
ባል ፈልጋ ሁለቱ አንድ
ሁነው ከነፍስ አባታቸው ጋር
መክረው ሥጋውን ደሙን
ይቀበሉ ሲል ነው፣ ደሙን
መቃን መድረኩን ቅቡት
ማለቱ ለጊዜው ያነን እያየ
ቸነፈሩ ይከለክልላቸው ነበር፣
ወሶበ ርእየ መልአከ ሞት ደመ
በግዕ ለበወ ሞተ እግዚእ ፈርሃ
ወኢቀርበ ኀበ መድረከ ኆኅት
እንዲል፣ ምሳሌው እንዲህ
የሆነ አማናዊውማ እንደ ምን
ይሆን ብሎ፣ እንደዚህም ሁሉ
ዛሬም ሥጋው ደሙን ከሚቀ
በሉ ምእመናን አጋንንት አይ



ቀርቧቸውም፣ ይከለክሉላ
ቸዋልና የዚያ ምሳሌ ነው፣
ዝግኑን ቅቅሉን አትብሉ ማለቱ
ሙስና መቃብር አገኘው አት
በሉ ሲል ነው፣ ብርንዶውን
አትብሉ ማለቱ ከብርንዶ
ደም አይታጣም፣ ደምም ካለ
ነፍስ አትለይም፣ እስመ ነፍስ
ተኃድር በደም እንዲል፣ ነፍስ
ያልተለየውን ሥጋ እንቀበላለን
አትበሉ ሲል ነው፤ አንድም
ብርንዶውን አትብሉት አለ፣
ዕሩቅ ብእሲ ነው፣ አትበሉት
የዕሩቅ ብእሲ ሥጋ ቢበሉት
ይመራል፣ ይተኩሳል ፍዳ
ይሆናል እንጂ ከኃጢአት
አያነፃም፣ የጌታ ግን ሥጋው
ከኃጢአት፣ ከፍዳ የሚያነፃ
ነውና፣ ጥብሱን ብሉት ማለቱ
መለኮት የተዋሐደውን ነፍስ
የተለየችውን ሥጋውን እንቀ
በላለን በሉ ሲል ነው፣ አታሳ
ድሩ አለ፣ ካሣ ሳይፈጸም
አላደረምና፣ ከአንዱ ወደ እንዱ
አትውሰዱት አለ፣ ለጊዜው
መካነ መስቀሉ ለመካነ መቃብሩ
ቅርብ ነው፤ ፍጻሜው ግን
ዛሬም መሥዋዕት ከአንዱ
ሠርቶ ወደአንዱ ወስዶ መሠ
ዋት አይገባምና፣ የበላችሁትን
በልታችሁ የተረፈውን /የተረ
ፋችሁን/ በእሳት አቃጥሉት
ማለቱ፣ የተቻላችሁን ያህል
ምሥጢሩን መርምራችሁ የቀ
ረውን መንፈስ ቅዱስ ያው
ቃል በሉ፣ አትጋፉ ሲል ነው፣
እሳትም የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ
ነው፣ ብልዑ ናዕተ ምስለ
ሐምለ ብሒዕ አለ፣ ለጊዜው
በዚያ ወራት የሚበሉት ቂጣ
ነበርና እንደ አረቄ ሁኖ
እንዲበትንላቸው ነው፣ ዛሬም
ሥጋውን ደሙን መቀበል
የሚገባ የበሉት የጠጡት
ከሆድ ሲጠፋ፣ ለአፍ ምሬት
ሲሰማው ነውና፣ ጫማችሁን
አዝባችሁ ማለቱ /አለ/ ምግባረ
ወንጌልን ሠርታችሁ ሲል
ነው፣ ተሰዒነክሙ ዘበሰላም
ምግባረ ወንጌል እንዲል ዝና
ራችሁን ታጥቃችሁ አለ፣
ንጽሕናን ይዛችሁ፣ ኩፌታች
ሁን ደፍታችሁ አለ፣ አክሊለ
ሶኩን እያሰባችሁ በሎታችሁን
ይዛ ችሁ አለ፣ ነገረ መስቀሉን
እያሰባችሁ ሲል ነው፣ እየቸ
ኰላችሁ ብሉት ማለቱ ለጊዜው
መንገደኞች ናቸው፣ ፍጻሜው
ግን ዕለተ ሞት መቃብር
ገሃነም አለብን እያላችሁ ኑሩ
ሲል ነው፣ የአረጋዊ መንፈ
ሳዊ ድርሳን አብድ ውእቱ
ዘይሔሊ ዘእንበለ መቃብሩ
ዘውእቱ ርስቱ እንዲል፣

www.ethiopianorthodox.org

አጥንቱን አትስበሩት ማለቱ ለጊዜው በዓል ነውና ስለዚህ ነው፣ ፍጻሜው ግን ለጊዜው ግብጻውያን ሲጐዱ እስራኤል አለመጐዳታቸውን መናገር ነው፤ አንድም ፍጻሜው ግን ኃጥአን ሲጐዱ ጻድቃን ላለመ ጐዳታቸው ምሳሌ ነው፣ አንድም በቀሙም እንዳለ ይሆናል፣ በዕለተ ዓርብ የሁለ ቱን ወንበዴች ጭን፣ ጭናቸ ውን እየሰበሩ ሲያወርዷቸው የጌታን ጭኑን አልሰበሩት ምና ኢሰበሩ ቍይያ እንዲል፤ አንድም እንደ አርዮስ ወልድ ፍጡር በመለኮቱ አትበሉ ሲል ነው፣ አርዮስ ሽክላ ሠሪ መደቧን፣ አንጥረኛ መዶሻ ውን ሠርቶ እንዲሠራበት ፈጥሮ ፈጠረበት ብሏልና፣ ወአመ ቀዳሚት ዕለት ታማ ስኑ ብሑዐ እምአብያቲክሙ አለ፣ እስመ ይቤ ተኃድጉ ዘቀደመ ግብረ ወትእኀዙ ሐዲስ ሕገ ይላል፣ የቀደመ ሥርዓተ ኦሪትን ትታችሁ የኋለኛ የሕገ ወንጌልን ሥርዓት ትይዛላችሁ ሲል ነው፣ ከዚህም ሕገ ወንጌልን ሲሠራ ሕገ ኦሪትን ከሠራት በኋላ አሳል ፏታል፤ ንጉሥ ዛሬ ቀድሞ ሹሞት የነበረውንና ኋላ የሚ ሾመውን አንድ ጊዜ አቅርቦ ያነን ወቅሶ ሽሮ፣ ይኸነን እንዲሾም፣ ጌታም ሕገ ኦሪትን የሚያሳልፍ ሕገ ወንጌልን የሚሠራ ነውና ስለዚህ ነው።

## ምዕራፍ ፲ወ፫ቱ

### ገባኤ

፩-፬፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ቀድስ ሊተ ኵሎ በኵረ ቀዳሚ ውሉድ፣ ኵሉ ዘይፈትሕ ማኅፀነ እምደቂቀ እስራኤል እምሰብእ እስከ እንስሳ ሊተ ውእቱ፣

ከእስራኤል ልጆች ወገኖች መጀመሪያ የተወለደው ከሰው ጀምሮ እስከ ከብቱ ድረስ ለእኔ ነውና፣ እግዚአብሔር ሙሴን መጀመሪያ የተወለ ደውን በኵር በኵሩን ሁሉ ለይልኝ አለው፤ አንድም እግዚአብሔር ሙሴን ከከብት ወገን መጀመሪያ የተወለደ ውን በኵር በኵሩን ሁሉ ለይልኝ፣ ወዘይፈትሕ፣ ከእስራ ኤልም ልጆች ወገኖች መጀ መሪያ የተወለደው ከሰው ጀምሮ እስከ ከብቱ ድረስ ወንድ ወንዱ ለእኔ ነው አለው፤

፫፣ ወይቤሎሙ ሙሴ ለሕዝብ ተዘከርዋ ለዛቲ ዕለት እንተ ባቲ ወፃእክሙ እምብሔረ ግብጽ እምቤተ ቅንየት እስመ በዕድ ጽንዕት አውፅአክሙ እግዚአብሔር እምዝየ ወኢትብልዑ ብሑዐ፣



ሙሴም ወገኖቹ እስራኤልን እግዚአብሔር በጽኑዕ ሥልጣኑ ከግብጽ አውጥቷችኋልና በግብጽ አገር ከጽኑዕ አገዛዝ የወጣችሁባት፤ አንድም ከግብጽ አገር ወእምቤተ ቅንየት፣ ከጽኑ አገዛዝም የወጣችሁባት ይህችን ቀን አስቧት፣ እናንተም በዚህ ቀን መፃፃውን አትብሉ አላቸው፤ አንድም ኢትብልዑ ተዘኪረክሙ ይላል እግዚአ ብሔር፣ ከግብጽ በጽኑ ሥልጣኑ አውጥቷችኋልና ከግብጽ አገር ከጽኑ አገዛዝም የወጣችሁባት ይህችን ቀን አስባችሁ በዚያች በወጣች ሁባት ቀን መፃፃ አትብሉ አላቸው፣

፬፣ እስመ በዛቲ ዕለት ትወፅኡ አንትሙ በወርኃ ሃሌ ሉያ ኔሳን፣

በወርኃ ኔሳን ዘውእቱ ሃሌ ሉያ ሲል ነው፣ ወርኃ ተሐድሶ፣ ወርኃ ስብሐት ማለት ነው፣ እናንተ በታደሳችሁባት፣ ጌታ ተአምራቱን በገለጠባት በሚ ያዝያ ወር ስለ ወጣችሁ ነው፤

፭፣ ወአመ ወሰደክሙ እግዚአብ ሔር ውስተ ምድረ ከናኔዎን ወኬጤዎን ወአሞሬዎን ወኤዌዎን ወኢያቡሴዎን ወጌርጌሴዎን ወፌርዜዎን ዘመሐለ ከመ የሀቦሙ ለአበዊክሙ ምድረ እንተ ትውኅዝ ሐሊበ ወመዓረ ተዘከርዋ ለዛቲ ሥርዓት በዝ ወርኀ፣

እግዚአብሔር በቸርነቱ ተድላ ደስታ የማይታጣባትን አገር ለአባቶቻችሁ ሊያወርሳቸው ወደ ማለባት ወደ ፌርዜዎንና ወደ ጌርጌሴዎን፣ ወደ ኢያቡ ሴዎንና ወደ ኤዌዎን፣ ወደ አሞሬዎንና ወደ ኬጤዎን ወደ ከነዓንም አገር በወሰዳችሁ ጊዜ በዚህ በሚያዝያ ወር የሠራላች ሁን ሥርዓት አስቧት አላቸው፤

፮፣ ሰዱስ ዕለተ ትበልዑ ናዕተ ወሳብዕት ዕለት በዓሉ ለእግዚአ ብሔር እግዚእ፣

በዚህም በሚያዝያ ወር ስድስት ቀን ቂጣ ብሉ፣ ይልቁንም ሰባተ ኛዪቱ ቀን የእግዚአብሔር ታላቅ በዓሉ ናት አላቸው፣ በዓል ሰባቱም ቀን ሁሉ በዓል ናቸው፣ እሱ ግን የመጀመሪያ ዪቱንና የመጨረሻዪቱን ቀን አክብሮ ይናገራል፣ እንደ ትን ሣኤና እንደ አግብኦተ ግብር ነው፤

፯፣ ብልዑ ናዕተ ሰቡዐ ዕለተ ወኢ ያስተርኢብክሙ ብሑዕ ወኢየሀሉ ብሑዓት ውስተ ኵሉ አድባሪክሙ፣

ሰባት ቀን ቂጣ ብሉ በቤታች ሁም መፃፃ አይታይ፣ በአገራ ችሁም ሁሉ መፃፃ አይታይ አላቸው፤

www.ethiopianorthodox.org

፰፤ ወትዜንዎ ለወልድከ በይእቲ ዕለት ወትብሎ በእንተዝ ገብሮ እግዚእ እግዚአብሔር ሊተ አመ ወፃእኩ እምብሔረ ግብጽ፤

ጠላቴን አጥፍቶልኝ ከግብጽ አገር በወጣሁ ጊዜ ፈጣሪዬ እግዚአብሔር ስለዚህ ነገር ይህንን ሥርዓት አድርጎ ሠራልኝ፤ ብለህ በዚህች ቀን ለልጅህ ንገረው፤

፱፤ ከመ ይኩን ለከ ተአምረ ውስተ እዴከ ወተዝካረ ቅድመ አዕይንቲከ ወከመ ይኩን ሕጉ ለእግዚአብሔር ውስተ እዴከ ወውስተ አፉከ እስመ በዕድ ጽንዕት አውፅአከ እግዚአብሔር እምግብፅ፤

እግዚአብሔር በጽኑ ሥልጣኑ ጠላትህን አጥፍቶ ከግብጽ አውጥቶሃልና ይህ የሠራልህ የእግዚአብሔር ሕጉ ለጣትህ /ለእጅህ/ እንደ ቀለበት በፊትህ እንደ መስታዎት አድርገህ በአንደበትህ ልታስተምረው ነው፤

፲፤ ወዕቀብዎ ለዝንቱ ሕግ በበጊዜሁ እምዕለት ለዕለት ፤

እምዕለት ዕለትም ይላል፤ ይህን ንም ሕጉን ሥርዓቱን ከዛሬ ነገ እያላችሁ፤ አንድም እምዕለት ዕለተ ይላል፤ ከዛሬ ነገ፤ ከነገ ማግስት እያላችሁ በየጊዜው ይህን ሥርዓት ጠብቁት፤

፲፩፤ ወሶበ ወሰደከ እግዚአብሔር ውስተ ምድረ ከናኔዎን ዘመሐለ ለአበዊከ ወወሀበካሃ፤

እግዚአብሔርም በቸርነቱ ለአባቶችህ ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ አወርሳቸዋለሁ ብሎ ወደ ማለላቸው ወደ ከነዓን አገር በወሰደህ ጊዜ እሷንም ባወረሰህ ጊዜ፤

፲፪፤ ፍልጥ ኵሎ ዘይፈትሕ ማኅፀነ እመራዕይከ ወእምእንስሳከ ዘይትወለድ ተባዕተ ለእግዚአብ ሔር፤

ከመንጋህ፤ ከሌላውም ከብትህ መጀመሪያ የተወለደውን ወንድ ወንዱን ሁሉ ለእግዚአብሔር ለይተህ ስጥ፤ አንድም መጀ መሪያ የተወለደውን ወንድ ወንዱን፤ ፍልጥ እመራዕይከ ከመንጋህ ከከብትህ ለይተህ ለእግዚአብሔር ስጥ፤

፲፫፤ ወኵሎ ዘይፈትሕ ማኅፀነ እድግት ትዌልጦ በበግዕ ወእመሰ ኢወለጥከሁ ትቤዝዎ ወለኵሉ በኵር ተባዕት እምውሉድከ ትቤዝዎ፤

ካህያዪቱ መጀመሪያ የተወለ ደውን በኵሩን በበግ ለውጠው፤ የአህያውን በኵር ግን በበግ ባትለውጠው አንተ ራስህ ተቤዠው አለ፤ ስለ አህያው በኵር ወርቁን ስጥ፤ የምትቤ ዠውም ይኸነን ብቻ አይደለም፤



ከልጆችህም መጀመሪያ የተወ ለደውን በኵሩን ልጅ ተቤ ዠው አለው፤ ወርቁን ሰጥተህ ልጅህን አስቀር ሲል ነው፤

፲፬፤ ወእመ ተስእለከ ወልድከ እምድኅረዝ ወይቤለከ ምንት ውእቱ ዝ ወትብሎ እስመ በእድ ጽንዕት አውፅአነ እግዚአብሔር እምድረ ግብጽ እምቤተ ቅንየት፤

ከዚህ በኋላ ልጅህ አባቴ ይህ ነገር ምንድነው ብሎ ቢጠ ይቅህ፤ እግዚአብሔር በጽኑ ሥልጣኑ ጠላቶቻችንን አጥፍቶ በግብጽ አገር ከጽኑ አገዛዝ፤ አንድም ከግብጽ አገር፤ ወእም ቤተ ቅንየት፤ ከጽኑ አገዛዝም አውጥቶናልና ስለዚህ ነው በለው፤

፲፭፤ ወከነ አመ አበየ ፈርዖን ፈንዎተነ ቀተለ እግዚአብሔር ኵሎ በኵረ በምድረ ግብጽ እምበኵረ ሰብእ እስከ እንስሳ ወበእንተዝ አነ እሠውዕ ለእግዚአ ብሔር ኵሎ ተባዕተ ዘይፈትሕ ማኅፀነ ወኵሎ በኵረ ውሉድየ እቤዙ፤

ፈርዖን ከግብጽ እኛን አሰና ብቶ አልሰድም ባለ ጊዜ ኮነ ያለውን ቀተለ ብሎ አመጣ፤ እግዚአብሔር ከሰው በኵር ጀምሮ እስከ ከብት በኵር ድረስ በግብፅ አገር የግብጻ ውያንን በኵር በኵሩን አጥፍ ቶልናልና፤ እኔም ይህን ሁሉ ነገር ስላደረገልኝ ከመንጋዬ መጀመሪያ የተወለደውን ሁሉ ለፈጣሪዬ ለእግዚአብሔር እሠዋለሁና፤ ከልጆቼም መጀ መሪያ የተወለደውን በኵሩን ሁሉ በገንዘብ እቤዠዋለሁና ስለዚህ ነው በለው፤ አንድም በእንተዝ ይላል፤ ፈርዖን ከግብጽ እኛን አሰናብቶ አልሰድድም ባለ ጊዜ እግዚአብሔር በግብጽ አገር የግብጻውያን በኵር በኵሩን ከሰው በኵር ጀምሮ እስከ ከብት በኵር ድረስ አጥፍቶልናል፤ ስለዚህ ነገር ከመንጋዬ መጀመሪያ የተወለ ደውን በኵር ሁሉ ለእግዚአ ብሔር እሠዋለሁ፤ ከልጆቼም መጀመሪያ የተወለደውን በኵሩን ሁሉ እቤዠለሁ በለው፤

፲፮፤ ወይኩን ተአምረ ውስተ እዴከ ወዘኢይሴስል እምቅድመ አዕይንቲከ እስመ በእድ ጽንዕት አውፅአከ እግዚአብሔር፤

አውፅአነም ይላል፤ እግዚአብ ሔር በጽኑ ሥልጣኑ ከግብጽ አውጥቶሃልና ይህ የሠራልህ ሕጉ ለጣትህ እንደ ቀለበት፤ ለፊትህ እንደ መስታዎት ይሁንልህ አለው፤

፲፯፤ ወሶበ ፈነዎሙ ፈርዖን ለሕዝብ ኢመርሆሙ እግዚአብሔር ፍኖተ ፍልስጥኤም እስመ ቅርብት ይእቲ፤ እስመ ይቤ እግዚአብሔር

www.ethiopianorthodox.org

የጊ ይኔስሕ እምከመ ርእየ ቀትለ ወይገብእ ውስተ ምድረ ግብጽ፣

ፈርዖን እስራኤልን አሰናብቶ ከግብጽ በሰደዳቸው ጊዜ እስራኤል ሰልፉን ካየ ያዝናል፣ አዝኖም ወደ ግብጽ ይመለሳል ብሏልና፣ ፍልስጥኤም የግብጽ አቅራቢያ ስለሆነች እግዚአብሔር ወደ ፍልስጥኤም ጎዳና አልመራቸውም፤

፲፰፣ ወአዖዶሙ እግዚአብሔር ለሕዝብ ሳዕለ ፍኖተ ሐቅለ ባሕረ ኤርትራ ወበኃምስ ትውልድ ዐርጉ ደቂቀ እስራኤል እምድረ ግብጽ፤

እግዚአብሔርም ይህን ብሎ ወገኖቹ እስራኤልን በኤርትራ ባሕር ዳር በአለው ጐዳና አዞራቸው አ[illegible]፣ ፊት ለፊት የሆነ እንደሆነ ተሻግረው ያጡአቸ ዋልና ብሎ፤ አንድም በፍልስጥኤም ያለው ባሕር ቅርብ ስለሆነ ጉጭኝ ነውና ለማስጠም አይመችም ብሎ፤ አንድም ሰልፉን አይተው ፈርተው ይመለሳሉና ብሎ ወበኃምስ ትውልድ፣ እስራኤልም ከግብጽ አገር በአምስተኛው ትውልድ ወጡ፣ በቤተ ክህነት የቈጠሩ እንደሆነ ያዕቆብ ሌዊ ቀዓት እንበረም ሙሴ ነው፣ በቤተ መንግሥት የቈጠሩ እንደሆነ ፋሬስ ኤስሮም አራም አሚናዳብ ነአሶን ነው፤

፲፱፣ ወነሥአ ሙሴ አዕፅምቲሁ ለዮሴፍ ምስሌሁ፣ እስመ መሐላ አምሐሎሙ ለደቂቀ እስራኤል ወይቤሎሙ አመ ሐውፆ ሐወፀክሙ እግዚአብሔር ንሥኡ አዕፅምትየ ወአውፅኡ ምስሌክሙ እምዝየ፣

ኢትኅድጉ አዕፅምትየ ውስተዛ ሀገርም ይላል፣ ዮሴፍ በሕይወተ ሥጋ ሳለ እስራኤልን እግዚአብሔር በምድር በጎበኛችሁ ጊዜ አጥንቴን በዚህ አገር አትተዉብኝ ከእናንተ ጋር ይዛችሁት ውጡ ብሎ አምሎአቸው ነበርና፣ እስራኤል ከግብጽ በወጡ ጊዜ ሙሴ የዮሴፍን አጥንት ከእሱ ጋር ይዞት ወጣ፣ ዮሴፍም እንዲህ ማለቱ አሁን በግብጽ ብቀበር እረክሳለሁ፣ በከነዓን ብቀበር እቀደሳለሁ ብሎ አይደለም፣ ለመውጣት እንዲተጉ፤ አንድም ተስፋ እንዲያደርጉ ነው እንጂ፣ እንኳን እኛ አጥንታችን አይቀር ብለው፤ አንድም ግብጽ የኃጢአት፣ ከነዓን የጽድቅ፣ አንድም ግብጽ የገሃነም፣ ከነዓን የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ናትና ስለዚህ ነው እንጂ፤

፳፣ ወግዕዙ ደቂቀ እስራኤል እምሰኩት ወኃደሩ ውስተ ኦቶም ዘመንገለ በድው፣

የእስራኤልም ልጆች ከሰኩት ተነሥተው ተጉዘው ሒደው



በምድረ በዳው አጠገብ ባለ በኦቶም ሰፍረው አደሩ፤

፳፩፣ ወእግዚአብሔር ይመርሆሙ መዓልተ በደመና ወሌሊተ በብርሃነ እሳት፣

እግዚአብሔርም ቀን በዓምደ ደመና፣ ሌሊት በዓምደ እሳት ይመራቸው ነበር፣

፳፪፣ ወኢሰሰለ ዓምደ ደመና መዓልተ ወኢዓምደ እሳት ሌሊተ እምቅድመ ኵሉ ሕዝብ፣

ቀን ዓምደ ደመናው፣ ሌሊት ዓምደ እሳቱ ከወገኖቹ ከእስራኤል ሁሉ ፊት አይርቅም ነበር (አልራቀም) ነበር፣ ይህም ማካፈል አይደለም፣ ቀን ዓምደ ደመና ሁኖ የሚመራቸው ሌሊትም ያው ዓምደ እሳት ሁኖ ይመራቸው ነበር ሲል ነው።

## ምዕራፍ ፲ወ፬

፩-፪፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ በሎሙ ለደቂቀ እስራኤል ይግብኡ ወይኅድሩ አንጻረ ኤጳውሎስ /ኤጴውሎስ/ ማዕከለ መግደሎ ወማዕከለ ባሕር መንገለ ብኤልሴፎን ቅድሜሆሙ ይኅድሩ ኀበ ባሕር፣

ባሕርና ባሕር፣ ይኅድሩና ይኅድሩ አንድ ወገን፣ እግዚአብሔር ሙሴን የእስራኤልን ልጆች በፊታቸው ባለ በብኤልሴፎን አጠገብ ባለ ባሕርና በመግደሎ መካከል ባለ በኤጳውሎስ አንጻር ተመልሰው ሔደው ያድሩ ዘንድ ተመልሳችሁ ሒዳችሁ በኤጳውሎስ አንጻር እደሩ በላቸው አለው፣ ኤጳውሎስ አንፃረ ኀኒሩት አንጻረ ብርሃን ማለት ነው፤ አንድም በቅድሜሁ ይላል፣ ለብኤልሴፎን ሲቀጽል ነው፤

፫፣ ወይብል ፈርዖን በእንተ ደቂቀ እስራኤል ሰኩዩ /ሳኩዩ/ እሙንቱ ውስተ ምድር ወአርከበቶሙ ሐቅል፣

ፈርዖንም የእስራኤልን ልጆች ነገር እንዲህ አለ፣ እሊህ እስራኤል በአገሬ በግብጽ ተቅበዘበዙ፣ የአገሬ ምድረበዳ አስገኘቻቸው ጎዳናውን አያውቁትም፤ አንድም ያቺ ፈዛዛ ባሕር አስገኘቻቸው አለ፤

፬፣ ወአነ አጸንዕ ልቦ ለፈርዖን ወይዴግኖሙ ድኅሬሆሙ /እምድኅሬሆሙ/ ወእሴባሕ አነ በፈርዖን ወበኵሉ ሐራሁ ወየአምሩ ኵሉ ግብጽ ከመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር ወገብሩ ከማሁ፣

እኔም የፈርዖንን ልቡና በክፋት አጸናለሁ፣ እሱም እነሱን ተከትሎ ሒዶ ይሞታል፣ እኔም ፈርዖንንና ሠራዊቱን አጥፍቼ እመሰገናለሁ፣ ወገኖቹ ግብጻውያንም ሁሉ እኔ ገናና ፈጣሪ

www.ethiopianorthodox.org

ለምን እንዲህ አደረግህ? አንድም ከግብጽ አገር የወጣ ኸን አንተ በምድረ በዳው ልታ ስጠፋን ለምን እንዲህ አደረግኸ? አሉት፤

፲፪፤ አኮኑ ዝውእቱ ቃልነ ዘንቤለከ በብሔረ ግብጽ ኅድገነ ንትቀነይ ለግብጽ እስመ ይኄይሰነ ተቀንዮ ለግብጽ እመዊት በበድው፤

በምድረ በዳ ከመሞት ለግብጽ ሰዎች መገዛት ይሻለናልና፤ ለግብጽ ሰዎች ተወን እንገዛ፤ አንድም እንገዛ ተወን ብለን በግብጽ አገር ሳለን ጥንቱን የነገርንህ ቃል ይኸ አይደለ ምን አሉት፤ ከመሞት መሰንበት እንዲሉ፤

፲፫፤ ወይቤሎሙ ሙሴ ለሕዝብ ተአመኑ ወቁሙ ትርአዩ /ወትሬእዩ/ መድኃኒተ እንተ እምነበ እግዚአብሔር ዘይገብር ለነ ዮም፤ እስመ በከመ ትሬእይዎሙ ዮም ለግብጽ ዳግመ ኢትሬእይዎሙ እንከ ጕንዱየ ለዓለም፤

ሙሴም እስራኤልን ዛሬ ግብጻውያን ተሰብስበው መጥተው እንዳያችኋቸው ዳግመኛ ኑረው በሕይወት አታዩአቸውምና ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ዛሬ የሚያደርግልንን ከፈጣሪያችን ከእግዚአብሔርም ዘንድ ታገዛ የምናገኛት ድኅነታችንን ልታዩ አምናችሁ ቁሙ፤ አንድም እና ንተ አምናችሁ ቁሙ፤ ፈጣሪ ያችን እግዚአብሔር ዛሬ የሚ ያደርግልንን እኛም ከፈጣሪ ያችን ከእግዚአብሔር ዘንድ የምናገኛት ድኅነታችንን /መድኃኒታችንን/ ታያላችሁ አላቸው ፤

፲፬፤ ወእግዚአብሔር ይፀብዕ ለክሙ ወአንትሙሰ አርምሙ፤

ጠላታችሁን የሚያጠፋላችሁ እግዚአብሔር ነው፤ እናንተ ግን ዝም በሉ አላቸው፤ ዘይ ገብር ለነ ያለውን አመጣ፤ ይኸንንም ብሎ በጽራሐ ልቡና ወደ እግዚአብሔር አመለከተ፤

፲፭፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ለምንት ትጸርሕ ኀቤየ በሎሙ ለደቂቀ እስራኤል ይንድኡ እንስሳሆሙ ፤ /ሳሕሞሙ/

እግዚአብሔርም ይኸነን ሰምቶ ሙሴን ወደ እኔ ለምን ትጮ ሃለህ /ትለምናለህ/፤ አሁንም የእስራኤልን ልጆች ከብታች ሁን ንዱ በላቸው፤

፲፮፤ ወአንተሰ ንሣእ በትረከ ወስፋሕ እዴከ ዲበ ባሕር ወዝብጣ ወይባኡ ደቂቀ እስራኤል ውስተ ማዕከለ ባሕር በየብስ፤

እነሱ ከብቶቻቸውን፤ ይንዱ አንተ ግን ተአምራት ያደረግ



ህባት በትርህን ይዘህ ሒድ፤ ከባሕሪቱ ስትደርስ እጅህን ዘርግተህ በበትሪቱ ባሕሪቱን ምታት፤ ከሦስት ከአራት ትከፈላለች፤ እስራኤልም ተከ ፍሎላቸው የብስ ወደ ሆነው ባሕር ይግቡ፤ አንድም ተከፍ ሎላቸው በየብሱ ለመሻገር ወደ ባሕሩ ይግቡ፤

፲፯፤ ወናሁ አነ አጸንዕ ልቦ ለፈርዖን ወለኵሉ ግብጽ ወይበውኡ ድኅሬሆሙ ወእሴባሕ አነ በፈርዖን ወበኵሉ ሐራሁ ወበሠረገላቲሁ ወበኵሉ አፍራሲሁ፤

እኔም የግብጽን ሰዎችና የፈርዖ ንን ልቡና በክፋት አጸናለሁ፤ ግብጻውያንም እስራኤልን ተከ ትለው ወደ ባሕሩ ይገባሉ፤ እኔም ሠራዊቱንና ፈርዖንን፤ ሠረገላውንና ፈረሱን ሁሉ አስጥሜ እመሰገናለሁ፤

፲፰፤ ወየአምሩ ኵሉ ግብጽ ከመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር አመ ተሰባሕኩ በፈርዖን ወበሠረገላቲሁ ወበኵሉ አፍራሲሁ፤

ፈረሱንና ሠረገላውን ፈርዖን ንም በኤርትራ ባሕር አስጥሜ በተመሰገንኩ ጊዜ ገናና ፈጣሪ እንደ ሆንኩ ግብጻውያን ያንጊዜ ያውቃሉ፤ አንድም ተሰቢሕየ ይላል፤ ፈርዖንንና ሠረገላውን ፈረሶቹንም ሁሉ በኤርትራ አስጥሜ የተመሰገንሁ ገናና ፈጣሪ እኔ እንደሆንኩ የግብጽ ሰዎች ያን ጊዜ ያውቃሉ በላቸው አለው፤

፲፱፤ ወሰሰለ መልአከ እግዚአብሔር ዘየሐውር ቅድመ ትዕይንቶሙ ለእስራኤል ወቆመ እምድኅሬሆሙ ወሰሰለ ዓመደ ደመናሂ እምቅድሜሆሙ ወቆመ እምድኅሬሆሙ፤

ያንጊዜም በእስራኤል ፊት ለፊት ይሔድላቸው የነበረው መጋቤ ብሉይ ቅዱስ ሚካኤ ልም ተመልሶ በስተኋላቸው ቆመ፤ ፊት ለፊት ይመራቸው የነበረ ዓምደ ደመናም ተመልሶ በስተኋላቸው ቆመ ተጋረደ፤

፳፤ ወቦአ ማዕከለ ትዕይንቶሙ ለግብጽ ወማዕከለ ትዕይንቶሙ ለእስራኤል ወኮነ ቆባር ወጽልመት ወኢተደመሩ በበይናቲሆሙ ኵሳ ይእተ ሌሊተ፤

ደመናውም በእስራኤል ሠራዊ ትና በግብጻውያን ሠራዊት መካከል ገብቶ ተጋረደ፤ ያንጊዜ ጭጋግ ጨለማ ሆነ፤ በዚያች ሌሊት ስንኳን ሌላው እስራ ኤልና እስራኤል አልተገና ኙም አልተያዩም፤ ይህስ አይ ደለም ብሎ ግብጻውያንና እስራኤል አልተገናኙም ሳይ ተያዩ ሳይተዋወቁ በአንድ ችካል ከብት አስረው አድረ ዋል፤

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

፳፩፣ ወሰፍሐ እዴሁ ሙሴ ዲበ ባሕር ወአምጽአ እግዚአብሔር ነፋሰ አዜብ ጽኑዐ ኵሎ ሌሊተ ወገብሮ ለባሕር የብሰ ወሠጠጠ ለማይ፣

ሙሴም እጁን ዘርግቶ በበትሩ ባሕሩን መታው፣ እግዚአብሔርም በዚያች ሌሊት ጽኑዕ ኃያል የሆነ የአዜብን ነፋስ ወደ ባሕሩ አመጣ፣ ባሕሩንም ከሦስት ከአራት ከፍሎ የብስ አደረገው ነፋሱ፤ አንድም እግዚአብሔር፣

፳፪፣ ወቦኡ ደቂቀ እስራኤል ማዕከለ ባሕር ላዕለ የብስ ወማይሰ ኮነ አረፍተ በየማኖሙ ወአረፍተ በጸጋሞሙ፣

እስራኤልም ከሦስት ከአራት ተከፍሎ የብስ ሆነላቸው ወደ ባሕሩ ገቡ፣ ማይኒ ሲል ነው፣ ውሃውም በቀኝ በግራ እንደ ግድግዳ ሆነላቸው፤ አንድም ማይሰ ውህውሳ ትለኝ እንደሁ ውህውስ በቀኝ በግራ ተከፍሎ እንደ ግድግዳ ጸናላቸው፣ ሐተታ ከሦስት ተከፍሏል ያሉ እንደ ሆነ፣ አራት አራቱ ነገድ ተሻግረዋል፣ ከአራት ተከፍሏል ያሉ እንደሆነ፣ ሦስት ሦስቱ ነገድ ተሻግረዋል፣ ውህውንም እንዳይፈሩ ብሎ እንዲተያዩ እንደ መስታዎት አድርጎላቸዋል፣ አንድም በውህው መስኮት መስኮት አውጥቶላቸዋል፣ ግራና ቀኝ እየተያዩ እንዲሔዱ ብሎ፤

፳፫፣ ወዴገንዎሙ ግብጽ ወቦኡ ድኅሬሆሙ ወኵሉ አፍራሰ ፈርዖን ወሠረገላቲሁ ወመስተዕዕናን ቦኡ ማዕከለ ባሕር፣

ቦኡና ቦኡ አንድ ወገን፣ ያንጊዜ የግብጽ ሰዎች የፈርዖን ፈረሶች ሠረገላውም፣ በፈረስ በሠረገላ የተቀመጡ ሰዎችም ሁሉ እስራኤልን ተከትለው ወደ ባሕሩ ገቡ፣ ለሰው አገሮች ለእስራኤል የተከፈለች ውሃ፣ የአገራችን ውህ ለእኛማ ምን ትለናለች ብለው፣ ለኩ ለለኩ እጅ ለእጅ ተያይዘው፣ አይዞኅ አይዞኅ ተባብለው፣ ተያይዘው ገብተዋል፣

፳፬ ወሶበ ኮነ ዕቅበተ ሌሊት እንተ አፈ ጽባሕ ነጸረ እግዚአብሔር ውስተ ትዕይንቶሙ ለግብጽ በዓምደ እሳት ወደመና ወአዘዘ ላዕለ ትዕይንተ ግብጽ፣

ንጋት የተከተለው ሦስተኛው አካች (ሠልፍ) በሆነ ጊዜ፤ አንድም አካችን አራት የሚሉ አሉ፣ ንጋት የተከተለው አራተኛው አካች በሆነ ጊዜ፤ አንድም ንጋት በሚከተለው ከሦስተኛው አካች (ሠልፍ) አስቀድሞ የሚሆን ሁለተኛው አካች በሆነ ጊዜ፣ እግዚአብሔር በዓምደ እሳትና በዓምደ ደመና ሁኖ የግብጽን ሠራዊት በዓይነ መዓት አያቸው፣ በግብጸውያንም ከተማ መዓት አዘዘባቸው፤

፳፭፣ ወዓሠረ ማዕሠርተ ሠረገላቲሆሙ ወወሰዶሙ በሥቃይ ወይቤሉ ግብጽ ንንፋጽ እምገጸሙ ለእስራኤል እስመ እግዚአብሔር ይፀብዕ ሎሙ፣

አዘዘ ያለውን፣ አሠረ ማእሠርተ ብሎ አመጣው፤ አንድም ወወሰዶሙ በሥቃይ ብሎ አመጣው፣ ያን ጊዜ ግብጸውያን ለእስራኤል የሚጣላላቸው የሚዋጋላቸው ፈጣሪያቸው እግዚአብሔር ነውና ከእስራኤል ፊት እንሽሽ አሉ፣ ጌታ ግን እንዳይመለሱ ብሎ ቅል ለቅል፣ ለኩ ለለኩ አያያዛቸው፣ ወወሰዶሙ በሥቃይ፣ በነፋሱም እያጣደፈ ወደ ባሕሩ ወሰዳቸው፤

፳፮፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ስፋሕ እዴከ ዲበ ባሕር ወይትጋባእ ማይ ዲበ ግብጽ ወዲበ ሠረገላቲሆሙ ወመስተዕዕናኒሆሙ፣

ከዚህ በኋላ የፊተኛው ፈረስ ግንባሩ፣ የኋለኛው ፈረስ ጭራው ሲቀር፣ እግዚአብሔር ሙሴን እጅህን ዘርግተህ ባሕሪቱን ምታት፣ በግብጽ ሰዎች፣ በሠረገሎቻቸው፣ በፈረስ በሠረገላ በተቀመጡትም ሁሉ ላይ ውሃው ይጠራቀምባቸው አለ፤



፳፯፣ ወሰፍሐ እዴሁ ሙሴ ዲበ ባሕር ወከደኖሙ ባሕር በጊዜሁ /በዕለቱ/ ወአገቶሙ እምድኅር ወጌዩ ግብጽ ውስተ ባሕር ወወገሮሙ እግዚአብሔር ለግብጽ ማዕከለ ባሕር፣

ሙሴም እጁን ዘርግቶ ባሕሩን መታው፣ ባሕሩም ያንጊዜ በስተፊት ያለው ውሃ ተንዶ ተጫናቸው፣ ወደኋላ እንመለስ አሉ፣ በስተኋላ ያለው ውሃ ተናደባቸው፣ ተመልሰው ወደ መካከል ሔዱ፣ እግዚአብሔርም በባሕሩ መካከል አሠጠማቸው፤

፳፰፣ ወተመይጠ ባሕር ወተሠጥሙ ምስለ ሠረገላቲሆሙ ወምስለ ጽኑዓኒሆሙ ወኵሉ ኃይሉ ለፈርዖን በከመ መጽኡ ውስተ ባሕር ወአልቦ ዘተርፈ እምኔሆሙ እለ መጽኡ ወኢአሐዱ እምኔሆሙ፣

ባሕሩም እንደ ቀደመው ሆነ፣ የግብጽ ሰዎችም ከሠረገላቸው ጋር፣ ከአርበኞቻቸውም ጋር፤ አንድም ምስለ መስተጽዕናኒሆሙ ይላል፣ በፈረስ በሠረገላ ከተቀመጡት ሰዎች ጋር የፈርዖን ሠራዊቱም ሁሉ ወደ ባሕሩ እንደ መጡ ሠጠሙ፣ እስራኤልን ተከትለው ከመጡ ከግብፃውያን ሁሉ አንድ ስንኳን የቀረ የለም፣ መላው ሰጠሙ፤ አንድም ከግብጽ ከመጡ ከእስራኤል ሁሉ አንድ ስንኳን የቀረ የለም መላው ወጡ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፱፣ ወደቂቀ እስራኤልሰ ሖሩ ውስተ ይብስት ባሕር ወባሕርሰ ዓረፍተ ኮኖሙ እምይምን ወእም ጽግም፣

እስራኤል ግን እንደ ለሩ መስክ ሆኖላቸው በተከፈለ ችው ባሕር አልፈው ሔዱ፣ ባሕርኒ ሲል ነው፣ ባሕሩም ከዚህ አስቀድሞ በቀኝ በግራ እንደ ግድግዳ ሆነላቸው፤

፴፣ ወአድኃኖሙ እግዚአብሔር ለእስራኤል በይእቲ ዕለት እምእዴሆሙ ለግብጽ ወርእዩ እስራኤል ከመ ሞቱ ግብጽ በውስተ ድንጋጉ ለባሕር፣

እግዚአብሔርም በዚያች ቀን እስራኤልን ከግብጻውያን እጅ አዳናቸው፣ እስራኤልም ጠላቶቻቸው ግብጻውያን እንደ ሞቱላቸው በባሕር ዳር ሁነው አዩ፤

፴፩፣ ወርእዩ እስራኤል እደ ዐቢየ ዘገብረ እግዚአብሔር በግብጽ ወፈርሁ ወአምኑ በእግዚአብሔር ወሙሴሃ ላዕኮ አዕበዩ፣

እስራኤልም የጠላቶቻቸው የግብጻውያንን ሞት፣ ፈጣሪያቸው እግዚአብሔር በግብጽ ሰዎች ያደረገባቸውን ተአምራቱን አይተው እግዚአብሔርን ፈሩ፣ አምለኩ፣ በእግዚአብሔርም አመኑ፣ ፈርሀን አምለከ ሲል ነው፣ ሶበሰ በፍርሀተ ይስሐቅ አቡየ እምፈነውከኒ. እራቅየ እንዲል አገልጋዩ ሙሴንም አከበሩ።

## ምዕራፍ ፲ወ፭

### ገባኤ

፩፣ ወባረኩ ዘ ቡራኬ ሙሴ ወደቂቀ እስራኤል ለእግዚአብሔር በፍትሐተ ቃል እንዘ ይብሉ ንባርኮ ለእግዚአብሔር እስመ ክቡር ውእቱ ወሉቱ ይደሉ ስባሔ፣

ያንጊዜ ሙሴ ከእስራኤል ልጆች ጋር ሁኖ ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀረቡ፤ አንድም ወባረኩ ይላል፣ ያንጊዜ የተደረገላቸውን ተአምራት አይተው በፍትሐተ ቃል ዲዳዎች አንደበታቸው ተፈትቶላቸው፤ አንድም በርትዓተ ቃል ይላል፣ ሕፃናቱ እንደበታቸው ረትቶላቸው እስመ ጥበብ ከሠተት አፈ በሐማን፣ ወልሳነ ሕፃናት ረሰየት ርቱዐ ነባቤ እንዲል፤ አንድም በኅብረተ ቃል ይላል ጕርናና ሻካራ ድምፅ ሳይኖር እንደ አንድ ልብ መካሪ፣ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሁነው ሙሴ አሮን የወንዶች አቀንቃኝ፣ ማርያም እኅተ ሙሴ የሴቶች አቀንቃኝ ሁነው እግዚአብሔር ክቡር ምስጉን



ነውና ለእሱም ምስጋና ይጋባዋልና እግዚአብሔርን እናመስግነው እያሉ ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀረቡ፤ አንድም መተርጕም እንዲህ ይላል፣ እግዚአብሔር ክቡር ምስጉን ነውና ለእሱም ምስጋና ይገባዋልና እግዚአብሔርን እናመስግነው እያሉ ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀረቡ ይላል፤

ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ስቡሐ ዘተሰብሐ ፈረሰ ወመስተፅዕነ /ወዘተፅዕኖ/ /ወመስተፅዕኖ/ ወረወ ውስተ ባሕር፣

ፈረሱን፣ በፈረሱ ላይ የተቀመጠውን አርበኛ ሁሉ በኤርትራ ባሕር አስጥሟቸዋልና ምስጉን ሁኖ የተመሰገነ እግዚአብሔርን እናመስግነዋለን አሉ፣ ምስጉን ሁኖ የተመሰገነ አለው፣ ሰው ባልሆነው ይመሰገናል፣ ደካማው ብርቱ፣ ደንቆሮው ብልህ፣ ንፉግ ለጋስ፣ ድኃው ባለጸጋ፣ ተብሎ ይመሰገናል፣ ጌታ ግን በኃይሉ ድካም፣ በብዕሉ ንድየት፣ በጥበቡ ድንቁርና፣ በቸርነቱ ንፍገት የለበትምና ምስጉን ሁኖ የተመሰገነ አለው፤ አንድም ያካፍላል እግዚአብሔርን እንግዲህ ወዲያ እናመስግነዋለን፣ ወዘተሰብሐ ከዚያም ቀድሞ ተአምራት ያደረገ፣ /አድርጎ/ የተመሰገነ እግዚአብሔርን ንሴብሖ፤ አንድም ምስጉን ሆኖ የተመሰገነ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን፤ አንድም ፈረሰ ሠራዊተ አጋንንትን፣ ወመስተፅዕነ ሊቃነ አጋንንትን በባሕረ ገሃነም አስጥሟልና ምስጉን ሆኖ የተመሰገነ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን አለ፤

፪፣ ረዳኤ ወመሠውረ ኮነኒ ለአድኅኖትየ፣

ረዳኤ በደመ በግዕ፣ ወመሠውረ በደመና፣ እኔን ለማዳን ረዳት ሆነኝ፤ አንድም ረዳኤ በደሙ፣ ወመሠውረ በመንፈስ ቅዱስ እኔን ለማዳን ረዳት ሆነኝ፤

ውእቱ አምላኪየ እሴብሖ አምላከ አቡየ ወአሌዕሎ፣

ይኸውም እንደ እንግዳ ደራሽ፣ እንደ ውሀ ፈሳሽ አይደለም፣ ጥንቱንም ፈጣሪዬ ነው አመሰግነዋለሁ፣ ጥንቱንም የአባቶቼ የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ ፈጣሪ ነው አከብረዋለሁ፣ አገንነዋለሁ አለ፣ ልዕልናውን ገናንነቱን እናገራለሁ፣ አንድም ሥጋው ቃል ጥንቱንም ፈጣሪዬ ነው አመሰግነዋለሁ፣ ጥንቱንም የአባቶቼ የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ ፈጣሪ ነው

www.ethiopianorthodox.org

አከብረዋለሁ አገንነዋለሁ አለ፣ ክብሩን ገናንነቱን እናገራለሁ፣ እምቅድመ ይት ወለድ አብርሃም ሀሎኩ አነ እንዲል፣ ሥጋ በተዋሕዶተ ቃል ቀዳማዊ አምላክ መሆኑን መናገር ነው፡፡

፫፣ እግዚአብሔር ይቀጠቅጥ ፀብዓ ወእግዚአብሔር ስሙ፣

ፀባዔ ሲል ነው፣ እግዚአብሔር አርበኛ ፈርዖንን ያጠፋል፤ አንድም እንዳለም ይሆናል፣ የግብፃውያንን ጦር ያጠፋል፤ ስሙም አቸናፊ ይባላል፣ አንድም አርበኛ ዲያብሎስን ያጠፋል፤ አንድም ፀብዓ አጋንንትን ያጠፋል፤ ስሙም አምላክ ወሰብእ ይባላል፤

፬፣ ሠረገላቲሁ ለፈርዖን ወሠራዊቶ ወረወ ውስተ ባሕር ኅሩያነ ወመስተፅዕናነ በመሥልስት ወተሠጥሙ ውስተ ባሕረ ኤርትራ፣

የፈርዖንን ሠረገላዎቹን ሠራዊቶቹን በባሕረ ኤርትራ አሠጠመ፣ ኅሩያን በመሥልስት፣ መስተጽዕናን በመሥልስት ብለው ይገጥሙታል፣ ኅሩያን በመሥልስት እለዚህም ለሹመት፣ ለምክር፣ ለጦር በሦስት ወገን የተመረጡ አላቸው፣ ለሹመት ራስ፣ ቢትወደድ፣ ጥቃቅን፣ ብላቴን ጌትነት፤ አንድም ንጉሥ፣ ራስ፣ ቢትወደድ ለሹመት ይህ ነው፣ ለምክር የተመረጡ አለ፣ ለጦር፣ ለፍርድ፣ ለቤት ማስተንተን፣ የሚመክሩ መካሮች በሦስት ወገን ይመረጣሉና መስተጽዕናን በመሥልስት አላቸው፣ ድር፣ እግር፣ ሠረገላ ሁነው መጥተዋልና፤ አንድም በአንዱ ሠረገላ ሦስት ወገን ሁነው ይሰለፉበታል፣ ነፍጠኛ ቀስተኛ፣ ጋሻ ጦር ያየዘ ነው፤ አንድም አንዱ ሰው በአንዱ ሠረገላ ጋሻ፣ ጦር፣ ጐራዴ፣ ይዞ ይሰለፍበታልና፣ አብነት ወረወን ያየ እንደሆነ ኅሩያነ ወመስተፅዕናነ በመሥልስት ይላል፣ እንደዚህም ይጽፋል፣ እነዚህም ሁሉ በባሕረ ኤርትራ ሠጠሙ፤ አንድም የዲያብሎስን ሠራዊት አጋንንትንና ሊቃነ አጋንንትን በባሕረ ገሃነም አሠጠመ፤ ኅሩያን በመሥልስት መስተፅዕናን በመሥልስት ብለው እንደዚያው ይገጥሙታል፣ ኅሩያን በመሥ እለዚህም በሦስቱ ሰማያት ከአሉ መላእክት ተመርጠው በኢየሩሳሌም ሰማያዊት ሊኖሩ የተፈጠሩ አጋንንት ናቸው፣ መስተፅዕናን በመሥልስት አላቸው፣ እለዚኽውም በሦስተኛዪቱ ከተማ በኢየሩሳሌም ሰማያዊት ሊኖሩ የተፈጠሩ



ነበሩ፣ (ናቸው)፣ ኢየሩሳሌም ሰማያዊትን መሥልስት አላት፣ መንበረ መንግሥት፣ (ፀባዖት) ሰማይ ውዱድ፣ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ሦስተኛ ናትና ጽርሐ አርያምን፣ ትቶ ነው፣ በላይ እንደ አኀበር ነውና፣ አንድም ዛሬ በአየር በዚህ ዓለም በእንጦርጦስ ወድቀው ያሉ ናቸው፣ ቦ ዘወድቀ ውስተ አየር፣ ወቦ ዘወድቀ ውስተ ምድር፣ ወቦ ዘወድቀ ውስተ እንጦርጦስ ዘውእቱ መትሕተ ታሕቲት እንዲል፤ አንድም በሦስቱ ነገድ አድረው ያሉ አለ፣ በነገደ ሤም፣ በነገደ ያፌት፣ በነገደ ካም ነው፤ አንድም በነፍስ በሥጋ በልቡና አድረው የሚያስቱ ናቸው፣ እነዚህም ሁሉ በባሕረ ገሃነም ሠጠሙ፤

፭፣ ወደፈኖሙ ማዕበል ወተሠጥሙ ውስተ ቀላይ ከመ ዕብን፣

ማዕበሉ ሞገዱም ቀበራቸው፣ ድንጊያ ሲጥሉት እንዲሠጥም በውሀ ውስጥ ሠጠሙ፤ አንድም አጋንንትን ማዕበለ ገሃነም ቀበራቸው፣ ደንጊያም እንዲሠጥም በባሕረ ገሃነም ሠጠሙ፤

፮፣ የማንከ እግዚኦ ተሰብሐ በኃይል የማነ እዴከ እግዚኦ ሠረወቶሙ ለፀር፣

አቤቱ የማንከ ሙሴ፣ አንድም ቅዱስ ሚካኤል፣ አንድም ሥልጣንህ ባደረገው ተመሰገነ፣ የማነ እዴከ እግዚኦ ሠረወቶሙ ለፀር፣ አቤቱ የሥልጣንህም ኃይል ግብጻውያንን አጠፋቻቸው፤ አንድም አቤቱ አብ ልጅህ፤ አንድም የልጅህ ሥልጣን፤ አንድም አቤቱ ወልድ፣ ሥልጣንህ ባደረገው ኃይል ተመሰገነ፣ አቤቱ አብ ልጅህ፣ አንድም የልጅህ ሥልጣን፤ አንድም አቤቱ ወልድ የሥልጣንህ ኃይል አጋንንትን አጠፋቻቸው፤

፯፣ ወበብዝኃ ስብሐቲከ ቀጥቀጥ ኮሙ ለጸላእትከ ፈኖከ መዓተከ ወበልዖሙ ከመ ብርዕ፣

አቤቱ በተአምራትህ ብዛት ግብጻውያንን አጠፋሃቸው፣ ቍጣህንም አብዝተህ አመጣህ፣ እንደ ቋያ እሳት አጠፋሃቸው፤ አንድም አቤቱ ወልድ በተአምራትህ ብዛት አጋንንትን አጠፋሃቸው፣ ቍጣህንም አብዝተህ አመጣህ፣ እንደ ቋያ አጠፋሃቸው፤

www.ethiopianorthodox.org

፰፡ ወበመንፈስ መዓትከ ቆመ ማይ ወጠግዐ ከመ ዓረፍት ማይ ወረግዐ ማዕበል በማዕከለ ባሕር፣

ቀኑ ጣህን በምትፈጽምበት በረቂቅ ሥልጣንህ፤ አንድም በነፋሱ፤ አንድም በቅዱስ ሚካኤል ውሀው ተከፍሎ ፀና፣ ውሀውም ተከፍሎ ግራና ቀኝ እንደ ግድግዳ ጸና፣ ማዕበል ሞገዱም በባሕሩ መካከል ረጋ፤ አንድም አቤቱ አብ ቀኑጣህን በምትፈጽምበት በረቂቅ ልጅህ፤ አንድም አቤቱ ወልድ ቀኑጣህን በምትፈጽምበት በረቂቅ ሥልጣንህ ባሕረ ገሀንም ተከፍሎ ጸና፣ ባሕረ ገሀነምም ተከፍሎ ግራና ቀኝ እንደ ግድግዳ ጸና፣ ማዕበለ ገሃነምም በባሕረ ገሃነም መካከል ረጋ፤

፱፡ ወይቤ ጸላዒ ዴግኖ እእኀዞሙ እትካፈል ምህርካ ወእጸግባ ለነፍስየ እቀትል በመጥባሕትየ ወእኴንን በእዴየ፣

ጸላዒ ፈርዖን እስራኤልን ተከትዬ እይዛቸዋለሁ፣ ምርኮውንም ከባለ ሚሎቼ ጋር እካፈላለሁ፣ ልቡናዬን ደስ አሰኛታለሁ፣ በሾተሌ እገድላለሁ በሥልጣኔም እገዛለሁ፤ አንድም ወንድ ወንዱን እገድላለሁ፣ ሴት ሴቱን እገዛለሁ፤ አንድም እምቢ ያለኝን እገድላለሁ፣ እሺ ያለኝን እገዛለሁ ብሎ ነበር፤ አንድም ጸላዒ ዲያብሎስ ምእመናንን ግብራቸውን ተከትዬ እቈራኛቸዋለሁ፤ የነፍሳትንም ምርኮ ከባለሚሎቼ ከአጋንንት ጋር እካፈላለሁ፣ ባህርዬን ደስ አሰኛታለሁ፣ በሥልጣኔ ነፍስን ከሥጋ እየለየሁ በሥልጣኔ ነፍስን በሲኦል ሥጋን በመቃብር ተቈራኝቼ እኖራለሁ እቈራኛለሁ ብሎ ነበር፤

፲፡ ፈኖከ መንፈስከ ወደፈኖሙ ባሕር ወተሠጥሙ ከመ አረር ውስተ ማይ ብዙኅ፣

አቤቱ ነፋሱን፤ አንድም ረቂቅ ሥልጣንህን፤ አንድም ቅዱስ ሚካኤልን አመጣህ፣ ባሕረ ኤርትራ ቀበራቸው፣ እሙቅ ስፉሕ ሲል ነው፣ እርሳስ በውሀ ውስጥ እንዲሠጥም እንደዚያ ሠጠሙ፤ አንድም አቤቱ አብ ረቂቅ ልጅህን ለልብስተ ሥጋ ወደዚህ ዓለም ልከኸ ሰደድክ፤ አንድም አቤቱ፣ ወልድ ሥልጣንህን በዚህ ዓለም ገለጥህ፣ ባሕረ ገሃነም ቀበራቸው፣ አጋንንትም እርሳስ በውሃ እንዲሠጥም እንደዚያ ጽኑ ፍዳ ባለበት በገሃነም ሠጠሙ፤



፲፩፡ መኑ ይመስለከ እምነ አማልክት እግዚእ ወመኑ ከማከ ስቡሕ በውስተ ቅዱሳን መንክር ስብሐቲከ ዘትገብር መድምመ፣

አቤቱ በስም አማልክት ከሚባሉ በስመ አማልክት ከሚጠሩ አንተን የሚመስልህ ማነው? በነቢያት በካህናትስ ሸንጐ እንዳንት የተመሰገነ ማነው? ዘትገብር መድምመ፣ ድንቅ ተአምራትን የምታደርግ አንተ ተአምራትህ ጌትነትህ መንክር ድንቅ ነው፤ አንድም ወዘትገበር ይላል፣ ከዚህ ቀድሞ ያደረግኸው ተአምራትህ እንግዲህም ወዲያ የምታደርገው ተአምራትህ መንክር ድንቅ ነው፤ አንድም አቤቱ ወልድ ከጸጋ ልጆችህስ ከካህናት አንተን የሚመስልህ ማነው? በመምህራንስ ሸንጎ እንዳንተ የተመሰገነ ማነው? አለ ለራሳቸው፤ አንድም በእነሱ ለሌላው መንክር ስብሐቲከ ሐተታ እንዳለፈው፤

፲፪፡ ሰፋሕከ የማንከ ወውሕጦሙ ምድር፣

አቤቱ ሥልጣንህን፤ አንድም ሙሴን፤ አንድም ቅዱስ ሚካኤልን አመጣህ፣ ኤርትራ ቀበረቻቸው፣ ምድር አላት ኤርትራን ስለ ጽናቷ፤ አንድም በዚያውም እንደ ዳታን እንደ አቤሮን ወርደዋልና፤ አንድም አቤቱ አብ ልጅህን ለልብስተ ሥጋ ወደዚህ ዓለም ሰደድህ፤ አንድም አቤቱ ወልድ ሥልጣንህን በዚህ ዓለም ገለጽክ፣ አጋንንትን ምድር ገሃነም ቀበረቻቸው፤

ወመራህኮሙ ለሕዝብከ ለእለ ቤዘውከ፣

በደመ በግዕ በደመና የተቤዠሃቸው ወገኖችህ እስራኤልን መርተህ ወደ ከነዓን ወሰድኻቸው፤ አንድም በደምህ በመንፈስ ቅዱስ የተቤዠሃቸው ምእመናንን መርተህ ወደ ገነት ወደ መንግሥተ ሰማያት ወሰድካቸው፤

፲፫፡ ወአስተፍሣሕከ በኃይልከ ተረፈ መቅደስከ፣

ባደረግህላቸውም ተአምራት የአብርሃም ልጆች የሚሆኑ እስራኤልን ደስ አሰኘሃቸው አለ፣ አብርሃምን መቅደሰ እግዚአብሔር ይለዋልና፤ አንድም በቤተ መቅደስ ተረፈ መሥዋዕቱን ሰጥተህ ነቢያት ካህናትን ደስ አሰኘሃቸው፤ አንድም ለአብርሃም ልጆች ለምእመናን ገነት መንግሥተ ሰማያትን አውርሰህ ደስ አሰኘሃቸው፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፬፤ ሰምዑ አሕዛብ ወተምዑ
ወአኃዞሙ ማሕምም ለእለ ይነብሩ
ፍልስጥኤም፤

አሕዛብም ይኸን ሰምተው
ተበሳጩ፤ በፍልስጥኤምም
የሚኖሩት ሰዎች ለመውለድ
የቀረበች ሴት በምጥ ተይዛ
እንድትጨነቅ፤ እንደዚያ የሚ
ያስጨንቅ መከራ ያዛቸው፤
አንድም አጋንንት ይህን
ሰምተው ተበሳጩ፤ አሕዛብ
አላቸው አጋንንትን በማደሪ
ያቸው በኢየሩሳሌም ሰማያዊት
ሊኖሩ የተፈጠሩ አጋንንትም
ለመውለድ የቀረበች ሴት
በምጥ ተይዛ እንድትጨነቅ
እንደዚያ በመከራ ገሃነም ተይ
ዘው ተጨነቁ ምጥ ያዛቸው፤

፲፭፤ ወውእተ አሚረ መምዑ
መሳፍንተ ኤዶም ወአኀዞሙ ረዓድ
ለመላእክተ ሞአብ ወተመስዉ
ኵሎሙ እለ ይነብሩ ከነዓን፤

ያንጊዜም የኤዶምያስ መሳፍ
ንት ተሸበሩ፤ የሞአብንም
አለቆች ረዓድ ያዛቸው፤ በከነ
ዓንም የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ
እንደ ሰም ቀለጡ፤ አንድም
ያንጊዜ በዕለተ ስቅለት የገሃነም
አለቆች አጋንንት ተሸበሩ፤
የገሃነምንም አለቆች አጋን
ንትን ረዓድ ያዛቸው፤ በኢየሩ
ሳሌም ሰማያዊት ሊኖሩ
የተፈጠሩ አጋንንትም ሁሉ
እንደ ሰም ቀለጡ፤

፲፮፤ ወአኀዞሙ ፍርሃት ወረዓድ
ኃይለ መዝራዕትከ ጸንዐ እምኰ
ኵሖ እስከ የኀልፉ ሕዝብከ እግዚኦ
እስከ የኃልፉ ሕዝብከ ዝንቱ
ዘቤዘውከ፤

አሕዛብን የከነዓንን አለቆች
ፍርሃት ረዓድ ያዛቸው አለ፤
ፍርሃት የልቡና፤ ረዓድ የጉል
በት ድንጋጤ የኖላ ነው፤
ዝንቱን እሉ ሲል ነው፤ እስከ
የኀልፉና እስከ የኀልፉ አንድ
ወገን፤ አቤቱ በደመ በግዕ
በደመና የተቤዠሃቸው ወገኖ
ችህ እስራኤል አልፈው እስኪ
ሔዱ ድረስ በኃይለ መዝራዕ
ትከ ሲል ነው፤ በሥልጣንህ
ኃይል ተከፍሎ ውሀው ከድን
ጋይ ይልቅ ጸና፤ አንድም
ወገኖችህ እስራኤል አልፈው
እስኪሔዱ ድረስ የሥልጣ
ንህ ኃይል ከድንጋይ ይልቅ
በፈርዖን ጸናበት፤ አንድም
ከድንጋይ ይልቅ፤ ጸንዐ በኰኵሕ፤
በፈርዖን ጸናበት፤ አንድም
አጋንንትን በዕለተ ዓርብ
ፍርሃት ረዓድ ያዛቸው፤ እሉ
ዘቤዘውከ ሲል ነው፤ እስከ
የኃልፉና እስከ የኃልፉ አንድ
ወገን፤ አቤቱ ወልድ በደምህ
የተቤዠሃቸው ወገኖችህ ምእ
መናን አልፈው እስኪሔዱ
ድረስ በኃይለ መዝራዕትከ
በሥልጣንህ ኃይል ተከፍሎ
ባሕረ ገሀነም ከድንጋይ ይልቅ



ጸና፤ አንድም ኃይለ መዝራዕ
ትከ ይላል፤ የሥልጣንህ ኃይል
ከድንጋይ ይልቅ በዲያብሎስ
ጸናበት፤ አንድም የሥልጣንህ
ኃይል ከድንጋይ ይልቅ ጸንዐ
በኰኵሕ በዲያብሎስ ጸናበት፤
ኰኵሕ ያለው ዲያብሎስን
ነው፤ በድንጋይ ላይ አዝርዕት
አትክልት እንዳይገኙ በእሱም
ምግባር ሃይማኖት አይገኝበ
ትምና ኰኵሕ አለው፤

፲፯፤ ወሰድኮሙ ወተከልኮሙ ውስተ
ደብረ መቅደስከ ውስተ ድልው
ማኅደርከ እግዚኦ ዘገበርከ፤

ከዚያም ወስደህ በአብርሃም
በይስሐቅ በያዕቆብ ርስት
በከነዓን አጽንተህ አኖርካቸው፤
ከዚያም ዘንድ በአትክልት
በአዝርዕት በአዘጋጀሃት በከነዓን፤
አንድም ለምስጋና ባዘጋጀሃት
በቤተ መቅደስ አጽንተህ አኖር
ካቸው፤ አንድም በጣዕም
በመዓዛ በስን በብርሃን ባዘጋጀ
ሃት በምስጋናህ ማደሪያ በገነት
በመንግሥተ ሰማያት አጽንተህ
አኖርካቸው፤

፲፰፤ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘአስተ
ዳለዋ እደዊከ ይነግሥ እግዚአ
ብሔር ለዓለመ ዓለም ወዓዲ፤

ንጹሕ ክቡር እግዚአብሔር
ይሆችውም ከነዓን ሥልጣንህ
በአዝርእት በአትክልት ያዘጋ
ጃት ናት፤ አንድም እንዳለም
ይሆናል፤ እጆችህ ያዘጋጁዋት
ናት አለ፤ ጌታ ለአብርሃም
ልጆችህ እስራኤል በአራት
መቶ ሠላሳ ዘመን ከዚህ
እስከዚህ ይወርሷታል ብሎ
የከነዓንን ምሥራቋን፤ ምዕራ
ቧን፤ ሰሜኗን፤ ደቡቧን
አሳይቶታልና እንዲህ አለ፤
እንዲህም አድርጎ አጥፊ
ለጥፋት የሚለው የለምና እግዚ
አብሔር ለዘለዓለሙ ነግሦ
ይኖራል፤ ወዓዲ እንግዲህም
ወዲያ፤ አንድም ወዓድ ይላል፤
ዘልፈ ሲል ነው፤ አንድም
ንጹሕ ክቡር እግዚአብሔር
ይህችውም ለምእመናን ያወረ
ሰካት ገነት መንግሥተ ሰማ
ያት ሥልጣንህ በጣዕም በመዓዛ
በስን በብርሃን ያዘጋጀቻት
ናት፤ አንድም ይህችውም
መንግሥተ ሰማያት ሥልጣንህ
የፈጠራት ናት፤ ምነዋ ስንኳን
የወዲያውን ዓለም የወዲሁን
ዓለም የፈጠረለት፤ ሌላን
አምላክ አለ? ቢሉ፤ በወዲሁ
ዓለም ሰውን ሰው ይገዛዋል፤
በወዲያው ዓለም ግን፤ ወአስከቦ
ለውእቱ ሰይፍ ዲበ ምስካቡ
እንዲል፤ ገዥና ተገዥ የለምና
እንዲህ አለ፤ ይነግሥ እግዚ
አብሔር ለዓለመ ዓለም ወዓዲ፤
ሐተታ እንዳለፈው፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፱፣ እስመ ቦአ ሠረገላቲሁ ለፈርዖን ምስለ አፍራሲሁ ወመስተፅዕናን ውስተ ባሕር ወአስተጋብአ እግዚአብሔር ላዕሌሆሙ ማየ ባሕር ወደቂቀ እስራኤልሰ ኃለፉ እንተ የብስ ማዕከለ ባሕር ማይሰ ሎሙ ዓረፍት በይምን ወዓረፍት በጽግም፣

የፈርዖን ሠረገላ ከፈረሶቹ ጋር በፈረስ በሠረገላ የተቀመጡት ሁሉ በባሕረ ኤርትራ ሠጥመዋልና እግዚአብሔር በግብጻውያን ውሀውን አጠራቀመባቸው፤ ኃለፉ ማንሻ፤ አንድም እግዚአብሔር በግብጻውያን ውሃውን አጠራቅሞባቸዋልና የእስራኤል ልጆች ግን ውሃው ተከፍሎላቸው በባሕሩ መካከል በየብስ አልፈው ሔዱ፤ ማይኒ ማንሻ፤ አንድም የእስራኤል ልጆች ውሀው ተከፍሎላቸው በባሕሩ መካከል በየብስ አልፈው፤ ሒደዋልና ውሃው በቀኝ በግራ እንደግድግዳ ተከፍሎ ጸናላቸው፤ አንድም እስራኤል ውሃው ተከፍሎላቸው በውሃው መካከል በየብስ አልፈው ሔዱ፣ ማይሰ፣ ውሀውሳ ትለኝ እንደሆነ ውሀውስ ግራና ቀኝ ተከፍሎ እንደ ግድግዳ ጸናላቸው፤ አንድም ሊቃነ አጋንንት ሠራዊተ አጋንንት በባሕረ ገሃነም ሠጥመዋልና እግዚአብሔር በአጋንንት ባሕረ ገሃነምን አጠራቀመባቸው፣ ኀለፉ ማንሻ፤ አንድም እግዚአብሔር በአጋንንት ባሕረ ገሃነምን አጠራቅሞባቸዋልና እስራኤል ዘነፍስ ባሕረ ገሃነም ተከፍሎላቸው አልፈው ሔዱ፣ ማይሰ ማንሻ፤ አንድም ማይኒ ሲል ነው፣ እስራኤል ዘነፍስ ባሕረ ገሃነም ተከፍሎላቸው አልፈው ሒደዋልና ባሕረ ገሃነምም ተከፍሎ ግራና ቀኝ እንደ ግድግዳ ጸናላቸው፤ አንድም እስራኤል ዘነፍስ ባሕረ ገሃነም ተከፍሎላቸው አልፈው ሔዱ፣ ማይሰ ባሕረ ገሃነምሳ ትለኝ እንደሆነ ባሕረ ገሃነምስ ግራና ቀኝ ተከፍሎ እንደ ግድግዳ ጸናላቸው፤

፳፣ ወነሥአት ማርያም ነቢዪት እኅቱ ለአሮን ከበሮ በእዴሃ ወወፅአ ኵሎን አንስት ድኅሬሃ በከበሮ ወበቡራኬ፣

ያንጊዜ የአሮን እኅት ሀብተ ትንቢት ያደረባት ማርያም እኅተ ሙሴ ከበሮውን በእጇ አንሥታ ሔደች፣ ሌሎች ሴቶችም ሁሉ ከምስጋና ጋር ከበሮውን ይዘው እሷን ተከትለው ሄዱ አለ፣ የኅዳና፤ አንድም የአሮን እኅት ማርያም ከበሮውን ይዛ በቃሏ አስቀድማ አመሰገነች አለ፣ አቀነቀነች፣ ሌሎችም ሴቶች ሁሉ ከእሷ በኋላ ከበሮውን ይዘው ምስጋናውን አመሰገኑ፤ አንድም የአሮን እኅት ማርያም ከበሮውን ይዛ በቃሏ አመሰገነች፣ ሌሎችም ሴቶች ሁሉ ከበሮውን ይዘው እንደ እሷ አመሰገኑ፤ አንድም የአሮን እኅት ማርያም ከበሮውን ይዛ በቃሏ አመሰገነች፣ ምስሌሃ፣ ሌሎችም ሴቶች ሁሉ ከበሮውን ይዘው ከእሷ ጋራ እንደ እሷ አመሰገኑ፤



የግል ቤተ መጻሕፍት

፳፩፣ ወቀደመት ማርያም ወትቤ ንባርኮ ለእግዚአብሔር ይትነከር ውእቱ ይትነከር ፈረሰ ወዘይጼዓን ላዕሌሁ ወረወ ውስተ ባሕር፣

ማርያም እኅተ ሙሴ ከሴቶች ቀድማ ሔደች፣ እግዚአብሔርን እናመሰግንዋለን፣ ፈረሱን፣ በፈረሱ ላይ የተቀመጠውን በባሕረ ኤርትራ አስጥሟልና እሱም ይደነቃል ይደነቃል አለች፤ አንድም ማርያም እኅተ ሙሴ ከሴቶቹ ሁሉ አስቀድማ አቀነቀነች፣ ንባርኮ፣ እግዚአብሔርን እናመስግነው፣ ፈረሱን፣ በፈረስ ላይም የተቀመጠውን በባሕረ ኤርትራ አስጥሟልና እሱም ይደነቅ ይደነቅ አለች፣ ይኸውም ምሳሌ ነው፣ ግብጽ የኃጢአት፣ ኤርትራ የጥምቀት፣ ሕዝቡ የምእመናን፣ ደመና የመንፈስ ቅዱስ፣ ሙሴ የወልደ እግዚአብሔር፣ ከግብጽ ከኤርትራም ከወጡ በኋላ መና ከደመና እየወረደላቸው ውሃ ከደንጊያ እየፈለቀላቸው ፵ ዘመን ሙሉ ሲመገቡ ኑረው ኋላ ምድረ ርስት ገብተዋል፣ ይኸም ምሳሌ ነው፣ መና የሥጋው የደሙ፣ ውሀ ከደንጊያ ማፍለቁ የማየ ገቦ፣ ምድረ ርስት የገነት የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ፣ እስራኤል ከግብጽ ከኤርትራ ከወጡ በኋላ ዕለቱን ምድረ ርስት አልገቡም፣ በምድረ በዳ ፵ዓ ዘመን ኑረው ኋላ ምድረ ርስት ገብተዋል፣ ዛሬም ምዕመናን /ጥሙቃን/ ተጠምቀው ዕለቱን ገነት መንግሥተ ሰማያት አይገቡም፣ በዚህ ዓለም ሥራ ሲሠሩ ኑረው ኋላ ገነት መንግሥተ ሰማያት ይገባሉ እንጂ፤ አንድም ግብጽ ኤርትራ አንድ ወገን የገሃነም፣ ደመና የልጅነት፣ ሙሴ የጌታ /የወልደ እግዚአብሔር/፣ ሕዝቡ የነፍሳት፣ መና ከደመና የወረደላቸው የሥጋው የደሙ፣ ውሀ ከደንጊያ የፈለቀላቸው የማየ ገቦ፣ ፵ው ዘመን የመዋዕለ ንስሐ፣ ከነዓን የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ነው፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፪፤ ወአውፅአሙ ሙሴ ለደቂቀ እስራኤል እምባሕር ዕሙቅ ወወሰዶሙ ውስተ ገዳም ዘሱር ወግዕዙ ሠሉሰ ዕለተ ገዳመ ወኢረከቡ ማየ ከመ ይስተዩ፤

ሙሴም የእስራኤልን ልጆች ከጥልቁ ባሕር አውጥቶ በሱር አጠገብ ወዳለ ምድረ በዳ ወሰዳቸው፤ በምድረ በዳውም ሦስት ቀን ተጓዙ፤ ዘይስትዩ ሲል ነው፤ የሚጠጡት የጣፈጠ ውሀ አላገኙም፤ አንድም እንዳለም ይሆናል፤ ሊጠጡት የጣፈጠ ውሀ አላገኙም፤ አንድም ወረከቡ ማየ ወኢሰትዩ ይላል፤ በምድረ በዳው ማግኘቱንስ ውሀውን አገኙ መሯቸው ጎም ዝሏቸው አልጠጡትም እንጂ፤

፳፫፤ ወስእኑ ሰትየ ማይ እምረራ /እመራ/ /በምረራ/ እስመ መሪር ማዩ ወበእንተዝ ተሰምየ ውእቱ ፍና መሪር፤

ውሀው መራራ ጐምዛዛ ነውና ከመምረሯ ከመጐምዘዟ የተነሣ፤ አንድም በምረራ ይላል፤ በመምረሯ በመጐምዘዟ እስራኤል ውሀውን መጠጣት ተሳናቸው፤ ስለዚህም ነገር ያ ቦታ መራራ ውሀ የተገኘበት ቦታ ተባለ፤

፳፬፤ ወአንጐርጐሩ ሕዝብ ላዕለ ሙሴ ወይቤሉ ምንተ ንሰቲ፤

ሕዝቡም እንዲህ ቢሆንባቸው በሙሴ ላይ አንጐራጐሩ፤ ምን እንጠጣለን፤ አንድም ምንተ ንስተይ ምን እንጠጣ አሉ፤

፳፭ ፤ ወአውየወ ሙሴ ኀበ ፈጣሪ ወአርአዮ እግዚአብሔር ዕፀ ወወደዮ ውስተ ማይ ወጥዕመ ማዩ ወበህየ አርአዮ ጽድቀ ወፍትሐ ወአመከሮ፤

ሙሴም ይህን ሰምቶ ያንጊዜ ወደ ፈጣሪው ወደ እግዚአብሔር ጮኸ ለመነ፤ ፈጣሪው እግዚአብሔርም ዞጲ የሚባል መራራ ዕንጨት አሳየው ወዲያውም ቈርጠህ ጣልበት አለው፤ ዞጲውን ዕንጨት ቈርጦ ከውሀው ጣለበት፤ ውሀውም ጣፈጠ፤ ጽድቀ ወፍትሐ አንድ ወገን፤ በዚያም ቦታ እውነት ፍርድን ገለጠለት፤ አንድም ጽድቀ ኢታምልክን፤ ወፍትሐ ዘጠኙን ሕግጋት ገለጠለት፤ በዚያም ሁሉ ተፈታተነው፤ ይኸውም ምሳሌ ነው፤ መሬት የአዳም፤ የውሀው ምረት የፍዳ የመርገም፤ ሙሴ የጌታ፤ ሕዝቡ የምእመናን፤ ዕፅ የመስቀል ምሳሌ ነው፤ መራራው ውሃ በመራራው ዞጲ ዕንጨት እንደ ጣፈጠ፤ በዕፀ በለስ የመጣ ፍዳ መርገምም በዕፀ መስቀል የመጥፋቱ ምሳሌ ነው፤



፳፮፤ ወይቤ ለእመ ትሰምዕ ወታጸምዕ ቃለ እግዚአብሔር ፈጣሪከ ወጽድቀ ትገብር በቅድሜሁ ወታጸምዕ ትእዛዞ ዘአዘዘከ ኵሎ ደዌ ዘአምጻእኩ ላዕለ ግብጽ ኢይፌኑ ላዕሌከ አነ እግዚአብሔር ፈዋሲከ፤

ሙሴም የፈጣሪህ የእግዚአብሔርን ቃል ፈጽመህ ብትሰማ፤ እሱ ባወቀው በእሱ ፈቃድ በጎ ሥራ ብትሠራ፤ ያዘዘኽንም ትእዛዝ ሰምተህ ብታደርገው፤ ፈዋሲከም ይላል፤ ድኅነትህን የማደርግልህ እኔ እግዚአብሔር በግብጽ ያመጣሁትን ሁሉ መከራ በአንተ አላመጣብህም አለ እግዚአብሔር ይላል ሙሴ፤ አንድም እስመ አነ እግዚአብሔር ፈውስከ ይላል፤ ድኅነትህን የማደርግልህ እኔ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ነኝና በግብጽ ያመጣሁትን መከራ ሁሉ በአንተ አላመጣብህም አለ እግዚአብሔር ይላል ሙሴ፤ አንድም ጌታ የእኔን የፈጣሪህን ቃል ፈጽመህ ብትሰማ በቅድሜየ ሲል ነው፤ በእኔ ፈቃድ፤ በእኔ ትእዛዝ በጐ ሥራ ብትሠራ፤ ዘአዘዝኩከ ሲል ነው፤ ያዘዝኩህንም ትእዛዝ ሰምተህ ብታደርገው ድኅነትህን የማደርግልህ እኔ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ነኝ፤ አንድም እስመ አነ ይላል ድኅነትህን የማደርግልህ እኔ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ነኝና በግብጽ ሰዎች ያመጣሁትን መከራ ሁሉ በአንተ አላመጣብህም አለ፤ አንድም ወአነ ይላል፤ በግብጽ ያመጣሁትን መከራ ሁሉ በአንተ አላመጣብህም፤ እኔ ፈጣሪህ እግዚአብሔርስ ለአንተ ድኅነትን አደርግልሃለሁ አለው፤ ፈዋሲከ ባለው መሐኪከ የሚል አብነት ይገኛል፤ እንደዚሁ ያስተረጕማል፤

፳፯፤ ወበጽሑ ኀበ ኤሌም ወሀለዉ ህየ ፲ወ፪ አንቅዕተ ማያት ወ፸ ፀበርተ ተመርት ጥቃ ማያት ብቅለቶን፤

እስራኤልም ሲጓዙ ውለው ኤሌም ከምትባል አገር ደረሱ፤ በዚያ ቦታ ዓሥራ ሁለት ምንጮች አሉ፤ አበቃቀላቸው በውሀ ዳር የሚሆን፤ አንድም በቀልቶን ይላል፤ ዘንባባነታቸው በውሀ ዳር የሚሆን ሰባ ዘንባቦች አሉበት፤ በቀልት ግንዱ፤ ፀበርት ቅጠሉ፤ ተመርት ፍሬው ነው፤ ይኸውም ምሳሌ ነው፤ አሥራ ሁለቱ ምንጮች የዓሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል፤ ሰባው ዘንባቦች የሰባ ሊቃናት፤ ውሀው የረድኤተ እግዚአብሔር ነው፤ አንድም አሥራሁለቱ ምንጮች የዓሥራ

www.ethiopianorthodox.org

ሁለቱ ሐዋርያት፣ ሰባው ዘንባቦች የሰባ ሁለቱ አርድዕት፣ ሁለቱን ከወደቱ ያመጣቸዋል ቢሉ ለመጽሐፍ ጅምር፣ ጭርስ አድርጎ መናገር ልማዱ ነውና፣ ከዚያ ሁሉ ሰሎሞን ጅምር፣ ጭርስ አድርጎ ውነደርኩ ውስተ ከርሠ እምየ ፲ተ አውራኃ ርጉዐ በደም ወተገለፍኩ ሥጋ ከመ ኵሉ ሰብእ እንዳለ፤

ወተዐየኑ ህየ በኀበ ማይ፣

ከዚያም በውሃው አጠገብ ሠፈሩ።

## ምዕራፍ ፲ወ፮

### ገባኤ

፩፣ ወግዕዙ እምኤሎም ወበጽሑ ውስተ ገዳም ዘሲን ወውእቱ ማዕከለ ኤሎም ወሲና አመ አሡሩ ወኃሙሱ ለካልእ ወርኀ እምዘ ወፅኡ እምድረ ግብጽ፣

ከዚህ በኋላ እስራኤል ከኤሎም ተጉዘው ሒደው በሲን አጠገብ ወዳለ ምድረ በዳ ደረሱ፣ ይኸውም ምድረ በዳው በሲናና በኤሎም መካከል ነው፣ ይኸሳ የተደረገ በምን ቀን ነው፤ ትለኝ እንደሁ እስራኤል ከግብጽ አገር ከወጡ በኋላ በሁለተኛ ወር በግንቦት በአሥራ አምስተኛው ቀን ነው፤

፪፣ ወአንጐርጐሩ ኵሉ ሕዝብ ውሉደ እስራኤል በላዕለ ሙሴ ወአሮን፣

ያንጊዜ የእስራኤል ልጆች ሁሉ በሙሴና በአሮን አንጐራጐሩባቸው /ተበሳጩባቸው/

፫፣ ወይቤልዎሙ እምነየሰነ ሶበ ሞትነ በመቅሠፍተ እግዚአብሔር በምድረ ግብጽ አመ ንነብር ጥቃ ጽሕርት ዘሥጋ ወንበልዕ ሥጋ ወኅብስተ አስከ ንጸግብ፣ አምጻእከነ አንተ ውስተዝ ገዳም ከመ ትቅትለነ ለኵልነ በነበ ተጋባዕነ፤

አንተ በተሰበሰብንበት ቦታ ሁላችንን ልታጠፋን ወደዚህ ወደምድረ በዳው አመጣኸን እኮን፣ እኛ ግን እስክንጠግብ ድረስ ዳቦውን፣ ሥጋውን በምንበላበት ሥጋው በሚቀቀልበት በድስቱም አጠገብ በምንቀመጥበት ጊዜ በግብጽ አገር ሳለን እግዚአብሔር በግብጽ ሰዎች ባመጣው መቅሠፍት ብንሞት በተሻለን ነበር፤ አንድም በምድረ ግብጽ አመ ንበልዕ ይላል፣ (በምድረ ግብጽ) በግብጽ አገር ሳለን እስክንጠግብ ድረስ ዳቦውን ሥጋውን በምንበላበት ጊዜ፣ ሥጋው በሚቀቀልበት በድስቱም አጠገብ በምንቀመጥበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር በግብጻውያን ባመጣው መቅሠፍት ብንሞት በተሻለን ነበር፣ አንተስ፣ አንተ



ግን በተሰበሰብንበት ቦታ ሁላችንን ልታጠፋን ወደዚህ ወደ ምድረ በዳው አመጣኸን አሏቸው፣ ያንጊዜ ሙሴ ወደ እግዚአብሔር አመለከተ፤

፬፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ናሁ አነ አወርድ ለክሙ ኅብስተ እምሰማይ ወይፃኡ ሕዝብ ወያስተጋብኡ ለለዕለቱ ከመ አመክሮሙ ለእመ የሐውሩ በትእዛዝየ ወእመ አልቦ፣

እግዚአብሔርም ሙሴን እነሆ እኔ ነገ መናውን ከሰማይ አወርድላችኋለሁ፣ ሕዝቡም በትእዛዜ ጸንተው ይኖሩ እንደሆነ፣ አይኖሩም እንደሆነ ልፈትናቸው፣ (እንድፈትናቸው) የዕለት የዕለት ምግባቸውን ወጥተው ይሰብስቡ፤ አንድም ይፃኡ ወያስተጋብኡ ወከመ አመክሮሙ ይላል፣ እግዚአብሔርም ሙሴን እነሆ እኔ ነገ መናውን ከሰማይ አወርድላችኋለሁ፣ ሕዝቡም የዕለት የዕለት ምግባቸውን ሊሰበስቡ ይውጡ፣ እኔም ይኸንን ያደረግ ሁላቸው ሕዝቡ በሕጌ በሥርዓቴ ፀንተው ይኖሩ እንደሆነ፣ አይኖሩም እንደሆነ እፈትናቸው ዘንድ ነው አለው፤

፭፣ ወአመ ዕለተ ዓርብ ያስተዳልዉ ዘአብኡ ይኩኖሙ ካዕበተ ዕለት ወዘአስተጋብኡ ዘልፈ ለለዕለቱ፣

ካዕበተ ለለዕለት ሲል ነው፣ ዓርብ ቀን የሰበሰቡት መናው ለሁለት ቀን ይሆናቸው ዘንድ ለዓርብና ለቀዳሚት የሚሆናቸውን ዓርብ ቀን ያዘጋጁ፤ አንድም ዘአብኡ ይኩኖሙ ለለዕለት ያስተዳልዉ ካዕበተ ይላል፣ የሰበሰቡት መናው ለሁለቱ ቀን ለዓርብና ለቅዳሚ ይሆናቸው ዘንድ ዓርብ ቀን ሁለት ጎሞር ያዘጋጁ፣ በቀረው ቀን ግን የዕለት የዕለት ምግባቸውን አንድ አንድ ጎሞር መስፈሪያ ይሰብስቡ አለው፤

፮፣ ወይቤሉ ሙሴ ወአሮን ለኵሉ ሕዝበ እስራኤል በሠርክ /እምሠርክ/ ተአምሩ ከመ እግዚአብሔር አውፅአክሙ እምድረ ግብፅ፣

ሙሴ አሮንም ሒደው ለሕዝቡ ሁሉ እግዚአብሔር ከግብጽ አገር እንዳወጣችሁ ከሠርኩ ጀምሮ፤ አንድም በሠርክ ታውቃላችሁ፤

፯፣ ወበነግህ ትሬእዩ ኀይለ እግዚአብሔር በሠርክ ይሁበክሙ ሥጋ ትብልዑ ወበነግህ ኅብስተ እስከ ትጸግቡ እስመ ሰምዐ እግዚአብሐር /ሰሚዖ እግዚእ ነጐር

www.ethiopianorthodox.org

ኀረክሙ ነጐርጓረ ዘታንጐረጕሩ አንትሙ በላዕሌነ፤

እስከ ነግህም ይላል፣ ሲነጋ፤ አንድም ከሠርኩ፤ ጀምሮ እስኪነጋ ድረስ የእግዚአብሔርን ተአምራት ታያላችሁ፣ በሠርክ ተአምሩ ብሎ አንድ አርእስት፣ ወበነግህ ትሬእዩ ብሎ ሁለት አርእስት ተናግሯል፣ ለሁለቱም ያመጣል እናንት በእኛ የምታንጐራጒሩትን ማንጐራጐር ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ሰምቶ፤ አንድም ሰምቶአልና፤ አንድም ስለ ሰማ፣ ሥጋ ዘትበልዑ ሲል ነው፣ የምትበሉትን ሥጋ ውን፣ አንድም ልትበሉት ሥጋ ውን በሠርክ ይሰጣችኋል አለ፣ በሠርክ ተአምሩ ላለው፤ አንድም እናንት በእኛ የምታንጐራጕሩትን ማንጐራጐር ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ሰምቶ፤ አንድም ሰምቶአልና፤ አንድም ስለሰማ እስክትጠግቡ ድረስ መናውን በነግህ ይሰጣችኋል አለ፣ ወበነግህ ትሬእዩ ላለው፣

፰፣ ወንሕነ ምንት ንሕነ ወዝ ነጐርጓርክሙ አኮ በላዕሌነ ዘታንጐረጕሩ አላ በላዕለ ፈጣሪ፣

በእኛ የምታንጐራጕሩብን እኛ ምንድን ነን? ይህ በእኛስ የምታንጐራጕሩት ማንጐራጐር ምንድር ነው? አሏቸው፣ አኮ በላዕሌነ ማንጐ፤ አንድም የእኛስ የእኛ ነው፣ በእኛማ ብታንጐራጕሩ ምን ትጐዱበታላችሁ የገዛ ወንድሞቻችሁ አይደለንም? አንድም እንደ እናንተ ፍጡራን አይደለንም? ይህስ የምታንጐራጐሩት ማንጐራጐር በእኛ አይደለም፣ በፈጣሪያችሁ ነው እንጂ፤ አንድም በእኛ ብቻ አይደለም በፈጣሪያችሁም ነው እንጂ አሏቸው፤

፱፣ ወይቤሎ ሙሴ ለአሮን በል ለኵሉ ኀበ ተጋብኡ ውሉደ እስራኤል ቅረቡ ቅድመ ፈጣሪ እስመ ሰምዐ ነጐርጓረክሙ፣

ያን ጊዜ ሙሴ ወንድሙ አሮንን ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ያን ጐራጐራችሁትን ማንጐራጐር ሰምቷልና የእስራኤል ልጆች በተሰበሰቡበት ቦታ ሒደህ ለእስራኤል ሁሉ ወደ ፈጣሪያችሁ ቅረቡ በላቸው፤ አንድም ኀበ ተጋብኡ ኵሉ ውሉደ እስራኤል ይላል፣ ያን ጊዜ ሙሴ ወንድሙ አሮንን የእስራኤል ልጆች ሁሉ በተሰበሰቡበት ቦታ ሒደህ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ክፉ ማንጐራጐራችሁን ስለ ሰማባችሁ ወደ ፈጣሪያችሁ ቅረቡ ብለህ ንገራቸው አለው፤



፲፣ ወሶበ ተናገሮሙ አሮን ለኵሉ ኀበ ተጋብኡ ውሉደ እስራኤል ወተመይጡ ውስተ ገዳም ወሱራኄ እግዚአብሔር ተርእየ በደመና፣

የእስራኤል ልጆች በተሰበሰቡበት ቦታ ሒዶ አሮን ለሁሉ በነገራቸው ጊዜ እነሱም በአሉበት ቦታ ሁነው ፊታቸውን መልሰው ወደ ምድረ በዳው በአዩ ጊዜ፤ አንድም ኀበ ተጋብኡ ኵሉ ውሉደ እስራኤል ይላል፣ የእስራኤል ልጆች ሁሉ በተሰበሰቡበት ቦታ አሮን ሒዶ ይህንን በነገራቸው ጊዜ፣ እስራኤልም ከአሉበት ቦታ ተገዝተው ወደ ምድረ በዳው በተመለሱ ጊዜ፣ የእግዚአብሔር ብርሃን በደመና ታየ /ተገለጸ/፤

፲፩-፲፪፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ሰማዕኩ ቃለ ነጐርጓሮሙ ለውሉደ እስራኤል ወበሎሙ በሠርክ ትበልዑ ሥጋ፣ ወጸቢሐ ትፀግቡ ኅብስተ ወተአምሩ ከመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር ፈጣሬ ዚአክሙ፣

እግዚአብሔርም ሙሴን የእስራኤል ልጆች ክፉ ማንጐራጐራቸውን ሰማሁ፣ ይቤ ያለበት ነው፣ በሠርክ ሥጋውን ትበላላችሁ፣ ሲነጋ መናውን ትጠግባላችሁ፣ እኔንም ያንጊዜ ፍጠረን ሳትሉኝ የፈጠርኳችሁ ፈጣሪያችሁ እንደ ሆንኩ ታውቃላችሁ በላቸው አለው፤

፲፫፣ ወመስየ ወመጽአ ፍርፍርት ወከደነ ኵሎ ትዕይንቶሙ ወበነግህ እንዘ የኀድግ ህቦ በከርጓኔ ትዕይንቶሙ፣

ከመሸም በኋላ ድርጭት፣ ዓሣ፣ የባሕር ዶሮ፣ ሲያርዱት ስብ፣ ሲያዩት ከሻዋ፣ እንዲያገዘ ሁኖ ለእጃቸው ቀርቦ ወርዶላቸዋል /ወረደላቸው/፤ አንድም የተወራረደ ሥጋ ታላቅ ታናሽ በከተማቸው ዳር በዝቶ ወረደ፣ ሲነጋ /በነግህ/ ውርጭ ሲጥል፤ አንድም የውርጭ ገበታ እየተነጠፈ በኰርጓኔ ትዕይንቶሙ በከተማቸው ዙሪያ፤ አንድም እምጽንፈ ትዕይንቶሙ ሲል ነው፤

፲፬፣ እምፍጽመ ገዳም ድቁቅ ከመ ተቅዳ ወፀዓዳ ከመ አስሐትያ ዲበ ምድር፣

ከከተማቸው ዳር ጀምሮ አካሉ ድንብላል ድንብላል የሚያህል፣ መልኩ እንደ ውርጭ የሚነጣ መና ወረደላቸው፤

፲፭፣ ወርእዩ ደቂቀ እስራኤል ወይቤ ብእሲ ለካልኡ ምንት ውእቱ ዝ እስመ ኢያእመሩ ወይቤሎሙ ሙሴ ዝውእቱ ኅብስት ዘወሀበክሙ እግዚአብሔር ከመ ትብልዑ፣

የእስራኤልም ልጆች ይህንን ከዚያ ቀድሞ አይተውት አያውቁም ነበርና አንዱን አንዱ ይህ ምንድነው? አለው፣ ሙሴም ልትበሉት እግዚአብሔር የሰጣችሁ መናው ይህ ነው አላቸው፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፮፣ ዝውእቱ ቃል ዘይቤ እግዚአብሔር ከመ ትግበሩ አስተጋብኡ እምኔሁ በበንዋይክሙ ለለብእሲ በበጎሞሮ ሰብኡ ለለርእሱ በንዋዩ ለያስተጋብእ፣

ለታደርጉት /ለትሠሩት/ እግዚአብሔር አድርጉት /ሥሩት/ ብሎ የተናገረው ቃል ይህ ነው፣ ተነግሮ የማይሠራ፣ ሳይደረግ ሳይሠራ የሚቀር ቃል አለና፣ ከመ ትግበሩ አለ፣ ከዚህም ከመናው በየዕቃችሁ ሰብስቡ፣ እያንዳንዱ በቤተሰቡ በየሰዉ ቍጥር እየራስ እየራሱ በዕቃው ይሰብስብ፣ ብሎ የተናገረው ቃል ይህ ነው አላቸው፤

፲፯፣ ወገብሩ ከማሁ ውሉደ እስራኤል ወአስተጋብኡ ዘብዙኅኒ ወዘኅዳጥኒ፣

የእስራኤልም ልጆች ጌታ እንዳዘዛቸው፣ ሙሴ እንደ ነገራቸው አደረጉ፤ አንድም እግዚአብሔር አዞት ሙሴ እንደ ነገራቸው አደረጉ፤ ገብሩ ያለውን አመጣ፣ አብዝተውም አሳንሰውም ሰበሰቡ፣ እንደልባ ምኞታቸው እንደ ስንፍናቸው፣ ይህስ አይደለም፣ የጎሞሩን ልክ ከታች ተናግሮታልና ብሎ አብዝተው የሰበሰቡ የጎሞሩን ልክ ሳያውቁ ይጐድልብናል ብለው፣ አሳንሰው የሰበሰቡ የጎሞሩን /የቁናውን/ ልክ አውቀው ይተርፍብናል ብለው፤ አንድም አብዝተው የሰበሰቡ ዘወሀበክሙ ትብልዑ ብሎናል፣ ቢተርፍም ውሰዱት ይለናል ብለው፣ አሳንሰው የሰበሰቡ ቢያንስም ቢጐድልም ምንጊዜም ለእኛ ነው ብለው፤

፲፰፣ ወሰፈሩ በጎሞር ወኢፈድፈዶ ለዘብዙኃ አስተጋብአ ወኢሐፀ ለዘኅዳጠ አስተጋብአ ብእሲ ብእሲ ለለማኅደሩ አስተጋብአ፣

ምንም ቢሆን ወስደው በጎሞሩ ሰፈሩት፣ ይተርፍልኛል ብሎ ብዙ ለሰበሰበው ሰው ከጎሞሩ አልተረፈለትም፤ ቢያንስም ይነስ፣ ቢጐድልም ይጉደል ብሎ አሳንሶ /ጥቂት/ ለሰበሰበው ሰው ከጎሞሩ አላነሰበትም፣ ይኸነንም አንዱም አንዱም ሰው በየቤቱ ሰበሰበ፣

፲፱፣ ወይቤሎሙ ሙሴ ለደቂቀ እስራኤል ኢታትርፉ ለጌሠም፣

ሙሴም የእስራኤልን ልጆች ለነገ ይሆነናል ብላችሁ አትርፋችሁ አታሳድሩ አላቸው፤

፳፣ ወዓበዩ ወኢሰምዕዎ ለሙሴ ወአቤቱ ለነግህ ወሀፀየ ወዔአ ወተምዐ ሙሴ ላዕሌሆሙ፣

እስራኤልም የሙሴን ቃል አንሰማም እንቢ ብለው፤ አንድም እምቢ አንሰማም ብለው ለነገ ይሆነናል ብለው አትርፈው አሳደሩ፣ መናውም ተላ፣ ሸተተ ሙሴም ይህን ሰምቶ ተቈጣባቸው፤

፳፩፣ ወአስተጋብኡ በበነግህ ለለርእሱ ወእምከመ ሞቀ ፀሐይ ይምሑ፣

እስራኤልም ማለዳ ማለዳ ወጥተው አንዱም አንዱም ለየራሱ መናውን ይሰበስቡ ነበር፣ መናውም ፀሐይ ከወጣበት ቦታ ቀልጦ ይጠፋባቸው ነበር፤

፳፪፣ ወበዕለተ ዓርብ ያስተጋብኡ ካዕበተ ጎሞር ለለአሐዱ አሐዱ ወቦኡ ኵሉ መኳንንተ ማኅበር ወይቤልዎ ለሙሴ ምንተ ንግበር፣

ዓርብ ቀን እያንዳንዱ ጎሞር ሁለት፤ አንድም ለእያንዳንዱ ሰው ሁለት ጎሞር ይሰበስቡ ነበር፤ አንድም ሁለት ሁለት ጎሞር ለእያንዳንዱ ሰው ይሰበስቡ ነበር፣ ወአቤቱ ለነግህ ወአጸየ ወዔአ ብሎ ነበርና ለነገ ይሆነናል ብለው አትርፈው ያሳደሩት መና ቢተላባቸው ቢሸትባቸው የእስራኤል አለቆች ሁሉ ተሰብስበው ሙሴ ወዳለበት ገብተው ንገረኝ ያለበት ነው፣ ምን እናድርግ? አንድም ምንት ዘንገብር የምናደርገው ምንድ ነው? ንገረን አሉት፤



፳፫፣ ወይቤሎሙ ሙሴ ዝውእቱ ዘእቤለክሙ ሰንበት ዕረፍት ወቡርክት ለእግዚአብሔር ጌሠመ ዘትገብሩ ሀለወክሙ ግበሩ ወዘታበስሉ ሀለወክሙ አብስሉ ወዘተርፈ አትርፉ፣

ሙሴም ንግረኒ ዘንገብር ቢሉት ቅዳሜ ቀን ለሰው ዕረፍት ናት፣ ለእግዚአብሔርም የከበ ረች በዓል ናት ብዬ ቀድሞ የነገርኳችሁ ቃል ይህ ነው፣ ነገ የምታደርጉትን ሥራ ዛሬ አድርጉት፣ ነገም የምታበስ ሉትን ዛሬ አብስሉት የተረፈ ውን አሳድሩት አላቸው፤

፳፬፣ ወአትረፉ ለነግህ በከመ አዘዞሙ ሙሴ ወኢሤዐ ወዕፄሂ ኢተረክበ ወኢተፈጥረ በላዕሌሁ፣

ሕዝቡም ሙሴ እንደ አዘዛቸው የተረፈውን ለነገ አሳደሩ፣ እንደ ቀድሞው አልሸተተባቸውም ትልም በእሱ አልተገኘም፣

፳፭፣ ወይቤሎሙ ሙሴ ብልዑ ዮም እስመ ዮም ሰንበት ዘእግዚአብሔር ኢትትረከቡ በገዳም፣

ሙሴም እስራኤልን ዛሬ ቀዳሚት የእግዚአብሔር የከበረች በዓሉ ናትና፣ ዛሬ መናውን ብሉ፣ ቅዳሚ ቀን ግን መናውን ለመልቀም በምድረ በዳ አትገኙ አላቸው፤ አንድም ቀዳሚት ቀን የእግዚአብሔር የከበረች በዓሉ ናትና መናውን ዛሬ ብሉ

www.ethiopianorthodox.org

እንጀ. መናውን ለመልቀም ቅዳሜ ቀን በምድረ በዳ አትገኙ አላቸው፤

፳፮፣ ሰዱሰ ዕለተ ታስተጋብኡ ወአመ ሳብዕት ዕለት ሰንበት ኢት ትረከቡ በገዳም፣

ስድስቱን ቀን ምግባችሁን ዕለት ዕለት ሰብስቡ፣ በሰባተኛዪቱ ቀን ግን የከበረች በዓል ናት፣ መናውን ለመልቀም በምድረ በዳ አትገኙ፤ አንድም የከበ ረች በዐል ናትና መናውን ለመ ልቀም በምድረ በዳ አትገኙ፤

፳፯ ፣ ወአመ ሳብዕት ዕለት ቦ ዘወፅአ እምሕዝብ ከመ ያስተጋብዕ ወኢረከበ፣

በሰባተኛዪቱ ቀን ቅዳሜ አዋጁን ጥሶ አፍርሶ ከሕዝቡ ወገን አንድ ሆዳም ስሱ ሰው መናውን ሊለቅም ወደ ምድረ በዳው ወጣ፣ አላገኘም፤ አንድም አላገኘም እንጀ. ሊለቅም ወጣ፤

፳፰፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ እስከ ማዕዜኑ ተዐብዩ ሰሚዐ ትእዛዝየ ወሕግየ፣

እግዚአብሔርም ሙሴን ጠርቶ ሕጌን ሥርዓቴን አንሰማ ብላ ችሁ እምቢ የምትሉት እስከ መች ድረስ ነው? አንድም እስከ ምንትኑ፣ ሕጌን ሥርዓቴን አለመስማታችሁ ምን እስከት ሆኑ ድረስ ነው? አለው፤

፳፱፣ ወርእዩ ከመ እግዚአብሔር ወሀበክሙ ዛ ዕለተ ሰንበት በእንተዝ ወሀበክሙ በዕለተ ዐርብ ምሳሐ ለ፪ቱ ዕለት ወይንበር ብእሲ ብእሲ ለለማኀደሩ ወኢይፃእ እምንባሪሁ አመ ዕለተ ሰንበት፣

ይህ ከመ በባለቤት የገባ ነው፣ በዚያው አያይዞ እንዲህ አለ፣ እግዚአብሔርነቴ ቸርነቴ ዕረፉባት ጸልዩባት ብሎ የሰጣ ችሁ ይህችን ቅዳሜ ቀን እዩ ተመልከቱ፤ አንድም እንዲለም ይሆናል፣ እግዚአብሔርነቴ ቸርነቴ ይህችን ቅዳሜ ቀን ዕረፉባት ጸልዩባት ብሎ አክብሮ እንደሰጣችሁ እዩ ተመልከቱ፣ ዕረፉባት ጸልዩባት ብሎ ስላለ ስለዚህ ነገር ዓርብ ቀን ለሁለት ቀን የሚሆን ምግባችሁን ሰጣችሁ፣ አሁንም አንዱም አንዱም ሰው ቅዳሜ ቀን ከቦታው አይውጣ፣ በየቤቱ ይቀመጥ፤ አንድም አንዱ ሰው ቅዳሜ ቀን በየቤቱ ይቀመጥ ከቦታው አይውጣ፤ አንድም ጌታ እስከ ማዕዜኑ ቢለው ሙሴ ሕዝቡን እግዚአ ብሔር ዕረፉባት ጸልዩባት ብሎ አክብሮ የሰጣችሁ ቅዳሜን ቀን እዩ ተመልከቱ፤ አንድም እግ ዚአብሔር ቅዳሜን ቀን ዕረፉ ባት ጸልዩባት ብሎ አክብሮ እንደሰጣችሁ እዩ ተመልከቱ አለ፣ አክብሯት ሲል ነው፣



ዕረፉባት ጸልዩባት ብሎ ስላላችሁ ስለዚህም ነገር ዓርብ ቀን ለሁለት ቀን የሚሆን ምግባችሁን ሰጣችሁ ወይንበር ብእሲ ሐተታ እንዳለፈው፤

፴፣ ወአሰንበተ ሕዝብ በዕለተ ሰንበት፣

ሕዝቡም ይህን ሰምቶ ቅዳሜን ቀን አከበረ፤

፴፩፣ ወሰመይዎ ውሉደ እስራኤል መና ወውእቱ ድቁቅ ከመ ፍሬ ተቅዳ ወፀዓዳ ከመ አስሐትያ ወጣዕሙ ከመ አያየተ መዓር፣

የእስራኤልም ልጆች መናውን አይተው ምንት ውእቱ አሉት፣ ይህ ነገር ምንድን ነው? ሲሉ፤ አንድም ምንም ያይታጠበት መፍቅድ አሉት፤ አንድም ምንም ምን መፍቅድ የማይ ታጣበት አሉት፣ እነሱ እንዲህ አሉት እንጀ. መናውስ አካሉ ድንብላል ያኽላል፣ መልኩም እንደ ውርጭ ነው፣ ጣዕሙም እንደ ማር ወለላ ነው፤

፴፪፣ ወይቤ ሙሴ ዝ ውእቱ ቃል ዘአዘዘ እግዚአብሔር ከመ ትምልዑ ጎሞረ መና ውስተ መዛይምቲ ክሙ ከመ ይትዐቀብ ለትውልድ ክሙ ከመ ይርአዩ ኅብስተ ዘአብላዕኩ ክሙ አመ አውፃእኩክሙ እምድረ ግብጽ፣

ሙሴም ከግብጽ አገር ባወጣኋ ችሁ ጊዜ ያበላኋችሁን መናውን የኋላ ልጆች እንዲያዩ ለልጆ ቻችሁ ይጠበቅላቸው ዘንድ በየዕቃችሁ ጎሞር ምሉ፣ መና መልታችሁ ልታኖሩ እግዚአ ብሔር ያዘዘው ቃል ይህ ነው አለ፤

፴፫፣ ወይቤሎ ሙሴ ለአሮን ንሣእ ቈጽለ ወርቅ ረቃቀ ወግሉ ባቲ መሶበ ወአንብር ውስቴታ መና ምሉዓ ጎሞር ወአንብሮ ቅድመ እግዚአብሔር ለደኃሪ መዋዕል ለደቂቅክሙ፣

ይልቁንም ሙሴ ወንድሙ አሮንን ጠርቶ ወርቁን እንደ ቅጠል አሳስተህ መሶቡን ውስጡን አፍአውን በወርቅ ለብጠው፣ በውስጧም ዘመን ሳትወስን ጎሞር ሙሉ መና አኑርባት፤

፴፬፣ ከመ ይርአዩ ኅብስተ ዘበላዕክሙ አንትሙ በገዳም እስመ ከመዝ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ዘእንበለ ዓም፣

አዘዘኒ ሲል ነው፣ እኔን ባሪያ ውን አገልጋዩን ሙሴን ዘመን ሳትወስን ጎሞር ሙሉ መና አኑር ብሎ ፈጣሪዬ እግዚአብ ሔር አዝዞኛልና አለ፤ አንድም መተርጉም አዘዞ ይላል፣ አገል ጋዩ ሙሴን ዘመን ሳትወስን ጎሞር ምሉ መና አኑር ብሎ እግዚአብሔር አዝዞታልና በምድረ በዳ ሳላችሁ የበላች

www.ethiopianorthodox.org

ሁት መናውን የኋላ ሰዎች እንዲያዩት ለልጆቻችሁ ለኋላ ዘመን ሊጠበቅላቸው ጎሞር ምሉ መና ያለባት መሶቢቱን ወስደህ በደብተራ ኦሪት አኑራት አለው፤

ወአንበሮ አሮን ቅድመ መርጡል ከመ ይትዐቀብ፤

አሮንም የሙሴን ቃል ሰምቶ ለልጅ ልጅ ዘመን ይጠበቅላቸው ዘንድ ወስዶ በደብተራ ኦሪት አኖረው፤ ይኸውም ምሳሌ ነው፤ ለጊዜው ውሉድ በአበው መፈራረጃ እንዲያደርጉባቸው እንዲህ ያል መና ሲመግባችሁ ትክዱት? ብለው፤ አንድም ይህን የመሰለ መና ሲመግባችሁ እንዴት ካዳችሁት፤ ብለው መፈራረጃ እንዲያደርጉባቸው ነው፤ ፍጻሜው ግን መሶበ ወርቅ የእመቤታችን፤ ወርቁ የንጽሕናዋ የቅድስናዋ፤ መና የወልደ እግዚአብሔር፤ ዘእንበለ ዓም አለ ያብዙ ዘመን ሲኖር ዘመን እንዳልለወጠው፤ ጌታም ሰው ሲሆን አምላክነቱ ላለመለወጡ ምሳሌ ነው፤

፴፭፤ ወደቂቀ እስራኤል በልዑ መና ፵ዓ ክረምተ እስከ ይበጽሑ ምድረ ኀበ ያነብሮሙ እግዚአብሔር ልዑል እስከ ይበጽሑ ደወለ ፊንቆን፤

እስከ ይበጽሑና እስከ ይበጽሑ አንድ ወገን ነው፤ ምድረ ያለውን ደወለ ፊንቆን ብሎ ገለጠው፤ የእስራኤል ልጆች ግን ልዑል እግዚአብሔር መርቶ ወስዶ በከነዓን እስኪያኖራቸው ድረስ አርባ ዘመን ሙሉ መናውን ተመገቡ፤ አንድም እየራሱን ለማውጣት የእስ ራኤል ልጆች ግን እስከ ከነዓን አገር ተጉዘው ሒደው ልዑል እግዚአብሔር በከነዓን ውስጥ ባለች በፊንቆን አውራጃ እስኪያኖራቸው /እስኪያደርሳቸው/ ድረስ ፵ ዘመን ሙሉ መናውን ተመገቡ፤

፴፮፤ ወጎሞር አሥርቱ እድ ዘሠለስቱ ዘመስፈርተ ኢፍ ይእቲ፤

ጎሞርም የኢፍን ዐሥረኛዪቱን መስፈሪያ ይወስን ነበር፤ ዐሥረኛዪቱም መሥፈሪያ በሙሴ እጅ ሦስት እፍኝ ናት፤ አንድም ወጎሞር አሥርቱ እድ በመስፈርተ ኢፍ ዘሠለስቱ መስፈርት ይእቲ ብሎ ገልጦ ይጥፋል፤ ጎሞርም በሙሴ እጅ ሦስት እፍኝ የሚሆን /የምትሆን/ የኢፍን ዐሥረኛውን እጅ ይወስን ነበር፤ አንድም ጎሞርም የኢፍን ዐሥረኛውን እጅ ይወስን ነበር፤ ይኸውም ዐሥረኛው እጅ በሙሴ እጅ ሦስት እፍኝ ነው።



## ምዕራፍ ፲ወ፯

፩፤ ወአንሥኡ ትዕይንቶሙ ኵሉ ወሉደ እስራኤል እምገዳም ዘሲን /ዘሢን/ በበትዕይንቶሙ በቃለ እግዚአብሔር ወበጽሑ ኀበ ራፊድ ወአልቦ ህየ ማይ ዘይሰትዩ፤

በዚያ ወራት የእስራኤል ልጆች ሁሉ ሲን ከሚባለው አገር አጠገብ ካለው ምድረ በዳ ሠራዊቶቻቸውን አንሥተው በእግዚአብሔር ትእዛዝ በየወገን በየወገናቸው ተጉዘው ሒደው ራፊድ ከሚባል አገር ደረሱ፤ ከዚያም ደርሰው የሚጠጡት ውሀ አጡ፤

፪፤ ወግዕዝዎ ሕዝብ ለሙሴ ወይቤልዎ ሀበነ ማየ ዘንሰቲ፤ ወይቤሎሙ ሙሴ ምንት ትግዕዙ ኪያየ ወታመክርዎ ለእግዚአብሔር፤

ወአልቦ ህየ ማይ ዘይሰትዩ ብሎ ነበርና የሚጠጡት ውሀ ቢያጡ ሕዝቡ ሙሴን ነቀፉት፤ የምንጠጣውም ውሀ ስጠን አሉት፤ ይቀማጠሉበታል፤ አንድም የእግዚአብሔር ባለሟል ነውና ጸልዮ ያፈልቅልናል ብለው፤ ሙሴም እኔን ለምን ትነቅፉኛላችሁ? አንድም ምንት ዘትግዕዙ ኪያየ ይላል፤ እኔን የምትነቅፉበት ነገር ምንድር ነው? አንድም በምንት ይላል እኔን የምትነቅፉበት ነገር በምንድርነው? አንድም ለምንት ይላል፤ እኔን ለምን ትነቅፉኛላችሁ? እኔንስ ይሁን ንቀፉኝ ፈጣሪያችሁ እግዚአብ ሔርን ለምን ትነቅፉታላችሁ አላቸው፤

፫፤ ወጸምዐ በህየ ሕዝብ ማየ ወአንጐርጐሩ ዲበ ሙሴ ወይቤልዎ ለምንት አውፃእከነ እምግብጽ ከመ ትቅትለነ ምስለ ውሉድነ ወምስለ እንስሳነ በጽምዕ፤

ሕዝቡም በዚያ ቦታ ውሀ ጥም ጸንቶባቸው /ቢጠናባቸው/ በሙሴ ላይ አንጐራጐሩበት ከልጆቻችን ከከብቶቻችን ጋራ በውሃ ጥም /ልታጠፋን/ ልትገድለን ጥንቱን ከግብጽ አገር ለምን አወጣኸን? አሉት፤

፬፤ ወጸርሐ ሙሴ ኀበ እግዚአብሔር ወይቤ ሚ እግበሮ ለዝ ሕዝብ ንስቲተ ከመ ተርፎሙ ይወግሩኒ በዕብን፤

ሙሴም ያንጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ ለመነ፤ እሊህ ወገኖች በድንጋይ ወግረው፤ በእሳት አቃጥለው ሊገድሉኝ ጥቂት ብቻ ቀርቷቸዋል፤ ይህነን ወገን ምን ላድርገው? አለ፤ አንድም ይህነን ወገን ምን ላድርገው? በድንጋይ ወግረን በእሳት አቃጥለን እንግደለው ብለው መክረውብኛል፤ ወይዌግሩኒ በዕብን ይኸውም አይቀር በድንጋይ

www.ethiopianorthodox.org

ወግረው በእሳት አቃጥለው ይገድሉኛል ብሎ ወደ እግዚ. አብሔር ጮኸ ለመነ፤

## ገባኤ

፭፣ ወይቤሎ እግዚ.አብሔር ለሙሴ ሑር ቅድሜሆሙ ለሕዝብ ወንሣእ ምስሌከ፣ መላሕቅተ ሕዝብ፣ ወበትረከ ዘዘበጥከ ፈለገ ጽብጥ በእዴከ፣

እግዚ.አብሔርም ሙሴን በሕዝቡ ላይ የተሾሙ አለቆችን አስከ ትለህ፣ ውሃውን የመታህባት በትሪቱንም በእጅህ ይዘህ፤ አንድም በእጅህ አንሥተህ የግብጽን ወንዝ /ፈሳሽ/ ውሀ የመታህባት በትሪቱንም ይዘኸ እስራኤል እያዩህ ሒድ፤

፮: ወትመጽእ ለፌ ኀበ አነ እቀውም መንገለ ኰኵሕ ዘኰሬብ ወትዘብጦ ለኰኵሕ ወይወፅእ እምውስቴቱ ማይ ወይሰትዩ ሕዝብ፣

አለቆችንም በትሪቱንም ይዘኸ እኔ ወደ ቆምኹበት ወደ ኮሬብ /ዋሻ/ ድንጋይ ና፣ መጥተህም ድንጋዩን ትመታዋለህ ከድንጋዩም ውሀ ይፈልቅላቸዋል፣ ሕዝቡም ውሀውን ይጠጣሉ አለው፤

ወገብረ ሙሴ በከመ አዘዞ እግዚ. አብሔር በቅድሜሆሙ ለደቂቀ እስራኤል፣

ሙሴም በእስራኤል ልጆች ፊት እግዚ.አብሔር እንዳዘዘው አደረገ፣ አንድም ዘአዘዞ ይላል፣ ያዘዘውን አደረገ፤

፯፣ ወሰመዮ ለውእቱ መካን ፍና መንሱት ወጋእዝ በእንተ ግእዘት ዘግእዝዎ ውሉደ እስራኤል ወአመከሩ ፈጣሬ ኵሉ ወይቤሉ ለእመ ሀሎ እግዚ.አብሔር ምስሌነ ወለእመ ኢሀሎ፣

ሙሴም ያነን ቦታ ፀብ ክርክርና ጥፋት ያለበት ቦታ አለው፣ ፍና መንሱት ፍና ጋእዝ ብሎ ሁለት አርእስት ተናግሯል፣ ለሁለቱም የመጣል፣ የእስራኤል ልጆች ክፉ ነቀፋ /ጽኑ ነቀፋ/ ስለ ነቀፋት ፍና ጋእዝ ላለው፣ እግዚ.አብ ሔር በእኛ አድሮብን አለ ይሆን ወይስ አላደረብንም ይሆን ? ብለው የሁሉ ፈጣሪ የሚሆን እግዚ.አብሔርን ተፈታትነውት ተበቅሎ ስላጠፉቸው ፍና መንሱት ላለው፤

፰፣ ወመጽአ አማሌቅ ከመ ይትቃተሉ ምስለ እስራኤል በራፊድ፣

አማሌቃውያንም በዚያ ወራት በራፊድ ከእስራኤል ጋር ሊዋጉ መጡ፣

፱፣ ወይቤሎ ሙሴ ለኢያሱ ኅረይ ለከ ዕደወ ወፃእ ወተአኃዞሙ ለአማሌቅ ጌሠመ ወናሁ አነ እቀውም ዲበ ርእሰ ወግር ወበትር ዘእግዚ.አብሔር ውስተ እዴየ፣

ሙሴም ኢያሱን ከእስራኤል አርበኞች አርበኞቹን መርጠህ ሒደህ ነገ አማሌቃውያንን፣



ተዋጋቸው፣ እኔም ሒጄ በኮረብታው ራስ እቆማለሁ፣ እግዚ. አብሔርም ተአምራት ያደረገባት በትሪቱን በእጄ ይዤት፤ አንድም እግዚ.አብሔር በእጄ ተአምራት ያደረገባት በትሪቱን ይዤት እሔዳለሁ አለው፤

፲፣ ወገብረ ኢያሱ በከመ አዘዞ ሙሴ ወተራከቦሙ ለአማሌቅ ወሙሴ ወአሮን ወሖር ዐርጉ ዲበ ርእሰ ወግር፣

ኢያሱም ሙሴ ያዘዘውን አደረገ፤ አንድም ሙሴ እንደ አዘዘው አደረገ፣ አማሌቃውያንንም ወጥቶ ተዋጋቸው፣ ሙሴና አሮን ሖርም ሆነው ወደ ኮረብታው ራስ ወጡ፤

፲፩፣ ወሶበ ያነሥእ ሙሴ እደዊሁ ይትዌጽኡ አማሌቅ ወሶበ የዓዕብ ሙሴ ያወርድ እደዊሁ ወይትዌጽኡ እስራኤል ወአንበሩ ሎቱ ዕብነ ወነበረ ላዕሌሁ፣

ሙሴም እጁን (እጆቹን) በዘረጋ ጊዜ አማሌቃውያን ይሰንፉ ይደክሙ ነበር፤ አንድም ይትዌጽሑ ይላል፣ ድል ይነሡ ይሸሹ ነበር፣ ዳግመኛም ሙሴ እጁ በከበደው ጊዜ የዘረጋውን ያጥፋል እስራኤልም ይሰንፋሉ ይደክማሉ፤ አንድም ወይትዌጽሑ ይላል፣ እስራኤል ድል ይነሡ ይሸሹ ነበር፣ ያንጊዜ በኮረብታውም ላይ ደንጊያ ተከሉለት፣ ሙሴ ሒዶ በዚያ ላይ ተቀመጠ፣

፲፪፣ ወእደዊሁ ለሙሴ ክቡዳት ወአሮን ወሖር ይፀውሩ እደወ ሙሴ አሐዱ በለፌ ወሐዱ በለፌ ወቆማ እደዊሁ ለሙሴ ርቡዓቲሆን እስከ ዕርበተ ፀሐይ፣

የሙሴም እጆቹ የከበዱ ነበሩ፣ አሮንና ሖርም አንዱ በቀኝ አንዱ በግራ ሁነው የሙሴን እጆች ተሸክመው ይውሉ ነበር፤ አንድም ዘሀለወ ያለበት ነው፣ አሮንና ሖር አንዱ በቀኝ አንዱ በግራ ያሉ የሙሴን እጆች ተሸክ መው ይውሉ ነበር፤ አንድም አንዱ በቀኝ አንዱ በግራ ያሉ አሮንና ሖር የሙሴን እጆች ተሸክመው ይውሉ ነበር፤ አንድም አሐደ በለፌ ወአሐደ በለፌ ይላል፣ አሮንና ሖር የሙሴን እጆች አንዱን በቀኝ አንዱን በግራ አድርገው ተሸክ መው ይውሉ ነበር፣ በዚያም ቀን የሙሴ እጆቹ ፀሐይ ከወጣ ጀምሮ ፀሐይ እስኪገባ ድረስ ተዘርግተው ዋሉ፤

፲፫፣ ወሜጠሙ ኢያሱ ለአማሌቅ ምስለ ሕዝቡ ወቀተሎሙ በሐፂን፣

ኢያሱም በዚያች ቀን ከወገኖቹ ከእስራኤል ጋር ሁኖ ጦሩን አሰልፎ አማሌቃውያንን ድል ነሣቸው፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፬፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ጸሐፎ ለዝ ለተዝካር ወአይድዖ ለኢያሱ ድምሳሴ እደመስሶሙ ለአማሌቅ እምታሕተ ሰማይ፣

እግዚአብሔርም ሙሴን ለእስራኤል መታሰቢያ ሊሆናቸው ይህንን ነገር ጻፈው፣ ለኢያሱም ከሰማይ በታች ከምድር በላይ ያሉ አማሌቃውያንን ፈጽሜ አጠፋቸዋለሁ ብሏል ብለህ ንገረው፣ ይህ የተሳለፈ ነው፤ አንድም እንግዲህ ወዲያ የሚነሡ አማሌቃውያንን ከሰማይ በታች ከምድር በላይ አጠፋቸዋለሁ ብሏል ብለህ ንገረው አለው፤

፲፭-፲፮፡ ወአሕነፀ ሙሴ ምሥዋዐ ለእግዚአብሔር ወሰመዮ ስሞ መምሕፃን ወይቤ እስመ በእደ ኅቡዕት ይጸብዖሙ እግዚአብሔር ለአማሌቅ ለዘመደ ዘመድ፣

ለናለ የተደራረበ ነው፣ ለአብ ለዘይኬንን፣ ለብእሲት ለመር ዓተ በግዑ፣ ለካህናት ለደቂቀ አሮን፣ ለእስራኤል ለርቱዓነ ልብ እንዳለው ያለ ነው፣ ለእስራኤል ፍጹም ዘመድ የሚሆኑ አማሌቃውያንን እግዚአብሔር በተሠወረች /በረቂቅ/ ሥልጣኑ ያጠፋቸዋልና፣ ይህ ስለ ተደረገለት ሙሴ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ጸፈጸፈ፣ ያንንም ስሙን የእግዚአብሔር መማጸኛ ነው አለው፣ ለዘመደ ዘመድ አላቸው አማሌቃውያንን፣ የኤሳው ልጆች ናቸውና፤ አንድም ለአማሌቅ ዘመድ በዘመድ ይላል፣ ለዘመድ አማሌቃውያንን፣ በዘመድ በኢያሱ ያጠፋቸዋልና፤ አንድም በዘመደ ዘመድ ይላል፣ በኢያሱ ያጠፋቸዋልና፣ ኢያሱን ዘመደ ዘመድ አለው፣ ከነገደ ኤፍሬም ነውና ይኸው ምሳሌ ነው፣ ሙሴ የወልደ እግዚአብሔር፣ ኢያሱ የአዳም፣ እስራኤል የነፍሳት፣ አማሌቃውያን የአጋንንት፣ ደብር የቀራንዮ፣ አብ የመስቀል፣ አሮን የፈያታዊ ዘየማን፣ ሖር የፈያታዊ ዘጸጋም፣ ሙሴ እጁን ባጠፈ ጊዜ እስራኤል ድል መነሣታቸው ጌታ እጁን ዘርግቶ በመልዕልተ መስቀል እስኪ ሰቀል ድረስ እስራኤል ዘነፍስ በመንጸፈ ደይን ወድቀው በእግረ አጋንንት ተጠቅጥቀው የመኖራቸው ምሳሌ፣ ሙሴ እጁን በዘረጋ ጊዜ አማሌቃውያን ድል መነሣታቸው፣ ጌታ በዕለተ ዓርብ እጁን ዘርግቶ በመልዕልተ መስቀል በተሰቀለ ጊዜ አጋንንት ድል የመነሣታቸው ምሳሌ፣ ፀሐይ እስኪገባ ድረስ የሙሴ እጆች ተዘርግተው ዋሉ አለ፣ ጌታም እጆቹን ዘርግቶ በዕለተ ዐርብ



ከስድስት ሰዓት እስከ ዘጠኝ ሰዓት በተሰቀለ ጊዜ ጨለማ ሁኗልና፣ ወእምስሱ ሰዓት እስከ ተስዑ ሰዓት ጸልመ ኵሉ ዓለም እንዲል፣ አጋንንትን ለዘመደ ዘመድ አላቸው በተፈጥሮ፣ ወዝንቱ ዘመድ ኢይወፅእ ዘእንበለ በጾም ወበጸሎት እንዲል፤ አንድም ለዘመድ በዘመድ ይላል፣ ለዘመድ አጋንንት ናቸው፣ በዘመድ ክርስቶስ ነው፤ አንድም በዘመደ ዘመድ ይላል በክርስቶስ አጠፋቸው፣ ክርስቶስን ዘመድ አለው በልብስተ ሥጋ ነው።

## ምዕራፍ ፲ወ፰

፩፡ ወሰምዐ ዮቶር ካህነ ምድያም ሐሙሁ ለሙሴ ኵሎ ዘገብረ ሎቱ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለእስራኤል ሕዝቡ ወዘከመ አውፅኦሙ እምግብጽ፣

በዚያ ወራት የሙሴ አማት የምድያም ካህን ዮቶር እግዚአብሔር ለሙሴ ያደረገለትን ለወገኖቹ ለእስራኤልም ያደረገላቸውን ሰማ፣ ሕዝቡ ለሙሴ ነው፤ አንድም ለእግዚአብሔር ነው፣ ገብረ ያለውን አውፅኦሙ ብሎ አመጣው፣ ከግብጽ እንዳወጣቸው ሰማ፤ አንድም ወአውፅኦሙ ይላል፣ እግዚአብሔር ከግብጽ አውጥቶ ለወገኖቹ ለእስራኤልም ለሙሴም ያደረገላቸውን ሁሉ ሰማ፤

፪፡ ወነሥአ ዮቶር ሐሙሁ ለሙሴ ሲፓራሃ ብእሲቶ ለሙሴ እምዘ ኃደጋ ወ፪ተ ደቂቆ፣

የሙሴ አማት ዮቶርም ይኸን ሰምቶ ካኖረባት ቦታ የሙሴን ሚስት ሲፓራን ሁለቱንም ልጆቹን አድርጎ ይዞ ሔደ፤

፫፡ ስሙ ለወልደ ሙሴ ፩ዱ ጌርሳም ወይቤ እስመ ፈላሲ አነ በምድረ ባዕድ፣

አንዱ የሙሴ ልጅ ስሙ ጌርሳም ይባላል፣ በተወለድኩበት በባዕድ ሀገር ስደተኛ መጻተኛ ነኝና ሲል ጌርሳም አለው፤

፬፡ ወስሙ ለካልእ ወልዱ ኤልዛር ወይቤ ፈጣሪ ዘአቡየ ረዳእየ ወአድኃነኒ እምእዴሁ ለፈርዖን፣

የሁለተኛውም የሙሴ ልጅ ስሙ ኤልዛር ይባላል፣ ረዳእየ ወመድኃንየ ሲል ነው፣ የአባቴ ፈጣሪ እግዚአብሔር ረዳቴ መድኃኒቴ ነው፤ አንድም ረድአኒ ወአድኃነኒ ይላል፣ የአባቴ ፈጣሪ ከፈርዖን እጅ ረዳኝ፣ አዳነኝ /ረድቶ አዳነኝ/ ሲል ኤልዛር አለው፤

www.ethiopianorthodox.org

፭፣ ወመጽአ ዮቶር ሐሙሁ ለሙሴ ወብእሲቱ ወደቂቁ ኀበ ሙሴ ውስተ ገዳም ኀበ ኃደሩ ጕንደ ደብር ዘእግዚአብሔር፣

የሙሴ አማት ዮቶርም ሚስቱን ልጆቹን ይዞ ሙሴ ወዳለበት ወደ ምድረ በዳው መጣ፣ ይኸውም ምድረ በዳው እግዚአ ብሔር በሚገለጽበት በደብረ ሲና አጠገብ ያለ እስራኤል ያደሩበት ምድረ በዳ ነው፤

፮፣ ወይቤልዎ ለሙሴ ናሁ ዮቶር ሐሙከ መጽአ ኀቤከ ወብእሲትከ ወክልኤሆሙ ደቂቅከ፣

ሙሴን ሒደው እነሆ አማትህ ዮቶር መጣ፣ ሚስትህም ሁለቱ ልጆችህም ወደ አንተ መጡ ብለው ነገሩት፤

፯፣ ወወፅአ ሙሴ ወተቀበሎ ለሐሙሁ ወአምኆ ወሰዓሞ ወተአ ምኁ በበይናቲሆሙ ወቦኡ ውስተ ትዕይንት፣

ሙሴም ለአክብሮ አማቱ ዮቶርን ወጥቶ ተቀበለው፣ ዮቶርም እጅ ነሥቶ ሙሴን ሳመው፤ አንድም ሙሴ እጅ ነሥቶ ዮቶርን ሳመው ከዚያ በኋላ እርስ በእርሳቸው እጅ ተነሣሥተው ወደ ከተማው /ወደ ሰፈር/ ገቡ፣

፰፣ ወዜነዎ ሙሴ ለሐሙሁ ኵሎ ዘገብሮ እግዚአብሔር ለፈርዖን ወለግብጽ በእንተ እስራኤል ወኵሎ ሕማመ ዘከመ ሐሙ በፍኖት ወዘከመ አድኃኖሙ እግዚአብሔር፣

ሙሴም ለአማቱ ለዮቶር እግ ዚአብሔር ስለ ወገኖቹ ስለ እስራኤል ብሎ በግብጻውያ ንና በፈርዖን ያደረገውን /ያደ ረገባቸውን/ ሁሉ ነገረው፣ ይኸ ከመ በባለቤት የገባ ከመ ነው፣ እስራኤልም በጐዳናው /በመንገድ/ የተቀበሉትን መከራ ሁሉ እግዚአብሔርም ከመከራው ያዳናቸውን ማዳን ሁሉ ነገረው፤ አንድም ወገኖቹ እስራኤል በጎዳና መከራውን ሁሉ እንደ ተቀበሉ እግዚአ ብሔርም በቸርነቱ ከመከራው ሁሉ እንደ አዳናቸው ነገረው፣

፱፣ ወደንገፀ ዮቶር በኵሉ ሰሚዖ ኵሎ ዘከመ ገብረ ሎሙ እግዚአ ብሔር ወዘከመ አድኃኖሙ እምእደ ግብጽ ወእምእደ ፈርዖን፣

ዮቶርም እግዚአብሔር ለወገ ኖቹ ለእስራኤል ያደረገላ ቸውን ተአምራት ከፈርዖንና ከግብጻውያንም እጅ ያዳና ቸውን ማዳን ሰምቶ በዚህ ሁሉ ደነገጠ፤ አንድም እንዳለ ይሆናል፣ ዮቶር እግዚአብ ሔር ለወገኖቹ ለእስራኤል ተአምራቱን ሁሉ እንደ አደረ



ገላቸው ከፈርዖንና ከግብጻ ውያንም እጅ በቸርነቱ እንደ አዳናቸው ሰምቶ በዚህ ሁሉ የደስታ ድንጋጤ ደነገጠ፤

፲፣ ወይቤ ዮቶር ቡሩክ እግዚ አብሔር ዘአድኃነ ሕዝቦ እምእደ ግብጽ ወእምእደ ፈርዖን፣

ዮቶርም ከፈርዖንና ከግብጻ ውያን እጅ ወገኖቹ እስራ ኤልን ያዳነ እግዚአብሔር ክቡር ምስጉን ነው፤

፲፩፣ ይእዜ አእመርኩ ከመ ዐቢይ እግዚአብሔር እምኵሉ አማልክት ወእንበይነዝ /በበይነዝ/ ተኰነኑ ሎቱ፣

እኔም እስካሁን አላወቅሁም ነበር፣ ዛሬ ግን በስም አማል ክት ከሚባሉ በስመ አማል ክት ከሚጠሩ ከጣዖታቱ ይልቅ እግዚአብሔር ገናና ፈጣሪ እንደሆነ አወቅሁ፣ እናንተም እስራኤል ይኸን ሁሉ ስላደረገ ላችሁ ተገዙለት አለ፤ አንድም በበይነዝ ተኰነኑ ሎሙ ይላል፣ አሕዛብ በዚህ ሁሉ ስለ ተገዙ ላቸው፣ በስም አማልክት ከሚባሉ በስመ አማልክት ከሚጠሩ ይልቅ እግዚአብ ሔር ገናና ፈጣሪ እንደ ሆነ አወቅሁ አለ፣ ይህም በኋላ በዘመነ ሐዲስ አጋንንት ለጌታ እንዲገዙ ያጠይቃል፣ ነአምረከ መኑ አንተ ቅዱሱ ለእግዚአብሔር በኢየሱስኒ አአምን ወለጳውሎስኒ አአ ምሮ እንዲል የሐሥራ ምዕ ፲፱ ቍ ፲፩-፲፯ ሉቃ ፬-፴፬፤

፲፪፣ ወነሥአ ዮቶር ሐሙሁ ለሙሴ ወገብረ መሥዋዕተ በጽድቅ ለእግዚአብሔር፣

የሙሴ አማት ዮቶርም ያንጊዜ የሚሠዋውን ላሙን ፍየሉን ወስዶ ለእግዚአብሔር እውነ ተኛ መሥዋዕት አቀረበ፤ አንድም ገብረ በጽድቅ፣ ለእግዚ አብሔር መሥዋዕቱን በእው ነት አቀረበ፣ በጽድቅ አለ በሐሰት ማቅረብ አለና፤

ወመጽኡ አሮን ወሊቃናተ እስራ ኤል ከመ ይብልዑ ኅብስተ ምስለ ሐሙሁ ለሙሴ በቅድመ እግዚ አብሔር፣

የእስራኤል አለቆችና አሮንም ለአክብሮ በደብተራ አሪት ከሙሴ አማት ከዮቶር ጋራ ተረፈ መሥዋዕት ሊበሉ ወደ ደብተራ አሪት መጡ፤

፲፫፣ ወአመ ሳኒታ ነበረ ሙሴ ይኰንን ሕዝበ ወይጸንሕ ሕዝብ ሙሴሃ እምነግህ እስከ ሠርክ፣

በበነጋውም ሙሴ ወገኖቹን ሊሠራ ሊቀጣ፤ አንድም ለወገ ኖቹ ሊፈርድላቸው ሊፈርድ ባቸው በአደባባይ ተቀመጠ፣

www.ethiopianorthodox.org

ሕዝቡም ተራው ባይደርሰው ከነግህ እስከ ሠርክ ከጧት ጀምሮ እስከ ማታ ድረስ ሙሴን ሲጠብቅ ዋለ፤

፲፬፣ ወርእየ ዮቶር ኵሎ ዘይገብር በላዕለ ሕዝብ ወይቤሎ ለሙሴ ምንትኑዝ ዘትገብር በሕዝብ ባሕቲትከ ትነብር ወኵሉ ሕዝብ ይቀውም እምነግህ እስከ ሠርክ፣

ዮቶርም ሙሴ በሕዝቡ ላይ የሚያደርገውን ሥራ ሁሉ አይቶ ሙሴን በወገኖችህ በእስራኤል የምታደርገው የምትሠራው ይህ ምንድን ነው? አንተ ብቻህን በአደባባይ ትቀመጣለህ፣ ሕዝቡም ሁሉ ተራውን እየጠበቀ አልደርሰው ብሎ ከጧት እስከ ማታ ቁሞ ይውላል፣ ነገሩ ምንድን ነው? ብሎ ጠየቀው፣

፲፭፣ ወይቤሎ ሙሴ ለሐሙሁ እስመ ይመጽኡ ኀቤየ ሕዝብ ወይሴአሉኒ ፍትሐ በኀበ እግዚአብሔር፣

ሙሴም አማቱ ዮቶርን እንዲህ አለው፣ ሕዝቡ ወደ እኔ መጥተው በእግዚአብሔር ዘንድ /ከእግዚአብሔር ዘንድ/ የሚገኝ ፍርዱን ይጠይቁኛልና፣

፲፮፣ ወእምከመ ተገዓዙሂ ይመጽኡ ኀቤየ እፍትሐሙ አስተናጺሕየ ለለ፩፩ ወሕጉ በኵነኔ እግዚአብሔር፣

ከተጣሉም በኋላ በእግዚአብሔር በሕጉ በሥርዓቱ ጸንቼ፣ እያንዳንዱን አውጥቼ አውርጄ መርምሬ፤ አንድም አንጥሬ አጥርቼ እፈርድላቸው ዘንድ ሕዝቡ ተሰብስበው ወደ እኔ ይመጣሉና ስለዚህ ነው አለው፣

፲፯፣ ወይቤሎ ሐሙሁ ለሙሴ አኮ ርቱዕ ዝነገር ዘአንተ ትገብር፣

የሙሴ አማት ዮቶርም አንተ በሕዝቡ የምታደርገው ይህ ነገር የቀና አይደለም፣

፲፰፣ ዐቢየ ሕማመ ተሐምም አንተ ወኵሉ ሕዝብ ዘሀሎ ምስሌከ ይከብደከ ዝቃል ወኢትክል ለባሕቲትከ ገቢሮቶ፣

ይህም ነገር ታላቅ ነገር ነው፣ ተሐምም ማንኛ፤ አንድም አንተ ጽኑ መከራ ትቀበላለህ ከአንተም ጋራ ያለው ሕዝብ ሁሉ መከራ ይቀበላል፣ ይከብደከ ማንኛ፤ አንድም አንተ ጽኑ መከራ ትቀበላለህ ከአንተም ጋራ ያለው ሕዝብ ይበዛብሃል ይከብድብሃል፣ ዝ ቃል ማንኛ፤ አንድም ይህ ነገር ይበዛብሃል ይከብድሃል፣ ይህነንም ነገር አንተ ብቻ ማድረግ አይቻልህም፤

፲፱፣ ወይእዜኒ ስምዓኒ ወአነ እመክረከ ወእግዚአብሔር የሀሉ ምስሌከ ወኩኖሙ አንተ ለሕዝብ ሉኀበ እግዚአብሔር ወታበትክ ቃሎሙ በኀበ እግዚአብሔር፣



አሁንም አንተ የምነግርህን ስማኝ፣ እኔም የተቻለኝን እመክርሃለሁ፣ እግዚአብሔርም ከአንተ ጋር በረድኤት አድሮ ብህ ይኑር፣ አንተ ነገሩን ከእግዚአብሔር ዘንድ ጠይቀህ ለሕዝቡ ንገራቸው፣ ፍርዱንም ከእግዚአብሔር ዘንድ አስቈርጥላቸው አለው፤

፳፣ ወአስምዮሙ ትእዛዞ ለእግዚአብሔር ወሕጎ ወትዜንዎሙ ፍኖቶ በእለ የሐውሩ ውስቴቶን ወግብረ ዘይገብሩ፣

የእግዚአብሔርን ትእዛዙን ሥርዓቱንም ንገራቸው አስተምራቸው፣ ጸንተው የሚኖሩበትንም ሥርዓት የሚሠሩበትንም ሥራ ንገራቸው አለው፤

፳፩፣ ወአንተሂ ለሊከ ምክር ወኅሥሥ እምኵሉ ሕዝብ ኃያላነ ዕደወ ወጻድቃነ ስብአ እለ ይጸልዑ ትዕቢተ ወሚም ሉሙ መኳንንት ለ፲ቱ ፻ት ወለ፻ት ወለ፶ ወለ፲ቱ፣

አንተም ለራስህ አውጥተህ አውርደህ ምክር፣ ከእስራኤል ወገንም ኃያላን አእምሮ ዕውቀት ያላቸውን፣ ወዕደወ ጻድቃነ ደጋጎችን፣ ትዕቢትንም የሚጠሉ ሰዎችንም ሁሉ መርጠህ ለሺህ አለቃ፣ ለመቶው አዝማች ለሃምሳው ደምሳሽ፣ ለዐሥሩ መጨኔ ሹም፤ አንድም መኳንንት ፲ቱ፻ት ይላል፣ የሺህ አለቃ፣ የመቶ አዝማች፣ የሃምሳ ደምሳሽ፣ የዐሥር መጨኔ ሹም፤ አንድም አብነት መኳንንት ለ፲ቱ፣ መኳንንት ለ፶፣ መኳንንት ለ፻፣ ወመኳንንት ለ፲ቱ ፻ት ይላል፣ ለዐሥር መጨኔ፣ ለሃምሳ ደምሳሽ፣ ለመቶ አዝማች፣ ለሺሁ አለቃ፤ አንድም መኳንንት ፲ወ፶ወ፻ወ፲፻ ይላል፤ የዐሥር መጨኔ፣ የአምሳ ደምሳሽ፣ የመቶ አዝማች፣ የሺህ አለቃ ሹምላቸው አለው፤

፳፪፣ ወይኰንኑ ሕዝበ ኵሎ ሰዓተ ወቃለ ዘየዐጽቦሙ ያምጽኡ ኀቤከ ወቀሊለ ኵነኔ እሙንቱ ይኰንኑ ወይቀልለከ ወይረድኡከ፣

ሹማምቱም በአደባባይ ተቀምጠው በየሰዓቱ ለሕዝቡ ይፍረዱላቸው፣ የጸናናቸውን የከበዳቸውን ፍርድ ግን ወደ አንተ ያምጡ፣ ቀላል ቀላሉን ፍርድ ግን እነሱ ከዚያው ይፍረዱ፣ የእኔን ምክር ሰምተህ ይህነን ያደረግህ እንደሆነ ለአንተም ነገሩ ይቀልልሃል፣ እነሱም በፍርዱ ይረዱሃል አለው፤

፳፫፣ ወዘንተ ቃልየ ለእመ ገበርከ ያኀይለከ እግዚአብሔር ወትክል ኵንኖ ወሕዝብ ይግባእ ውስተ ምን ባሪሁ በፍሥሐ፣

ብታደርገውስ የመከርኩህ ምክር ይህ ነው፤ አንድም ዘንተ ቃለ

www.ethiopianorthodox.org

ለእመ ገበርከ ይላል፣ ይኸነን የመከርኩህን ምክሬን ብታደርገው እግዚአብሔር በዕውቀት ያጸናሃል፣ የጸነነውንም ፍርድ አቃንቶ መፍረድ ይቻልሃል ይገብእ ሲል ነው፣ ሕዝቡም ተፈርዶበት ተፈርዶለት ደስ እያለው ወደ ቤቱ ይመለሳል፣ የተፈረደለትስ ይሁን፣ የተፈረደበት እንደምን ደስ ይለዋል? ቢሉ በዚያው አስጠግቶ፤ አንድም የተፈረደበትም ከከተማ ኑሮ ወደ ቤቱ ሲመለስ ደስ ይለዋልና፤

፳፬፣ ወሰምዐ ሙሴ ቃለ ሐሙሁ ወገብረ በከመ ይቤሎ፣

ሙሴም የአማቱ የዮቶርን ቃል ሰምቶ ወሚም ለሙ መኳንንተ ያለውን ቃል አደረገ፤ አንድም የአማቱ የዮቶርን ቃል ምክር ሰምቶ ወሚም ለሙ መኳንንተ እንዳለው አደረገ፤

፳፭፣ ወኃረየ ሙሴ ዕደወ ዘይክሉ እምኵሉ እስራኤል /እምውስተ ኵሉ/ ወሤመ በላዕሌሆሙ መኰንነ ፲ቱ ፻ት ወዘ፶ት ወዘ፶ ወዘ፲ቱ፣

ሙሴስ ሰምቶ ምን አደረገ? ትለኝ እንደ ሆነ፣ ከእስራኤል ወገኖች አውጥተው፣ አውርደው መርምረው የሚፈርዱ፤ አንድም አጥርተው አንጥረው መፍረድ የሚቻላቸው ደኃግ ሰዎችን መረጠ፣ መርጠም የሺህ አለቃ፣ የመቶ አዝማች፣ የሃምሳ ደምሳሽ፣ የዐሥር መጨኔ ሾመላቸው፤ አንድም መኰንነ ለ፲፻ ወለ፻ ወለ፶ ወለ፲ቱ ይላል፤ አንድም መኰንነ ፲ወ፶ ወ፻ ወ፲፻፤ አንድም መኰንነ ለ፲ ወለ፶ ወለ፻ ወለ፲፻ ይላል፤ ሐተታ እንዳለፈው፤

፳፮፣ ወይኴንኑ ኵሎ ሕዝበ ኵሎ ሰዓተ ወዘየዓዕቦሙ ኵነኔ ያዕርጉ ኀበ ሙሴ ወቀሊለ ኵነኔ እሙንቱ ይፍትሑ፣

እሊህም ሹማምቱ በየጊዜው በየሰዓቱ ሕዝቡን እንዲሠሩ እንዲቀጡ፤ አንድም በየጊዜው በየሰዓቱ እንዲፈርዱላቸው እንዲፈርዱባቸው የጠነናቸውንም ፍርድ ወደ ሙሴ ሊያደርሱ፤ የቀለለውን ጥቃቅኑን ፍርድ ግን እነሱ ይፈርዱ ዘንድ ሤመ ላዕሌሆሙ ሾመላቸው፣ ሾመባቸው፤

፳፯፣ ወፈነዎ ሙሴ ለሐሙሁ ውስተ ምድሩ ወኃለፈ፣

ሙሴም ከዚህ በኋላ አማቱ ዮቶርን ወደ ሀገሩ ሸኝቶ ወኃለፈ ተመይጠ ሲል ነው፣ ተመለሰ፤ አንድም ሙሴ አማቱ ዮቶርን ሸኝቶ ወደ ሀገሩ ሰደደው እሱም ተነሥቶ ሔደ።



## ምዕራፍ ፲ወ፱

### ገባኤ

፩፣ ወበሣልስ ወርኅ እምዘወፅኡ ውሉደ እስራኤል እምድረ ግብጽ በዛቲ ዕለት፣

የእስራኤልም ልጆች ከግብጽ አገር ከወጡ በኋላ እምዘ ነሡቱኪ ትትሐነጊ እንዲል፣ በሦስተኛው ወር በሰኔ በዚህች ቀን፣

፪፣ ወዕኡ ወሖሩ እምራፌድ ወበጽሑ ውስተ ገዳም ዘሲና /ዘሢን/፣

ከራፌድ ወጥተው ሔዱ፣ ሒደውም በደብረ ሲና አጠገብ ወዳለ ምድረ በዳ ደረሱ፤

ወኃደሩ ህየ መንጸረ ደብሩ፣

ከዚያም ደርሰው በደብረ ሲና ፊት ለፊት ሰፍረው አደሩ፤

፫፣ ወሙሴ ዐርገ ውስተ ደብረ እግዚአብሔር ወጸውዖ እግዚአብሔር ለሙሴ እምዲበ ደብር ወይቤሎ በሎሙ ለቤተ ያዕቆብ ወዜንዎሙ ለውሉደ እስራኤል፣

ሙሴም ያንጊዜ ወደ እግዚአብሔር መዲና ወደ ደብረ ሲና ወጣ፣ እግዚአብሔርም ከደብረ ሲና ሁኖ ሙሴን ጠራው፣ ይቤሎን ጠብቀው ለእስራኤል ልጆች፣ ለያዕቆብ ወገኖች ለእስራኤል እናንተ በግብጻውያን ያመጣሁባቸውን /ያመጣሁትን/ መከራ አያችሁ? አንድም በግብጻውያን መከራ እንዳመጣሁባቸው አያችሁ?

፬፣ ወአንትሙ ርኢክሙ መጠነ ገበርክዎሙ ለግብጽ ወነሣእኩክሙ ከመ ክንፈ ንሥር ወአቅረብኩክሙ ኀቤየ፣

እናንተን ግን እንደ ጭላት አወጣኋችሁ አለ፣ ፈጥኜ ከግብፅ አወጣኋችሁ ሲል ነው፣ አሁንም አውጥቼ ወደ እኔ በባለሟልነት አቀረብኳችሁ አለ ብለህ ንገራቸው፤

፭፣ ወይእዜኒ ለእመ ሰማዕክሙኒ ቃልየ ወዐቀብክሙ ትእዛዝየ ትከውኑኒ ሕዝበ ዘጽድቅ እምኵሉ አሕዛብ እስመ ዚአየ ይእቲ ኵለንታሃ ምድር፣

ዛሬም ቃሌን ብትሰሙ ያዘዝኳችሁንም ብትጠብቁ መላዋ ምድር የእኔ ገንዘብ፣ ናትና በሎሙ ትከውኑኒ ሕዝበ ዘጽድቅ፣ ከአሕዛብ ሁሉ ይልቅ ተለይታችሁ እናንተ እውነተኛ ወገኖቼ ትሆናላችሁ፣

፮፣ ወአንትሙ ትከውኑኒ እለ መንግሥት ወእለ ትሠውዑ ሊተ ወሕዝበ ዘጽድቅ ዘ ቃለ አይድዮሙ ለውሉደ እስራኤል፣

እናንተም የነገሥታት ወገን ትሆናላችሁ አለ ነገሥታቱ ከእናንት ይወለዳሉ /ይወለዱልኛል/፣ መሥዋዕቱንም ትሠ

www.ethiopianorthodox.org

ውልኛላችሁ አለ፣ ሌዋውያን ካህናት ከእናንት ይወለዱ ልኛል፣ እውነተኛ ወገኖቼም ትሆኑኛላችሁ አለ፣ ምግባር ሃይማኖት የሚጠብቁ ወገኖች ከእናንት ይወለዱልኛል፣ አለ እግዚአብሔር ብለህ ንገራቸው፣ ይቤሎ ዘ ቃለ አይድ ዖሙ ብለው ይገጥሙታል፣ ለእስራኤል ልጆች ይህን ሁሉ ነገር ንገራቸው አለው፤

፯፣ ወመጽአ ሙሴ ወጸውዐ ሊቃናተ ሕዝብ ወአይድዖሙ ኵሎ ቃለ ዘአዘዞሙ እግዚአብሔር፣

ሙሴም ከደብረ ሲና ሒዶ ወያ መጽኡ ክብሩ ለወለተ ጽዮን እንዲል፣ በሕዝቡ የተሾሙ አለቆችን ጠራቸው፣ ጠርቶም እግዚአብሔር ሊሠሩት፣ ሊጠ ብቁት የአዘዛቸውን ቃል ሁሉ ነገራቸው፤ አንድም ኵሎ ቃለ ዘአዘዞ እግዚአብሔር ይላል፣ ዘ ቃለ አይድዖሙ ብሎ እግዚ አብሔር ያዘዘውን ቃል ሁሉ ነገራቸው፤

፰፣ ወአውሥኡ ኵሉ ሕዝብ በአሐዱ ቃል ወይቤሉ ኵሎ ዘአዘዘነ እግዚአብሔር ንገብር ወንሰምዕ ወአዕረገ ሙሴ ቃለ ሕዝብ ኀበ እግዚአብሔር፣

ሕዝቡም ሁሉ እንደ አንድ ልብ መካሪ፣ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሁነው እግዚአብሔር ያዘዘንን ቃል ሁሉ እንሰማ ለን፣ ሰምተነውም አይቀር እናደርገዋለን አሉ፣ ሰምተ ውት ሳይደረግ የሚቀር ቃል አለና፤ አንድም እንዳለ ይሆ ናል፣ እግዚአብሔር ያዘዘንን ቃል ሁሉ ሰምተን እናደርገ ዋለን አሉ፣ መገቦሙ ወመር ሆሙ እንዲል፣ ሙሴም የሕዝቡን ቃል ይዞ እግዚአ ብሔር ወደ አለበት ወደ ደብረ ሲና ወጣ፤

፱፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ እመጽእ አነ ኀቤከ በዓምደ ደመና ከመ ይስምዑ ሕዝብ እንዘ እትናገር ምስሌከ ወይእመኑ ብከ ለዓለመ ዓለም፣

እግዚአብሔርም ሙሴን እኔ ከአንተ ጋር ስነጋገር ሕዝቡ እንዲሰሙ፣ እኔም የላክሁህ እውነተኛ ነቢይ እንደሆንክ ለዘለዓለሙ እንዲያምኑብህ በዓምደ ደመና ሁኜ ነገ ወደ አንተ እመጣለሁ አለው፤

ወአይድዐ ሙሴ ቃለ ሕዝብ ኀበ እግዚአብሔር፣

አዕረገ ሙሴ ያለውን አይድዐ ሙሴ ብሎ ገለጠው፤ አንድም አዕረገ ሙሴ ብሎ ነበርና ቃሉን ይዞ ወደ ደብረ ሲና ወጣ እንጂ መች ለእግዚአ ብሔር ተናገረ ትለኝ እንደሁ



ሙሴ የሕዝቡን ቃል ይዞ ወጥቶ ምላሹን ለእግዚአብሔር ነገረ፣ ይኸውም የተላለፈ ነው፣ ወአዕረገ ሙሴ ቃለ ሕዝብ ኀበ እግዚአብሔር፣ ወአይድዐ ሙሴ ቃለ ሕዝብ ኀበ እግዚ አብሔር ብሎ ወይቤሎ እግዚአ ብሔር ለሙሴ እመጽእ አነ ኀቤከ በዓምደ ደመና ይላል፤

፲፣ ወወሪደከ ኩንን ሕዝበ ያንጽሑ ርእሶሙ ዮም ወጌሠመ ወይሕፅቡ አልባሲሆሙ፣

እመጽእ ኀቤከ ብሎት ነበርና ያን ጊዜ እግዚአብሔር ሙሴን እስራኤል ልብሳቸውን አጥበው ሊያደርቁ፣ እስከ ሦስት ቀን ድረስ ከሴት ሊርቁ፣ ንጽሕ ናቸውን ሊጠብቁ፣ እንኪያስ ከዚህ ወርደህ ሕዝቡን ሥራልኝ ቅጣልኝ አለው፤

፲፩፣ ወይጽንሑ ድልዋኒሆሙ ለአመ ሣልስት ዕለት እስመ አመ ሣልስት ዕለት እወርድ ዲበ /ውስተ/ ደብር ዘሲና በቅድሚሆሙ ለሕዝብ፣

በሦስተኛው ቀን ሕዝቡ እያዩኝ በዓምደ ደመና ሁኜ ወደ ደብረ ሲና እወርዳለሁና ለምወርድበት ለሦስተኛው ቀን ልብሳቸውን አጥበው አድርቀው፣ እስከ ሦስት ቀን ድረስ ከሴት ርቀው፣ ንጽሕ ጠብቀው፣ የተዘጋጁ ሁነው ይጠብቁኝ አለው፤

፲፪፣ ወትከፍል ሕዝበ ይዑድዋ ለደብር ወለይትዓቀቡ ኢይዕርጉ ውስተ ደብር ዜኑ በቅድሚሆሙ ለሕዝብ ወኵሉ ዘለከፎ ለደብር ሞተ ለይሙት፣

ሕዝቡንም ከሦስት ከፍለህ በደብረ ሲና በዙሪያዋ ይቁሙ አለ፣ ሕዝቡ በእግረ ደብር፣ ሌዋውያን በመንፈቀ ደብር፣ አንተ አሮን በርእሰ ደብር፣ ሁናችሁ ጠብቁኝ ሲል ነው፣ እሊህም ከሦስት የተከፈሉት ሕዝቡ ከእግረ ደብር ወደ መንፈቀ ደብር፣ ሌዋውያን ከመንፈቀ ደብር ወደ ርእሰ ደብር፣ ሙሴ አሮን ከርእሰ ደብር እኔ ወዳለሁበት እንዳ ይወጡ ይጠበቁ፣ ይህንንም እግዚአብሔር ብሏል ብለህ የእኔን ቃል ንገራቸው፤ አንድም እኔ ለአንተ የነገርኩህን ቃል አንተ ለሕዝቡ አዋጅ አድርገህ ንገራቸው፤ ተራራውንም የነካ፤ አንድም ዘቀረቦ ይላል፣ የቀረበው ሰው ሁሉ የሞት ሞት ይሙት አለው፤ አንድም እኔ ለአንተ የነገርኩኽን ይህን ቃል አንተ ለሕዝቡ የሞት ሞት ይሙት ብለህ አዋጅ አድርገህ ንገር አለው፤

፲፫፣ ወበእደዊሆሙ ኢያርእዩ ወኵሉ ዘይወግር ዕብነ አው ዘይወጽፍ፡ ሞጸፈ ኢይሕየው እመኒ ሰብእ ወእመኒ እንስሳ ዘቀርበ

www.ethiopianorthodox.org

ኢይሕየው ወእምከመ ቃለ መጥቅዕ ወደመና ኃለፈ እምደብር ይዕርጉ ኀበ ደብር፤

ተራራውንም በእጃቸው ጠቅ ሰው አያሳዩ፤ ንቀት ነውና ለጊዜው በዘፈቀደ ታይቶበ ታል፤ ፍጻሜው ግን ደብረ ሲና የቤተ ክርስቲያን አምሳል ናት፤ ቤተ ክርስቲያንን በጣት ጠቅሶ ማሳየት አይገባም ሲል ነው፤ ደንጊያም በእጁ አንሥቶ ወደ ተራራው የወረወረ ሰው ሁሉ ወደ ተራራውም በወንጭፍ ደንጊያ የወነጨፈ ሰው ሁሉ አይደን፤ ሰውም ቢሆን ከብትም ቢሆን ወደ ተራራው ከቀረበ አይዳን፤ መልሶ መልሶ የሚመታውም ረቂቅ የነጋሪት ድምፅ ከተሰማ በተራራውም ደመናው ሰፍሮ ከታየ በኋላ የዐርጉ ሲል ነው፤ ከአንዱ ተራራ ወደ አንዱ ተራራ ከወጡ አይዳኑ ይሙቱ አለው፤ አንድም ከአንዱ ተራራ ወደ አንዱ ተራራ ከወጡ እግዚአ ብሔር አይዳኑ ይሙቱ ብሏል ብለህ የእኔን ቃል ለሕዝቡ አዋጅ አድርገህ ንገር አለው፤ አንድም እኔ ለአንተ የነገር ኩህን ምስለኔ ሁን እንደ እኔ ነህና አይዳኑ ይሙቱ ብለህ አንተ አዋጅ አድርገህ ንገረው አለው፤ እምደብር ኀበ ደብር አለ፤ አሁን ከደብረ ሲና ወደ አንዱ ተራራ ቢሔዱ ይሞታሉ ማለቱ አይደለም፤ በእግረ ደብር ያሉ ሕዝቡ ወደ መን ፈቀ ደብር፤ በመንፈቀ ደብር ያሉ ሌዋውያን ወደ ርእሰ ደብር፤ በርእሰ ደብር ያሉ ሙሴ አሮን እኔ ወደ አለሁ በት ቢወጡ ይሙቱ ሲል ነው እንጂ፤

፲፬፤ ወወረደ ሙሴ ዲበ ደብር ኀበ ሕዝብ ወቀደሶሙ ወሐፀቡ አልባሲሆሙ፤

ሙሴም ከደብረ ሲና ሕዝቡ ወደ አሉበት ወደ እግረ ደብር ወርዶ ከሴት ለያቸው፤ አንድም የቦታ ነው፤ ሕዝቡን በእግረ ደብር፤ ሌዋውያንን በመንፈቀ ደብር አድርጎ ለያቸው፤ እነ ሱም ከዚያ አስቀድሞ ልብሳ ቸውን በውሀ አጠቡ፤ በዐሐይ አደረቁ፤

፲፭፤ ወይቤሎሙ ለሕዝብ ተደለዉ ለሠሉስ ዕለት ወኢትቅረቡ ኀበ አንስት፤

ሙሴም ከዚያ አስቀድሞ ሕዝቡን እስከ ሦስት ቀን ድረስ ከሴት ራቁ፤ ንጽሕናችሁን ጠብቁ፤

፲፮፤ ወአመ ሣልስት ዕለት ገይሶ ከሙ በጽባሕ ናሁ ትሰምዑ ቃለ መብረቅ ወደመና ወጊሜ በደብሩ ለሲና ወቃለ መጥቅዕ ዓቢይ ይደምፅ



ወይደነግጹ ኵሉ ሕዝብ በውስተ ትዕይንት፤

በሦስተኛውም ቀን ማለዳ ገስግ ሳችሁ ሒዳችሁ እነሆ መብ ረቁን ነጐድጓዱን ትሰማላችሁ፤ በደብረ ሲናም ደመናው ጉሙ ሰፍኖ ታያላችሁ፤ መልሶ መልሶ የሚመታውም ረቂቅ የነጋሪቱ ድምፅ ገንትቶ በርትቶ ይሰማል፤ በከተማውም ያሉ ሕዝቡ ሁሉ መብረቅ ነጐድጓ ዱን፤ አንድም የነጋሪቱን ድምፅ ሰምተው ደመናው ጉሙ በተራራው ሰፍሮ አይተው ይደነግጣሉ አሳቸው፤

፲፯፤ ወአውፅአ ሙሴ ሕዝበ እማዕከለ ትዕይንት ይትራከቡ ምስለ ፈጣሪ ወበጽሑ ኀበ ደብር፤

ከዚያ በኋላ ሙሴም ከፈጣሪያ ቸው ጋር ሊገናኙ ሕዝቡን ከከተማ አውጥቶ ይዟቸው ሔደ፤ ሲሔዱም ደብረ ሲና ደረሱ፤

፲፰፤ ወደብረ ሲና ይጠይስ ኵለንታሁ ከመ ጢስ ዕቶን እምቅድመ ይረድ እግዚአብሔር ላዕሌሁ አድለ ቅለቀት ደብር ጥቀ እስመ ወረደ እግዚአብሔር ውስቴቱ በእሳት ወይወፅእ እምውስቴቱ ከመ ጢስ ዘእምዕቶን ወደንገፀ ኵሉ ሕዝብ ጥቀ፤

እግዚአብሔር ወደ እርሱ ከመውረዱ አስቀድሞ ደብረ ሲና እንደ ጉድጓድ ጢስ በዝቶ ሁለመናው ይጢያጢያስ ነበር፤ ደብረ ሲናም በእሳት ተከብቦ ሳለ እግዚአብሔር በወረደ ጊዜ፤ አንድም እግዚአብሔር በእሳትነት ወደ ደብረ ሲና በወረደ ጊዜ፤ አንድም ወበእሳት እስመ ወረደ እግዚአብሔር ውስቴታ ይላል፤ ደብረ ሲና በእሳት ተከብባ ሳለች እግዚአ ብሔር ወደ እርሷ ወርዷልና፤ አንድም እግዚአብሔር በእሳ ትነት ወደ እርሷ ወርዷልና፤ በባሕርይዋ መነዋወጥ የሌለ ባት ደብረ ሲና ያንጊዜ ፈጽማ ተነዋወጠች፤ ሕዝቡም ሁሉ ያንን አይተው ፈጽመው ደነገጡ፤

፲፱፤ ወይደምፅ ድምፀ መጥቅዕ እንዘ ይበልህ ወይኄይል ጥቀ ወሙሴ ይትናገር ወእግዚአብሔር ያወሥእ በቃሉ፤

መልሶ መልሶ የሚመታው የነጋሪቱም ድምፅ ፈጽሞ ገንትቶ በርትቶ ፈጥኖ ይሰማ ነበር፤ ሙሴም ያንጊዜ እግዚ አብሔርን ይጠይቅ ነበር፤ እግዚአብሔርም ሙሴ ለጠየ ቀው ይመልስለት ነበር፤ አንድም ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ይነጋገር ነበር፤ እግዚአብ ሔርም ከሙሴ ጋር ቃል ለቃል ይነጋገረው ነበር፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፣ ወወረደ እግዚአብሔር ውስተ ደብረ ሲና ዲበ ከተማሁ ለደብር ወዐርገ ሙሴ፣

ውስተ ደብረ ሲናና ደብረ ከተማሁ ለደብር አንድ ወገን፣ እግዚአብሔርም ያን ጊዜ ወደ ደብረ ሲና ራስ ወረደ፤ አንድም እየራሱ ለማውጣት እግዚአብ ሔር ያንጊዜ በደብረ ሲና በራሱ ወረደበት፣ ሙሴም ያንን አይቶ ወደ ደብረ ሲና ወጣ፤

፳፩፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ሑር ረድ ወአይድዖሙ ለሕዝብ ኢይቅረቡ ኀበ ደብር ለጠይቆ ኢይደቅ እምኔሆሙ ብዙኅ፣

እግዚአብሔርም ሙሴን ከዚህ ከተራራው ወርደህ እስራኤል ወዳሉበት ወደ እግዚአብሔር ደብር ሒድ፣ ይህን ነገር ለመረዳት ሕዝቡ ከእግረ ደብር ወደ መንፈቀ ደብር እንዳይ ቀርቡ፣ በዚህም ምክንያት ከእነሱ ወገን ብዙ ሰው እንዳይ ጠፋባቸው ለወገኖችህ ለእስራኤል ከእግረ ደብር ወደ መንፈቀ ደብር አትቅረቡ ብለህ ንገራቸው፤

፳፪፣ ወሠዋዕት እለ ይቀርቡ ኀቤየ ይትቀደሱ ኢየኀልቅ እምኔሆሙ፣

የእኔ አቅራቢያ ባለሟሎች የሚሆኑ ሌዋውያንም እስከ ሦስት ቀን ድረስ ከሴት እንዳ ለዩ፤ አንድም ከሕዝቡ ተለይ ተው በመንፈቀ ደብር እንዲ ቆሙ፤ አንድም ከሙሴ ከአሮን ተለይተው በመንፈቀ ደብር እንዲቆሙ፣ እነሱም ከመንፈቀ ደብር ሙሴ አሮን ወደ አሉበት ወደርእሰ ደብር ደፍረው ወጥ ተው እኔም በዚህ ምክንያት ተቈጥቼ ከእነሱ ብዙዎቹን እንዳላጠፋ ሌዋውያንን ከመን ፈቀ ደብር ወደ ርእሰ ደብር አትውጡ ብለህ ንገራቸው፤

፳፫፣ ወይቤሎ ሙሴ ለእግዚአብ ሔር ኢይክሉ ሕዝብ ዐሪገ ውስተ ደብረ ሲና አስማዕከነ ወትቤለነ ኢትልክፉ ደብረ ወባርክዎ፤

ሙሴም እግዚአብሔርን ሕዝቡ ወደ ደብረ ሲና እንዳይወጡ አዳኝህብን፤ አንድም እስመ አስማዐከነ ሕዝቡ ወደ ደብረ ሲና እንዳይወጣ አዳኝተህብ ናልና አክብሩት እንጂ ደብረ ሲናን አትንኩት፣ ወደ ደብረ ሲናም አትቅረቡ ብለኸናልና፣ ሕዝቡ ወደ ደብረ ሲና መው ጣት አይቻላቸውም አለው፣

፳፬፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ሑር ወረድ ወዕርግ አንተ ወአሮን ምስሌከ ወሠዋዕትሰ ወሕዝብ ኢይትኀየሉ ዐሪገ ውስተ ኀበ ደብር ከመ ኢያኀጕል እምኔ ሆሙ፣

እግዚአብሔርም ሙሴን አንተ ከወንድምህ ከአሮን ጋር ሁነህ



ነገ እኔ ወደ አለሁበት ወደ ተራራው ራስ ና፣ ሌዋውያን ግን በመንፈቀ ደብር ይሁኑ፣ ሕዝቡም በእግረ ደብር ይሁኑ፣ ሕዝቡ ከእግረ ደብር ወደ መንፈቀ ደብር ሌዋውያንም ከመንፈቀ ደብር፣ ወደ ርእሰ ደብር፣ አንተ እና ወንድምህ አሮንም ከርእሰ ደብር እኔ ወደ አለሁበት በርትተው ደፍረው እንዳይወጡ፣ ወከመ ኢያሕጕል እኔም ተቈጥቼ ከእነሱ ብዙዎቹን እንዳላጠፋ ቸው፣ ከዚህ ከተራራው ወርደህ ሒደህ ለሕዝቡም፣ ለሌዋውያን ካህናትም ንገራቸው አለው፤ አንድም እግዚአብሔር ሙሴን እኔ ተቈጥቼ ከእነሱ ብዙዎቹን እንዳላጠፋ፣ እነሱም ሕዝቡ ሌዋውያን ወዳሉበት ወደ መንፈቀ ደብር፣ ሌዋውያንም እናንተ ወደ አላችሁበት ወደ ርእሰ ደብር በርትተው ደፍረው እንዳይወጡ፣ ከዚህ ወርደህ ሒደህ በርትታችሁ ደፍራችሁ አትውጡ በላቸው አለው፤

፳፭፣ ወወረደ ሙሴ ኀበ ሕዝብ ወይቤሎሙ ከመዝ፣

ሙሴም ከደብረ ሲና ወርዶ ሕዝቡ ወደ አሉበት /ወደ ሠፈሩበት/ ሒዶ እግዚአብሔር አይድዖሙ ብሎ እንዳዘዘው ሕዝቡ ከእግረ ደብር ሌዋውያን ወደ አሉበት ወደ መንፈቀ ደብር፣ ሌዋውያንም ሙሴ አሮን ወዳሉበት ወደ ርእሰ ደብር፣ ሙሴ አሮንም ጌታ ወደ አለበት በርትተው ደፍ ረው እንዳይወጡ በርትተው ደፍረው አይውጡ ብሏል እግዚአብሔር ብሎ ነገራቸው፤ አንድም ሙሴ ለእግዚአብሔር ምስለኔ ሁን እንደኔ ነውና እሱው ራሱ ደፍራችሁ በርት ታችሁ አትውጡ ብሎ አዋጅ ነገረላቸው፣ መላልሶ ተናገረው ለአጽንዖተ ነገር ነው፤ ሐተታ ንጉሥ በውጭ ሳየምን የነበረውን ሹም አምኖ ሊገብ ርለት በመጣ ጊዜ በቀኝ በግራ፣ በፊት በኋላ ኃያላኑን አሰልፎ፣ ጠርሙዝ በሎታውን ከራስጌው አስቅሎ፣ በቀኝ በግራ ሰይፍ ጃግሬውን አቁሞ፣ አርዕድ አንቀጥቅጥ ልብሰ መንግሥቱን ለብሶ ግባ በሉት ይላል፣ ለእኔ ብትገዛ አንተን እንዲህ ባለ ግርማ እጠብቅ ሃለሁ፣ ለእኔ ባትገዛ ግን አንተን እንዲህ ባለ ግርማ አጠ ፋሃለሁ ሲለው ነው፣ ጌታም

www.ethiopianorthodox.org

ሕጌን ብትጠብቁ እንዲህ ባለ ሥልጣን እጠብቃችኋለሁ፣ ሕጌን ባትጠብቁ ግን እንዲህ ባለ ሥልጣን አጠፋችኋለሁ ሲል እንዲህ ሁኖ ታይቷቸ ዋል፣ ይኸውም ምሳሌ ነው፣ እሳት የፈታሒነቱ፣ ነፋስ የመንቅሒነቱ፣ ጨለማ የርቀቱ፣ ጭጋግ የዕበየ ግርማው፣ አበዊ ነሰ ይሰምዩከ ቄባረ ወዓውሎ እንዘ ደመናተ ብርሃን የዓው ዱከ በእንተ ዕበየ ሥዋሬከ እንዲል፣ ድምፀ መጥቅዕ ግርማ ምጽአቱን ያጠይቃል፤ አንድም ደብረ ሲና የእመቤታችን፣ እሳት የመለኮት፣ ጽልመት የትስብእት፣ እምደብረ ሲና ወዕአ እሳት ወጽልመት ወእም ኔከ ወዕአ አምላክ ወሰብእ እንዲል፣ ነፋስ የመንፈስ ቅዱስ፣ ጭጋግ ሰው ሲሆን ያለመመ ርመሩ፣ እንዘ ሰብእሂ መኑ ይክል ያእምሮ እንዲል፣ ድምፀ መጥቅዕ የምጽአተ ሰብአ ሰገል፣ እምደብረ ሲና ኮነ ድንጋፄ ወሀውክ ላዕለ እስራ ኤል ወእምኔከ ኮነ ድንጋፄ ወሀውክ ላዕለ ዲያብሎስ ወላዕለ ሄሮድስ ወላዕለ ሠራ ዊቱ፣ ወላዕለ አጋንንቲሁ ርኩሳን እንዲል።

## ምዕራፍ ፳

፩፣ ወነበቦ እግዚአብሔር እግዚእ ለሙሴ ዘ ኵሎ ቃለ፣

ገኸር እግዚአብሔር ለሙሴ ይህን ሁሉ ቃል ነገረው፤

፪፣ ወይቤ አነ ውእቱ እግዚእ እግዚአብሔር ዘአውፃእኩከ እምድረ ግብፅ እምቤተ ቅንየት፣

እምድረ ግብፅና እምቤተ ቅንየት አንድ ወገን፣ ጽኑ አገዛዝ ከምትገዛበት ከግብጽ አገር ያወጣሁህ ፈጥሬ የምገዛህ እግዚአብሔር እኔ ነኝ ብሎ ነገረው፤ አንድም እምድረ ግብጽ ከግብጽ አገር ወእምቤተ ቅንየት ከፈርዖንም አገዛዝ ያወጣሁህ ፈጥሬ የምገዛህ እግዚአብሔር እኔ ነኝ ብሎ ነገረው፣

፫፣ ኢታምልክ አማልክተ ወኢምን ተኒ ዘእንበሌየ፣

አሁንም ያለ እኔ ምንም ምን ሌላ ባዕድ አምላክ አታምልክ፤

፬፣ ወኢትግበር ለከ አምላከ ዘበው ስተ ሰማይ በላዕሉ ወዘበውስተ ምድር በታሕቱ ወዘውስተማያት ዘበታሕ ቴሃ ለምድር፣

ከምድር በላይ ባለ በሰማይ፣ ከሰማይም በታች ባለ በምድር፣ ከምድር በታች ባለ በውሀውም ያለ ሥነ ፍጥረትን ሁሉ አም ላክ አታድርግ፤



፭፣ ኢትስግድ ሎሙ ወኢታምልኮሙ እስመ አነ እግዚእ እግዚአብሔር አምላክከ አምላክ ቀናዒ ዘእፈዲ ኃጢአተ አበው ላዕለ ውሉድ እስከ ሣልስ ወራብዕ ትውልድ ለእለ ይጸልዑኒ፣

ፈጥሬ የምገዛህ እኔ እግዚአ ብሔር ነኝና ጣዖታቱን አምል ከህ አትስገድላቸው፣ አምላክ፣ ቀናዒ ማንሻ፤ አንድም ፈጥሬ የምገዛህ እኔ እግዚአብሔር ነኝና እስከ ሦስት እስከ አራት ትውልድ፤ አንድም ሦስትና አራት ሰባት ነው፣ ለሚጠሉኝ ሰዎች እስከ ሰባት ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት ፍዳ በልጆች የማመጣ ለአምላክነቴ የምቀና አምላክ ነኝ አለው፣ አምላክ ቀናዒ አለ፣ የሚገባ ቅናት አለና፣ አምላክ በአምላክነቱ፣ ጐልማሳ በሚስቱ፣ ንጉሥ በመንግሥቱ መቅናት የሚገባቸው ስለሆነ፤

፮፣ ወእገብር ምሕረተ ለ፲ቱ ፻ት ትውልድ ለእለ ያፈቅሩኒ ወለእለ የዐቅቡ ትእዛዝየ ወሕግየ፣

እኔን ለሚወዱ፣ ሥርዓቴን ትእ ዛዜንም ለሚጠብቁ፤ አንድም ትእዛዝየ ዘጠኙን፣ ሕግየ ኢታ ምልክን ለሚጠብቁ ሰዎች ግን እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ይቅርታዬን አደርግላቸዋለሁ አለ፣ አሁን ሺህ ትውልድ ኑሮ አይደለም በፍጹም ቁጥሮ ነው፤

፯፣ ኢትምሐል ስመ እግዚአብሔር ፈጣሪከ በሐሰት እስመ ኢያነጽሖ ለዘያነሥእ ስሞ በሐሰት፣

ስሙን በሐሰት ጠርቶ የሚ ምለውን ሰው እግዚአብሔር ከፍዳ አያነጻውምና፣ የፈጣሪህ የእግዚአብሔርን ስም ጠር ተህ በሐሰት አትማል፤

፰፣ ተዘከር ዕለተ ሰንበት ከመ ትቀድሳ፣

ሰባተኛዪቱን ቀን ቅዳሜን ልታከብራት /እንድታከብራት/ አስባት፣ አሁን አስበሃት ቅር ማለት አይደለም፣ አክብራት ሲል ነው፤

፱፣ ሰዱስ ዕለተ ትገብር ኵሎ ግብረከ ወኵሎ ትካዘከ፣

ሥራህን ሁሉ ግዳጅህንም ሁሉ በስድስቱ ቀን ሥራው፤

፲፣ ወሳብዕት ዕለት ሰንበቱ ለእግዚ አብሔር አምላክከ ኢትግበር ባቲ ወኢምንተኒ ግብረ ኢአንተ ወኢ ወልድከ ወኢወለትከ ወኢገብርከ ወኢአመትከ ወኢአድግከ ወኢኵሉ እንስሳከ ወኢፈላሲ ዘይነብር ኀቤከ፣

ሰባተኛዪቱ ቀን ቅዳሜ ፈጣሪህ እግዚአብሔር የአከበራት በዓሉ ናትና፣ ምንም ምን ሥራ አት ሥራባት፣ አንተ፣ ወንድ ልጅ ህም ሴት ልጅህም፣ ወንድ

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ባሪያህም ሴት ባሪያህም፣ ምንም ምን ሥራ አትሥሩ ባት፣ አህያህም፣ ከብትህም፣ በሬህም አይሥራ አለ፣ አታውስ ሲል ነው፣ ተሰድዶ መጥቶ በአንተ ዘንድ የሚኖር መጻተኛውም አይሥራባት፤

፲፩፣ እስመ በሰዱስ ዕለት ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ ወባሕረ ወኲሎ ዘውስቴቶሙ ወአዕረፈ አመ ሳብዕት ዕለት በበይነዝ ባረካ እግዚአብሔር ለሳብዕት ዕለት ወቀደሳ፣

ይኸ እስመ ዋዌ ነው፣ እስመ አርኖን ደወሎሙ ለሞአብ እንዲል፣ እግዚአብሔርም በስድስቱ ቀን ሰማይና ምድሩን ባሕሩንም በውሥጣቸው ያለ ፍጥረቱንም ሁሉ፤ አንድም ወኲሎ ዘውስቴቱ ይላል፣ በባሕር ውስጥ ያለውንም ፍጥረት ሁሉ ፈጠረ፣ ምነዋ /የሰማይና የምድርማ ተፈጥሮ/ ሰማይና ምድርማ የተፈጠሩ እሑድ አይደለም? ስለ ምን በሰዱስ ዕለት አለ ቢሉ፣ በስድስቱ ዕለታት የተፈጠሩ ፍጥረታት በሰማይና በምድር መካከል እስትጉቡዓን ስለሆኑ፤ አንድም እግዚአብሔር በስድስተኛው ቀን በዕለተ እሑድ ሰማይና ምድርን ፈጠረ፣ ምነው ዕለተ እሑድማ መጀመሪያ አይደለምን ስለ ምን ሰዱስ ዕለት አለው? ቢሉ ስድስተኛ ነቱ ለዕለተ ዓርብ ነው፣ ቍጥር ከየትም ቢነሱ ይመላልና፣ እንደ ሉቃስ ወንጌል ከታች ወደ ላይ እንደ ቈጠረ፣ ይህም ከዓርብ ጀምሮ ወደ ኋላ ወደ እሑድ ቈጥሮ ሰዱስ አለ በሰባተኛዪቱ ቀን ቅዳሚ ግን አረፈ አለ፣ ድካም ኑሮበት አይደለም መፍጠር ተወ ሲል ነው፣ ስለዚህም ነገር እግዚአብሔር ከስድስቱ ቀን ለይቶ ሰባተኛዪቱን ቀን ቅዳሚን አከበራት፣ ፍጥረትስ ነበረው ቀን አጣ እንዳይሉት ቀን አተረፈ፣ ቀንስ ነበረው ፍጥረት አጣ፣ እንዳይሉት ቀደሳ ወአክበራ አለ፤

፲፪፣ አክብር አባከ ወእመከ ከመ ይኩንከ ጽድቀ ወይኑኅ መዋዕሊከ በውስተ ምድር ዘይሁበከ እግዚአብሔር አምላክከ፣

ቸርነቱ ረድኤቱ ይደረግልህ ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔርም በዚህ ዓለም የሰጠህ ዘመን /ዘመንህ/ ይበዛ ዘንድ እናት አባትህን አክብር ዕርዳ፤

፲፫፣ ኢትቅትል፣

ነፍስ አትግደል፤

፲፬፣ ወኢትዘሙ፣

አትሰስን አታመንዝር፣



፲፭፣ ወኢትስርቅ፣

የሰው ገንዘብ አትስረቅ፤

፲፮፣ ወኢትኩን ስምዐ በሐሰት በላዕለ ቢጽከ፣

በባልንጀራህም ላይ ሐሰት አትመስክርበት፤

፲፯፣ ወኢትፍቱ ብእሲተ ካልዕከ ወኢትፍቱ ቤቶ ለካልዕከ ወኢገራሁቶ ወኢገብሮ ወኢአመቶ ወኢላህሞ ወኢብዕራይሁ ወኢኲሎ እንስሳሁ ዘአጥረየ አጥርዮ ቢጽከ፣

የባልጀራህን ሚስት አትመኝበት፣ አትውደድበት የባልንጀራህንም ቤቱን፣ እርሻውንም ወንድና ሴት ባሮቹን፣ ላምና በሬውን፣ ባልንጀራህ የገዛው ከብቱን ሁሉ አትመኝበት /አትውደድበት/፣

፲፰፣ ወኲሉ ሕዝብ ይሬኢ ቃለ ወብርሃነ ዘለንጳስ ወቃለ መጥቅዕ ወደብሩ ይጠይስ ወፈሪሆ ኲሉ ሕዝብ ቆመ ርኁቀ፣

ሕዝቡ ሁሉ በደብረ ሲና ቃሉን ይሰማ ነበር፣ ዘነበልባል ሲል ነው፣ ነበልባል ያለበት፣ ብርሃኑንም ያይ ነበር፣ የነጋሪቱንም ድምፅ ይሰማ ነበር፣ ተራራውም ይጤስ ነበር፣ ሕዝቡም ሁሉ ፈርቶ ርቆ ቆመ /ቆሞ ነበር/

፲፱፣ ወይቤልዎ ለሙሴ አንተ ተናገር ምስሌነ ወይትናገር እግዚአብሔር ምስሌከ ከመ ኢንሙት፣

እግዚአብሔር ለአንተ ይንገርህ እንዳንሞት፣ አንተ ለእኛ ንገረን፤ አንድም አንተ ተናገር ምስሌነ ወኢይትናገር እግዚአብሔር ምስሌነ ከመ ኢንሙት፣ ሕዝቡም ሙሴን አንተ ለእኛ ንገረን፣ እግዚአብሔር ግን እንዳንሞት አይናገር አሉት፤

፳፣ ወይቤሎሙ ሙሴ በእንተዝ ከመ ያመክርክሙ መጽአ እግዚአብሔር ኀቤክሙ ከመ ይኅድር ፍርሃተ እግዚአብሔር ላዕሌክሙ ከመ ኢተአብሱ፣

ሙሴም እናንተ ዳግመኛ እንዳትበድሉ እግዚአብሔርን መፍራት ማምለክ በእናንተ አድሮ ይኖር /ያድርባችሁ/ ዘንድ ስለዚህ ነገር እግዚአብሔር ሊፈታተናችሁ ወደ እናንተ መጣ አላቸው፤

፳፩፣ ወቆሙ ሕዝብ ርሑቀ ወሙሴ ቦአ ውስተ ብርሃን ኀበ ሀሎ እግዚአብሔር፣

ሕዝቡም ያንጊዜ ፈርተው ርቀው ቆሙ፣ ሙሴም እግዚአብሔር ወዳለበት ወደ ብርሃን መጋረጃ ገባ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፪፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ በሎሙ ለቤተ ያዕቆብ አንትሙ ርኢክሙ ከመ እምሰማይ ተናገርኩክሙ፣

እግዚአብሔርም ሙሴን ለያዕቆብ ወገኖች እናንተ ከሰማይ ወርጄ እንደ ተናገርኋችሁ አያችሁ? አለ ብለህ ንገራቸው።

፳፫፣ ኢታምልኩ አምላከ ዘብሩር ወኢታምልኩ ዘወርቅ ወኢታምልኩ አምላከ ዘዕፅ ወዘዕብን ወኢትግበሩ ለክሙ ዘከመዝ አምላከ፣

የወርቁንና የብሩን አምላክ፣ የድንጋዩንና የዕንጨቱንም አምላክ አታምልኩ፣ ይረባናል ይጠቅመናልም ብላችሁ፣ እንደዚህ ያለውን አምላክ አትሥሩ።

፳፬፣ ምሥዋዐ በዲበ ምድር ግበሩ ሊተ ወሡዑ በላዕሌሁ መባዐክሙ ወቤዛክሙ በግዐ ወላህመ በኵሉ መካን በኀበ ሰመይኩ ስምየ በህየ ወእመጽእ ኀቤከ ወእባርከከ፣

ምሥዋዑንም ጸፍጽፋችሁ ሥሩልኝ፣ ለእኔ ብላችሁ ያቀረባችሁትን መባውንም በላዩ ላይ ሠዉበት፣ ስሜንም ባስጠራሁበት ቦታ ሁሉ መቤዠቻችሁ ላሙና በጉንም ሠዉበት፣ ቤተ እስራኤል ይኸን ያደረግህልኝ እንደሆነ፣ እኔ ወደ አንተ መጥቼ አከብርሃለሁ አለ በላቸው።

፳፭፣ ወለእመ ምሥዋዐ ዘዕብን ገበርከ ሊተ ኢትንድቆ ፈጺሐከ እስመ መጥባሕተከ አንበርከ ላዕሌሁ ወአርኰስከ፣

የደንጊያ መሠዊያም ብትሠራልኝ በብረት ፈልጠህ ጠርበህ አትሥራው፣ በብረት ብትጠርበው ማርከስህ ነውና፣ ሐተታ አሁን ብረት የሚያረክስ ሁኖ አይደለም፣ ቀድሞ ደንጊያውን በብረት ጠርበው አለዝበው እያቆሙ ጣዖት ያመልኩ ነበርና በዚያ አምሳል እንዳይሆን ሲል ነው፣ ወደፊትም ለሚነሣ ትውልድ ተቀርፆ ተለዝቦ ሲገኝ ወደ አምልኮተ ጣዖት ይስባልና ሲል፤ አንድም እስመ በቤተ ባዕድ ጸአንኩከ ይላል አብነት፣ ከግብጽ መገዛት ነፃ አውጥቼ በአሕዛብ ላይ አሰልጥኜሃለሁና ሁለተኛ የተገዢነት ሥራ አትሥራ ለማለት እንዲህ አለ።

፳፮፣ ወርኰሰ ኢታዕርግ ዲበ ምሥዋዕየ ወኢትክሥት ኃፍረተከ በህየ፣

ከዚህም ወሡዑ በላዕሌሁ መባዓክሙ ብሎ ነበርና፣ ሠዋልኝም ካለኝ ብለህ ለመሥዋዕትነት ያልበቃውን የማይሆነውን ርኵሱን መሥዋዕት በመሠዊያዬ ላይ አትሠዋልኝ፣ በቤተ እግዚአብሔርም ኃፍረትክን



አትጣል፣ አንድም ኃጢአትህን በሰው ፊት ገልጠህ አትሥራው፣ ምነዋ ኃጢአቱን ሠውረህ ሥራው ማለቱ ነው? ቢሉ ሠውሮ የሠራው ኃጢአት ለሰው አብነት አይሆንበትም፣ ገልጦ የሠራው ኃጢአት ግን ለሰው አብነት ይሆንበታልና ስለዚህ ነው፣ ኃጢአትን ኃፍረት አለው በግብሩ፣ በሰው በእግዚአብሔር ዘንድ የሚያሳፍረው ስለሆነ፣ ፲ቱ ቃላትንም ከዚህ ይቈጥሯቸዋል፣ ኢታምልክ፣ ኢትምሐል፣ አክብር ሰንበቶ፣ አክብር አባከ ወእመከ፣ ኢትቅትል፣ ኢትዘሙ፣ ኢትስርቅ፣ ኢትኩን ስምዓ በሐሰት፣ ኢትፍቱ ዘጠኙ ቃላት፣ ዐሥረኛውን አፍቅር ቢጸከን፣ በኦሪት ዘሌዋውያን ክታብ የመጣ ዋል፣ ይህስ አይደለም ኢትፍቱስ ከሁሉ ይገባልና ብሎ ሐዋርያት በሲኖዶስ ዐሐይ ጨረቃን ከዋክብትን ምሥላቸውን እየራሱ ሁለት አድርገው ቈጥረዋቸዋልና ብሎ ፲ቱ ቃላት የሚላቸው እሊህ ናቸው።

## ምዕራፍ ፳ወ፩

### ግባኤ

፩፣ ወዝውእቱ ኵነኔ ዘታነብር በቅድሜሆሙ፣

በፊታቸው አጽንተህ የምታኖረው አገዛዙ ፍርዱ ይህ ነው።

አንድም ዘትገብር በቅድሜሆሙ ይላል፣ እስራኤልን ሰብስበህ በፊታቸው የምታደርግባቸው የምታደርግላቸው አገዛዙ ፍርዱ ይህ ነው፣ የምታደርግባቸው በክፉዎች፣ የምታደርግላቸው ለበጎዎች ነው፣ ዘታነብር ዘትገብር ያለውንም ወደፊት እየተረተረ ያመጣዋል፣

፪፣ ለእመ አጥረይከ ገብረ አይሁዳዊ /ዕብራዊ/ ቅንዩ ፮ቱ ክረምተ ወበሳብዕ ዓም /ክረምት/ አግዕዞ በከንቱ፣

ዘትገብር በቅድሚሆሙ ያለውን አመጣ፣ ዕብራዊ ባሪያ ብትገዛ ስድስት ዓመት ግዛው፣ በሰባተኛው ዓመት ግን ደመወዝ /መቤዠ/ ሳትቀበል ነፃ አውጣው።

፫፣ ወለእመ ባሕቲቶ አጥረይኮ ባሕቲቶ ይፃእ ወለእመ ምስለ ብእሲቱ አጥረይኮ ይፃእ ምስለ ብእሲቱ፣

ብቻውን ከገዛኸው ባሕቲቱ ይፃእ እሱ ብቻ ይውጣ፣ ከሚስቱ ጋር ብትገዛው ግን ባሪያው ከሚስቱ ጋር ነፃ ይውጣ።

፬፣ ወለእመ ወሀቦ እግዚኡ ብእሲተ ወወለደት ሎቱ ሮሰ ወአዋልደ ብእሲቱ ወደቂቁ ይትቀነዩ ለእግዚኡ ወውእቱ ባሕቲቱ ይግዓዝ፣

ጌታው ሚስት ቢያጋባው፣ ወንድ ልጅ፣ ሴት ልጅ ብትወልድለት ሚስቱ ልጆቹ ለጌታው ይገዙ፣ እሱ ብቻ ግን ነፃ ይውጣ።

www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

፭፣ ወለእመ ይቤ ገብር አፍቀርኩ እግዚእየ ወእግዝእትየ ወብእሲትየ ወደቂቅየ ወኢይፈቅድ ግዕዛነ፣

ያው ባሪያው ጌታዬንና እመቤ ቴን፣ ሚስቴንና ልጆቼን እወዳ ለሁ፣ ለብቻዬ ነፃ ልወጣ አልወድም ቢል ግን፤

፮፣ ይስዶ እግዚኡ ኀበ ቤተ ፈጣሪ ወያቅርቦ ኀበ ኆኅት ዘኀበ መድረክ ወይስቍሮ እንዘ በመስፌ ወይት ቀነይ ሎቱ ዘልፈ፣

ጌታው ወደ ቤተ እግዚአብሔር ይውሰደው፣ ወስዶም ወደ መድ ረኩ ደጃፍ (መድረኩ ወደ አለበት) ደጃፍ ያቅርበው ከዚ ያም አቅርቦ በወስፌ አፍን ጫውን ይብሳው፣ ከዚያ በኋላ ለዘለዓለሙ ይገዛ፣ ይኸውም ምሳሌ ነው፣ ገብር ዕብራዊ የአዳም፣ ስድስት ዓመት ይገዛ አለ፣ ስድስት ሺህ ዘመን ለአጋንንት ሲገዛ የመኖሩ ምሳሌ፣ በሰባተኛው ነፃ ይውጣ አለው ጌታም በሰባተኛው ሺህ አዳምን ከግብርናተ ዲያብሎስ ነፃ የማውጣቱ ምሳሌ፣ ነፃ ከወጣ በኋላ ጌታዬን እመቤ ቴን ሚስቴን ልጆቼን እወዳ ለሁ እንደገና ነፃ ልወጣ አልወድም ቢል አፍንጫውን በስዩት ለዘለዓለሙ ይገዛ አለ፣ ዛሬም ጌታ ለሰው ሙቶ ተሰቅሎ ግዕዛነ ነፍስ ካደረገለት በኋላ፣ እንደገና ተመልሶ ገሃነም እመቤቴ፣ ዲያብሎስ ጌታዬ ነው፣ ግዕዛነ ነፍስን አልወድም ቢል በመንጸፈ ደይን ወድቆ በእግረ አጋንንት ተጠቅጥቆ ለዘላለሙ ለአጋንንት ሲገዛ የመኖሩ ምሳሌ ነው፤

፯፣ ወለእመቦ ዘአስተዋሰበ ወለቶ ኢትጸጐጕ በከመ ይጸጐኃ አዕማት፣

ጌትዬው ሴት ልጁን ለባል ቢድራት፣ ሌሎች ሴቶች ባሮች ትሎት እንዲሔዱ፣ የዕብራዊ ባሪያ ሴት ልጁ ትሎት አትሒ ድበት፣ ስለ ምን ቢሉ እሱ ተገዝቶባታልና፤

፰፣ ወለእመ ኢያሥመረት ለእግዚኣ ለሊሃ ዘአምኀት ያድኅና ወለእመ ለሕዝብ ካልእ እግዚኣ ኀበ ፈቀደ ይሚጣ እስመ ለሊሃ ፈቀደት፣

ትሎት አትሒድ ብዬ ስላልኩ ግን፣ ከቤት ቀርታ ጌታዋን ደስ አሰኝታ ባታገለግል፣ ለሊሃ ዘአምኀት ያድኅና፣ ከእስራኤል ወገን እገሌ ይግዛኝ ሳለችው ተሸጣ ይግዛት፤ አንድም ከእስ ራኤል ወገን ለእገሌ ይሸጠኝ ሳለችው ይሸጣት፣ እሷ ጌታዋን ደስ አሰኝታ አለማገልገሏ መሸጥ መለወጧን ወድዳለችና፣ ጌታዋ በወደደበት ቦታ እንደ ወደደ ለሌላ ወገን ይሸጣት፤



አንድም ከመ ፈቀደ ይላል፣ ጌታዋ እንደ ወደደ ለአሕዛ ብም ቢሆን ይሸጣት፤

፱፣ ወለእመ ፈቀደ ለወልዱ የሀባ ከመ እንተ አዋልዱ ይረስያ፣

ለወንድ ልጁ ሊያጋባትም ቢወድ እንደ ሴቶች ልጆቹ ያድርግ ሳት አለ፣ ጌጥ ልብስ፣ ገንዘብ ሰጥቶ ይዳራት፣

፲፣ ወለእመ ካልዕተ ነሥአ ሎቱ ዘባ ወአልባሲሃ የሀባ፣

ኋላ ግን ተጸጽቶ ማማሽ ከማ ማዬ፣ ጋማሽ ከጋማዬ፣ የም ላት ለልጄ አጋባለሁ እንጂ ብሎ ሌላ ሚስት ቢያጭለት ግን፣ ያላት ገንዘቧን ልብሷን ጌጧን ይስጣት፤

፲፩፣ ወስምዐ ያስምዕ ላቲ ከመ ኢየዓምፃ ወዘንተ ሠለስተ ለእመ ኢገብረ ላቲ ትፃእ እምኀቤሁ ዘእንበለ ቤዛ፣

ይህንንም ሁሉ እንዳይከዳት ምስክር ያዳኝላት፣ ዘባ ወአልባ ሲሃ ወስምዐ ያስምዕ ላቲ ያለውን ነው፣ ይህነን ሦስቱን ባያደርግላት ግን መቤዣ ሳትሰጥ ከእሱ ወጥታ ትሒድ፣

፲፪፣ ወለእመቦ ዘአቍሰለ ካልዐ ካልዖ ወሞተ መቍሰሊሁ ለይሙት፣

አንዱን አንዱ አቍስሎት ቢሞት ያቈሰለው ሰው ይሙት፤ አንድም መቍሰሊሁ፣ ያ የቈሰለ ሰው ቢሞት አቍሳዩ /ያቈሰለው/ ሰው ይሙት፤

፲፫፣ ወለእመ አቍሰለ እንዘ ኢይፈቅድ ወመጠዎ እግዚአብሔር በየማነ መቍሰሊ አእምርኬ መካነ ኀበ ይትመሐፀን ቀታሊ፣

ነገር ግን ለወፍ ለዛፍ ብሎ ወርውሮት እግዚአብሔር በዚያ በወረወረው እጅ ለሞት አሳልፎ ሰጥቶት ቢሞት፣ ያ የገደለው ሰው ሀገረ ምስካይ ገብቶ እንዲማፀን ዕወቅ አለ፣ ይማፀን ማለቱ ነው፤

፲፬፣ ወለእመቦ ዘቈጸረ ከመ ይቅትል ጻላዒሁ ወተማኅፀነ ይንሥእዎ እምህየ ወይቅትልዎ፣

ዘመከረ ሲል ነው፣ ሊገድለው መክሮ ቂም ይዞ እርሱን ገድሎ ሀገረ ምስካይ ገብቶ ቢማፀን ግን፣ ከሀገረ ምስካዩ አውጥ ተው ይግደሉት፣

፲፭፣ ዘይዘብጥ አባሁ ወእሞ ይሙት መዊተ ፣

እናት አባቱን የሚመታ የሚሳ ደብ ሰው በአደባባይ ተፈርዶ በት ይሙት፤ አንድም እናት አባቱን የሚበድል ሰው የእናት የአባቱን ርስት አይውረስ፣ /አይወርስም/፤ አንድም ሰማያዊ አባቱ እግዚአብሔርን የሚክድ ሰማያዊት እናቱ ሕግን አልቀ በልም የሚል ሰው ግን ሰማያዊ ርስቱን አይወርስም አይውረስ፤

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

፲፮፣ ወለእመቦ ዘሰረቀ እምውሉደ እስራኤል ወረዲአክሙ አግባዕክሙ በላዕሌሁ ዘረከብክሙ ይሙት መዊተ፣

ከእስራኤል ልጆች አፍኖ ሸፍኖ ሰርቆ የወሰደ ሰው ቢኖር እናንተ በዕሪታ በጩኸት ተረ ዳድታችሁ ልጁን ብትመል ሱት ልጁን ያገኛችሁበት ሰው የሞት ሞት ይሙት፣ ምነዋ ያልገደለ አይሙት ይል የለም? ቢሉ በነፍስ ገድሎታልና፤

፲፯፣ ዘይረግም አባሁ ወእሞ ሞተ ለይሙት፣

አባትና እናቱን የሚሰድብ ሰው ሞትን ይሙት፣ ሐተታ እንዳለፈው፣

፲፰፣ ወለእመ ተበፀሱ ክልኤቱ ዕደው በበይናቲሆሙ ወአቊሰለ ካልኦ ለእመኒ በዕብን ወለእመኒ በበትር አስከቦ ላዕለ ምስካቡ ፣

ሁለት ሰዎች እርስበርሳቸው ቢጣሉ፣ በድንጋይም ቢሆን በበትርም ቢሆን መትቶት አንዱ አንዱን ቢያቈስለው ያ ያቈሰለውም ሰው በመኝታው ቢያስተኛው፤

፲፱፣ ወያንሶሱ ጽጉ ዘአቊሰሎ ይድኅን መቊሰሊ ባሕቱ ጽርዓቲሁ ለየሀቦ ወአስቦ ለየአስቦ ለዓቃቤ ሥራይ፣

የቈሰለው ሰው በኍ ሁኖ በአጥር ጥግ፣ /በአደባባይ/ ቢመላለስ ከዚያ በኋላ ቢሞት ያቈሰለው ሰው ከሞት ይዳን፣ ነገር ግን ታሞ ተኝቶ ከሞት ቢድን፣ ከሥራ የቦዘነበትን ዋጋ ለባለመ ድኃኒትም የሰጠውን ዋጋ ይስጠው፤ አንድም ያቈሰለ በትን ካሣውን ይስጠው፤

፳፣ ወለእመቦ ዘአቊሰለ ገብሮ ወእመኒ አመቶ በበትር ወሞተ ይመውት መዊተ መቊሰሊ፣

ወንድ ባሪያውን ሴት ባሪያው ንም ቢሆን በበትር መትቶት ከሴት ከወንድ ባሪያው አንዱም አንዱ ቢሞት ያቈሰለው ጌታው ይሙት፤

፳፩፣ ወለእመ በጽሐ አሐተ ዕለተ ወለእመ በሳኒታ ይድኅን እመዊት እስመ ዘዚአሁ ብሩር ውእቱ፣

የቈሰለው ባሪያው በአንድ ቀን ቢሞት ያ ያቈሰለው ጌትየው ይሙት፣ አድሮ ውሎ ቢሞት ግን ያ ያቈሰለው ጌትየው ከሞት ይዳን፣ ብሩ ገንዘቡ የእርሱ ስለሆነ፣ በአንድ ቀን ቢሞት ጌትዮው ይሙት አለ፣ በትሩ ቢበስል ነው፣ አድሮ ውሎ ቢሞት ግን ጌትየው ከሞት ይዳን አለ፣ በትሩ ባይበስል ነው፣ ይኸስ አይደለም፣ በትሩ በስሎ ውሎ አድሮ የሚሞት በትሩም ሳይበስል በአንድ ቀን የሚሞት አለና ብሎ፣ ይድኅን እመዊት እስመ ዘዚአሁ ብሩር ውእቱ ያለበት ምክንያቱ አልታወቀም፤



፳፪፣ ወለእመ ተበፀሱ ክልኤቱ ዕደው በበይናቲሆሙ ወአቊሰሉ ብእሲተ ጽንስተ ወአድኃፀት ወምስለ ሰብእ አልቦ የነሥርዎ ለእመ ዕርቀ ተፀረቀ ምስለ ምታ እንዘ ያስተበቊዕ አልቦ ሞት ወለእመ አድኅነት እንዘ ምሱል ውእቱ ይፍዲ መንፈሰ፣

ሁለት ሰዎች እስበሳቸው ቢጣሉ፣ አንዱም አንዱ ሲታገሉ ወድቆ የፀነሰችውን ሴት ቢያቆስላት፣ እሷንም ቢያስወርዳት ተሥዕ ሎተ መልክዕ ያልተፈጸ መለት ቢሆን እስከዚያው ድረስ አሥረው አግዘው ያኑሩት፣ አማላጅ ልከ ተነሥቶ ወድቆ ከባልዋ ጋር ቢታረቅ ግን /አይሙት/ ሞት የለበትም፣ ተሥዕሎተ መልክዕ ከተፈጸ መለት በኋላ ግን ቢያስወርዳት ይሙት ይኸስ አይደለም፣ ተሥዕሎተ መልክዕስ የሚፈ ጸም በዓርባ ቀን ነውና፣ ብሎ መጽነሷ ባይታወቅ ይዳን፣ መጽነሷ ቢታወቅ ግን ይሙት አለ፤

፳፫-፳፬ ፣ መንፈስ ፍዳ መንፈስ፣ ዓይን ፍዳ ዓይን፤ ስን ፍዳ ስን፣ እድ ፍዳ እድ፣ እግር ፍዳ እግር፣

አያይ፡ ሥርዓት ይሠራል፣ ነፍስ ቢገድል እሱ ይሙት፣ ዓይን ቢያፈስስ ዓይኑ ይፍሰስ፣ ጥርስ ቢያረግፍ ጥርሱ ይርገፍ፣ እጅ እግር ቢሰብር እጅ እግሩ ይሰበር፤

፳፭፣ ውዕየት ህየንተ ውዕየት ፍቅዓት ህየንተ ፍቅዓት ቊስል ህየንተ ቊስል፣

ቢያቃጥል እሱ ይቃጠል፣ ቢገምስ ይገመስ፣ ቢያቆስል እሱ ይቊሰል አለ፤

፳፮፣ ወለእመቦ ዘአቊሰለ ዓይነ ገብሩ ወለእመሂ ዘአመቱ ወአየሮሙ ያግዕዞሙ ቤዛ ዓይኖሙ፣

ጌትየው የወንድ ባሪያውን፣ የሴት ባሪያውን ዓይን አቈስሎ ዕውር ቢያደርጋቸው፣ ዓይና ቸውን ስላጠፋቸው ፈንታ ነፃ ያውጣቸው አይግዛቸው አለ፤

፳፯፣ ወለእመኒ ሰበረ ጥረሰ ወስነ ዘገብሩ ወዘአመቱ ያግዕዞሙ ቤዛ ስኖሙ፣

ጌትየው የወንድ ባሪያውን፣ የሴት ባሪያውን ጥርስ መንጋጋቸውን ወስነ የፊት ጥርሳቸውን ቢያወ ልቃቸው፣ የፊት ጥርሳቸውን መንጋጋቸውን ስለ አወለቀ ባቸው ፈንታ ነፃ ያውጣቸው፣ አይግዛቸው፤

፳፰፣ ወለእመ ወግዐ ላሕም ብእሴ ወብእሲተ ወቀተለ፣ በዕብን ይውግ ርዎ ለላሕም ወሥጋሁ ኢይብልዑ ወበዓለ ላሕሙ ይድኃን እምኃጢ አት፣

በሬ /ላም/ ወግሾቶ (ጐፍቶ) ወንድም ሴትም ቢሆን በቀንዱ ወግቶ ቢገድል /ላሙን/ በሬ ውን በደንጊያ ወግረው ይግደ

www.ethiopianorthodox.org

ሉት፣ ሥጋውንም አይብሉት አለ ለማጸየፍ ነው፣ ባለ በሬው ግን አይሙት ይዳን፤

፳፱፣ ወለእመ ወግዐ ላሕሙ ከመ ትማልም ወሣልስት ወአስምዑ ቦቱ ለእግዚኡ ወኢአማሰኖ ወቀተለ ብእሴ ወእመኒ ብእሲተ ላሕሞ ይውግሩ ወእግዚኡኒ ይቅትሉ፣

በሬው ዛሬም፣ ትናንትም፣ ነገም ሣልስትም እያለ፣ ሰው ቢወጋ ይህነን በሬህን ሽጠው ለውጠው እረደው ብለው ለጌታው ቢያዳኙበት፣ ባይሸጠው፣ ባይለውጠው፣ ባያርደው፣ በሬው ወንድም ቢሆን ሴትም ቢሆን ከሰው ወገን ወግቶ ቢገድል፣ ላሙን በድንጋይ ወግረው ይግደሉት፣ ጌታውንም ይግደሉት፣ አልሸጥ አልለውጥ አላርድ ብሎ ነፍስ አስገድሏልና፣ ተናካሽ ውሻህን ተዋጊ በሬህን ያገ እንዲሉ፣

፴፣ ወለእመ ሰአለ ቤዛ ርእሱ የሀብ ቤዛ መንፈሱ እምቃለ ተከህሎ፣

የነፍስ ዋጋ ልስጥ ተዉኝ አትግደሉኝ ብሎ ቢለምን ግን ይህን ያህል እሰጥሃለሁ ያለውን፤ አንድም መጠነ ተከህሎ ይላል የተቻለውን ያህል ለሰውነቱ ቤዛ ይስጥ፤

፴፩፣ ወለእመ ወግዐ ሮሰ ወአዋልደ ዘአየኑ ያስተዋህቡ፣

በሬው ወንድ ልጅ ሴት ልጅ ቢወጋ እናት አባት የገመገሙትን፣ ሽማግሎች ያሰጡ፤ አንድም ሽማግሎች የገመገሙትን ለእናት ለአባት ይስጡ፤

፴፪፣ ወለእመ ወግዐ ገብረ አው አመተ ፴ ብሩረ የሀብ ለእግዚአሙ ወላሕሙ ይትወገር፣

ሴት ባሪያ ወንድ ባሪያም ቢወጋ፣ ባለበሬው ለባሮቹ ጌታ ፴ ብር ይስጥ፣ በሬውም በደንጊያ ተወግሮ ይሙት፤

፴፫፣ ወለእመቦ ዘከሠተ አዘቅተ ወለእመኒ ከረየ ግበ ወኢከደኖ አፉሁ ወወድቀ ውስቴቱ ላሕም ወእመኒ አድግ፣

አንዱም አንዱ የቀደመ የኖረ ጉድጓድ ቢከፍት፣ ሌላ አዲስ ጉድጓድም ቢቈፍር፣ አፉን ባይገጥመው /ላሙም/ በሬውም ቢሆን አህያውም ቢሆን ከዚያ ወድቆ ቢሞት፤

፴፬፣ እግዚአ አዘቅት ይፍዲ ብሩረ ወገደላሁ ውእቱ ይንሣእ፣

የጉድጓዱ ጌታ ለባለ በሬው ለባለ አህያው በተገመገመ ዋጋውን ይክፈል፣ ወደቃውን ግን እሱ ይወሰድ፣



፴፭፣ ወላሕመ ብእሲ ለእመ ወግዐ ላሕመ ዘካልኡ /ላሕመ ካልኡ/ ወሞተ ይሢጥዎ ለውእቱ ላሕም ሕያዎ ወይትካፈሉ ሤጦ ወገደላሁኒ ይትካፈሉ፣

የአንዱም የአንዱ ሰው በሬ የአንዱም የአንዱን ሰው በሬ ወግቶ ቢገድለው፤ አንድም ላሕመ ካልአ ይላል፣ አብሮት የተሰማራውን በሬ ወግቶ ቢገድለው፣ በሬው የሞተበት ሰውና በሬውን የገደለበት ሰው በሬውን ሸጠው ዋጋውን ይካፈሉ፣ /ውድቃኑንም/ ወደቃውንም ይካፈሉ፤

፴፮፣ ወለእመ ወግዐ ላሕሙ ከመ ትማልም ወሣልስት ወአስምዐ ቦቱ ይፍዲ ላሕመ ተክለ ላሕሙ ወገደላሁ ውእቱ ይንሣእ፣

በሬው ዛሬም ትላንትም ነገም ሣልስትም እያለ የአንዱን በሬ ወግቶ ቢገድል ያ ባለ በሬው ሸጠው፣ ለውጠው፣ እረደው፣ እንዲህ አደረገኝ ብሎ ቢያዳኝበት፣ ይኸን ከነገረው በኋላ ሳይሸጠው ሳይለውጠው ሳያርደው ቀርቶ በሬው ወግቶ ቢገድልበት ባለ በሬው ስለ ሞተበት /ላም/ በሬ ፈንታ በተገመገመ በሬ ይክፈለው /ውድቃኑንም/ ወደቃውንም እሱ ይውሰድ።

# ምዕራፍ ፳ወ፪

፩፣ ወለእመቦ ዘሰረቀ ላሕመ ወእመሂ በግዐ ወጠብሖ ይትክል ህየንተ አሐዱ ላሕም ትኅምስተ ወህየንተ አሐዱ በግዕ ትርብዕተ፣

ላም በግ ሰርቆ ያረደ ሰው ቢኖር አንድ ላም ስለ ሰረቀ አምስት ላም ይክፈል፣ አንድ በግ ስለ ሰረቀ አራት በግ ይክፈል አለ፣ አንድ በግ በሰረቀ አራት በግ ይክፈል አለ፣ በግ በልብስም በምንም ይሠወራል፣ ላም ግን በልብስ አይሠወርም ድፍረት ነውና፤

፪፣ ወከሪዮ ሰራቂ ለእመ ቈስለ ወሞተ ኢይከውኖ ቀቲለ ለዘቀተለ፣

ሌባ ሌሊት ቤት ሲቈፍር ተገኝቶ ቈስሎ ቢሞት፣ ለገደለው ሰው ዕዳ አይሆንበትም፣ አውሬ ስለ ገደለው ቊጥር ነው፤

፫፣ ወለእመሰ ሠረቀ ፀሐይ ላዕሌሁ ደሙ ወይሙት ዘቀተሎ ለብእሲ ዘሰረቀ ለእመ አኃዝዎ ወለእመ አልቦ ውስተ እዴሁ ይሠየጥ ህየንተ ዘሰረቀ፣

ፀሐይ ከወጣ በኋላ ቢገድለው ግን ፣ የደሙ ፍዳ በእሱ ላይ ነው፣ የገደለውም ሰው ይሙት፣ ይህስ አይደለም፣ ፀሐይ ያለው ሰው ነው፣ ሰው ሳያየው ቢገድለው አይሙት ይዳን፣ ሰው ካየው በኋላ ግን ይሙት አይዳን፣

www.ethiopianorthodox.org

ሌባውን ሰው ሰርቆ ሲሔድ አግኝተው ቢይዙት፣ ከእጁ ገንዘብ ቢታጣበት፣ ስለ ሰረቀው ገንዘብ ፈንታ ይገዛ፤

፬፣ ወለእመ አኀዘዎ ወረከቡ በእዴሁ ለዘሰረቀ እመሂ ላሕመ ወእመሂ አድገ ካዕበተ ይፍዲ፣

ሲሰርቅ አግኝተው ቢይዙት በሌባውም እጅ ገንዘብ ቢያገኙበት /ገንዘብ፣ ያለውን/ ላምም ቢሆን አህያም ቢሆን በአንድ ሁለት ይክፈል፤ አንድም ዘሰረቀ ላሕመ አው በግዐ አው አድገ ይላል፣ የሰረቀው ላሙን በጉን አህያውን ቢሆን ሰርቆ ሲሔድ ከያዙት በአንድ ሁለት ይከፍላል፤

፭፣ ወለእመቦ ዘአብልዐ ገራህተ ሰብእ እንስሳሁ ወዓፀደ ወይን ዘባዕድ ይርአይዎ /ይትረዐይዎ/ ወአስማሮ ይፍዲ ወለእመስ አግመረ ገራህተ እንዘ ያበልዕ በሠምረ ገራህቱ ይፍዲ ወለእመኒ ዓፀደ ወይን በሠምረ ዓፀደ ወይን ይፍዲ፣

የሰውን እርሻ ከብቱን ሰድዶ ያስበላ ሰው ቢኖር፣ የሌላውንም ሰው የወይን ቦታ ያስበላ ሰው ቢኖር፣ እርሻውን ዙረው ይገምግሙት፣ በበጀው እህል፣ በበጀው ተክል ልክ ይክፈል፣ እንዲህ ስላለ ግን የተበላው እርሻ፣ የተበላው ተክል ተሰፍሮ

ታይቶ በዚያ ልክ ነው፣ ከብቱ እርሻውን ጨርሶ ቢበላው ግን የወይኑንም ቦታ ጨርሶ ቢበላው፣ በኀረቤቱ እርሻ ልክ በኀረቤቱ የወይን ቦታ ልክ ይክፈል፤

፮፣ ወለእመ ወፅአ እሳት ወአኀዘ ገዳመ ወአውአየ ዐውደ ወእመሂ ክምረ ዘአውአየ ይፍዲ፣

እሳት ከየትም ተነሥቶ ምድረ በዳውን፣ አንድም መንጠሩን ቢያቃጥል፣ ዓውድማውን ቢያቃጥል ክምሩንም ቢያቃጥል ያ ያቃጠለ ሰው ይክፈል፤

፯፣ ወለእመቦ ዘአዕቀበ ብሩረ ወእመሂ ንዋየ ወተሰርቀ ለዘአዕቀብዎ ወረከቦ ለዘሰረቆ ይፍዲ ካዕበተ፣

የብር አደራ ያኖረ ሰው ቢኖር፣ ሌላም ገንዘብ አደራ ያኖረ ሰው ቢኖር፣ አደራ ያኖሩበት ሰው ገንዘቡ ቢሰረቅበት ሌባውን ፈልጎ ቢያገኘው ሌባው በአንድ ሁለት ይክፈል፤

፰፣ ወለእመ ኢተረክበ ሰራቂ ለይሑር በዓለ ቤት ቅድመ ፈጣሪ ወይምሐል በማኅፀን ዘአማኅፀንዎ ከመ ኢተኬነወ ወከመ ኢቄጸረ፣

ሌባው ተፈልጎ ባይገኝ ግን ባለ ገንዘቡ ወደ ቤተ እግዚአ ብሔር ይሒድ፣ በሆነው ነገር ሁሉ በአደራ ወግ በተመራ መሩት ገንዘብ ይማል፤



፱፣ እመሂ ላሕመ ወእመሂ አድገ ወእመሂ በግዐ በዘኃሠሥዎ በማኅፀን በዘኮነ ከዊኖ በህየ ይኄልቆዎሙ በበይናቲሆሙ ወዘገደፈ ካዕበተ ይፍዲ ለማዕቀቢሁ፣

በግም ቢሆን አህያም ቢሆን ላምም ቢሆን ተተንኮሎዬም አልሰረቅሁትም ብሎ በአደራ ወግ ይማል፣ በዚህ ነገር ደግሞ ባለ አደራውንና ባለገንዘቡን ያቈጣጥሯቸው ያ የጠፋበት ባለ አደራው በአንድ ሁለት ይክፈል፤ አንድም ዘገደፈ ይህን ወስደሃል ይህ ቀርቶብኛል ያለውን ይክፈል፤ አንድም ይህን ወስጃለሁ፣ ይህ ቀርቶ ብሃል ያለውን ይክፈለው፤ አንድም ዘገደፉ ይላል፣ ይኄል ቆዎሙ ብሎ ነበርና፣ ሽማግ ሌዎች ያቈጣጠሯቸውን ገንዘብ ለባለአደራው ይክፈል፤

፲፣ ወለእመቦ ዘወሀበ ብዕራይሁ አው ላሕሞ እመሂ በግዖ ዘኮነ እምእንስሳሁ ወሞተ ቈሲሎ ወእመሂ ማህረኩ ቦቱ ወአልቦ ዘአእመረ ሎቱ፣

በሬውን ከከብቱም ወገን በጉን፣ ላሙን ያዋሰ ሰው ቢኖር ያ ያዋሰው ከብቱ በሔደበት ቈስሎ ቢሞት ወራሪ ወታደሮ ችም ማርከው ቢወስዱበት የሚያውቅለት ምስክር ባይኖር፤

፲፩፣ መሐላ ዘእግዚአብሔር ተርፈ ማዕከሌሆሙ ከመ ተፈቲዎ ኢተኬነወ ተማኅፃኒ ወበበይነዝ ኢይፈዲ ዘተማኅፀኖ፣

ባለ አደራው ገንዘብኑቱን ወድዶ እንዳልተተነኰለው በመካከላ ቸው እግዚአብሔር የአዘዘው መሐላ ተሠርቷል ታገዟል፣ በእውነት ነገር ስለ ማለም ባለ አደራው አይከፍልም፣

፲፪፣ ወለእመ ሰረቅዎ ዘአዕቀብዎ ይፍዲ ለዘአዕቀቦ፣

ሳይጠብቀው ሌቦች ሰርቀው ቢወስዱበት፣ አደራ የተቀመ ጠበት ሰው ለባለአደራው ይክፈል፣

፲፫፣ ወለእመኒ አርዌ አኀዞ በገዳም ይመርሀ ገደላሁ ወኢይፈዲ፣

የአደራውን ከብት በምድረ በዳ አውሬ ቢገድልበት፣ መርቶ ወስዶ ወደቃውን ያሳይ፣ እሱ ግን አይክፈል፤

፲፬፣ ወለእመ ተውሕሰ ብእሲ እምቢፁ ወተሰብረ ወሞተ ወኢሀሎ አውሐሲ እግዚእ ንዋይ ይፍዲ /ይፈዲ/፣

ሰው ከባልንጀራው ፈረስ በቅሎ አህያ ቢዋስ፣ በጎዳና ተሠብሮ ቢሞት የአዋሰው ባለገንዘቡ /የገንዘቡ/ ጌታም ባይኖር ይክፈል፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፭፤ ወለእመ ሀሎ እግዚኡ ኢይፈዲ ወለእመ ገባኢሁ ውእቱ አስቦ ይፍዲ፤

የገንዘቡ ጌታ ቢኖር ግን አይክ ፈል፤ እንዲህ ማለቱ ከጎንደር እስከ ፍርቃበር እስከ ይፋግ ብሎ አውስታል፤ አውሶት ብትሞት፤ አንድም ከጐንደር እስከ ወገራ ብሎት ከዚያ ወዲህ ብትሞት አይክፈል፤ ከወገራ እስከ ሰቈጣ፤ ከይፋግ እስከ ደብረ ታቦር አልፎ ወስዷት ብትሞት ግን ይክፈል፤ አንድም ለእመ ሀሎ ወለእመ ኢሀሎ አለ፤ ከብት አውሶት አብረው ገበያ ሒደዋል፤ ከስርጥ ጎዳና ሲደርሱ እሷን በመሄሪያ ውሰዳት፤ እኛ በስ ርጡ እንውጣ አለው፤ ከአንተስ እኔ ጉልበቷን አውቀዋለሁ፤ በዚህ በስርጡ ትሒድ ብሎ በስርጡ ስትሔድ ወድቃ ብትሞት ይክፈል፤ ባለቤቱ በአዘዘው በመሄሪያ ስትሔድ ወድቃ ብትሞት ግን አይክ ፈል፤ ይኸን ያደረገ ምንደኛው ቢሆን ግን ደመወዙን ብቻ ይክፈል፤

፲፮፤ ወለእመቦ ዘአስሐታ ለድንግል እንተ ኢኮነት ፍሕርተ ወሰከበ ምስሌሃ ይንሥኣ ትኩኖ ብእሲተ፤

ያልታጨችው ድንግሊቱን ልጅ አፍኖ ሸፍኖ ቢደርስባት፤ ሚስት ትሁነው፤ ይካተታት ማለት በግድ ሚስት ትሁነው፤

፲፯፤ ወለእመ አበየ አቡሃ ከመ ኢየሀቦ ሕዒሃ የሀብ ለአቡሃ ከመ የሐዕይዋ ለድንግል፤

አባቷ ልጄን ለእሱ አልሰጠ ውም ብሎ እምቢ ቢል ግን ድንግሊቱ ልጅ የምትታጭ በትን ማጫ፤ አንድም እንደም ትታጨው መጠን ለአባቷ ማጫዋን ይስጥ፤

፲፰፤ ወምስለ ዘሥራይ ኢትትዋሰቡ፤

ተጋቡ ካለን ብላችሁ ግን ከሚር ተኛው ጋር አትጋቡ፤ አንድም ወዘሥራይ አይሕየው ይላል፤ ሥር የሚምስ፤ ቅጠል የሚበ ጥስ ሚርተኛ ሰው ቢኖር በድንጋይ ተወግሮ በእሳት ተቃጥሎ ይሙት አይዳን፤

፲፱፤ ወኵሉ ዘየሐውር ኀበ እንስሳ ሞተ ለይሙት፤

ከእንስሳት የሚደርስ ይሙት፤ ከፈረስ ከበቅሎ ከአህያ ከእንስሳት ሁሉ የሚደርስ ሰው ቢኖር በድንጋይ ተወግሮ፤ በእሳት ተቃጥሎ ይሙት፤

፳፤ ዘይሠውዕ ለአማልክት ዘእንበለ ለእግዚአብሔር ባሕቲቱ ይሠረው፤

ለእግዚአብሔር ብቻ ነው እንጂ እግዚአብሔርን ትቶ ለጣዖት



የሚሠዋ ሰው ቢኖር በድንጋይ ተወግሮ በእሳት ተቃጥሎ ይሙት፤

፳፩፤ ወኢታኅሥሙ ለግዩር ወኢታ ጥቅዖ እስመ አንትሙኒ ግዩራነ ኮንክሙ በምድረ ግብጽ፤

እናንተም በግብጽ አገር መጻተ ኞች ሁናችሁ ተጨንቃችሁ ነበርና /ነበራችሁና/ መጻተኛ ውን አታስጨንቁት፤ በመጻተ ኛውም ክፉ ሥራ አትሥሩበት፤

፳፪፤ ወለኵሉ ዕቤራት ወለዕጓለ ማውታ ኢታኅሥሙ፤

በባልቴቶችም እናት አባት በሌላቸው በድኖች ልጆችም ክፉ ሥራ አትሥሩባቸው፤ ኩን ጠቢበ ለእድውከ እንዲል፤ ማቴ፤፳ ቍ.፳፩ ፤

፳፫፤ ወለእመ አኅሠምክሙ ወጸርሑ ወአውየዉ ኀቤየ ሰሚዐ እሰምዕ ገዓሮሙ፤

እናንተ በእነሱ ክፉ ሥራ ሠርታችሁባቸው፤ እነሱም ወደ እኔ ቢጮሁ ጩኸታ ቸውን ፈጽሜ እሰማለሁ፤

፳፬፤ ወእትመዐዕ በመዓትየ ወእቀ ትለክሙ በሐፂን ወይከውና አንስቲ ያክሙ መበለታተ ወውሉድክሙ ዕጓለ ማውታ፤

እኔም ተቈጥቼ በጦር አጠፋ ችኋለሁ፤ እናንተም አልቃችሁ ሚስቶቻችሁ ረዳት፤ ልጆቻችሁ አባት አጥተው ድኖች ይሆናሉ፤ አንድም መካናተ ይላል፤ እናንተ ሙታችሁ፤ በኃዘን በድንጋጤ ሚስቶቻችሁ መካኖች ይሆናሉ፤ አንድም የወላድ መካን ይሆናሉ፤

፳፭፤ ወለእመ ለቃሕከ ብሩረ ለነዳይ ሕዝብከ ኢታጥቆ ወኢትትረደዮ፤

ለድኃ ወገንህ ብር ብታበድረው አስጨንቀህ አራጣ አትክፈ ለው፤ አንድም አስጨንቀህ አራጣ አትቀበለው፤

፳፮፤ ወለእመ አንገከ ልብሰ ቢጽከ ዘእንበለ ይዕርብ ፀሐይ አግብእ ሎቱ እስመ ይእቲ ባሕቲታ አራዙ፤

የባልንጀራህን ልብስ መያዣ አድርገህ ብትይዘበት፤ ለብሷት የሚያድር እሷ ብቻ ናትና ፀሐይ ሳይገባ ልብሱን መልስ ለት፤

፳፯፤ ወኃፍረት ሎቱ እስመ አልቦ በዘይበይት ወለእመ ገዓረ ኀቤየ ፍጡነ እሰምዖ እስመ መሐሪ አነ፤

ኃፍረት ሎቱ ማንሻ፤ አንድም ለብሷት የሚያድር ልብሱ እሷ ብቻ ስለሆነች ለብሶ በሚያድር ገንዘብ ለብሶት የሚያድር ሌላ ልብስ የለውምና ልብሱን ገፍፈህ ራቁቱን ብታሳድረው ኃፍረት ነው፤ አይገባም መልስለት፤ አንተ ግን በእሱ ግፍ ሠርተህበት ልብሱንም ገፍፈኸው አድረህ እሱ ወደ

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

እኔ ሬጩሆ ቢለምን ሬጩኸቱን ፈጥኜ እሰማዋለሁ፣ እኔ ርኅሩኅ አምላክ ነኝና እንደ አንተ ጨካኝ አይደለሁምና፤

፳፰፣ አማልክተ ኢትሕሚ ወለመ ኰንነ ሕዝብከ እኪተ ኢትበሎ ፣

ካህናቱን አትማ፣ አትጥላ በወገኖችህ የተሾመውንም ሹም /ገዥ/ በእሱ ዘመን መከራ ቢመጣብህ የእገሌ ዘመን ዘመን አይሁን ብለህ አትንቀፈው፤

፳፱፣ ከተማ ዓውድከ ወዓውደ ዓውድከ ኢተአሐር ወበኵረ ውሉድከ ትሁበኒ ሊተ፣

ፍሬልባውን፤ አንድም ከተማ ዓውደ ዓውድከ ይላል፣ በዓውድማው መካከል ያለ ፍሬልባውን፤ አንድም ከተማ ዓውድከ፤ ወዘዓውድከ ይላል፣ ከተማ ዓውድከ ፍሬልባ ውን ወዘዓውድከ፤ በአውድ ማው ዙሪያ ያለውን አትጥ ረገው የልጆችህንም /የልጅህ ንም/ ከልጅህም በኵር በኵሩን ለኔ ስጠኝ፤

፴፣ ከማሁ ትገብር ሊተ ላሕመከ ወበግዓከ ወአድገከ ሰቡዐ ዕለተ ይንበር ኀበ እሙ ወአመ ሳምንት ዕለት ትሁበኒ ሊተ፣

በኵረ ውሉድከ ትሁበኒ ሊተ ብሎ ነበርና፣ የልጅህን በኵር እንደሰጠኸኝ የላምህን የበግህን የአህያህን በኵር ስጠኝ፣ ስጠ ኝም ስለአልኩህ፣ ዕለቱን ተወ ልዶ አይደለም፣ ሰባት ቀን ሲጠባ ከእናቱ ጋር ይሰንብት፣ በስምንተኛው ቀን ለእኔ ትሰጠ ኛለህ አለ፣ ሹም አይቶት ይደግ፤

፴፩፣ ወትከውኑኒ ዕደወ ቅዱሳነ ወሥጋ ገደላ አርዌ ኢትብልዑ ለከልብ ግድፍዎ፣

ይኸን ያደረጋችሁልኝ እንደ ሆነ የከበራችሁ ወገኖቼ ትሆ ናላችሁ፣ የአውሬውን ትራፊ ውን ወደቃውን ሥጋም አት ብሉ ይህስ ምን ጊዜም አይበ ላምና ብሎ አውሬ ነክሶት የሞተውን /ወደቃውን/ አት ብሉ አላ ያለበት ነው፣ ለውሻ ጣሉት እንጂ።።

## ምዕራፍ ፳ወ፫

### ገባኤ

፩፣ ወስምዐ ዘሐሰት ኢትሰጠው ወኢትንበር ምስለ ዘይዔምፅ ከመ ኢትኩን ስምዐ በዓመፃ፣

ወስምዐ ሐሳዊ ወስምዐ ሕስው ወስምዐ ዘሕስው ሲል ነው፣ የሐሰተኛውን ሰው ምስክርነት አትቀበል፤ አንድም እንዳለ ይሆናል፣ የሐሰቱን ነገር ምስክ ርነቱን አትቀበል፤ አንድም ስምዐ በሐሰት፣ በሐሰት የመሰ ከረውን ምስክርነት አትቀበል፣



በእውነትና በሐሰት መመስ ከሩ በምን ይታወቃል ቢሉ ዳኛ ሁኖ መሾሙ ይኸን ሊመ ረምር ነውና፣ ይኸን ባለው ውዴተ ዘሐሰት ኢትሰጠው ይላል፣ ዘሕስው ሲል ነው፣ የሐሰተኛውን ሰው ነገር ሥራ አትቀበል፣ የእውነተኛውን ሰው ነገር ሥራት ይቀበል ማለቱ ነው? ቢሉ እውነተኛማ ከሆነ ጥንቱንስ መች ነገር ይሠራል፤ አንድም ውዴተ ዘሐሰት ውዴተ በሐሰት ይላል፣ በሐሰት የመጣውን ነገር አት ስማ፤ ነገር መሥራቱ በእው ነትና በሐሰት መሆኑ በምን ይታወቃል ቢሉ፣ ደግ ሰው የሆነ እንደ ሆነ እገሌ ወዳጄ ነው አይለኝም ይላል፣ ደግ ዳኛ የሆነ እንደ ሆነ ሁለቱንም ጠርቶ አጋጥሞ ያረታታልና እንዲህ ሳታደርግ የሐሰተኛ ነገር እውነተኛ ነው ብለህ አትቀበል፣ በሐሰት እንዳት መሰክር፤ አንድም ከመ ኢትኩን ስምዐ መዓምፀ ይላል ሐሰተኛ ምስክር እንዳትሆን ከሐሰተኛ ምስክር ከሐሰተኛ ዳኛ ጋር አብረህ አትቀመጥ፤

፪፣ ወኢትደመር ምስለ ብዙኅ ለዓምፆ ወኢትትወሰክ ምስለ ብዙኅ ለገሚዐ ፍትሕ፣

ሐሰት ለመመስከር ሐሰት ለመፍረድ ከብዙ ሰዎች ጋራ በነገር በምክር በቦታ አንድ አትሁን፤ ፍርድም ለማገድላት ከብዙ ሰዎች ጋር አትጨመር፤

፫፣ ወለነዳይ ኢትምሐሮ በፍትሕ፣

በፍርድ ጊዜም ድኃ ነው ብለህ ለድኃው አትዘንለት፣ አትራ ራለት፤

፬፣ ወለእመ ረከብከ ላሕመ ጸላዒከ ወእመሂ አድጎ ዘተገድፈ ሚጥ ወአግብእ ሎቱ፣

የጠላትህን የወደቀ፣ ገንዘቡን አንድም የጠፋ አህያውንና ላሙን ብታገኝ ከዚህ አለ ብለህ መልስለት፤

፭፣ ወለእመ ርኢከ አድገ ጸላዒከ ዘተነየሎ ፆሩ /ዙነየሎ/ ኢትትዓ ደዎ አላ ተራድኦ ምስሌሁ /አላ አስተላዕል ምስሌሁ/

ሸክሙ ያጋደለበት የጠላትህን አህያ በጎዳና ብታየው፤ አንድም የጠላትህን አህያ ሸክሙ /ፍሬነቱ/ አጋድሎበት በጎዳና ብታየው አልፈኸው አትሒድ፣ አጫጭነው እንጂ፤

፮፣ ወኢትሚጥ ፍትሐ ነዳይ ወበፍ ትሕ ኢተዓምፅ፣

ድኃውንም ድኃ ነው ብለህ እውነቱን በሐሰት አትለውጥ በት፤ አንድም ሐሰቱን በእውነት አትለውጥለት፣ በማናቸውም ፍርድ ሁሉ ሐሰት አትፍረድ፤

www.ethiopianorthodox.org

፯-፰፣ ወእምኵሉ ፍትሕ ዘዓመፃ ተገኃሥ ዘአልቦ ጌጋይ ወጻድቀ ኢትቅትል ወኃጥአ ኢታድኅን፣ ወሕልያነ ኢትንሣእ እስመ ሕልያን የዐውሮሙ አዕይንተሆሙ ለጠቢባን ወይመይጥ ቃለ ጽድቅ፤

ከሐሰት ፍርድ ሁሉ ራቅ፣ መማለጃ መቀበል የብልሆችን ዓይነ ልቡናቸውን ዕውር ያደርጋቸዋልና አለ፣ አዋቆችን አለአዋቂ ያደርጋልና፣ ዕውነ ተኛ ቃላቸውንም ወደ ሐሰት ይለውጠዋልና፣ መማለጃ ተቀ ብለህ ይድን በቃውን ይሙት በቃ፣ ይሙት በቃውን ይድን በቃ ብለህ አትፍረድ፤ አንድም እንዲህ ይሆናል፣ ከሐሰት ፍርድ ሁሉ ራቅ፣ ተገኃሥ ያለውን አመጣ፣ ይድን በቃውን ይሙት በቃ፣ ይሙት በቃውን ይድን በቃ ብለህ አትፍረድ፣ መማለጃም አትቀበል ፍርድ፣ አላድላ እንጂ. እሱ ወዶ ከሰጠኝ ምነዋ? መማለጃ ብቀ በል ትለኝ እንደሆነ፣ መማለጃ መቀበልስ የብልሆችን ዐይነ ልቡናቸውን ዕውር ያደር ገዋል እኮን፣ እውነተኛውንም ቃላቸውን ወደ ሐሰት ይለው ጠዋል እኮን፣ አንተ መማለጃ መቀበልህ ላታደላን ነው? እሱስ ለአንተ መማለጃ መስጠቱ ላታደላለትን ነው?

፱፣ ወግዩራነ ኢትግፍዑ እስመ አንትሙ ግዩራነ ኮንክሙ በምድረ ግብጽ፣

እናንተ በምድረ ግብጽ መጻተ ኞች /ስደተኞች/ ነበራችሁና መጻተኞችንም አትበድሏቸው፤

፲፣ ፮ተ ክረምተ ዝራእ ገራህተከ ወአስተጋብእ እክለከ፣

ስድስት ዓመት በእርሻህ ዘርህን ዝራ፣ በስድስቱ ዓመት የዘራ ኸውንም ሰብስብ፤

፲፩፣ ወበሳብዕት ክረምት ኅድጋ ታዕርፍ ወይብልዖ ነዳይ ሕዝብከ ወዘተርፈ ይብልዖ አርዌ ዘገዳም ከመዝ ትገብር ዓፀደ ወይንከኒ ወዘይተከኒ፣

በሰባተኛዪቱ ዓመት ግን እርሻ ዪቱን ከመታረስ ከመቆፈር ታርፍ ዘንድ ተዋት፣ አትረሳት አትቆፍራት፣ የበቀለውንም ገቦ ችግረኛ ወገንህ፤ አንድም ነዳየ ሕዝብከ ይላል፣ ወገንህ የሆነ ችግረኛው፤ አንድም ነዳይ እምሕዝብከ ከወገንህ ችግረኛው ይብላው፣ ከዚያ የቀረውን የምድረ በዳ አውሬ ይብላው፣ እንደዚህም የምታደርግልኝ የእኽሉን ብቻ አይደለም የወይ ኑንና የዘይቱንም ቦታ ነው፤



፲፪፣ ሰዱሰ ዕለተ ትገብር ኵሎ ግብረከ ወአመ ሳብዕት ዕለት ተዐርፍ ከመ ያዕርፍ ላሕምከ ወአድግከ ወከመ ያስተንፍስ ወልደ አመትከ ወግዩር፣

ስድስቱን ቀን ሥራህን ሁሉ ሥራ፣ በሰባተኛው ቀን ቅዳሜ ግን መሬቱ ከእርሻ ከቁፋሮ ትረፍ፤ አንድም አንተ ከእርሻ ከቁፋሮ እረፍ፣ በብሉይ ቤት ካልአይ በትእዛዝ፣ ትእዛዝ በካልአይ ይተረጐማል፣ ይኸንም ማለቱ አንተ ብቻ ታርፍ ዘንድ አይደለም፣ /ላምሕም/ በሬህም፤ አህያህም፣ የሴት ባሪያህ ልጅም፣ በአንተ ዘንድ ተጠ ግቶ የሚኖር መጻተኛውም /እኸ ብሎ/ አርፎ እንዲውል ባት /ሊውልባት/ ነው እንጂ፣

፲፫፣ ወኵሎ ዘነበብኩ ዕቀብ ወስ ሞሙ ለአማልክተ ባዕድ ኢትዝክሩ ወኢትትናገሩ በአፉክሙ፣

ጠብቅ ብዬ የነገርኩኽን ሁሉ ጠብቅ፤ አንድም ኵሎ ዕቀብ ዘነበብኩከ ይላል፣ አንተ ጠብቅ ያልኩኽን ሁሉ ጠብቅ፣ ወዘነበብኩ እኔም የነገርኩኽ ይኸነን ነው፣ ለአማልክት ባዕዳን ይላል፣ ልዩ ልዩ የሆኑ የጣዖታ ቱን ስም፤ አንድም ለአማልክተ ባዕድ ይላል፣ የሞአብ የአሞንን ጣዖታት ስም፤ አንድም ወስሞሙ ለአማልክት ይላል፣ የጣዖታቱን ስም፤ አንድም ለአማልክተ ባዕዳን ይላል አናብቦ፣ የባዕዳን የአ ሕዛብን የአማልክት ስም፣ ቤል ዳጎን ብላችሁ አትጥሩ፣ ለጣዖታቱም በአንደበታችሁ ምስጋና አታቅርቡ፤ አንድም ኢትዝክሩ ጥንቱንም ስማቸውን እንጥራቸው ጣዖታቱንም እና ምልካቸው ብላችሁ በልቡና ችሁ አታስቡ፣ ኋላም ደፍ ራችሁ በአፋችሁ ቤል ዳጎን ብላችሁ አትጥሯቸው አለ፤

፲፬፣ ሠለስተ ጊዜያተ በዓመት ግበሩ ሊተ በዓለ፣

በአንዱ ዓመት ውስጥ ሦስት ጊዜ በዓል አድርጉልኝ አለ፣ ሠለስተ ጊዜያተ ያለውን ወደፊት እየቈጠረ እየተረተረ ያመጣዋል፤

፲፭፣ ወዕቀቡ በዓለ ዘናዕት ሰቡዐ ዕለተ ትበልዑ ናዕተ በከመ አዘዝ ኩክሙ በወርኃ ሐዲስ እስመ ቦቱ ወጻእክሙ እምድረ ግብዕ፣

ቂጣ የምትበሉበት በዓለ ፋሲካን ጠብቁት አለ፣ አክብሩት፣ ከግብጽ አገር የወጣችሁበት ወር ነውና፣ የሚያዝያ ወር ቂጣውን በልታችሁ አክብሩ ብዬ እንዳዘዝኳችሁ፣ ዛሬም ሰባት ቀን ቂጣውን በልታ ችሁ /እየበላችሁ/ አክብሩት፤ አንድም ሰባት ቀን ቂጣውን

www.ethiopianorthodox.org

እየበላችሁ ሰባት ቀን አክብ ሩት፣ በዓለ ዘናዕት ያለው በዓለ ፋሲካን ነው፣ ከሦስቱ አንዱን አመጣ፡

ወኢትትረአይ በቅድሜየ ዕራቀከ፣

በቤተ እግዚአብሔር ባዶ እጅ ህን አትትታይ ራቁትህን አትጣል፡ አንድም ወደ ቤተ እግዚአብሔር ባዶ እጅህን አትሒድ፣ በቅድሜየ አለ፣ ምንም ለእግዚአብሔር ሁሉ ቅድሙ ቢሆን በዘመነ ብሉይ ደብተራ ኦሪት ቤተ መቅደስ፣ ቤተ እግዚአብሔር ትባላለች /ትባል ነበር/፣ በረድኤት ያድርባት ነበርና፣ በዘመነ ሐዲስ ቤተ ክርስቲያን ማኀደረ ክርስቶስ ትባላለች፣ በሥጋው በደሙ ይገለጽባታልና፣ ስለዚህ ከሁሉ አብልጦ ቅድሜየ አላት፡

፲፮፣ ወበዓለ ዘአመ አፂድ ዘቀዳሚ እክልከ ግበር በምግባሪከ በውስተ ዘዘራዕከ ገራህተከ ወበዓለ ዘፍጻሜ /ዘአስተጋብኦ/ አመ ይወፅእ ዓመት በጊዜ አስተጋባእከ ኵሎ ተግባረከ እምውስተ ገራህትከ፣

መጀመሪያ የደረሰው እህልህ በሚታጨድበት ጊዜ በእርሻህ ከተዘራው አዝመራ እሸት ነዶ ውን እያቀረብክ በዓለ ሰዊ ትን አክብር አለ፣ ሁለተኛውን አመጣ፣ ዘአመ ወጸእከ በዓመት፣ ከግብጽ በወጣህ ጊዜ ሰባት ደመና ጋርዶ እንደ አወጣህ

አንተም ዛሬ በእርሻህ የዘራኸ ውን አዝመራ በምትሰበስብበት ጊዜ የመኸር ክታች በዓል፣ ዳስ ጥለህ በዓለ መጸለትን አክብር፣ ሦስተኛውን አመጣ፡

፲፯፣ ሠለስተ ጊዜያተ በዓመት ይትረዓይ ኵሉ ተባዕትከ በቅድሜየ አነ እግዚእ እግዚአብሔር፣

ይቤ ያለበት ነው፣ በዓመት ሦስት ጊዜ ወንድ ወንዱ ልጅህ ለገቢረ በዓል እየወጣ ይታይ፣ ይኸንንም ያዘዝኩህ ፈጥሬ የምገዛህ እኔ እግዚአብ ሔር ነኝ፣ ሳይፈጥር የሚገዛ አለና ይቤ ያለውን ያመጣል፣

፲፰፣ ወኢትሡዕ መሥዋዕትየ በብኑዕ ደም ወኢይቢት ስብሕ ዘበዓልየ እስከ ሳኒታ፣

መሥዋዕቴንም ባደረ ደም አትሠዋው፣ ለበዓሌ ተብሎ የቀረበውንም ስብ እስከ ነገ ይደር ብላችሁ አታሳድሩ፣

፲፱፣ ቀዳሚ ፍሬ ገራውኒከ ታበውዕ ሊተ እምዚአከ ወኢታብስል ማዕዋ በሐሊበ እሙ፣

መገርመሪያ ከእርሻህ የተገኘ ውን፣ መገርመሪያ ከእርሻህ አዝመራ የተሰፈረውን የእህሉን ቀዳምያት አቅርብልኝ፣ ይህን ንም አቅርብልኝ ያልኩህ ከገንዘ ብህ ነው እንጂ ከሌላ ሰርቀህ ቀምተህ አይደለም፣ ወይፈ ኑንም በእናቱ ወተት አትቀቅ



ለው፡ አንድም የእናቱን ጡት የሚጠባውን ጥጃውን አርደህ አትቀቅለው ይህም ርኅራኄ ነው፡ አንድም የእናቱን ጡት ሲጠባ ያደገውን ወይፈ ኑንና እናቲቱን አንድ ቀን አትረዳቸው፣ ይኸውም ርኅ ራኄ ነው፡

፳፣ ወናሁ እፌኑ መልአኪየ ቅድመ ገጽከ ከመ ይዕቀብከ በፍኖትከ ወከመ ያብእከ ውስተ ምድር ዘአስተዳሉኩ ለከ፣

እነሆ ቅዱስ ሚካኤልን፡ አንድም ሙሴን፡ አንድም መላክተኛዬ ኢያሱን ፊት ፊት የሚመራህ እሰድልሃለሁ፣ በሠራሁልህ ሕግ አጽንቶ ይጠብቅህ ዘንድ፡ አንድም በምትሔድበት ጎዳና ይጠብቅህ ዘንድ፣ በአትክልት በአገርዕት ወደ አዘጋጀኋት ወደ ከነዓንም መርቶ ያገባህ ዘንድ እፌኑ አለ፡

፳፩፣ ዕቀብ ርእሰከ ስምዖ ወኢትዕበዮ እስመ ኢየኃድገከ ወይሰመይ ስምየ በላዕሌከ፣

ከመ ይዕቀብከ በፍኖትከ ብሎት ነበርና ራስህን፡ አንድም ራስህ ሕግን ጠብቅ፡ አንድም ዕቀብ ለርእስከ ለራስህ ብለህ አለ፣ ይረባኛል ይጠቅመኛል ብለህ ለራስህ ሕጉን ጠብቅ፣ ስምዖ፣ ሕጉን ተማረው፣ ወኢትዕበዮ፣ እምቢ

አልማርም አትበል፣ በላዕሌከ ሲል ነው፣ ይኸን ያደረግ ህልኝ እንደ ሆነ ስሜ በአንተ ይጠራልኝ ዘንድ በረድኤት አልለይህምና፡ አንድም እኔ በረድኤት አልለይህምና ወይ ሰመይ ስምየ በላዕሌከ፣ ስሜም በአንተ ይጠራልኛልና አለ፣ አምላከ እስራኤል ተብዬ /ተብሎ/ በአንተ ይጠራልኛ ልና፣ ስምዖ ወኢትዕበዮ ሕጉን ተማረው እምቢ አትበለው፡ አንድም ዕቀብ ርእስከ ሊሠራህ ሊቀጣህ አለቃህ አድርጌ የሾምኹት ሙሴን ኢያሱን ጠብቀው አለ፣ አክብረው፣ የአዘዘህንም ስማው የአዘዘህን እምቢ አትበለው፣ የእኔ ስም በእሱ ይጠራበት ዘንድ እሱ ከአንተ አይለይህምና፡ አንድም እሱ ከአንተ አይለይህምና ወይሰመይ ስምየ በላዕሌሁ፣ የእኔም ስም በእሱ ይጠራልና አለ፣ ነቢየ እግዚአብሔር ተብሎ ይጠራልና ስምዖ ወኢትዕበዮ ብለህ እሥር፡

፳፪፣ ወለእመሰ ሰማዕከ ቃልየ ወዐቀብከ ኵሎ ዘእቤለከ እጸልዕ ጸላዒከ ወእፃረሮ ለዘይፃረረከ፣

ቃሌን ብትሰማ ያልኩህንም ነገር ሁሉ ብትጠብቀው፣ የሚ ጠላህን ጠላትህን እጠላዋለሁ፣ ጠላት የሚሆንህንም ሰው ጠላት እሆነዋለሁ፡

www.ethiopianorthodox.org

፳፫፤ ወየሐውር መልአኪየ እንዘ ይመርሐከ ወያበውአከ ውስተ ምድረ አሞሬዎን ወኬጤዎን ወፌርዜዎን ወከናኔዎን ወጌርጌሴዎን ወኤዌዎን ወኢያቡሴዎን ወአጠፍኦሙ፤

የእኔ መላክተኛ ቅዱስ ሚካኤል፤ አንድም ሙሴ ኢያሱ አንተን እየመራ ወደ ከነዓን ይሔዳል፤ መርቶም ወስዶ ወደ አሞሬዎንና ወደ ኬጤዎን፤ ወደ ፌርዜዎንና ወደ ከናኔዎን፤ ወደ ጌርጌሴዎንና ወደ ኤዌዎን ወደ ኢያቡሴዎን አገር ወደ ከነዓን ያገባሃል፤ እኔም በእሱ አድሬ ጠላቶችህን ሁሉ አጠፋቸዋለሁ፤ አንድም ወያጠፍዖሙ ይላል፤ አንተን ይዞ ገብቶ ጠላቶችህን ሁሉ ያጠፋቸዋል፤

፳፬፤ ወኢትስግድ ለአማልክቲሆሙ ወኢታምልኮሙ ወኢትግበር ከመ ምግባሪሆሙ ነሢተ ንሥቶሙ ወቀጥቅጦ ቀጥቅጥ ምሥዋዓቲሆሙ፤

ከዚያም ገብተህ የከነዓንን አማልክት አምልከህ አትስገድላቸው፤ ይህ ከመ በባለቤት የገባ ነው፤ ሥራቸውንም አትሥራ አለ፤ ለጣዖታቱ መሥዋዕት ጸሎት አታቅርብ፤ አንድም ሰብአ ከነዓን እንደሚያደርጉላቸው አታድርግላቸው፤ አላ ያለበት ነው፤ ቤተ ጣዖቱን ፈጽመህ አፍርስባቸው እንጂ፤ መሠዊያቸውንም ቀጥቅጠህ አጥፋባቸው እንጂ፤

፳፭፤ ወአምልክ እግዚአብሔርሃ ፈጣሪከ ወእባርክ ኅብስተከ ወወይነከ ወማየከ ወአሴስል ዕበሰ እምላዕሌከ፤

ከዚያም ገብተህ እኔን ፈጣሪህ እግዚአብሔርን ብቻ አምልክ፤ ይኸን ያደረግህ እንደሆነ የምትበላውን እንጀራህን፤ ወይንህን የምትጠጣውን ውሃህን አበዛልሃለሁ፤ ከድካምህ አጸናሃለሁ፤ ደዌህንም ከአንተ አርቅልሃለሁ፤

፳፮፤ ወአልቦ መካን ዘኢይወልድ በውስተ ምድርከ ኅልቈ መዋዕሊከ እፌጽም ለከ፤

በአገርህ የማይወልድ መካን የለም፤ የዘመንህንም ቍጥር በተድላ በደስታ እንድትፈጽም አደርግሃለሁ፤

፳፯፤ ወፍርሃተ እፌኑ ቦቱ ለዘይደጸንዓከ ወይደነግፁ ኵሎሙ አሕዛብ ዘቦእከ ኀቤሆሙ ወእሬሲ ኵሎ ፀረከ ከመ ይጕየዩከ፤

የአንተን መፍራት በሚበረታበህ በጠላትህ አመጣበታለሁ አለ፤ አንተ ትፈራው የነበረ ጠላትህ አንተን እንዲፈራ አደርገዋለሁ፤ አገራቸውንም ልትወርስ ወደ እነሱ የገባህባቸው አሕዛብ ሁሉ ከአንተ የተነሣ ይደነግጣሉ፤ ጠላቶችህ ሁሉ አንተን ፈርተው ይሸሹ ዘንድ እንዲሸሹህ አደርጋለሁ፤



፳፰፤ ወእፌኑ ዘያደነግፆሙ ቅድሜከ ለአሞሬዎን ወያወፅአሙ ለኬጤዎን ወለኤዌዎን ወለከናኔዎን፤

ወእሬሲ ኵሎ ፀረከ ከመ ይጕየዩከ ብሎ ነበርና ከአንተም አስቀድሜ በፊትህ የአሞሬዎንን ሰዎች የሚያስደነግጣቸውትንኙን አመጣባቸዋለሁ፤ ትንኙም ከሀገራቸው አስወጥቶ ይሰድዳቸዋል፤ አንድም ያወፅአሙ ይላል፤ የአሞሬዎንን ሰዎች ከሀገራቸው አስወጥቶ ይሰድዳቸው ዘንድ ከአንተ አስቀድሜ የሚያስደነግጣቸውትንኙን አመጣባቸዋለሁ፤ አንድም ወታወፅአሙ ይላል፤ ከአንተ አስቀድሜ ፈታውራሪ አድርጌ የሚያስደነግጣቸውትንኙን አመጣባቸዋለሁ፤ ከዚያ በኋላ አንተ ገብተህ ከሀገራቸው አስወጥተህ ትሰድዳቸዋለህ፤ አንድም ቅድሜየ ብሎ ወአወፅአሙ ይላል ከዚያ አስቀድሞ ፈታውራሪ አድርጌ የሚያስደነግጣቸው ትንኙን አመጣባቸዋለሁ፤ ከዚያ በኋላም ከሀገራቸው አስወጥቼ እሰድዳቸዋለሁ፤

፳፱፤ ወኢያወፅአሙ በአሐቲ ዓመት ከመ ኢትኩን ምድር ዐፀ ወከመ ኢይብዝኁ ላዕሌከ አራዊተ ገዳም፤

አወፅአሙ ብሎ ነበርና ሳወጣቸውም ምድር ከሰው ተለይታ በረኃ እንዳትሆን፤ የምድረ በዳ አራዊትም በአንተ እንዳይበዙብህ የከነዓንን ሰዎች ከሀገራቸው በአንዲት ዓመት ብቻ አላወጣቸውም፤

በበንስቲት አወፅአሙ እምኔከ እስከ ትትባዛኅ ወትወርሳ ለምድር፤

አንተ ፈጽመህ እስክትበዛ ድረስ በዝተህም ከነዓንን ጨርሰህ እስክትወርሳት ድረስ አላ ያለበት ነው፤ ጥቂት ጥቂት እያልኩ በብዙ ዘመን ከአንተ ለይቼ አስወጥቼ እሰድዳቸዋለሁ እንጂ፤

፴፤ ወአሰፍሕ አድዋሊከ እምባሕረ ኤርትራ እስከ ፍልስጥኤም፤ ወእም ገዳም እስከ ፈለግ ዐቢይ ፈለገ ኤፍራጥስ ወእሜጡ ውስተ እዴከ እለ ይነብሩ ውስተ ምድር ወአወፅአሙ እምኔከ፤

ድንበር ይመታል በወዲህ ከኤርትራ ባሕር እስከ ፍልስጥኤም፤ በወዲያ ከሶርያ ምድረ በዳ ጀምሮ እስከ ታላቁ ወንዝ እስከ ኤፍራጥስ ድረስ ያሉትን አውራጃህን፤ አንድም አድዋለከ ይላል፤ ጥቃቅኑን አገሮችህን ሁሉ አቀናልሃለሁ፤ በከነዓንም የሚኖሩትን ሰዎች ሁሉ በእጅህ ጭብጥ በእግርህ እርግጥ ሁነው እንዲገዙልህ አድርጌ እሰጥሃለሁ፤ ለአንተ የማይገዙትን ግን ከአንተ ለይቼ አስወጥቼ እሰድልሃለሁ፤

www.ethiopianorthodox.org

፴፩፣ ወኢ.ታኀድሮሙ ወለአማልክ ቲሆሙ ኢ.ትትአዘዝ፣

ለአንተ የማይገዙልህ የከነዓንን ሰዎች ከአንተ ጋር አታኑራቸው፣ ለካህናተ ጣዖቱም አትታዘዝ አለ፣ መሥዋዕት ሠዋ፣ ጣዖት አምልክ ቢሉህ አይሆንም በላቸው፤ አንድም ለጣዖታቱ አትታዘዝ አለ፣ ወድደህ አንተው ራስህ በፈቃድህ ለጣዖታቱ መሥዋዕት ጸሎት ላቅርብ /አቀርባለሁ/ አትበል፤

፴፪፣ ወኢ.ይንበሩ ውስተ ምድርከ ከመ ኢ.ይግበሩከ ተዓብስ ወለእመ አምለከ አማልክቲሆሙ እሙንቱ ይከውኑከ ዕቅፍተ፣

ፈጣሪህን ትበድል ዘንድ እንድ ትበድል እንዳያደርጉህ ለአንተ የማይገዙ ሰብአ ከነዓን፤ አንድም ጣዖታቱ በአገርህ አይኑሩ፣ ጣዖታቱን ካመለክሃቸው፤ አን ድም የሰብአ ከነዓንን ጣዖታት ከአመለክህላቸው የከነዓን ሰዎች ዕንቅፋት ይሆኑሃል አለ፣ እነሱ ያጠፉሃል፤ አንድም ጣዖታቱ ዕንቅፋት ይሆኑሃል አለ፣ ከፈጣሪህ ይለዩሃል ሲል ነው::

## ምዕራፍ ፳ወ፬

፩፣ ወይቤሎ እግዚ.አብሔር ለሙሴ ዕርግ አንተ ወአሮን ወናዳብ ወአብ ዩድ ወመላሕቅተ ሕዝብ ፸ እም እስራኤል ወይሰግዱ ሊ.ተ እምር ኁቅ፣

እግዚ.አብሔር ሙሴን አንተና ወንድምህ አሮን፣ ናዳብና አብ ዩድ ከእስራኤል የተመረጡ በሕዝቡ የተሾሙ፤ አንድም ዘእስራኤል ይላል የእስራኤል ወገን የሚሆኑ በሕዝቡ የተሾሙ ሰባ ሊ.ቃናትም ሁናችሁ ወደ ደብረ ሲና ውጡ፣ ከአንተም ጋር ከወጡ በኋላ ለእኔ ለፈጣሪያቸው ለእግዚ.አብሔር ከሩቅ ሁነው ይስገዱ፣

፪፣ ወቅረብ አንተ ባሕቲትከ ወእሙንቱሰ ኢ.ይቅረቡ ወሕዝብከሂ ኢ.ይዕርጉ ምስሌሆሙ፣

ከእነሱ ተለይተህ አንተ ብቻ፤ አንድም ባሕቲትከ ይላል፣ አንተ ብቻህን እኔ ወደ አለሁበት ወደ ተራራው ራስ ቅረብ፣ ሌዋውያን ግን አንተና ወንድ ምህ አሮን ወደ አላችሁበት ወደ ተራራው ራስ አይቅረቡ፣ ወገኖችህ እስራኤልም እንደ እነሱ፤ ከእነሱ ጋራ ሌዋውያን ወደ አሉበት ወደ መንፈቀ ደብር አይውጡ፤ አንድም ኀቤሆሙ ይላል፣ ሕዝቡ ሌዋ ውያን ወደ አሉበት አይቅረቡ፤



፫፣ ወቦአ ሙሴ ወአይድዓ ለሕዝብ ኵሎ ቃለ እግዚ.አብሔር ወጽድቆ ወአውሥኡ ኵሉ ሕዝብ በ፩ዱ ቃል ወይቤሉ ኵሎ ቃለ ዘነበበ እግዚ.አብሔር ንገብር ወንሰምዕ፣

ሙሴም ሕዝቡ ወደ አሉበት ወደ ከተማው ገብቶ የእግዚ. አብሔር እውነተኛ ቃሉን ለሕዝቡ ነገራቸው፣ ሕዝቡም እንደ አንድ ልብ መካሪ፣ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነው እግዚ.አብሔር የነገረንን ነገር ሁሉ ሰምተን እናደርገዋለን አሉ፣ ሐተታ እንዳለፈው፤

፬፣ ወጸሐፈ ሙሴ ኵሎ ቃለ እግዚ.አብሔር ወተንሥአ በጽባሕ ወሐነፀ ምሥዋዐ ታሕተ ደብር በ፲ቱ ወ፪ቱ አዕባን በኍልቈ ፲ቱ ወ፪ቱ ሕዝበ እስራኤል፣

ሙሴም የእግዚ.አብሔርን ቃል ሁሉ ጻፈ፣ ጧት ተነሥቶ፤ አንድም ፈጥኖ ተነሥቶ በዐሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ወገኖች ልክ አሥራ ሁለት ደንጊያዎች አንሥቶ አምጥቶ በተራራው ሥር ምሥዋዕ ሠራ ጸፈጸፈ፣

፭፣ ወፈነወ ወራዙቶሙ ለውሉደ እስራኤል ወአዕረጉ መሥዋዕተ መድ ኃኒት ለእግዚ.አብሔር አልህምተ፣

ሙሴም ለማገረድ ለማወራረድ እንዲፋጠኑ ብሎ የእስራኤልን ልጆች ጐልማሶች ወደ ምሥዋዑ ልኮ ሰደዳቸው፣ ሒደውም ላሞቹን እስራኤል ከመከራ የሚድኑበት መሥዋዕት አድር ገው ለእግዚ.አብሔር አቀረቡ፤ አንድም እስራኤል ከመከራ የሚድኑበት መሥዋዕት አድር ገው ላሞቹን ለእግዚ.አብሔር አቀረቡ፣

፮፣ ወነሥአ ሙሴ መንፈቀ ደሙ ወአንበረ ውስተ መቅለድ ወመንፈቀ ደሙ ከዐወ ላዕለ መሥዋዕት፣

ሙሴም የደሙን እኩሌታ ወስዶ በብርቱ አኖረው፣ የደሙንም እኩሌታ ወስዶ በመሥዋዕቱ ዙሪያ አፈሰሰው፤ አንድም የደሙን እኩሌታ ወስዶ በብርት አኖረው የመንፈቅ መንፈቅ ነው፣ የዕኩሌታውን ዕኩሌታ ደም ወስዶ በምሥዋዑ ላይ አፈሰሰው፤

፯፣ ወነሥአ ሙሴ መጽሐፈ ሕግ ወአንበበ በዕዝነ ሕዝብ ወይቤሉ ኵሎ ዘነበበ እግዚ.አብሔር ንገብር ወንሰምዕ፣

ሙሴም ሕጉ የሚነገርበትን መጽሐፍ ወስዶ አነበበላቸው መጽሐፍ አለው፣ ከሆነ በኋላ፤ አንድም መጽሐፍ ይላል፣ ሕጉ የተጻፈበትን ሠሌዳውን፣ አንድም ሕግ ሥርዓት ሁኖ የተጻፈላቸ ውን ቃል ወስዶ ሕዝቡ እየሰ ሙት አነበበላቸው፣ ሕዝቡም እግዚ.አብሔር የተናገረውን ነገር ሁሉ ሰምተን እናደርገዋ ለን አሉ፣ ሐተታ እንዳለፈው፤

www.ethiopianorthodox.org

፰፣ ወነሥአ ሙሴ ደመ ወነዝኃ ላዕለ ሕዝብ ወይቤ ናሁ ደመ ሕግ ዘሐገገ ለክሙ እግዚአብሔር በእንተ ኵሉ ዝ ቃል፣

ነሥአ ሙሴ መንፈቀ ደሙ ወአንበረ ውስተ መቅለድ ብሎ ነበርና፣ ሙሴም በብርት ያኖረ ውን ደሙን ወስዶ ሕዝቡን ረጫቸው፣ እናንተ፣ ኵሎ ቃለ ዘነበበ እግዚእ ዘንገብር ወንሰ ምዕ /ብላችሁ/ ስላላችሁት ቃል እግዚአብሔር ሕግ ሥርዓት አድርጎ የሠራላችሁ ደሙ ይህ ነው፤ አንድም ሕጉ ሥርዓቱ የሚጸናበት /ጸንቶበት/ የሚኖር ደሙ ይህ ነው፤ አንድም ሕጉ የተነበበበት ደሙ ይህ ነው፤

፱፣ ወዐርጉ ሙሴ ወአሮን ናዳብ ወአብዩድ ወ፸ ሊቃናተ እስራኤል፣

ሙሴና አሮን አብዩድና ናዳብ በእስራኤልም የተሾሙ ሰባ ሊቃናት ዕርጉ እንዳላቸው ወደ ደብረ ሲና ወጡ፤

፲፣ ወርእዩ መካነ ኀበ ይቀውም እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ወታሕተ እግሩ ከመ ግብረተ ግንፋል ዘሰንፔር ወከመ ርእየተ ጽንዐ ሰማይ ሶበ ሐወፀት፣

ወጥተውም የእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔር በቆመበት በእግሩ በታች ባለው ቦታ ሰንፔር እንደሚባል ዕንቍ ጡብ ሥራ ያለ ጽንዕት ሰማይ ሲል ነው፣ የጸናችም ሰማይ ባበራች ጊዜ እንደሚታይ ያለ ብርሃን አዩ አለ፣ ጡብ ከመጣል አወጣችኋለሁ ሲል፣ እንዲህ ሁኖ ታይቷቸዋል፣ ወከመ ርእየተ ሰማይም አለ፣ ሰማይ የመሰለ ባሕር ከፍሎ ከግብጽ አወጣኋችሁ ሲል፤ አንድም ቀድሞ ሰማይ የመሰለ ባሕር ከፍሎ ከግብጽ እንዳወጣኋችሁ ዛሬም በደብረ ሲና ሰማያዊ ሕግ ሠራሁላችሁ ሲል እንዲህ ሁኖ ታይቷቸዋል፤

፲፩፣ ወኅሩያኒሆሙ ለእስራኤል /ወኃያላኒሆሙ/ ዘኢልቦ ዘይመስሎሙ አስተርአዩ በመካነ ዘእግዚአብሔር ወበልዑ ወሰትዩ፣

እስራኤል የተመረጡ ጉልማሶች እግዚአብሔር በተገለጸበት በደብረ ሲና እግር ላሙን አርደው አወራርደው መሥዋዕቱን ሠውተው ተገለጹ፣ ተረፈ መሥዋዕቱንም ተመገቡ፤ አንድም የሚመስላቸው የሌለ ከእስራኤል የተመረጡ ሌዋውያንም ደሙን ለማፍሰስ፣ ስቡን ለማጤስ እግዚአብሔር በተገለጸበት በደብረ ሲና እግር ተገለጡ፣ ተረፈ መሥዋዕቱንም ተመገቡ፤ አንድም የሚመስላቸው የሌለ ከእስራኤል ዘነፍስ የተመረጡ ቀሳውስት ዲያቆናት ስሙን ለመቀደስ ክብሩን



ለመውረስ በእግዚአብሔር ማደሪያ በቤተ ክርስቲያን ተገለጡ፣ ሥጋውን ደሙን እነሱ ተቀብለው ለምእመናን አቀበሉ፤ አንድም የሚመስላቸው የሌለ ከእስራኤል ዘነፍስ የተመረጡ ጻድቃን በዕለተ ምጽአት ከመቃብር ተነሥተው ፍጹም ብርሃን ለብሰው አበጋዛቸው ኢየሱስ ክርስቶስን መስለው በእግዚአብሔር ማደሪያ በመንግሥተ ሰማያት ተገለጹ፣ ጸጋ ክብሩንም ወረሱ፣ በልዑ ወሰትዩ አለ፣ የበሉት የጠጡት ደስ እንዲያሰኝ እነሱም ጸጋ ክብሩን ሲወርሱ ደስ ይላቸዋልና፣ ወኅሩያኒሆሙ ለእስራኤል ባለው ወኃያላኒሆሙ ለእስራኤል ይላል፣ አብነት እንደዚሁ ያስተረጉማል፤

፲፪፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ዕርግ ኀቤየ ውስተ ደብር ወሀሉ ዝየ /ህየ/ ወእሁበከ ሰሌዳተ ዘዕብን ዘሕግ ወዘትእዛዝ ዘጸሐፍኩ /ተሐግግ/ ወትሔግግ ሎሙ፣

እግዚአብሔርም ሙሴን የምነግርህ ነገር አለኝና ኢያሱን አስከትለህ እኔ ወዳለሁበት ወደ ደብረ ሲና ውጣ፣ በደብረ ሲናም አርባ ቀን ሰንብት፣ አንተ ለእስራኤል ሥርዓት አድርገህ ትሠራላቸው ዘንድ እኔ የጻፍኩት ዘጠኙ ቃላትና ኢታምልክ ያሉበት ሁለቱን የዕንቍ ጽላት እሰጥሃለሁ፤ አንድም በግብር አምላካዊ የጻፍኳቸው ዘጠኙ ቃላትና ኢታምልክ ያሉባቸው ሁለቱን የዕንቍ ጽላት እኔ እሰጥሃለሁ፣ ወትሔግግ ሎሙ አንተ ከእኔ ወስደህ ሥርዓት አድርገህ ትሠራላቸዋለህ አለው፤

፲፫፣ ወይቤሎሙ ሙሴ ለሊቃናተ ሕዝብ ኢትትዋከቱ /ኢትትዋከሑ/ እስከ ንሰወጥ ኀቤክሙ ወናሁ አሮን ወሆር ምስሌክሙ ወለእመኒ ዘቦ ነገር ይሖር ኀቢሆሙ፣

ሙሴም በሕዝቡ የተሾሙ አለቆችን ጠርቶ እኔና ኢያሱ ደብረ ሲና ደርሰን እስክን መለስ ድረስ አትጣሉ፣ አትከራከሩ፣ አትናወጡ፣ ግርግር አትበሉ፣ ነገር ያለውም ሰው ቢኖር አንዱም አንዱ ወደ እነሱ ይሒድ፣ እነሆ አሮንና ሆር ከእናንተ ጋር አሉ፣ እነሱ ይፍረዱላችሁ አላቸው፤

፲፬፣ ወተንሥኡ ሙሴ ወኢያሱ ወዐርጉ ውስተ ደብረ እግዚአብሔር ወሠወረ ደብሮ ደመና፣

ይኸን ነግሯቸው ሙሴና ኢያሱ ተነሥተው እግዚአብሔር ወዳለበት ወደ ደብረ ሲና ወጡ፣ ያንጊዜ ተራራውን ደመና መጥቶ ሸፈነው፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፮፣ ወወረደ ሳርሁ /ስራኄሁ/ ለእግዚአብሔር ውስተ ደብረ ሲና ወሠወሮ ሰዱስ ዕለተ ወበሳብዕት ዕለት ፀውዖ እግዚአብሔር ለሙሴ እማዕከለ ደመና፣

እነሱ ከወጡ በኋላ የእግዚአብሔር ብርሃኑ ወደ ደብረ ሲና ወረደ፣ ወርዶም ተራራውን ስድስት ቀን ሸፈነው፣ በሰባተኛውም ቀን እግዚአብሔር ከደመናው መካከል ሁኖ ሙሴን ጠራው፤

፲፯፣ ወአስተርአየ ሳርሁ ለእግዚአብሔር ከመ ነደ እሳት ሶበ ያንበለብል ዲበ ከተማሁ ለደብር በቅድሜሆሙ ለውሉደ እስራኤል፣

እሳት በነደደ ጊዜ ነበልባሉ ከሩቅ እንዲታይ በእስራኤል ልጆች ፊት በተራራው ራስ ላይ የእግዚአብሔር ብርሃኑ እንደ ሰንደቅ አላማ ሁኖ በሩቅ ይታይ ነበር፤ አንድም ለቅድሜሆሙ ይላል፣ እሳት በነደደ ጊዜ ነበልባሉ ለሰው ሁሉ ከሩቅ እንዲታይ የእግዚአብሔርም ብርሃኑ በደብረ ሲና እንደ ሰንደቅ አላማ ሁኖ ለእስራኤል ከሩቅ ይታያቸው ነበር፤

፲፰፣ ወቦአ ሙሴ ማዕከለ ደመና ወዐርገ ውስተ ደብር ወነበረ ፵ዓ መዓልተ ወ፵ዓ ሌሊተ፣

የተሳለፊ ነው፣ ወዐርገ ሙሴ ውስተ ደብረ ሲና ወቦአ ማዕከለ ደመና ሲል ነው፣ ሙሴም ወደ ደብረ ሲና ወጥቶ ሰባት የብርሃን መጋረጃ አለ፣ ወደዚያ ገባ፤ አንድም እንዳለም ይሆናል፣ ወሰወረ ደብሮ ደመና ብሎ ነበርና ደመና በጋረደው በተራራው መካከል ገብቶ እግዚአብሔር ወዳለበት ወደ ተራራው ራስ ወጣ፣ ወጥቶም አርባ ቀን፣ አርባ ሌሊት በደብረ ሲና ተቀመጠ፣ /ሐተታ/ ተነሥተውም ሒደው ኢያሱ ከእግረ ደብር ቀርቷል፣ ሙሴ ከተራራው ላይ ወጥቷል፣ ስድስቱን ቀን በስድስቱ ዕለታት የተፈጠሩ ሃያ ሁለቱን ስነ ፍጥረት በልቡናው ሲሥልበት ሲቀርዕበት ሰንብቷል፣ ሠላሳ አራቱን ቀን ግን አምስቱ ሙቶ ሰባ ወነበቦን ቃል ለቃል ሲነግረው ሰንብቷል፣ አርባ ቀን ያለው ይህ ነው፣ ኢያሱሳ ምን ሲመገብ ሰንብቷል ቢሉ ሙሴን ያጸና አምላክ አጽንቶታል፤ አንድም መና ከደመና እየወረደለት ውሃ ከደንጊያ እየፈለቀለት ሲመገብ ሰንብቷል።



# ምዕራፍ ፳ወ፭

## ገባኤ

፩፣ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ በሎሙ ለደቂቀ እስራኤል ንሥኡ ሊተ እምጥሪትክሙ መባዓ ዘሐለይክሙ በልብክሙ፣

ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር ሙሴን ጠርቶ የእስራኤልን ልጆች ከገንዘባችሁ በልቡናችሁ ያሰባችሁልኝ መባውን አቅርቡልኝ ብሏል ብለህ ንገራቸው ብሎ ተናገረው፤

፪፣ ወዝንቱ ውእቱ መባዕ ዘትነሥኡ እምኔሁ ወርቀ ወብሩረ ወብርተ፣

ንሥኡ ሊተ እምጥሪትክሙ ብሎ ነበርና ከገንዘባችሁ ለይታችሁ የምታመጡልኝ መባዑም ይህ ነው፣ ዘትነሥኡ ያለውን ወርቀ ወብሩረ ወብርተ ብሎ አመጣው፣ የምታመጡልኝም ወርቁን ብሩን ብርቱን ነው፤ አንድም ዝንቱ መባዕ ወርቅ ወብሩር ወብርት ይላል፣ ይኸውም ከገንዘባችሁ የምታቀርቡልኝ መባው ወርቅ ብር ብርት ነው አለ በላቸው አለው፤ አንድም እምኔሆሙ ይላል፣ ሙሴ አሮን ከእስራኤል የምትቀበሏቸው መባው ወርቁን ብሩን ብርቱን ነው፤ አንድም ዝንቱ መባዕ ዘትነሥኡ እምኔሆሙ ይላል፣ ይኸውም ከእነሱ የምትቀበሉት መባው ወርቅ ብር ብርት ነው አላቸው፤

፫፣ ወያክንተ ወኅብረ ክብድ ወለየ ክዑበ ወቢሶስ ክዑበ ወፀጕረ ጠሊ፣

ያክንቱ ሰማያዊ ሐርን፣ ኅብረ ክብድ ብጫ ሐርን፣ ወለየ ክዑበ እጥፍ ሁኖ የተሠራ ቀይ ሐርን፣ ለየ ባለው ነተ ይላል፣ በዓረቢ፣ ወቢሶስ ክዑበ እጥፍ ሁኖ የተሠራ አረንጓዴ ሐርን፣ ወፀጉረ ጠሊ ቀለም የገባ የፍየል ጠጉርን አምጡ በላቸው አለው፤

፬፣ ወማዕሰ በግዕ ኅሡየ ወማዕሰኒ ዘሥርየቱ ኅብረ ያክንት ወዕፀ ዘኢይነቅዝ፣

ማዕሰ በግዕ ኅሡየ፣ የለፋ ዘስርየቱ ኅብረ ያክንት ለማለት ደገመው፤ አንድም ማዕሰ በግዕ ኅሡየ አለ፣ አልፍተው ቀለም ሳያገቡ የሚያመጡት አለና፣ ወማዕሰኒ ዘሥርየቱ ኅብረ ያክንት አለ፣ አልፍተው ቀለም አግብተው የሚያመጡት አለና ሸምሸርስጢን የሚባል የማይነቅዝ ዕንጨትንም አምጡ አላቸው፤ አንድም የማይነቅዝ ሸምሸርስጢን የሚባል እንጨትንም አምጡ በላቸው፤

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

፮፤ ወቅብአ ለማኅቶት ወአፈዋተ ለተቀብዖ ወዕጣናተ ለማዕጠንት፤

ለመብራት የሚሆን ዘይቱን፤ ሊቀቧቸውም ሺቶዎችን፤ ሊያጥኗቸውም ዕጣኖችን አምጡ፤

፯፤ ወእዕባነ መረግድ ወእዕባነ ዘይትኄረው ለኤፉድ ወለለምግዮ፤

ለምግዮ ልብሰ መትከፍ፤ ኤፉድ ልብሰ እንግድዓ ነው፤ ለኤፉድና ለለምግዮ ፈርጥ ጌጥ የሚሆኑ መረግድ የሚባሉ እዕናቍን አምጣ አለው፤ ወእዕባነ ዘይትኄረው ዘይትኄረዉ ለማለት ደግሞታል፤ አንድም የማይቀረፁ ወርቁን ሐሩን አጒድጒደው የሚይዟቸው እዕናቍ አሉና አዕባነ መረግድ አለ፤ የሚቀረፁ በሐር ተጠልፈው የሚያዙ እዕናቍ አሉና ወእዕባነ ዘይትኄረዉ አለ፤

፰፤ ወትገብር ሊተ መቅደሰ ወአኃድር በማዕከሌሁ፤

ግበር ሊተ ሲል ነው፤ የምመሰገንበት ደብተራ ኦሪትንም ሥራልኝ፤ ይኸን ያደረግህልኝ እንደሆነ በረድኤት አድሬበት እኖራለሁ፤ አንድም አንተ የምመሰገንበት ደብተራ ኦሪትን ሥራልኝ፤ ወአኃድር በማዕከሌሆሙ፤ እኔም በወገኖቼ በእስራኤል መካከል በረድኤት አድሬባቸው እኖራለሁ፤

፱፤ ወትገብር ሊተ ኵሎ ዘአነ አርእየከ በውስተ ደብር አርአያ ደብተራ ወአርአያ ንዋያ ለደብተራ ወኵሎ ከማሁ ትገብር፤

ትገብርና ትገብር አንድ ወገን ነው፤ በደብረ ሲና እኔ የማሳይህ የደብተራ ብርሃንን ሥራ አምሳል፤ የደብተራ ብርሃን የዕቃዋንም ሥራ አምሳል፤ ይህን ሁሉ እኔ እንደ ነገርኩኽ ሥራ አለው፤ አንድም እየራሱ ለማውጣት ከመ አነ አርእየከ እኔ የደብተራ ብርሃንን ሥራ ዋን፤ የደብተራ ብርሃንን የእቃ ዋንም ሥራ በደብረ ሲና እኔ እንደማሳይህ /እንደ አሳየሁህ/ የደብተራ ኦሪትን ሥራ የእቃ ዋንም ሥራ ሁሉ ከማሁ እንደ ደብተራ ብርሃን አድርገህ ሥራ፤ አንድም ዘከመ አነ አርአይኩከ እኔ ከዚህ ቀድሞ ደብተራ ብርሃንን፤ የደብተራ ብርሃንን እቃዋንም እንደ አሳየሁህ ደብተራ ኦሪትን፤ የደብተራ ኦሪት እቃዋንም እንደዚያ ሥራ አለው፤ ጌታ በደብረ ሲና ሳለ ሙሴን በተመስጦም ቢሉ በደመናም ቢሉ አውጥቶ የደብተራ ብርሃንን ሥራዋን የእቃዋንም ሥራ ሁሉ አሳይቶታል፤ ስለ ምን ቢሉ በደብተራ ብርሃን አምሳል ደብተራ ኦሪት፤ በደብተራ ኦሪት አምሳል ቤተ መቅደስ፤ በቤተ መቅደስ አምሳል ቤተ ክርስቲያን የምትሠራ ናትና ስለዚህ ነው፤



፲፤ ወግበር ታቦተ ዘመርጡል እምዕፀ ዘኢይነቅዝ ዘካዕበ እመት ወመንፈቀ እመት ኑኃ /ኑኁ/ እመት ወመንፈቀ እመት ራኅባ /ራኅቡ/ እመት ወመንፈቀ እመት ቆማ /ቆሙ/፤

ክንድ ከስንዝር ቁመቷ፤ ክንድ ከስንዝር ወርዷ፤ ሁለት ክንድ ከስንዝር አቈልቋዩዋ፤ የሚሆን ከማይነቅዝ ሸምሸር ስጢን ከሚባል ዕንጨት ቈርጠህ ታቦትን ሥራልኝ አለው፤ አንድም ዕፀ ዘኢይነቅዝ ይላል፤ ከዚያም ራኅባ ባለው ጽፍሓ /ጽፍሑ/ ይላል፤ ሸምሸርስጢን የሚባል የማይነቅዘውን ዕንጨት ቈርጠህ አቈልቋዩዋ፤ ሁለት ክንድ ከስንዝር፤ ወርዷ ክንድ ከስንዝር፤ ቁመቷ ክንድ ከስንዝር የሚሆን ታቦትን ሥራልኝ አለው፤ ዘመርጡል ዘዘመን ዘስምዕ ዘሕግ ዘሥርዓት ዘርስት ዘምዕዋድ ዘዐውደ ዘመርጡል አላት፤ ሰቀልኛ ናትና ዘዘመን አላት፤ በዘመነ ሙሴ ተሠርታለችና፤ ዘስምዕ አላት፤ አምልኮቱ ይመሰከርባታልና ጸንቶባት ይኖራልና፤ ዘሕግ ዘሥርዓት አላት፤ ሕጉ ተነግሮባታል፤ ሥርዓቱ ተፈጽሞባታልና ዘርስት አላት፤ ምድረ ርስት ገብተውባታልና፤ /ምድረ ርስትን ወርሰውባታልና/፤ ዘምዕዋድ አላት፤ ከብበዋት ይሰፍራሉና፤ ዘዐውደ አላት፤ ይዞዋት ይዞራሉና፤

፲፩፤ ወትቀፍላ ወርቀ ንጹሐ እምውሳጤሃኒ ወእምአፍዓሃኒ ትቀፍላ ወትገብር ላቲ ቀጸላ ዘወርቅ በዓውዳ /ቀጸላ ወርቅ ዘዓውዳ/፤

ትቀፍላና ትቀፍላ አንድ ወገን ነው፤ ከውስጧ ጀምረህ እስከ እዳሪዋ ድረስ ንጹሕ ያለው ጽሩየ ሲል ነው፤ በጠራ ወርቅ ለብጣት፤ አንድም ውስጡዋን አፍአዋን በጠራ ወርቅ፤ አንድም በውስጥ በአፍአ የጠራ ወርቅ ለብጣት በዙሪያዋም የወርቅ ከንፈር ሥራላት፤

፲፪፤ ወትዘብጥ ጽበነ አርባዕ ዘወርቅ ወታነብር ላዕለ (ውስተ) ፬ቱ ምስማካቲሃ ጽበነ ክልኤተ (ክልኤ) ውስተ ምስማክ አሐዱ ወዕበነ ክልኤተ ውስተ ዳግም ምስማክ፤

የወርቁን አራቱን ቀለበት መትተህ ሥራው፤ አንድም ዕበነ ወርቅ አርባዕ ይላል፤ አራት የወርቅ ቀለበት ሥራ፤ አንድም ዕበነ ወርቅ ትዘብጥ አርባዕ ይላል፤ የወርቁን ቀለበት

www.ethiopianorthodox.org

አራት አድርገህ ሥራው፤ አንድም ዕበነ አርባዕ ዘወርቅ ዕበነ ወርቅ አርባዕ ይላል፣ የአራት ወቄት ወርቅ ቀለበት ሥራ፣ አንድም ወርቀ አርባዓ ትገብር ዕበነ አርባዓ ይላል፣ አራቱን ወቄት ወርቅ አራት አምባር አድርገህ ሥራው፣ ይኸነንም በአራቱ ማዕዘን አኑረው፤ ከዚያም ከአራቱ ሁለቱን ቀለበት በአንድ ወገን፣ ሁለቱን ቀለበት በአንድ ወገን አኑረው፣ አንድም ዕበነ ክልኤተ ውስተ ምስማክ፣ አሐዱ በክልኤቱ ምስማክ ወዕበነ ክልኤተ ውስተ ዳግም ምስማክ በክልኤቱ ምስማክ ይላል፣ ሁለቱን የወርቅ ቀለበት በአንድ ወገኑ በሁለት ወገን አድርገው፣ ሁለቱንም የወርቅ ቀለበት በሁለተኛው ወገን በሁለት ወገን አድርገው አለው፣ አብነት ዕበን አፃብዕ ኖፃዳት ሕልቀት ይላል፣ እንደዚሁ ያስተረጕማል፤

፲፫፣ ወግበር ላቲ መፃውርቲሃ እምዕፅ ዘኢይነቅዝ ወትቀፍሎሙ ወርቀ፣

መሸከሚያዋን ሸምሸርስጢን ከሚባል ከማይነቅዝ ዕንጨት ቈርጠህ ሥራው፤ አንድም ዕፀ ዘኢይነቅዝ ይላል የማይነቅዝ ሸምሸርስጢን የሚባለውን ዕን ጨት ቈርጠህ፣ ግበር መፃውሪሃ፣ መሸከሚያ አድርገህ ሥራው፤ አንድም ቈርጠህ መሸከሚያ አድርገው፣ መሸከ ሚያዎቹንም ወርቅ ለብጣቸው መፃውርቲሃ ባለው መፃውሪሃ ወርቀ ባለው በወርቅ ይላል፤

፲፬፣ ወታበውእ መፃውሪሃ ውስተ ውእቶን ዕበን አርባዕ ዘዲበ ምስማክ ዘታቦት፣

መሸከሚያዎቹንም ከታቦቲቱ በላይ በአራቱ ማዕዘን ወዳሉ ወደ አራቱ ቀለበቶች አግባው አለው፤

፲፭፣ መሳክሚሃ ለታቦት በዘይሰክ ምዋ ቦሙ በዕበን ዘዲበ ታቦት ለይኩን ድንባዛቲሃ ዘይትቀደዱ ወዘኢያንቀለቅሉ፣

በታቦቲቱ ላይ በአራቱ ማዕዘን ባሉ በአራቱ ቀለበቶች ሌዋውያን እሷን በእነሱ በሚሸከሙ ገንዘብ የታቦቲቱ መሸከሚ ያዎች፣ ለይኩኑ ድንባዛቲሃ መሳክሚሃ ያለውን ድንባዛቲሃ ብሎ ደገመው፣ ወለቅ ወለቅ የማይሉ ከላይ እስከ ታች የተሰማሙ ይሁኑ፣ አብነት መፃውር መሳክም ድንባዛት ይላል፣ እንደዚሁ ያስተረጕ ማል፤



፲፯፣ ወግበር ላቲ ተድባበ ዘወርቅ ንጹሕ ዘካዕበ እመት ወመንፈቀ እመት ኑኁ እመት ወመንፈቀ እመት ራሕቡ /ዕፍሑ/፣

ንጹሕን ጽሩይ ሲል ነው፣ አቄ ልቋዩ ሁለት ክንድ ከስንዝር፣ ወርዱ ክንድ ከስንዝር የሚሆን /የሆነ/ የጠራ ወርቅ ያለበት መግጠሚያ ለታቦቲቱ ሥራላት አለው፣ ይህ በታቦቲቱ በላይ እንደ አኀበር ያለ ነው፤

፲፰፣ ወግበር ክልኤተ ኪሩቤነ ዘወርቅ ፍሕቆ ወትገብሮሙ እምክ ልኤቱ ምስማካቲሁ ለተድባብ፣

ፍሕቆን ልዝብ ጽሩይ ሲል ነው፣ ሁለቱን ኪሩቤል ከለዘበ ከጠራ ወርቅ ሥራላት እነዚ ህንም ሁለቱን ኪሩቤል በመግጠሚያው ላይ ከሁለት ወገን አድርጋቸው፤ አንድም ሁለት ወገን በሆነ በመግጠሚ ያው ላይ አድርጋቸው፤ አንድም ለመግጠሚያው በሁለት ወገን አድርጋቸው ይኸ እም በ ሲሆን ነው፣ እስመ እምይተረጐም ለነበ ብዙኅ ያታ እንዲል፤

፲፱፣ ወይትገበር አሐዱ ኪሩብ እምጽንፈ ምስማክ ወአሐዱ ኪሩብ እምጽንፈ ካልእ ምስማክ ዘተድባብ ወትገብሩ ክልኤሆሙ ኪሩቤነ ላዕለ ክልኤሆሙ ምስማካት፣

አንዱ ኪሩብ በአንድ ወገን፣ አንዱም ኪሩብ በአንድ ወገን፣ በመግጠሚያው ላይ ይቀረጹ፤ አንድም እምጽንፈ ምስማክ አሐዱ እምጽንፈ ካልእ ምስ ማክ አሐዱ ይላል፣ በአንዱ መግጠሚያ ላይ አንዱ ኪሩብ፣ በሁለተኛው በአንዱ መግጠሚያም ላይ አንዱ ኪሩብ ይቀረፁ /ይቀረፅ/ አለ ይሠሩ፣ እኒህንም ሁለቱን ኪሩቤል በሁለቱ መግጠሚያዎች ላይ እንዲህ አድርጋችሁ ቅረፁዋ ቸው፤

፳፣ ወይኩኑ ኪሩቤን እንዘ ይረብቡ ክነፊሆሙ እመልዕልት ወይጼልሉ በክነፊሆሙ እመልዕልተ ተድባብ ወገጾሙ ይትናጸር በበይና ቲሆሙ ውነበ ተድባብ ይኩን ገጾሙ ለኪሩባን፣

ኪሩቤልም ከላይ ክንፉቻቸውን ዘርግተው መግጠሚያውንም በላይ ሸፍነው፤ አንድም በታቦቲቱ በላይ ያለ መግጠ ሚያውን ሸፍነው የኪሩቤል ፊታቸው ወደ መግጠሚያው ዞሮ እንደሚናከሱ ዶሮዎች ፊት ለፊት እርስ በርሳቸው ይተያዩ፣

፳፩፣ ወታነብር ተድባበ ዲበ ታቦት መልዕልቴሃ ወውስተ ታቦት ትወዲ ትእዛዘ ዘአነ እሁበከ፣

መግጠሚያውን በታቦቲቱ ላይ አኑረው፣ ከዚህ አስቀድሞ እኔ የሰጠሁህ አሠርቱ ቃላት የተ ጻፉባቸው ሁለቱን ጽላት በታቦቲቱ ውስጥ አኑር፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፪፣ ወእትኤመር ለከ በሀየ ወእት ናገረከ እምላዕለ ተድባብ ማዕከለ ክልዔቱ ኪሩባን እለ ሀለዉ ዲበ ታቦት ዘመርጡል ኵሎ ትእዛዘ ዘእኤዝዘከ ኀበ ውሉደ እስራኤል /ለውሉደ እስራኤል/፣

እኔ በዚያ ሁኜ ለአንተ የምገ ለጥልህ ከመግጠሚያውም ላይ ሁኜ አንተን የምነጋገርበት ፲ቱ ቃላት የተጻፉባቸው ሁለቱን ጽላት በታቦቱ ውስጥ አኑር፣ አንድም አንተ ከዚህ አስቀድሞ እኔ የሰጠሁህ ፲ቱ ቃላት የተ ጻፉባቸው ሁለቱን ጽላት በታቦቱ ውስጥ አድርግ፣ እኔም በዚያ ሁኜ ለአንተ እገለጽልሃለሁ፣ በእስራኤል ልጆች ዘንድ፤ አንድም ለእስ ራኤል ልጆች ብዬ እኔ የማ ዝዝህን ትእዛዝ ሁሉ ስቀልኛ በሆነች በታቦቱ ላይ ባሉ በሁለቱ ኪሩቤል መካከል ባለ በመግጠሚያው ላይ ሁኜ ይህን አድርግ እያልኹ እነጋገርሃለሁ አለው፣ ይኸውም ምሳሌ ነው፣ ታቦት የእመቤታችን፤ ወርቁ የንጽሕናዋ የቅድስናዋ፣ ፈለግ የልቡናዋ፣ ብጽብጽ ወርቅ የሁከት መንፈሳዊ፣ ያ እንዳ ይረጋ ሁከት መንፈሳዊም ከእመቤታችን ልቡና አይጠ ፋምና፣ ታቹ መቀመጫው የንጹሐት አንስት፣ ላዩ መግ ጠሚያው የንጹሐን አበው፣ ሁለቱ ክንፈሮች የሐና እና የኢያቄም፣ ወደ ውስጥ የገባች ዩቱ የእመቤታችን፣ በመካከ ላቸው እንደ ሆነች እመቤታ ችንም በትድምርተ ሐና ወኢያቄም ለመገኘቷ ምሳሌ ነው፣ ሁለት ክንድ ከስንዝር ምላልነቱ ከአዳም እስከ ኖኅ ያለው ዘመን ነው፣ ይህን ቢቈጥሩት ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ ስድስት ዘመን ነው፣ በሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ ስድስት ዘመን አርአያ ድንግል ታቦተ ኖኅ ለመገኘቷ ምሳሌ ነው፣ ክንድ ከስንዝር ወርዱ ከኖኅ እስከ ሙሴ ያለው ዘመን ነው፣ ይህን ቢቈጥሩት ሽህ ከስድስት መቶ ሀያ ሁለት ዘመን ነው፣ በሺህ ከስድስት መቶ ሃያ ሁለት ዘመን አርአያ ድንግል ታቦተ ሙሴ ለመገኘቷ ምሳሌ ነው፣ ክንድ ከስንዝር ቁመቱ ከሙሴ እስከ አማናዊት ድንግል ያለው ዘመን ነው፣ ይህን ቢቈ ጥሩት ሺህ ከስድስት መቶ ሀያ ሁለት ዘመን ነው፣ በሺህ ከስድስት መቶ ሃያ ሁለት ዘመን አርአያ ድንግል ታቦተ ኖኅ አርአያ ድንግል ታቦተ ሙሴ ምሳሌዎቿ የሚሆኑ በአምስት ሺህ ከአምስት መቶ ዘመን አማናዊት ድንግል ለመገኘቷ



ምሳሌ ነው፣ አራቱ ቀለበት በአራት ወገን ንጽሕት ናትና፣ ከርእይ ከገሢሥ ከሰሚዕ ከአፄ ንዎ፣ ሁለቱ መሎጊያ የፍቅረ ቢጽና የፍቅረ እግዚአብሔር፤ አንድም የዮሴፍና የሰሎሜ፣ በስደቷ ጊዜ ተከትለዋታልና፤ አንድም የአርኒና የሶፍያ ምሳሌ ናቸው፣ ባስልዮስን እኔ በተሳ ልኩበት ሁሉ አትለያቸው፣ በአጠገቤ ሣላቸው ብላዋለችና፤ በመግጠሚያው ላይ ሁለቱን ኪሩቤል እንደሚናከሱ ዶሮዎች አድርገህ ሣላቸው ቅረፃቸው ማለቱ በዓመት በዓመቱ ሊቀ ካህናቱ ከዚያ ገብቶ ከምሥዓል ከአዕናቀኍ ቃል ሰምቶ ይወጣ ነበር፣ እመቤታችንም በመልአከ ዑቃቢዋ በቅዱስ ሚካኤል ተጠብቃ፣ ከመልአከ መበሥሯ ከቅዱስ ገብርኤል ቃል ሰምታ አካላዊ ቃልን ወልዳ በቃል ሰብአዊ ሲያስተምር ለመገኘቱ ምሳሌ ነው፤

፳፫፣ ወግበር ማዕደ እምዕፅ ዘኢይ ነቅዝ ኑኁ ካዕበ እመት ወራኅቡ እመት ወቆሙ እመት ወመንፈቀ እመት፣

ሸምሸርሰጢን ከሚባል ከማይ ነቅዝ ዕንጨት ቈርጠህ ማዕድ ሥራ፣ ይኸውም ሥራ ያልከሁ ማዕድ አቈልቋዩ ሁለት ክንድ፣ ወርዱ ክንድ፣ ቁመቱ ክንድ ከስንዝር ነው፤

፳፬፣ ወትቀፍሎ ወርቀ ንጹሐ ወግበር ሎቱ ቀጸላ በዓውዱ፣

ጽሩየ ሲል ነው፣ ይኸንንም በጠራ ወርቅ ለብጠው፣ በዙሪያ ውም ክንፈር አውጣለት፤ አንድም ክንፈር በዙሪያው አውጣለት፤

፳፭፣ ወግበር ሎቱ ክንፈረ መጠነ ፬ቱ አዝብዕ በዓውዱ፣

በዙሪያው ያለ የክንፈሩን ክፈፍ ጋት ሙሉ አድርግለት፤

፳፮፣ ወግበር ፬ተ አውቃፋተ ዘወርቅ ወአንብር ውስተ ፬ቱ መዓዝኒሁ ለማዕድ ዲበ ፬ቱ እገሪሁ፣

የወርቅ አምባር አራት ሥራ ለት፤ አንድም አራት የወርቅ አምባር ሥራለት፣ ይኸንንም ሠርተህ በማዕድ በአራት እግሩ በላይ ባለ ክንፈሩ በአራቱ ማዕዘን አኑረው፤

፳፯፣ ወይኩኑ አውቃፋት መንገለ ክንፈሩ ለማዕድ ወይኩኑ አውቃ ፋቲሁ አብያተ ለመፃውሪሁ ዘያነ ሥኡ ማዕደ፣

ይከኑና ይኩኑ አውቃፋትና አውቃፋት አንድ ወገን፣ በማዕድ ክንፈሮች ላይ ያሉ የወርቅ አምባሮች ማዕድን ለሚያነሡ መሸከሚያዎች ቤት ይሁኑ፤ አንድም እየራሱ ለማውጣት አምባሮች በማዕድ ክንፈር ላይ

www.ethiopianorthodox.org

በአራቱ ማዕዘን ይሁኑ፣ በአራቱ ማዕዘንም ሁነው ማዕድን ለሚያነሡ መሸከሚያዎች ቤት ይሁኑ፤

፳፯፣ ወግበር መሣውሪሁ እምዕፅ ዘኢይነቅዝ ወትቀፍሎሙ ንጹሐ ወርቀ ወቦሙ ይትገኃሥ ማዕዱ፣

መሸከሚያውንም ሸምሸር ሰጢን ከሚባል ከማይነቅዝ ዕንጨት ቁርጠህ ሥራው፤ አንድም ሸምሸርሰጢን ከሚባል ከማይነቅዝ ዕንጨት ቁርጠህ አድርገው አለው፣ ሌላ ዕንጨት አይሁን ሲል ነው፣ ንጹሕን ጽሩየ ሲል ነው፣ መሸከሚያዎችንም በጠራ ወርቅ ለብጣቸው፣ ማዕዱም በእነሱ ይነሣ አለ፣ እስራኤል በተጓዙ ጊዜ ነው፤

፳፱፣ ወግበር መጻብሒሁ ወአጽሕልቲሁ /ወአጽሕልቲሁ/ ወመዳምሒሁ ወመዋጽሒሁ በዘቦቱ ታወፅሕ እምንጹሕ ወርቅ ግበሮሙ፣

መጻብሒሁ ታላቅ ሥልስ ወጭት፣ ወአጽሕልቲሁ ታናሽ ሥልስ ወጭት፣ ወመዳምሒሁ ማንካ፣ ይህን ባለው መአንፍቲሁ ይላል በዓረብ ምላሽ፣ ዘይቱን የምታፈስስበት ጽዋውን፤ አንድም እንጻለ ይሆናል፣ ዘይቱን በምታፈስስበት ገንዘብ ጽዋውንም ከጠራ ወርቅ ሥራላቸው፤

፴፣ ወአንብር ኅብስተ ዴቢ ማዕድ በቅድሜየ ዘልፈ፣

ኅብስቱንም ዘወትር በፊቴ ጧት ማታ ሠዋው አለ፣ ኅብስቱ ዐሥራ ሁለት ነው፣ ከዚህ ስድስቱ ጧት፣ ስድስቱ ማታ ይሠዋ ነበር፣ ይኸውም ምሳሌ ነው፣ ማዕድ የኢየሩሳሌም፣ ዓሥራ ሁለቱ ኅብስት የዓሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል፣ ከዚህ ስድስቱ ጧት፣ ስድስቱ ማታ ይቀርብ ነበር፣ ዓሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤልም ስድስቱ በጌባል፣ ስድስቱ በገሪዛን ቀርበዋልና፤ አንድም ማዕድ የደብተራ ኦሪት፣ ዓሥራ ሁለቱ ኅብስት የአሥራ ሁለቱ ቃላተ ኦሪት፣ ዐሥራ ሁለት ያላቸው ፲ቱ ቃላት፣ ሕግ፣ ርትዕት፣ ሃይማኖት ናቸው፣ ከዚህ ስድስቱ ጧት ስድስቱ ማታ ይሠዋ ነበር፣ እነዚህንም ቃላት መሥዋዕተ ነግህ፣ መሥዋዕተ ሠርክ ሲሠዉ ይናገሯቸው /ያደርሷቸው/ ነበርና፤ አንድም ማዕድ የሕገ ኦሪት፣ ኅብስት የሕገ ወንጌል፣ በዚያ ላይ መሠዋቱ ሕገ ወንጌል በሕገ ኦሪት ላይ የመሠራቱ ምሳሌ፣ ከዚሁ ስድስቱ ጧት፣ ስድስቱ ማታ ይሠዋ ነበር ስድስቱ ቃላተ ወንጌልም ጧት ማታ የመነገራቸው ምሳሌ ነው፣ አራቱ



ንዋያት የአራቱ ወንጌላውያን ምሳሌ ነው፣ እነዚህም መጻብሕ፣ አጽሕልት፣ መዳምሕ፣ መዋጽሕ ናቸው፤ አንድም ማዕድ የመስቀል፣ ኅብስት የጌታ፣ ስድስቱ ጧት ስድስቱ ማታ ይቀርብ ነበር፣ ስድስቱ ቃላተ ወንጌልን የሠራ ጌታ ጧት ማታ እየተሠዋ ስንቀበለው የመኖራችን ምሳሌ ነው፣ አራቱ ንዋያት የአራቱ ወንጌላት፤ አንድም የአራቱ ሊቃነ ጳጳሳት ምሳሌ ነው፤

፴፩፣ ወግበር ተቅዋመ ማኅቶት እምወርቅ ንጹሕ ፍሑቅ ወለተቅዋመ ማኅቶት ዓምዳ ወአብሪኢሃ ወመአኃዚሃ ወክበበ ርእሳ ወጽጌያቲሃ እምኔሃ ይትገበሩ፣

ከጠራ ከለዘበ ወርቅ ፋናው የሚቀመጥባት መቅረዝንም ሥራ፣ ፋናው ለሚቀመጥባት ለተቅዋም ዓምዳ ዓምድነቷ፣ ወአብሪኢሃ ግራ ቀኝ ያሉ አዕቆቿ፣ ወመዓኃዚሃ ሸቦዎቿ፣ ወይም መሸቢያዎቿ፣ ወክበበ ርእሳ መግላሊቷ፣ ወጽጌያቲሃ አበባዎቿ፣ ከእሷ የማይለዩ ሥረወጥ ሁነው ይሠሩ፣ እምኔሃ ባለው እምውስቴታ ይላል፤ እንደዚሁ ያስተረጉማል፤

፴፪፣ ወስድስቱ አብራዕ እለ ይትገበሩ በገቦሃ ለተቅዋመ ማኅቶት ፫ቱ አብራዕ እምጀጹ ፍናሃ ወ፫ቱ አብራዕ እምፍናሃ ካልእ /እምካልዕ ፍናሃ/

ፋናው በሚያበራባት በተቅዋም በጐኗ የተሠሩ አጽቆች ስድስት ናቸው፣ እነዚህም ሦስቱ በአንድ ወገን፣ ሦስቱ በአንድ ወገን ናቸው፤

፴፫፣ ወሠለስቱ መአኃዚሁ እለ የኀብሩ ምሳሌ ለፅጹ ክበበ ርእስ ጽጉይ ከማሁ ለስድስቲሆሙ አብራዕ እለ ይወፅኡ እምተቅዋመ ማኅቶት፣

በሥራ አንድ የሆኑ የተባበሩ መሸቢያዎች /ሸቦዎች/ ሦስት ናቸው፤ አንድም ሦስቱ ሸቦዎች፣ በሥራ የተባበሩ ናቸው፣ ለአንዱ መግላሊት አበባ እንዳለው መብራቱ ከሚበራበት ከተቅዋም ሥረወጥ ሁነው ለተሠሩ ለስድስቱ መግላሊቶችም አበባ አላቸው፤

፴፬፣ ወለተቅዋመ ማኅቶት መአኃዚሃ ፬ቱ ወጽጌያቲሃ፣

መብራቱ ለሚበራባት ለተቅዋም መሸቢያዎች ሸቦዎችዋ አራት ናቸው፣ አበባዎቿም ከዚያው ሥረወጥ ናቸው፤

፴፭፣ ወክበብ መትሕተ ፪ቱ ፪ቱ አብራዕ እለ ይወፅኡ እምተቅዋመ ማኅቶት፣

ፋናው ከሚበራባት ከተቅዋም ሥረወጥ ሁነው በተሠሩ በሁ

www.ethiopianorthodox.org

ለት በሁለት አጽቆች በታች ሦስት መሽቢያዎች /ሽቦዎች/ አሉ፤ ምነዋ መአኃዚሃ ፬ቱ ብሎ የለም? ስለምን እንዲህ አለ ቢሉ እውነት ነው፤ ከዚያ ፬ቱ ያለ ከታች ከእግሩ ያለውን መቀመጫውን ቈጥሮ ነው፤ ከዚህ ግን ከአዕቆች ጋር ያለውን ሽቦ ቆጥሮ ሦስት አለ፤

፴፬፤ ክበባቲሆሙ ወአብራኢሆሙ እምኔሃ ይኩኑ ኵሎሙ ፍሕቆ እም ፩ዱ ወርቅ ንጹሕ፤

መግላሊቶቻቸው አዕቆቻቸው ከእሷ የማይለዩ ሥረወጥ ይሁኑ፤ እነዚህም ሁሉ ከአንድ ከለዘበ ከጠራ ወርቅ የተሠሩ ናቸው፤

፴፭፤ ወትገብር መኃትዊሃ ፯ተ ወትሠርዕ መኃትዊሃ ወያበርህ እም አሐዱ ገጽ ወዘእምድኅሬሃ፤

መግላሊቷን ሰባት አድርገህ ሥራው፤ አንድም ምንባረ ፈትሏን ሰባት ሰባት አድርገው፤ መግላሊቷን አዘጋጀው፤ አንድም በመግላሊቷ ውስጥ ምንባረ ፈትሏን ሰባት ሰባት አድርገህ አዘጋጀው፤ አንድም በምንባረ ፈትሏ ውስጥ ሰባት ሰባት ፈትል አኑርበት፤ ዘይቱንም አድርግበት፤ አንድም ወትገብር መኃትዊሃ ስድስተ ይላል፤ አጽቆቿን ስድስት አድርገው፤ ሰባተኛውን ግን ሥረወጥ አድርገው፤ በዚያ የገባው ዘይት አዕጹቅን እንዲገልጻቸው፤ ይኸውም ከሥረወጡ ሌላ ሦስቱ በአንድ ወገን ሦስቱ በአንድ ወገን ሁኖ ያብራ፤ አንድም ሦስቱ በፊት፤ ሦስቱ በኋላ ሁኖ ያብራ፤ አንዱን ለአንዱ ድኅር ይለዋልና ስለዚህ ነው እንጂ ቅድምና እና ድኅር የላቸውም፤ አንድም ስድስቱ አጽቆች በሦስት መሽቢያ ተይዘው ከሦስት ላይ ናቸው፤ ለሦስተኛው ሁለተኛውን፤ ለሁለተኛው መጀመሪያውን ድኅር አለው፤ አንድም አንዱን ለአንዱ ድኅር ይላልና ብሎ ለመጀመሪያው ሁለተኛውን፤ ለሁለተኛው ሦስተኛውን ድኅር አለው፤

፴፮፤ ወበዘየሚንይዋ ወጽዋዓቲሃ ዘወርቅ፤

ፈትሉን የሚስቡበት ወለባውን የሚኰስትሩበት መቀሱ፤ ዘይቱን የሚቀዱበት ጽዋው፤ ከጠራ ከለዘበ ወርቅ የተሠራ ነው፤

፴፯፤ መክሊተ ወርቅ ትገብራ፤

ግበራ ሲል ነው፤ ወትቀብዓ በፒሳ እንዲል፤ ቅብዓ ሲል፤ ይህን ሁሉ ከአንድ መክሊት ወርቅ ሥራው፤ አንዱ መክሊት ሺህ ከሰባት መቶ ሃያ



ስምንት ወቄት ነው፤ ዐሥራ ሁለቱ ወቄት አንድ ልጥር፤ ዐሥራ ሁለቱ ልጥር አንድ ምናን፤ ዐሥራ ሁለቱ ምናን አንድ መክሊት ነው፤ ምናንን ዐሥር ያሉ እንደሆነ መክሊትም ይጐድላል፤

፴፰፤ ወእሳንተ ኵሎ ንዋያቲሃ ግበር በአርአያ ዘከመ አርአይኩከ በደብር፤

በደብረ ሲና ሁኜ በደብረ ሲና ሁነህ ያሳየሁኽን የነገርኩኽን ሥራ፤ አንድም እንዳሳየሁህ እንደነገርኩኽ አድርገህ ሥራ አለው፤ ሐተታ እንዳለፈው ይኸውም ምሳሌ ነው፤ ተቅዋም የስነ ፍጥረት፤ ሦስቱ መሽቢያ የሦስቱ ዕለታት፤ እሑድ፤ ሰኞ፤ ማክሰኞ ናቸው፤ ስድስቱ አዕጹቅ የስድስቱ ዕለታት፤ ሐሙስ፤ ዓርብ፤ ቅዳሜ፤ እሑድ፤ ሰኞ፤ ማክሰኞ ናቸው፤ መካከሉ ሥረወጡ የዕለተ ረቡዕ በዚያ የገባው ዘይት አዕፁቅን እንዲገልጻቸው በዕለተ ረቡዕ የተፈጠሩ ፀሐይ ጨረቃ ከዋክብት ሰባቱን ዕለታት ሲያበሩ ለመኖራቸው ምሳሌ፤ አንድም መላ ተቅዋም የዘመነ አበው፤ ከፍ ብለህ በአንድ መሽቢያ ቃጥተህ ተወው ማለቱ በዘመነ አበው ምክር እዝናት ተደርጓል እንጂ መጻሕፍት አልተጻፉም፤ ከፍ ብለህ በሦስት መሽቢያ ቃጥተህ ተወው ማለቱ የዘመነ መሳፍንት፤ በዘመነ መሳፍንት ምክር እዝናት ተደርጓል /መምህራን ተሠርተዋል/ መጻሕፍት ተጽፈዋል፤ ስድስቱ አዕፁቅ የቀሩት መጻሕፍት፤ ሥረወጥ የወንጌል ምሳሌ፤ በዚያ የገባው ዘይት አዕፁቅን እንዲገልጻቸው ምንም ብሉይ ሐዲስ ቢባል ወንጌልን ሳይገዘ የሚተረጐም የለምና፤ ብርሃን የሰብአ ሥላሴ የመምህራን፤ አዕፁቅን የሚገልጻቸው ብርሃኑ ነው፤ የመጻሕፍትንም ምሥጢራቸውን የሚገልጹልን መምህራን ናቸውና፤ ያልተነበበውን አንብበው፤ ያልተተረጐመውን ተርጒመው፤ አንድም መላው ተቅዋም የእመቤታችን፤ ወርቁ የንጽሕናዋ የቅድስናዋ፤ ሦስቱ መሽቢያ የንጽሐ ሥጋ የንጽሐ ነፍስ የንጽሐ ልቡና ምሳሌ፤ አንድም ሦስቱ መሽቢያ የሦስትነት፤ ማሠሪያው የጽንዓ ተዋሕዶ፤ ስድስቱ አዕፁቅ የእኛ፤ ሥረወጥ የጌታ፤ ንሕነ አባል ወውእቱ ርእስ እንዲለው፤ በዚያ የገባው፤ አዕፁቅን እንዲገልጻቸው፤ የእሱን የባሕርይ ሕይወቱን ለእኛ የጸጋ አድርጎ ይሰጠናልና፤ ምንባረ ፈትል የማኅዐደ፤ ፈትል

www.ethiopianorthodox.org

የትስብእት፣ እሳት የመለኮት፣ ዘይት የመንፈስ ቅዱስ፣ እሳቱ ንና ፈትሉን የሚያገናኘው ዘይቱ ነው፣ ያነባ የከፈለ ያዋሐደ መንፈስ ቅዱስ ነውና፣ ማፈኛ መኰስተሪያ፣ ወለባ፣ በሦስት ወገን ንጽሕት ናትና፣ ይህንም ሰባት ሰባት ምንባረ ፈትል ቢቈጥሩት አርባ ዘጠኝ ይሆናል፣ እመቤታችን ጌታን ከወለደች በኋላ በዚህ ዓለም የኖረችው ዘመን ፵፱ ዘመን ነው፣ ብርሃን ዜና ሞቷን የሚ ያስተምሩ የጴጥሮስ የጳውሎስ ምሳሌ ነው።

## ምዕራፍ ፳ወ፮

### ግባኤ

፩-፱፤ ወለደብተራ ግበር ላቲ ፲ተ አዕፃደ እምቢሶስ እዑፍ ወእም ኅብረ ያክንት ወእምኅብረ ከብድ ወለይ ክዑብ ወኪሩቤነ ግበሩ ወበግብረ ምእናም ትገብርዎ፤

ለደብተራ አሪት እዕፍ ሁኖ ከተሠራ ከነጭ ሐርና ከሰማያዊ ሐር፣ ከብጫና ዕዕፍ ሁኖ ከተሠራ ከቀይ ሐር ዐሥር ፈርጅ ሥራላት፣ ከእሊህም ከአራቱ ኅብር የኪሩቤልን ሥዕል ቅረፀ /ሥሩ/፣ ኪሩቤ ልንም ስትሠሯቸው የኪሩቤ ልን ሥራ በግብረ መርፌ ሥራ ሥሩት፤ አንድም ግብረ ምእናም ትገብርዎ ይላል፣ የግብረ መር ፌውን ሥራ ኪሩቤልን አስመ ስላችሁ ጥለፉት፤

፪፤ ወኑኁ ለአሐዱ ዓፀድ ፳ወ፰ቱ በእመት ወራኅቡ ፬ቱ በእመት ለ፩ዱ ዓፀድ በመሥፈርቱ ከማሁ ለይኩን፤

የአንዱ ፈርጅ አቈልቋዩ /፳፰/ ሃያ ስምንት ክንድ ነው፣ ወርዱ አራት ክንድ ነው፣ በመስፈ ርቱ ለአሐዱ ዓፀድ ሲል ነው፣ በአንዱ ፈርጅ በአቈልቋዩ በወርዱም ልክ የዘጠኙም ፈር ጆች ወርዳቸውም አቈልቋያ ቸውም እንደዚሁ ይሁን፤ አንድም የዘጠኙም ፈርጆች አቈልቋያቸውም ወርዳቸውም እንደ አሥረኛው ፈርጅ አቈ ልቋይ ወርድ ይሁን፤ አንድም በዓሥረኛው ፈርጅ ወርድ አቈልቋይ ልክ ይሁን፤

፫፤ ወኃምስቱ አዕፃድ ይሳመኩ ፩ዱ ምስለ ካልኡ ወ፭ቱ አዕፃድ ይሳመኩ በበይናቲሆሙ፤

ኃምስቱና ኃምስቱ ይሳመኩና ይሳመኩ አዕፃድና አዕፃድ አንድ ወገን፣ ነው፣ ፭ቱ ፈርጅ አንድ ወገን፣ ፭ቱ ፈርጅ አንድ ወገን ሁነው ፩ዱ ወካልኡ፣ አንዱ ከአንዱ ጋር ይገናኙ፣ ይሳመኩ ባለው ይስናስሉ ይላል፣ እንደዚሁ ያስተረጕ ማል፤



፬፤ ወግበር ሎሙ ፶ መማስጠ ዘኅብረ ያክንት ላዕለ ከንፈረ ፩ዱ ዓፀድ እምአፍአ ወ፶ መማሥጠ ግበር በጽንፈ አጸድ ካልእ እምገጸ አፍአ ገጸሙ እንዘ ያሰምክ ይሳመኩ በበይናቲሆሙ

ከመ ይሳመኩ ሲል ነው፣ እርስ በሳቸው ከንፈር ለከንፈር ይገናኙ ዘንድ፤ አንድም እንዘ ያሰምክ በበይናቲሆሙ ይላል፣ እርስ በርሳቸው እንዲያገናኛ ቸው በአንዱ ፈርጅ ከንፈር በጫፉ፣ አንድም ከጫፉ ከሰማ ያዊ ሐር የተሠራ ፶ ተባት ቍልፍ በሁለተኛውም ፈርጅ ከንፈር በጫፉ፤ አንድም ከጫፉ፤ ከሰማያዊ ሐር የተሠራ ፶ ተባት ቍልፍ ሥራላቸው አለው፤

፮፤ ወግበር ፶ ኖኅዳተ ዘወርቅ ወደምር አዕፃዳተ ፩ደ ምስለ ካልኡ በኖኅዳት ወይኩን ፩ደ ደብተራ፣

፶ የወርቅ ቀለበት ሥራ፤ አንድም ኖኅዳተ ፶ ዘወርቅ ይላል፣ የወርቅ ፶ ቀለበት ሥራ ፈርጆችን አንዱን ከአንዱ ጋር በቀለበት አገናኘው፣ ድንኳ ኑም በቀለበት አንድ ይሁን፣ አንድም ፈርጁ ሁሉ በቀለ በት አንድ ድንኳን ይሁን፤

፯፤ ወግበር ፲ተ ወ፩ደ ዐዕፃደ ዘሠቅ ዘይከድኖ እምላዕሉ ለደብተራ፣

ድንኳኑን ከላይ ጀምሮ እስከ ታች ድረስ የሚሸፍነው የብስጥ ዓሥራ አንድ ፈርጅ ሥራ፣

፰፤ ወለለ፩ዱ ሠቅ ኑኁ ፴ በእመት ወራኅቡ ርብዕ በእመት ከመዝ አምጣኒሆሙ ለ፲ወ፩ዱ፣

የብስጥ እየአንዳንዱ አቈልቋዩ ፴ ክንድ ነው፣ የወርዱም ስፋቱ አራት ክንድ ነው፣ የአሥራ አንዱም ፈርጆች መጠናቸው ልካቸው እንደዚህ ነው፤

፱፤ ወደምር ፭ተ ሠቃተ በበይና ቲሆሙ፣ ወ፮ተ ሠቃተ ደምር በበይናቲሆሙ ወታዐጽፍ ስድስተ ሠቃተ እመንገለ ገጸ ደብተራ፣

አምስቱን ፈርጅ ብስጥ በየራሳ ቸው በቀለበት አንድ አድርጋ ቸው፣ ስድስቱን ፈርጅ ብስጥም በየራሳቸው በቀለበት አንድ አድርጋቸው፣ ስታለብስም ስድስቱን ፈርጅ ብስጥ ከደብተራ አሪት ከፊቷ ጀምረህ ወደ ኋላዋ አልብስ፣ ከዚያ ቀጥለህ አምስቱን ፈርጅ ብስጥ አልብስ፣ እንዲህ መሆኑ እንዲተሳለፍ ነው፤

፲፤ ወግበር ፶ መማስጠ ላዕለ ከንፈረ አሐዱ ሠቅ ወ፶ መማስጠ ግበር ውስተ ከንፈረ ሠቅ ካልእ በዘትዴምር ቀዳማየ፣

በከመ ደመርከ ቀዳማየ ሲል ነው፣ የቀድሞውን ዓሥሩን ፈርጅ አንድ እንዳደረግኸው በብስጥም በአንዱ ብስጥ ፈርጅ ከንፈር ላይ ሃምሳ ተባት ቍልፍ

www.ethiopianorthodox.org

በሁለተኛውም ብስጥ ፈርጅ ከንፈር ላይ ፶ ተባት ቀለፍ ሥራበት አለው፤

፲፩፣ ወግበር ፶ ኆፃጸተ ዘብርት ወትዴምር መማስጠ በኆፃጸት ወተኃብር ሠቃተ ወይኩን አሐደ፣

ከላይ ፶ ተባት ቀለፍ ሥራ ብሎት ነበርና ከዚህም የብረት እንስት ቀለፍ ፶ ሥራ፤ አንድም የብረት ፶ እንስት ቍልፍ ሥራ አለው፣ ተባት ቍልፋንም በእንስት ቍልፍ አያይዘው፣ አምስቱን ፈርጅ ብስጥና ስድስቱን ፈርጅም በተባት ቍልፍና በእንስት ቀለፍ አንድ አድርገው፣ አምስቱ ፈርጅ ብስጥና ስድስቱ ፈርጅ ብስጥም በቀለበት አንድ ይሁን፤ አንድም አም ስቱ ፈርጅ ብስጥና ስድስቱ ፈርጅ ብስጥ በቀለበት አንድ ድንኳን ይሁን፤

፲፪፣ ወታኅብር ዘይፈደፍድ እምሠርቅ ዲበ ደብተራ ዘተርፈ ወትከድን ከዋላ ደብተራ፣

ከብስጥ የተረፈውን ከአራቱ ኀብር የበለጠውን በአራቱ ኀብር ላይ አልብሰው፤ አንድም ከብስጥ የተረፈውን ከአራቱ ኀብር የበለጠውን ቀድሞ ሳይለብስ በቀረው በአንዱ ክንድ ሙሉ ላይ አልብሰው፣ ስታለብስም በፊት በኋላ ያለውን አልብሰው፤

፲፫፣ እመተ ዘይተርፍ ሠቃተ ደብተራ (እምገጸሚሃ) እምግድሚሃ፣ እምአፍአሃ ለደብተራ እምለፌ ወእምለፌ ይከድኖ፣

የምታለብሰውም ከከበሮ ቤት እስከ ደጃፉ ከግራ እስከ ቀኝ ያለውን አምድ ከብስጥ የተረፈው ክንድ ሙሉ ይሸፍነው፤

፲፬፣ ወአግብር ማዕሰ በግዕ ኀሡየ ዘሥርየቱ ያክንት ዘይከድኖ ለሠቅ እምላዕሉ፣

ብስጥን ከላይ ጀምሮ እስከ ታች ድረስ የሚሸፍነው ተለፍቶ ቀለም የገባ ማዕሰ መጸዊትን ሥራላት፤

፲፭፣ ወአግብር አዕማደ ለደብተራ እምዕፅ ዘኢይነቅዝ፣

ሽምሽርሰጢን ከሚባል ከማይነ ቅዝ ዕንጨት ቈርጠህ ለደብ ተራ አዕማድን ሥራላት፤

፲፮፣ ዘዓሥር በእመት ቆሙ ለአሐዱ አምድ ወራኅቡ እመት ወመንፈቀ እመት፣

ይኸውም የአንዱ ዓምድ ቁመቱ ዐሥር ክንድ ወርዱ ክንድ ከስንዝር ነው፤

፲፯፣ ወመሳምክተ ሥረዊሁ ፪ቱ ለ፩ዱ ዓምድ እንዘ ይሳመክ ዓምድ ለዓምድ ከማሁ ግበር ለለኵሉ አዕማደ ደብተራ ፣

ከመ ይሳመክ፣ ዓምድ ከዓምድ ጋር ተጠግቶ ይቆም ዘንድ፣



አንድም እንዳለም ይሆናል፣ አምድ ከአምድ ጋር ተጠግቶ ሲቆም አንዱ ዓምድ በሁለት ጥፍሩ የሚቆምበት ምዕማዱ ሁለት ነው፣ ለአንዱ ዓምድም እንዲህ እንዳለው /እንደዚህ አድርገህ እንድትሠራለት/ ለደብተራ አሪትም አዕማድ ሁሉ እንደዚህ አድርገህ ሥራላቸው፤

፲፰፣ ወአግብር ፳ አዕማደ መንገለ አዜብ፣

ኻያውን አዕማድ በአዜብ አኩል እንዲቆሙ አድርገህ ሥራቸው፤

፲፱፣ ወግበር ሎሙ ምዕማደ ዘብሩር ፵ዓ ለ፳ አዕማድ ፪ቱ ምዕማዱ ለአሐዱ ዓምድ በክልኤሆሙ ገጸቲሁ ወ፪ቱ ምዕማዱ ለ፩ዱ ዓምድ በ፪ኤሆሙ ገጸቲሁ፤

ለኻያው አዕማድ አርባ የብር ምዕማድ ሥራላቸው፣ ለአንዱ ዓምድ በሁለቱ ጥፍሮቹ የሚቆ ምባቸው ሁለት ምዕማድ ናቸው፤ አንድም የአንዱ ዓምድ ሁለቱ ምዕማዶቹ በሁለቱ ጥፍሮቹ የሚቆምባቸው ናቸው፣ አንዱ አምድ በሁለቱ ጥፍሮቹ የሚቆ ምባቸው ምዕማዱ ሁለት ናቸው፤ አንድም የአንዱ ዓምድ ሁለቱ ምዕማዱ በሁለቱ ጥፍሮቹ የሚቆምባቸው ናቸው፤

፳፣ ወካልእ እምገጸ ሰሜን ፳ አዕማድ ፣

ሁለተኛው በሰሜን በኩል ሃያ አዕማድ ይቁሙ፤ አንድም ወካልአን እምገጸ ሰሜን ፳ አዕማድ ይላል፤ በአዜብ በኩል ከቆሙት ሌሎች ከሰሜን ጀምረው እስከ ምሥራቅ ድረስ ሃያ አዕማድ ይቁሙ፣ እምገጸ ሰሜን ባለው እምገጸ ምዕዋፍን ይላል /ጥሬ/ እንደዚሁ ያስተረ ጉማል፤

፳፩፣ ወምዕማዲሆሙ ዘይዐውሩ አዕማደ ፵ዓ ዘብሩር ለለ፩ዱ ዓምድ ፪ቱ ምዕማድ እምክልኤሆሙ ገጸቲሁ፣

አዕማዱን የሚሸከሙ ምዕማዶ ቻቸውም የብር ሥራ የሚሆኑ ዓርባ ናቸው፣ እየአንድ አንዱ ዓምድ በሁለቱ ጥፍሩ የሚቆ ምባቸው ምዕማዱ ሁለት ሁለት ናቸው፤ አንድም እየአንዳንዱ ዓምድ ሁለት ሁለቱ ምዕማዶቹ በሁለቱ ጥፍሩ የሚቆምባቸው ናቸው፤

፳፪፣ ወእምድኅር እምገጸ ደብተራ መንገለ ባሕር ግበር ፮ተ አዕማደ፣

ከፊት በስተኋላ በምዕራብ በኩል የሚቆሙ ስድስት አዕማድ ሥራ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፫፣ ወ፪ኤቱ አዕማደ ግበር ዓዲ ለመዓዝነ ደብተራ እምድኅር ወዕሩያነ ይኩኑ፣

በስተኋላ ዳግመኛ ለማዕዘን ማቅኛ መሰብሰቢያ የሚሆኑ ሁለቱን አዕማድ ሥራ እለዚህም ከላይ እስከ ታች የተካከሉ ይሁኑ፣

፳፬፣ ወይዳረጉ ፍጹመ እምላዕሉ እስከ ታሕቱ፣

ደርገን ይዞ ይዳረጉ አለ፣ እነዚህም ከላይ ጀምሮ እስከ ታች ድረስ፤ አንድም እምታሕቱ እስከ ላዕሉ ከታች ጀምሮ እስከ ላይ ድረስ አንድ ይሁኑ፤

ወከማሁ ግበር ለ፪ኤሆሙ መዓዝን

አሁን እንደተናገርኩት ለሁለቱ ማዕዝን ማቅኛ መሸቢያ ሁለት ሁለት ምዕማድ ሥራላቸው፣ ለ፪ኤሆሙ መዓዝን ባለው ለ፪ኤሆሙ ቀፈረ ዓምድ ይላል አብነት፤

፳፭፣ ወይኩኑ ፰ተ አዕማደ ወምዕማዲሆሙ ዘብሩር ፲ቱ ወ፮ቱ ወለለ፩ዱ ዓምድ ፪ቱ ፪ቱ ምዕማዱ እም፪ኤሆሙ ገፃቲሁ፣

አዕማድ ስምንት ይሁኑ፣ የብር የሚሆኑ ምዕማዶቻቸውም ዓሥራ ስድስት ናቸው፣ እያንዳንዱ ዓምድም ምዕማዱ ሁለት ሁለት ናቸው፣ ያ ግን በሁለቱ ጥፍሩ የሚቆምባቸው፤ አንድም በሁለቱ ጥፍሩ የሚቆምባቸው ሁለት ሁለቱ ምዕማድ ለእያንዳንዱ ዓምድ ናቸው፤

፳፮፣ ወግበር መናሥግተ ለአዕማደ ደብተራ እምዕፀ ዘኢይነቅዝ ፭ተ መናሥግተ እምአሐዱ ገጽ፣

ሸምሸርስጢን ከሚባል ከማይ ነቅዝ ዕንጨት ቁርጠህ ለደብተራ አሪት አዕማድ ማገር ሥራላቸው፣ እነዚህንም አምስቱን ማገር በአንድ ወገን አድርጋቸው አለ በአዜብ ነው፤

፳፯፣ ወኃምስተ መናሥግተ እምካልእ ገጽ ወኃምስተ መናስግተ ዘመንገለ ባሕር፣

አምስቱን ማገር በአንድ ወገን አድርገው አለ፣ በሰሜን ነው፣ አምስቱን ማገር በምዕራብ በኩል አድርገው፤

፳፰፣ ወግበሮ ለመንሥግ ዘማዕከል ይዕዱ በማዕከለ አዕማድ እምጽንፍ ኀበ ጽንፍ፣

ለማገሩ ከዳር ጀምሮ እስከ ዳር ድረስ በአዕማዱ መካከል ውስጥ ለውስጥ እንዲሔድ አድርግለት ዘማዕከል ይዕዱ ባለው በጥበብ ይዕዱ ይላል፣ እንደ ሲዖሎ መዝጊያ፣ እንደ ሸማኔ መወርወሪያ ውስጥ ለውስጥ እንዲሔድ አድርጎታል፤ አንድም ከዳር ጀምሮ እስከ ዳር ድረስ በአዕማዱ መካከል በኩላብ እየጠረቀ እየጠረቀ ሠርቶታል፤ አንድም አዕማዱንም ፈልፍሎ ማገሩንም ፈልፍሎ እንደናርጅ ገጥሞታል፤

፳፱፣ ወለአዕማድኒ ወለመናሥግትኒ ቅፍሎሙ ወርቀ ወግበር አውቃፋተ ዘወርቅ ዘይከውኑ አብያተ ለመናሥግት፣

አዕማድንም ማገሮችንም ወርቅ ለብጣቸው፣ ለማገሮች ቤት የሚሆኑ የወርቅ አምባሮችንም ሥራ፣ አምባር በቁሙ ነው፤ አንድም ስቀሩረተ አዕማድ ነው፤

፴፣ ወግበራ ለደብተራ በአርአያ ዘአርአይኩከ በደብር፣

ድንኳኒቱንም በደብረ ሲና በአሳየሁህ በደብተራ ብርሃን አምሳል ሥራት፤

፴፩፣ ወግበር ላቲ መንጦላዕተ ዘኀብረ ያክንት ወኅብረ ከብድ ወለይ ክዑብ ወቢሶስ ፍቱል፣

ክዑብ ፍቱል ባለው ዑፅፍ ይላል፣ እንደዚሁ ያስተረጉማል፣

ወግበር በግብረ ምዕናም ኪሩቤነ፣

ከአራቱ ኅብር መጋረጃ ሥራላት ኪሩቤልንም በግብረ መርፌ ሥራ ጠልፈህ ሥራቸው፤ አንድም ግብረ ምዕናም ይላል፣ የግብረ መርፌውንም ጥልፍ ሥራ፣ ኪሩቤልን አስመስለህ ሥራው፤

፴፪፣ ወግበር ፬ተ አዕማደ እምዕፀ ዘኢይነቅዝ ወቅፍሎሙ ወርቀ ወአርእስቲሆሙኒ ወርቅ ወግበር ሎሙ ፬ተ ምዕማደ ዘብሩር፤

ሸምሸርስጢን ከሚባል ከማይነቅዝ ዕንጨት ቈርጠህ አራቱን አዕማድ ሥራ፤ አንድም ዕፀ ዘኢይነቅዝ ይላል፣ ሸምሸርስጢን የሚባል የማይነቅዝ ዕንጨት ቈርጠህ አራት አዕማድ አድርገህ ሥራው፣ እነዚህንም በወርቅ ለብጣቸው፣ ክባሳቸውም ወርቅ ይሁን፣ አርእስቲሆሙኒ ወርቅ ብሎ ነበርና አራቱንም ምዕማድ የብር አድርግላቸው፤ አንድም ለእኒህ ለአራቱ አዕማድ የብር አራት ምዕማድ ሥራላቸው፤

፴፫፣ ወአንብር መንጦላዕተ ዲበ አዕማድ ወአብዕ ውስተ ውሳጤሁ ለመንጦላዕት ታቦተ ዘመርጡል ወይፈልጥ መንጦላዕት ውሳጢተ ወቀዋሚየ ቤተ መቅደስ፣

መጋረጃውን በአዕማዱ ላይ አድርገው /ጋርደው/፣ ከዚህ አስቀድሞ ሕገ ሥርዐቱ የሚጸናባት ታቦቲቱን ከመጋረጃው ውስጥ አግባት፣ መጋረጃውም የቤተ መቅደሱን ውስጡንና አፍአውን የሚለይ ይሁን፤



www.ethiopianorthodox.org

፴፬፣ ወይሚውር መንጦላዕት ታቦተ ዘመርጡል በቅድስተ ቅዱሳን፣

መጋረጃውም በዓሥራቱ ክንድ በቅድስተ ቅዱሳን ሁኖ ሕጉ ሥርዓቱ የሚጸናባት ታቦቲቱን ይጋርዳት፤

፴፭፣ ወአንብሮ ለማዕድ እምአፍአሁ ለመንጦላዕት መንገለ መስዕ ወለተቅዋም አንብሮ አንፃረ ማዕድ ለገጸ ደብተራ መንገለ አዜብ፣

ማዕድን ከመጋረጃ ውጪ በመስዕ በኩል አኑረው፣ ተቅዋምንም በማዕድ አንፃር ከመጋረጃ ውጭ በአዜብ በኩል አኑራት፣ ጨለማ በአዜብ በኩል ይጸናልና፤

፴፮፣ ወግበር ላቲ መንጦላዕተ ዘይከድና ለኖኅተ ደብተራ እምያክንት ወኅብረ ከብድ ወለይ ክዑብ ወቢሶስ ክዑብ በብዑድ ግብረት፣

ከአራቱ ኅብር በልዩ ሥራ የተሠራ የደብተራ አሪትን፤ አንድም የኻያውን ክንድ ደጃፍ የሚሸፍናት /የሚጋርዳት/ መጋረጃ ሥራላት፤

፴፯፣ ወግበር ለመንጦላዕት ፭ተ አዕማደ እምዕፅ ዘኢይነቅዝ ወቅፍሎሙ ወርቀ ወአርእስቲሆሙ ወርቅ ወግበር ሎሙ ፭ተ አዕማደ ዘብርት፣

ሽምሽርሰጢን ከሚባል ከማይነቅዝ ዕንጨት ቈርጠህ ለመጋረጃው አምስት አዕማድ ሥራለት፤ አንድም ዕፀ ዘኢይነቅዝ ይላል፣ ሽምሽርሰጢን የሚባለውን ዕንጨት ቈርጠህ ለመጋረጃው ዓምድ አድርገው፣ እነዚህንም በወርቅ ለብጣቸው ክባሳቸውም ወርቅ ይሁን፣ ለእነዚህም ለአምስቱ አዕማድ የብርት የሚሆኑ ምዕማድ አምስት አድርገህ ሥራላቸው፤ አንድም አምስት የብርት ምዕማድ ሥራላቸው፣ የብርት አድርገው አለው፣ ሲወጡበት ሲገቡበት እንዲችል ነው።

## ምዕራፍ ፳ወ፯

፩፣ ወአግብር ምሥዋዓ ዘመሥዋዕት እምዕፅ ዘኢይነቅዝ ዘ፭ቱ በእመት ኑኁ ወ፭ቱ በእመት ራኅቡ ርቡዓ ለይኩን ወሠልሰ በእመት ይኩን ቆሙ፣

አቈልቋዩ አምስት ክንድ ወርዱ አምስት ክንድ የሚሆን መሥዋዕት የሚሠዋበት ምሥዋዕን /መሠዊያውን/ ከማይነቅዝ ዕንጨት አሠራ፣ ይኸውም አራት ገጽ ያለው ይሁን፣ ቁመቱም ሦስት ክንድ ይሁን፤

፪፣ ወግበር ሎቱ አቅርንተ ዲበ አርባዕቱ መዓዝኒሁ ወእምኔሁ ይፃኡ አቅርንቲሁ ወቅፍሎ ብርተ፣

በአራቱ ማዕዘን አራት ቀንድ /ኩላብ/ አውጣለት፣ ቀንዶቹም ሥረወጥ ይሁኑ በብርትም ለብጠው፤



፫፣ ወግበር ሎቱ ቀጸላ ወግበር ንዋይቶ ለምሥዋዕ ምግኃሣተ ወጸሕራተ ወፍያላተ ወሙኖስሰ ሥጋ ወመመውሰደ እሳት ወኵሎ ግበር እምብርት፣

በዙሪያው እንደ አፊድስት ያለ ከንፈር አብጅለት፣ ለመሠዊያው ዕቃ ሥራ፣ አመድ የሚያፈሱበት ዕንቅቡን፣ ሥጋ የሚቀቅሉበት ድስቱን፣ ደሙን የሚቀዱበት ጣሱን፣ ከድስቱ ሥጋ የሚያወጡበት ሦስት ልሳን ያለው ጉጠት፣ እሳት የሚወስዱበት መጫሪያውን ይህን ሁሉ ከብርት ሥራው፣

፬፣ ወአግብር መጥበስቶ ለምሥዋዕ ስቅሱቀ ከመ መሥገርተ ዓሣ ዘብርት፣

መጥበስቶ ለብርት ስቅሱቀ ከመ መሥገርተ ዓሣ ሲል ነው፣ ስቡ ለሚቀልጥበት ለምሥዋዕ እንደ ዓሣ መረብ ያለ የብረት ወንፊት ሥራለት፤

ወአግብር ሎቱ ለመጥበስት ፬ተ ኀልቀታተ ዘብርት ውስተ ፬ቱ መዓዝኒሁ፣

ስቡ ለሚቀልጥበት ለመጥበሻው /ለወንፊቱ/ በአራት ወገን አራት የብረት ቀለበት አብጅለት፤

፭፣ ወአንብሮ ለመጥበስት በቤተ መሥዋዕት ታሕተ ወይኩን በመንፈቀ ቤተ መሥዋዕት፣

ስቡ የሚቀልጥበት መጥበሻውንም በምሥዋዑ ውስጥ አኑረው፣ ይኸውም በምሥዋዑ ውስጥ በእኩሌታው ይንጠልጠል፤

፮፣ ወግበር አርባዕተ አውቃፋተ ዘብርት በአርባዕቱ መዓዝኒሁ ከመ ይኩኑ አብያተ ለመሃውሪሁ፣

ለሚሸከሙባቸው ለመሎጊያዎቹ መያገር እንዲሆኑ በአራት ወገን አራት የብርት ቀለበት አብጅለት፤

ወግበር መሃውርተ እምዕፅ ዘኢይነቅዝ ለቤተ ምሥዋዕ ወቅፍሎሙ ብርተ፣

ምሥዋዑን የሚሸከሙባቸው መሎጊያዎቹን ከማይነቅዝ ዕንጨት ሠርተህ በብርት ለብጣቸው፤

፯፣ ወአብእ መሃውሪሁ ውስተ አውቃፋት ዘላዕለ ገበዋተ ምሥዋዕ ከመ ያንሥኡ በሙ፣

ምሥዋዑን ያነሡባቸው ዘንድ /ይሸከሙባቸው ዘንድ/ መሎጊያዎቹን በምሥዋዑ በሁለቱ ወገን ባሉት ቀለበቶች አግባቸው፤

፰፣ ወፍሉገ ይኩን ሰሌዳሁ፣

በምሥዋዑ በሁለት ወገን መሎጊያው የሚገባበት ፈሰስ አውጣለት፣

በከመ አርአይኩከ በደብር ከማሁ ግበር፣

ይህን ሁሉ በደብረ ሲና እንዳሳየሁህ አድርገህ ሥራ፣ /ሐተታ/

www.ethiopianorthodox.org

ምሥዋዕን ሸምሸርሰጢን ከሚባል ከማይነቅዝ ዕንጨት አምጥተህ ርዝመቱን /አቈል ቋዩን/ አምስት ክንድ፣ ወርዱን አምስት ክንድ፣ ወደ ላይ ቁመቱን ሦስት ክንድ አድርገህ ሥራ ብሎታል፣ አፍአውንም ውስጡንም በብርት ለብጠው፣ አራት ቀንድ አውጣለት፣ እንደ አፈ ድስት ያለ ከንፈር አብጅለት ብሎታል፣ ስቡ ለሚቀልጥበት ለምሥዋዓ ብርቱ አራት ቀለበት አለው፣ ያነንም ከአራቱ ቀንዶች ያገባዋል፣ በዚያ ላይ ስቡን ያደርጋል፣ ከታች ከምሥዋዑ እግር እሳት ያነዳሉ፣ ምሥዋዓ ብርቱ /መጥበሻው/ እንደ ዓሣ መረብ ያለ ነው፣ ስቡ በዚያ እየቀለጠ ይወርዳል፣ ይህስ አይደለም፣ ስቡ ይበሳሻል ብሎ ስቡን ለሚሠዉበት ብርት አራት ሐብል አለው፣ ከምሥዋዑ ከሦስት ክንድ በላይ ሐብሉን ያገባዋል፣ የሐብሉ ቁመት ክንድ ከስንዝር ነው፣ ምሥዋዓ ብርቱ ወደታች ክንድ ከስንዝር ወርዶ በምሥዋዑ እኩሌታ ላይ ይገታል፣ በዚያ ላይ ስቡ ይሆናል፣ አሁን መንፈቀ ምሥዋዕ ያለው ይወጣል፣ እስከ አቅርንቲሁ ለምሥዋዕ የሚያስኘውም ይህ ነው፤ አንድም ለምሥዋዑ ክንድ ተስንዝር በላይ ኩላብ አለው፣ ስቡን ለሚሠዉበት ለብርቱም አራት ቀለበት አለው፣ አራቱን ቀለበት በአራቱ ኩላብ ላይ ያገባዋል፣ በዚያ ላይ ስቡን ይመላዋል፣ ስቡ እስከ ኩላቡ የመላ እንደ ሆነ በጐ ዘመን መሆኑ ይታወቃል፣ ያልመላ እንደ ሆነ ግን እያዘኑ ወደ እግዚአብሔር ይለምናሉ፣ የታዘዘ መዓት መቅሠፍት ይመለስላቸዋል፣ በሚጓዙበትም ጊዜ በብርት የተለበጠ ሁለት መሎጊያ አለ፣ በምሥዋዑ በሁለት ወገን በተፈለፈለው አግብተው ሁለት ሰው በፊት፣ ሁለት ሰው በኋላ ሁነው ተሸክመው ያገዙት ነበር፤

፱፣ ወግበር ላቲ ዓፀደ ለደብተራ መንገለ አዜብ እንተ የማን፣

ለደብተራ አሪት በአዜብ በኩል በስተቀኝ ለቅጽር የሚሆን ስፍራ አብጅለት፤ አንድም ሃያ አዕማድ አቁመህ መቶ ክንድ መጋረጃ ጋርድ፤ የማንነቱ ለደብተራ አሪት ነው፤

ወመንጦላዕቱ ለዓፀድ እምቢሶስ እዑፍ ወኑኁ ምዕት በእመት እምአሐዱ ምስማክ፤

ቅጽሩ የሚጋረድበት የሸማው አጥርም /የእድሞው መጋረጃ/



ድርብ ሁኖ ከተሠራ ከነጭ ሐር ይሁን፣ የመጋረጃውም የአንዱ ወገን ርዝመት መቶ ክንድ ይሁን

፲፣ ወአዕማዲሁ እሥራ ወምዕማዲሆሙ እሥራ ዘብርት፣

በመቶው ክንድ የሚቆሙት አዕማድ ሃያ ይሁኑ፣ የብርት የሚሆን ምዕማዳቸውም /ስክተታቸው/ ሃያ ይሁኑ፣

ውኖፃዲሆሙ ወጥነፊሆሙ ለአዕማድ ዘብሩር፣

የአዕማዶቹ ቀለበቶቻቸውም ኩላባቸውም የብር ይሁን፣ በቀለበቱ የብሩን ዘንግ እያገባ ወስዶ ይስቀለው፤

፲፩፣ ከመዝ ግበር ለምስማክ ዘመንገለ ሰሜን ወመንጦላዕቱ ምዕት በእመት፣

በሰሜንም በኩል እንደዚሁ አድርገህ ለቅጽር የሚሆን ስፍራ አብጅላት፤ አንድም የሸማ አጥር ሥራላት የመጋረጃውም ርዝመት መቶ ክንድ ይሁን፤

ወአዕማዲሁ ፳ ዘብሩር ወምዕማዲሆሙ ፳ ዘብርት ውኖፃዲሆሙ ወጥነፊሆሙ ለአዕማድ ዘብሩር፣

ሃያውም አዕማድ በብር የተለበጡ ይሁኑ፣ የብርት የሚሆኑ ምዕማዶቻቸውም ሃያ ይሁኑ፣ ቀለበቶቻቸውም ዘንጎቻቸውም የብር ይሁኑ፣ /ሐተታ/ ኖፃዳት እንደ ሱሪ ወገብጌ ያለ ነው፣ ጥነፍ የሚለው እንደ ሸምቀቆ ያለ ነው፣ መቶውን ክንድ መጋረጃ በሃያው አዕማድ ላይ በእነዚህ እየጠለፈ ይዞታል፤ አንድም ኖፃዳት አይለወጥም፣ ጥነፍ የሚለው እንደ ብር ዘንግ ያለ ነው፣ የብሩን ዘንግ እንደ ወገብጌ ካለው ከኖፃዳቱ እያገባ በሃያ አዕማድ መቶውን ክንድ መጋረጃ ጋርዶታል፣ ዛሬም የገጠር ቄስ ሸምበቆውን በሰሌኑ ውስጥ ለውስጥ እያገባ ይጋርዷል፤ አንድም ጥነፍ ያለው ኩላብ፣ ኖፃዳት ቀለበት ነው፣ ለሃያው አዕማድ ሃያ ኩላብ አለው፣ ቀለበቱን ከኩላቡ እያገባ መቶውን ክንድ መጋረጃ ጋርዶታል፤

፲፪፣ ወለራኅበ ዓፀድ ዘገጸ ባሕር መንጦላዕቱ ፶ በዕመት ወአዕማዲሁ ፲ቱ ወምዕማዲሆሙ ፲ቱ፣

በምዕራብ በኩል ያለው የቅጽሩ መጋረጃም ፶ ክንድ ይሁን፣ በ፶ ክንድ ርዝመት የቆሙትም አዕማድ ዐሥር ይሁኑ፣ ዐሥሩ አዕማድ የሚቆሙባቸው ምዕማድም ዐሥር ይሁኑ፤

፲፫፣ ወለራኅበ ዓፀድ ዘመንገለ ጽባሕ ፶ በእመት፣

በምሥራቅም በኩል ዐሥር አዕማድ አቁመህ ፶ ክንድ ነጭ ሐር ጋርደው፤

www.ethiopianorthodox.org

አዕማዲሁ ፲ቱ ወምዕማዲሆሙ ፲ቱ፣

አዕማዱ ዐሥር ምዕማዶቹም ዐሥር ይሁኑ፤

፲፬፣ ወዐሥርቱ ወኃምስቱ በእመት ኑኁ ለመንጦላዕት እምገጸ አሐዱ ምስማክ አዕማዲሁ ሠለስቱ ወምዕማዲሆሙ ሠለስቱ፤

በስተምሥራቅ በአንድ ወገን ያለው የመጋረጃው ርዝመት ዐሥራ አምስት ክንድ ይሁን፣ በዐሥራ አምስት ክንድ ርዝመት የሚቆሙት አዕማድ ሦስት ይሁኑ፣ ሦስቱ አዕማድ የሚቆሙባቸው ምዕማድም ሦስት ይሁኑ፤

፲፭፣ ወእምካልዕ ምስማክ ፲ቱ ወ፭ቱ በዕመት፣ ኑኁ ለመንጦላዕት አዕማዲሁ ሠለስቱ ወምዕማዳቲሆሙ ሠለስቱ፣

በምሥራቅ በሁለተኛው ወገን ያለው የመጋረጃው ርዝመት ዐሥራ አምስት ክንድ ይሁን፣ በዓሥራ አምስት ክንድ የሚቆሙት አዕማድም ሦስት ይሁኑ፣ አዕማድ የሚቆሙባቸው ምዕማዶቹም ሦስት ይሁኑ፣

፲፮፣ ወለአናቅጸ ዓፀድ መንጦላዕቱ ፳ በእመት ኑኁ ዘያክንት ወኅብረ ከብድ ወለይ ክዑብ ወቢሶስ ክዑብ፣

በቀኝ ዐሥራ አምስት ክንድ፣ በግራ ዐሥራ አምስት ክንድ ተነሥቶለት የቀረው የበሩ መጋረጃ አንድ ክንድ ይሁን፣ መጋረጃውም ከሰማያዊ ሐር ከብጫ ሐር ድርብ ሁኖ ከተሠራ ከቀይ ሐር ከነጭ ሐር የተሠራ ይሁን፤

ወብዑደ ይኩን በግብረ መርፍዕ አዕማዲሁ አርባዕቱ ወምዕማዲሆሙ አርባዕቱ፣

ይኸውም በግብረ መርፌ /በጥልፍ/ ልዩ ሁኖ የተሠራ ይሁን፣ በሃያው ክንድ የሚቆሙት አዕማድ አራት ይሁኑ ምዕማዱም አራት ይሁን፣

፲፯፣ ወኵሉ አዕማደ ዓፀድ ዘዓውዱ ይትቀፈሉ ብሩረ ወአርእስቲሆሙኒ ብሩር ወምዕማዲሆሙ ብርት፣

በዙሪያው የቆሙ አዕማድ ሁሉ በብር የተለበጡ ይሁኑ፣ ክባሳቸውም በብር የተለበጠ ይሁን፣ ምዕማዳቸውም /ስክተታቸው/ የብርት ይሁን፤

፲፰፣ ወኑኃ ዓፀዱ ፻ በእመት ወራኅቡ ፶ በእመት ወቆሙ ፭ቱ በእመት እምቢሶስ ክዑብ ወምዕማዲሆሙ ብርት፤

ድርብ ከሆነ ከነጭ ሐር የተሠራው የመጋረጃው አጥር አግዳሚ ርዝመቱ መቶ ክንድ ወርዱ ፶ ክንድ ወደላይ ቁመቱ አምስት ክንድ ይሁን፣ ምዕማዳቸውም የብርት ይሁን፤



፲፱፣ ወኵሉ ንዋየ ደብተራ በኵሉ ግብሩ ወመታግሪሁ ወመታክሊሁ ወመታክለ ዓፀዱ ብርት፣

የደብተራ ኦሪት ዕቃ በሚሠራበት ሥራ ሁሉ አውታሩ መምቻውና የድንኳኑ ካስማ ከብርት የተሠራ ይሁን፤

፳፣ ወአንተ አዝዞሙ ለደቂቀ እስራኤል ይንሥኡ ቅብዓ ዘይት ዘቀዳሚ ቅስመታ ንጹሐ ወውጉዓ ለብርሃን፣

አንተም የእስራኤልን ልጆች መጀመሪያ የተቀዳውን መላልሶ የተነጠረውን ዘይት ለመብራት እንዲሆን አምጡ ብለህ እዘዛቸው፤

ከመ ያኅትዉ ማኅቶተ በውስተ ደብተራ አፍኣ እመንጦላዕት ዘቅድመ ትእዛዝ፣

ሕግ የተጻፈበት ጽላት ባለበት ታቦት ፊት ከዓሥሩ ክንድ መጋረጃ ውጭ በደብተራ ኦሪት ውስጥ ያበሩት ዘንድ፤

፳፩፣ ወያኅትዉ አሮን ወደቂቁ እምሠርክ እስከ ነግህ ቅድመ እግዚአብሔር፣

ይህንንም አሮንና ልጆቹ ከመጀመሪያው ሰዓተ ሌሊት ጀምረው እስከ መጀመሪያው ሰዓተ መዓልት በእግዚአብሔር ፊት ያብሩት፤

ሕግ ለዝሉፉ ለትውልዶሙ እም ደቂቀ እስራኤል፣

ይኸውም ለእስራኤል ልጆች እስከ ልጅ ልጃቸው ሥርዓት ሁኖላቸው ይኑር፣ /ታሪክ/ የደብተራ ኦሪትን አሠራር ከዚህ ይናገሩታል፣ የደብተራ ኦሪት አቈልቋይ ርዝመቷ ሠላሳ ክንድ፣ ወርዷ ዐሥር ክንድ፣ ወደ ላይ ቁመቷ ዐሥር ክንድ ነው፣ ከ፴ው ክንድ ውስጥ ዐሥሩቱ ክንድ ቅድስተ ቅዱሳን ናት፣ የአዕማድ አቋቋም እንዲህ ነው፣ በስተቀኝ በአርባ ምዕማድ ላይ ሃያ አዕማድ፣ በስተግራም በአርባ ምዕማድ ላይ ሃያ አዕማድ ያቆማል፣ የእያንዳንዱ ዓምድ ወደ ላይ ቁመቱ ዓሥር ክንድ፣ ወርዱ ክንድ ከስንዝር ነው፣ በስተቀኝ በኩል ሃያው አዕማድ ሠላሳውን ክንድ ይይዙታል፣ በስተግራም ሃያው አዕማድ እንዲሁ ሠላሳውን ክንድ ይይዙታል፣ በስተኋላም በከበሮ ቤቱ በኩል በዐሥራ ሁለት ምዕማድ ላይ ስድስት አዕማድ ያቆማል፣ እነዚህም ዘጠኙን ክንድ ይዘውት በቀኝ ስንዝር፣ በግራ ስንዝር ክፍት ይቀራል፣ ለእነ ዚህም መግጠሚያ ሁለት አዕማድ አምጥቶ አንዱን በቀኝ አንዱን በግራ ያቆመዋል፣

www.ethiopianorthodox.org

የአዕማድም ወርዳቸው ክንድ ከስንዝር ነው፣ አንዱን ዓምድ ካንድ ወገን፣ ስንዝሩን በሁለተኛው ወገን፣ ስንዝሩን ፈልፍሎ በስተቀኝ ክፍት ሁኖ በነበረው ላይ በመካከል ያገባዋል፣ ሁለተኛውንም ዓምድ እንደዚሁ በሁለት ወገን ስንዝር ስንዝሩን ፈልፍሎ በስተግራ በኩል ክፍት ከሆነው ላይ ያገባዋል፣ እንደዚህም ሲሆን በከበሮ ቤቱ በኩል ያሉት አዕማድ ስምንቱ ምዕማድ ዐሥራ ስድስት ይሆናሉ፣ በስተምሥራቅ በመጋቢያው በኩል አምስት አዕማድ ያቆማል፣ ከነዚህም ከአምስቱ ሁለቱን አዕማድ በግራ፣ ሁለቱን አዕማድ በቀኝ ያቆማቸዋል፣ እነዚህም አዕማድ በግራ ሦስቱን ክንድ፣ በቀኝ ሦስቱን ክንድ ይዘውት አራት አራት ክንድ ይተርፋል፣ በተረፈው በአራቱ ክንድ መካከል አምስተኛውን አምድ ያቆመዋል፣ ይህም ክንድ ከስንዝሩን ይዞት በግራ ክንድ ከጋት፣ በቀኝ ክንድ ከጋት ክፍት ይቀራል፣ ደብተራ ኦሪት ለወፍራም ሰው ፊት ለፊት አታስገባም ነበር፣ ከወደ ውስጥም ሃያ ክንድ ሰፍሮ ዐሥር ሲቀር በአራት ዓምድ ከፍሎታል፣ የምዕማድም አቀማመጥ እንዲህ ነው፣ ለእያንዳንዱ ዓምድ ሁለት ሁለት ምዕማድ /የዓምድ መቆሚያ/ አብጅ ብሎታል፣ ይኸውም አንዱ በውስጥ ይነጠፋል፣ አንዱ በላይ ይሆናል፣ በላይ ያለው ከሁለት ላይ ይፈለፈላል፣ በዚያ ላይ አንዱ አምድ በሁለት እግሩ ይቆምብታል፤ አንድም ምዕማዶች ግራና ቀኝ በተራ ሁነው ሁለቱም ይፈለፈላሉ፣ በዚያ ላይ አንዱ ዓምድ በሁለት እግሩ ይቆምባቸዋል፤ አንድም ምዕማዱን በላይና በታች አድርጎ አነባብሮ ሁለቱንም ፈልፍሎታል፣ የሁለቱን አዕማድ ሁለቱን ወንዳወንዴ በአንድ ጉድጓድ፣ የሁለቱን አዕማድ ሁለቱን ወንዳወንዴ በአንድ ጉድጓድ ያገባዋል፣ ይህን ጊዜ አዕማድ ተካክለው ይቆማሉ፣ የመጋረጃውም አለባበስ እንዲህ ነው፣ ደብተራ ኦሪት በመጀመሪያ የምትለብሰው ከአራት ኅብር የተሠራ ዓሥር ፈርጅ ግምጃ ነው፣ የአንዱ ፈርጅ አግዳሚ ርዝመቱ ሃያ ስምንት ክንድ፣ ወርዱ አራት ክንድ ነው፣ ይህም የዐሥሩ ፈርጅ ወርድ በአንድነት አርባ ክንድ ይሆናል፣ አምስቱን ፈርጅ በአንድ ወገን፣ አምስቱን ፈርጅ በአንድ ወገን አድርጎ አሰፍቶ



መካከሉን ጠርዝና ጠርዙን በመግስጥና በኖፃዳት አያይዞታል፣ መግስጥ ተባት ቍልፍ ነው፣ እንደ ኳስ ያለ ነው፣ ኖፃዳት እንስት ቍልፍ ነው ቀለበት ነው፣ መግስጥ በፈርጁ ጠርዝ በግራ በቀኝ ነው፣ በኖፃዳት አልፎ አልፎ እንቅ እንቅ አድርጎ ይይዘዋል፤ አንድም መግስጥ እንደ ድንኳን ባሕረ ዓረብ አብሮ የተሰፋ ነው፣ ኖፃዳት እንደ ባሕረ ዓረብ ቍልፍ በዚያ ከላይ አንሥቶ እስከታች ድረስ እየጠለፈ ይይዘዋል፤ አንድም መግስጥ እንደ ደበሎ ቍልፍ፣ ኖጻዳት እንደ ጠፍሩ ነው፣ አልፎ አልፎ በዚያ እንቅ እንቅ ያደርገዋል፤ አንድም መግስጥና ኖፃዳት እንደ ጸሐፊ ኮረጆ ከላይ እስከ ታች እየተጠላለፈ የወረደ ነው፣ ስታለብሰውም በወርዱ አልብ ሰው ብሎታል፣ የግምጃው ወርድ አርባ ክንድ ነው፣ ሠላሳውን ክንድ የመቅደሱ ርዝመት ይይዘዋል ዐሥር ይተርፋል፣ ከዐሥሩ አንዲቱ ክንድ በስተመግቢያው በኩል ትወርዳለች፣ ዘጠኙ ክንድ በከበሮ ቤቱ በኩል ይወርዳል፣ የዓምዱ ቁመት ዐሥር ክንድ ስለሆነ ዘጠኙ ክንድ ለብሶ ክንድ ሙሉ ሳይለብስ ይቀራል፣

የግምጃው ርዝመት ሃያ ስምንት ክንድ ነው፣ ዐሥሩን ክንድ የመቅደሱ ወርድ ይይዘዋል፣ ዓሥራ ስምንቱ ክንድ ይቀራል፣ ዘጠኙ ክንድ በቀኝ፣ ዘጠኙ ክንድ በግራ ይወርዳል፣ አሁንም አዕማድ ክንድ ክንድ ሙሉ ሳይለብሱ ይቀራሉ፣ የደብተራ ኦሪት ሁለተኛ ልብሱ ብስጥ ከፀጉር የተሠራ ማቅ ነው፣ ፈርጁ ዓሥራ አንድ ነው፣ ወርዱም አራት አራት ክንድ ነው፣ መላው አርባ አራት ክንድ ይሆናል፣ አግዳሚ ርዝመቱ ሠላሳ ክንድ ነው፣ ይህንንም አምስቱን ፈርጅ በአንድ ወገን፣ ስድስቱን ፈርጅ በአንድ ወገን አድርጎ ሰፍቶ በመግስጥና በኖፃዳት አያይዞታል፣ ኖፃዳት ባለፈው የወርቅ ቀለበት ነው፣ አሁን ግን እንዲችል የብርት ቀለበት ነው፣ የመግስጥና የኖፃዳት አቈላለፋቸው እንደ ፊተኛው ነው፣ ይህንም ስታለብስ በወርዱ አልብስ ብሎታል፣ የብስጥ ወርዱ አርባ አራት ክንድ ነው፣ ሠላሳውን ክንድ የመቅደሱ ርዝመት ይይዘዋል፣ ዐሥራ አራት ክንድ ይተርፋል፣ አራቱ ክንድ በመግቢያው በኩል፣ ዐሥሩ በከበሮ ቤቱ በኩል ይወርዳል፣ የብስጥ አግዳሚ

www.ethiopianorthodox.org

ርዝመቱ ሠላሳ ክንድ ነው፣
ዐሥሩን ክንድ የመቅደሱ ወርድ
ይይዘዋል፣ ሃያ ክንድ ይቀራል፣
ዐሥሩ ክንድ በቀኝ፣ ዐሥሩ
ክንድ በግራ ይወርዳል፣ በዚህ
ጊዜ አዕማድ እግራቸው ጨርሶ
ይለብሳል፣ በብስጡ ላይ ማዕሰ
መጻጺትን ያለብሳል፣ በዚያ
ላይ ዓምደ እሳት ሰፍሮ ይታይ
ነበር፣ በዐሥሪቱ ክንድ
በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ያሉ
ታቦትና ማዕጠንት መሶበ
ወርቅና በትረ አሮን ናቸው፣
ከመጋረጃው በአፍኣ በሃያው
ክንድ ውስጥ ያሉት ግን በቀኝ
ማዕድ፣ በግራ ተቅዋመ ወርቅ
ናቸው፣ ምሥዋዕ ከደብተራ
ኦሪት በአፍኣ ነው፣ እንደ
ቤተልሔም፣ የቅጽሩም አሠ
ራር እንዲህ ነው፣ ደብተራ
ኦሪት እንደ በረት እንደ
ገቢያ እንዳትሆን ከወደ ውጭ
ወጥተህ በስተቀኝ መቶ ክንድ
ሰፍረህ አምስት አምስት
ክንድ እያለፍክ በሃያ አዕማድ
መቶ ክንድ ነጭ ሐር ጋርድ፣
በስተግራም መቶ ክንድ ሰፍረህ
አምስት አምስት ክንድ
እያለፍክ በሃያ አዕማድ መቶ
ክንድ ነጭ ሐር ጋርድ፣ በስተ
ኋላም በከበሮ ቤቱ በኩል
ኃምሳ ክንድ ሰፍረህ በዓሥር
አዕማድ ኃምሳ ክንድ ነጭ ሐር
ጋርድ፣ በስተመግቢያው በኩል
ኃምሳውን ክንድ ሰፍረህ ከኃም
ሳው ሃያውን ክንድ ከመካከል
ትተህ በቀኝ አሥራ አምስት
ክንድ ሠፍረህ በአምስት በአም
ስት ክንድ ሦስት አዕማድ
አቁመህ ዐሥራ አምስት ክንድ
ነጭ ሐር ጋርድ ብሎታል፣
በግራም ዐሥራ አምስት ክንድ
ሰፍረህ በአምስት በአምስት
ክንድ ሦስት አዕማድ አቁመህ
ዓሥራ አምስት ክንድ ነጭ
ሐር ጋርድ ብሎታል፣ ከመቶው
ክንድ ወደ ውስጥ ገባ ብለህ
አራት አዕማድ አቁመህ ሃያ
ክንድ ነጭ ሐር ጋርድ ብሎ
ታል፣ ደብተራ ኦሪትን ፊት
ለፊት አይገቡባትም ነበር፣
በቀኝ የመጣ ዙሮ በግራ፣
በግራም የመጣ ዙሮ በቀኝ
ይገባ ነበር፣ መጋረጃውንም
በአዕማዱ ላይ ኩላብ እያደረገ
የብር ዘንግ እያገባ ጋርዶ
ታል፣ የቅጽሩ ዓምድ ወደ ላይ
ቁመቱ አምስት አምስት
ክንድ ነው፣ ስለዚህ ቅጽሩ
ዝቅ ደብተራ ኦሪት ብቅ ብላ
ሲያዩዋት የታጠቀ ጐልማሳ
መስላ ትታይ ነበር፣ እግዚአ
ብሔር በባሕርይ ጥበቡ ሰማይ
ንና ምድርን እንደ ፈጠረ
እንዲሁም ለሰው የባሕርይ
ጥበቡን የጸጋ አድርጎ እንደ



ሰጠ ለማጠየቅ፣ በባስልኤልና
በኤልያብ አድሮ ደብተራ
ኦሪትን ሠራ፣ ቀዳሚሃ ለጽዮን
ሰማየ ሣረረ ወበዳግም አርአዮ
ለሙሴ ዘከመ ይገብር ግብራ
ለደብተራ እንዲል፣ ደብተራ
ኦሪት እንደዚህ ሁና መሠራቷ
ለጊዜው ምስአል ወምስጋድ
ወምስትሥራየ ኃጢአት ልት
ሆን ነው፣ ፍጻሜው ግን ምሳሌ
ነው፣ ደብተራ ኦሪት የቤተ
እስራኤል፣ ዐሥሩ ክንድ የ፲ቱ
ቃላት፣ ዘጠኙ ክንድ የዘጠኙ
በረከት፣ ከዚሁም ስድስቱ
በረከተ ገሪዛን፣ ሦስቱ በረከተ
በለዓም ነው፣ አምስቱ ፈርጅ
የአምስቱ መጽሐፈ ሙሴ፣
በስተመግቢያው በኩል የወረ
ደው አራቱ ክንድ የአራቱ
ደቂቀ አሮን፣ እኚሁም
አልዓዛር አብዩድና ናዳብ
ኢታምር ናቸው፣ ፴ው ክንድ
የሠላሳው በረከት ምሳሌ፣
አብርሃም ይስሐቅን፣ ይስሐቅ
ያዕቆብን ባርኮታል፣ ፩ድ
ያዕቆብ አሥራ ሁለቱን ነገደ
እስራኤል ባርኳቸዋል፣ ዐሥራ
አራት፣ በተለየ ሌዊን ለክህ
ነት፣ ይሁዳን ለመንግሥት
ባርኳቸዋል፣ ዐሥራ ስድስት፣
ርብቃን ወንድሞቿ እኅትነ
ኩኒ እልፈ ወአዕላፈ ብለው
ባርከዋታል፣ ዐሥራ ሰባት፣
ሙሴ ዐሥራ ሁለቱን ነገደ
እስራኤል ባርኳቸዋል፣ ሃያ
ዘጠኝ፣ አሮን ዕለት ዕለት
ይባርካቸው ነበር፣ ፴ በረከት
የተባለ ይህ ነው፣ በስተመግ
ቢያው የወረደችው አንዲቱ
ክንድ ግምጃ የበረከተ ዲቦራ
ምሳሌ ናት፣ ደብተራ ኦሪት
የእመቤታችን ምሳሌ፣ አራቱ
ኅብር የአራቱ ባሕርያት፣
ብስጥ የደማዊት ነፍስ፣ ማዕሰ
መጻጺት የነባቢት ነፍስ ምሳሌ፣
በዚያ ላይ ብርሃን ሰፍሮ ይታይ
እንደነበር ጌታም ከእመቤታ
ችን አራቱን ባሕርያተ ሥጋ
አምስተኛዪቱን ባሕርየ ነፍስን
የመዋሐዱ ምሳሌ፤ አንድም
ደብተራ ኦሪት የቤተ ክርስቲ
ያን፣ ዐሥሩ ክንድ የዐሥሩ
ቃላት፣ ስድስቱ ክንድ የስድ
ስቱ ቃላተ ወንጌል፣ ዘጠኙ
የዘጠኙ መዓርጋት፣ አምስቱ
የአምስቱ አዕማደ ምሥጢር፣
አራቱ የአራቱ ሊቃነ ጳጳሳት፣
ሁለቱ የፍቅረ ቢጽና የፍቅረ
እግዚአብሔር፣ አንዲቱ የግዕዝ
ርትዕት፣ አራቱ ኅብር የአራቱ
ዖታ ምእመናን ምሳሌ፣ ብጫው
የደናግል፣ ንጹሐን ናቸውና፣
ነጩ የንጹሐን አበው ባለተስፋ
ናቸውና፣ ጥቁሩ የጻድቃን
መከራቸው ጽኑ ነውና፣ ቀዩ
የሰማዕታት ደማቸውን ያፈሳ
ሉና፣ በስተግራ ያሉት አዕማድ

www.ethiopianorthodox.org

የካህናት ብሊት፣ ግራ ደካማ ነው፣ እነሱም ልጅነትን አያስ ጡምና፣ በስተቀኝ ያለች አዕ ማድ የካህናተ ሐዲስ፣ ቀኝ ብርቱ ነው፣ እነሱም ልጅነትን ያሰጣሉና በስተመግቢያው ያሉት አዕማድ የሰማዕታተ ብሊት፣ በዚያ ሁሉ ይወጣበ ታል ይገባበታል፣ ሰማዕታተ ብሊትም በልጅነት ስለአልታ ደሱ መከራ ጸንቶባቸዋል፣ በስተኋላ በከበሮ ቤቱ በኩል ያሉት አዕማድ የሰማዕታተ ሐዲስ፣ በዚያ የሚወጣበት የሚገባበት እንደሌለ እነሱም በልጅነት ስለ ታደሱ መከራ አልጸናባቸውምና፣ በዙሪያው ያሉት የቅጽሩ አዕማድ እስከ ምጽአት ድረስ የሚነሡ የደጋ ርት ጻድቃን ምሳሌ፣ በቅጽር ግቢ ያለው ቦታ የዚህ ዓለም፣ ቅድስት የገነት፣ ቅድስተ ቅዱሳን የመንግሥተ ሰማያት፣ ዙሪያው መጋረጃ የሕገ ልቡና፣ የደብ ተራ አሪቱ በር መጋረጃ የሕገ ኦሪት፣ የቅድስተ ቅዱሳን መጋረጃ የወንጌል ምሳሌ ነው::

## ምዕራፍ ፳ወ፰

### ገባኤ

፩፣ ወአቅርቦ ኀቤከ ለአሮን እኁከ ወለደቂቁ ምስሌሁ እምደቂቀ እስራኤል ከመ ይሡዑ ሊተ አሮን ወናዳብ ወአብዩድ ወአልዓዛር ወይታምር፣

ከእስራኤል ልጆች ለይተህ ወንድምህ አሮንን ከልጆቹ ጋር ለሹመት ወደ አንተ አቅርበው፣ አሮንና ልጆቹ ናዳብ አብዩድ አልዓዛር ይታምር መሥዋዕት እያቀረቡ ያገለግሉኝ ዘንድ፤

፪፣ ወግበር አራዘ ቅዱሰ ለአሮን ለክብር ወለሰራኒ፣

ለአሮንም አሸብርቆ ክብሮ ሊታ ይበት በጌጥ የተለየ ልብስ አሠራለት፤

፫፣ ወአንተ አይድዕ ለኵሉ ጠቢባነ ልብ ዘመላዕኩ ላዕሌሆሙ መንፈሰ ጥበብ፣

ጥበብን የሚገልጽ መንፈስ ረድ ኤትን ላሳደርኩባቸው ዕውቀት ላላቸው ሰዎች አንተ ንገር፤

ወእሙንቱ ይግበሩ አራዘ ቅዱሰ ለቤተ መቅደስ በዘቦቱ ይቄድሱ ኪያየ፣

እነሱም ካህናቱ ለብሰው በቤተ መቅደስ እኔን የሚያመስግ ኑበትን የተለየ ልብስ ይሥሩ፣ /ሐተታ/ ደብተራ ኦሪትን ቤተ



መቅደስ አላት የሚመሰገንባት ስለሆነ፤ አንድም ማደሪያዬ ለሆነ ለአሮን የከበረ ልብስን ይሥሩ ሲል ነው፤

፬፣ ወእሉ አልባስ ዘይገብሩ ኤፉድ ወሎግዮ ወጳደሬ ወቢሶስ ዘቀኖጽር ወአክሊል ወድርማንቅ ዘሐቌ ወቅናታት፣

የሚሠሯቸውም ልብሶች እሊህ ናቸው፣ የደረት ልብስ፣ የጫ ንቃ ልብስ፣ እጀ ሰፊ ቀሚስ፣ ከነጭ ሐር የተሠራ እጀ ጠባብ ቀሚስ፣ ኩፌት፣ በወገብ የሚ ታጠቁት ልባልባ /ሰናፊል/፣ የሐር መታጠቂያ ናቸው፤ አንድም ይገብሩ ይላል፣ እነዚ ህን ሁሉ ይሥሩ፤

፭፣ ወእሙንቱ ይንሥኡ ወርቀ ወያክንተ ወኀብረ ከብድ ወለየ ክዐበ ወቢሶስ፣

እነሱም ወርቁን፣ ሰማያዊ ሐር፣ ብጫውን ሐር፣ እጥፍ ሁኖ የተፈተለውን ቀይ ሐር፣ ነጩን ሐር ከእስራኤል ተቀብለው፤

፮፣ ወይገብሩ ኤፉደ እምወርቅ ወያክንት ወኀብረ ከብድ ወለይ ወቢሶስ ፍቱል በግብረ መርፍዕ ወግብሩ ግብረ ምዕናም ብዑድ፣

ከሰማያዊ ሐር፣ ከብጫ ሐር፣ ከቀይ ሐር፣ እጥፍ ሁኖ ከተፈ ተለ ከነጭ ሐር፣ ከእነዚህ ከአራቱ ኅብር ግምጃ ጋር ወርቁን በጥልፍ እያስማሙ ይሥሩ፣ አሠራሩም በተለየ በጥልፍ ሥራ ይሁን፤

፯፣ ወክልኤ ይኩና መታክፈሁ እለ ይትላጸቃ በበይናን አሐቲ ዲበ አሐቲ እምክልኤሆን ገጸ ግብረቶን፣

በጫንቃው የሚለብሳቸው የኤፉድ ፊርጆችም አሠራራ ቸው ሁለት ወገን ሁኖ አንዷቱ ከአንዷቱ ጋር እርስ በርሳቸው የተገጠሙ ሁለት ይሁኑ፣ /ሐተታ/ የኤፉድ መጠኑ ክንድ ሙሉ ነው፣ ስንዝሩን ለብቻ ስንዝሩን ለብቻ በመኸን ሠርቶ በሐር ጠልፎ ያያይዘዋልና፣ ሁለት ወገን ሁነው የተገጠሙ ይሁኑ አለ፣ መታክፈሁም ማለቱ በአሮን በጫንቃው የሚውል ስለሆነ ነው፤

፰፣ ወእንመተ ኤፉድ ዘላዕሌሁ እምግብረቶን ድሙራተ ይኩና ዘወርቅ ወያክንት ወኅብረ ከብድ ወለይ ክዐብ ወቢሶስ ክዑብ፣

መደባቸው ሁለት ሲሆን አንድ የሚሆኑበት በኤፉድ ላይ የሚ ሆን የጥልፉም አሠራር በአራት ኅብር ሐርና በአምስተኛ ወርቅ የተጠለፈ ይሁን፣ እንመተ ኤፉድ ባለው እንመተ ትብል ያሁ ይላል፣ ትርጓሜው አንድ ነው፤

www.ethiopianorthodox.org

፱፤ ወንሣእ ክልኤተ አዕባነ መረግድ ወግልፍ ላዕሌሆሙ አስማተ ደቂቀ እስራኤል፤

መረግድ የሚባሉ ሁለት አዕናቍ አምጥተህ የዐሥራ ሁለቱን ነገደ እስራኤል ስም በላያቸው ቅረፅ፤

፲፤ ፮ተ አስማተ ላዕለ አሐዱ ዕብን ወ፮ተ አስማተ ላዕለ አሐዱ ዕብን በበአዝማዲሆሙ፤

ስትቀርፅም የስድስቱን ስም በአንድ ዕንቍ፤ የስድስቱን ስም በአንድ ዕንቍ አድርገህ በየወገናቸው ቅረፅ፤ /ሐተታ/ በየወገናቸው ማለቱ በአንድ ዕንቍ የልያን ስድስቱን ልጆች፤ በአንድ ዕንቍም የራኄልን ሁለቱን፤ የባላን ሁለቱን፤ የዘለፋን ሁለቱን ልጆች እነዚህን ሲል ነው፤

፲፩፤ ወግበር ግብረ ዘኪን ኀርወተ ዓይነ ማኅተም ወበክልኤቱ አዕባን ዘላዕሌሆሙ አስማተ ደቂቀ እስራኤል መአኃዘ ወርቅ ትግብር በዓውዶሙ፤

በዕንቍ ላይ የሚጻፍ የስማቸውንም አቀራረፅ እንደ ዓይን መልክ ቅርፅ ያለው አድርገህ በጥበብ ሥራው፤ የእስራኤል ልጆች ስም በተጻፈባቸው በሁለቱ አዕናቍ ዙሪያም ዕንቍን የሚይዝ የወርቅ ቀለበት አብጅለት፤ /ሐተታ/ የዓይን ነጩም ጥቁሩም ልዝብ ነውና አለዝበህ ቅረፀው ሲል ነው፤ አንድም ዘሮቤል ዘጋድ የሚለው ቅርፅ ያለው መልክ ነውና መአኀዘ ወርቅ ማለቱም ስንዝርና ስንዝሩን በግብረ መርፌ አያይዞ በሐር ይጠልፈዋል፤ ሐሩን አጐድጕዶ ወርቁን ያደርግበታል፤ ወርቁንም አጐድጕዶ ዕንቍ ያደርግበታልና፤ አንድም በዕንቍ ዙሪያ የወርቅ ቀለበት አበጅቶ የወርቁን ቀለበት እንደ ድባብ ገብገብ በኤፉድ ላይ በሐር እየጠለፈ ያያይዘዋልና እንዲህ አለ፤

፲፪፤ ወታነብሮሙ ለክልኤቱ አዕባን ላዕለ መትከፈ ኤፉድ ተዝካረ በእንቲአሆሙ ወይነሥእ አሮን አስማቲሆሙ በቅድመ እግዚአብሔር ላዕለ ክልኤቱ መታክፍቲሁ ለአዘክሮቶሙ፤

ሁለቱም ዕንቍዎች ለእስራኤል መታሰቢያ ሊሆኑ በልብሰ መትከፍ በኤፉድ ላይ በሐር ጠልፈህ አያይዛቸው፤ አሮንም ወደ ቤተ መቅደስ በሚገባበት ጊዜ እስራኤልን ለማሳሰብ የዐሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ስም የተጻፈባቸው አዕናቍ ያሉበት ኤፉድን ለብሶ ይግባ፤

፲፫፤ ወግበር አራዊተ ምድር እም ወርቅ ንጹሕ፤

ከጠራ ወርቅ የእባብ እራስ አስመስለህ ጠመም ጠመም እያ



ደረግህ ተባት ቍልፍ ሥራ፤ ከበበ ጥውዮ ብሎ ኋላ ያመጣዋል፤

፲፬፤ ወአግብር ክልኤተ ሰናስለ እምወርቅ ንጹሕ ድሙረ ግብረ ጽፉረ ወአንብር ሰናስለ ዲበ አራዊተ ምድር፤

እንደ ቋድ ሥራ የተታታ አድርገህ ከጠራ ወርቅ ሁለት የወርቅ ሰንሰለት አሠርተህ የእባብ ራስ አስመስለህ ከሠራኸው ጋር አያይዘህ አኑረው፤

፲፭፤ ወግበር ሎግዮ ዘፍትሕ በግብረ ምእናም በሐሳበ ኤፉድ ግበር በወርቅ ወበያክንት ወበኅብረ ከብድ ወለይ ክዑብ ወቢሶስ ክዑብ፤

ፍርድ የሚሰማበት የደረት ልብስንም በጥልፍ አሠራር /በግብረ መርፌ/ ከአራት ኅብር ከአምስተኛ ወርቅ በኤፉድ መጠን አድርገህ ሥራ፤ /ሐተታ/ ፈርዶ የሚያመጣው መዓትም ምሕረትም የሚሰማበት ስለሆነ ዘፍትሕ አለው፤

፲፮፤ ወትገብሮ ርቡዓ ወውጡሐ ወይኩን አጽፍ ዘእመት ኑኁ ወእመት ራኅቡ፤

ይህንም አራት መዓዝን ያለው የተነፋ /የተከመረ/ አድርገህ ሥራው፤ ልብስነቱም ርዝመቱ ክንድ ወርዱም ክንድ ይሁን፤

፲፯፤ ወአንብር ላዕሌሁ አዕባነ በአርባዕቱ ፆታ አሐዱ ፆታ ዘዕብን ይትገበር ዘሰርድዮን ወዘጳዝዮን ወዘመረግድ፤

አሥራ ሁለቱን አዕናቍ አምጥተህ በአራት ረድፍ /ወገን/ ጥለፍበት በመጀመሪያው ረድፍ የምትጠልፈው /የምትሠራው/ ሰርድዮን፤ ጳዝዮን መረግድ የሚባል ዕንቍ ይሁን፤

፲፰፤ ወካልእ ጾታ ዘዕብን ከመ ፍሕም ወሰንፔር ወኢያስጲድ፤

በሁለተኛውም ረድፍ የምትጠልፈው ፍሕም የሚመስል ዕንቍና ሰንፔር ኢያስጲድ የሚባል ዕንቍ ይሁን፤

፲፱፤ ወሣልስ ጾታ ዘለግርዮን ወአካጥስ ወአሜቴስጢኖስ፤

በሦስተኛውም ረድፍ የምትጠልፈው /የምትሠራው ለግርዮን፤ አካጥስ፤ አሜቴስጢኖስ የሚባል ዕንቍ ይሁን፤

፳፤ ወራብዕ ፆታ ዘዕብን ዘኅብረ ወርቅ ወቢረሌ ወሶም ወይኩን ልቡጠ በወርቅ ወእሡረ በወርቅ በበፆታሁ፤

በአራተኛው ረድፍ /ወገን/ አይነቱ ወርቅ የሚመስል ዕንቍና ቢረሌ፤ ሶም የሚባል ዕንቍ ይሁን፤ በአራት ወገን ጌጥ ሁነው የተሠሩትም የዐሥራ ሁለቱ አዕናቍ አሰካክ በወርቅ

www.ethiopianorthodox.org

የተያያዘ ይሁን፣ /ሐተታ/ ልቡጠ ማለቱ ወርቁን አጎድጉዶ እንደ አጎበር አድርጎ ዕንቍን እንደፈርጥ በወርቁ ላይ ይሰካ ዋልና እንዲህ አለ፣ እነዚህንም ዐሥራ ሁለት አዕናቍ በሎግዮ ላይ ስድስቱን በአንድ ወገን፣ ስድስቱን በአንድ ወገን አድርጎ በጥልፍ ያያይዛቸዋል፣ በአራት በአራት ረድፍ አድርጎ አግድም ሠርቶታል፣ አቆልቁሎ ሲያዩት ሦስት ሦስት ሁኖ ይታያል፣ አግድም /በረድፉ/ ሲያዩት አራት አራት ሁኖ ይታያልና፣ በበአርባዕቱ ያታ አለ፤

፳፩፣ ወአዕባኒሁ ይትገበራ በአስማቲሆሙ ለዐሠርቱ ወ፪ቱ ሕዝበ እስራኤል ወይትገለፉ ከመ ግልፈተ ዓይነ ማኅተም ለለ ስሞሙ ለዐሠርቱ ወክልኤቱ ሕዝበ እስራኤል፣

አዕናቍም በዐሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ስሞች ቍጥር ይሁኑ፣ እንደ ማኅተም ቅርፅ አሠራር ሁኖ የዐሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ስሞች በአዕናቍ ላይ ይቀረፁባቸው፤

፳፪፣ ወግበር ሎቱ ሰናስለ ዘወርቅ ለሎግዮ ዘጽፍሮ ወጽፉሮሁኒ ከመ ዘርዜቅ ዘወርቅ ንጹሕ፣

ለሎግዮም የተታታ የወርቅ ሰንሰለት ሥራለት፣ አሠራሩም እንደ ወንፊት ትት /ሥራ/ ሁኖ ከጥሩ ወርቅ የተሠራ ይሁን፤

፳፫፣ ወግበር ክልኤተ ሕልቀታተ ወርቅ ወታነብሮሙ ለክልኤቱ ሕልቀታት ላዕለ ክልኤቱ ጽነፊሁ ለሎግዮ፣

ሁለት የወርቅ ቀለበቶች ሥርተህ በሎግዮ በሁለት ወገን በጠርዝና በጠርዙ ላይ አያይዛቸው፣

፳፬፣ ወታነብሮሙ ለክልኤቱ ጽፍሮ ወርቅ ላዕለ ክልኤቱ ኅልቀታት ዘጽንፈ ሎግዮ፣

እንደ ዓሣ መረብ ሁነው የተሠሩትን ሁለቱን የወርቅ ሰንሰለቶችም በሎግዮ ጠርዝ ከሁለት ከሁለቱ ቀለበቶች ጋር አያይዛቸው፤

፳፭፣ ወለክልኤቱ ጽነፊሁ ታነብር ክልኤተ ጽፍሮ ላዕለ ክልኤቱ ክበበ ጥውዮ ወታነብሮ ላዕለ መትከፈ ኤፉድ መንገለ ገጹ በማኅበርቱ፣

እንደ እባብ ራስ ሁነው ከተሠሩ ከሁለቱ ተባት ቍልፍ ጋር የተያያዙ ሁለቱን የወርቅ ቋድም በሎግዮ ጠርዝ በሁለት ወገን አድርጋቸው፣ በኤፉድ ጫንቃ ላይ በስተፊቱ ይሁን፤ አንድም በአሮን በስተፊቱ ይሁን፤



፳፮፣ ወግበር ክልኤተ ኅልቀታተ ወርቅ ወታነብሮሙ ላዕለ ክልኤቱ ጽነፊሁ ለሎግዮ ኀበ ከንፈሩ ኀበ ዘየኃልፍ ኤፉድ እንተ ውስጥ፣

ሁለት የወርቅ ቀለበት ሥርተህ ኤፉድ ውስጥ ለውስጥ በሚሄድበት በሎግዮ በሁለቱ ጠርዝ አድርጋቸው /ሐተታ/ ቋዱ በበላዩ ስለ ሔደ እንተ ውስጥ አለ፤

፳፯፣ ወግበር ክልኤተ ኅልቀታተ ወርቅ ወታነብሮሙ ላዕለ ክልኤቱ መታክፈ ኤፉድ ኀበ ይትረዓይ መንገለ ገጹ በማኅበርቱ መልዕልቴሁ ለእንመተ ኤፉድ፤

ሁለት የወርቅ ቀለበት ሥርተህ ኤፉድና ሎግዮ በሚገናኙበት ፊቱም በሚተያይበት በኤፉድ በሁለቱ ጫንቃዎች ላይ አኑራቸው፤

፳፰፣ ወያስተአኀዝዎ ለሎግዮ በሕልቀታቲሁ ኀበ ሕልቀታተ ኤፉድ በፈትለ ያክንት ከመ ይኩን ላዕለ እንመተ ኢፉድ ወኢያንጠልል ሎግዮ እምኤፉድ፣

የሎግዮንና የኤፉድን ቀለበቶች በሰማያዊ ሐር አያይዘው፣ ኤፉድንና ሎግዮን ያገናኟቸው ሰዎቹ፤ አንድም ቀለበቶቹ ናቸው፣ ሎግዮ ከኤፉድ ተለይቶ እንዳይነጠል በኤፉድ ጠርዝ ላይ ይሆን ዘንድ፣ /ሐተታ/ ኤፉድንና ሎግዮን አራት መዓዝን አድርጎ አስተካክሎ ሠርቶ ለሁለቱም አራት አራት የወርቅ ቀለበት ሠርቶ በዳርና በዳር እያደረገ ኤፉድንና ሎግዮን በጫንቃ በጫንቃው በቀለበቱ ሐር እያገባ አያይዞታል፣ ለሎግዮና ለኤፉድ ሁለት ሁለት የወርቅ ቋድ አራት አራት ቍልፍ አድርጎ የግራውን ወደ ቀኝ፣ የቀኙን ወደ፣ ግራ ከቀለበቶቹ ጋር እየጠለፈ አያይዞታል፤

፳፱፣ ወይነሥእ አሮን አስማተ ደቂቀ እስራኤል መልዕልተ እንግድዓሁ ለሎግዮ ዘፍትሕ በበዊአቱ ውስተ መቅደስ ከመ ያዘክሮሙ ቅድመ እግዚአብሔር ዘልፈ፣

አሮንም ወደ ቤተ መቅደስ በሚገባበት ጊዜ እስራኤልን ወደ እግዚአብሔር ዘወትር ያሳስባቸው ዘንድ የቸርነቱ ፍርድ በሚፈረድበት በሎግዮ በደረቱ ላይ አድርጎ የእስራኤልን ልጆች ስም ይዞ ይሒድ ማለት የእስራኤል ልጆች ስም የተቀረፀበት ሎግዮን ለብሶ ገብቶ ይጸልይ፤

፴፣ ወታነብር ኀበ ሎግዮ ዘፍትሕ መብርሂያተ ወማኅተማተ ወይከውኑ ላዕለ ልበ አሮን ሶበ ይበውእ ቤተ መቅደስ ቅድመ እግዚአብሔር ያብእ ፍትሐሙ ለውሉደ እስራኤል ዲበ እንግድዓሁ ዘልፈ፣

የተቀረፁ የሚያበሩ የዐሥራ ሁለቱን አዕናቍ ድምፅ በሚያ

www.ethiopianorthodox.org

ሰማበት፤ እንድም የቸርነቱ ፍርድ በሚፈረድበት በሎግዮ በጥልፍ አያይዘህ አሮን ወደ ቤተ መቅደስ በሚገባበት ጊዜ ከልቡ በላይ ከደረቱ ሁነው የእስራኤልን ልጆች ልመና ዘወትር ወደ እግዚአብሔር ያቅ ርብላቸው፣ /ሐተታ/ ጸሎቱን ፍትሕ አለው፣ የለመኑትን ሰምቶ የሚፈርድላቸው ስለሆነ፤

፴፩፣ ወግበር ጸደሬ ዘኰለንታሁ ቢያክንት፣

ከእግር እስከ ራሱ በሰማያዊ ሐር የተሠራ እጀ ሰፊ ቀሚስ ስፋለት፣

፴፪፣ ወአፈ መልበስቱ እምኔሁ ይኩን ማዕከለ በዓውዱ በግብረ ምዕናም ወድማሬሁ እንሞ እምኔሁ ከመ ኢይትበተክ፣

አንገትየውም ሥረ ወጥ ሁኖ መሐል ለመሐል ዙሪያውን በመህን ሥራ የተሠራ ይሁን፣ ክሣዱ ታካሪሱም ከእርሱ እንዳ ይለይ ሥረ ወጥ ሁኖ የተሠራ ይሁን፤

፴፫፣ ወግበር አማልክቲሁ በዓውዱ መትሕተ መልበስቱ ከመ ፍሬያተ ሮማን ዘያክንት ወኅብረ ክብድ ወለይ ክዑብ ወቢሶስ ክዑብ ወጸናጽላተ ወርቅ፤

ከኤፉድና ከሎግዮ በታች በቀ ሚሱ ላይ እጥፍ ሁኖ የተሠራ የቀይ ሐርና የነጭ ሐር የሰማያዊና የብጫ ሐር ፈትል የሮማን ፍሬ አስመስለህ ከወርቁ ሻኩራ ጋር ሥራ፤

፴፬፣ በማዕከለ ጸናጽለ ወርቅ ሮማን ወማዕከለ ሮማን ጸናጽለ ወርቅ መልዕልተ ጸደሬ እንተ ዓውዱ፣

በእጀ ሰፊው ቀሚስ ላይ በዙሪ ያው የሮማን ፍሬ አስመስለህ በሠራኸው በሐሩ መካከል የወርቅ ሻኰራ፣ በወርቁ ሻኰራ መካከልም የሮማን ፍሬ የሚመስለውን የሐሩን እንክ ብል እያከታተልክ ሥራ፤

፴፭፣ ወይከውን ላዕለ አሮን ለተልእኮ ወይግበር አሮን ሶበ ይሠውዕ በቃል ዘይሰማዕ እንዘ ይበውእ ቤተ መቅደስ ቅድመ እግዚአብሔር ወእንዘሂ ይወፅእ ከማሁ ከመ ኢይሙት፣

ይህንንም አሮን ለብሶ ያገል ግልበት፣ አሮን መሥዋዕት በሚሠዋበት ጊዜ እግዚአብ ሔርን ለማገልገል ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባም ሲወጣም እንዳይቀሠፍ ድምፅ እንዲያ ሰማ ይሁን፣ /ሐተታ/ ከንጉሥ እልፍኝ ብላቴና ሳይናገርለት ወይም ድምፅ ሳያሰማ ቢገባ ቅጣት እንዲያገኘው አሮንም እንዳይቀሠፍ በዚያ ልማድ ሥርዓት ሠርቶለታል፣ ሕዝቡም



ሲወጣ ሲገባ ድምፁን እየሰሙ ተግተው ነቅተው እንዲጸልዩ ነው፣ ይኸውም የደወል ምሳሌ ነው፣ ፍጻሜው ግን ልብስ የእ መቤታችን፣ ጸናጽል ጌታችን ከእርሷ የነሣው ሥጋ፣ ድምፁ የአካላዊ ቃል ምሳሌ ነው፤

፴፮፣ ወግበር ቀጸላ ወርቅ ረቃቀ እምወርቅ ንጹሕ ወትገብር ላዕሌሃ አርአያ ማኅተም ቅዱስ ለእግዚአ ብሔር፣

ከጠራ ወርቅ የረቀቀ የወርቅ ቀጸላ /ከለቻ/ ሠርተህ ለእግዚ አብሔር የተለየ የሚሆን የማኅተም ቅርፅ በላዩ ቅረፅ በት፣ አኸያ ሸራኸያ ብለህ ቅረፅበት ማለቱ ነው፤

፴፯፣ ወታነብራ ዲበ ዘኅብረ ያክንት ፈትሎ ወታነብራ ዲበ አክሊል መንገለ ፍጽሙ፣

በሰማያዊ ሐር ፈትል አያይ ዘህ በኰፌቱ ላይ በፊቱ በኩል አድርጋት፤

፴፰፣ ወትኩን ውስተ ፍጽሙ ለአሮን ወይንሣእ አሮን ኃጢአተ ቅዱሳት ዘቀደሱ ውሉደ እስራኤል እምኰሉ ሀብተ ቅድሳቶሙ፣

በኰፌቱ ላይ ሁና በአሮን በስተፊቱ የምትታይ ትሁን፣ አሮንም የእስራኤል ልጆች ከገን ዘባቸው ለይተው ከሚሰጡት ስጦታ ሁሉ በተለየ ለኃጢአት

ማስተሥርያ የሚያመጡትን መሥዋዕት ተቀብሎ ኃጢአ ታቸውን ያስተሠርይላቸዋል፤

ወይኩን ውስተ ፍጽሙ ለአሮን ከመ ይኩን ሎሙ ሥጥወ ለእግዚአብሔር፣

እግዚአብሔር ወዶ ይቀበላ ቸው ዘንድ ሁልጊዜ በአሮን ግንባር ሁኖ ይታይ፤

፴፱፣ ወትገብር ዓራዘ እምቢሶስ ወአክሊለ ዘቢሶስ ወቅናዓተ ዘኅብረ ግብረቱ፤

የነጭ ሐር ቀሚስ የነጭ ሐር ኰፌት አሠራሩ ጥልፍ የሆነ መታጠቂያም ሥራ፤

፵፣ ወለደቂቀ አሮን ትገብር ሎሙ አልባሰ ዘቢሶስ ወቅናዓታተ ወቆብዓተ ወይኩን ሎሙ ለክብር ወለአንክሮ፣

የአሮንም ልጆች ከሕዝቡ ተለ ይተው ሊከበሩበት ከነጭ ሐር ቀሚስ መታጠቂያ ኰፌትም ሥራላቸው፤

፵፩፣ ወአግብር ሎሙ ድርማንቀ ዘአጌ ከመ ይሠውሮሙ ኃፍረቶሙ ውነበ ይከድና እምሐቌ እስከ መናቅዕ ለይኩና፣

ዕርቃናቸውን ይሠውርላቸው ዘንድ ከወገባቸው እስከ ቍርጭ ምጭምታቸው የሚያለብስ አድርገህ የተልባ እግር ሰናፊል አሠራላቸው፤

www.ethiopianorthodox.org

፵፩፣ ወታለብሶ ለአሮን እኁከ ወለደቂቁሂ ምስሌሁ ወትቀብኦሙ ወአጽሕዶሙ እደዊሆሙ ወእገሪሆሙ ወቀድሶሙ ከመ ይሡዑ ሊተ፣

እንዲህም አድርገህ ሠርተህ ወንድምህ አሮንና ልጆቹን አልብሳቸው፣ መሥዋዕትንም ያቀርቡልኝ ዘንድ እጆቻቸውን እግራቸውን ቀብተህ አክብረህ ሹማቸው፤

፵፫፣ ወከማሁ ለይልበሱ አሮን ወደቂቁ ሶበ ይበውኡ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ሶበ ይቀርቡ ይሡዑ ኀበ ምሥዋዓ ቤተ መቅደስ፣

አሮንና ልጆቹም መሥዋዕት ለማቅረብ ወደ ደብተራ ኦሪት በሚገቡበት ጊዜ እንደዚሁ እየለበሱ ይግቡ፤

ወኢያምጽኡ ላዕሌሆሙ ኃጢአተ ወኢይሙቱ፣ ሕግ ዘለዓለም ውእቱ ሎቱ ወለዘርኡ እምድኅሬሁ፣

የተወሰነላቸውን ሥርዓት አፍርሰው በራሳቸው ዕዳ አምጥተው እንዳይቀሠፉ ለእሱም ከእሱም በኋላ ለሚነሡ ልጆቹ ይህ የዘለዓለም ሥርዓት ይሁን፣ /ሐተታ/ መጀመሪያ ሰናፊል ይታጠቃል፣ ቀጥሎ እጀ ጠባብ ይለብሳል፣ በዚያ ላይ እጀ ሰፊ ቀሚስ፣ ከእጀ ሰፊ ቀሚስ በላይ ኤፉድና ሎግዮን ይደርባል፣ በኤፉድና በሎግዮ ላይ እንደቋድ ሁኖ የተሠራ አራት የወርቅ ሰንሰለት፣ ሁለቱን በትከሻው በስተፊቱ፣ ሁለቱን በስተኋላው የግራውን ወደ ቀኝ፣ የቀኙን ወደ ግራ እያመሳቀለ የእባብ ራስ አስመስሎ በሠራው ቍልፍና በቀለበቱ ያያይዛቸዋል፣ ከዚህ በኋላ እንደ ጅግራ መልክ ያለ የወርቅ ነጠብጣብ ያለበት በራሱ ላይ ይጠመጥማል፣ ከዚህ በኋላ አኽያ ሸራኽያ ተብሎ የተጻፈበት የወርቅ ከለቻ ያለበት ኮፊት ይደፋል፣ ይኸውም ምሳሌ ነው እጀ ጠባብ የንጽሐ ሥጋ፣ እጀ ሰፊ ቀሚስ የንጽሐ ነፍስ፣ ኤፉድና ሎግዮ የንጽሐ ልቡና፣ አራቱ ቋድ የአራቱ ወንጌላውያን፣ ስምንቱን ቀለበት ሁለት ሁለቱን አያይዞ ታል፣ ቍጥር ሳይሹ የአራቱ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ኮፊት የጸጋ እግዚአብሔር፣ መጠምጠሚያ የረድኤተ እግዚአብሔር፤ አንድም ሙሴ የሊቃነ ጳጳሳት፣

አሮን የጳጳሳት፣ ደቂቀ አሮን የኤጲስቆጶሳት፣ ሌዋውያን የቀሳውስት፤ አንድም ሙሴ የሊቃነ ጳጳሳት የጳጳሳት፣ አሮን የኤጲስቆጶሳት፣ ደቂቀ አሮን የቀሳውስት፣ ሌዋውያን የዲያቆናት፣ ሕዝቡ የምእመናን ምሳሌ።



# ምዕራፍ ፳ወ፱

## ገባኤ

፩፣ ወዝ ውእቱ ዘትገብር ሎሙ እመ ትቄድሶሙ ከመ ይትለአኩኒ፣

ያገለግሉኝ ዘንድ እነሱን አክብረህ በምትሾምበት ጊዜ የምትሠራላቸው ሥራ ይህ ነው፤

ንሣእ ፩ደ ላህመ እምአልህምት ወአባግዓ ንጹሐነ ፪ተ፣

ከላሞች መርጠህ አንድ ወይፈን ቀንዳቸው ያልከረከረ፣ ጥፍራቸው ያልዘረዘረ ሁለት የበግ ጠቦቶች አምጣ፣

፪፣ ወኅብስተ ናዕት ልውሰ በቅብዕ ወጸራይቀ ናዕት ዘበቅብዕ ዘስንዳሌ እምሥርናይ ትገብሮን፣

ልጦ ጒርዶ ከወጣለት ስንዴ ተጋግሮ በዘይት የታሸ ቂጣ በዘይት የተለወሰና የታሸ አምባሻ አምጥተህ፤

፫፣ ወታነብሮን ዲበ መሶብ ወታቄርቦን በመሶብ ወለላህም ወለ፪ቱ አባግዕ፣

ዲበ መሶብና በመሶብ አንድ ወገን ነው፣ እነዚህን በመሶብ አድርገህ አቅርባቸው፣ ወይፈኑንና ሁለቱን የበግ ጠቦቶችም አቅርባቸው፤ አንድም እነዚህን ሁሉ በአንድነት አምጥተህ በምሥዋዑ ላይ አኑራቸው፤

፬፣ ወለአሮን ወለደቂቁ ታቀርቦሙ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ወተ ሐጽቦሙ በማይ፣

አሮንና ልጆቹን ወደ ደብተራ ኦሪት ደጃፍ አቅርበህ በውሀ እጠባቸው፣

፭፣ ወነሢአከ አልባሲሁ አልብሶ ለአሮን እኁከ ልብሰ ቢሶስ ወጸደሬ ወኤፉደ ወሎግዮ ወታስተሣንዕ በሰናስሊሃ፣

ልብሶቹን አምጥተህ ወንድምህ አሮንን አልብሰው፣ የነጭ ሐሩን እጀ ጠባብ እጀ ሰፊውን ቀሚስ፣ ኤፉድና ሎግዮን በቀለበቱና በቍልፉ በወርቁ ሰንሰለት አያይዘህ አልብሰው፤

፮፣ ወታነብር አክሊለ ዲበ ርእሱ ወታነብር ቀጸላ ዘወርቅ ዲበ አክሊሉ፣

ኮፊቱንም በራሱ ላይ ደፍተህ የወርቁን ከለቻ በኮፊቱ ላይ አድርግለት፤

፯፣ ወትነሥእ እምቅብዕ ዘባረከ ወትከዑ ዲበ ርእሱ ወትቀብኦ፣

አክብረህ ካስቀመጥኸው ከቅብዓቱ ዘይት አምጥተህ በራሱ ላይ አፍስሰህ ቅባው፤

፰፣ ወለደቂቁኒ ታቀርቦሙ ወታለብሶሙ አልባሲሆሙ፣

ልጆቹንም አቅርበህ የሚገባ ልብሳቸውን አልብሳቸው፣

www.ethiopianorthodox.org

፱፤ ወታቀንቶሙ ቅናታቲሆሙ ወትወዲ ዲቤሆሙ ቅብዓ ወይከውኑኒ ሠዋዕተ ሊተ ለዓለም፤

መታጠቂያውን አስታጥቃቸው፤ ኮፊቱንም በራሳቸ ላይ ድፋላቸው፤ እንዲህ ሁነው ለዘላለም መሥዋዕት እየሠዉ አገልጋዮች ይሆኑኛል፤

ወትፈጽም እዴሁ ለአሮን ወእደወ ደቂቁ፤

የአሮንንና የልጆቹን ቀኝ ቀኝ እጃቸውን በፊት ደሙን፤ በኋላ ዘይቱን ቅባቸው፤

፲፤ ወታቀርብ ላሕመ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ወያነብሩ አሮን ወደቂቁ እደዊሆሙ ዲበ ርእሰ ላሕም በቅድመ እግዚአብሔር በኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል፤

መሥዋዕተ ኃጢአት የሚሆነውን ወይፈንም ወደ ደብተራ ኦሪት ደጃፍ አቅርበህ አቁመው፤ አሮንና ልጆቹም እግዚአብሔር በሚገለጽባት በደብተራ ኦሪት ደጃፍ ሁነው እጃቸውን በወይፈኑ ራስ ላይ ይጫኑበት፤ /ሐተታ/ ኃጢአታችን ለጊዜው በአንተ፤ ኋላ ግን በክርስቶስ ይሠረይልናል ሲሉ ነው፤

፲፩፤ ወተሐርዶ ለላሕም በቅድመ እግዚአብሔር ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል፤

ወይፈኑንም እግዚአብሔር በሚገለጽባት በደብተራ ኦሪት ደጃፍ ሠዋው፤

፲፪፤ ወትነሥእ እምደመ ላህም ወትወዲ ዲበ አቅርንተ ምሥዋዕ ዘቤተ መቅደስ በአጽባዕትከ ወዘተርፈ ኵሉ ደሞ ትክዑ ጥቃ ቤተ መቅደስ፤

የወይፈኑንም ደም በብርት ተቀብለህ በጣትህ እየነከርክ በቤተ መቅደስ አጠገብ ባለው በአቅርንተ ምሥዋዕ ላይ ቅባው፤ የተረፈውንም ደም ሁሉ በደብተራ ኦሪቱ አጠገብ /በዙሪያው/ አፍስሰው፤

፲፫፤ ወትነሥእ ኵሎ ስብሐ ከርሡ ወከብዶ እንተ ትንዕስ ወክልኤ ኰልያቶ ወስብሐ ዘላዕሌሆን ወታነብር ውስተ ምሥዋዕ፤

የሆድ ዕቃውን ስብ ግልገል ገበቱን፤ ግራ ቀኝ ኩላሊቱን በእነርሱ ላይ ያለውን ስብ ሁሉ አምጥተህ በምሥዋዑ ላይ አድርገህ አጢሰው፤ /ሐተታ/ ስቡን አጢስ አለ፤ ስብ በኋላ የሚገኝ ትርፍ ነገር ነው፤ ከታዘዛችሁት ሕግ ወጥታችሁ፤ ኃጢአት አትሥሩ ብትሠሩም በዚህ ይሠረይላችኋል ሲል ነው፤ ግልገል ገበቱን አጢስ አለው፤ የሐሞት መኖሪያው በገበት ላይ ነው፤ ቍጣም የሚነሣ ከሐሞት ላይ ነውና ተበሳጭታችሁ ኃጢአት አትሥሩ፤ ብትሠሩም በዚህ ይሠረይላችሁ ሲል ነው፤ ሁለቱን



ኵላሊቶቹን አጢስ አለው፤ በገዳመ ኮሬብም ሁለት ዕጓላተ ላሕም አቁመው በድለው ነበርና በዚህ ይሠረይላችሁ ሲል ነው፤

፲፬፤ ወሥጋ ላህም ወማዕሶ ወጽፍአ ታውዒ በእሳት አውዒአከ አፍአ እምትዕይንት እስመ ዘኃጢአት ውእቱ፤

የወይፈኑንም ሥጋ ቁርበቱን ፈርሱንም ከከተማ ውጭ አውጥተህ በእሳት አቃጥለው፤ የኃጢአት ማስተሥርያ መሥዋዕት ነውና፤ ከከተማ ውጭ አቃጥለው ማለቱ ለጊዜው ከሕገ እግዚአብሔር ወጥታችሁ የሠራችሁት ኃጢአት በዚህ ይሠረይላችኋል ሲል ነው፤ ፍጻሜው ግን ጌታ ከከተማ ውጭ በቀራንዮ ተሰቅሎ የዓለሙን ሁሉ ኃጢአት እንዲያስተሠርይ ያጠይቃል፤

፲፭፤ ወትነሥእ አሐደ በግዓ ወያነብሩ አሮን ወደቂቁ ላዕለ ርእሰ በግዑ፤

ከሁለቱ የበግ ጠቦቶች አንዱን አቅርበህ አሮንና ልጆቹ በራሱ ላይ እጃቸውን ይጫኑበት፤

፲፮፤ ወተሐርዶ ለውእቱ በግዕ ወትነሥእ ደሞ ወትክዑ ላዕለ ምሥዋዕ ወውስተ ኵሉ ዓውዱ ትነሰንሶ፤

በጉን አርደህ ደሙን በብርት ተቀብለህ በምሥዋዑ ላይ እርጨው፤ የተረፈውንም ደም በምሥዋዑ ዙሪያ ረብርበው፤

፲፯፤ ወትጠብሖ በበመሌሊቱ ወተሐጽብ ንዋየ ውስጡ ወእገሪሁ ወታነብር ኀበ ዘይሌልየከ፤

በጉንም በየብልቱ አውጥተህ ሆድ ዕቃውን እግሩንም አጥበህ በየብልቱ ለይተህ ካኖርከው ሥጋ ላይ ጨምረው፤

፲፰፤ ወታዓርግ ኵሎ በግዐ ላዕለ ምሥዋዕ ቍርባን ውእቱ ለእግዚአብሔር፤

እንዲህ አድርገህ በጉን በመላው ከምሥዋዑ ላይ አድርገህ አቃጥለው፤ ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ /እግዚአብሔር የሚቀበለው መሥዋዕት ነውና/፤

፲፱፤ ወትነሥእ ካልዓ በግዓ ወያነብሩ አሮን ወደቂቁ እደዊሆሙ ላዕለ ርእሱ፤

ሁለተኛውንም በግ አምጥተህ አሮንና ልጆቹ እጃቸውን በራሱ ላይ ይጫኑበት፤

፳፤ ወሕርዶ ወንሣእ እምደሙ ወአንብር ዲበ ከተማ ዕዝኑ ለአሮን እንተ የማን ወዲበ ከተማ አጽባዕተ እዴሁ ዘየማን ወዲበ ከተማ አጽባዕተ እግሩ ዘየማን፤

በጉንም አርደህ ከደሙ ጠልቀህ /ተቀብለህ/ የአሮንን ቀኝ ጆሮውን የቀኝ እጁንና የቀኝ እግሩን ጣቶች ጫፍ ጫፋቸውን ቅባ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወዲበ ከተማ ዕዘኒሆሙ ለደቂቀ አሮን ዘየማን ወዲበ ከተማ አፃብአ እደዊሆሙ ዘየማን ወዲበ ከተማ አፃብአ እገሪሆሙ ዘየማን፣

የልጆቹንም የቀኝ ጆሮዋቸውን ጫፍ የቀኝ እጃቸውንና የቀኝ እግራቸውን ጣት ጫፍ ቀባ፤

፳፩፣ ወትነሥእ እምደም ዘመሥዋዕት ወእምቅብዕ ቡሩክ ወትነሰንሶ ላዕለ አሮን ወላዕለ አልባሲሁ፣

ከመሥዋዕቱ ደም ከከበረው ከዘይቱ ቅባትም አምጥተህ በአሮንና በልብሱ ላይ እርጨው፤

ወእምድኅሬሁ ላዕለ ደቂቁ ወላዕለ አልባሲሆሙ ወይትቄደስ ውእቱ ወአራዙ ወደቂቁ ወአራዚሆሙ ምስሌሆሙ፣

ከሱም በኋላ በልጆቹና በልብሳቸውም ላይ እርጨው፣ በዚህ ምክንያት እርሱም ልብሶቹም ልጆቹም ልብሳቸውም ይከብራሉ፣

፳፪፣ ወደሞ ለውእቱ በግዕ ትክዑ ውስተ ቤተ መቅደስ በዓውዱ ወትነሥእ እምውእቱ በግዕ ስብሐ ዘይገለብብ ከርሦ ወከብዶ ወክልኤሆን ኰልያቶ ወስብሐ ዘላዕሌሁ፣

የዚያንም በግ ደም በደብተራ ኦሪት ዙሪያ ረብርበው፣ ከዚህም በግ ሆድ ዕቃውን የሚሸፍነውን ስቡን ጉበቱን ግራ ቀኝ ኩላሊቱን በእነርሱም ላይ ያለውን ስብ አምጥተህ፤

ወትነሥእ አገዳሁ ዘየማን እስመ በዝንቱ ይትፌጸም፣

ቀኝ ወርቹንም አምጥተህ በምሥዋዑ ላይ አጢሰው፣ በዚህ አሮን ሀብተ ክህነቱን ሊያገኝ የሚቀባበት ነውና፤ አንድም ይትፌጸም ይላል፣ የአሮን የክህነቱ ሥራ የሚፈጸምበት ነውና፣

፳፫፣ ወኅብስተ አሐተ ወጸሪቀ አሐተ እምውስተ መሶብ ዘውስቴቱ ንቡር ኵሉ ዘሢሞሙ ቅድመ እግዚአብሔር፣

«ወታቀርቦን በመሶብ፣ ብሎ ነበርና ሌዋውያን በቤተ እግዚአብሔር አዘጋጅተው ካኖሩት በመሶብ ውስጥ ካለው በዘይት ከታሸ ከአምባሻውና ከድፎው አንድ አንድ አምጣ፤

፳፬፣ ወታነብር ኵሎ ዘውስተ እዴሁ ለአሮን ወውስተ እደወ ደቂቁ ወትፈልጦ ፍልጣነ በቅድመ እግዚአብሔር፣

ይህንንም ለአሮንና ለልጆቹ በእጅ በእጃቸው አስይዛቸው፣ ይህንንም ለእግዚአብሔር የተለየ አድርገው፤

፳፭፣ ወትትሜጠዎ እምእደዊሆሙ ወታነብሮ ዲበ ምሥዋዕ ለመዓዛ ሠናይ በቅድመ እግዚአብሔር መሥዋዕት ውእቱ ለእግዚአብሔር፣

ከሰጠኻቸው በኋላ ከእጃቸው ተቀብለህ በእግዚአብሔር ፊት



የተወደደ መሥዋዕት ሊሆን በምሥዋዑ ላይ አድርገህ አጢሰው፣ ይኸውም እግዚአብሔር የሚቀበለው መሥዋዕት ነው፣ /ሐተታ/ መጀመሪያ በእጃቸው አስይዛቸው ማለቱ ለጊዜው መሥዋዕተ ክህነት ገንዘባችሁ ነው ሲል ነው፣ ኋላ ተቀብለህ አቃጥለው ማለቱ ያልፍባችኋል ሲል ነው፤

፳፮፣ ወትነሥእ ተላየ ለበግዕ ዘፍጻሜ ለአሮን ወትፈልጦ ፍልጣነ በቅድመ እግዚአብሔር ወይኩን ለከ ክፍለ እምኔሁ፣

አሮን ሲሾም የተሠዋውን የበግ ፍሪንባ አንሥተህ በእግዚአብሔር ፊት የተለየ አድርገው፣ አሮንን ከመሾምህ የተነሣ ለአንተ ዕድል ፈንታ ይሁን፤

፳፯፣ ወመገዝራዕቶኒ ትፈልጥ በከመ ፈለጥከ በግዓ ፍጻሜ እምነበ አሮን ወእምነበ ደቂቁ፣

አሮንና ልጆቹ ተቀብተው የተሾሙበትን የበጉን ፍሪንባ እንደ ለየህ ወርቹንም ለይተህ ለአሮንና ለልጆቹ ስጣቸው፤

፳፰፣ ወይኩኖሙ ለአሮን ወለደቂቁ ሕገ ዘለዓለም በኀበ ውሉደ እስራኤል እስመ ፍልጣን ውእቱ ዝ፣

ይኸውም በእስራኤል ልጆች ዘንድ ለአሮንና ለልጆቹ ለዘለዓለም ሥርዓት ይሁንላቸው፣ ይህ የተለየ የእነሱ ዕድል ፈንታ ነውና፤

ወፍልጣነ ይኩን በኀበ ውሉደ እስራኤል እምዝብሖት ዘይዘብሑ ለፍርቃኖሙ ፍልጣን ለእግዚአብሔር፣

ለእግዚአብሔር የተለየ መሥዋዕተ መድኃኒት አድርገው ከሚያቀርቡት ሁሉ ይህ በእስራኤል ልጆች ዘንድ ለእግዚአብሔር የተለየ ይሁን፤

፳፱፣ ወልብሰ ቅድሳቱ ለአሮን ለይኩን ለውሉዱ እምድኅሬሁ ከመ ይትቀብዑ ቦቱ ወከመ ይፈጽሙ እደዊሆሙ፣

አሮን ተሹሞ የከበረበት ልብስም ልጆቹ ቀኝ ቀኝ አካላቸውን ተቀብተው ይከብሩበት ዘንድ ከእሱ በኋላ ለሚነሡ ለልጆቹ ይሁን፤

፴፣ ወሰቡዓ ዕለተ ለይልበሶ ካህን ዘህየንቴሁ እምደቂቁ ዘይበውእ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ከመ ይሠየም በቅድሳት፣

በንዋየ ቅድሳቱ ይሾም ዘንድ ከልጆቹ ተመርጦ ከእሱ በኋላ በእሱ ምትክ ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ የሚገባው ካህን እስከ ሰባት ቀን እየለበሰው ይግባ፤ አንድም ስለ እሱ ፈንታ የሚሾመው ካህን መሥዋዕት ሲሠዋ፤ ሽቱ ሲቀባ ሰንብቶ በሰባተኛው ቀን ልብሱን ይልበሰው፤

www.ethiopianorthodox.org

፴፩፤ ወበግዓ ዘፍጻሜ ትነሥእ ወታበስል ሥጋሁ በመካን ቅዱስ፤

ደሙን ሊቀቡት የተሠዋው ንም በግ ሥጋውን ወስደህ በከበረ ቦታ ቀቅለው፤

፴፪፤ ወይብልዑ አሮን ወደቂቁ ሥጋ በግዕ ወኅብስተ ዘውስተ መሶብ በኀበ ሞኅተ ደብተራ ዘመርጡል፤

የተቀቀለውን ሥጋና በመሶብ የቀረበውን ኅብስት /አምባሻ/ አሮንና ልጆቹ በደብተራ ኦሪት ደጅ ሆነው ይብሉት፤

፴፫፤ ወይብልዕዎ በኀበ ተቀደሰ በህየ ከመ ይፈጽሙ እደዊሆሙ ለተቀድሶቶሙ ወወልደ ባዕድ ኢይብልዖ እስመ ቅዱስ ውእቱ፤

ቀኝ ቀኝ አካላቸውን ተቀብተው ይሾሙበት ዘንድ ለእነርሱ ክብር በተለየ ቦታ ሁነው ይብሉት፤ ነገር ግን የከበረ ነውና ከአሕዛብ የተወለደ አይብላው፤ /ሐተታ/ አሕዛብ ንስ ኢይባእ ሞዓባዊ ወአሞናዊ ብሎ ከነመግባቱ ሳይቀር ይከለ ክላቸዋል ብሎ ከሌዊ ያልተ ወለደ አይብላው ሲል ነው፤

፴፬፤ ወለእመ ተርፈ እምሥጋ መሥዋዕት ዘፍጻሜ ወኅብስትኒ እስከ ደግደግ ታውዕዮ በእሳት ለዘተርፈ ወኢይትበላዕ እስመ ቅዱስ ውእቱ፤

ደሙን ተቀብተው ሊከብሩበት ከተሠዋው ሥጋና ከኅብስቱ ቢተርፍ የተረፈው እንዳያድር በእሳት አቃጥለው፤ የዕለት መሥዋዕት ሊሆን የታዘዘ ነውና አድሮ ሊበሉት አይገባም፤

፴፭፤ ወግበር ለአሮን ወለደቂቁ ከመዝ ኵሎ ዘከመ አዘዝኩከ ሰቡዓ ዕለተ ከመ ትፈጽም እደዊሆሙ፤

ሰባት ቀን ቀኝ ቀኝ አካላቸውን ትቀባቸው ዘንድ እንዳዘዝ ኩህ ለአሮንና ለልጆቹ የምት ሠዋውን መሥዋዕት እንደ ዚሁ ሰባት ሰባት ቀን አድርግ ላቸው፤

፴፮፤ ወላሕመ ዘእንበይነ ኃጢአት ትገብር ለለዕለቱ በዘቦቱ ታነጽሕ ምሥዋዓ ሶበ ትቄድስ ቦቱ ወትቀብዖ፤

ደሙን ቀብተህ በምታከብር በት ጊዜ ምሥዋዑን በምታነፃ ገንዘብ ስለ ኃጢአት የሚሠ ዋውንም መሥዋዕት ዕለት ዕለት አንዳንድ ላም ሠዋ፤

፴፯፤ ሰቡዓ ዕለተ ታነጽሖ ለምሥዋዕ ወትቄድሶ ወይከውን ምሥዋዒከ ቅዱሰ ቅዱሳን ወኵሉ ዘለከፎ ለውእቱ ምሥዋዕ ለይትቀደስ፤

እስከ ሰባት ቀን ደሙን እየቀ ባህ አንጽተህ አክብረው፤ እንዲህ ሁኖ ምሥዋዑ ከከበሩ የከበረ፤ ከተለዩ የተለየ ይሁን፤ ምሥዋዑንም የሚነካ ሰው ሁሉ ከኃጢአት የተለየ ይሁን አለ፤ ንጹሕ ያልሆነ አይንካው



ሲል ነው፤ አንድም ምሥዋዑን የነካ ሁሉ ይከብራል ሲል ነው፤

፴፰፤ ወዝ ውእቱ ዘትገብር ለመሥ ዋዕት ዘዘልፍ አባግዓ ንጹሓነ እለ አሐቲ ዓመቶሙ ፪ተ ለለዕለቱ፤

ዕለት ዕለት ለምትሠዋው መሥ ዋዕት የምታደርገው ይህ ነው፤ ዓመት የሆናቸው ቀንዳቸው ያልከረከረ ጥፍራቸው ያልዘ ረዘረ ነውር የሌለባቸው ሁለት ሁለት ጠቦቶች እያመጣህ በየቀኑ ሠዋ፤

፴፱፤ ወአሐደ በግዓ ትገብር በጽባሕ ወአሐደ ፍና ሠርክ፤

ከእነዚህም አንዱን ጧት አንዱን ማታ ሠዋ፤

፵፤ ወአሥራታ ለኢፍ ስንዳሌ ልፉጽ በቅብዕ ወልቱም በራብዕታ ለኢን ወሞጻሕተ ወይን ራብዕታ ለኢን ለለአሐዱ በግዕ፤

ለአንዱ በግ የሚቀርበው የኢፍ ዐሥረኛ የሚሆን ልጦ ገርዶ የወጣለት ስንዴ ዱቄት የገንቦ አራተኛ በሚሆን ዘይት ታሽቶ የተጋገረ ዳቦ ፍልቅ አድርገው አፍስሰው የሚጠጡትም ወይን የገንቦ አራተኛ ይሁን፤

፵፩፤ ወለካልዕኒ በግዕ ዘትገብሮ ፍና ሠርክ በሐሳበ መሥዋዕትከ ዘነግህ ትገብሮ ወከማሁ ሞጻሕቶኒ ትገብሮ ለመዓዛ ሠናይ፤

ሁለተኛውንም በግ በምትሠዋ በት ጊዜ በሠርክ የምታቀርበው ወይኑም ኅብስቱም የጧቱን መሥዋዕት በምታቀርብበት ልክ ይሁን፤ በጐ መዓዛ አድርጎ ሊቀበለው ወይኑንም እንደዚሁ አድርግ፤

፵፪፤ መሥዋዕት ውእቱ ለእግዚአ ብሔር ዘወትር ለትውልድክሙ ኀበ ሞኅተ ደብተራ ዘመርጡል በቅድመ እግዚአብሔር በዘእት ኤመር ለከ በህየ ከመ እንብብከ፤

ይኸውም አነጋግርህ ዘንድ ለአንተ በምገለጥልህ በደብተራ ኦሪት ደጃፍ ዘወትር ወደ እግዚአብሔር የምታቀርቡት የመሥዋዕቱ ሥርዓት ለልጅ ልጅ ይሁን፤

፵፫፤ ወእኤዝዞሙ በህየ ለውሉደ እስራኤል ወእትቄደስ በክብርየ፤

እኔም በዚህ በጌትነቴ ክብር ተገልጬ ለእስራኤል ልጆች ሊሠሩት የሚገባቸውን አዛቸዋ ለሁ፤ አንድም የእስራኤልን ልጆች ይህን አዝዤ በክብሬ እመስገናለሁ፤ ሳይከብሩ መመ ስገን አለና፤

፵፬፤ ወእቄድሳ ለደብተራ መር ጡል ወለምሥዋዒሃ ወእቄድሶሙ ለአሮን ወለደቂቁ ከመ ይሡዑ ሊተ፤

ደብተራ ኦሪትን መሠዊያዋ ንም አከብራለሁ፤ መሥዋዕት ያቀርቡልኝ ዘንድ አሮንና ልጆቹንም ከሌዋውያን ለይቼ አከብራቸዋለሁ፤

www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

፵፭፣ ወአሐድር ማዕከሌሆሙ ለውሉደ እስራኤል ወእከውኖሙ አምላኮሙ፣

እነሱ በሚያቀርቡልኝ መሥዋ ዕት ምክንያት በእስራኤል ልጆች መካከል አድሬ እኖራ ለሁ፣ አቡሆሙ ሲል ነው፣ የፍቅር የሃይማኖት አባት እሆናቸዋለሁ፤ አንድም እንዳለ ይሆናል፣ የፍቅር የሃይማኖት አምላክ እሆናቸዋለሁ፣ ሳይወ ዱት የሚወደድ ሳይፈጥር የሚመለክ አለና፤

፵፮፣ ወየአምሩ ከመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር አምላኮሙ ዘአውፃ እክዎሙ እምድረ ግብፅ ከመ እሰመይ በላዕሌሆሙ ወእከውኖሙ አምላኮሙ፤

ባደርኩባቸውም ጊዜ የእስራ ኤል አምላክ ተብዬ እጠ ራባቸው ዘንድ እነሱም የእግዚ አብሔር ልጆች ተብለው በእኔ ስም ይጠሩ ዘንድ ከግብጽ ያወጣ ኋቸው ፈጣሪያቸው እግዚአብ ሔር እኔ እንደ ሆንኩ ያውቃሉ።

## ምዕራፍ ፴

፩፣ ወግበር ሊተ ምሥዋዐ ዘዕጣን እምዕፅ ዘኢይነቅዝ፣

ሽምሽርሰጢን ከሚባል ከማይነ ቅዝ ዕንጨት ቈርጠህ ዕጣን የሚያሳርጉበትን ምሥዋዕ ሥራልኝ፤

፪፣ ዘእመት ኑኁ ወእመት ራኅቡ ርቡዓ ግበሮ ወካዕበ እመት ቆሙ ወእምኔሁ ይትገበሩ አቅርንቲሁ፣

ወደ ላይ ቁመቱ ሁለት ክንድ፣ ርዝመቱ ክንድ፣ ወርዱ ክንድ የሚሆን አራት ማዕዘን አድር ገህ ሥራው፣ ቀንዶቹም ሥረ ወጥ ይሁኑ፤

፫፣ ወቅፍሎ ወርቀ ንጹሐ ምድሮ ወዓውደ ዓረፍቲሁ ወአቅርንቲሁ ወግበር ሎቱ ቀጸላ ዘወርቅ በዓውዱ፣

ዕጣንና ፍሕም የሚሆንበት ውስጡንና ውጭውን ዙሪያው ንም ሁለቱንም ቀንዶች በጠራ ወርቅ ለብጠው፣ ዙሪያውንም የወርቅ ክፈፍ ሥራለት፤

፬፣ ወግበር ሎቱ ክልኤተ አውቃ ፋተ ወርቅ መትሕተ ቀጸላሁ ላዕለ ክልኤቱ ፍናዊሁ ወትገብር ላዕለ ክልኤቱ ገበዋቲሁ ወይኩኑ አብያተ ለመባውሪሁ ከመ ያንሥኡ በሙ ኪያሁ፣

በሁለት ወገን የሚሆኑ ሁለት የወርቅ ቀለበቶች ሠርተህ በሁለት መዓዝን አድርጋቸው፣ እነዚህም መሎጊያዎቹን አግብ ተው ማዕጠንቱን የሚሸከሙ ባቸው ይሁኑ፤

፭፣ ወግበር መባውርተ እምዕፅ ዘኢይነቅዝ ወቅፍሎሙ ወርቀ፣

ሽምሽርሰጢን ከሚባል ከማይ ነቅዝ ዕንጨት ቈርጠህ መሎጊ ያዎቹን አብጅተህ በለዘበ ወርቅ ለብጣቸው፤



፮፣ ወታነብሮ ቅድመ መንጦላዕት ዘሀሎ ዲበ ታቦት ዘመርጡል በዘእትኤመር ለከ በህየ፣

ማዕጠንቱን ሠርተህ እኔ በምገ ለጥልህ በደብተራ አሪት ውስጥ ባለው ታቦት አጠገብ በተጋረደው መጋረጃ ውስጥ አኑረው፤

፯፣ ወይዕጥን በውስቴቱ አሮን ዕጣነ ዘቅታሬ ድቁቀ በበነግህ፣

/ዘቅታሬ/ ዘመዓዛ ሲል ነው፣ አሮንም በጎ መዓዛ ያለው፤ አንድም ጢሱ ተኖ የሚወጣ የደቀቀ ዕጣን ማለዳ ማለዳ በውስጡ ይጠንበት፤

፰፣ ወሶበ ይገብር መኃትወ በሠርክ ይዕጥን በውስቴቱ ዘዘልፍ በቅድመ እግዚአብሔር በትውልድክሙ፣

ማታ መብራት በሚያበራበት ጊዜ ዘወትር በውስጡ ይጠ ንበት፣ እግዚአብሔር በሚወ ደው ሥራ እስከ ልጅ ልጅ ሥርዓት ይሁንላችሁ፤

፱፣ ወኢትደምሩ ውስቴቱ ዕጣነ ዘካልዕ ቅታሬሁ መሥዋዕተ ወሞፃ ሕተ ኢታውጽሑ ዲቤሁ፣

መዓዛው ልዩ የሆነ ሌላ ዕጣን አትጨምሩበት፣ በዚህ በማዕ ጠንቱ መሥዋዕትም ቢሆን ወይንም ቢሆን አታጢሱበት፣

፲፣ ወይትመሐለል አሮን በአቅር ንቲሁ ለለዓመት ምዕረ ወይነሥእ እምደም ዘያነጽሕ ኃጢአተ ምዕረ ለለዓመት፣

አሮንም በየዓመቱ አንዳንድ ቀን ሁለቱን አቅርንተ ምሥዋዕ /የማዕጠንቱን ቀንዶች/ ይዞ ጉብቶ ወገኖችህን ይቅር በል እያለ ይጸልይ፣ ከዓመት አንድ ጊዜ ኃጢአት ለማንጻት ከሚ ሠዋው መሥዋዕትም ደሙን ተቀብሎ አቅርንተ ምሥዋዑን ይቀባ፤

ወይገብር ከመ ያንጽሕ ትውልዶሙ ወቅዱሰ ቅዱሳን ውእቱ ለእግዚ አብሔር፣

የእስራኤልን ልጆች ከኃጢ አት ያነፃቸው ዘንድ እንዲህ ያድርግላቸው፣ ይኸውም ለእግ ዚአብሔር ከተለዩ የተለየ፣ ከከበሩ የከበረ ገንዘብ ነው፣ /ሐተታ/ ሽምሽርሰጢን ከሚባል ዕንጨት ወርዱ ክንድ፣ ርዝ መቱ ክንድ፣ ቁመቱ ሁለት ክንድ፣ አድርገህ ክንዱን ትተህ ክንዱን ፈልፍለህ ማዕ ጠንት አብጅተህ በውስጥ በአፍአ በወርቅ ለብጠው፣ በቀኝና በግራ ሁለት አቅርንት አውጣለት፣ ለመሸከሚያም ሁለት ቀለበት አሠርተህ በቀለ በቱ ውስጥ አግብተው የሚሸ ከሙበት ሁለት መሎጊያ አብ ጅተህ በዚያ ተሸክመውት

www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

ይኀዙ፣ በማዕጠንቱም ውስጥ ፍሕሙን ዕጣኑንም ጨምረህ በወርቅ ዘንግ አስማምተህ ወርቁ አይቻልምና ፈጥነህ በብርት ተቀበለው ብሎታል፣ ይኸውም ምሳሌ ነው፣ ማዕጠንት የእመቤታችን፣ ወርቅ የቅድስናዋ የንጽሕናዋ፣ አቅርንት የሥልጣኑ እግዚአብሔር፣ ክንዱን ፈልፍለህ ክንዱን ተወው ማለቱ ድንግል ወእም የመባሏ፣ የወርቅ ዘንግ የመንፈስ ቅዱስ፣ ፍሕም የመለኮት፣ ዕጣን የትስብእት፣ የከፈለ ያዋሐደ መንፈስ ቅዱስ ነውና፣ ጢሱ የመሥዋዕትነቱ፤ አንድም እሳት የሥግው ቃል፣ ዕጣን የመሥዋዕትነቱ፣ ጢሱ የምእመናን የዕርገተ ጸሎታቸው ምሳሌ፣ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ስብ ቢያጤሱ ደም ቢያፈሱ ቅድመ እግዚአብሔር አልደረሰላቸውም፣ ጌታ ሰው ከሆነ በኋላ ግን ልመናቸው ቅድመ እግዚአብሔር የሚደርስላቸው ሁኗል፤

## ግባኤ፣

፲፩፣ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፣

እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፣

፲፪፣ ለእመ ነሣእከ ሐሊናሆሙ ለውሉደ እስራኤል ከመ ትኊልቁሙ ለየሀብ ፩ዱ ፩ዱ ቤዛ ነፍሱ ለእግዚአብሔር፤

የእስራኤልን ልጆች ፈቃዳቸውን አውቀኸው እንደሆነ፤ አንድም ልቡናቸውን አግኝተኸው እንደሆነ፣ በቈጠርካቸው ጊዜ አንዱም አንዱም ለሰውነቱ ቤዛ የሚሆን ወርቁን ለእግዚአብሔር ይስጥ፤

ወኢይምጻእ ላዕሌሆሙ ድቀት አመ ትኌልቆሙ፣

በቈጠርካቸው ጊዜ በእነሱ ላይ መቅሠፍት እንዳይመጣባቸው፤

፲፫፣ ወዝውእቱ ዘይሁቡ ኵሎሙ እለ የሐውሩ ከመ ይትኊለቁ መንፈቀ ለሰቅል፣ በሰቅል ቅዱስ እስራ አቦሊ ሰቅል ወመንፈቀ ለሰቅል ቍርባኑ ለእግዚአብሔር፣

ለመቈጠር የሚመጡም ሁሉ የሚያመጡት ገንዘብ ይህ ነው፣ በቤተ መቅደስ አዋቂ ሚዛን የወቄት እኩሌታ ነው፣ ወቄቱም ሃያ አቀመት ነው፣ ለእግዚአብሔር መባዓ የሚሰጠውም የወቄት እኩሌታ ነው፤

፲፬፣ ወኵሉ ዘየሐውር ከመ ይትኊለቍ ዘእምዕሥራ ክራማቲሁ ወፈድፋደ፣

ለመቈጠር የሚሔዱትም ሃያ ዓመት የሞላቸው ከዚያም በላይ ያሉ ናቸው፤



፲፭፣ ባዕል ኢይወስክ ወነዳይ ኢያንትግ እመንፈቃ ለሰቅል እለ ያበውኡ ቍርባኖሙ ለእግዚአብሔር ቤዛ ነፍሶሙ፣

ለሰውነታቸው ቤዛ ሊሆን ለእግዚአብሔር መብዓ የሚሠጡ ሰዎች ሁሉ ባለጸጋ ከወቄት እኩሌታ አያብዛ፣ ድኃም ከዚያ አያሳንስ፤

፲፮፣ ወትነሥእ ብሩረ ዘአብኡ ቍርባኖሙ ውሉደ እስራኤል ወትሁቦ ለምግባረ ደብተራ ዘመርጡል ወይኩኖሙ ተዝካሮሙ ቅድመ እግዚአብሔር ቤዛ ነፍሶሙ፣

ለሰውነታቸው ቤዛ ሊሆን በእግዚአብሔር ዘንድ፣ መታሰቢያ ይሆንላቸው ዘንድ የእስራኤል ልጆች መብዓ አድርገው ያገቡትን ወርቁን ብሩን ተቀብለህ ለደብተራ ኦሪት መሥሪያ አድርገው፤

፲፯፣ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፣

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው፤

፲፰፣ ግበር መቅለደ ዘብርት ወመንበሩሂ ዘብርት ወታንብሮ ማዕከለ ደብተራ ዘመርጡል ወማዕከለ ምሥዋዕ ወትሠውጥ ውስቴቱ ማየ፣

የናስ ሠን ከእግሩ ዛቅኔው /መቀመጫ/ ጋር ሠርተህ በደብተራ ኦሪትና በምሥዋዑ መካከል አድርገህ ውሃ ሙላው፤

፲፱፣ ወይትሐፀቡ አሮን ወደቂቁ እምውስቴቱ እደዊሆሙ ወእገሪሆሙ፣

አሮንና ልጆቹ በሠን ካለው ውሃ እጃቸውንና እግራቸውን ይታጠቡ፤

፳፣ ወሶበ ይበውኡ ውስተ ደብተራ መርጡል ከመ ይሡዑ ወሶበ የዓርጉ ይሡዑ መሥዋዕተ ለእግዚአብሔር ይትሐፀቡ እደዊሆሙ ወእገሪሆሙ ከመ ኢይሙቱ፣

መሥዋዕት ለማቅረብ ወደ ደብተራ ኦሪት በሚገቡበት ጊዜ ከደብተራ ኦሪትም ወጥተው የሚቃጠል መሥዋዕት ለማቅረብ ወደ ምሥዋዓ ብርት በሚሔዱበት ጊዜ እንዳይቀሥፉ እጃቸውንና እግራቸውን ይታጠቡበት፣ /ሐተታ/ ለጊዜው ከእድፍ ሳይነጹ ቢገቡ ይቀሥፉሉና፣ ፍጻሜው ግን ከኃጢአት ሳይነጹ ሥጋውን ደሙን ቢቀበሉ ፍዳ እንዳያመጣ ያጠይቃል፤

፳፩፣ ወይኩኖሙ ሕግ ዘለዓለም ሎሙ ወለውሉዶሙ እምድኅሬሆሙ፣

ይኸውም ለእነሱ ከእነሱ በኋላም ለሚነሡ ለልጆቻቸው የዘለዓለም ሥርዓት ይሁንላቸው፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፪፣ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፣

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ተናገረው፤

፳፫፣ አንተ ንሣእ አፈዋተ ጽጌ ዘከርቤ ቅድወ ኃምስተ ምዕተ ሰቅለ ወቀናንሞ ቅድወ በመንፈቁ ለቀዳሚ ክልኤተ ምዕተ ወኃምሳ ወቀጺመተ ቅድወ ፪ተ ፻ተወ፶፣

ካማረ ከተወደደ ከርቤ ከሚባል ሽቱ አበባ የተጣፈጠ አምስት መቶ ወቄት፣ ካማረ ከተወደደ ቀናንሞ ከሚባል ሽቱ የተጣፈጠ ከርቤ ለሚባለው ሽቱ እኩሌታ ሁለት መቶ አምሳ ወቄት፣ ካማረ ከተወደደ ቀጺመት ከተባለ ሽቱ የተጣፈጠ ሁለት መቶ አምሳ ወቄት ተቀበል፤

፳፬፣ ወአበሜ ፭ተ ምዕተ በሰቅል ቅዱስ ወቅብዓ ዘይት በመስፈርተ ኢን፣

አበሜ የሚባለውንም ሽቱ በቤተ እግዚአብሔር ዓዋቂ /ሚዛን/ አምስት መቶ ወቄት፣ የዘይት ቅብዓትም አንድ ገንቦ ተቀብለህ፤

፳፭፣ ወግበር ቅብዓ ቅዱሰ ጽሁጠ ዘጸዓጢ፣

ብልህ አዋቂ ሰው ያጣፈጠው የተለየ ቅብዕ አድርገህ አጣፍጠህ አኑረው፣

፳፮፣ ወትቀብዓ እምኔሁ ለደብተራ ዘመርጡል ወለታቦተ መርጡል፣

ከዚህ ከተጣፈጠው ሽቱ ደብተራ ኦሪትንና በደብተራ ኦሪት ውስጥ ያለች ታቦትን ቅባት፤

፳፯፣ ወማዕደ ወኵሎ ንዋዮ ወለተቅዋመ ማኅቶት ወለኵሉ ንዋያ ወለምሥዋዕኒ ዘዕጣን፣

ኅብስት የሚቀርብበት ሰደቃውን ከዕቃው ሁሉ ጋር ቅባው፣ መብራት የሚያበሩበት መቅረዙንም ከዕቃው ሁሉ ጋር ቅባው፣ ዕጣን የሚያሳርጉበት ምሥዋዑንም ቅባው፤

፳፰፣ ወለምሥዋዕ ዘመሥዋዕት ወለኵሉ ንዋዩ ወለመቅለድ ምስለ መንበሩ፣

መሥዋዕት የሚሠዋበት ምሥዋዑን ከዕቃው ሁሉ ጋር ሠኑን ኰስኩስቱን ከእግረ ዛቀኔው ጋር /ከማስቀመጫው ጋር/ ቅባው፤

፳፱፣ ወትቄድሶሙ ወይከውኑ ቅዱሳነ ወዘኪያሆሙ ለከፈ ለይትቀደስ፣

እንዲህ አድርገህ አክብራቸው የከበሩም ይሁኑ፣ እነሱን የነካ ሁሉም የከበረ ይሁን፤



፴፣ ወለአሮን ወለደቂቁ ቅብዖሙ ወቀድሶሙ ከመ ይሡዑ ሊተ፣

አሮንንና ልጆቹንም መሥዋዕት ያቀርቡልኝ ዘንድ ይህን ሽቱ ቀብተህ አክብራቸው፤

፴፩፣ ወበሎሙ ለውሉደ እስራኤል ዝ ቅብዕ ዘይትቀብዑ ቅዱሰ ለይኩን ማዕከሌሆሙ ለትውልድክሙ፣

ለእስራኤል ልጆች እንዲህ በላቸው፣ ሌዋውያን የሚቀቡት ይህ ዘይት /ሽቱ/ በእናንተና በሌዋውያን መካከል ለልጅ ልጆችሁ የተለየ ይሁን አለ፣ እናንተ አትቀቡት ሲል ነው፤

፴፪፣ ወባዕድ ሰብእ ኢይትቀባዕ እምኔሁ ወከመ አምሳሊሁ ኢትግበሩ ለክሙ ከማሁ እስመ ቅዱስ ውእቱ ዝ ቅብዕ አመ ትገብርዎ፣

ከእስራኤል ያልተወለደ አሕዛብ ከዚህ ሽቱ አይቀባ፣ ይህስ ምን ጊዜም አይሆንም ብሎ ከሌዊ ያልተወለደ ሰው አይቀባው፣ እሱንም አስመስላችሁ፤ ሌላ አጣፍጣችሁ ቤታችሁ አታኑሩ በምትቀቡበት ጊዜ ይህ ቅብዕ የከበረ ነውና፤

፴፫፣ ወዘወሀበ እምኔሁ ለባዕድ ዘመድ ለይሠሮ እምሕዝብ፣

ከነገደ ሌዊ ሳልተወለደ /ላላመነ/ ሰው ከዚህ ቅብዕ የሰጠ ከወገኑ ተለይቶ ይሙት፤

፴፬፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ንሣእ ለከ አፈዋተ ማየ ልብን ወቀንዓተ ቅድወ ወስኒነ ዘያንፀበርቅ ወኵሉ ዕሩየ ለይኩን ድልወቱ፣

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፣ ልባንጃ የሚባል ሽቱ ያማረ የተወደደ ቀንዓት የሚባል ሽቱ የጠራ ንፁሕ ዕጣን ከእስራኤል ተቀበል፣ የሁሉም ሚዛኑ የተካከለ ይሁን፣ አንድም በድልወቱ ይላል፤ ሁሉም በሚዛኑ የተካከለ ይሁን፤

፴፭፣ ወግበርዎ ዕጣነ ኪያሁ ግብረ ዕጣን ቅድወ ወግብረ ንጹሐ ወቅዱሰ ግበር፣

ይህንም በታጠነ ጊዜ መዓዛው ያማረ የተወደደ ሊሆን አሠራሩ የተለየ የጠራ አድርጋችሁ ሥሩት፣

፴፮፣ ወተሐርዕ እምኔሁ ድቁቀ ወታነብሮ ቅድመ ደብተራ ዘመርጡል በዘቦቱ እትኤመር ለከ እምህየ ወቅዱሰ ቅዱሳን ለይኩን ክሙ ዝ ዕጣን፣

ከዚህም ከፍለህ ወቅጠህ አድቅቀህ እኔ በምገለጽልህ በደብተራ ኦሪት በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ አኑረው፣ ይህም ዕጣን የከበረ የተለየ ይሁን፤

www.ethiopianorthodox.org

፴፯፣ ወበዝ ግብረት ኢትግበሩ አርዓያ ዝ ዕጣን ኅሩመ ለይኩን ከሙ ዝንቱ ወቅዱስ ለእግዚአብ ሔር፣

በዚህም አምሳል ሌላ ዕጣን አታድርጉ ይህም ለእናንተ ታደርጉት ዘንድ የማይገባ ለእግዚአብሔር የተለየ ገንዘብ ይሁን፤

፴፰፣ ወዘአግበረ እምኔሁ ከመ ያጼንዎ ለይማስን እምሕዝቡ፣

ከቤቱ ሊያጥነው ይህን አስመ ስሎ ያዘጋጀ ሰው ቢኖር ከወገ ኖቹ ተለይቶ ይሙት /ይጥፋ/።

## ምዕራፍ ፴ወ፩

፩፣ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፣

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፤

፪፣ ናሁ ተሰመይኩ በስሙ ለባስ ልኤል ወልደ ኡሪ ወልደ ሑር ዘእምነገደ ይሁዳ፣

ከይሁዳ ወገን የተወለደ ሑር የወለደው የኡሪ ልጅ በሚሆን በባስልኤል ስም እነሆ ተጠራሁ አለው፣ /ሐተታ/ ባስልኤል ማለት ኃይለ እግዚአብሔር፣ ንጉሥ እግዚአብሔር ማለት ነውና፤ አንድም ጸዋዕክዎ በስምየ ይላል፣ እነሆ ባስል ኤልን በስሜ ጠራሁት አለ፣ ኃይለ እግዚአብሔር ብዬ ጠራሁት፤

፫፣ወመላእክዎ መንፈሰ ቅዱስ ወጥበበ ወአእምሮ ወእቁም በኵሉ ምግባር የሐሊ፣

በባስልኤል መንፈሰ ረድኤትን አሳደርኩበት፣ ጥበብንና ዕውቀ ትንም፣ ገለጽኩለት የሚሠራ ውንም ያስብ ዘንድ በሥራው ሁሉ የተከናወነ ነው፤

፬፣ ወይኩን ሊቀ ዐረብት ወከመ ይግበር ወርቀ ወብሩረ ወብርተ ወኅብረ ያክንት ወኅብረ ከብድ ወለይ ክዑብ ወቢሶስ ክዑብ፣

ብልህ ገበዝ አንባ /የአናጢ ዎች አለቃ ሁኖ፣ ብሩሂ ሐር ቀይ ሐር ዕጥፍ ሁኖ የተሠራ ነጭ ሐር ይሠራ ዘንድ፤

፭፣ ወግብረ ዕብንሂ ዘይትገበር ውስተ ምግባር ወዘይፀርብ እምዕፀ ከመ ይግበር እምኵሉ ግብሩ፣

በኤፉድና በሎግዮ ላይ የሚቀ ረጹ የአዕናቍንም ሥራ ይሠራ ዘንድ ከዕንጨትም ወገን የሚጠረበውን የዕንጨቱን ሥራ ሁሉ ክባስ ምዕማድ አድርጎ ይሠራ ዘንድ መንፈሰ ረድኤትን አሳደርኩበት፤

፮፣ ወአነ ወሀብኩ ኤልያብሃ ወልደ አክሲምክ ዘእምነገደ ዳን፣

ከነገደ ዳን የተወለደ የአክሴ ምክ ልጅ ኤልያብን ለባስል ኤል አጋዥ አድርጌ ሰጠሁት፣



ወለኵሉ ጠቢባነ ልብ ወሀብኩ አእምሮ ወይግበሩ ኵሎ ዘአዘዝኩከ፣

ያዘዝኩህን ሁሉ ይሠሩ ዘንድ የልቡና ጥበብ ላላቸው ሁሉ ዕውቀትን ገለጽኩላቸው፤

፯፣ ደብተራ ዘመርጡል ወታቦተ ዘኅርመት ወምሕዋዐ ዘላዕሌሃ ወንዋያ ለደብተራ፣

ሰቀልኛ ድንኳን ይሠሩ ዘንድ ሕግ የተጻፈበት ጽላት ያለበ ትንም ታቦት ይሠሩ ዘንድ እስራኤልን በረድኤት የሚጎ በኝበትን፣ በላይዋ ያለውን መግጠሚያም ይሠሩ ዘንድ የደብተራ አሪትን ንዋየ ቅድሳቱን ሁሉ ይሠሩ ዘንድ ዕውቀትን ገለጥኩላቸው፣ ምሕዋድ አለው፣ መግጠሚ ያውን ቃለ እግዚአብሔር ጠይቀው ይሰሙበታልና፤

፰፣ ወምሥዋዓ ዘዕጣን ወተቅዋመ ማኅቶት ንጽሕተ ወኵሎ ንዋየ ወማዕደ ወኵሎ ንዋዮ፣

ዕጣን የሚታጠንበት ማዕጠ ንቱን ፋና የሚበራባት መቅረ ዚቱን ከጠራ ወርቅ ይሠራ ዘንድ አዕፁቋን ምንባረ ፈትሏንም ይሠሩ ዘንድ ማዕዱን /ሰደቃውን/ ከቀለበ ቱና ከመሎጊያው ጋር ይሠሩ ዘንድ፤

፱፣ ወምሥዋዓ ዘመሥዋዕት ወኵሎ ንዋያቲሁ ወማዕከከ ወመንበሮ፣

ስብ የሚጤስበት ምሥዋዓ ብርቱን መጫሪያውንም ሁሉ ይሠሩ ዘንድ ኵስኵስቱን ከነ መቀመጫው /እግረ ዛቀኔ/ ይሠሩ ዘንድ፤

፲፣ ወአልባሲሁኒ ዘክብሩ ለአሮን ወአልባሰ ደቂቁ በዘቦቱ ይገብሩ ሊተ ገብረ፣

አሮንም የሚከበርባቸውን ልብሶች፣ ልጆቹም እኔን በሚያ ገለግሉበት ጊዜ የሚለብሱትን ልብስ ይሠሩ ዘንድ፣

፲፩፣ ወቅብዓ ዘይትቀብዑ ወዕጣነ ዘየዓጥኑ ለመቅደስ ወኵሎ ዘአዘዝኩከ ይግበሩ፣

ካህናቱ የሚቀቡትን ሽቱ ለመቅ ደስም የሚያጥኑትን ዕጣን ያዘጋጁ ዘንድ ያዘዝኩህንም ሁሉ ይሠሩ ዘንድ ዕውቀትን ገለጽኩላቸው፤

፲፪፣ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፣

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፤

፲፫፣ አንተ አዝዞሙ ለደቂቀ እስራ ኤል ወበሎሙ ዑቁ ከመ ትዕቀቡ ሰንበትየ እስመ ትእምርት ውእቱ በኀቤየ ወበኀቤክሙኒ ወበትውል

www.ethiopianorthodox.org

ድክሙ ከመ ታእምሩ ከመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር ዘእቄድ ሰክሙ፣

ቀዳሚት ሰንበትን እንድታከብሩ ዕወቁ ብለህ አንተ የእስራኤልን ልጆች እዘዛቸው፣ የማከብራችሁ እግዚአብሔር እኔ እንደ ሆንኩ ታውቁ ዘንድ፣ በእኔና በእናንተ በልጆቻችሁም መካከል የገኘና የተገኘ ምልክት ነውና፤ አንድም የዕረፍተ ነፍስ ምልክት ነውና፤

፲፬፣ ወዕቀቡ ሰንበትየ እስመ ቅድስት ይእቲ ለክሙ፣

ለእናንተ ዕረፍት እንድትሆናችሁ ከስድስቱ ዕለታት ተለይታ የከበረች ናትና ቀዳሚት ሰንበትን ጠንቅቃችሁ አክብሩ፤

ወዘአርከሳ ሞተ ለይሙት ወኵሉ ዘይገብር ባቲ ግብረ ለትሠሮ ይእቲ ነፍስ እምሕዝባ፣

ቀዳሚትን የሻራት ሰው የሞት ሞት ይሙት፣ ሥራን የሚሠራባትም ሁሉ ሰውነቱ ከወገኖቿ ተለይታ ትጥፋ፣ /ሐተታ/ ዘአርከሳ ያለውን ዘይገብር ባቲ ብሎ ስለምን ደገመው ቢሉ የበዓል ስሪት፣ የጾም ግድፈት ስለቱ ብዙ ነውና፤

፲፭፣ ሰዱስ ዕለተ ተገበር ግብረከ ወሳብዕት ዕለት ሰንበት ዕረፍት ወቅድስቱ ለእግዚአብሔር፣

ስድስቱን ቀን ሥራህን ሥራ ሰባተኛዪቱን ቀን ግን ከሥራ የምታርፍባት ናትና እግዚአብሔርንም ለማገልገል ተለይታ የከበረች ናት፤

ወኵሉ ዘይገብር ግብረ በዕለተ ሰንበት ሞተ እመዊት ለይሙት፣

በቅዳሜ ቀን ሥራ የሚሠራ ሰው ሁሉ የሞት ሞት ይሙት፣ /በደንጊያ ተወግሮ በእሳት ተቃጥሎ ይሙት/

፲፮፣ ወይዕቀቡ ደቂቀ እስራኤል ሰንበተ ከመ ይግበሩ በትውልዶሙ፣

የእስራኤል ልጆች በልጅ ልጆቻቸው ሁሉ በዓል ያደርጓት ዘንድ ቀዳሚት ሰንበትን ጠንቅቀው ያክብሩ፤

፲፯፣ ሥርዓት ይእቲ ለዓለም ሊተ ወለደቂቀ እስራኤል ውእቱ ዘለዓለም፣

ይህች ለኔ የዘለዓለም ሥርዓት ናት ለእስራኤል ልጆችም ለዘለዓለም የገኘና የተገኘ ምልክት ናት፤ አንድም የዕረፍተ ነፍሳቸው ምልክት ናት፤



እስመ በሰዱስ ዕለት ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ ወበሳብዕት ዕለት ፈጸመ ወአዕረፈ፣

እግዚአብሔር በስድስቱ ዕለታት በሰማይና በምድር ያሉ ፍጥረታትን ፈጥሮ በሰባተኛዪቱ ቀን ፈጽሞ አርፏልና፣ ድካም ኑሮበት አረፈ ማለት አይደለም፣ መፍጠሩን ተወ ሲል ነው፤

፲፰፣ ወሶበ ፈጸመ ተናግሮ ምስሌሁ በደብረ ሲና ወሀቦ ለሙሴ ፪ተ ጽላተ ዘትእዛዝ፣

ጌታ በደብረ ሲና ከእርሱ ጋር ተነጋግሮ ከፈጸመ በኋላ ዐሥሩ ትእዛዛት /ቃላት/ የተጻፈባቸው ሁለቱን ጽላት ለሙሴ ሰጠው፤

ጽላት ዘዕብን ጽሑፋት በአጽባዕተ እግዚአብሔር፣

በእግዚአብሔር ጣት ዐሥሩ ቃላት የተጻፈባቸው እሊህ ሁለቱን ጽላትም ከዕንቁ /ከዕብነ በረድ/ የተቀረጹ ናቸው፣ /ሐተታ/ አሁን እግዚአብሔር ብርዕ ቀርጾ፣ ብራና ዳምጦ፣ ቀለም በጥብጦ የሚጽፍ ሁኖ አይደለም፣ በግብር አምላካዊ ተጽፈው ስለተገኙ እንዲህ አለ እንጂ።

# ምዕራፍ ፴ወ፪

፩፣ ወሶበ ርእዩ ሕዝብ ከመ ጐንደየ ሙሴ ወሪደ እምደብር ተንሥኡ ላዕለ አሮን ወይቤልዎ ግበር ለነ አማልክተ እለ የሐውሩ ቅድሜነ፣

ሕዝቡም ሙሴ ከደብረ ሲና መውረድን እንደ ዘገየ ባዩ ጊዜ በአሮን ላይ በነገር ተነሥተው በፊት በፊታችን የሚሔዱልን አማልክት ሥራልን አሉት፤

እስመ ዝኩ ብእሲ ሙሴ ዘአውፅአነ እምድረ ግብጽ ኢነአምር ምንተ ኮነ፣

ከግብጽ ምድር ያወጣን ያ ሙሴ የሚባል ሰው ምን እንደሆነ አናውቅምና ማለት ወደ ግብጽ ተመልሶ ሒዶ እንደሆነ በደብረ ሲና የኢያት እሳትም አቃጥላው እንደሆነ አናውቅምና፤

፪፣ ወይቤሎሙ አሮን ንሥኡ ሠርጐ ወርቅ ዘውስተ አዕዛነ አንስቲያክሙ ወአዋልዲክሙ ወአምጽኡ ኀቤየ፣

አሮንም በልጆቻችሁና በሚስቶቻችሁ ጆሮ ያለውን የወርቅ ጌጥ ተቀብላችሁ ወደ እኔ አምጡ አላቸው፣ /ሐተታ/ አሮን እንዲህ ማለቱ አይሆንም ያልኳቸው እንደሆነ እስራኤል

www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

ቂጡአን ናቸውና በድንጋይ ወግረው በእሳት አቃጥለው ይገድሉኛል፣ ይሁን ብላቸ ውም ፈጣሪዬ ይፈርድብኛል፣ የወርቅ ጌጣቸውን አምጡ ያልኳቸው እንደሆነ ግን እስራ ኤል ገንዘብ ወዳጆች ናቸው፣ ነገ ሣልስት ሲሉ ወንድሜ ሙሴ ይመጣልኛል ከነገር እድናለሁ ብሎ ነው፤

፫፣ ወነሥኡ ኵሉ ሕዝብ ሠርጐ ወርቅ ዘውስተ እዕዛኒ አንስቲያሆሙ ወአምጽኡ ኀበ አሮን፣

ሕዝቡም በሚስቶቻቸው ጆሮ ያለውን የወርቅ ጌጥ ወስደው ለአሮን ሰጡት፣ /ሐተታ/ ቀድሞ ገንዘብ ያስወድዳቸው የነበረ ሰይጣን በዚያን ቀን አስ ጠልቶአቸው እንዋል እንደር ሳይሉ ዕለቱን አምጥተው ሰጥ ተውታል፤

፬፣ ወተመጠወ እምእደዊሆሙ ወመሰሎ በአምሳል ወገብሮ ላሕመ ዘስብከ ወይቤሎሙ እሉ እሙንቱ አማልክቲከ እስራኤል ዘአውዕኡከ እምድረ ግብጽ፣

አሮንም ከእጃቸው ተቀብሎ ወስዶ በላም አምሳል ሠርቶ እስራኤል ከግብጽ ምድር ያወ ጧችሁ አማልክቶቻችሁ እኒህ ናቸው አላቸው፣ /ሐተታ/ እሳት ቢበላው ምን ልበል ብሎ ምክንያት ለመስጠት ነበር፣ ጕድጓድ አስቈፍሮ እሳት አስነድዶ ከዚያ ላይ ቢጥለው፣ አንዳንድ ቀንዳቸው የወርቅ፣ አንዳንድ ቀንዳቸው የብር፣ ጅራታቸው የሐር ጉፍላ የሆኑ ሁለት የጥጃ ምስሎች ወጥተው ቆመዋል፣ ይህስ ምትሐት ይመስላል ብሎ ተድበልብሎ ቢወጣ መሆኑስ ካልቀረ በምር ደስ ይበላቸው ብሎ ቀጥቅጦ በላም አምሳል አድርጎ ሠርቶላ ቸዋል፤

፭፣ ወሶበ ርእየ አሮን ነደቀ ምሥዋዓ አንጻሮ ወአየደ እንዘ ይብል በዓለ እግዚእ ጌሠመ፣

አሮንም እስራኤል ጣዖቱን ወድደው እንደ ተቀበሉት ባየ ጊዜ በጣዖቱ ፊት ለፊት መሠዊ ያውን ጸፈጸፈ፣ ነገ የጣዖቱ በዓል ነው ብሎ አዋጅ አስነገረ፣

፮፣ ወጌሠ አሮን በሳኒታ ወአዕረገ መሥዋዕተ ወአብአ ቍርባነ ዘመሥ ዋዕተ ፍርቃን፣

አሮንም በማግስቱ ማልዶ ሒዶ ለጣዖቱ መሥዋዕት ሠዋ፣ ዘመሥዋዕተ ፍርቃን መሥዋ ዕተ መድኃኒት ሲል ነው፣ ምክንያተ ድኅነት የሚሆነውን መሥዋዕት ምክንያተ ሞት አድርጎ አቀረበው፤ አንድም የመድኃኒት የጌታን መሥዋ ዕት ለጣዖት አቀረበው፤



ወነበሩ ሕዝብ ይብልዑ ወይስተዩ ወተንሥኡ ይዝፍኑ ወይትዋነዩ፣

ሕዝቡም ለጣዖቱ መሥዋዕት ሠውተው ሊበሉ ሊጠጡ ተቀ መጡ፣ በልተው ጠጥተው ከጠ ገቡ በኋላም ይዘፍኑ ይጫወቱ ዘንድ ተነሡ፤

፯፣ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ሑር ወእፍጥን ወሪደ እምዝየ እስመ አበሱ ሕዝብከ ዘአውፃእከ እምድረ ግብጽ፣

ያንጊዜ እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፣ ከግብጽ ያወጣሃቸው ወገኖችህ እስራኤል ፈጽመው በድለዋ ልና ከዚህ ከደብረ ሲና ፈጥነህ ውረድ አለው፣ /ሐተታ/ ጠብ በዚህ ጊዜ ተጀመረ፣ ሕዝብየ ይላቸው የነበረ ሕዝብከ አለው፣ አባት ልጁን በተጣላው ጊዜ እናቱን ያ ልጅሽ እንዲህ አደረገኝ እንዲላት፤

፰፣ ወወዕኡ እምፍኖት ዘአዘዝ ክዎሙ ወገብሩ ላሕመ ወሰገዱ ወሦዑ ሎቱ፣

ጠብቁ ብዬ ካዘዝኳቸው ትእዛዝ ወጥተው በላም አምሳል ጣዖት አቁመው ሰግደውለታልና፣ መሥ ዋዕትም ሠውተውለታልና፣ ወይቤሉ እሉ እሙንቱ አማልክቲከ እስራኤል ዘአውዕኡከ እምድረ ግብጽ፣

እስራኤል ከግብጽ ያወጡህ አማልክቶችህ እኒህ ናቸው ብለዋልና፣ /ሐተታ/ ለማቃለል አሮንን ብቻ ይቤሉ አለው፤ አንድም ወገኖቹ ሌዋውያንን ጨምሮ ይቤሉ አለ፤

፱፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ርኢኩ ዘንተ ሕዝበ ወናሁ ዝንቱ ሕዝብ ግዙፈ ክሳድ፣

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፣ ይህን ሕዝብ ክሳደ ልቡናው የጸና ሆኖ አየሁት፤

፲፣ ወይእዜኒ ኅድገኒ ዕጥስዮሙ በመዓትየ ወእሠይመከ ላዕለ ሕዝብ ክቡድ ወዐቢይ፣

አሁንም ፈርጄ ላጥፋቸው ተወኝ አትማልደኝ፣ አንተን ግን ከዚህ በሚበልጥና በሚበዛ ወገን ላይ እሾምሃለሁ አለው፤

፲፩፣ ወሰአለ ሙሴ ቅድመ አምላኩ ወይቤ ለምንት እግዚእ መዓተ ትትመዓዕ ላዕለ ሕዝብከ ዘአውፃእከ እምድረ ግብጽ በኃይል ጽኑዕ ወበመዝራዕት ልዑል ወዓቢይ፣

ሙሴም በታላቅ ተአምራትና ጽኑ ገናና በሆነ ሥልጣን ከግብጽ ያወጣሃቸው ወገኖችህ እስራኤልን ላጥፋቸው እንደ ምን ትላለህ? አቤቱ መዓትህን

www.ethiopianorthodox.org

ወደ ምሕረት ቁጣህን ወደ ትዕግሥት መልስ ብሎ ፈጣሪ ውን ለመነ፤

፲፪፣ ከመ ኢይበሉ ግብጽ በእኩይ አውፅኦሙ ከመ ይቅትሎሙ በውስተ አድባር ወከመ ያጥፍኦሙ እምድር አቀኁርር መዓተከ ዘተማዕከ ወመሐሬ ኩን ላዕለ እከዮሙ ለሕዝብከ፣

ከሞት የተረፉ ግብጻውያን ለካ የእኛን ወገኞች በባሕር አስጥሞ እነሱን ያወጣቸው በምድረ በዳ ሊፈጃቸው ከዚህም ዓለም ጨርሶ ሊያጠፋቸው ነው እንጂ ለበጐ አይደለም እንዳይሉ፣ ፈርደህ የምታመጣው መቅሠፍትህን አርቅላቸው፣ የበደሉህንም በደል ይቅር በላቸው፣ /ሐተታ/ እከይ አለው ኃጢአቱን በክፋታቸው ስለ ሠሩት ነው፤ አንድም ኃጢአቱን ከሠሩት በኋላ በነሱ ክፉ መከራ የሚያመጣ ባቸው ስለሆነ በግብሩ እከይ አለው፤

፲፫፣ ተዘከር አብርሃምሃ ወይስሐቅሃ ወያዕቆብሃ አግብርቲከ ዘመሐልከ ሎሙ በርእስከ፣

ይህንስ ትተህ «አማንየ በርእስየ ሕያው አነ» ብለህ የማልክላቸው፤

ወትቤሎሙ ብዙኃ አበዝኁ ዘርአክሙ ከመ ከዋክብተ ሰማይ ብዙኀ ወኵሎ ዘንተ እሁብ ለዘርእክሙ ወይመልክዋ ለዓለም፣

ልጆቻችሁንም እንደ ሰማይ ኮከብ እጅግ አበዛቸዋለሁ፣ ይህንንም ሁሉ ለልጆቻችሁ እሰጣቸዋለሁ፣ እነሱም ከነዓንን ለዘለዓለም ወርሰዋት ይኖራሉ /ይገዙዋታል/ ብለህ ተስፋ የነገርካቸው ባለሟሎችህ አብርሃም ይስሐቅ ያዕቆብን አስበህ ይቅር በላቸው ብሎ ለመነ፤

፲፬፣ ወሠረየ እግዚአብሔር በእንተ እኪት ዘይቤ ይገብር ላዕለ ሕዝብ፣

እግዚአብሔርም የሙሴን ልመና ሰምቶ በሕዝቡ ላይ ያደርገው ዘንድ የተናገረውን ክፉ ነገር ይቅር አለ፣ /ሐተታ/ አሁን ጌታ እስራኤልን ሲያጠፋ ሙሴን አማክሮ የሚያጠፋ ሁኖ አይደለም፣ ሙሴም ጌታን ተከራክሮ የሚያድን ሁኖ አደለም፣ ለጌታ ርኅራኄ ይቀር ማለት ፈቃዱ እንደ ሆነ፣ ለሙሴም ማማለድ የቀሃት ፈቃዱ እንደ ሆነ ለማጠየቅ እንዲህ አለ እንጂ፤



፲፭፣ ወተመይጠ ሙሴ ወወረደ እምደብር ወክልኤቱ ጽላት ዘትእዛዝ ውስተ እደዊሁ ጽላት ዘዕብን ወጽሑፋት እንተ ክልኤቱ ገበዋቲሆን እንተ ለፌኒ ወእንተ ለፌኒ፣

ሙሴም ዐሥሩ ቃላት የተጻፉ ባቸው ሁለቱን ጽላት ይዞ ከደብረ ሲና ተመልሶ እስራኤል ወደ አሉበት ሔደ፣ እኒሁም በሁለት ወገን ዐሥሩ ቃላት የተጻፉባቸው ሁለቱ ጽላት የዕንቊ ናቸው፣ /ሐተታ/ ዐሥሩን በአንዱ ጽሌ ጽፎ ሰጥቶታል፣ ሃያ ሕግ ማለት አይደለም፣ ለአንድ መነኮሴ ሁለት ዳዊት፣ ሁለት ወንጌል የሐንስ አለው እንደ ማለት ነው፤ አንድም አምስቱን በአንዱ ጽሌ አምስቱን በአንድ ጽሌ ጽፏቸዋል፣ እንተ ክልኤ ሆን ገበዋቲሆን ማለቱ ግን በአንድ ወገን የተጻፈው በአንድ ወገን የሚታይ ስለሆነ ነው፣ እንደ ጠራ ብራና ባዚቃው እንደ ረገፈ መስታዋት፤

፲፮፣ ወግብረቶን ግብረተ እግዚእ ወጽሕፈቶን ጽሕፈተ እግዚአብሔር ውእቱ ወግሉፋት ላዕለ ጽላት፣

ወግብረቶን ለጽላት ጽሕፈቶን ለቃላት ነው፣ ቅርፃቸውም ጽሕፈታቸውም ግብር አምላካዊ ነው፣ ቃላቱ በጽላቱ ላይ ተጽፈው በሁለት ወገን ይታያሉ፤

፲፯፣ ወሰሚዖ ሆሴዕ ቃለ ሕዝብ እንዘ ይጸርሑ ይቤሎ ለሙሴ ድምፀ ጸባዒት ውስተ ትዕይንት፣

ኢያሱም የሕዝቡን ጩኸት ሰምቶ በሰፈር የዓርበኞችን ድምፅ እሰማለሁ ምን ይሆን? ብሎ ሙሴን ጠየቀው፤

፲፰፣ ወይቤሎ ሙሴ ኢኮነ ዝንቱ ድምፅ ዘመላእክት እለ ይትኄየሉ ወኢኮነ ድምፀ መላእክት ዘዐብዕ አላ ድምፀ መልእክቱ ለወይን እሰምዕ አንሰ፣

ሙሴም ኢያሱን የዓርበኞች ድምፅ አይደለም፣ በሰልፍ የሚዋጉ የአለቆች ድምፅም አይደለም፣ ጉሽ ጠጅ ጠጥተው የሚጫወቱ የአለቆችን ድምፅ እሰማለሁ እንጂ፣ አንድም ድምፀ መልእክቱ ድምፀ ፋሕሱ ለወይን ይላል፣ ጉሽ ጠጅ እየጠጡ «ስምዓኒ በዓል ስምዓኒ ዳኅን» እያሉ ለጣዖቱ ይጮሃሉ እንጂ፣ የዓርበኛ ድምፅ አይደለም አለው፤

፲፱፣ ወሶበ ቀርበ ሙሴ ኀበ ትዕይንት ርእዮ ለውእቱ ላሕም ወተውኔት ወተምዐ ሙሴ ወገደፎን እምውስተ እደዊሁ ለእልክቱ ፪ቱ ጽላት ወቀጥቀጦን በታሕተ ደብር፣

ሙሴም ወደ ሰፈሩ በደረሰ ጊዜ በላም አምሳል ያቆሙትን ጣዖት፣ ለጣዖቱ የሚዘፍኑትን

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ዘፈን፣ አይቶ ሙሴ ተበሳጭቶ በተራራው ሥር ባለ በእስራኤል ሠፈር ሲደርስ ሁለቱን ጽላት ከእጁ ወርውሮ ጥሎ ሰበራቸው፣ /ሐተታ/ እግዚአብሔር በሚመለክበት ቦታ ጣዖት ሲያመልኩ ቢያገኛቸው ደንግጦ ሁለቱ ጽላት ከእጁ ወድቀው ተሰበሩ፣ ዛሬ ከቄስ እጅ መስቀል ጽዋ ወድቆ እንዲሰበር፤ አንድም አንዱን ጣዖት በአንዱ ጽሌ፣ አንዱን ጣዖት በአንዱ ጽሌ መታው፣ ጽላቱም ጣዖቱም ተሰበረ፤

፳፣ ወነሥአ ለውእቱ ላሕም ዘገብሩ ወአውዓዮ በእሳት ወሐረጾ ወአድቀቆ ወዘረዎ ውስተ ማይ ወአስተዮሙ ኪያሁ ለደቂቀ እስራኤል፣

በላም አምሳል ያቆሙትንም ጣዖት ወስዶ በእሳት አቃጥሎ አልሞ ፈጭቶ በውሃ በጥብጦ ያን ለእስራኤል ልጆች አጠጣቸው፣ /ሐተታ/ እስራኤላውያንም ያንን በጠጡ ጊዜ ፍቅረ ጣዖት ያለበት ከግንባሩ ከከንፈሩ እንደ ወርቅ ቀለም የመሰለ ለምጽ ተቀርያበታል፣ በዚህ ለይቶ አውጥቶታል፤

፳፩፣ ወይቤሎ ሙሴ ለአሮን ምንተ ረሰይከ ዘንተ ሕዝበ ከመ ታምጽእ ላዕሌሆሙ ኃጢአተ ዐቢየ፣

ሙሴም አሮንን ጽኑዕ ኃጢአት ታመጣባቸው ዘንድ በእስራኤል ላይ እንዲህ ያለ ሥራ ለምን ሠራህ? አለው፤

፳፪፣ ወይቤሎ አሮን ለሙሴ ኢትትመዓዕ እግዚእየ ላዕሌየ ለሊከ ተአምር ግዕዞሙ ለእሉ ሕዝብ፣

አሮንም ሙሴን የእስራኤልን ነገር አንተ ታውቃለህና አቤቱ አትፍረድብኝ አለው፤

፳፫፣ ወሶበ ይቤሉኒ ግበር ለነ አማልክተ እለ የሐውሩ ቅድሜነ እስመ ዝንቱ ሙሴ ዘአውፅአነ እምድረ ግብጽ ኢነአምር ምንተ ኮነ፣

ከግብጽ ያወጣን ሙሴ ምን እንደሆነ አናውቅምና በፊታችን የሚሔዱ አማልክትን ሥራልን ባሉኝ ጊዜ አይሆንም ብላቸው በደንጊያ ወግረው በእሳት አቃጥለው ይገድሉኛል ብዬ፤

፳፬፣ ወእቤሎሙ ዘቦ እምኔክሙ ወርቅ አምጽኡ፣ ወአምጽኡ ወወሀቡኒ ወወረውክዎ ውስተ እሳት ወፅአ ዝንቱ ላሕም፤

እስራኤል ገንዘብ ወዳጆች ናቸውና ገንዘባቸውን ሲሉ ይተዉ



ኛል መስሎኝ፣ የወርቅ የብር ጌጣችሁን አምጡልኝ ብላቸው ያደረባቸው ሰይጣን ነገ ሣልስት ሳያሰኛቸው ቀርቶ አምጥተው ሰጡኝ፣ ጠፍቶ ይቀራል ብዬ ከእሳት ብጥለው ይህ የላም ምስል ጣዖት ወጥቶ ቆመ አለው፣

፳፭፣ ወሶበ ርእየ ሙሴ ከመ ዓለዉ ሕዝብ እስመ ዓዕለዎሙ አሮን ወኮኑ ሰሐቀ ለጸላእቶሙ፣

ሙሴም አምልኮተ እግዚአብሔርን ትተው ፈቃዳቸውን ለመፈጸም አሮን ችላ ስላላቸው ሕዝቡ እግዚአብሔርን በድለው የጠላቶቻቸው መዘባበቻ እንደሆኑ አይቶ /ባየጊዜ/፤

፳፮፣ ቆመ ቅድመ ትዕይንት ወይቤ ዘኃረዮ እግዚአብሔር ይምጻእ ኀቤየ ወተጋብኡ ኀቤሁ ኵሉ ደቂቀ ሌዊ፣

በእስራኤል ሰፈር ፊት ለፊት ቆሞ የእግዚአብሔር ወገን የሆነ ሁሉ ወደኔ ይምጣ ብሎ በተናገረ ጊዜ የሌዊ ልጆች የሆኑት ሁሉ ተሰብስበው ወደ እርሱ መጡ፤

፳፯፣ ወይቤሎሙ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ፩ዱ ፩ዱ ይዐር ሰይፎ ወሑሩ ወዕግቱ እምአንቀጽ እስከ አንቀጸ ትዕይንት ወ፩ዱ ፩ዱ ይቅትል እኅዋሁ ወ፩ዱ ፩ዱ ይቅትል ካልኦ ወ፩ዱ ፩ዱ ይቅትል ዘቅሩቡ፣

የእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ አንዱም አንዱም ሰይፉን ታጥቆ ሒዳችሁ ከፊት በር እስከ ኋላ በር ሰልፉን ክበቡ፤ አንዱም አንዱም ወንድሙን ይግደል፣ ባልንጀራ ባልንጀራውን፣ ዘመድ ዘመዱን ይግደል ብሏል እግዚአብሔር አላቸው፤

፳፰፣ ወገብሩ ደቂቀ ሌዊ በከመ ይቤሎሙ ሙሴ ወወድቀ እምሕዝብ ይእተ አሚረ ፴፻ ብእሲ፣

የሌዊ ልጆችም ሙሴ እንዳዘዛቸው አደረጉ አለ፣ ወንድም ወንድሙን፣ ባልንጀራ ባልንጀራውን፣ ዘመድ ዘመዱን ገደለ፣ ያንጊዜም ከእስራኤል ሦስት ሺህ ሰው ሞተ፣

፳፱፣ ወይቤሎሙ ሙሴ አንፈስክምዎ የዮም ለእግዚአብሔር በእደዊክሙ ፩ዱ ፩ዱ በወልዱ ወበእኁሁ ከመ ትትወሀብ ለክሙ በረከት፣

ሙሴም ይህንን አይቶ አባት ልጁን፣ ወንድም ወንድሙን፣ በመግደሉ በቃላችሁ በመከራችሁት ምክር በእጃችሁ በሠራችሁት ሥራ አሁን እግዚአብሔርን ደስ አሰኛችሁት፣ ለእናንተ በረከት ትሰጥ ዘንድ አላቸው፤

www.ethiopianorthodox.org

## ጉባኤ

፴፡ ወኮነ በሳኒታ ይቤሎሙ ሙሴ ለሕዝብ አንትሙ ጌገይክሙ ጌጋየ ዐቢየ ወይእዜኒ አዓርግ ኀበ እግዚአብሔር ከመ አስተሥሪ ለክሙ ኃጢአተክሙ፤

ይህ በሆነ በበነጋው ሙሴ ሕዝቡን ሰብስቦ ጽኑ በደል በድላችኋልና አሁንም ኃጢአታችሁን ይቅር ይላችሁ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ለማመልከት ወደ ደብረ ሲና እወጣለሁ አላቸው፤

፴፩፡ ወገብአ ሙሴ ኀበ እግዚአብሔር ወይቤ እስእለከ እግዚአናሁ አበሱ እሉ ሕዝብ አበሳ ዐቢየ ወገብሩ ሎሙ አማልክተ ዘወርቅ፤

ሙሴም እግዚአብሔር ወደ ሚገለጽባት ወደ ደብረ ሲና ተመልሶ አቤቱ ጽኑ በደል በድለዋልና በላም አምሳል የተሠራ የወርቅ ጣዖትም አቁመዋልና ይቅር ትላቸው ዘንድ እለምንሃለሁ አለ፤

፴፪፡ ወይእዜኒ እመ ተኃድግ ሎሙ ዘንተ ኃጢአተ ኅድግ ወእመ አኮሰ ደምስስ ኪያየ እመጽሐፍከ ዘጸሐፍከኒ፤

አሁንም ኃጢአታቸውን ይቅር የምትላቸው እንደ ሆነ ይቅር በላቸው፤ ይቅር የማትላቸው ከሆነ ግን ከመጽሐፍህ እኔን ፋቀኝ፤ ማለት እኔን አጥፋኝ /ከልቡናህ አውጣኝ/ አለ፤

፴፫፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ለዘንቱ ሕዝብ ዘአበሰ በቅድሜየ እደመስሶ እመጽሐፍየ፤

እግዚአብሔርም ሙሴ እኔን አጥፋኝ ቢለው ይስማ ይልማ ብለው የበደሉኝን ሕዝቡን አጠፋለሁ እንጂ አንተን ምን ባልክ አጠፋሃለሁ? አለው፤

፴፬፡ ወይእዜኒ ሑር ወምርሆሙ ለሕዝብ ውስተ መካን ዘእቤለከ፤

ይልቁንስ እኔ ወደማዝህ ቦታ ይዘኻቸው ሒድ፤

ወናሁ መልአኪየ የሐውር ቅድመ ገጽከ ወአመ ዕለተ እዋኅዮሙ አገብእ ላዕሌሆሙ ኃጢአቶሙ፤

እነሆ መልእክተኛዬ ኢየሱም በፊት በፊትህ ይሔዳል፤ አንድም ሊረዳህ የማዝዝልህ መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል በፊትህ እየሔደ ይመራሃል፤ በመዓት በጐበኘኋቸውም ጊዜ የኃጢአታቸውን ፍዳ አመጣባቸዋለሁ፤

፴፭፡ ወቀተለ እግዚአብሔር እም ሕዝብ በእንተ ዘገብሩ ላሕመ ዘገብረ ሎሙ አሮን፤

አሮን ሠርቶ የሰጣቸውን የላም ምስል ስላመለኩ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ወገን ብዙ ሰው አጠፋ፤ /ሐተታ/ ባለፈው «ወወድቀ እምሕዝብ ፴፻ ብእሲ» ብሎ ነበርና እነዚያን ሲያይ ቀተለ አለ፤ አንድም «አመ ዕለተ እዋኅዮሙ አገብእ ላዕሌሆሙ ኃጢአቶሙ» ብሎ ነበርና ገና ወደፊት የሚያመጣውን ድርስ አድርጎ ቀተለ አለ።

## ምዕራፍ ፴ወ፫

፩፡ ወይቤ እግዚአብሔር ለሙሴ ሑር ወዕርግ እምዝየ አንተ ወሕዝብከ ዘአውፃእከ እምድረ ግብጽ፤

እግዚአብሔርም ሙሴን ከግብፅ ያወጣሃቸው ወገኖችህ እስራኤልን ይዘህ ከዚህ ተነሥተህ ውጣ፤

ውስተ ምድር ዘመሐልኩ ለአብርሃም ወለይስሐቅ ወለያዕቆብ እንዘ እብል ለዘርእክሙ እሁባ፤

ወዴት ነው የምወጣ ትለኝ እንደሆነ ለልጆቻችሁ እሰጣታለሁ ብዬ ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ ወደ ማልኩላቸው ምድር ወደ ከነዓን ውጣ፤

፪፡ ወእፌንዎ ለመልአኪየ ቅድሜከ

ከዚህ ቀድሞ እየመራ ያወጣህንም መልአክ በፊት በፊትህ እንዲሄድ አዝዝልሃለሁ፤

ወያወፅኦሙ ለከናኔዎን ወለአሞሬዎን ወለኬጤዎን ወለፌርዜዎን ወለጌርጌሴዎን ወለኤዌዎን ወለኢያቡሴዎን፤

እርሱም እነዚህን ሰባቱን ነገሥተ ከነዓን አውጥቶ ያጠፋቸዋል፤

፫፡ ወያበውአከ ውስተ ምድር እንተ ትውኅዝ /ታውኅዝ/ ሐሊበ ወመዓረ፤

አንተን ግን ተድላ ደስታ ወዳለባት አገር ወደ ከነዓን ያገባሃል፤

ወኢየዓርግ ምስሌከ በእንተ ሕዝብከ እለ ያገዝፉ ክሳዶሙ ከመ ኢያኅልቆሙ በፍኖት፤

ክሣደ ልቡናቸውን ስለሚያጸኑ ስለ ወገኖችህ በጉዳና ጨርሼ እንዳላጠፋቸው እኔ ከአንተ ጋራ አብሬህ ተገልጬ አልሔድም፤ /ሐተታ/ ፍጹማን የሆኑ እንደሆነ ተገልጦ ያድርባቸዋል፤ ኃጢአት ሲሠሩም በመከራ ይገሥጻቸዋል፤ ወጣንያን የሆኑ እንደሆነ ግን ተገልጦ አያድርባቸውም፤ ኃጢአት ሲሠሩም ይታገሣቸዋልና፤

፬፡ ወሰበ ሰምዐ ሕዝብ ዘንተ ነገረ እኩየ ለሀዉ ላሃ ዐቢየ፤

ለሕዝቡም ሙሴ ወጥቶ ነገራቸው ይህን ክፉ ነገር በሰሙ ጊዜ ፊጣሪያቸን እንዲህ አድ



www.ethiopianorthodox.org

ርገን አሳዝነነዋልን ብለው ጽኑ ኃዘን አዘኑ፤ አንድም «ከመ ኢያኅልቆሙ በፍኖት ያለውን ቃል በሰሙ ጊዜ በኃጢአታችን ፈርዶ በጐዳና ሊያጠፉን ነው? ብለው ጽኑ ልቅሶ አለቀሱ፤

፭፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ በሎሙ ለደቂቀ እስራኤል አንተ ሙሰ ሕዝብ ዘያገዝፍ ክሣዶ አንትሙ ዑቁ ካልዕተ መቅሠፍተ ኢያምጽእ ላዕሌክሙ ወአጠፍአክሙ፣

እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው፣ የእስራኤልን ልጆች እናንተ ክሣደ ልቡናች ሁን ያጸናችሁ ወገኖች ናች ሁና ሁለተኛ ሌላ መቅሠፍት አምጥቼ እንዳላጠፋችሁ፣ ዳግመኛ እንዳትበድሉ ዕወቁ፣ አንሰማም ብትሉ ግን አጠፋ ችኋለሁ፤ አንድም ከዚህ ቀድሞ ባጠፋኋችሁ መቅሠፍት አጠፋችኋለሁ እንጂ በሌላ መቅሠፍት እንዳላጠፋችሁ ዕወቁ አለ፣ ከዚህ ቀደም በጦር በሰይፍ እንዳጠፋኋችሁ አሁ ንም በዚያው አጠፋችኋለሁ ሲል እንዲህ አለ፤

ወይእዜኒ አሰስሉ አልባሰ ክብር ክሙ ወሠርጐክሙ ወአርእየክሙ ዘእሬስየክሙ፣

አሁንም የማደርግባችሁን ነገር አሳያችኋለሁና ለጣዖቱ በዓል ያደረጋችሁበትን ጌጥ ጣዖቱን ያከበራችሁበትን ልብስ ወዲያ ጣሉ፣

፮፣ ወአሰሰሉ ደቂቀ እስራኤል ሠርጓቲሆሙ ወአልባሲሆሙ በደብረ ኰሬብ፣

እስራኤልም በደብረ ኰሬብ ሳሉ ለጣዖቱ በዓል ያደረጉ በትን ጌጣቸውን ልብሳቸውን አውልቀው ጣሉ፤

፯፣ ወነሥአ ሙሴ ሐይመቶ ወተከለ አፍኣ ርኁቀ እምትዕይንት ወተሰምየት ደብተራ ዘመርጡል፣

ሙሴም ድንኳኑን ከከተማ በአፍኣ /በውጭ/ አርቆ ተከለ፣ የመገናኛ ድንኳንም ተባለች፣

ወኮነ ኵሉ ዘየኃሥሥ ለእግዚአብ ሔር የሐውር ኀበ ይእቲ ደብተራ ዘአፍኣ እምትዕይንት፣

ቃለ እግዚአብሔር ሊጠይቅ የሚሻ ሰውም ሁሉ ድንኳኒቱ ወደ ተተከለችበት ቦታ ይሄድ ነበር፤

፰፣ ወሶበ የሐውር ሙሴ ይባእ ውስተ ይእቲ ደብተራ ዘአፍኣ እምትዕይንት ይቀውም ኵሉ ሕዝብ ወይኔጽር ፩ዱ ፩ዱ ኀበ ኆኅተ ደብተራሁ ወይሬእይዎ ለሙሴ ሶበ የሐውር እስከ ይበውእ ውስተ ደብተራ፣

ሙሴም ወደ ድንኳኑ ለመግባት በሔደ ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ በውጭ



ቆሞ ሙሴ ሒዶ ከድንኳኑ እስኪ ገባ ድረስ አንዱም አንዱም በድንኳኑ ደጃፍ ሁኖ ይመለ ከት ነበር፤ አንድም ሙሴን በድንኳኑ ደጃፍ ሆኖ አንዱም አንዱም ይመለከተው ነበር፤

፱፣ ወእምከመ ቦአ ሙሴ ይወርድ ዐምድ ዘደመና እንዘ ይቀውም ኀበ ኆኅተ ደብተራ ወይትናገሮ እግዚአ ብሔር ለሙሴ፣

ሙሴ ከድንኳኑ ከገባ በኋላ ዐምደ ደመና ወርዶ ከድንኳኑ ደጃፍ ተተክሎ ይታይ ነበር፣ እግዚአብሔርም ሙሴን በደመና ይናገረው ነበር፤

፲፣ ወይሬእዩ ኵሉ ሕዝብ ለውእቱ ዓምድ ዘደመና እንዘ ይቀውም ኀበ ኆኅተ ደብተራ ወይትናገር እግዚ አብሔር ምስለ ሙሴ ወቀዊሞሙ ኵሉ ሕዝብ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ሆሙ ይሰግዱ፣

የደመናውንም ዐምድ በድንኳኑ ደጃፍ ተተክሎ ሕዝቡ ሁሉ ያየው ነበረ፣ እግዚአብሔርም ከሙሴ ጋር ሲነጋገር ሕዝቡ ሁሉ በየድንኳናቸው ደጃፍ ቁመው ይሰግዱ ነበር፤

፲፩፣ ወይትናገር እግዚአብሔር ገጸ በገጽ ከመ ዘይትናገር ብእሲ ምስለ ዓርኩ ወይገብእ ውስተ ትዕይንት፣

ሰው ከወዳጁ ጋር እንዲነጋገር እግዚአብሔር ሙሴን ተነጋግ ሮት ሙሴ ወደ ሠፈሩ ይመለስ ነበር፤

ወጽሙዱሰ ሆሤዕ ወልደ ነዌ ወሬዛ ውእቱ ወኢይወፅእ እምትዕይንት፣

አገልጋዩ /ደቀ መዝሙሩ/ የነዌ ልጅ ኢያሱ ግን ኃያል ጐልማሳ ነበርና ከሠፈር ሳይለይ ይጠ ብቅ ነበር፣ ከኔ ጋር የምትልከ ውን /የምትሰደውን/ አልነገ ርከኝም የሚል ነውና እንደ አርእስት አነሣው፤

፲፪፣ ወይቤሎ ሙሴ ለእግዚአብሔር ናሁ ትቤለኒ አንተ ስዶ ለዝንቱ ሕዝብ ወባሕቱ ኢነገርከኒ ዘትፌኑ ምስሌየ ወለሊከ ትቤለኒ ኪያከ አእመርኩ እምኵሉ ወረከብከ ሞገሰ በኀቤየ፣

ሙሴም እግዚአብሔርን እንዲህ አለው፣ ይህንን ወገን ይዘህ ሒድ አልከኝ፣ ነገር ግን ከእኔ ጋር የምትልከውን ሰው ዕገሌ ነው ብለህ አልነገርከ ኝም፣ ከሁሉም ይልቅ አንተን መርጬ በእኔ ዘንድ ባለሟል ነትን አግኝተሃል ብለኸኛል፤

፲፫፣ ወለእመሰ ረከብኩ ሞገሰ በኀቤከ አስተርእየኒ ገሐደ ሊተ ወአእምር ወእርአይከ ከመ ይኩነኒ ረኪበ ሞገስ በቅድሜከ ዮም፣

በአንተ ዘንድ ባለሟልነትን ማግኘቴ እውነት ከሆነስ ፊት ለፊት ተገልጸህልኝ ልይህና በአንተ ዘንድ ባለሟልነትን ማግኘቴን ልወቀው፤

www.ethiopianorthodox.org

ወከመ አእምር ከመ ሕዝብከ ውእቱ ዝንቱ ሕዝብ ዐቢይ፤

ይህ ታላቅ ወገን እስራኤልም ያንተ ወገን እንደ ሆነ አውቅ ዘንድ እውዳለሁ፤ አንድም በፊትህስ ባልሟልነትን ካገኘሁ በባሕርይህ ላይህ እወዳለሁ፤

፲፬፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር አነ አሐውር ቅድሜከ ወአዐርፈከ፤

እግዚአብሔርም ሙሴን እኔ በፊትህ እሔዳለሁ፤ አንተንም በዋሻ አሳርፍሃለሁ አለው፤ ይህንን ከዚህ እንደአርእስት ተናግሮታል፤ ወደፊት ያመጣዋል፤

፲፭፤ ወይቤሎ ሙሴ ለእግዚአብሔር እመ አንተ ለሊከ ኢተሐውር ምስሌነ ወኢታውፅአነ እምዝየ፤

ሙሴም እግዚአብሔርን እንዲህ አለው፤ አሁን እታይሃለሁ እንዳልከኝ ከእኛ ጋራ በፊት በፊታችን እየሄድክ ካላወጣኸን፤

፲፮፤ በምንት ይትዓወቅ ከመ አማን ረከብኩ ሞገሰ በቅድሜከ አነኒ ወሕዝብከኒ ዘእንበለ ሶበ ሖርከ ምስሌነ፤

ወገኖችህ እስራኤልና እኔ በአንተ ዘንድ ባለሟልነትን ማግኘታችን የሚታወቀው አብረኸን ብትሔድ ነው እንጂ፤

ወንከብር አነኒ ወሕዝብከኒ በኀበ ኵሉ አሕዛብ ዘሀሎ ውስተ ኵሉ ምድር፤

እንዲህ ቢሆን ግን፤ ወገኖችህ እስራኤልም እኔም በአራቱ መዓዝን ባሉ አሕዛብ ዘንድ እንከብራለን ማለት ይፈሩናል ያከብሩናል፤

፲፯፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ዘንተኒ ነገረ ዘትቤለኒ እገብር ለከ ወረከብከ ሞገሰ በቅድሜየ ወአአምረከ እምኵሉ፤

እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው፤ ከሁሉም ይልቅ አንተን መርጬ ባለሟል አድርጌሃለሁና ይህን ያልከኝንም ነገር ሁሉ አደርግልሃለሁ፤

፲፰፤ ወይቤሎ ሙሴ ለእግዚአብሔር አርእየኒ ስብሐቲከ፤

ሙሴም እግዚአብሔርን ባለሟልህስ ካደረግኸኝ ጌትነትህን /ባሕርይህን/ ግለጽልኝ አለው፤

፲፱፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ አነ አኃልፍ ቅድሜከ በስብሐትየ ወእጼውዕ ስመ እግዚእናየ በቅድሜከ፤

እግዚአብሔርም ሙሴን እኔ «መሐሪ ወመስተሣህል አነ» እያልኩ የጌትነቴን ስም እየጠራሁ በብርሃን ሠረገላ ሁኜ በፊትህ ሳልፍ ታየኛለህ፤



ወእምሕሮ ለዘመሐርክዎ ወእሣሃሎ ለዘተሣሃልክዎ፤

የምምረውን እምረዋለሁ፤ ይቅር የምለውንም ይቅር እለዋለሁ፤ አንድም እንድምረው ሁኖ ያገኘሁትን እምረዋለሁ፤ እንድጣላው ሁኖ ያገኘሁትን እጣላዋለሁ አለው፤ «እስመ ይኄይስ እምሐይው ሣህልከ» እንዲል፤

፳፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ኢትክል ርእዮተ ገጽየሰ እስመ አልቦ ሰብእ ዘይሬኢ ገጽየ ወየሐዩ፤

እግዚአብሔርም ሙሴን በባሕርዬ ፊቴን አይቶ የሚድን የለምና ፊቴን ማየት አይቻልህም አለው፤

፳፩፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ናሁ መካን ኀቤየ ሀሎ ወትቀውም ውስተ ኰኵሕ እስከ የኃልፍ ስብሐትየ፤

እግዚአብሔርም ሙሴን እኔ በምገለጽልህ ቦታ ዋሻ አለና በብርሃን ሠረገላ ሁኜ እስካልፍ ድረስ በዋሻው ውስጥ ቁመህ ታየኛለህ፤

፳፪፤ ወአነብረከ ውስተ ስቊረተ ኰኵሕ ወእከድን እዴየ በላዕሌከ እስከ አኃልፍ፤

በብርሃን ሠረገላ ሁኜ እስካልፍ ድረስ ባሕርዬን አይተህ ደንግጠህ እንዳትሞት ስቁረት /ቀዳዳ/ ባለው ዋሻ አድርጌ በእጄ እሠውርሃለሁ፤

፳፫፤ ወአሴስል እዴየ ወይእተ ጊዜ ትሬኢ ድኅሬየ ወገጽየሰ ኢያስተርኢ ለከ፤

በብርሃን ሠረገላ ሁኜ ካለፍኩ በኋላ እጄን እንሥቼልህ ከወደ ኋላዬ ታየኛለህ እንጂ በባሕርዬ ግን ፊቴን ማየት አይቻልህም አለው፤ /ሐተታ/ ምነው እጁስ ብርሃን አይደለምን ብርሃን ያሳየል እንጂ ይሠውራልን ቢሉ፤ እሱ ሠውር ካለው ይሠውራልና፤ ይህንም ፊትና ኋላ በሚሔድ ሰው ግሥ ተናግሮታል፤ በፊት የሚሔድ ሰው ኋላው እንጂ ፊቱ እንዳይታይ፤ ጌታም በዘፈቀደ ታይቶታል እንጂ ባሕርዩን አልገለጸለትምና፤ አንድም ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ናሁ መካን ኀቤየ ሀሎ፤ የሞት የመቃብር ሥልጣን በኔ ፈቃድ ነውና፤ ወትቀውም ውስተ ኰኵሕ በአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሰው ሁኜ ሥጋ ለብሼ ኋላ በደብረ ታቦር እስክገለጽልህ ድረስ አንተ በመቃብር ተወስነህ ትኖራለህ፤ ወአነብረከ በመቃብር አኖርሃለሁ፤ ወእከድን እዴየ ላዕሌከ በደብረ ታቦር የባሕርይ ልጅነቴን እስክገልጽ ድረስ ሥልጣኔን በአንተ አጸናለሁ፤ ወአሴስል እዴየ፤ ነገር ግን ሰው ሁኜ ሥጋ ለብሼ

www.ethiopianorthodox.org

በዚህ ዓለም በተገለጽኩ ጊዜ የሞትን ሥልጣን ከአንተ አር ቃለሁ፣ አንተም ከመቃብር ትነሣለህ፣ ወይእተ ጊዜ ትሬኢ ድኅሬየ /ምዕዛርየ/ ያንጊዜ በደብረ ታቦር በክበበ ትስብ እት ታየኛለህ፣ ወገጽየሰ ኢያስ ተርኢ ለከ ዛሬ ግን በባሕርዬ አታየኝም አለው፣ ይኸውም አልቀረ ጌታን ከሦስቱ ባለ ሟሎቹ ጋር በደብረ ታቦር አይቶታል::

## ምዕራፍ ፴፬

፩፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ቀር ለከ ክልኤተ ጽላተ ዘዕብን በከመ ቀዳምያት ወዕርግ ኀቤየ ውስተ ደብር ወእጽሕፍ ውስተ ውእቱን ጽላት ዝክተ ነገረ ዘሀሎ ውስተ ቀዳምያት ጽላት ዘቀጥ ቀጥኮን፣

እግዚአብሔርም ሙሴን እን ዲህ አለው፣ የቀደሙትን ጽላት አስመስለህ ሁለት ጽላት ቀርፀህ እኔ ወደምገለጽበት ተራራ ውጣ፣ ቀድሞ በሰበርካ ቸው ጽላቶች ተጽፈው የነበሩ ዐሥሩን ቃላትም በእነዚህ ጽላቶች ጽፌ እሰጥሃለሁ፤

፪፣ ወኩን ድልወ ለነግህ ወተዐርግ ውስተ ደብረ ሲና ወቁም ህየ ላዕለ ርእሰ ደብር፣

ማለዳ ወደ ደብረ ሲና ትወ ጣለህና ተዘጋጅተህ ንጹሕ ሁነህ እደር፣ ማልደህም ወደ ደብረ ሲና ወጥተህ ቁም፣

፫፣ ወአልቦ ዘየዓርግ ምስሌከ ወአልቦ ዘይሄሉ ውስተ ኵሉ ደብሩ ወአባግዕኒ ወአልሕምትኒ ኢይት ረዓዩ ቅሩበ ለውእቱ ደብር፣

ሌላ ሰው ግን ከአንተ ጋር ወጥቶ ከተራራው ላይ አብሮህ የሚቆም አይኑር፣ ላሞችም በጎችም ቢሆኑ በተራራው አቅራቢያ ሊሠማሩ አይገባም አለው፤

፬፣ ወወቀረ ሙሴ ክልኤተ ጽላተ ዘዕብን በከመ ቀዳምያት ወነሥአ በእዴሁ እልክተ ክልኤተ ጽላተ ዘዕብን ወጌሠ በጽባሕ ወዓርገ ሙሴ ውስተ ደብረ ሲና በከመ አዘዞ እግዚአብሔር፣

ሙሴም የቀደሙትን ጽላቶች አስመስሎ ሁለት የዕብን በረድ ጽላት ቀርፆ ይዞ እግዚአብሔር እንዳዘዘው ማልዶ ገሥግሦ ወደ ደብረ ሲና ወጣ፤

፭፣ ወወረደ እግዚአብሔር በደመና ወቆመ ህየ ወጸውዓ በስመ እግዚአ ብሔር፣

ጌታም በደመና ወርዶ በደብረ ሲና ራስ ላይ ቁሞ እኔ «መሐሪ ወመስተሣህል» ነኝ ብሎ ተናገረ፤



፮፣ ወኃለፈ እግዚእ ቅድመ ገጹ ወስምየ እግዚእ እግዚአብሔር መሐሪ ወመስተሣህል ርሑቀ መዓት ወብዙኃ ምሕረት ወጻድቅ፣

ጌታም በሙሴ ፊት በብርሃን ሠረገላ ሁኖ የጌትነቱን ስም እየጠራ አለፈ፣ ስሜም ይቅር ባይ ከመዓት የራቀ ቸርነቱ የበዛ ፈጥሮ የሚገዛ መባል ነው፤

፯፣ ዘየዓቅባ ለጽድቅ ወይገብር ምሕረተ ለአዕላፍ ወዘያሴስል ዓመፃ ወጌጋየ ወኃጢአተ ወለመአብስስ ኢያነጽሖ፣

የአብርሃምን መሐላ አጽንቼ ለአዕላፈ እስራኤል ቸርነትን የማደርግ ዓመፅን በደልን ኃጢ አትን የማርቅ ማለት ይቅር የምል እኔ ነኝ፤ /ሐተታ/ ዓመፃ የድፍረት፣ ጌጋይ የስሕተት፣ ኃጢአት የድካም ነው፣ በድሎ የማይመለሰውን ግን ከኃጢአት አላነጻውም /ይቀር አልለውም/፣

ዘያገብእ ኃጢአተ አበው ላዕለ ውሉድ ወላዕለ ውሉደ ውሉድ እስከ ሣልስ ወራብዕ ትውልድ፣

አባቶቻቸው የሠሩትን ኃጢ አት ልጆች ቢሠሩ፣ በልጆችና በልጅ ልጆች ላይ እስከ ሦስትና እስከ አራት ትውልድ የምመ ራመር እኔ ነኝ፤ አንድም ሦስትና አራት ሰባት ነው፣ እስከ ሰባት ትውልድ ድረስ ፍዳን አመጣባቸዋለሁ ሲል ነው፤

፰፣ ወጐጕዓ ሙሴ ወደነነ ውስተ ምድር ወሰገደ ለእግዚአብሔር፣

ሙሴም ጌታ ይህን ሲናገር በሰማ ጊዜ ደንግጦ አንገቱን ሰበር አድርጎ ለእግዚአብሔር የፍርሃት ስግደት ሰገደ፤

፱፣ ወይቤሎ ሙሴ ለእግዚአብሔር ለእመ ረከብኩ ሞገሰ በቅድሜከ ይሑር እግዚእየ ምስሌየ እስመ ዝንቱ ሕዝብ ጽኑዓ ክሣድ ውእቱ ወተሠሃል ኃጣውአ ወአበሳሁ ለሕዝብከ ወንከውን ለከ፣

ሙሴም እግዚአብሔርን በአንተ ዘንድ ባለሟልነትን ካገኘሁ አንተ ጌታዬ ከእኔ ጋራ በረድ ኤት አብረኸኝ ሒድ፣ እስራ ኤል ክሣደ ልቡናቸው በኃጢ አት የጸና ነውና የወገኖች ህን ፍጹም ኃጢአት ይቅር በል፣ ይህን ያደረግህልን እንደ ሆነ ለአንተ ስንገዛ እንኖራለን አለው፤

፲፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ናሁ አነ እሠይም ለከ ኪዳነ በቅድመ ኵሉ ሕዝብከ ወእገብር ለከ ዓቢያተ ወመንክራተ /ወክቡራተ/ ዘኢኮነ ከማሁ ውስተ ኵሉ ምድር ወውስተ ኵሉ አሕዛብ፣

ጌታም ሙሴን በወገኖችህ ዘንድ የኪዳን ምልክት የሚሆን ብርሃ ንን በፊትህ እሥልብሃለሁ፣ በአራቱ መዓዝን ባሉ በአሕዛብ ዘንድ ሁሉ ተደርጎ የማያውቅ ጭጋግ ተአምራት አደርግል ሃለሁ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወይሬኢ ኵሉ ሕዝብ እለ ውስቴቶሙ ሀሎከ ገብሮ ለእግዚ አብሔር እስመ መድምም ውእቱ ዘአነ እገብር ለከ፤

አንተ ተሹመህባቸው ያለህ ወገኖች ሁሉ የእግዚአብሔርን ተአምራት ያያሉ ማለት በፊትህ ብርሃን ተሥሎበት ያያሉ፤ እኔ የማደርግልህ ነገር ድንቅ ነውና፤

፲፩፤ ወዐቅ አንተ ባሕቲ ኵሎ ዘአነ እኤዝዘከ፤

ነገር ግን እኔ የማዝዝህን ትእዛዝ እንድትፈጽም አስተውል፤

ወናሁ አነ አወፅአሙ እምቅድመ ገጽከ ለከናኔዎን ወለአሞሬዎን ወለኬጤዎን ወለፌርዜዎን ወለጌርጌሴዎን ወለኤዌዎን ወለኢያቡሴዎን፤

እነሆ እኔም እነዚህን ሰባቱን ነገሥተ አሕዛብ ከፊትህ አስወጥቼ እሰዳቸዋለሁ፤ /አጠፋቸዋለሁ/ ኋላ በኢያሱ የሚደረገውን ለሙሴ ሰጥቶ ተናገረ፤

፲፪፤ ወዐቅ እንከ ርእሰከ ከመ ኢትምሐል ምስለ እልክቱ ሰብእ እለ ይተርፉ ውስተ ይእቲ ምድር እንተ ውስቴታ ይበውኡ ከመ ኢይኩን ጌጋይ ላዕሌክሙ፤

እናንተ ከምትገቡበት አገር ውስጥ ካሉ ከሞት ከቀሩት ከአሕዛብ ጋር ኃጢአት ለመሥራት ጣዖት ለማምለክ እንዳት ማማል ለራስህ ዕወቅ ይህ በእናንተ ዕዳ በደል እንዳይሆንባችሁ፤

፲፫፤ ምሥዋዓቲሆሙ ንስቱ ወምስላቲሆሙ ስብሩ ወአዕዋሞሙ ግዝሙ ወግልፎ አማልክቲሆሙ አውዕዩ በእሳት፤

መሠዊያቸውን አፍርሳችሁ፤ ምስላቸውን ሰብራችሁ፤ የሚሰግዱበትን ዛፋቸውን ቈርጣችሁ እጅ እግር ያወጡላቸውን ጣዖቶቻቸውን በእሳት አቃጥሉ፤

፲፬፤ ከመ ኢትስግዱ ለካልዕ አምላክ እስመ እግዚአብሔር ቀናኢ ስሙ፤ ወእግዚአብሔር ቀናኢ ውእቱ፤

እስመ ስሙ ለእግዚአብሔር ቀናኢ ብለህ አቅና፤ የእግዚአብሔር ስሙ ቀናተኛ ነውና፤ ለአምልኮቱም ቀናኢ ነውና ለሌላ አምላክ እንዳትሰግዱ ጣዖቶቻቸውን በእሳት አቃጥሉ፤ /ሐተታ/ ምነው ስምዖኒ መሐሪ ወመስተሣህል ብሎ አልነበረምን ስለ ምን ስሜ ቀናኢ ነው አለ? ቢሉ ንጉሥ በመንግሥቱ፤ ጉልማሳ በሚስቱ እንዲቀና እሱን ትተው ጣዖት ቢያመልኩ አይወድምና /ይፈርዳልና/፤

፲፭፤ ዮጊ ትትመሐሉ ምስለ እለ ይነብሩ ውስተ ይእቲ ምድር ወትዜምዉ ድኅረ አማልክቲሆሙ



ወትሠውዑ ለአማልክቲሆሙ ወይጼውዑከ ወትበልዕ እመሥዋዕቶሙ፤

በከነዓን ከሚኖሩ ሰዎች ጋራ ተማምላችሁ እነሱን መስላችሁ ወይምእኮ ጣዖቶቻቸውን ታመልኩ ይሆናል፤ እየጠሩህም ተረፈ መሥዋዕታቸውን ትመገብ ይሆናል፤

፲፮፤ ወትነሥእ እምአዋልዲሆሙ ለደቂቅከ ወአዋልዲከ ትሁብ ለደቂቆሙ ወያዜምዋሆሙ ለደቂቅከ ድኅረ አማልክቲሆን ወይዜምዋ አዋልዲከ ድኅረ አማልክቲሆሙ፤

የእነሱን ሴቶች ልጆች ላንተ ወንዶች ልጆች አጋብተህ፤ ያንተንም ሴቶች ልጆች ለእነሱ ወንዶች ልጆች ታጋባ ይሆናል፤ የአንተን ወንዶች ልጆች የእነሱ ሴቶች ልጆች በፍቅር ስበው ጣዖት ያስመልኳቸው ይሆናል፤ የአንተም ሴቶች ልጆች በእነዚያ ወንዶች ልጆች ፍቅር ተስበው ጣዖቶቻቸውን ያስመልኳቸው ይሆናል፤

፲፯፤ ወአማልክተ ዘስብኮ ኢትግበር ለከ፤

ተመትተው የተሠሩትን ጣዖታት አታምልክ፤

፲፰፤ ወሐገ ናዕት ዕቀብ ሰቡዓ መዋዕለ ብላዕ ናዕተ በከመ አዘዝኩከ በዘመኑ በወርኃ ሚያዝያ እስመ በወርኃ ሚያዝያ ወፃእከ እምድረ ግብጽ፤

በቂጣ የምትከበር በዓለ ፋሲካንም ጠንቅቀህ አክብር፤ በሚያዝያ ወር ሰባት ቀን ቂጣ እየበላህ አክብር እንዳልኩህ እስከ ሰባት ቀን ድረስ ቂጣ እየበላህ በዓለ ፋሲካን አክብር፤ በሚያዝያ ወር ከግብጽ የወጣህበት ነውና፤

፲፱፤ ወኵሉ ተባዕት ዘይፈትሕ ማኅፀነ ሊተ ውእቱ በኵሩ ለላሕም ወበኵሩ ለበግዕ፤

በኵር ሁኖ የሚወለደው ወንድ ሁሉ የኔ ገንዘብ ነው፤ የላሙም የበጉም በኵር የኔ ነው ለኔ ይገባል፤

፳፤ ወለበኵረ አድግስ ትቤዝዎ በበግዕ ወእመሰ ኢቤዘውካሁ ሤጠ ትሁብ ወኵሎ በኵረ ውሉድከ ትቤዙ ወኢታስተርኢ ቅድሜየ ዕራቀከ፤

የአህያውን በኵር ግን በበግ ለውጠው፤ በበግ ባትለውጠው ግን ሸጠህ ዋጋውን ስጥ፤ ከልጆችህም መጀመሪያ የተወለደውን ልታስቀር ብትወድ ግን ገንዘብ ሰጥተህ አስቀር፤ በቤተ እግዚአብሔር ዕራቁትህን አትታይ አለ፤ መብዓ ሳትይዝ አትሒድ፤ እንዲህም ማለቱ ቤተ እግዚአብሔር መከልከሉ አይደለም፤ ወደ ቤተ እግዚአብሔር ሲሔዱ ጥቂት መብዓ ይዞ መሔድ ይገባል ሲል ነው እንጂ፤

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

፳፩፤ ሰዱስ መዋዕለ ትገብር ግብረከ ወበሳብዕት ዕለት ተዓርፍ፤

ስድስት ቀን አርሰህ ቈፍረህ በሰባተኛው ቀን ከማረስ ከመቈፈር ታርፋለህ /አርፈህ ዋል/

፲ተ ዓመተ ተገበር ግብረከ ወበሳብዕ ዓመት ተዓርፍ፤ ወተዓርፍ ዘሪአ ወዓፂደ፤

ስድስት ዓመት አርሰህ ቈፍረህ በሰባተኛው ዓመት ከማረስ ከመቈፈር ከመሥራት ከማጨድ ዕረፍ፤ አንድም ምድሪቱ ከመታረስ ከመቈፈር ከመዘራት ትረፍ፤

፳፪፤ ወበዓለ ሰንበት ትገብር ሊተ አመ ይቀድሙ ዓፂደ ሥርናይ ወበዓለ ምኵራብ፤

የስንዴ አዝመራ ከሚታጨድ በት ወራት አስቀድሞ በሱባዔ የሚከበር በዓለ ሰዊትን በእሸት በነዶ አክብር፤ በዓለ መጸለትንም አክብር፤ /ሐተታ/ ደመና ጋርዶ፤ ባሕር ከፍሎ ያወጣን ሲሉ ዳስ ጥለው ድንኳን ተክለው ያከብሩታልና በዓለ ምኵራብ ባለው በዓለ እልጆኒ ይላል ጥሬ፤

፳፫፤ ሠለስተ ጊዜያተ ማዕከለ ዓመት ያስተርኢ ኵሉ ተባዕትከ ቅድመ ታቦተ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል፤

ከዓመት ሦስት ጊዜ ወንድ የሆነ ሁሉ የእስራኤል አምላክ የእግዚአብሔር ማደሪያ በምት ሆን በታቦተ ጽዮን ፊት ይታይ ማለት በዓል ለማክበር ሦስት ጊዜ ይውጣ፤

፳፬፤ ወአመ አወፅአሙ ለሕዝብ እምቅድመ ገጽከ እሰፍሖን ለአድዋሊከ ወአልቦ ዘይፈትዋ መኑሂ ለምድርከ ወሶበ ተዓርግ ሠለስተ ጊዜያተ በዓመት ታስተርኢ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ፤

አሕዛብን ከአንተ አርቄ ከነዓንን ባወረስኹህ ጊዜ አውራጃህን አስፋልሃለሁ፤ ከወረስኻትም በኋላ አገርህን የሚመኛት ማንም ማን የለም፤ መመኘትማ ምነው ብሎ የሚያገኛት የለም ሲል ነው፤ በዓል ለማድረግ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ፊት ለመታየት በዓመት ሦስት ጊዜ ለገቢረ በዓል ብትወጣም፤

፳፭፤ ወኢትዝባሕ ላዕለ ደም ብሑዕ መሥዋዕትየ ወኢይቢት ለነግህ መሥዋዕተ በዓል ዘፋሲካ፤

ተሠውቶ ያደረውን ደም መሥዋዕት አድርገህ አትሠዋ፤ አንድም ባደረ ደም መሥዋዕቱን አትሠዋ፤ /ሐተታ/ ሸክላ ቢሆን ይሰበሩት፤ ብርት ቢሆን ይወልውሉት ይላልና፤ ለበዓለ ፋሲካ የተሠዋው መሥዋዕትም ተርፎ አይደር፤



፳፮፤ ቀዳሜ እክለ ምድርከ ትወስድ ቤተ እግዚአብሔር አምላክከ ወኢታብስል በግዐ እንዘ ይጠቡ ሀሊበ እሙ፤

በእርሻህ ከበቀለው እህል መጀመሪያ የደረሰውን አንተ ሳትቀምስ ወደ ቤተ እግዚአብሔር ወስደህ ለሊቀ ካህናቱ ስጥ፤ በጉን የእናቱን ጡት ሲጠባ ሳለ፤ አንድም ጠብቶ ሳይጨርስ አትሠዋው አለ ርኀራኄ ነው፤ አንድም ለሊቀ ካህናቱ ሳታሳይ አታሳድገው ሲል ነው፤ /ሐተታ/ ሰባት ቀን የእናቱን ጡት ሲጠባ ይሰነብታል፤ በስምንተኛው ቀን የሊቀ ካህናቱ ሹም ሒዶ አይቶ ይጽፈዋል ከዚያው ያድጋልና እንዲህ አለ፤

፳፯፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ጸሐፍ ለከ ዘንተ ነገረ እስመ በዝንቱ ነገር አቀውም ለከ ኪዳነ ወለእስራኤል፤

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፤ ይህን የነገርኩህን ነገር ሁሉ ጻፈው፤ በዚህ በተናገርኩት ነገር ለአንተና ለእስራኤል መሐላዬን አጸናለሁና ሕጌን ብትጠብቁ እጠብቃችኋለሁ ሲል ነው ፤

፳፰፤ ወነበረ ቅድመ እግዚአብሔር አርብዓ መዓልተ ወአርብዓ ሌሊተ ኢበልዐ እክለ ወኢሰትየ ማየ ወጸሐፈ እግዚአብሔር ውስተ ጽላት ዘንተ ነገረ ፲ተ ቃላተ፤

ሙሴም በደብረ ሲና እህል ሳይበላ፤ ውሃ ሳይጠጣ አርባ መዓልት አርባ ሌሊት ተቀመጠ፤ እግዚአብሔርም ዐሥሩን ቃላት በሁለቱ ጽላት ጽፎ ሰጠው፤ ምሳሌ ነው፤ የቀድሞው ፅላት የአዳም፤ እምነበ አልቦ እንደ ተገኘ አዳምም እንበለ ዘርእ ለመገኘቱ ምሳሌ፤ ሁለት ወገን መሆኑ የነፍሱ የሥጋው፤ በጣዖት ምክንያት እንደ ተሰበረ አዳምም በኃጢአት ለመጐዳቱ ምሳሌ፤ የኋለኛው ጽላት የእመቤታችን፤ ቀር ከመቀዳምያት ማለቱ እመቤታችን በዘር በሩካቤ ለመገኘቷ ምሳሌ፤ ጽሕፈቱ ጌታችን ከሷ የነሣው ሥጋ፤ ቃሉ የአምላካዊ ቃል፤ በግብር አምላካዊ መገኘቱ ጌታም እንበለ ዘርእ ለመወለዱ ምሳሌ፤ አንድም የቀደመው ጽላት የኦሪት፤ የኋለኛው ጽላት የወንጌል፤ የቀደመው ጽላት እንደ ተሰበረ ሕገ ኦሪትም አልፏልና፤ የኋለኛው ጽላት ጸንቶ እንደኖረ ሕገ ወንጌልም ጸንቶ ይኖራልና፤

www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

፳፱፣ ወሶበ ወረደ ሙሴ እምደብረ ሲና ወሀለዋ ክልኤ ጽላት ውስተ እደዊሁ ወእንዘ ይወርድ እምደብር ኢያእመረ ከመ ተሰብሐ ኅብረ ገጹ እንዘ ይትናገር ምስለ እግዚ. አብሔር፣

ሙሴ ከደብረ ሲና በወረደ ጊዜ ሁለቱ ጽላት በእጆቹ ተይዘው ነበር፣ ከደብረ ሲናም ሲወርድ ከእግዚአብሔር ጋር ስለ ተነጋገረ በፊቱ ብርሃን እንደ ተሣለበት አላወቀም ነበር፤

፴፣ ወሶበ ርእይዎ አሮን ወኵሉ ደቂቀ እስራኤል ለሙሴ ከመ ተሰብሐ ርእየተ ኅብረ ገጹ ፈርሁ ቀሪቦቶ፣

አሮንና የእስራኤል ልጆች ሁሉ የሙሴን ፊት ብርሃን ሁኖ፣ አንድም ብርሃን እንደ ተሣለ በት ባዩ ጊዜ ወደ እሱ መቅረ ብን ፈሩ፤

፴፩፣ ወጸውዖሙ ሙሴ ወገብኡ ኀቤሁ አሮን ወኵሉ መኳንንተ ትዕይንት ወተናገሮሙ ሙሴ፣

ሙሴም ፈርተው ወደሱ አንቀ ርብም ሲሉ ባየ ጊዜ እኔ ነኝ አይዟቸሁ ብሎ ጠራቸው፣ አሮንና የእስራኤል አለቆችም ሸሽተው ሔደው ነበርና ተመል ሰው ወደሱ ሔዱ፣ ሙሴም ተናገራቸው፤

፴፪፣ ወእምድኅረ ዝንቱ ቀርቡ ኀቤሁ ኵሉ ደቂቀ እስራኤል ወአዘዞሙ ኵሎ ዘተናገሮ እግዚአ ብሔር በደብረ ሲና፣

ከዚህ በኋላ የእስራኤል ልጆች ሁሉ ተሰብስበው ወደ እሱ ቀረቡ፣ እሱም ጌታ በደብረ ሲና የነገረውን ሁሉ ሥሩ ብሎ አዘዛቸው፤

፴፫፣ ወሶበ አሕለቀ ተናግሮቶሙ ወደየ ሳዕለ ገጹ ግልባቤ በዘይሜ ውር ገጾ፣

ሙሴም እግዚአብሔር ያዘዘ ውን ነገር ለእስራኤል ነግሮ ከጨረሰ በኋላ ፊቱን የሚሰው ርበትን ልብስ /ሻሽ/ በፊቱ ላይ አደረገ፤

፴፬፣ ወሶበ የሐውር ሙሴ ቅድመ እግዚአብሔር ከመ ይትናገሮ ያሴስል ግልባቤሁ እስከ ይወፅእ ወእምከመ ወፅአ ይነግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ኵሎ ዘአዘዞ እግዚአብሔር፣

ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ለመ ነጋገር በሔደ ጊዜ ተነጋግሮ እስኪመለስ ድረስ ፊቱን የሸፈነበትን ልብስ አንሥቶ ይሔድ ነበር፣ እግዚአብሔር ያዘዘውን ሁሉ ለእስራኤል ልጆች ይነግራቸው ዘንድ ተነጋግሮ ከወጣ በኋላ ግን ፊቱን ይሸፍን ነበር፤



፴፭፣ ወርእዩ ደቂቀ እስራኤል ከመ ተሰብሐ ገጹ ወከመ ወደየ ግልባቤ በዘይሜውር ገጾ እንዘ ይወፅእ ከመ ይትናገሮሙ፣

የእስራኤል ልጆችም በሙሴ ፊት ብርሃን እንደ ተሣለበት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሊነ ግራቸው ወደነሱ በሚመጣ በት ጊዜ ፊቱን በልብስ ሸፍኖ እንዲመጣ ተረዱ፤ /ሐተታ/ ለጊዜው ፊቱን መሸፈኑ እስራ ኤል ባዩት ጊዜ ፈርተው የሚ ሸሹ ስለሆነ ነው፣ ፍጻሜው ግን ወደነሱ ሲሔድ ፊቱን መሸፈኑ ኃጢአት ብትሠሩ ጣዖት ብታመልኩ ድንቁርና ይሠለጥንባችኋል ሲል ነው፣ ወደ ጌታ ሲሒድ መሸፈኛውን ገልጦ መሔዱ ለጊዜው እስራ ኤል አይተው አይፈሩትምና ፍጻሜው ግን ወደ እግዚአብ ሔር ብትመለሱ ድንቍርና ይርቅላችኋል ሲል ነው።

## ምዕራፍ ፴ወ፭

፩፣ ወአስተጋብአሙ ሙሴ ለኵሉ ማኅበረ ደቂቀ እስራኤል ወይቤ ሎሙ ዝንቱ ውእቱ ነገር ዘይቤ እግዚአብሔር ከመ ትግበርዎ፣

ሙሴም የእስራኤልን ወገኖች ሁሉ ሰብስቦ እንዲህ አላቸው፣ ትሠሩት ዘንድ እግዚአብሔር ያዘዛችሁ ነገር ይህ ነው፤

፪፣ ሰዱሰ መዋዕለ ትገብሩ ግብረ ክሙ ወበሳብዕት ዕለት ተዓርፉ ቅድስት ሰንበት ዕረፍት ለእግዚአ ብሔር ኵሉ ዘይገብር ባቲ ግብረ ለይሙት፣

ስድስት ቀን ሥራታችሁ በሰባ ተኛው ቀን ዕረፍት አድርጉ፣ እግዚአብሔር ከመፍጠር ያረ ፈባት የከበረች በዓል ናትና በዚያች ቀን ሥራ የሚሠራ ባትም ሰው ሁሉ ተፈርዶበት ይሙት፤

፫፣ ወኢታንድዱ እሳተ በውስተ ኵሉ ማኅደርክሙ በዕለተ ሰንበትየ፣

በሰንበት ቀን በቤታችሁ ሁሉ እሳት አታንድዱ፤

፬፣ ወይቤሎሙ ሙሴ ለኵሉ ማኅበረ ደቂቀ እስራኤል እንዘ ይብል ዝንቱ ውእቱ ቃል ዘአዘዞ እግዚአብሔር እንዘ ይብል፣

ሙሴም ለእስራኤል ልጆች ወገኖች ሁሉ እንዲህ ብሎ ነገራቸው፣ እግዚአብሔር የተ ናገረው ቃል ይህ ነው፤

### ገባኤ

፭፣ ንሥኡ እምኔሆሙ መባዓ ለእግዚአብሔር ኵሎ ዘሐለየ ልቦሙ ያምጽኡ እምቀዳሚ ንዋዮሙ እምወርቅ ወእምብሩር ወእምብርት፣

ከእስራኤል ወገኖች የሚገባውን መባዓ ተቀበሉ፣ ከወርቁም

www.ethiopianorthodox.org

ከብሩም ከናሱም መጀመሪያ ካገኙት ገንዘብ ልባቸው ያሰበ ውን ሁሉ ያምጡ፤

፯፣ ወያክንት ወኅብረ ከብድ ወለይ ክሁብ ወቢሶስ ፍቱል ወፀጉረ ጠሊ፣

ሰማያዊ ሐር እጥፍ ሁኖ የተሠራ ቀይ ሐር ብጫ ሐር የተፈተለ የነጭ ሐር የፍየል ጠጉር፤

፰፣ ወማዕሰ በግዕ ግቡረ መሐን ወመሕነ መጸጺት ወዕፀ ዘኢይነቅዝ፣

ተለፍቶ ቀይ ቀለም የገባ የበግ ለምድ ሰማያዊ ቀለም የገባ የበግ ለምድ የማይነቅዝ ዕንጨት፤

፱፣ ወቅብዓ ለማኅቶት ወአፈዋተ ለተቀብዖ ወዕጣኑ ለማዕጠንት፣

ለመብራት የሚሆን ዘይት የሚቀቡት ሽቱ ለማዕጠንት የሚሆነውን ዕጣን፣

፲፣ ወአዕባነ መረግድ ወአዕባነ ዘይትሔረዉ ለኤፉድ ወለሎግዮ፣

መረግድ የሚባሉ ዕንቍዎች ንም ለኤፉድና ለሎግዮ ጌጥ የሚሆኑ ዕንቍዎችን፤

፲፩፣ ወኵሎሙ ጠቢባነ ልብ ዘውስ ቴትክሙ ይምጽኡ ወይግበሩ ኵሎ ዘአዘዘ እግዚአብሔር፣

ከእናንተ ወገን የልብ ዕውቀት ያላቸው ሰዎች ሁሉ መጥተው እግዚአብሔር ያዘዘውን ሥራ ሁሉ ይሥሩ፤

፲፩፣ ደብተራ ወሰቃቲሃ ወመክደና ውኖዓጸቲሃ ወአዕማዲሃ ወመናሥ ግቲሆን፣

አራቱን ኅብር ግምጃ፤ በግም ጃው ላይ የሚደረበውን ማቁን፣ በማቁ ላይ የሚደረበውን የማቁን ደበሎ ቀለበቶቹን ዓምዶቿን አዕማዱ የሚያዙባ ቸው ማገሮቹን፤

፲፪፣ ወታቦተ ዘመርጡል ወመፃ ውሪሃ ወተድባበ ወመንጦላዕተ ዘምሥዋር፣

ታቦቱን የሚሸከሙበት መሎ ጊያውን፣ የታቦቱን መግጠ ሚያ የቅድስተ ቅዱሳኑን መጋረጃ፤

፲፫፣ ወአዕማዲሃ ወምዕማዲሆን ወማዕደ ወመፃውርቲሁ፣

መጋረጃ የሚጋረድባቸውን ዓም ዶች ስክተታቸውን ሰደቃ ውን መሎጊያዎቹን፤

፲፬፣ ወኵሎ ንዋየ ወተቅዋመ ማኅቶት፣

መብራት የሚበራበት መቅረ ዙንና ዕቃውንም ሁሉ፤

ወኵሎ ንዋየ ወመኃትዊሃ ወቅብዓ ማኅቶት፣

ዕቃዋን ሁሉ አዕፁቋን ለመብ ራት የሚሆነውን ዘይቱን፤



፲፭፣ ወምሥዋዓ ዘዕጣን ወመፃው ርቲሁ ወቅብዓ ዘይትቀብዑ፣ ወዕጣነ ዘየዓጥኑ ወምክዳነ ሞኆት ዘደብተራ፣

ዕጣን የሚታጠንበት ማዕጠን ቱንና መሎጊያዎቹን የሚያጥ ኑበትን ዕጣኑንና የሚቀቡትን ዘይት የድንኳኑ ደጃፍ የሚጋ ረድበትን መጋረጃ፤

፲፮፣ ወምሥዋዓ ዘመሥዋዕት ወሰ ቅሰቀ ዘብርት ዘሎቱ መፃውሪሁ ወኵሎን ንዋየቲሁ ወማዕከከ ንዋየ ቲሁ ወማዕከከ ምስለ መንበሩ፣

መሥዋዕት የሚሠዋበት መሠ ዊያውንና ስቡ የሚቃለጥበ ትን የብረት ወንፊት መሎ ጊያዎቹንና ዕቃውንም ሁሉ ስኑንና ብርቱን፤

፲፯፣ ወመንጦላዕተ ዓፀድ ወአዕ ማዲሁ ወምዕማዲሆን ወመክድነ አንቀጸ ዓፀድ፣

የቅጽሩን መጋረጃ አዕማዱን ከነስክተታቸው የቅጽሩን በር መጋረጃ፤

፲፰፣ መታክሊሁ ለደብተራ ወመታ ክለ ዓፀድ ወአውታሪሆን፣

የደብተራ አሪትንና የቅጽሩን በር መጋረጃ የሚይዙባቸው ካስማዎች በካስማው የሚይዘ ውንም አውታር፣

፲፱፣ ወአልባሲሁ ለአሮን ካህን ወአልባሰ ደቂቁ ዘክህነቶሙ ወአ ልባሰ በዘይገብሩ በውስተ መቅደስ፣

ለአሮንና ለልጆቹ የክህነታቸው መለያ የሚሆኑትን ልብሶች በቤተ መቅደስ ለብሰው የሚ ያገለግሉበትንም ልብስ ይህን ንም ሁሉ ይሥሩ፣ /ሐተታ/ ይህንንም ጌታ ለሙሴ ሲነግ ረው ሙሴ ለእስራኤል ሲነግ ራቸው እነሱ ሲያመጡ ሲሠሩ መላልሶ ይናገረዋል፤

፳፣ ወወፅኡ ኵሉ ማኅበሮሙ ለደቂቀ እስራኤል እምኀበ ሙሴ፣

የእስራኤል ልጆች ወገኖች ሁሉ ይህን ከሰሙ በኋላ ከሙሴ ዘንድ ወጡ፤

፳፩፣ ወአምጽአ ፩ዱ ፩ዱ በከመ ሐለየ በልቡ ወበከመ ፈቀደ በነፍሱ አምጽአ መባዓ ለእግዚአብሔር ለኵሉ ግብረ ለደብተራ መርጡል ወለኵሉ መፍቅዳ ወለኵሉ አልባስ ዘመቅደስ፣

እያንዳንዱ ሊሰጥ ወዶ ልቡ እንደ አሰበ ለደብተራ አሪት ሥራና ለሚያሻው ሁሉ የቤተ መቅደስ ልብስ የሚሆነውንም ሁሉ ለእግዚአብሔር መብዓ አድርጎ አመጣ፤

፳፪፣ ወአምጽኡ ዕደው ዘእምኀበ አንስትኒ ዘከመ ፈቀደ ልቦን ማኅ ተማተ፣ ወአውዓበ ወሕልቀታተኒ

www.ethiopianorthodox.org

ወሐብላታቲኒ ወአውቃፈ ወኵሉ ሥርጕ ዘወርቅ፣

ሴቶች ልባቸው የወደደውን ያህል ስጥተዋቸው ወንዶች ከሴቶች ተቀብለው አመጡ፣ አምጽኡ ያለውን ይተረትራል፣ የወርቅ ማርዳ /የወርቅ ፈርጥ/ ወአውጸበ፣ ንሮ መንደልቶ ወሕልቀታቲኒ ተርታ ቀለበት፣ ወሐብላታቲኒ የወርቅ እንጥልጥል ወአውቃፈ የወርቅ የብር አምባር ወኵሉ ሥርጐ ዘወርቅ ነሣሣለትና የወርቁንም ጌጥ ሁሉ አመጡ፤

ወኵሉ አምጽኡ ወርቀ መባዓ ለእግዚአብሔር፣

ያልተሠራውንም ወርቅ ሁሉ ለእግዚአብሔር መብዓ አድርገው አመጡ፤

፳፫፣ ወኵሉ ብእሲ ዘረከበ ያክንተ ወኅብረ ከብድ ወለየ ክዑበ ወቢሶስ ክዑበ ወፀጕረ ጠሊ ወማዕሰ በግዕ ግቡረ መህን ወማዕሰኒ ዘሥርየቱ ኅብረ ያክንት፣

ሰማያዊ ሐር ያለው ብጫ ሐር ድርብ ሁኖ የተሠራ ቀይ ሐር ድርብ ሁኖ የተሠራ ነጭ ሐር የፍየል ጠጕር የመህን ሥራ የሚሆን የበግ ለምድና ሰማያዊ ቀለም የገባ አንቀልባ ያለው ሰው ሁሉ አመጣ፣

፳፬፣ ወአብዓ ኵሉ ዘበዕዓ ብዕዓተ ብሩረ ወብርተ መባዓ ለእግዚአብሔር፣

እሰጣለሁ ብሎ የተሣለውን ሁሉ ወርቁን ብሩን ለእግዚአብሔር መብዓ አድርጎ አመጣ፣

ወእምነበ ተረክበ ዕፅ ዘኢይነቅዝ ለኵሉ እምግብረ መፍቅዱ ለደብተራ አምጽኡ፣

ለደብተራ ኦሪት የሚያሻውን ሥራ ሁሉ የማይነቅዝ ዕንጨት ከሚገኝበት ቦታ አመጡ፤

፳፭፣ ወብእሲትኒ እንተ ትክል ፈቲለ በእደዊሃ አምጽአት ፈትለ ዘያክንት ወኅብረ ከብድ ወለይ ወቢሶስ፣

ፈትል የምታውቅ ሴትም ሰማያዊ ሐርን ብጫውን የቀዩን የነጩን ሐር እየፈተለች አመጣች፣

፳፮፣ ወኵሉን አንስት እለ ሐለየ በልቦን ወበጥበብ ፈተላሁ ለጸጕረ ጠሊ፣

በልባቸው የዕውቀትን ነገር የሚያስቡ ሴቶችም ሁሉ የፍየሉን ጠጕር በጥበብ ፈትለው አመጡ፤

፳፯፣ ወመላእክትኒ አምጽኡ አዕባነ መረግድ ወአዕባነ ዘይትኄረው ለኤፉድ ዘላዕለ መትከፍት ወለሎግዮ፣

አለቆችም መረግድ የሚባል ዕንቊ ከትከሻና ከደረት በሚውሉ ልብሶች ላይ የሚሆኑ ዕንቊዎችን አመጡ፤



፳፰፣ ወቅብዓ ማኅቶት ወቅብዐ ዘይትቀብዑ ወዕጣነ ዘየዓጥኑ፣

የሚያበሩትንና የሚቀቡትን ዘይት የሚያጥኑበትን ዕጣንም አመጡ፤

፳፱፣ ወኵሉ ብእሲ ወብእሲት ዘፈቀደ ልቦሙ ከመ ያብኡ ወይግበሩ ኵሎ ግብረ ዘአዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ አምጽኡ ደቂቀ እስራኤል መባዓ ለእግዚአብሔር፣

መብዓ ያገቡ ዘንድ እግዚአብሔርም ሙሴን ያዘዘውን ሁሉ ያደርጉ ዘንድ የእስራኤል ልጆች ሴቶችና ወንዶች ሁሉ ልቡናቸው የወደደውን መብዓ ለእግዚአብሔር አመጡ፤

፴፣ ወይቤሎሙ ሙሴ ለደቂቀ እስራኤል ናሁ ጸውዖ እግዚአብሔር በስሙ ለባስልኤል ወልደ ኡሪ ወልደ ሑር ዘእምነገደ ይሁዳ፣

ሙሴም የእስራኤልን ልጆች እንዲህ አላቸው፣ እነሆ ከነገደ ይሁዳ ከሚሆን ከሑር የተወለደ የኡሪ ልጅ ባስልኤልን እግዚአብሔር በስሙ ጠራው፤

፴፩፣ ወመልዖ መንፈሰ እግዚአብሔር ወጥበበ ወልቡና ወአእምሮ፣

መንፈሰ ረድኤትን፣ ማስተዋልን ዕውቀትን አሳደረበት፤

፴፪፣ ከመ ይኩን ሊቀ ላዕለ ኵሉ ፀረብት ወይግበር ኵሎ ምግባረ ወይግበር ወርቀኒ ወብሩረኒ ወብርተኒ፣

ከሠራተኞች ሁሉ በላይ አለቃ ይሆን ዘንድ ሥራውንም ሁሉ ወርቁን ብሩን ብርቱን ይሠራ ዘንድ፤

፴፫፣ ወኪነ ዕንቍኒ ወዕፀኒ ወይግበር ኵሎ ግብረ በጥበብ ወይምሐር፣

የዕንቍን ሥራ እየቀረፀ ለመግጠም ዕንጨቱንም እየጠረበ እያለዘበ ለመግጠም ሥራውን ሁሉ ራሱ እየሠራ ለሌሎቹም ያስተምር ዘንድ፤

፴፬፣ ወወደየ ውስተ ልቡ ሎቱኒ ወለኤልያብ ወልደ አክሴምክ ዘእምነገደ ዳን፣

ከነገደ ዳን በሚሆን በአክሴምክ ልጅ በኤልያብና በባስልኤል ልብ እግዚአብሔር ዕውቀቱን አሳደረ፤

፴፭፣ ወመልዖሙ ጥበበ ልብ ከመ ያእምሩ ገቢረ ኵሎ ግብረ መቅደስ ዘይትአነም ከመ ይእንሙ በያክንት ወበኅብረ ከብድ ወበለይ ክዑብ ወቢሶስ፤

ለደብተራ ኦሪት የሚሠራውን ሁሉ በዕውቀት ይሠሩ ዘንድ በሰማያዊ ሐር በብጫ ሐር ድርብ ሁኖ በተሠራ ቀይ ሐር በነጭ ሐር ይሠሩ ዘንድ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወከመ ይግበሩ ኵሎ ግብረ ጽርበት ዘዘዚአሁ፣

የዕንጨቱንም አጠራረብ ልዩ ልዩ እያደረጉ ይሠሩ ዘንድ ዕውቀትን አሳደረባቸው::

## ምዕራፍ ፴ወ፮

፩፣ ወገብሩ ባስልኤል ወኤልያብ ወኵሎሙ ጠቢባን ልብ እለ ተውኅበ ሎሙ ጥበብ ወአእምሮ ከመ ይግበሩ ኵሎ ግብረ መቅደስ ዘይትፈቀድ ኵሎ ዘአዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ፣

ለደብተራ ኦሪት የሚያሻውን ሥራ ሁሉ ይሠሩ ዘንድ ፍጹም ዕውቀት የተሰጣቸው ዓዋቂዎች ሁሉ ኤልያብና ባስልኤልም እግዚአብሔር ለሙሴ ያዘዘውን ሥራ ሁሉ ሠሩ፤

፪፣ ወጸውዖሙ ሙሴ ለባስልኤል ወለኤልያብ ወለኵሎሙ እለ ቦሙ ጥበብ ዘወሀቦሙ እግዚአብሔር አእምሮ ውስተ ልቦሙ፣

ሙሴም ኤልያብንና ባስልኤልን እግዚአብሔር በልቡናቸው ፍጹም ዕውቀት ያሳደረባቸውን ሰዎች ሁሉ ጠራቸው፣

ወለኵሎሙ እለ በፈቃደ ልቦሙ ይገብሩ ከመ ይግበሩ ወከመ ይሑሩ ውስተ ገነተ ግብር ከመ ይፈጽምዎ፣

በልባቸው ወደው የሚሠሩትን ሁሉ ሥራ ወደሚሠሩበት ቦታ ሒደው ሥራውን ይፈጽሙ ዘንድ ጠራቸው፤

፫፣ ወነሥኡ እምቅድመ ሙሴ መባዓ ዘአብኡ ደቂቀ እስራኤል ለኵሉ ምግባረ መቅደስ ከመ ይግበሩ፣

ለደብተራ ኦሪት የሚሆነውን ሥራ ሁሉ ይሠሩ ዘንድ የእስራኤል ልጆች ያገቡትን መባ ከሙሴ ፊት ተቀብለው ሔዱ፤

ወእሙንቱኒ ይትዌከፉ ዓዲ ዘያበውኡ እምነበ እለ ያመጽኡ ነግሀ ነግሀ፣

እነሱም እስራኤል ዕለት ዕለት የሚያመጡትን መባ ይቀበሉ ነበር፤

፬፣ ወመጺኦሙ ኵሎሙ ጠቢባን እለ ይገብሩ ግብረ መቅደስ ፩ዱ ፩ዱ በበምግባሪሁ ዘይገብር፣

የደብተራ ኦሪትን ሥራ እንደ ታዘዘው አድርገው የሚሠሩ ጥበበኞች ሁሉ አንዱም አንዱ በሙሴ ዘንድ መጥተው፤

፭፣ ይቤልዎ ለሙሴ ብዙኀ መባዓ ያበውዑ ሕዝብ እምግብር ዘአዘዘ እግዚአብሔር ከመ ይትገበር፣

ሕዝቡ እግዚአብሔር ይሠራ ብሎ ካዘዘው አብልጠው ደስ ብሏቸው ብዙ መባ ያመጣሉ፤ አንድም ብዙኅ መባዕ ዘያበውኡ ሕዝብ፣ ሕዝቡ የሚያገቡት ይሠራ ዘንድ እግዚአብሔር ካዘዘው ሥራ ይልቅ ብዙ ነው፤



፮፣ ወአዘዘ ሙሴ ወሰበከ ውስተ ትዕይንት ለዕድኒ ወለአንስትኒ ወይቤ እምይእዜ ኢይግበሩ መባዓ ዘመቅደስ ወተከልዓ ሕዝብ እምአብእ፣

ሙሴም እንግዲህ ወዲህ ለደብተራ ኦሪት ሥራ የሚሆን መባዕ አታምጡ ብሎ ለወንዶችም ለሴቶችም በከተማው ዐዋጅ ነገረ፣ ሕዝቡም መባ ከማግባት ተከለከለ፤

፯፣ እስመ አክሎሙ ለምግባር ዘይገብሩ ወተርፎሙ፣

ሕዝቡ ያገቡት መብዓ ለደብተራ ኦሪት ሥራ በቅቶ ተርፏቸዋልና፤

፰፣ ወገብሩ ኵሎሙ ጠቢባን ልብ ምግባረ ደብተራ ዐሠርተ አዕፃደ እምቢሶስ ክዑብ ወእምያክንት ወኅብረ ከብድ ወለይ ክዑብ ወኪሩቤነ ገብሩ በምግባረ ምዕናም፣

የልብ ዕውቀት ያላቸው ሰዎች ሁሉ ለደብተራ ኦሪት የሚሆን የልብሱን ሥራ ከሰማያዊ ሐር ከብጫ ሐር እጥፍ ሁኖ ከተሠራ ከቀይ ሐርና ከነጭ ሐር ዐሥር ፈርጅ አድርገው ሠሩ፣ ኪሩቤልንም ከመጋረጃው ላይ በጥልፍ ሥራ ሣሏቸው፤

፱፣ ወኑኑ ለአሐዱ ዓፀድ ፳ ወ፰ቱ በእመት ወርኅቡ ርብዕ በእመት ለአሐዱ ዓፀድ በመሥፈርቱ ከማሁ ለኵሎሙ አዕፃድ፣

የአንዱ ፈርጅ ቁመቱ ሃያ ስምንት ወርዱ አራት ክንድ ነው፣ የሁሉም ቁመታቸውም ወርዳቸውም በአንዱ ፈርጅ ልክ ነው፤

፲፣ ወኃምስተ አዕፃደ አስተሳመኩ በበይናቲሆሙ አሐዱ ምስለ ካልኡ ወኃምስተ አዕፃደ አስተሳመኩ በበይናቲሆሙ አሐዱ ምስለ ካልኡ፣

አምስቱን ፈርጅ በአንድ ወገን አምስቱን ፈርጅ በአንድ ወገን አድርገው አንዱን ከአንዱ ጋር በስፍ አያይዘውታል፤

፲፩፣ ወገብሩ ፶ መማስጠ ዘያክንት ላዕለ ከንፈረ አሐዱ ዓፀድ እምጽንፉ በዘዮኑብር፣

ሁለቱንም የሚያገናኝ በአንዱ ፈርጅ በጠርዙ ላይ ከሰማያዊ ሐር ሃምሳ ተባት ቍልፍ ሠሩ፤

፲፪፣ ወከማሁ ሃምሳ መማስጠ ገብሩ በከንፈረ ዓፀድ ካልዕ በዘዮኑብሩ፣

አንድ ወገን ሁኖ በተሰፋው በሁለተኛውም ፈርጅ በጠርዙ ላይ የሚገናኙበት ሃምሳ ተባት ቍልፍ ሠሩ፤

፲፫፣ ወገብሩ ፶ ኖፃዳተ ዘወርቅ ወአኅበሩ አዕፃዳተ አሐዱ ምስለ ካልኡ በኖፃዳት ወኮነ ደብተራሁ አሐዱ፣

ሃምሳ የወርቅ ቀለበትም ሠርተው አምስቱን ፈርጅ በአንድ

www.ethiopianorthodox.org

ወገን አድርገው በቀለበት አያ ያዙት፣ እንዲህም አድርገው አንድ ድንኳን አደረጉት፤

፲፬፣ ወገብሩ ዐሠርተ ወአሐደ አዕፃደ ዘሰቅ ዘይሴውር እምላዕሉ ለደብተራ፤

በግምጃውም ላይ በድንኳኑ ላይ የሚለብስ ከበግ ጠጕር የተሠራ ዐሥራ አንድ ፈርጅ ሠሩ፤

፲፭፣ ወለለ፩ዱ ዓፀድ ኑኁ ፴ በእመት ወርኅቡ ርብዕ በእመት ለለ፩ዱ ዓፀድ ከማሁ በአምጣኒሆሙ፣

የአንዱ ፈርጅ ቁመቱ ሠላሳ ወርዱ አራት ክንድ ነው፣ የዓሥራ አንዱም ሁሉ ፈርጅ ቁመታቸውም ወርዳቸውም በአንዱ ፈርጅ ልክ ነው፤

፲፮፣ ወአኀበሩ ኃምስተ አዕፃደ በበይናቲሆሙ ወስድስተ አዕፃደ አኀበረ በበይናቲሆሙ፣

አምስቱን ፈርጅ በአንድ ወገን፣ ስድስቱን ፈርጅ በአንድ ወገን አድርገው አንዱን ከአንዱ ጋር በስፍ አያይዘውታል፤

ወገብሩ ፶ መማስጠ ላዕለ ከንፈረ አሐዱ ዓፀድ በጽንፉ በዘየኃብሩ፣

አንድ ወገን ሁነው በተሰፋት በአምስቱ ፈርጅ ጠርዝ ላይ የሚገናኙበት ሃምሳ ተባዕት ቀኍልፍ ሠሩ፤

፲፯፣ ወኃምሳ መማስጠ ላዕለ ከንፈረ ዓፀድ ካልእ በዘየኃብሩ፤

አንድ ወገን ሁነው በተሰፋ በስድስቱ ፈርጅ በአንዱ ፈርጅ ጠርዝ ላይም የሚገናኙበት ኃምሳ ተባት ቀኍልፍ ሠሩ፣

፲፰፣ ወገብሩ ኃምሳ ኍፃዳተ ዘብርት በዘየኃብሩ ከመ ይኩን አሐደ፣

አገናኝተው አንድ የሚያደርግ ጉበት በአንዱ ፈርጅ ላይ የሚያገናኙበት ኃምሳ የብርት /የናስ/ ቀለበት ሠሩ፤

፲፱፣ ወገብሩ ዘይከድኖ ለሠቅ ማዕሰ በግዕ ኀሡየ፣

በብስጥ ላይ /በድንኳኑ ላይ/ የሚለብስ ተለፍቶ ቀይ ቀለም የገባ የበግ ለምድ ሰብስበው ሠፉ፣

፳፣ ወገብሩ አዕማደ ዘደብተራ እምዕፅ ዘኢይነቅዝ፣

ለደብተራ አሪትም ከማይነቅዝ ዕንጨት አዕማድን /ምሰሶ ዎችን/ ሠሩ፤

፳፩፣ ዘዐሥር በእመት ቆሙ ለ፩ዱ ዓምድ ወርኅቡ እመት ወመንፈቀ እመት፣

የአንዱም ዓምድ /ምሰሶ/ ቁመቱ ዓሥር ክንድ ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል /ከስንዝር/ ነው፤

፳፪፣ ወመሣምክተ ሥረዊሁ ክልኤቱ ለአሐዱ ዓምድ እንዘ ይሳመክ



አሐዱ ምስለ ካልኡ ወከማሁ ገብሩ ለኵሉ አዕማደ ደብተራ፣

አንዱ ከአንዱ ጋራ ተገናኝቶ የሚቆምበት የአንዱን ዓምድ ሁለት ምዕማድ እያደረገ ለደብተራ አሪት አዕማድ ሁሉ እንደዚሁ ሁለት ሁለት ምዕማድ እያደረገ ሠሩ፤

፳፫፣ ወገብሩ ዕሥራ አዕማደ እምገጸ አዜብ፣

በአዜብ /በደቡብ/ በኩል ሃያ አዕማድ ሠሩ፤

፳፬፣ ወገብሩ ለሙ ለ፳ አዕማድ አርብዓ ስክተታተ ዘብሩር ፪ቱ ስክተቱ ለአሐዱ ዓምድ በክልኤሆሙ ገጸቲሁ ወክልኤቱ ስክተቱ ለአሐዱ ዓምድ በክልኤሆሙ ገጸቲሁ፣

ለሃያው አዕማድ በብር የተለበጡ አርባ ምዕማድ ሠራላቸው እግሩ የሚቆምበት የአንዱን ዓምድ ምዕማድ ሁለት ሁለት እያደረገ በሁለቱ እግሩ የሚቆምበት የአንዱንም ዓምድ ምዕማድ ሁለት ሁለት እያደ ረገ ሠሩ፤

፳፭፣ ወእምካልዕ ገጸ ደብተራ መንገለ ሰሜን ገብሩ ፳ አዕማደ፣

በመስዕ በኩል ላለው ለአንዱ ወገንም ሃያ አዕማድ ሠሩ፤

፳፮፣ ወስክተቶሙ አርባዕ ዘብሩር ለለ፩ዱ ዓምድ ወ፪ቱ ስክተቱ እምክልኤቱ ገጸቲሁ፣

የሚቆሙበትም በብር የተለበጡ አርባ ምዕማዶች ሠሩላቸው በሁለት ወገን የሚቆሙበት፣ እያንዳንዱ አዕማድ /ምዕማዶች/ ሁለት ሁለት ናቸው፤

፳፯፣ ወእምድኅር እምገጸ ደብተራ መንገለ ባሕር ፮ቱ አዕማደ፣

በደብተራ አሪት በስተኋላዋ በምዕራብ በኩል ስድስት አዕማድ ሠሩ፤

፳፰፣ ወ፪ተ አዕማደ ገብሩ ዓዲ ለመዓዝነ ደብተራ እምድኅር፣

ዳግመኛም በስተከበሮ ቤት በኩል ለመዓዝን መጋፉ ሁለት ምሰሶዎች አምጥተው በቀኝና በግራ አቆሙ፤

፳፱፣ ወዕሩየ ኮኑ ወኃብሩ እምታሕቱ እስከ ላዕሉ ወከማሁ ገብሩ ለክልኤሆን መዓዝን፣

አንድ ሁነው ከላይ እስከታች ተካክለው ቆሙ፣ ለሁለቱም መዓዝን እንዲህ አደረጉ ማለት የመዓዝን መጋፉ ሠሩ፤

፴፣ ወኮኑ ፰ቱ አዕማድ ወምዕማዲሆሙ ዐሡሩ ወስሱ ዘብሩር ወለለ ፩ዱ ፩ዱ ዓምድ ፪ቱ ፪ቱ ምዕማዱ፣

መላው ስምንት ምሰሶዎች ሆኑ በብር የተለበጡ ምዕማዳቸውም /እግሮቻቸውም/ አሥራ ስድስት ናቸው፣ የእያንዳንዱ ዓምድ ምዕማድ /እግር/ ሁለት ሁለት ነው፤

www.ethiopianorthodox.org

፴፩፤ ወገብሩ መናሥግተ ለአዕማደ ደብተራ እምዕፀ ዘኢይነቅዝ ፭ተ መናሥግተ እምአሐዱ ገጽ፤

ከማይነቅዝ ዕንጨት ቈርጠው ለደብተራ አሪት አዕማድ ማገር ሠሩ፤ በአንድ ወገን አምስት ማገር፤

፴፪፤ ወኃምስተ መናሥግተ እምካልእ ገጽ ወኃምስተ መናሥግተ ዘመንገለ ባሕር፤

አምስቱን በግራ፤ አምስቱን በቀኝ፤ አምስቱን በስተከበሮ ቤት በኩል ላሉ አዕማድ ማገር ሠሩ፤

፴፫፤ ወገብሮ ለመንሠግ ዘማዕከል ከመ ይዕዱ በማዕከለ አዕማድ እምጽንፍ ኀበ ጽንፍ፤

የመካከለኛውን ማገር ውስጥ ለውስጥ ከዳር እስከ ዳር እንዲሔድ አደረገው፤

፴፬፤ ወለአዕማድ ወለመማሥጡ ወለመናሥግቲሁ ቀፈልዎሙ ወርቀ፤

አዕማዱንም ምሰሶዎቹንም ማገሩንም የማገሩንም መያገ ቀለበቶቹን በወርቅ ለበጡአቸው ፤

፴፭፤ ወገብሩ መንጦላዕተ ዘያክንት ወኅብረ ከብድ ወለይ ክዑብ ወቢሶስ ፍቱል ወገብሩ በግብረ ምዕናም ኪሩቤነ፤

እጥፍ ሁኖ ከተሠራ ከቀይ ሐርና ከነጭ ሐር ከብጫ ሐርና ከሰማያዊ ሐር መጋረጃን ሠሩ፤ ኪሩቤልንም በመጋረጃው ላይ በጥልፍ ሥራ ሣሏቸው፤

፴፮፤ ወገብሩ ላቲ ፬ተ አዕማደ እምዕፀ ዘኢይነቅዝ ወቀፈልዎሙ ወርቀ ወአርእስቲሆሙኒ ዘወርቅ ወገብሩ ሎሙ ፬ተ ምዕማደ ዘብሩር፤

ከማይነቅዝ ዕንጨት /ከግራር/ ቈርጠው መጋረጃውን የሚጋርዱባቸው አራት አዕማድ /ምሰሶዎች/ ሠርተው በወርቅ ለበጧቸው፤ ክባሳቸውም የወርቅ ነው፤ አራቱ አዕማድ የሚቆሙበት አራቱንም ምዕማድ /እግር/ በብር ለበጧቸው፤

፴፯፤ ወገብሩ ላቲ መንጦላዕተ ዘይከድኖ ለኆኅተ ደብተራ እምያክንት ወኅብረ ከብድ ወለይ ክዑብ ወቢሶስ ፍቱል በብዑድ ግብረት ፤

የደብተራ አሪትን ደጃፍ የሚጋርዱበት እጥፍ ሁኖ ከተሠራ ከቀይ ሐርና ከነጭ ሐር ከሰማያዊ ሐርና ከብጫ ሐር በልዩ አሠራር መጋረጃን ሠሩላት፤

፴፰፤ ወገብሩ ላቲ ለመንጦላዕት ፭ተ አዕማደ እምዕፀ ዘኢይነቅዝ ወቀፈልዎሙ ወርቀ ወአርእስቲሆሙኒ ዘወርቅ ወገብሩ ሎሙ ኃምስተ ምዕማደ ዘብሩር፤

መጋረጃ የሚጋረድባቸው ከማይነቅዝ ዕንጨት ቈርጠው አምስት ምሰሶዎች ሠርተው በወርቅ ለበጧቸው፤ ክባሳቸውም የወርቅ ነው፤ በብርት ለብጠው አምስት ምዕማድም ሠሩላቸው፤ ሁሉ የሚረግጠው ስለሆነ።



# ምዕራፍ ፴ወ፯

## ገባኤ

፩፤ ወገብረ ባስልኤል ታቦተ እምዕፅ ዘኢይነቅዝ ዘካዕበ እመት ወመንፈቀ እመት ኑኃ እመት ወመንፈቀ እመት ራኅባ እመት ወመንፈቀ እመት ቆማ፤

ባስልኤልም ከማይነቅዝ ዕንጨት ቈርጦ ወርዱን ክንድ ከስንዝር፤ ወደ ላይ ቁመቱን ክንድ ከስንዝር፤ ርዝመቱን ሁለት ክንድ ከስንዝር አድርጎ ለጽላቱ ማደሪያ ታቦትን ሠራ፤

፪፤ ወቀፈላ ወርቀ ንጹሐ እምውስጣ ወእምአፍአሃ ወገብረ ላቲ ቀጸላ ወርቅ በዓውዳ ወገብረ በውስቴታ ማዕበለ ዘወርቅ ዘኖፃዳት እምዓውዳ፤

በውጭም በውስጥም በጠራ ወርቅ ለበጣት፤ በዙሪያዋም የወርቅ ቀጸላ /አክሊል/ አበጀላት፤ ወርቁን አቅልጦ ቀለበቱ የሚገባበት በአራቱ ማዕዝን የወርቅ ገብገብ ሠራላት፤

፫፤ ወሰበከ ላቲ ጽበነ አርባዕተ ዘወርቅ ወአንበሮን ላዕለ አርባዕቱ ምስማካቲሃ ጽበነ ክልኤተ ውስተ አሐዱ ምስማክ ወጽበነ ክልኤተ ላዕለ ዳግም ምስማክ፤

አራት የወርቅ ቀለበት ሠርቶ በዳርና በዳር በአራቱ መዓዝን አንጠለጠላቸው፤ ሁለቱን ቀለበት በአንድ ወገን፤ ሁለቱን ቀለበት በአንድ ወገን አድርጎ አኖራቸው፤

፬፤ ወገብረ ላቲ መፃውርተ እምዕፅ ዘኢይነቅዝ ወቀፈሎሙ ወርቀ፤

ከማይነቅዝ ዕንጨት መሎጊያ አበጅቶ በወርቅ ለበጣቸው፤

፭፤ ወአብአ ድንባዛቲሃ ውስተ እልኩ ጽበን አርባዕ እለ ውስተ ምስማክ ዘታቦት መሳክሚሃ ለታቦት በዘይሰክምዋ ቦሙ፤

ታቦቱን የሚሸከሙባቸው መሎጊያዎችንም በታቦቱ በአራቱ መዓዝን በተንጠለጠሉት በአራቱ ቀለበት ውስጥ አገባ፤

፮፤ ወገብረ ላቲ ተድባበ ዘወርቅ ንጹሕ ዘካዕበ እመት ወመንፈቀ እመት ራኅቡ፤

ርዝመቱ ሁለት ክንድ ከስንዝር ወርዱ ክንድ ከስንዝር የሆነ የጠራ የወርቅ መግጠሚያ አበጀላት፤

፯፤ ወገብረ ላቲ ክልኤተ ኪሩቤነ ዘወርቅ ፍሑቆ፤

ተመትቶ ከለዘበ ወርቅ የሁለቱን ኪሩቤል ምስል ቀረፀ፤

ወገብሮሙ እምክልኤቱ ምስማካቲሁ ለተድባብ፤

በታቦቱ መግጠሚያ ላይ በዳርና በዳር አኖራቸው፤

www.ethiopianorthodox.org

፰፣ አሐዱ ኪሩብ እምለፌ፣ ወአሐዱ ኪሩብ እምለፌ እምስማካቲሁ ለተድባብ፣

አንዱን ኪሩብ በአንድ ወገን፣ አንዱን ኪሩብ በአንድ ወገን አድርጎ ቀረፃቸው፤

፱፣ ወኮኑ ኪሩቤን ይረብቡ ክንፊሆሙ እመልዕልት እንዘ ይጼልሉ በክንፊሆሙ መልዕልተ ተድባብ ወገጾሙ ይትናጸር በበይናቲሆሙ በዲበ ተድባብ፣

ሁለቱም ኪሩቤል የታቦቱን መግጠሚያ በሁለቱ ክንፋቸው ሸፍነው ረበው ይታዩ ነበር፣ በመግጠሚያውም ላይ በዳርና በዳር ሁነው እንደሚናተፍ ዶሮ ፊት ለፊት ይተያዩ ነበር፤

፲፣ ወገብረ ማዕደ እምዕፀ ዘኢይነቅዝ ኑኁ ካዕበ ዕመት ወራኅቡ ዕመት ወቆሙ ዕመት ወመንፈቀ ዕመት፣

ስደቃውንም ከማይነቅዝ ዕንጨት ቁርጠ ርዝመቱን ሁለት ክንድ፣ ወርዱ ክንድ፣ ቁመቱን ክንድ ከስንዝር አድርጎ ሠራ፤

፲፩፣ ወቀፈሎ ወርቀ ንጹሐ ወገብረ ሎቱ ቀጸላ ዘወርቅ በዓውዱ፣

በጠራ ወርቅ ለብጦ ዙሪያውን እንደ አፊ ድስት ያለ የወርቅ ከንፈር አበጀለት፤

፲፪፣ ወገብረ ማዕበለ ዘወርቅ በዓውዱ መጠነ አርባዕቱ አፃብዕ ወገብረ ለቀጸላሁ ጽበነ አርባዕተ፣

በከንፈሩ ዙሪያ ከፍታው ጋት የሚያኽል የወርቅ አክሊል አሆረበት፣ በከንፈሩም ላይ አራት የወርቅ ቀለበት አበጀለት፤

፲፫፣ ወገብረ ኆፃዳተ ዘማዕበል ለቀጸላሁ ወገብረ አርባዕተ አውቃፋተ ዘወርቅ ወአንበሮን ዲበ አፃብዕ ውስተ አርባዕቱ ፍና ዘእገሪሁ መንገለ ቀጸላሁ፣

ለመግጠሚያው አራት ቀለበት ሠራለት፣ ለማዕድም አራት የወርቅ አምባሮች ሠርቶ ከመግጠሚያው አጠገብ በእግሩ በኩል ባለ በአራቱ መዓዝን በቀለበቶቹ ውስጥ አንጠለጠላቸው፤

፲፬፣ ወኮኑ አጽብዒሁ አብያተ ለመሃውሪሁ ዘያነሥኡ ማዕደ፣

ቀለበቶቹም ማዕድን ለሚሸከሙባቸው ለመሎጊያዎቹ መግቢያ ሆኑ፤

፲፭፣ ወገብረ መሃውርቲሁ እምዕፀ ዘኢይነቅዝ ወቀፈሎሙ ወርቀ ንጹሐ ከመ ያንሥኡ ቦሙ ማዕደ፣

መሎጊያዎቹን ከማይነቅዝ ዕንጨት ሠርቶ ማዕዱን አንሥተው ሊሸከሙባቸው በጠራ ወርቅ ለበጣቸው፤



፲፮፣ ወገብረ ንዋያተ ዘማዕድ መጽብሒሁ ወአጽሕልተ ወመዳምሃ ወመዋጽሒሁ በዘቦቱ ያወጽሑ ዘወርቅ፣

በማዕድ ላይ የሚሠራባቸውን ዕቃዎች ሁሉ ሠራ፣ ወጥ የሚቀርብበትን ወጭት፣ ኅብስት የሚቀርብበትን ፃህል፣ ማንከ ዎችን፣ ደሙን የሚያፈሱበት ጽዋ ይህን ሁሉ ከወርቅ ሠራ፣

፲፯፣ ወገብረ መራናተ እምወርቅ ንጹሕ ፍሑቆ ገብራ ለመራናት ዓምደ ወአብራኢሃ ወመአሃዚሃ ወክበበ ርእሳ ወጽጌያቲሃ እምኔሃ ተገብሩ፣

መብራት የሚበራበትን መቅረዝ ከጠራ ከለዘበ ወርቅ ሠራ፣ የተቀዋምን መካከለኛውን ቋሚ ዋን ክፍት አድርጎ ወይም ሥረ ወጥ አድርጎ ሠራ፣ ከዚያም አጽቆቹንና መሸቢያዎቹን መግጠሚያዋንም ሠራ አበባዎቹም ከእሷ ተሠሩ ማለት ምንባረ ፊትሎቹም ሥረወጥ ሁነው ተሠሩ፤

፲፰፣ ስድስቱ አብራዕ እለ ይበውኡ እምገቦሃ ለተቅዋመ ማኅቶት ሠለስቱ አብራዕ እምአሐዱ ፍናሃ ወሠለስቱ አብራዕ እምካልእ ፍናሃ፣

በመቅረዚቱ በግራ በቀኝ ሥረወጥ ሁነው የተሠሩት ስድስቱ አዕጹቅ ሦስቱ በአንድ ወገን፣ ሦስቱ በአንድ ወገን ሁነው ተሠርተዋል፤

፲፱፣ ወሠለስቱ መዓንዚሃ እለ የኀብሩ ምሳሌ ለአሐዱ ክበበ ርእስ ጽጉይ ከማሁ ለ፳ቲሆሙ አብራዕ እለ ይወፅኡ እምተቅዋመ ማኅቶት፣

ሦስቱ መሸቢያዎቹም በመመሳሰል አንድ ናቸው፣ ለአንዱ አጽቅ ምንባረ ፊትል አበባ የመሰለ መግጠሚያ እንዳለው ከተቀዋም ሥረወጥ ሁነው ለወጡ ለስድስቱም አዕፁቅ ምንባረ ፊትልና እንደ አበባ የመሰለ መግጠሚያ አላቸው፤

፳፣ ወለተቅዋመ ማኅቶት መዓኅዛቲሃ አርባዕቱ ወጽጌያቲሃ ወክበበ ርእሳ፣

በመካከል ቋሚ ለሆነችው መቅረዝ መሸቢያዎቹ አራት ናቸው፣ አበባ መስለው የተሠሩ ምንባረ ፊትሎቹም መግጠሚያ ያላቸው ናቸው፤

፳፩፣ ወክቡብ መትሕተ ፪ቱ ፪ቱ አብራዕ ለስድስቲሆሙ አብራዕ እለ ይወፅኡ እምኔሃ፣

ሁለት ሁለት ሁነው በተሠሩት አዕፁቅ በታች ክቡብ ሁኖ የተሠራ ምዕማድ አለ፣ ስድስቱ አዕፁቅ ከርሷ ሥረ ወጥ ሁነው የተሠሩ ናቸው፤

፳፪፣ ክበበ ርእሳ ወአብራኢሃ እምኔሃ ኮኑ ኮሎሙ ፍሑቆ እምአሐዱ ወርቅ ንጹሕ፣

ከተቅዋም ሥረ ወጥ ሁነው የተሠሩ መግጠሚያዋና ምንባረ

www.ethiopianorthodox.org

ፈትሏ ሁሉም ከአንድ ጥሩ ወርቅ ልዝብ ሁነው የተሠሩ ሆኑ፤

፳፫-፳፬፤ ወገብረ መኃትዊሃ ፯ተ ወገብረ ጽዋዓቲሃ ወበዘያሜንይዋ ዘወርቅ ወለኵሉ ንዋያቲሃ መክሊተ ወርቅ ገብራ፤

በሰባቱም ምንባረ ፈትል ሰባት ፈትሎችን አደረገ፤ አንድም በተቅዋም በቀኝም በግራም ስድስት አዕፁቅ ሠርቶ ራሷን ፯ተኛ አደረገ፤ ዘይቱን የሚመሉበትን ጽዋ ፈትሉን የሚጠቅሱበትን ወለባና የሚኮስትሩበትንም መቀስ ከወርቅ ሠራ፤ ይህንንም ሁሉ ከአንድ መክሊተ ወርቅ ሠራ፤

፳፭፤ ወገብረ ምሥዋዓ ዘዕጣን እምዕፅ ዘኢይነቅዝ ዘዕመት ኑኁ ወእመት ራኅቡ ርቡዓ ገብሮ፤

ዕጣን የሚታጠንበትንም ማዕጠንት ከማይነቅዝ ዕንጨት ርዝመቱ ክንድ፤ ወርዱ ክንድ የሚሆን ቆርጦ አራት ገጽ አድርጎ ሠራው፤

ወካዕበ እመት ቆሙ ወእምኔሁ ተገብሩ አቅርንቲሁ፤

ቁመቱ ሁለት ክንድ ነው፤ እንደ ቀንድ ሁነው የተሠሩ መያዣዎቹም ከሱ ሥረ ወጥ ሁነው የተሠሩ ናቸው፤

፳፮፤ ወቀፈሎ ወርቀ ንጹሐ ምድሮ ወዓውደ ዓረፍቱ ወአቅርንቲሁ፤

ወለሉን የግድግዳውን ዙሪያና መያዣዎቹንም በጠራ ወርቅ ለበጠው፤

፳፯፤ ወገብረ ሎቱ ቀጸላ ዘወርቅ በዓውዱ ወ፪ኤተ አውቃፈተ ወርቅ ገብረ ሎቱ መትሕተ ቀጸላሁ ላዕለ ፪ቱ ገበዋቲሁ ዘይከውኑ አብያተ ለመፃውሪሁ ከመ ያንሥኡ በሙኪያሁ፤

በዙሪያውም እንደ አፈድስት ያለ የወርቅ ክንፈር ሠራለት፤ ማዕጠንቱን፤ ይሸከሙባቸው ዘንድ መሎጊያዎቹ የሚገቡባቸውን ሁለት የወርቅ ቀለበቶችንም ከክንፈሩ በታች በሁለት ወገን ሠራ፤

፳፰፤ ወገብረ መፃውርቲሁ እምዕፅ ዘኢይነቅዝ ወቀፈሎሙ ወርቀ፤

መሎጊያዎቹንም ከማይነቅዝ ዕንጨት ቆርጦ ሠርቶ በወርቅ ለበጣቸው፤

፳፱፤ ወገብረ ቅብዐ ዘይትቀባዑ እምዘይት ወአፈዋተ ቅድወ ጽዑጠ ዘጸዓጢ፤

ካህናት የሚቀቡትንም ቅባት አስማምቶ የሚቀመም ሽቱ አጣፋጭ ከሚያዘጋጀው ያማረ የተወደደ ከሆነ ሽቱና ከዘይት አደረገ።



## ምዕራፍ ፴ወ፰

### ገባኤ

፩፤ ወገብረ ምሥዋዓ ለመሥዋዕት እምዕፅ ዘኢይነቅዝ ዘኃምስቱ በዕመት ኑኁ ወኃምስቱ በዕመት ራኅቡ ርቡዓ ኮነ ወሠልሰ በዕመት ቆሙ፤

የሚሠዋበትን ምሥዋዕ ወደ ላይ ቁመቱ ሦስት ክንድ፤ ወርዱ አምስት ክንድ፤ ርዝመቱ አምስት ክንድ የሚሆን አራት ገጽ አድርጎ ከማይነቅዝ ዕንጨት ሠራ፤

ወገብረ አዕጋሪሁ ውስተ አርባዕቱ መዓዝኒሁ ወእምኔሁ ይእቲ ምቅዋማቲሁ፤

በአራቱ መዓዝን የሚቆምበት እግር አበጀለት፤ ይኸውም መቆሚያዎቹ ሥረ ወጥ ሁነው የተሠሩ ናቸው፤

፫፤ ወገብረ ሎቱ አቅርንተ ዲበ አርባዕቱ መዓዝኒሁ ወእምኔሁ ወዕኡ አቅርንቲሁ ወቀፈሎ ብርተ፤

በአራቱም ገጽ አራት ቀንድ /ኩላብ/ አወጣለት፤ አራቱም ቀንዶች ሥረ ወጥ ሁነው የተሠሩ ናቸው በናስም ለበጠው፤

፬፤ ወገብረ ኵሎ ንዋየ ምሥዋዕ ምግኃሣተ ወጸሕራተ ወፍያላተ ወመ ኖስሳተ ወመውስደ እሳት ኵሎ ገብረ እምብርት፤

የምሥዋዑን ዕቃ ሁሉ፤ አመዱን የሚያፈሱበትን ዕንቅብ ሥጋውን የሚቀቅሉበትን ድስት፤ ደሙን የሚቀበሉበት ጣሱን፤ ከድስቱ ሥጋ የሚያወጡበትን ባለ ሦስት ልሳን መውጊያ፤ እሳት የሚወስዱበትን መጫሪያ፤ ይኸንንም ሁሉ ከናስ /ከብርት/ ሠራ፤

፭፤ ወገብረ መጥበስተ ለመሥዋዕት ስቅሡቀ ከመ መሥገርተ ዓሣ ዘብርት፤

ስቡ ለሚቀልጥበት ለምሥዋዓ ብርቱ እንደ ዓሣ መረብ ያለ የብረት ወንፊት ሠራለት፤

ወገብረ ሎቱ ለመጥበስት ፬ተ ኅልቀታተ ዘብርት ውስተ አርባዕቱ መዓዝኒሁ፤

ስቡ ለሚቀልጥበት ለምሥዋዓ ብርቱ በአራት ወገን አራት የብረት ቀለበት አበጀለት፤

ወአንበሮ ለመጥበስት በቤተ መሥዋዕት ታሕተ ወኮነ በመንፈቀ ቤተ መሥዋዕት፤

ስቡ የሚቀልጥበት መጥበሻውን በምሥዋዑ ውስጥ አኖረው፤ ይኸውም በምሥዋዑ ውስጥ በእኩሌታው ላይ ሆነ፤

፯፤ ወሰበከ አርባዕተ አውቃፋተ ዘብርት ለአርባዕቱ መዓዝኒሁ ከመ ይኩኑ አብያተ ለመፃውርቲሁ፤

ለሚሸከሙባቸው መሎጊያዎች መያዣ እንዲሆኑ በአራቱ ወገን /ገጽ/ አራት የብረት ቀለበቶች ሠራ፤

www.ethiopianorthodox.org

፮፣ ወገብረ መሣውርተ እምዕፀ ዘኢይነቅዝ ወቀፈሎሙ ብርተ፣

ምሥዋዑን የሚሸከሙባቸው መሎጊያዎቹን ከማይነቅዝ ዕንጨት ሠርቶ በናስ ለበጣቸው፤

፯፣ ወአብአ መሣውርቲሁ ውስተ አውቃፋት ዘላዕለ ገበዋተ ምሥዋዕ ከመ ያንሥኡ ቦሙ ኪያሁ ፍሉግ ሰሌዳ ገብሮ፣

ምሥዋዑን ያነሡባቸው ዘንድ መሎጊያዎቹን በምሥዋዑ በሁለቱ ወገን ባሉት ቀለበቶች ውስጥ አገባ፣ ሥራውንም የተፈለፈለ አድርጎ ሠራው፤

፰፣ ወገብረ ማዕከለ ዘብርት ወመንበሩሂ ዘብርት፣

የብርት ሰን /መታጠቢያ/ ሠራ፣ መቀመጫውንም ከብርት ሠራ፤

ወአንበሮ በአንፃረ አንስት እለ ይመጽኡ ከመ ይጸልዩ ኀበ አንቀጸ ደብተራ ዘመርጡል በዘይትሐጸቡ ቦቱ፣

የብርቱን ሰንና መቀመጫውን ሌዋውያን በሚታጠቡበት በደብተራ ኦሪት ደጃፍ ሊጸልዩ በሚመጡ ሴቶች አንፃር አኖረው፤

፱፣ ወገብረ ሳቲ ዓፀደ ለደብተራ መንገለ አዜብ እንተ የማን ወመንጦላዕተ ዓፀዱ እምቢሶስ ክዑብ ወኑኑ ምዕት በዕመት፣

ለደብተራ ኦሪት በአዜብ በኩል በስተቀኝ ለቅጽር የሚሆን ቦታ አበጀላት፣ ቅጽሩ የሚጋረድ በት የሸማውንም አጥር ድርብ ከሆነ ከነጭ ሐር ሠራ፣ አግዳሚ ርዝመቱንም መቶ ክንድ አደረገው፤

፲፣ ወአዕማዲሁ ዕሥራ ዘብሩር ወምዕማዲሆሙ ዕሥራ ዘብርት፣

በብር የተለበጡ አዕማዱ ሃያ ናቸው፣ የብርት የሚሆኑ ምዕማዶቹም ሃያ ናቸው፤

ውኖፃዱቲሆሙ ወጥነፊሆሙ ለአዕማድ ዘብሩር፤

የሃያው አዕማድ ቀለበቶቻቸውም ዘንጎቻቸውም የብር ናቸው፤

፲፩፣ ወለመንገለ ሰሜን መንጦላዕቱ ምዕት በዕመት ኑኑ፣

በሰሜንም በኩል የቅጽሩ መጋረጃ ርዝመቱ መቶ ክንድ ነው፤

ወአዕማዲሁ ፳ ዘብሩር፣ ወምዕማዲሆሙ ፳ ዘብርት፣ ውኖፃዱቲሆሙ ወጥነፊሆሙ ለአዕማድ ዘብሩር፣

ሃያው አዕማድ በብር የተለበጡ ናቸው፣ ሃያ የሚሆኑ ምዕማዶቻቸውም የብርት ናቸው፣ የሃያው አዕማድ ቀለበቶቻቸውም ዘንጎቻቸውም የብር ናቸው፤

፲፪፣ ወዘመንገለ ባሕር መንጦላዕቱ ሃምሳ በእመት ኑኑ አዕማዲሁ ፲ቱ ዘብሩር ወምዕማዲሆሙ ዐሠርቱ ዘብርት፣

በምዕራብ በኩል በስተከበሮ ቤት በኩል ያለው የቅጽሩ መጋረጃ ርዝመቱ አምሳ ክንድ ነው፣ ዐሥሩ አዕማድም በብር የተለበጡ ናቸው፣ የብርት የሚሆኑ ምዕማዶቻቸውም ዐሥር ናቸው፤

ውኖጻዱቲሆሙ ወጥነፊሆሙ ለአዕማድ ዘብሩር፣

የዐሥሩ አዕማድ ቀለበቶቻቸውም ዘንጎቻቸውም የብር ናቸው፤

፲፫፣ ወዘመንገለ ጽባሕ መንጦላዕቱ ሃምሳ በዕመት ኑኑ ወአዕማዲሁ ዐሠርቱ ዘብሩር፣

በምሥራቅ በኩል የቅጥሩ መጋረጃ ርዝመት ሃምሳ ክንድ ነው፣ ዐሥሩ አዕማድም በብር የተለበጡ ናቸው፣

፲፬፣ ወምዕማዲሆሙ ዐሠርቱ ዘብርት፣ ዐሠርቱ ወኃምስቱ በዕመት ኑኑ ለመንጦላዕት እምገጸ አሐዱ ምስማክ፣

የብርት የሚሆኑ ምዕማዶቻቸውም ዐሥር ናቸው፤ አንድም አሥር የሚሆኑ ምዕማዶቻቸውም በናስ የተለበጡ ናቸው፣ በስተምሥራቅ በአንድ ወገን ያለ የመጋረጃው ርዝመትም አሥራ አምስት ክንድ ነው፣

አዕማዲሁ ሠለስቱ ወምዕማዲሆሙ ሠለስቱ፣

በዓሥራ አምስቱ ክንድ ርዝመት የሚቆሙት አዕማድ ሦስት ናቸው፣ ምዕማዶቻቸውም ሦስት ናቸው፤

፲፭፣ ወእምካልእ ምስማክ ዐሠርቱ ወኃምስቱ በዕመት ኑኑ ለመንጦላዕት፣

በምሥራቅ በሁለተኛው ወገን ያለው የመጋረጃው ርዝመት ዓሥራ አምስት ክንድ ነው፤

፲፮፣ አዕማዲሁ ሠለስቱ ወምዕማዲሆሙ ሠለስቱ ወኵሉ መንጦላዕተ ዓፀድ ዘዓውድ እምቢሶስ፣

በአሥራ አምስት ክንድ ርዝመት የሚቆሙት አዕማድ ሦስት ናቸው፣ የዙሪያው መጋረጃው ሁሉ ከነጭ ሐር የተሠራ ነው፤

፲፯፣ ወኵሉ አዕማድ ዘዓፀድ ወአርእስቲሆሙ ቅሩላን በብሩር ወምዕማዲሆሙ ዘብርት፣

በዙሪያው ያሉ አዕማዱና ክባሳቸው ሁሉ በብር የተለበጡ ናቸው፣ ምዕማዶቻቸውም የብርት ናቸው፤

፲፰፣ ወለአንቀጸ ዓፀድ መንጦላዕቱ ፳ በዕመት ኑኑ በያክንት ወኅብረ ክብድ ወለይ ክዑብ ወቢሶስ ክዑብ፣

የቅጽሩ በር መጋረጃ ርዝመቱ ሃያ ክንድ ነው፣ መጋረጃውም ከሰማያዊ ሐርና ከብጫ ሐር ድርብ ሁኖ ከተሠራ ከቀይ ሐርና ከነጭ ሐር የተሠራ ነው፤



www.ethiopianorthodox.org

ወብዑደ ኮነ በግብረ መርፍዕ ወቆሙ ኃምስቱ፡ በዕመት እመንገለ ራኅቡ ከመ መንጦላዕተ ዓጸድ፣

በጥልፍ ሥራ /በግብረ መርፌ/ ልዩ ሁኖ የተሠራ የሆነ በወርዱ በኩል ያለው ቁመቱም እንደ በሩ መጋረጃ አምስት ክንድ ነው፤

፲፱-፳፣ ወአዕማዲሁ አርባዕቱ ዘብሩር ወምዕማዲሆሙ አርባዕቱ ዘብርት ወኮሉ መታክለ ደብተራ ዘዓውደ ዓፀድ ዘብርት፣

አራት የሚሆኑ ምሰሶዎቻቸውም በብር የተለበጡ ናቸው፣ አራት የሚሆኑ ምዕማዶቻቸውም የናስ ናቸው፣ የደብተራ ኦሪት የዙሪያው መጋረጃ ካስማ ሁሉ የናስ ነው፤

፳፩፣ ወከመዝ ሥርዓታ ለደብተራ መርጡል ዘከመ ተአዘዘ ሙሴ እምእግዚአብሔር ከመ ይኩኖሙ ግብሮሙ ለሌዋውያን በእደ ይታምር ወልደ አሮን ካህን፣

የሌዋውያን ግብራቸው /ሥርዓታቸው/ በአሮን ልጅ በይታምር ይደረግ ዘንድ ሙሴ ከእግዚአብሔር እንደ ታዘዘ የደብተራ ኦሪት ጌጡ ሥርዓቱ እንዲህ ነው፤

፳፪፣ ወባስልኤል ወልደ ኡሪ ወልደ ሖር ዘእምነገደ ይሁዳ ገብረ ኵሎ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ፣

ከነገደ ይሁዳ የተወለደ የሖር ልጅ የሚሆን የዑሪ ልጅ ባስልኤልም እግዚአብሔር ለሙሴ እንደ አዘዘው አድርጎ ሁሉን ሠራ፤

፳፫፣ ወምስሌሁ ኤልያብ ወልደ አክሴምክ ዘእምነገደ ዳን ዘኮነ ሊቀ ኪነት ዘበምዕናም ወበዘመርፍዕ ወበዘአስቅ፣

ከእሱም ጋር ከዳን ወገን የሚሆን የአክሴምክ ልጅ ኤልያብ የመሀን ሥራና የጥልፍ ሥራ የማቅም ሥራ በሚሠሩት ላይ አለቃ ሁኖ ተሹሞ ነበር፤

ከመ ይዕንም ቢያክንት ወበኅብረ ከብድ ወበለይ ክዑብ ወቢሶስ ክዑብ፣

በሰማያዊ ሐር በብጫ ሐር ዕጥፍ ሁኖ በተሠራ በነጭ ሐርም የጥልፍ ሥራ ይሠራ ዘንድ ተሹሞ ነበር፣

፳፬፣ ወኮሉ ወርቅ ዘመባዕ ዘተገብረ ለምግባረ ደብተራ፣

ለደብተራ ኦሪት ሥራ የሆነው መባ ሁኖ የገባው ወርቅ ሁሉ፣

ኮነ ፳ወ፱ተ መካልየ ወ፯ተ ፻ተ ወ፴ ሰቅለ በሰቅል ቅዱስ፣

በቤተ እግዚአብሔር ዓዋቂ /ሚዛን/ ሃያ ዘጠኝ መክሊት ሰባት መቶ ሠላሳ ወቄት ሆነ፡



፳፭፣ ወብሩርኒ ዘመባዕ ዘአስተሩቀዱ እምትዕይንት፣

ከሠፈሩ ተቈጣጥረው ያወጡት የብሩ መባ፤

ምዕት መካልይ ወዐሠርቱ፡ ምዕት ወሰብአቱ፡ ምዕት ሰብ ወኃምስቱ፡ ሰቅል በሰቅል ቅዱስ፣

በቤተ እግዚአብሔር ዓዋቂ /ሚዛን/ መቶ መክሊት ሺህ ሰባት መቶ ሰባ አምስት ወቄት ነው፤

፳፮፣ ዘአስተዋዕኦ በበርእሶሙ አሐተ አሐተ ዲድርክመ ወአሐቲ ዲድርክም መንፈቁ ለሰቅል፣

በየራሳቸው ያወጡት አንዳንድ ድሪም ነው፤ አንዱም ድሪም የወቄት እኩሌታ ነው

ወኵሉ ዘሖረ ውስተ መፍቅድ ዘእም፳ ዓም ወላዕሉ ፷ ወ፴፻ት ወ፭ቱ፡ ፻ት ወ፶፣

ይህን ገንዘብ እንዲሰጥ ለመቍጠር የሔደው ከሃያ ዘመን ጀምሮ እስከ አምሳ ዘመን ያለው ሰው ሁሉ ስድሳ እልፍ ከሦስት ሺህ ስድስት መቶ ሦስት ሺህ አምስት መቶ አምሳ ነው፤

፳፯፣ ወተገብረ ዝኩ፡ ምእት መካልይ ዘብሩር ለምዕማደ አዕማድ ዘደብተራ ወለምዕማደ አዕማድ ዘመንጦላዕት፣

ይኸውም መቶ መክሊት ብር ለደብተራ ኦሪትና ለቅድስተ ቅዱሳን መጋረጃ አዕማድ ምዕማዶች /መቀመጫ/ ተለበጠ /ተሠራ/፤

ምዕት መካልይ ለምዕት ምዕማድ በበአሐቲ መክሊት ለለአሐቲ ርእስ፣

ለእያንዳንዱ ምዕማድ አንድ አንድ መክሊት እያደረጉ ለመቶው ምዕማድ መቶ መክሊት አፍስሰው ለበጡት፣

፳፰፣ ወለዝንቱ፡ ፲ቱ፡ ፻ት ወ፯ቱ፡ ምዕት ወ፸ወ፭ቱ፡ ሰቅል ገብርዎ ለአዕማደ ዓፀድ፣

ይህንን ሺህ ከሰባት መቶ ሰባ አምስቱን ብር ግን ለደብተራ ኦሪት አዕማድ ኩላብ አድርገው ሠሩት፤ አንድም ለቅጽሩ አዕማድ ክባስ አድርገው ሠሩት፤

፳፱፣ ወኮነ ብርት ዘመባዕ አርባዕቱ፡ ምዕት ወሰብዓ መካልይ ወ፳ ፻ት ወ፬ቱ፡ ፻ት ሰቅል፣

የብርቱ /የናስ/ ስጦታ አራት መቶ ሰባ መክሊት ሁለት ሺህ አራት መቶ ወቄት ነው፤

፴፣ ወገብረ እምኔሁ መንበረ ኖኅተ ደብተራ ዘመርጡል ወምሥዋዐ ዘመሥዋዕት፣

ከዚህም ከፍሎ በደብተራ ኦሪት ደጃፍ ላሉ አዕማድ ምዕማድና መሥዋዕት የሚሠዋበትን መሠዊያን ሠራ፤

www.ethiopianorthodox.org

ጎጆት ሪቃና ቤተሰቡ የግል ቤተ መጻሕፍት



፴፩፣ ወመጥበስተ ወኰሎ ንዋየ ምሥዋዕ ወመንበረ ዓፀድ ዘዓውድ ወመንበረ አንቀጸ ዓፀድ፣

ስብ የሚጤስበትን የብርት ወንፊት የምሥዋዓ ብርትን ዕቃ ሁሉ የቅጽሩንና የቅጽሩን በር ምዕማድ፤

ወኰሎ መታክለ ደብተራ ወመታክለ ዓፀድ ዘዓውድ፣

የደብተራ አሪትን ካስማ የዙሪያ ቅጽሩንም መጋረጃ ካስማ ሁሉ ከናስ ሥራ።

## ምዕራፍ ፳ወ፱

፩፣ ወዘተርፈ ወርቅ ዘመባዕ ተገብረ ንዋይ በዘይገብሩ ቅድመ እግዚአብሔር፣

መባ ከገባ ወርቅ ተሠርቶለት የተረፈው ወርቅ በቤተ እግዚአብሔር በሚያገለግሉበት ገንዘብ የሚያገለግሉበት ዕቃ ተሠራ፤

ወእምነ ያክንት ወኀብረ ከብድ ወለይ ወቢሶስ ተገብረ አልባሰ ለመልእክተ መቅደስ ወገብሩ አልባሰ ቅዱሰ ለአሮን በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ፣

ከሰማያዊና ከብጫ ሐር ከቀይና ከነጭ ሐር የተረፈውም በመቅደስ ሲያገለግሉ የሚለብሱት ልብስ ተሠራ፣ እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው ለአሮንም የክበረ /የተለየ/ ልብስ ሠራ፤

፪፣ ወገብሩ ኤፉደ በወርቅ ወበያክንት ወበኀብረ ከብድ ወበለይ ክዑብ ወቢሶስ ክዑብ፣

ልብሰ መትከፍ /የደረት ልብስ/ የሚሆን ኤፉድንም በሰማያዊና በብጫ ሐር በቀይና በነጭ ሐር እየጠለፉ በወርቅ እያስጌጡ ሠሩ፤

፫፣ ወገብሩ ቈጽለ ዘወርቅ ወሠጠቅዎ ወገብርዎ ከመ ይትፈተል ምስለ ያክንት ወምስለ ኀብረ ከብድ ወምስለ ለይ ክዑብ ወምስለ ቢሶስ ክዑብ፣

ወርቁን እንደ ቅጠል አሳስተው ሠርተው እየሠነጠቁ ከሰማያዊና ከብጫ ሐር ዕጥፍ ሁኖ ከተፈተለ ከቀይና ከነጭ ሐር ጋር ተስማምቶ እንዲፈተል አደረጉት፤

፬፣ ወገብርዎ ልብሰ መትከፍት ዘይወርድ ውስተ ክልኤሆን መታክፍቲሁ፣

ለዚሁም በሁለት ወገን የሚገናኝበት ሁለት ፈርጅ ሠርተው፤

ወአኀዙ ክልኤተ ኤጴሞሳተ እምኔሆሙ እለ ይትላጸቁ በክልኤቱ ገበዋቲሁ፤

በሁለቱ ጫንቃዎቹ የሚወርድ የጫንቃ ልብስ አድርገው ሠሩት፣ ሐተታ ስንዝሩን ለብቻው፣ ስንዝሩን ለብቻው አድርጎ በመሀን ሠርቶ ኋላ በጥልፍ ያያይዘዋል፤

፭፣ ወለትብልያሰ ዘልብሰ መትከፍት እነምዎ እምኔሆሙ በከመ አነሙ ኪያሃ በወርቅ ወበያክንት ወበኀብረ ከብድ ወበለይ ክዑብ ወቢሶስ ክዑብ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ፣

በኤፉድ ያለ የጥልፉን ሥራ ሥረ ወጥ አድርገው፣ እሱን እንደ ሠሩ በሰማያዊና በብጫ ሐር በቀይና በነጭ ሐር እየጠለፉ በወርቅ እያስጌጡ እግዚአብሔር ለሙሴ እንዳዘዘው አድርገው ሠሩት፤

፮፣ ወገብሩ አዕባነ መረግድ ወወደይዎሙ ውስተ ወርቅ ወገለፍዎሙ ከመ ግልፈተ ማኅተም በበአስማቲሆሙ ለደቂቀ እስራኤል፤

መረግድ /ዕንቍ/ የሚባሉ ሁለት አዕናቍ በወርቅ ጕብጕብ ላይ አስጊጠው እንደ ማኅተም ቅርፅ አድርገው የዓሥራ ሁለቱን ነገደ እስራኤል ስም ቀርፀው፤

፯፣ ወአንበርዎሙ ዲበ ኤጲሞሳቲሃ ለልብሰ መትከፍት ለአዕናቍ ዘተዝካሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ዘከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ፤

እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው የእስራኤል ልጆች ስም የተጻፈባቸው አዕናቍን በኤፉድ ፈርጅ ጥልፍ ላይ አኖራቸው፤

፰፣ ወገብሩ ልብሰ ሎግዮ ግብረ ምዕናም እሱቀ ከመ ግብረተ ልብሰ መትከፍት በወርቅ ወበያክንት ወበኀብረ ከብድ፤

ሎግዮንም /የደረት ኪስ/ እንደ ኤፉድ አሠራር የጥልፍ ሥራ አድርገው በሰማያዊ ሐርና በብጫ ሐር ዕጥፍ ሁኖ በተሠራ በቀይ ሐርና በነጭ ሐር እየጠለፉ በወርቅ እያስጌጡ ሠሩ፤

፱፣ ርቡዕ ወውጡሕ ውእቱ ወልብሰ ሎግዮ እመት ኑኁ ወእመት ራኅቡ እንዘ ውጡኀ ውእቱ፣

ሎግዮም በጥልፍ ተደራርቦ የተሠራ ምዕዙን /አራት ገጽ/ ነው፣ ድርብ ሆኖ ተሠርቶ ርዝመቱ ክንድ ወርዱ ክንድ ነው፤

፲፣ ወተአንመ ውስቴቱ ፬ቱ ዖታ እንመት ዘአዕናቍ ፩ዱ ዖታ ዘሰርድዮን ወበጳዝዮን ወበመረግድ፣

አራት ረድፍ ሁኖ በጥልፍ የዕንቍ ፈርጥ ተጠለፈበት፣ በመጀመሪያው ረድፍ የተጠለፈው ሰርድዮን ጳዝዮን መረግድ የሚባል ዕንቍ ነው፤

፲፩፣ ወካልእ ዖታ ዘኀብሩ ከመ ፍሕም ወሰንፔር ወኢያስጲድ፣

በሁለተኛው ረድፍ /ወገን/ የተጠለፈው ፍሕም የሚመስል ዕንቍና ሰንፔር ኢያስጲድ የሚባል ዕንቍ ነው፤

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

፲፪፣ ወሣልስ ፆታ በለግርዮን ወበአካጥስ ወበአሜቴስጢኖስ፣

በሦስተኛውም ረድፍ የተጠለፈው ለግርዮን አካጥስ አሜቴስጢኖስ በሚባል ዕንቍ ነው፤

፲፫፣ ወራብዕ ፆታ በዕንቍ ዘኀብረ ወርቅ ወበቢረሌ ወበሶም ወዓውደሙ በወርቅ እሡር፣

በአራተኛውም ረድፍ የተጠለፈው /የተቀረፀው/ አይነቱ ወርቅ የሚመስለውና ቢረሌ ሶም የሚባል ዕንቍ ነው ዙሪያውንም በወርቅ የተሰኩ የተከበቡ ናቸው፤

፲፬፣ ወውእቶሙ አዕናቍ በበአስማቲሆሙ ለ፲ቱ ወ፪ቱ ደቂቀ እስራኤል ወግሉፋን ከመ ግልፈተ ማኅተም ለለአሐዱ በበስሞሙ፣

አዕናቍ በዓሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ስም ቁጥር ናቸው፣ እያንዳንዱ ነገድም በየስማቸው እንደ ማኅተም አቀራረፅ ሁነው ተቀርፃባቸዋል፤

፲፭፣ ወገብሩ ሎቱ ሰናስለ ጽፉረ በልብሰ ሎግዮ በግብረት ፍቱል ወበወርቅ ንጹሕ፣

በሎግዮም ላይ የተታታ የወርቅ ሰንሰለት ሠሩለት፤

## ገባኤ

፲፮፣ ወገብሩ ክልኤተ ክበበ ጥውዮ ዘወርቅ ወክልኤተ ሕልቀታተ ወርቅ ወወደይዎን ለውእቶን ሕልቀታት ውስተ ክልኤሆን ጽነፊሁ ለልብሰ ሎግዮ፣

በሎግዮ በጠርዝና በጠርዙ የእባብ ራስ እየስመሰሉ ሁለት የወርቅ ቀለበት፣ ሁለት ተባት ቍልፍ ሠርተው፣ ሁለቱን የወርቅ ሰንሰለት በጠርዝና በጠርዙ በሁለት ወገን ባሉ በሁለት ቀለበቶች አያያዙት፤

፲፯፣ ወወደይዎ ለዝንቱ ጽፍሮ ወርቅ ላዕለ እልኩቱ ክልኤቱ ሕልቀታት እምክልኤሆሙ ገበዋቲሁ ለልብሰ ሎግዮ ውስተ ክልኤሆሙ ማኅበርቱ ወክልኤቱ ጽፍሮ፣

በሚገናኙበት በሁለቱ ጠርዞችም ሁለት የወርቅ ቋድ ሠርተው የእባብ ራስ አስመስለው ከሠሩት ተባት ቍልፍ ጋር አገናኙት፣

፲፰፣ ወአንበርዎን ላዕለ ክልኤቱ ክበበ ጥውዮ ወወደይዎን ማዕከለ መታክፍቲሁ ለልብሰ መትከፍት አንፃረ ገጹ፣

የጫንቃ ልብስ በሚሆን በኤፉድ በጠርዝና በጠርዙ ፊት ለፊት አድርገው አያያዟቸው፤



፲፱፣ ወገብሩ ኀልቀታተ ወርቅ ወአንበርዎሙ ላዕለ ክልኤሆሙ ጽነፊሁ ለኤፉድ እምታሕቱ መንገለ ገጹ ኀበ ማኅበርቱ መልዕልተ እንመቱ ለልብሰ መትከፍት፣

ሁለት የወርቅ ቀለበት ሠርተው ጥልፍ ሁኖ በተሠራ በኤፉድ ሎግዮ ፊት ለፊት ተያይቶ በሚገናኝበት በኤፉድ በዳርና በዳር አያይዘዋቸዋል፤

፳፣ ወአስተአኃዝዎ ለልብሰ ሎግዮ እምኀልቀታቲሁ ኀበ ሕልቀታተ ኤፉድ በፈትለ ያክንት፣

የሎግዮና የኤፉድን ቀለበቶች ያክንት በሚባል ሐር አያይዘው፣ ኤፉድንና ሎግዮን አገናኙዋቸው፤

፳፩፣ ከመ ይኩን ላዕለ እንመተ ኤፉድ ወከመ ኢይንጠልል ልብሰ ሎግዮ እምልብሰ መትከፍት ዘከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ፣

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዳዘዘው ሎግዮ ከኤፉድ ተለይቶ እንዳይነጠል በኤፉድ ጠርዝ ላይ ይሆን ዘንድ፤

፳፪፣ ወገብሩ ጳደሬ በግብረ ምዕናም ዘኵለንታሁ በያክንት ከዑብ፣

ከእግር እስከ ራሱ በሰማያዊ ሐር እጥፍ ሁኖ የተሠራ እጀ ሰፊ ቀሚስ ሰፉ፤

፳፫፣ ወአፈ መልበስቱ እምኔሁ በዓውዱ ወድማሬሁ ዕንሞ ከመ ኢይትበተክ፣

አንገትያውም በዙሪያው ሥረወጥ ሁኖ የተሠራ፣ ክሳዱ ተካሪሱም እንዳይለይ ሥረወጥ ሁኖ ተሠራ፤

፳፬፣ ወገብሩ መልዕልተ ዓውዱ በልብሰ ጳደሬ መትሕቴሁ ከመ ፍሬያተ ሮማን ሶበ ይጸጊ እምያክንት ወኀብረ ከብድ ወለይ ከዑብ ወቢሶስ ከዑብ፣

ከኤፉድና ከሎግዮ በታች በእጀ ሰፊው ቀሚስ ላይ በዙሪያው የሰማያዊና የብጫ ሐር ዕጥፍ ሁኖ የተሠራ የቀይና የነጭ ሐር ፈትል ሮማን ባበበ ጊዜ እንደሚያፈራው ፍሬ አስመስለው ሠሩ፣

፳፭፣ ወገብሩ ጸናጽላተ እምወርቅ ንጹሕ ወአንበርዎን ለጸናጽላት እማዕከለ ሮማናት ዲበ ጽንፉ ለጳደሬ እንተ ዓውዱ፣

ሻኵራዎቹን ከጠራ ወርቅ ሠርተው የሮማን ፍሬ መስለው በእጀ ሰፊው ቀሚስ ዙሪያ ባሉት በሐሮቹ መካከል አያያዟቸው፤

፳፮፣ በውስተ ሮማናት ጸናጽል ዕዱ፣ ወሮማን ዕዱ፣ ጸናጽል ዕዱ፣ ወሮማን ዕዱ በዘቦቱ ይገብሩ ከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ፣

በሮማኑ መካከል /በእጀ ሰፊው ቀሚስ መካከል/ በአንድ ወገን

www.ethiopianorthodox.org

የወርቅ ሻኮራ፣ በአንድ ወገንም የሮማን ፍሬ መስሎ የተሠራ ውን የሐር ፈትል እያከታተሉ አያያዟቸው እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው የክህነት ሥራ በሚሠሩበት ገንዘብ፤

፳፯፣ ወገብሩ አልባሰ ዘቢሶስ ግብረ ምዕናም ለአሮን ወለደቂቁ፣

ለአሮንና ለልጆቹም የነጭ ሐር ልብሶችን በጥልፍ ሥራ ሠሩ፤

፳፰፣ ወአክሊለ ዘቢሶስ ወቆብዓ ዘቢሶስ ወድርማንቀ ዘቢሶስ

የነጭ ሐር ኮፊት የነጭ ሐር ቆብ የነጭ ሐር ሰናፊል /ሱሪ/ ሠሩ፤

፳፱፣ ወቅንዓታተ ዘቢሶስ ወዘያክንት ወዘኀብረ ከብድ ወዘለይ ክዑብ ወዕሡቅ ግብሩ ዘከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ፣

ከነጭና ከሰማያዊ ሐር ከብጫና ዕጥፍ ሁኖ ከተሠራ ከቀይ ሐር መታጠቂያዎችንም ሠሩ ላቸው፣ አሠራሩም እግዚአብ ሔር ሙሴን እንዳዘዘው ድርብ ሁኖ የተሠራ ነው፤

፴፣ ወገብሩ ቈጽለ ወርቅ ፍሉጠ እምወርቅ ንጹሕ ወጸሐፉ ላዕሌሁ መጽሐፈ በቅርፀተ ማኅተም ቅዱስ ለእግዚአብሔር፣

ከጠራ ወርቅ ልዩ የሆነ የወርቅ ከለቻ /አክሊል/ ሠርተው ከዚያ ላይ ለእግዚአብሔር የተለየ የሚሆን የማኅተም ቅርፅ ቀረፁ በት አኽያ ሽራኽያ ብለው ቀርጸውበታል፤

፴፩፣ ወወደዩ ሎቱ ነጽፈ ዘያክንት ከመ ይንበር መልዕልተ አክሊል ዘከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ፣

እግዚአብሔር ሙሴን እንደ አዘዘው ከኩፌቱ ላይ የሰማያዊ ሐር ገበር ሠሩለት፤

፴፪፣ ወተፈጸመ ኵሉ ምግባረ ደብተራ ወገብሩ ደቂቀ እስራኤል ኵሎ ዘከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ፣

የደብተራ ኦሪት ሥራ ሁሉ ተፈጸመ፣ የእስራኤል ልጆችም እግዚአብሔር ሙሴን እንደ አዘዘው አድርገው ሠሩ፤

፴፫፣ ወአምጽእዋ ለደብተራ ኀበ ሙሴ ወለሠቃቲሃ ወለኵሉ ንዋያቲሃ ወለአዕማዲሃ ወለኖግዳቲሃ ወለመናሥግቲሆን ወለመከየዲሆን፣

ደብተራ ኦሪትን ሙሴ ወዳለበት አመጧት፤ የማቁን ፈርጆችና መሣሪያዎቿን ሁሉ አዕማዶቿ ንና ቀለበቶቿን ማገሮቿንና ምዕማዶቿንም አመጡ፤

፴፬፣ ወለመክደንታቲሃ ዘአምዕስተ በግዕ ወአምዕስተ መጻጺት፣

በላይ የሚያለብሷትን ቀለም ያልገባ የበግ ለምድና ተሰፍቶ ቀለም የገባውን ለምድ አመጡ፤



፴፭፣ ወመንጦላዕተ ምክዳን ወታቦተ ስምዕ ወመሃውርቲሃ ወምሥሐለ፤

ሃያውንና ዐሥሩን ክንድ የሚለየውን መጋረጃ ታቦትንና መሎጊያውን መግጠሚያውንም አመጡ፤

፴፮፣ ወማዕደ ምስለ ኵሉ ንዋያቲሁ ወኅብስተ ገጽ ዘይሠርዑ፣

ሰደቃውን ከነመሣሪያዎቹ የሚያቀርብበትንም ኅብስተ ገጹን አመጡ፤

፴፯፣ ወተቅዋመ ማኅቶት ንጽሕተ ወመኀትዊሃ ዘየኃትዉ በሙ ወኵሎ ንዋያቲሃ ወቅብዓ ማኅቶት፣

ከጠራ ወርቅ የተሠራች የመብ ራት መቅረዝ በአዕፁቅ ላይ የሚያኖሩዋቸውን ፈትሎችና መሣሪያዎቿን ሁሉ የሚበራ ውን ዘይቱን፤

፴፰፣ ወምሥዋዓ ዘወርቅ ወቅብዓ ዘይትቀብዑ ወዕጣነ ዘየዐጥኑ፣

የወርቁን መሠዊያ ማለት የወርቁን ማዕጠንት የሚቀ ቡትን ዘይትና የሚያጥኑትን ዕጣን፣

፴፱፣ ወመክድነ ኆኅተ ደብተራ ወምሥዋዓ ዘብርት ወመጥበሰ ዘብርት ዘሎቱ ወለመሃውርቲሁ ወኵሎ ንዋያቲሁ ወማዕከከ ምስለ መንበሩ፤

የድንኳኑን ደጃፍ መጋረጃ የብርት መሠዊያውንና ስቡ የሚቃለጥበትን የብርት ወንፊት መሎጊያዎቹንና መሣ ሪያዎቹን ሁሉ ሰኑን ከነብርቱ /ከነመቀመጫው/

፵፣ ወመንጦላዕተ ዓፀድ ወአዕማዲሁ ወመከየዲሆን ወመክድነ አንቀጸ ዓፀድ ወሐብላታቲሁ ወመታክሊሁ ወኵሎ ንዋያተ ምግባረ ደብተራ ዘመርጡል፤

የቅዕሩን መጋረጃ ከአዕማዶ ቹና ከምዕማዶቹ /ከመቋሚ ያቸው/ ጋር የቅዕሩን በር መጋረጃም ከአውታሮቹና ከካስማዎቹ ጋር ልዩ የሆነች የድንኳኒቱን ሥራ ዕቃ ሁሉ አመጡ፤

፵፩፣ ወአልባሰ ቅድሳት ዘአሮን ወአልባሰ ደቂቁኒ ዘክህነቶሙ ወዘተርፉኒ አልባሳት ለምግባረ ደብተራ ወመክደንተ ባዕድኒ፤

አሮንና ልጆቹ የሚያገለግሉ ባቸውን የክብር ልብሶች ለደብተራ ኦሪት ሥራ የሚሆኑ የቀሩትንም ልብሶች ሁሉ ሌላውን ዕቃ የሚሸፍኑበትን ሁሉ ወደ ሙሴ አመጡ፤

፵፪፣ በከመ ኵሉ ዘአዘዞ እግዚአ ብሔር ለሙሴ ከማሁ ገብሩ ደቂቀ እስራኤል ኵሎ ሥርዓቶ፣

የእስራኤልም ልጆች እግዚአ ብሔር ሙሴን እንዳዘዘው አድርገው ሥራውን ሁሉ ሠሩ፤

www.ethiopianorthodox.org

፵፫፣ ወርእየ ሙሴ ኵሎ ዘተገብረ ዘገብሩ ዘከመ አዘዞ እግዚአብሔር ከማሁ ተገብረ ወባረኮሙ ሙሴ፣

ሙሴም የእስራኤል ልጆች የሠሩትን ሥራ ሁሉ እግዚአ ብሔር እንዳዘዘው ሁኖ እንደ ተሠራ አይቶ መረቃቸው::

## ምዕራፍ ፵

### ጉባኤ

፩፣ ወተናገሮ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፣

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፣

፪፣ አመ ርእሰ ሠርቀ ቀዳሚ ወርኅ ትተክላ ለደብተራ መርጡል፣

ሚያዝያ በባተ በመጀመሪያው ቀን ደብተራ ኦሪትን ትከላት፣

፫፣ ወታነብር ውስቴታ ታቦተ ዘስምዕ ወትከድና ለታቦት በመንጦላዕት፣

ሕግ የተጻፈበት ጽላት ያለበት ታቦትን በውስጧ አኑራት ታቦትንም በመጋረጃ ጋርዳት፤

፬፣ ወታበውዕ ማዕደ ወትሠርዕ በሥርዓቱ ወታበውዕ መራናተ ወትሠርዕ መኃትዊሃ፣

ማዕድን ከሃያው ክንድ ውስጥ አግብተህ ከእርሱ ላይ የሚሠ ራባቸውን መሣሪያዎች ሁሉ በየቦታቸው አኑራቸው፣ መቅ ረዞንም አግብተህ ፋትሎቹን አዘጋጅላት፤

፭፣ ወታነብር ማዕጠንተ ዘወርቅ ቅድመ ታቦት ዘወርቅ ወዘስምዕ ወታነብር መንጦላዕተ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል፣

ከወርቅ የተሠራችውን ማዕጠ ንት በታቦቱ አንፃር አኑራት፣ በደብተራ ኦሪት ደጃፍ መጋረ ጃውን ጋርድ፤

፮፣ ወታነብሮ ለምሥዋዐ ዘመሥ ዋዕት በቅድመ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል፣

የመሥዋዕቱንም መሠዊያ በደብተራ ኦሪት ደጃፍ ፊት ለፊት አኑረው፤

፯፣ ወታነብር ማዕከከ ማዕከለ ደብተራ ወማዕከለ ምሥዋዕ ወትወዲ ውስቴቱ ማየ፣

ሰኑን ከደብተራ ኦሪትና ከምሥ ዋዑ መካከል አኑረህ ውሃ ሙላበት፤

፰፣ ወትተክል ዓፀደ ዓውዱ ወታነብር መክደኒ አንቀጸ ዓፀድ፣

የቅጽሩንም መጋረጃ በዙሪያው ጋርድ፣ ቀጥለህ የቅፅሩን በር /ደጃፍ/ መጋረጃ ጋርድ፤

፱፣ ወትነሥእ ቅብዓ ዘቦቱ ይቀብዑ ወትቀብዓ ለደብተራ ወለኵሉ ዘውስቴታ ወትቄድስ



ኪያሃ ወኵሉ ንዋያቲሃ ወትከውን ቅድስተ፣

የሚቀቡትንም ዘይት አምጥተህ ደብተራ ኦሪትንና በውስጧ ያሉትን መሣሪያዎች ሁሉ ቅባ፣ እሷንም ዕቃዎቿንም ቀብተህ አክብር፣ እንዲህ አድርገህ በቀባሃት ጊዜ የከበረች ትሆናለች፤

፲፣ ወትቀብዖ ለምሥዋዕ ዘመሥዋ ዕት ወለኵሉ ንዋያቲሁ ወትቄድሶ ለምሥዋዕ ወይከውን ውእቱ ምሥዋዕ ቅዱስ ቅዱሳን፣

የመሥዋዕቱን መሠዊያና መሣ ሪያዎቹን ቅባ፣ መሠዊያውንም አክብረው፣ እርሱም ከከበሩት ሁሉ የከበረ ይሆናል ፤

፲፩፣ ወትቀብዖ ለማዕከክ ወለመንበሩ ወትቄድሶ፣

ሰኑንና ብርቱን /መቀመጫ ውን/ ቀብተህ አክብረው ፤

፲፪፣ ወታቀርቦሙ ለአሮን ወለደቂቁ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ወተሐፅቦሙ በማይ፣

አሮንንና ልጆቹንም ልዩ ከሆነች ከደብተራ ኦሪት ደጃፍ አቅርበህ በውሃ እጠባቸው፤

፲፫፣ ወታለብሶ ለአሮን አልባሰ ቅድሳት ወትቀብዖ ወትቄድሶ ወይከውነኒ ካህነ፣

አሮንን ልዩ የሆነ የክብር ልብስ አልብሰው፣ ቀብተህም አክብ ረው፣ እንዲህም ሁኖ ለእኔ አገልጋይ ይሆናል፤

፲፬፣ ወታቀርቦሙ ለደቂቁኒ ወታለ ብሶሙ አልባሲሆሙ ወትቀብዖሙ በከመ ቀባዕኮ አባሆሙ ወይከውኑኒ ካህናተ፣

ልጆቹንም አቅርበህ የክብር ልብሳቸውን አልብሳቸው፣ አባታቸው አሮንን ቀብተህ እንዳከበርክ እነሱንም ቀብተህ አክብራቸው እንዲህም ሁነው ለኔ አገልጋዮች ይሆናሉ፤

፲፭፣ ወይከውኖሙ ዝንቱ ቅብዓት ዘክህነት ዘለዓለም ለትውልዶሙ፣

ይኸም የሚቀቡት የክህነት ቅባት እስከ ልጅ ልጅ ድረስ ለዘላለም ሥርዓት ይሁንላቸው፤

፲፮፣ ወገብረ ሙሴ ኵሎ ዘአዘዞ እግዚአብሔር ከማሁ ገብረ፣

ሙሴም እግዚአብሔር ያዘዘ ውን ሁሉ እንዳዘዘው አድርጎ ሠራ፤

፲፯፣ ወኮነ በቀዳሚ ወርኅ በካልእት ዓመት እምዘወፅኡ እምድረ ግብጽ አመ ርእሰ ሠርቀ ወርኅ ተከልዋ ለደብተራ፣

እስራኤል ከግብጽ በወጡ በሁለተኛው ዓመት በመጀመ ሪያው ወር የሚያዝያ መባቻ ደብተራ ኦሪትን ተከሏት፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፰፣ ወተከላ ሙሴ ለደብተራ ወአስተናበረ ምዕማዲሃ ወአቀመ አዕማዲሃ ወወደየ መናሥግቲሆን ወአቀመ አዕማዲሃ፣

ሙሴም ደብተራ ኦሪትን ተክሎ ምዕማዶቿን አዘጋጅቶ አምዶቿን እያቆመ በማገር አያያዛቸው፤

፲፱፣ ወሰፍሐ አዕፃዲሃ ለደብተራ ወአግበረ ሠቃተ ዲበ ደብተራ፣

ከአራት ኅብር የተሠራውን ዓሥሩን ፈርጅ ግምጃ በአዕማዱ ላይ ዘርግቶ አለበሰ፣ ከማቅ የተሠራውን ዓሥራ አንዱን ፈርጅም በግምጃው መጋረጃ ላይ አለበሰ ዘረጋ፤

ወአንበረ መክደኒ መልዕልተ ሠቅ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ፣

በማቁም ፈርጅ ላይ ማገሰ መጸጺትን /የተለፋና ቀለም የገባ የበግ ለምድ/ እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው አድርጎ አለበሰው፣

፳፣ ወነሥአን ሙሴ ለመጻሕፍተ ትእዛዝ ወወደዮን ውስተ ታቦት ወአንበሮን ለመሃውርት ውስተ አውቃፋተ ታቦት ወአንበሮ ለምስሐል መልዕልተ ታቦት፣

ሙሴም ሥርዓት የተጻፈባቸው ሁለቱን ጽላት አምጥቶ በታቦቱ ውስጥ አኖራቸው፣ መሎጊያዎቹንም በታቦቱ ላይ ባሉት ቀለበቶች ውስጥ አስገባቸው መግጠሚያውንም በታቦቱ ላይ አደረገው፤

፳፩፣ ወአብአ ለታቦት ውስተ ደብተራ ወወደየ መክደና መንጦላዕተ ወሠወራ ለታቦተ መርጡል ዘከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ፣

ታቦትንም ከድኳኑ ውስጥ አግብቶ የሚሸፍናትን መጋረጃ ጋረደ፣ እንዲህም ባደረገላት ጊዜ እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው መጋረጃው ታቦትን ሠወራት፣

፳፪፣ ወአንበሮ ለማዕድ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል መንገለ ገቦሃ ዘመስዕ ለደብተራ መርጡል እምአፍአሁ ለመንጦላዕት፣

ማዕዱን /ሰደቃውን/ ከቅድስተ ቅዱሳን መጋረጃ ውጭ በድንኳኑ ውስጥ በቀኝ በኩል አኖረው፤

፳፫፣ ወሠርዓ ውስቴታ ኅብስተ ቍርባን ቅድመ እግዚአብሔር ዘከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ፣

ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርቡትንም ኅብስት እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው በማዕድ ላይ ሠራ፤



፳፬፣ ወአንበራ ለመራናት ውስተ ደብተራ መርጡል አንፃረ ማዕድ መንገለ አዜባ ለደብተራ፣

መብራት የሚበራበትንም መቅረዝ በድንኳኑ በስተግራ በኩል በማዕዱ ፊት ለፊት አኖራት፣

፳፭፣ ወሠርዓ መኀትዊሃ ቅድመ እግዚአብሔር ዘከመ አዘዞ እግዚ አብሔር ለሙሴ፣

እግዚአብሔር በሚገለጽባት በቅድስተ ቅዱሳን ፊት የሚበሩትን ፋትሎቿንም እግዚአ ብሔር ሙሴን እንዳዘዘው አዘጋጀ፤

፳፮፣ ወአንበረ ማዕጠንተ ዘወርቅ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ቅድመ መንጦላዕት፣

ከወርቅ የተሠራ ማዕጠንትንም በድንኳኑ ውስጥ በመጋረጃው ፊት አኖረው፤

፳፯፣ ወዐጠነ ውስቴቱ ዕጣነ ዘገብረ ዘከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ፣

በውስጡም እግዚአብሔር እንዳዘዘው ያዘጋጀውን ዕጣን አጠነበት፤

፳፰፣ ወአንበሮ ለመክደኒ ኆኅተ ደብተራ፣

የድንኳኑንም በር መጋረጃ ጋረደ፤

፳፱፣ ወለምሥዋዕ ዘመሥዋዕት አንበሮ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ወአዕረገ ላዕሌሁ መሥዋዕተ ወቍርባነ ዘከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ፣

የሚቃጠል መሥዋዕት የሚቀርብበት ምሥዋዓ ብርቱንም ከድንኳኑ ደጃፍ አድርጎ እግዚ አብሔር እንዳዘዘው መሥዋ ዕት ቁርባን አሳረገበት፤

፴፣ ወአንበሮ ለማዕከክ ማዕከለ ደብተራ ወማዕከለ ምሥዋዕ ወወደየ ውስቴቱ ማየ፤

ሰኑን /መታጠቢያውን/ በድንኳኑና በምሥዋዓ ብርቱ መካከል አድርጎ ውሃ መላበት፤

፴፩-፴፪፣ ከመ ይትሐፀቡ ቦቱ አሮን ወደቂቁ እደዊሆሙ ወእገሪሆሙ ሶበ ይበውኡ ውስተ ደብተራ ወሶበ ይቀርቡ ኀበ ምሥዋዕ ዘከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ፤

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዳዘዘው አሮንና ልጆቹ ወደ ድንኳኑ በሚገቡበት ጊዜ ወደ መሠዊያውም በሚቀርቡበት ጊዜ እጃቸውን እግራቸውን ይታጠቡበት ዘንድ ውሃ መላበት፤

፴፫፣ ወአቀመ ዓፀደ በዓውደ ደብ ተራ ወምሥዋዕ ወአንበሮ ለመክደኒ አንቀጽ ዘዓፀድ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ፣

በድንኳኑና በምሥዋዑ ዙሪያ የቅጽሩንም ዓምዶች አቁሞ

www.ethiopianorthodox.org

መጋረጃውን ጋረደ፣ የቅጽሩ ንም በር መጋረጃ እግዚአብ ሔር እንዳዘዘው አድርጎ ጋረደው፤

፴፬፣ ወፈጸመ ሙሴ ኵሎ ግብሮ ወከደና ደመና ለደብተራ መርጡል ወስብሐተ እግዚአብሔር ተመልዓት ደብተራ፣

ሙሴም እንዲህ አድርጎ ሥራ ውን ሁሉ ሠርቶ ጨረሰ፣ ድንኳኒቱንም ብሩህ ደመና ሸፈናት፣ የእግዚአብሔርም ብርሃን ሰፍሮባት ታየ፤

፴፭፣ ወስዕነ ሙሴ በዊአ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል፣ እስመ ጸለላ ደመና ወስብሐተ እግዚአብሔር ተመልዓት ደብተራ፣

ሙሴም ብሩህ ደመና ስለ ሸፈናት የእግዚአብሔርም ብር ሃን ስላረፈባት ወደ ደብተራ ኦሪት መግባት ተሳነው፤

፴፮፣ ወእምከመ ሰሰለ ደመና እምላዕለ ደብተራ ይግዕዙ ደቂቀ እስራኤል በበነገዶሙ፣

ደመናው ከድንኳኒቱ ላይ ከተነሣ በኋላ ግን የእስራኤል ልጆች በየነገዳቸው ይጓዙ ነበር፣ /ሐተታ ነገደ ብንያም ሁለቱን ነገድ ይዘው በፊት ይጓዛሉ፣ ቀጥለው ነገደ ሮቤል ሁለቱን ነገድ ይዘው ይጓዛሉ፣ ሌዋውያን ካህናትም ታቦትንና ንዋየ ቅድሳቱን ይዘው በመካ ከል ይጓዛሉ፣ ከዚያ ቀጥለው ነገደ ምናሴ ሁለቱን ነገድ ይዘው ይጓዛሉና በበነገዶሙ አለ፤

፴፯፣ ወእመሰ ኢሰሰለ ደመና ኢይግዕዙ እስከ አመ ይሴስል ደመና፣

ደመናው ከድንኳኑ ካልተነሣ ግን እስኪነሣ ድረስ አይጓ ዙም ነበር፣ ከድንኳኑ ላይ አለ መነሣቱ አትጓዙ ሲል ነውና፣

፴፰፣ እስመ ደመና ይነብር ላዕለ ደብተራ መዓልተ ወእሳተ ይከውን ላዕሌሃ ሌሊተ ቅድመ ኵሉ እስራኤል በኵለሄ ኀበ ግዕዙ፣

ተጉዘው በሚሰፍሩበት ቦታ ሁሉ ደመናው እስራኤል እያዩት ቀን በድንኳኑ ላይ ሰፍሮ ውሎ ሌሊት ዓምደ እሳት ሁኖ ሲያበራላቸው ያድር ነበርና፤

ተፈጸመ ኦሪት ዘፀአት ወለእግዚ አብሔር ክብር ወስብሐት፣

ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባውና ፫ኤል ከግብፅ መውጣታቸውን የሚናገር መጽሐፍ ደረሰ ተፈጸመ።።

www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org